# የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ

## ከዐፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ።

ተጻፈ ፤
ከተክለ ፡ ጻድቅ ፡ መኩሪያ።

## ፪ተኛ፡ መጽሐፍ።

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ መንግሥት ፡
ይህ መጽሐፍ ፡ በተስፋ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY


ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ፡ሥላሴ።



ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ አሥፋው።



ልዑል ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዬጵያ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ።

# ማውጫ

**መቅድም።** 10

**ያፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት (ሺ፪፻፷፪ - ሺ፪፻፸፯ ፡ ዓ.ም።)** 17

**ምዕራፍ ፡ ፩** 18

ይኵኖ ፡ አምላክና ፡ አፄ ፡ ነአኵቶ ፡ ለኣብ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት። 18

**ምዕራፍ ፡ ፪** 25

የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አጭር ፡ ታሪክ። 25

**ምዕራፍ ፡ ፫** 30

በአፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክና ፡ በአቡነ ፡ ተከለ ፡ ሃይማኖት ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ሲሶ ፡ መንግሥት። 30

**ምዕራፍ ፡ ፬** 38

ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ የነገሥታቱ ፡ ዝርዝርና ፡ የግዛታቸው ፡ ዘመን። 38

ከዐፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የሚዠምረው ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ፡ በኢት ፡ ቊጥር 41

ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የሚዠምረው ፡ በአውሮፓ ፡ አቆጣጠርና ፡ በፈረንጆቹ ፡ ሂሣብ። 43

**ምዕራፍ ፡ ፭።** 46

ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ በዘመኑ ፡ የፈጸመው። 46

**ምዕራፍ ፡ ፮** 48

የአፄ ፡ ያግብአ ፡ ጽዮንና ፡ የተከታዮቹ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት። 48

**ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።** 52

**ምዕራፍ ፡ ፯** 53

የታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ጽሑፍ። 53

**ምዕራፍ ፡ ፰** 56

በኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንና ፡ በዘመኑ ፡ ሊቃውንት ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ጠብ 56

**ምዕራፍ ፡ ፱** 61

የዘር ፡ ሐረግ። 61

**ምዕራፍ ፡ ፲** 66

የይፋትና ፡ የአዳል ፡ ባላባቶች ፡ በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ሸፍተው ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንደተዋጋቸው። 66

**ምዕራፍ ፡ ፲፩።** 70

አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከይፋትና ፡ ከአዳል ፡ ባላባቶች ፡ ጋር ፡ ያደረገውን ፡ ጦርነት ፡ የሚተርከው ፡ ጽሑፍ። 70

**ምዕራፍ ፡ ፲፪** 74

ኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከሰብር ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ ጦርነት። 74

**ምዕራፍ ፡ ፲፫** 81

ኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከኣዳሉ ፡ ንጉሥና ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ የመዠመሪያው ፡ ጦርነት። ____ 81
**ምዕራፍ ፡ ፲፬ ____ 90**
አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከአዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ ፪ተኛው ፡ ትልቅ ፡ ጦርንት። ____ 90
**ምዕራፍ ፡ ፲፭ ____ 112**
የመመለስና ፡ ጦርነቱን ፡ የመቀጠል ፡ ምክር—ያዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ገብተው ፡ ምሕረት ፡ መለመን—የመጨረሻው ፡ ጦርነት። ____ 112
**ምዕራፍ ፡ ፲፮ ____ 121**
የጦርነቱ ፡ ታሪክና ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ አንደኛ ፡ ፍጻሜ። ____ 121
**ምዕራፍ ፡ ፲፯። ____ 129**
ለአባ ፡ መጣዕ (ሊባኖስ)ገዳም ፡ ኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የሰጠው ፡ ጉልት። ____ 129
**ምዕራፍ ፡ ፲፰። ____ 136**
ያፄ ፡ ዓምደጽዮን ፡ ተከታይ ፡ አፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ። ____ 136
**ምዕራፍ ፡ ፲፱። ____ 139**
ባፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ፈቃድ ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ — ያፄ ፡ ንዋየ ፡ ማርያም ፡ ዘመን። ____ 139
**ያፄ ፡ ዳዊት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት። ____ 143**
**ምዕራፍ ፡ ፳። ____ 144**
ባፄ ፡ ዳዊት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከግብፁ ፡ ሱልጣን ፡ ጋር ፡ የተደ ፡ ረገው ፡ ስምምነትና ፡ የግማደ ፡ መስቀል ፡ መምጣት። ____ 144
**ምዕራፍ ፡ ፳፩። ____ 147**
የውስጥ ፡ ጦርነት። ____ 147
**ምዕራፍ ፡ ፳፪። ____ 155**
**የኣፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፩ኛ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት። ____ 155**
**ምዕራፍ ፡ ፳፫። ____ 156**
**የዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት። ____ 156**
**ምዕራፍ ፡ ፳፬ ____ 159**
በዐረብና ፡ በግብፃውያን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ዘንድ ፡ የሚገኘው ፡ ያፄ ፡ ይስሐቅ ፡ የውስጥ ፡ ጦርነት ፡ ያፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ፍጻሜና ፡ የተደረገላቸው ፡ ግጥም ፡ ____ 159
**ምዕራፍ ፡ ፳፭ ____ 168**
እንድርያስ--ተክለ ፡ ማርያም—ሠርዌ ፡ ኢየሱስ--ዓምደ ፡ ኢየሱስ። ____ 168
**ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት። ____ 170**
**ምዕራፍ ፡ ፳፮። ____ 171**
ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸው። ____ 171
**ምዕራፍ ፡ ፳፯ ____ 175**

ሥርዓተ ፡ ንግሥ—የሹማምንት ፡ የማዕርግ ፡ ስምና ፡ ደረጃ። ______________ 175
፲፫ ፡ አፈዋተ ፡ መንግሥት ______________ 178
**ምዕራፍ ፡ ፳፫። ______________ 186**
ስለ ፡ እቴጌዪቱ ፡ ሥርዓተን ፡ ግሥ። ______________ 186
**ምዕራፍ ፡ ፳፱። ______________ 188**
ስለ ፡ ንጕሡና ፡ ስለ ፡ ንግሥቶች ፡ የማዕርግ ፡ ስም። ______________ 188
**ምዕራፍ ፡ ፴። ______________ 196**
ልዩ ፡ ልዩ ፡ አምልኮን ፡ ለማጥፋት ፡ ያደረጉት ፡ ቅጣትና ፡ ያወጡት ፡ አዋጅ። _ 196
**ምዕራፍ ፡ ፴፩። ______________ 200**
ሹም ፡ ሽርና ፡ ባለሟልነት።______________ 200
**ምዕራፍ ፡ ፴፪። ______________ 207**
የማሂኮ ፡ ሽፍትነትና ፡ ፍጻሜው። ______________ 207
**ምዕራፍ ፡ ፴፫። ______________ 210**
የቤት ፡ ሥራና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዓትና ፡ ደንብ።______________ 210
**ምዕራፍ ፡ ፴፬። ______________ 218**
የጨዋ ፡ ድልድልና ፡ በአክሱም ፡ ጽዮን ፡ የተደረገ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ። ______________ 218
**ምዕራፍ ፡ ፴፭። ______________ 227**
የአሕመድ ፡ በድላይ ፡ ስሙና ፡ የዘሩ ፡ ሐረግ - ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በርሱ ፡ ሞት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳምና ፡ ሌሎቹም ፡ አድባራት ፡ ያገኙት ፡ ስጦታ። ______________ 227
የወላስሞች ፡ የዘር ፡ ሐረግ። ______________ 229
**ምዕራፍ ፡ ፴፮። ______________ 237**
የደቂቀ ፡ እስጢፋ ፡ ቅጣት—የደብረብርሃንና ፡ የቂርቆስ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ሥራ — ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥርዓትና ፡ ቅዳሜ ፡ እንዲከበር ፡ የወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ " ______________ 237
**ምዕራፍ ፡ ፴፯። ______________ 241**
አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቀብ ፡ የደረሱዋቸው ፡ መጻሕፍት። ______________ 241
**ምዕራፍ ፡ ፴፰። ______________ 246**
ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ የጻፉት ፡ ደብዳቤ። ______________ 246
**ምዕራፍ ፡ ፴፱። ______________ 252**
አባ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ብራንካ ፡ ሌዎንየፍሎራንስ ፡ ጉባዔ ፡ የአባ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ደብዳቤና ፡ መልክተኞች።______________ 252
**ምዕራፍ ፡ ፵። ______________ 259**
በእቴጌ ፡ ጽዮን ፡ ሞገሳ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ ቅጣት=ስለ ፡ ዐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዕረፍትና ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት—የዘመኑ ፡ ግጥም። ______________ 259
**ምዕራፍ ፡ ፵፩። ______________ 269**
መስቀልና ፡ ክብሩ-ሰንደቅ ፡ ዓለማ-የመገበያያው ፡ ገንዘብ። መስቀልና ፡ ክብሩ። 269

ሰንደቅ ፡ ዓላማ። 274
የመገበያያ ፡ ገንዘብ። 276
**ምዕራፍ ፡ ፶፪።** **277**
የመካከለኛው ፡ ምሥራቅና ፡ የአውሮፖች ፡ ሁኔታ። 277
**ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።** 283
**ምዕራፍ ፡ ፶፫ ፡** **284**
ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የመንግሥትን ፡ ሥልጣን ፡ መያዝ። 284
**ምዕራፍ ፡ ፶፬።** **286**
የእሥረኛ ፡ ምሕረትና ፡ ሹም ፡ ሽር-ያስተዳደር ፡ ልዩነት። 286
**ምዕራፍ ፡ ፶፭።** **290**
ወደ ፡ አማራ ፡ ሳይንትና ፡ ወደ ፡ ወረይሉ (ደብረ ፡ ነጐድጓድና ፡ አትሮንስ ፡ ማርያም) ጕዞ–የአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ሥራና ፡ የበዓሉ ፡ አከባበር። 290
**ምዕራፍ ፡ ፶፮።** **296**
ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ -- የሐሜተኞች ፡ ቅጣት ፡ የመሐመድ ፡ ቤን ፡ በድላይ ፡ መገበር ፡ የዚያን ፡ ዘመንና ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ የሕዝብ ፡ መብት ፡ ልዩነት። 296
ያፄ ይኩኖ አምላክ የዘር ሀረግ 299
**ምዕራፍ ፡ ፶፯።** **304**
የዶብዓ (ዋጅራት - ራያና ፡ አዘቦ) ጦርነት። 304
**ምዕራፍ ፡ ፶፰።** **313**
በአዳል ፡ ሽፍትነት ፡ የተነሣ ፡ ከዶብዓ ፡ እስከ ፡ ይፋት ፡ የተደረገ ፡ ጕዞ። 313
**ምዕራፍ ፡ ፶፱።** **319**
የመሐሪ ፡ ክርስቶስና ፡ የገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ በአዳሎች ፡ መሸነፍ ፡ - ፡ የአባ ፡ ሚካኤል ፡ ሕልምና ፡ ያመጣባቸው ፡ እሥራት። 319
**ምዕራፍ ፡ ፷።** **327**
በ፪ኛ ፡ ክፍል ፡ ተደግሞ ፡ የተጻፈው ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የዜና ፡ መዋዕል ፡ ጭማሪ 327
**ምዕራፍ ፡ ፷፩።** **332**
ስለ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕልስለሌዎን ፡ ብራንካ ፡ ስእል። 332
**ያፄ ፡ እስክንድር ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።** 337
**ምዕራፍ ፡ ፷፪።** **338**
በእስክንድር ፡ ሕፃንነት ፡ የተነሣ ፡ የንግሥት ፡ ሮምና ፡ የዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ተስፋ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ የጋራ ፡ ግዛት። 338
**ምዕራፍ ፡ ፷፫።** **341**
ያፄ ፡ እስክንድር ፡ አገር ፡ መጐበኘትና ፡ የአዳል ፡ ኣገር ፡ ዘመቻ-ያፄ ፡ እስክንድር ፡ አማሟት። 341

**ምዕራፍ ፡ ፶፬።** ____ **345**
የኢትዮጵያና ፡ የፖርቱጋል ፡ የመዠመሪያው ፡ ግንኙነት—ስለፔድሮ ፡ ኮቪልሐኦ ፡ መምጣት። ____ 345
**ያፄ ፡ ናዖድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።** ____ 351
**ምዕራፍ ፡ ፶፭።** ____ **352**
የዓፄ ፡ ናዖድ ፡ አነጋገሥ -የብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ ፍጻሜ ____ 352
**ምዕራፍ ፶፮።** ____ **354**
የተካ ፡ ክርስቶስ ፡ ሽፍትነትና ፡ ፍጻሜው--ባለፈ ፡ ኃጢአት ፡ ሰው ፡ እንዳይወቀስ ፡ የተደረገ ፡ አዋጅ። ____ 354
**ምዕራፍ ፡ ፶፯።** ____ **357**
የፈላሾች ፡ ሽፍትነትና ፡ ቅጣት–ስለሃይማኖት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያና ፡ በአውሮፓ ፡ የነበረው ፡ ግፈኛ ፡ ቅጣት። ____ 357
**ምዕራፍ ፡ ፶፰።** ____ **361**
ባፄ ፡ ናዖድና ፡ በማሕፉድ ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ጦርነት። ____ 361
**ምዕራፍ ፡ ፶፱።** ____ **365**
ኣምባ ፡ ግሼንና ፡ የነጋሢ ፡ ልጆች ፡ የቤተ ፡ ማርያምና ፡ የመርጡ ፡ ለማርያም ፡ ሥራ-ዓፄ ፡ ናዖድ፡ለቤተ ፡ ማርያም ፡ የሰጡዋቸው ፡ መጻሕፍት።____ 365
**ምዕራፍ ፡ ፷።** ____ **367**
አፄ ፡ ናዖድ ፡ በዘመናቸው ፡ የተቀኙዋቸው ፡ ቅኔዎች።____ 367
**ምዕራፍ ፡ ፷፩።** ____ **382**
ከዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ድረስ ፡ ያሉ ፡ የነገሥታትና ፡ የንግሥታት ፡ የመሳፍንትና ፡ የመኳንንት ፡ ዝርዝር። ____ 382
ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን።____ 383
ባፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዘመን።____ 384
ባፄ ፡ እስክንድር ፡ ዘመን ፡____ 386
ባፄ ፡ ናዖድ ፡ ዘመን።____ 387
**ስለደራሲው በጥቂቱ**____ **392**

# መቅድም።

ከኑብያ ፡ የአክሱምንና ፡ የዛጕዬን ፡ በማያያዝ ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ድረስ ፡ ከዓፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ካፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በየዘመኑ ፡ ከዚህ ፡ ካሁኑ ፡ ጋራ ፡ በአራት ፡ የተከፈሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ሲወጡ ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ከመዠመሪያው ፡ አሳቤን ፡ ላነሣ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ማናቸውንም ፡ ችግር ፡ በመሸከም ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዳደርስ ፡ ለደገፈኝ ፡ አምላኬ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ምስጋና ፡ በማቅረብ ፡ ልቤ ፡ ይደሰታል።

እነዚህ ፡ አራት ፡ ላይ ፡ የተከፈሉት ፡ ባገራችን ፡ ቋንቋ ፡ ተጽፈው ፡ በጠቅላው ፡ ከኑብያ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነመንግሥት ፡ ያለውን ፡ ያገራችንን ፡ ታሪክ ፡ የሚገልጹት ፡ አራት ፡ መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የዓላማ ፡ ፍጻሜ ፡ እቆጥራቸዋለሁ። እነሱም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ የሚያውቀውንም ፡ የማያውቀውንም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አንባቢ ፡ ያገሩን ፡ ታሪክ ፡ ለመፈለግ ፡ ወደ ፡ ፈረንጆች ፡ መጽሐፍ ፡ ከመሔድ ፡ ያድኑታል ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ፡ ይህ ፡ ያሁኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ካፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ለመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪካችን ፡ የመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ ሲሆን ፡ ላሳትመው ፡ የቻልሁት ፡ በመጨረሻ ፡ ነው። በርሱም ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ስማቸውን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሥራቸውን ፡ ጭምር ፡ ሊያውቃቸው ፡ የሚገባ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትን ፡ ማጻፍ ፡ የዠመረው ፡ የዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን (ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ገብረ ፡ መስቀል/የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ደራሲ ፡ የሆኑት ፡ የዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ቆስጠንጢኖስ) ፡ ታሪክ ፡ ይገኝበታል።

ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥትና ፡ የነገሥታት ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በመዠመሪያ ፡ ያዘጋጁት ፡ ከዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ በየጊዜው ፡ የተነሡት ፡ ጸሐፍተ ፡ ትእዛዞች ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓቶች ፡ ሌሎችም ፡ ስማቸውና ፡ የማዕርግ ፡ ስማቸው ፡ የማይታወቅ ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የቤተ

፡ ክህነት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው። ከዚያ ፡ በግራኝ ፡ አህመድ ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ በቃጠሎ ፡ በዘረፋ ፡ ከባከነ ፡ በኋላ ፡ የደጃች ፡ እሸቴ ፡ ልጅ ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ባዬ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ማኅደረ ፡ ማርያም (ቤገምድር) የነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ከየአገሩ ፡ ከየደሴቱ ፡ ሕዝብ ፡ ማቅረብ ፡ ነው። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ማስረጃ ፡ ከማግኘቱ ፡ ይበልጥ ፡ ማብራራቱ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል። በፊተኛው ፡ ዘመን ፡ ለነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ያገለገለው ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ አሳቡ ፡ ሳይብራራ ፡ እንዳለ ፡ ለዛሬው ፡ ዘመን ፡ ሕዝብ ፡ ቢቀርብለት ፡ ንባቡና ፡ አንባቢው ፡ በከንቱ ፡ ተፋጠው ፡ ከመተያየት ፤ ተያይተው ፡ ከመለያየት ፡ በቀር ፡ ሊጠቃቀሙ ፡ ኣይችሉም። እንደ ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ እንደ ፡ አስተዳደር ፡ ሁሉ ፡ ጽሑፍና ፡ ቋንቋ ፡ በየዘመኑ ፡ መልኩን ፡ ከነድምፁ ፡ አሳቡንና ፡ ከነትርጒሙ ፡ ለውጦ ፡ ስለሚገኝ ፡ ለመረዳት ፡ የአብራሪውን ፡ ጸሐፊ ፡ እርዳታ ፡ ያሻል። ጸሐፊው ፡ ደግሞ ፡ ወረቀትና ፡ ብርዕ ፡ ከመጨበጡ ፡ በፊት ፡ አሳቡንና ፡ ዕውቀቱን ፡ ለጒዳዩ ፡ ነክነት ፡ ወዳላቸው ፡ የቀድሞ ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ አስገብቶ ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጥናትና ፡ መለማመድ ፡ እንዲያደርግ ፡ ያስፈልጋል።

ይኸውም ፡ ሆኖ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ደንጊያ ፡ ጠጥሮ ፡ የሚቀረው ፡ ከአሳብ ፡ እየሸሸ ፡ የሚያመልጠው ፡ ብዙ ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ጒልበታቸው ፡ ኣዳዲስ ፡ በሆነ ፡ በሌሎች ፡ ጸሐፊዎች ፡ ትግል ፡ እየተሸነፈ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ተፈላጊው ፡ ታሪክ ፡ ወደመጣራት ፡ ይመጣል።

ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ የጥበብ ፡ የጽሑፍ ፡ የፍልስፍና ፡ ዕውቀት ፡ የግርድፍነትና ፡ የስልቅነት ፡ ጊዜውን ፡ ሳያሳልፍ ፡ በመዠመሪያ ፡ በወደቀው ፡ አሳብ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለዘለቄታ ፡ ተጣርቶ ፡ ለአገልግሎት ፡ ብቍ ፡ የሚሆን ፡ የለም። በኣሁኑ ፡ ዘመን ፡ ያዘጋጀነው ፡ ጽሑፍ ፡ ሁሉ ፡ የዚህን ፡ ሕግ ፡ ከመከተል ፡ አይዘልም። ዳሩ ፡ ግን ፡ የአውሮፓና ፡ የእስያ ፡ ሕዝብ ፡ ግርድፉን ፡ በየጊዜው ፡ በትጋት ፡ በተቀራረበ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እያለዘበ ፡ በየግንባሩ ፡ እየሠራ ፡ ሲጠቀም ፡ ሥራውም ፡ ሥልጡን ፡ ሲያሰኘው ፡ እኛ ፡ ለግርድፉ ፡ ብቻ ፡ የዘለቅንበት ፡ ዘመን ፡ ረዥም ፡ ነው ፡ ከዛጒዬ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ጐንደር ፡ መንግሥት ፡ መጨረሻ ፡ (፱፻-፲፰፻) ዓ.ም ፡ ድረስ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡

ሙሉ ፡ የያዝነውን ፡ ላለመልቀቅ ፡ ከመታገል ፡ በቀር ፡ በሥነ ፡ ጽሑፍም ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመሻሻል ፡ የመሠልጠን ፡ እርምጃ ፡ ያደረገችው ፡ በልክ ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ባገሪቱ ፡ በየጊዜው ፡ የተፈራረቁት ፡ መሪዎችና ፡ ሕዝቦች ፡ በዚህ ፡ ሲወቀሱ ፡ ያገሪቱን ፡ ነፃነት ፡ ብቻ ፡ ማቆየታቸው ፡ መልሶ ፡ ያስመሰግናቸዋል።

ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ በግዕዝ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ይቀመጥ ፡ የነበረው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትሁት ፡ በእንግሊዝኛም ፡ በፈረንሳዊኛም ፡ በኢጣልያንኛም ፡ እየተተረጐመ ፡ ለጐዳዩ ፡ ባዕድ ፡ የሆነው ፡ አሰብስበው ፡ ኣጽፈውታል። ይኸንኑ ፡ ለማስረዳት ፡ ይኸው ፡ የተሰበሰበው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ በመዠመሪያው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፈ ፡ ታሪክ ፡ ኣስተጋብኣ ፡ ደጅአዝማች ፡ ኃይሉ ፡ እምብዙኃን ፡ አህጉር ፡ ወደሰያት ፡ ከመኢይጥፋእ ፡ ዝክረ ፡ አበዊሁ ፡ ነገሥት ፡ ወመኳንንት ፡ እም ፡ አመ ፡ ጠፍኣበብዙኅ ፡ ዕለት ፡ እምቤተ ፡ መንግሥት» ይላል። ዝክረ ፡ አበዊሁ ፡ ነገሥት ፡ ብሎ ፡ የነጋሢ ፡ ዘርነታቸውን ፡ በትክክል ፡ ለመለየት ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ « ወዘኣጽሐፎሰ ፡ ደጅ ፡ አዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ወልዱ ፡ ለደጅ ፡ አዝማች ፡ እሸቴ ፡ ወእሙሂ ፡ ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ሩፋኤል ፡ ወለተ ፡ ኣድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ መንገለ ፡ አቡሃ ፡ ወመንገለ ፡ እማ ፡ ኣልቦ ፡ ዘይትኤረያ ፡ እያለ ፡ ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ ከሺ፯፻፸፬–ሺ፯፻፺፱ ፡ ዓ.ም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የነበሩት ፡ የታላቁ ፡ የአድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ መሆናቸውን ፡ ይገልጻል።

ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ ሰብስበው ፡ ያጻፉት ፡ ባፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በግዞት ፡ ማኅደረ ፡ ማርያም ፡ ሳሉ ፡ መሆኑን ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ስለሚናገር ፡ የግዞቱን ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቊም ፡ ነገር ፡ በመሥራት ፡ ኣሳልፈውታል ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ ደጃች ፡ ኃይሉን ፡ ጽሑፉን ፡ በመጻፍ ፡ ቀድሞ ፡ ከደከሙት ፡ ሊቃውንት ፡ እኩል ፡ እናመሰግናቸዋለን።

የዚሁ ፡ የታሪክ ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ አንዳንድ ፡ ቅጅ ፡ በሎንዶን ፤ በፓሪስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ስለነበረ ፡ ከዚያ ፡ በየጊዜው ፡ የተነሡ ፡ የአውሮፓ ፡ ሊቃውንት ፡ አውግስጦስ ፡ ዲልማን ፤ ዮሴፍ ፡ ሐለቪ ፤ ዡል ፡ ፔሩሾ ፤ ረኔ ፡ ባሴት ፤ ኮንሴልማን ፤ኢኛሲዎ ፡ ጉይዲ ፡ ምሼነ ፤ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ከውስጡ ፡

ስሜታቸው ፡ ያረፈበትን ፡ አንዳንዱን ፡ ክፍል ፡ እየለዩ ፡ ወደየ ፡ ቋንቋቸው ፡ እየተረጐሙ ፡ በማብራራት ፡ ከግዕዙ ፡ ጋር ፡ በማኅተም ፡ አራብተው ፡ ጽሑፉን ፡ ከአውሮፓ ፡ አንባቢ ፡ ጋር ፡ አስተዋውቀውታል።

በነዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በነዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ የነበሩት ፡ ያገራችን ፡ ሊቃውንት ፡ ባይጽፉት ፡ ኖሮ ፡ ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ ሊሰበስቡት ፡ ባልቻሉም ፡ ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ ባይሰበስቡት ፡ ፈረንጆቹም ፡ እኛም ፡ ያገሪቱ ፡ ተወላጆች ፡ ዛሬ ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ለማዘጋጀት ፡ መሠረት ፡ ባላገኘንም ፡ ነበር።

የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ቅኔ ፡ እንደ ፡ ግጥም ፡ ከልብና ፡ ከኣሳብ ፡ እየመነጨ ፡ አይሠራም። የዘመናዊው ፡ ጸሐፊ ፡ ተግባር ፡ ከሩቅ ፡ ዘመን ፡ የተጻፈውን ፡ ተፈላልጎ ፡ ማግኘት ፡ ያገኘውን ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ ኣወራርሶ ፡ ባለበት ፡ ዘመናዊ ፡ ያነጋገር ፡ ቅርጽ ፡ አሳቡን ፡ ከማብራራት ፡ ጋራ ፡ ለዘመኑ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ሲያነበው ፡ ለጉዳዩ ፡ ባለቤት ፡ ለሆነው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እንግዳ ፡ ሆኖ ፡ እስካሁን ፡ መኖሩም ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ነው። አሁን ፡ ግን ፡ ታሪካችን ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቡ ፡ በማይናገርበት ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ቀድሞ ፡ የተጻፈው ፡ በየገዳማቱ ፡ በየቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ከብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ዠምሮ ፡ የተኛውን ፡ እየተፈላለግን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ እየተረጐምን ፡ ያንቀላፋውን ፡ ያገራችንን ፡ ታሪክ ፡ እኛው ፡ ተወላጆቹ ፡ በቋንቋችን ፡ ልንቀሰቅሰው ፡ ይገባል።

በብራና ፡ ያለውን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የነገሥታት ፡ መቀመጫ ፡ በነበሩት ፡ ከተሞች ፡ በየዜና ፡ መዋዕሉ ፡ እየተመሩ ፡ በቊፋሮ ፡ እየፈለጉ ፡ የተቀበሩትን ፡ ታሪካውያን ፡ መሣሪያና ፡ ዕቃዎች ፡ በማግኘት ፡ ላለፈ ፡ ታሪካችን ፡ ትንሣኤ ፡ መስጠት ፡ የኛው ፡ ፈንታ ፡ ነው። መቼም ፡ ላገሪቱ ፡ የሚያስፈልጓት ፡ የሥራ ፡ ዘርፎች ፡ ብዙዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ሁላችንም ፡ የምናውቀው ፡ ነው ፡ ትምህርት ፤ እርሻ፣ ንግድ ፤ መገናኛ ፤ የጦር ፡ ድርጅት ፤ ሕግና ፤ አስተዳደር ፤ ጤና ፡ አጠባበቅ ፤ የብረታ ፡ ብረትና ፡ ማናቸውም ፡ የእጅ ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ ችላ ፡ የሚባል ፡ አንዳች ፡ የሥራ ፡ ዘርፍ ፡ የለም። በዚሁ ፡ ረገድ ፡ የታሪክና ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ወገን ፡ የሚገባውን ፡ ሥፍራ ፡ እንዲያገኝ ፡ እስካሁን ፡ የቆመውን ፡ ድርጅት ፡ እንዳቅማችን ፡ ከማገልገል ፡ ቸል ፡ አንልም።

“ ካፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በሚባለው ፡ በዚህ ፡ ባሁኑ ፡ መጽሐፍ ፡ በጀግንነት ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ የሆነው ፡ ዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፤ ከጀግንነት ፡ ጋር ፡ የቀለም ፡ ሰውነታቸውን ፡ ደርበው ፡ የያዙት ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሌሎችም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ሰፊው ፡ ግዛታቸው ፡ ከአክሱም ፡ ዝምሮ ፡ ያላቋረጠው ፡ ሥልጣናቸው ፡ እንዳይከፈል ፡ በሦሥቱ ፡ ማዕዘን ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ኣገር ፡ በሚያሳምኑበት ፡ ጊዜ ፡ ከይፋት ፡ ወላስሞች ፡ ከአዳልና ፡ ከሱማሌ ፡ ከስሜንና ፡ ከጸለምት ፡ ከዋጅራት ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ የተዋጉት ፡ በርክቶ ፡ ይገኛል። ከየአውራጃው ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ቀንደኛ ፡ በእንደራሴ ፡ የገዥነት ፡ አምሮቱን ፡ ለማርካት ፡ ሲል ፡ በየበኩሉ ፡ አንዳንድ ፡ የነጋሢ ፡ ዘር ፡ እየያዘ ፡ በደንብ ፡ ከነገሠው ፡ ጋር ፡ የሚያደርገው ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ ነው። የኢትዮጵያንም ፡ ሥልጣኔ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ከጐተቱት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ የውስጥ ፡ ጦርነት ፡ ነው። የዚያን ፡ ዘመን ፡ የነገሥታቱንም ፡ የመሣፍንትና ፡ የመኳንንቱንም፣ የሊቃውንቱንም ፡ አብዛኛ ፡ የዕውቀትና ፡ የማሰቢያቸውን ፡ ሥፍራና ፡ ጊዜ ፡ የሚወስደው ፡ የጦርነት ፡ የማሳመን ፡ የማስገበር ፡ ወታደሩንም ፡ የምርኮ ፡ የዘረፋ ፡ የፉከራ ፡ ጉዳይ ፡ ነው።

የሩቍ ፡ ዘመን ፡ ቀርቶ ፡ በቅርቡ ፡ በጉንደር ፡ መንግሥት ፡ መጨረሻ ፡ ከ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ወዲህ ፡ የጐንደር ፡ መሣፍንት ፡ ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ከእንደርታው ፡ ከራስ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴና ፡ ከስሜኑ ፡ ከራስ ፡ ገብሬ ፡ ራስ ፡ ማርዬ ፡ ከአጋሜው ፡ ከደጃች ፡ ሰባጋዲስ ፡ በጐጃም ፡ የዳሞቱ ፡ ደጃች ፡ ዘውዴ ፡ ከጐጃሙ ፡ ከደጃች ፡ ጓሉ፣ደጃች ፡ ብሩ ፡ ካባታቸው ፡ ከደጃች ፡ ጐሹ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ በሸዋም ፡ ተጉለቴው ፡ ከቡልጋው ፡ ወሎዬው ፡ ከሸዌው ፡ በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አዳሉ ፡ ከኢሣው ፡ ማረቆው ፡ ካሩሲ ፡ ጉራጌው ፡ ከጋላው ፡ እየተዋጋ ፡ በየጊዜው ፡ ያለቀው ፡ የተላለቀው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ብዙ ፡ ነው። በቀላል ፡ ምክንያት ፡ የከበረው ፡ የሰውልጅ ፡ ሕይወት ፡ ሲያልፍ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ቅርታው ፡ ያነሰ ፡ ነበር። በዚህ ፡ ፈንታ ፡ እዚህ ፡ ገዳይ ፡ እገሌን ፡ ገዳይ ፡ እያለ ፡ የወገኑን ፡ ስምና ፡ ስፍራ ፡ በመጥቀስ ፡ ሕዝባችን ፡ በአሳፋሪው ፡ ነገር ፡ እየፎከረ ፡ ይመካበት ፡ የነበረው ፡ እስከ ፡ ጊዜያችን ፡ ደርሷል።

ይህ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ በመጨረሻው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ እንኳን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሰላምና ፡ የጸጥታ ፡ ጊዜ ፡ ኣግኝታ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ አውሮፖች ፡ የተጠቀሙበትን ፡ የጤና ፡ አጠባበቅ ፡ በመከተል ፡ የሕዝቡን ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ በማድረግ ፡ ተጣጥራ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ዛሬ ፡ አገራችን ፡ ከሃምሳ ፡ ሚሊዮን ፡ የማያንስ ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝብ ፡ ያላት ፡ ታላቅ ፡ የምታኮራና ፡ የምታስመካ ፡ የአፍሪካ ፡ መንግሥት ፡ ትሆን ፡ ነበር። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ዕውቀት ፡ ሥልጣኔ ፡ ኃይልና ፡ ችሎት ፡ በአውሮፖች ፡ እጅ ፡ ስለነበረ ፡ እነሱም ፡ እስያንና ፡ አፍሪካን ፡ ተካፍለው ፡ የያዙ ፡ የኢትዮጵያም ፡ ነፃነት ፡ ቅር ፡ የሚያሰኛቸው ፡ መንግሥታት ፡ ኃይል ፡ እንዳታገኝ ፡ የሚያደርጉት ፡ መቆጣጠር ፡ ከውስጥ ፡ ጦርነታችን ፡ ጋር ፡ ተጨምሮ ፡ ለመሪዎቻችን ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንቅፋትነቱ ፡ አይዘነጋም።

ዛሬ ፡ ግን ፡ የአፍሪካ ፡ ሕዝብ ፡ ክርስቲያኑና ፡ እስላሙ ፡ አረመኔውና ፡ ይሁዲው ፡ ያንድነት ፡ ኑሮ (ፌዴራሲዮን) በሚመኝበት ፡ ጊዜ ፡ ያለፈው ፡ የርስበርስና ፡ የወንድማማችነት ፡ ጦርነት ፡ ለወደፊት ፡ በፍቅር ፡ እመገንባት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ያንድነትና ፡ የመዋሐድ ፡ ሕንፃ ፡ ሊያፈርሰው ፡ አይገባውም። ቂምና ፡ በቀል ፡ ሥፍራቸውን ፡ ለይቅርታ ፡ ለመተሳሰብ ፡ ለሕብረት ፡ ለፍቅር ፡ ሊለቁ ፡ ይገባል።

በዚህ ፡ መስመር ፡ ያላለፈ ፡ አንድም ፡ የውጭ ፡ መንግሥት ፡ የለም። የሰሜንና ፡ የደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ በግሪክ ፡ ደሴቶች ፡ ተበታትነው ፡ የነበሩ ፡ ነገዶች ፡ በጠቅላላው ፡ የአውሮፓም ፡ የእስያም ፡ ዛሬ ፡ በየስማቸው ፡ የምናውቃቸው ፡ መንግሥታት ፡ ሥልጣን ፡ ክብር ፡ በመቃማት ፡ ወገን ፡ ከወገኑ ፡ ሲዋጋ ፡ ኖሮ ፡ ዛሬ ፡ ኣንድነታቸውን ፡ እያጠነከሩ ፡ ከውጭ ፡ ብቻ ፡ ጠላት ፡ ሲመጣ ፡ እየተዋጉ ፡ በነፃነት ፡ አርፈው ፡ ይኖራሉ።

አገራችን ፡ ኢትዮጵያም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ከርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ አርፋ ፡ ልዩልዩ ፡ ቋንቋና ፡ ልማድ ፡ ያላቸው ፡ ሕዝቦቿ ፡ ኣንዱ ፡ ነገድ ፡ ሌላውን ፡ ለማጥቃት ፡ ሳይሞክር ፡ የሥልጣንም ፡ የክብርም ፡ የጥቅምም ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡ በመብት ፡ ተተካክለው ፡ በሰላምና ፡ በጸጥታ ፡ ሐብታምና ፡ ፍሪያማ ፡ የሆነችውን ፡ አገራችንን ፡ እንድንጠቀምባት ፡ እየተመኘን ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ጽሑፉ

፡ አካል ፡ ገብተን ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ እንመልከት።

ሚያዝያ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ.ም፡
ተክለ ፡ ጻድቅ ፡ መኵሪያ።

# መልካም ንባብ!

# ክፍል ፡ ፩።

## ያፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት (ሺ፪፻፷፪ - ሺ፪፻፸፯ ፡ ዓ.ም።)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ ፩

## ይኵኖ ፡ አምላክና ፡ አፄ ፡ ነአኵቶ ፡ ለኣብ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት።

ነአኵቶ ፡ ለአብ ፡ በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ሺ፪፻፲፫ ፡ ሺ፪፻፵፫ ፡ ዓ.ም ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የሚባል ፡ ሰሎሞናዊው ፡ ዘር ፡ ከሚባለው ፡ ከድልነዓድ ፡ ዘር ፡ የወረደ ፡ ወጣት ፡ በሸዋ ፡ ነበር ፤ እንደዚሁም ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የታወቁት ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ በዚሁ ፡ በሸዋ ፡ ነበሩ። ገድላቸውና ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደ ፡ ሚለው ፡ የርሳቸውን ፡ ከመጻፋችን ፡ በፊት ፡ ኣሁን ፡ ስለይኵኖ ፡ አምላክ ፡ እንመልከት።

ባለፈው ፡ ባነበብነው ፡ ውስጥ ፡ መራ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የዛጒዬን ፡ መንግሥት ፡ አደላድሎ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ በኣክሱም ፡ ይቀመጥ ፡ የነበረው ፡ የመጨረሻው ፡ ንጉሥ ፡ ድልነዓድ ፡ ከትግሬ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደሸዋ ፡ መምጣቱን ፡ ተመልክተናል። ከርሱ ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፡ በዛጒዬ ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ ተይዘው ፡ እንዳይታሰሩ ፡ በመፍራት ፡ ዘመናቸውን ፡ በሽሽትና ፡ በዋሻ ፡ በመደበቅ ፡ አሳልፈዋል ፡ የሚባሉት ፡ ዝርዝራቸው ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ነው።

፩ኛ ፡ ድልነዓድ ፡

፪ኛ ፡ ኣግብአ ፡ ጽዮን

፫ኛ ፡ ጽንፈ ፡ አርዕድ ፡

፬ ፡ ነጋሽ ፡ ዞሬ

፭ ፡ ኣሥፍሕ ፡

፮ኛ ፡ ያዕቆብ ፡

፯ ፡ ባሕር ፡ ኣሰግድ ፡

፰ኛ ፡ እድም ፡ ኣሰግድ ፡

፱ነኛ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡

ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ የመዠመሪያው ፡ ድልነዓድና ፡ የመጨረሻው ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ በዙፋን ፡ ሲቀመጡ ፡ ዕድሜያቸውን ፡ በሸሽትና ፡ በመደበቅ ፡ ያሳለፉ ፡ የድልነዓድ ፡ ተከታዮች ፡ ሰባቱ ፡ መሆናቸው ፡ ነው።

ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ የክርስትና ፡ ስሙ ፡ ተስፋ ፡ ኢየሱስ ፡ ተወልዶ ፡ ባደገ ፡ ጊዜ ፡ እንዳይገደልበት ፡ ፈርቶ ፡ አባቱ ፡ ሐይቅ ፡ ወስዶ ፡ ለቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ገዳም ፡ መምሕር ፡ ለአባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓ ፡ ኣደራ ፡ ብሉ ፡ ሰጣቸው። ይኵኖ ፡ ኣምላክም ፡ በሓይቅ ፡ ደሴት ፡ እየተማረ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ኖረ ፡ ከዕለታት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓን ፡ ለመጠየቅ ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ (የሽዋው) ፡ ወደ ፡ ሐይቅ ፡ ሄዱ ፤ በዚያም ፡ ሳሉ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክን ፡ ስላገኙ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ በሚመለሱበት ፡ ቀን ፡ ይህ ፡ የሐይቅ ፡ ገዳም ፡ ለላስታ ፡ ቅርብ ፡ ስለሆነ ፡ ያስፈራዋልና ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ይገኜው ፡ ልሂድ ፡ ብለው ፡ ከአባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓ ፡ አስፈቅደው ፡ ወደሽዋ ፡ ይዘውት ፡ መጡ። በሽዋም ፡ በይፋት ፡ በመንዝ ፡ በተጕለት ፡ በመራቤቴ ፡ እያዞሩ ፡ ከባላባቶቹ ፡ ጋር ፡ አስተዋወቁት። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜውን ፡ ያሳለፈው ፡ በተጕለት ፡ ነው። ፩ ፡ ኣንድ ፡ ጊዜ ፡ ይዙ ፡ ኖ ፡ አምላክ ፡ መሆኑን ፡ ሳይገልጽ ፡ በስውር ፡ ላስታ ፡ ድረስ ፡ እየሄደ ፡ አሽከርነት ፡ እያደረ ፡ የቤተ ፡ መንግሥትን ፡ ሥርዓትና ፡ ሕግ ፡ ያጠና ፡ ነበር ፡ ይላሉ። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ እሱን ፡ ለማንገሥ ፡ ስለቆረጡና ፡ ባላባቱን ፡ ሁሉ ፡ ወደዚሁ ፡ አሳብ ፡ ስለአሳደሙ ፡ እርሱም ፡ ያባቶቼ ፡ መንግሥት ፡ በርስዎ ፡ ጸሎት ፡ የተመለሰልኝ ፡ እንደሆነ ፡ ለእርስዎም ፡ የአባትዎን ፡ የአዛርያስን ፡ ሊቀ ፡ ካህናትነት ፡ እመልስልዎታለሁ፥ ፡ ከመንግሥቴም ፡ ከሦስቱ ፡ እጅ ፡ አንዱን ፡ እጅ ፡ እሰጥዎታለሁ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባላቸው ፡ ይባላል።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በየኣውራጃው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ወንጌል ፡ ሲያስተምሩ ፡ በዚሁ ፡ በሐዋርያነትና ፡ በመምህርነት ፡ በያገሩ ፡ ታውቀው ፡ ተፈርተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበርና ፡ በዚሁ ፡ በወንጌል ፡ ትምህርታቸው ፡

ላይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለየታላላቁ ፡ ሰው ፡ ዛጉዬዎች ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ ዙፋኑን ፡ ኣላገባብ ፡ ነው ፡ የወሰዱት ፡ ኣሁንም ፡ ለይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ሊመልሱ ፡ ይገባል ፡ እያሉ ፡ ይሰብኩ ፡ ነበር። ከዕለታት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ወደላስታም ፡ ሄደው ፡ ነአኵቶ ፡ ለአብን ፡ አግኝተው ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ የወሰዳችሁት ፡ በማይገባ ፡ ነውና ፡ አሁንም ፡ ለሚገባው ፡ ለይኵኖ ፡ አምላክ ፡ መልሱ ፡ ብለው ፡ በግልጽ ፡ ነገሩት ፡ እርሱም ፡ **እግዚአብሔርን** ፡ የሚፈራ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሰው ፡ ስላነበረ ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትንም ፡ ቃል ፡ እንዳይተላለፍ ፡ ፈርቶ ፡ ምክራቸውን ፡ ሰምቶ ፡ እሺ ፡ እለቃለሁ። ነገርግን ፡ የኔ ፡ ዘመን ፡ ከአለቀ ፡ በኋላ ፡ በውል ፡ ነው ፡ የምለቀው ፡ ብሎ ፡ ገለጸላቸው ፡ ይባላል።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ የታሪክ ፡ አነጋገር ፡ የሚገኘው ፡ በታሪክነገሥትና ፡ በገድለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው። በነዚህም ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ወደፊት ፡ እንደምንመለከተው ፡ በተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አማካይነት ፡ ነአኵቶ ፡ ለኣብ ፡ በመንግሥቱ ፡ መጨረሻ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዙፋን ፡ ለይኵኖ ፡ አምላክ ፡ መልቀቁን ፡ ይገልጻል ፡ እንጂ ፡ በይኵኖ ፡ ኣምላክና ፡ በነአኵቶ ፡ ለአብ ፡ ወይም ፡ በይትባረክ ፡ መካከል ፡ ጦርነት ፡ መደረጉን ፡ አይገልጽም ፡ "ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ግማሾቹ ፡ ነአኵቶ ፡ ለኣብ ፡ እያሉ ፡ ግማሾቹ ፡ ይትባረክ ፡ እያሉ ፡ የመጨረሻው ፡ የዛጉዬው ፡ ንጉሥ ፡ ለይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ መንግሥቱን ፡ የለቀቀው ፡ በጦርነት ፡ መሆኑን ፡ ይገልጻሉ። ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ካርሎ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ከአገራችን ፡ ጽሑፍና ፡ ከሽማግሌ ፡ ሰማሁት ፡ ብለው ፡ የጻፉትን ፡ እንመልከት።

ያማራ ፡ አገር (የግሼን ፡ እንደሌሎቹ ፡ የአምባሰል) ፡ ሹም ፡ የነበረ ፡ ስሙ ፡ ተስፋ ፡ ኢየሱስ ፡ ወይም ፡ ውድም ፡ ኣሰግድ ፡ የሚባል ፡ ነበር ፡ ለርሱም ፡ አንድ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የሚባል ፡ ልጅ ፡ ከአዛዥ ፡ ጫላ ፡ ገረድ ፡ የተወለደ ፡ ነበረው። እርሱንም ፡ የወለደው ፡ ወደመቆናኛ (ሰገራት) "ለጉዳዩ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ነው። ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ አገር ፡ ኣደገ ፡ በፍጥረቱም ፡ ቀበጥባጣና ፡ አስቸጋሪ ፡ ስለነበረ ፡ ኣባቱ ፡ በኣምባ ፡ ማሎጥ ፡ ኣሥሮት ፡ ሲኖር ፡ በኋለ ፡ ከእሥሩ ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ ሰው ፡ መሰብሰብ ፡ ጀመረ። ሰውም ፡ ቢሰበሰብለት ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ሸፈተ ፡ ከርሱም ፡ ጋር ፡ የሸዋ ፡

ኣውራጃዎችና ፡ ወግዳ ፡ ደምቢ ፤ ሙገርዋግ ፤ ወረብ ፤ ጽላልሽ ፡ ሙኣል ፡ ሁሉ ፡ ተባብረው ፡ ነበር። ይኸን ፡ ሲሰማ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ጋይንት ፡ በተለይ ፡ አንሲታ ፡ ወደሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ በሄደበት ፡ ጊዜ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ በድንገት ፡ ጦርነት ፡ ገጠመና ፡ በቶሎ ፡ ድል ፡ አደረገው። ንጉሡም ፡ ከዚያ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ቂርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ ጠላቶቹ ፡ በሐምሌ ፡ ፺ ፡ ቀን ፡ ገደሉት። ኣንዳንዶቹም ፡ ከላስታ ፡ ከራሱ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ከድተውት ፡ ስለነበረ ፡ በነርሱ ፡ ጥቅሻ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ እስከ ፡ ላስታ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ራሱ ፡ በጦርነት ፡ ገደለውና ፡ አፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ ነገሠ። » ፡ Storia di Ethiopia (የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ) የሚባለውን ፡ የኮንቲ ፡ ሮሲኒን (Carlo Conti Rossini) መጽሐፍ ፡ ከ፫፻፲፺ ፡ እስከ ፡ ፫፻፲፰ ፡ ገጽ ፡ ተመልከቱ።

የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ በሰው ፡ ጠባይ ፡ በኵል ፡ የገመትነው ፡ እንደሆነ ፡ በዙፋን ፡ ተቀምጦ ፡ መግዛት ፡ የለመደ ፡ ንጉሥ ፡ እንኳን ፡ ለሌላ ፡ ዘር ፡ በዘመኑ ፡ ለልጁ ፡ እንኳን ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ የሚወድ ፡ በልክ ፡ ነው። ያገራችንም ፡ ቢሆን ፡ የውጭ ፡ አገርም ፡ ታሪክና ፡ ገድል ፡ ቢሆን ፡ እገሌ ፡ መንግሥቱን ፡ ለልጁ ፡ ለዘመዱ ፡ ወይም ፡ ለወዳጁ ፡ ለቆ ፡ መነነ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ግል ፡ ሥራው ፡ ሄደ ፡ የሚሉት ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ በዕድሜው ፡ ያረጀ ፡ ሆኖ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ተድላና ፡ ደስታ ፡ ሹመትና ፡ ሥልጣን ፡ ማጣጣም ፡ ሲያቅተው ፡ ሲሰለቸው ፡ ወይም ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ጠላት ፡ ተነሥቶበት ፡ መመለስ ፡ ሲያቅተው ፡ ሕዝብ ፡ በኣድማ ፡ ተነሥቶበት ፡ መደምሰስ ፡ ባልቻለ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው። በሙሉ ፡ ዕድሜው ፡ ሳሉ ፡ እየተመቻቸው ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለሌላ ፡ የሚአሳልፉ ፡ ቢኖሩም ፡ በጣም ፡ ብርቅ ፡ ናቸው።

ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የተመለከትን ፡ እንደሆነ ፡ ነአኵቶ ፡ ለኣብ ፡ ከደንበኛው ፡ ወራሽ ፡ ከላሊበላ ፡ ልጅ ፡ ከራሱም ፡ ዘመድ ፡ ከይትባረክ ፡ ወስዶ ፡ ያገኘውን ፡ ዘውድ ፡ እንደልቡ ፡ የፈቀደውን ፡ የሚያደርግበትን ፡ የጠላውን ፡ የሚያስርበትን ፡ የወደደውን ፡ የሚሾምበትን ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ መንግሥቱን ፤ ምንም ፡ ቄስና ፡ መነኵሴ ፤ ጻጳስም ፡ ቢመክረው ፡ እንደዚሁ ፡ በሰላም ፡ የሚለቅ ፡ አይመስልም። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥነት ፡ እንደዛሬ ፡ አይደለም ፡ የዛሬ ፡ ንጉሥ ፡ ባንዳንድ ፡ አገር ፡ ከቀረው ፡ በቀር ፡ የቀረው ፡ ሥልጣኑና ፡ ችሎቱ ፡ የተወሰነ

፡ የፈቀደውን ፡ መሻርና ፡ መሾም ፡ የማይችል ፡ ነው። የዚያን ፡ ዘመን ፡ ንጉሥ ፡ ግን ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ እዙፋኑ ፡ ወጥቶ ፡ ሕዝብ ፡ ካኣወቀው ፡ በኋላ ፡ በሥልጣኑ ፡ ወሰን ፡ የለበትም። የፈለገውን ፡ የተመኘውን ፡ ይፈጽማል ፤ ኃጢኣትና ፡ ዓመጽ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ንጉሥ ፡ አደረገው ፡ ሲባል ፡ እንደ ፡ ጽድቅና ፡ እንደ ፡ ደንብ ፡ ይቆጠር ፡ ነበር ፤ ንጉሡ ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ሥልጣኑ ፡ የማይገሰስ ፡ ከ**እግዚአብሔር** ፡ የተቀባ ፡ ቅዱስ ፡ ብፁዕ ፡ ነውና ፡ ነአኵቶ ፡ ለአብም ፡ ይትባረክም ፡ ቢሆን ፡ የተገደዱበት ፡ ነገር ፡ ከሌለ ፡ ያለ ፡ ጦርነት ፡ ዙፋናቸውን ፡ በኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አሳሳቢነት ፡ ብቻ ፡ ለይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የሚለቀቍ ፡ አይመስልም ፡ "

ስለዚህ ፡ በየመንገዱ ፡ ታሪኩን ፡ ሁሉ ፡ ስንመረምር ፡ በመጨረሻ ፡ የምንረዳውና ፡ የሚመስለው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው።

ነአኵቶ ፡ ላኣብ ፡ በሚገዛበት ፡ ዘመን ፡ ይኵኖኣምላክ ፡ ያባቶቹን ፡ መንግሥት ፡ በዘመኑ ፡ ለማስመለስ ፡ በሸዋ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ አደራጅቷል። ደንበኛ ፡ ነጋሢና ፡ ሰሎሞናዊ ፡ ዘር ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቍ ፡ የሸዋና ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የተዘረዘሩት ፡ አገሮች ፡ ባላባቶች ፡ ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ጋር ፡ ባንድነት ፡ ስለኣበሩ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የነዚህን ፡ ኃይል ፡ አስከትሎ ፡ ነአኵቶ ፡ ለኣብን ፡ በጦርነት ፡ ኣስቸግሮት ፡ ይሆናል። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ላሊበላን ፡ የሚወዱ ፡ ከልጁ ፡ ከይትባረክ ፡ ነአኵቶ ፡ ለአብ ፡ ዙፋኑን ፡ ቀማው ፡ እያሉ ፡ የሚናደዱ ፡ የላስታና ፡ የዋግ ፡ ባላባቶች ፡ ይህን ፡ ቂም ፡ ለመበቀል ፡ እርሱን ፡ እየከዱ ፡ ለአፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ መሣሪያ ፡ ሆነው ፡ ይሆናል። እንደዚሁም ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ያሉት ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ጎርጎርዮስ? የኢትዮጵያው ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ (ቄርሎስ)፤የሐይቍ ፡ መምሕር ፡ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዐ ፡ የደብረ ፡ ዳሞው ፡ መምሕር ፡ አባ ፡ ዮሐኒ ፡ የሸዋው ፡ ኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የኣክሱም ፡ ንቡረ ፡ ዕድ ፡ በጠቅላላው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያሉት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሁሉ ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ ለሚወለደው ፡ ለአፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ ኣድልተው ፡ በአሳብም ፡ በሥራም ፡ እየደገፉ ፡ ሕዝብንና ፡ ባላባትንም ፡ በስብከት ፡ እያሥነሱ ፡ ስላስቸገሩትና ፡ ነኣኵቶ ፡ ለአብ ፡ በጦርነትና ፡ በስብከት ፡ በሁላት ፡ ወገን ፡ ስለተቸገረ ፡ ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ መምህሩ ፡ ኣቡነ ፡ ተክለ ፡

ሃይማኖት ፡ አብልጠው ፡ በነገሩ ፡ ስለተጕበት ፡ በርሳቸው ፡ አማካይነት ፡ ነኣኵቶ ፡ ለአብ ፡ ዙፋኑን ፡ በውል ፡ ለይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ ለቋል ፡ ማለት ፡ ነው።

ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ አሚድ (ጊዮርጊስ ፡ ኢብን ፡ ኣል ፡ አሚድ) የሚባለው ፡ የጻፈውና ፡ ከርሱ ፡ የተገለበጠው ፡ ያገራችን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል።

"ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ ዘሜጠ ፡ መንግሥተ ፡ እምነ ፡ ዛጓ ፡ በጸሎተ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፤ ወበጸሎት ፡ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓ ፡ መምሕረ ፡ ሐይቅ፣ ፡ ወበትንብልናሁ ፡ ለኣብ ፡ ብፁዓዊ ፡ ክቡር ፡ ርእሰ ፡ ኣበው ፡ ኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መምህር ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ። እስመ ፡ ነበሩ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ኵሎ ፡ ኖኅ ፡ መንግሥቱ ፡ ወበእንተዝ ፡ ወሀቦሙ ፡ ለውሉዱ ፡ ፩ደ ፡ እደ ፡ እም፫ቱ ፡ እድ ፡ መንግሥተ ፡ ወምኵናነ ፡ ወሥልጣነ ፡ ወሣመ ፡ እምውሉደ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እጨጌ ፡ በኪዳን ፡ ወመሐላ ፤ ወእምውሉደ ፡ ኣባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ከመ ፡ ይኵን ፡ ሎሙ ፡ ርስተ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ "ይህ ፡ ቃል ፡ ባጭሩ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ በጳጳሱ ፡ በኣባ ፡ ጌርሎስና ፡ በኣባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓ ፡ ይልቊንም ፡ በኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸሎትና ፡ እርዳታ ፡ መንግሥቱን ፡ ሲያገኝ ፡ ለዚሁ ፡ ውለታ ፡ ከመንግሥቱ ፡ ከ፫ ፡ እጁ ፡ አንዱን ፡ እጅ ፡ የእጨጌነት ፡ ማዕርግ ፡ ጨምሮ ፡ ለተክለ ፡ ሃይማኖት፥ለኣባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓና ፡ ለተከታዮቻቸው ፡ የዓቃቤ ፡ ሰዓትነት ፡ ማዕርግ ፡ መስጠቱን ፡ ያስረዳል።

ስለዚህ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ በመመልከት ፡ ነአኵቶ ፡ ለኣብ ፡ በኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አማካይነት ፡ በውል ፡ መንግሥቱን ፡ ላይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ለቀቀ።

ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ የሚባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ ራስ ፡ ሚካኤል ፡ ስሑል ፡ እንደራሴ ፡ አፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ንጉሥ ፡ በነበሩበት (ሺ፻፻፷፫–ሺ፻፻፷፱ ፡ ዓ. ምሕረት) ጐንደር ፡ መጥቶ ፡ የነበረው ፡ ሲመለስ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ሰብስቦ ፡ ሄዶ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ በ፭ ፡ ቦሉም ፡ የጻፈው ፡ የውሉን ፡ ዓይነት ፡ በመዠመሪያው ፡ መጽሐፍ (ቦሉም)፮፻፲፭ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ በዝርዝር ፡ ገልጾታል። ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይም ፡ ከርሱ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ዘንድ

፡ አግኝተውት ፡ ይሆን ፡ አላረጋግጥም ፡ አሳትመው ፡ ሳይጠረዝ ፡ በያለበት ፡ ተበትኖ ፡ ከሚገኘው ፡ መጽሐፉቸው ፡ ላይ ፡ ጽፈውታልና ፡ ይኸንኑ ፡ የውሉን ፡ ቃል ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ እንመልከት።

**፩ኛ** ፡ የነአኵቶ ፡ ለአብ ፡ ዘመን ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ ንጉሥ ፡ መባሉ ፡ እንዲረጋና ፡ የርሱ ፡ ዘመን ፡ ሲያልቅ ፡ አፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲነግሥ።

**፪ኛ** ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ መንግሥቱን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋለ ፡ ከዛጐዬ ፡ ዘር ፡ አንድ ፡ መስፍን ፡ እየመረጠ ፡ በላስታ ፡ ኣልጋ ፡ እንዲሾም ፡ የላስታም ፡ ግዛት ፡ ከዛጐዬ ፡ ወገኖች ፡ እንዳይወጣ።

**፫ኛ** ፡ ላስታን ፡ የሚገዛው ፡ መስፍን ፡ የዛጐዬ ፡ ዘር ፡ ለመሆኑ ፡ ምልክት ፡ ይሆነው ፡ ዘንድ ፡ ሁለት ፡ የብር ፡ ነጋሪት ፡ እንዲያስጭን ፡ የዘበኞቹ ፡ ጦር ፡ ባለብር ፡ ሽቦ ፡ የሰንደቅ ፡ ዓላማው ፡ መያዣ ፡ ጫፉ ፡ የብር ፡ እንዲሆን።

**፬ኛ** ፡ የቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ የሆነው ፡ ንጉሥ ፡ በወርቅ ፡ ዙፋን ፡ ሲቀመጥ ፡ የላስታው ፡ መስፍን ፡ በብር ፡ ወንበር ፡ እንዲቀመጥ።

**፭ኛ** ፡ የላስታው ፡ መስፍን ፡ ከንጉሡ ፡ በተገናኘ ፡ ጊዜ ፡ ወንድም ፡ ከወንድሙ ፡ በተገናኘ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚያደርገው ፡ እንዲሰላለሙ ፡ እንጂ ፡ የላስታው ፡ መስፍን ፡ እንደሌሎቹ ፡ መሳፍንት ፡ መሬት ፡ እንዳይስም።

**፮ኛ** ፡ እንደሌሉቹ ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ ግብር ፡ እንዳይገብር ፡ መጥን ፡ አውጣ ፡ ተብሎም ፡ እንዳይታዘዝ ፡

ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይኸን ፡ አዋውለው ፡ መንግሥቱን ፡ ከላስታ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ከዛጐዬ ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ሰሎሞናዊው ፡ ዘር ፡ ስለአስመለሱ ፡ በላይ ፡ በግዕዙ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ለዚሁ ፡ ውለታ ፡ እንዲሆን ፡ በጠቅላላው ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ በዝርዝር ፡ በያውራጃው ፡ ያሉትን ፡ ገዳማትና ፡ ኣብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መነኰሳቱንና ፡ ቀሳውስቱን ፡ ካህናቱን ፡ የሚያስተዳድሩበት ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሲሶ ፡ ከሦስት ፡ ኣንዱን ፡ እጅ ፡ በመሐላ ፡ ሰጣቸው ፡ ማለት ፡ ነው።

እንግዲህ ፡ በዚሁ ፡ በእርቀ፡ና ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ በመላው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሲነግሥ ፡ ከነአኵቶ ፡ ለአብ ፡ በኋላ ፡ የአፄ ፡ ላሊበላ ፡ ልጅ ፡ ይትባረክ ፡ በላስታ ፡ ኣልጋ ፡ ተቀመጠ። ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ መይራሪ ፤ ከመይራሪ ፡ ቀጥሎ ፡ ሐርቤይ ፡ ላስታን ፡ ብቻ ፡ በመግዛት ፡ ይቀጥሉ ፡ ጀመር። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ነአኵቶ ፡ ለአብ ፡ በውልና ፡ በመሐላ ፡ የለቀቀውን ፡ የዙፋን ፡ መብት ፡ ተከታዮቹ ፡ ይትባረክም ፡ መይራሪም ፡ ሐርቤይም ፡ ስላልተቀበሉት ፡ ሁሉም ፡ በየዘመናቸው ፡ ጦርነት ፡ እየቀሰቀሱ ፡ ተዋግተዋል ፡ ይባላል። ነገር ፡ ግን ፡ ይኵኖ ፡ አምላክና ፡ ተከታዮቹ ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብና ፡ መኳንንት ፡ የቤተ ፡ ክህነትም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ስለአበሩላቸው ፡ የነሱ ፡ ኃይልና ፡ ሥልጣን ፡ እየበረታ ፡ መንግሥታቸው ፡ እየደረጀ ፡ ሲሄድ ፡ የነዚያ ፡ ግን ፡ እየደከመ ፡ ሄደ።

ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ መንግሥትን ፡ የያዘበት ፡ ጊዜ ፡ ባንዳንድ ፡ መጽሓፍ ፡ እየተቃወሰ ፡ ቢገኝም ፡ ወደፊት ፡ ምክንያቱን ፡ ጭምር ፡ እንደምናስረዳው ፡ ሺ፪፻፷፪ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ ነው።

ይኸን ፡ ከተመለከትን ፡ በኋላ ፡ ይኸን ፡ መንግሥት ፡ በማዘዋወር ፡ ወይም ፡ የሐዋርያነት ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሆኑት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የግል ፡ ታሪካቸውን ፡ በሚቀጥለው ፡ እንመልከት።

# ምዕራፍ ፡ ፪

## የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አጭር ፡ ታሪክ።

የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ታሪክ ፡ የሚናገረው ፡ የራሳቸው ፡ ገድል ፡ ገድላ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚባለው ፡ ነው። በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ልደታቸው ፡ ዕድገታቸው ፡ ሐዋርያነታቸው ፡ ከሚያስደንቅ ፡ ከብዙ ፡ ተአምራትጋር ፡ ተጽፏል። ይኸውና ፡ ገድላቸው ፡ እንደሚለው ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘር ፡ ከላይ ፡ ከኣዳም ፡ እስካ ፡ ኣብርሃም ፡ ከአብርሃም ፡ እስከ ፡ አዛርያስ (ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጋር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደአክሱም ፡ የመጣው። ከኣዛርያስ ፡

እስከዘርዓ ፡ ዮሐንስ (ጸጋዘኣብ ፡ ኣባታቸው) ፡ ድረስ ፡ እየተቀጣጣላ ፡ የመጣ ፡ ነው። ከዚሁ ፡ በማያያዝ ፡ ይኸው ፡ ገድላቸው ፡ የሚለውን ፡ እንመልከት።

«ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ አግብቶ ፡ በቡልጋ ፡ አውራጃ ፡ እቲሳ ፡ በሚባል ፡ ኣገር ፡ ሲኖር ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ሞተለሚ ፡ የሚባል ፡ የወላሞ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር። ይኸን ፡ ንጉሥ ፡ ረኔ ፡ በሴትና ፡ ኣንድ ፡ ኣንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሞታላሚ ፡ የዳሞት ፡ ገዥ ፡ ብለውት ፡ ይገኛል። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሞተለሚ ፡ ሞታላሚ ፡ ካገሩ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ ፡ ሸዋን ፡ ያጠፋ ፡ ጊዜ ፡ ወደቡልጋ ፡ መጥቶ ፡ የጸጋ ፡ ዘአብን ፡ ሚስት ፡ እግዚእ ፡ ሐረያን ፡ ማርኮ ፡ ወሰዳት። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ በተኣምራት ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ወደ ፡ ኣገሯ ፡ ወደ ፡ ቡልጋ ፡ ተመልሳ ፡ ከባሏ ፡ ከጸጋዘአብ ፡ ጋር ፡ ተገናኘች። ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ስለሚስቱ ፡ መማረክ ፡ እያዘነ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ይኖር ፡ ነበርና ፡ ሚስቱን ፡ በማግኘቱ ፡ ደስ ፡ አለው። ብዙ ፡ ጊዜም ፡ እንደኖሩ ፡ በሺ፻፶፪ ፡ ዓም ፡ በታኅሣሥ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደችለትና ፡ ስሙ ፡ ፍሥሐ ፡ ጽዮን ፡ ተብሎ ፡ ተሠየመ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ በበረሀ ፡ ተገልጸ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብሎ ፡ ሠየማቸው ፡ ይላሉ ፤ ከዚያየዲቁና ፡ ማዕርግከአባ ፡ ጊርሎስ ፡ ተቀብለው ፡ ቀጥሉም ፡ የምንኵስና ፡ ማዕርግ ፡ ተቀብለው ፡ በሸዋ ፡ በዳሞት ፡ እየተመላለሱ ፡ ወንጌልን ፡ በትጋት ፡ ያስተምሩ ፡ ጀመር። ብዙ ፡ ኣረማውያን ፡ ወደክርስትና ፡ መለሱ ፤ በእጃቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተአምራት ፡ ተፈጸመ ፤ ከዚያ ፡ በወግዳ ፡ በግራርያ ፡ ገዳማትን ፡ ገደሙ። በሸዋ ፡ ያላውም ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ የተገደመው ፡ በርሳቸው ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ ገዳም ፡ የቀድሞ ፡ ስሙ ፡ ደብረ ፡ አስቦ ፡ ነው ፤ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ ባፄ ፡ ዘርዐያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ ነው።

የመጨረሻው ፡ ግብፃዊው ፡ ጳጳስ ፡ ለኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የዲቁና ፡ ማዕርግ ፡ የሰጡት ፡ አባ ፡ ጌርሎስ (ኪዬርሎስ) በሺ፪፻፵ ፡ ዓም ፡ ከሞቱ ፡ ወዲህ ፡ በግብፅ ፡ ኣገር ፡ እስላሞቹ ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ላይ ፡ ጥላቻ ፡ ስላበዙ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በጠቀስነው ፡ በመስቀል ፡ ጦርነት ፡ ምክንያት ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ በእስላሞቹ ፡ ላይ ፡ ስለተጫኑ ፡ እንደዚሁም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሸዋ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ከአዳሎቹ ፡ እስላሞች ፡ ጋር ፡ እየተዋጉ ፡ ስላጠቁ ፡ ይኸንንም

፡ የግብፁ ፡ ሡልጣን ፡ ስለሚያውቅ ፡ ከግብፅ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፡ እንዳይመጣ ፡ ከለከለ። ስለዚህ ፡ የጵጵስናው ፡ ሥፍራ ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ባዶ ፡ በመሆኑ ፡ ቅስናም ፡ ዲቍናም ፡ የሚሰጥ ፡ በመጥፋቱ ፡ ያሉትም ፡ እየሞቱ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ ተፈጠረ። በዚህም ፡ ዓይነት ፡ የቆየ ፡ እንደሆነ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ጨርሶ ፡ የመጥፋት ፡ አደጋ ፡ እንዳያገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ከየገዳማቱ ፡ ከየአድባራቱ ፡ ተሰብስበው ፡ ከግብፅ ፡ ጳጳስ ፡ የምናስመጣበት ፡ ጊዜ ፡ እስኪገኝ ፡ ድረስ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተወላጅ ፡ ፩ ፡ ምግባሩ ፡ የቀና ፡ ሃይማኖቱ ፡ የጸና ፡ ሰው ፡ እንምረጥ ፡ ብለው ፡ ጉባዔ ፡ አደረጉ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ምግባርና ፡ ሃይማኖት ፡ እየዞሩ ፡ ማስተማራቸው ፡ ሁሉ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ ታውቆ ፡ ነበርና ፡ በጉባኤው ፡ የተቀመጡት ፡ ሁሉ ፡ ርሳቸውን ፡ መረጧቸው።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በቀድሞ ፡ ክብራቸው ፡ ላይ ፡ የጵጵስና ፡ ሥልጣን ፡ ሲጨምሩ ፡ አባትነታቸውና ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥልጣናቸው ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተዘረጋ። እንግዴህ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዘውድና ፡ ዙፋንንም ፡ ከዛጉዬ ፡ ዘር ፡ ከነአኵቶ ፡ ለአብ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ዘር ፡ ወደ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ያስመለሱት ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ነው። መንግሥትንም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ ካዘዋወሩ ፡ በኋላ ፡ አዲሱን ፡ ንጉሥ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክን ፡ በጵጵስናቸው ፡ ቀብተው ፡ አነገሡ።

አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከሥጋዊው ፡ ወገን ፡ ይበልጥ ፡ ለመንፈሳዊው ፡ ወገን ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይልቁንም ፡ ለወንጌልና ፡ ለክርስትና ፡ መስፋፋት ፡ ስለጣሩ ፡ ባይበልጥ ፡ እንኳ ፡ ቀጥራቸው ፡ እንደ ፡ መዠመሪያው ፡ ጳጳስ ፡ እንደ ፡ ኣቡነ ፡ ዕላማ (ፍሬምናጦስ) እንደ ፡ ተሰዓቱ ፡ ቅዱሳን ፡ እንደነ ፡ አቡነ ፡ ኣረጋዊ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ናቸው። እነዚያ ፡ ከውጭ ፡ የመጡ ፡ ሲሆኑ ፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ያገር ፡ ተወላጅ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በመሆናቸው ፡ ይበልጥ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ ሊከበሩ ፡ ሊወደዱ ፡ ይገባል። በእርግጥም ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ከ፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ የተጻፈውን ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ሁሉ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱንም ፡ ስንከሣሩንም ፡ ገድሉንም ፡ ሁሉ ፡ ስንመለከት ፡ “ ኣብ ፡ ብፁዓዊ ፤ ክቡር ፤

ርእሰ ፡ አበው ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት» ፡ እያለ ፡ ለርሳቸው ፡ የሚሰጣቸው ፡ አርእስትና ፡ ስያሜ ፡ ከነዚያ ፡ የተለየ ፡ ነው።

ከእስክንድርያና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በክርስቶስ ፡ ባሕርይ ፡ የተነሣ ፡ ከቀድሞው ፡ ዠምሮ ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ ያለው ፡ ትልቍ ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንኳን ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ውስጥ ፡ እርሳቸውን ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ጻድቅ ፡ ቆጥሮ ፡ በቅዱሳኑ ፡ መንፈሳዊ ፡ መዝገብ ፡ አግብቶ ፡ በዓላቸውን ፡ ያከብራል ፤ አንቷን ፡ ዳባዲ ፡ ያዘጋጀውን ፡ የእጅ ፡ ጽሑፋችንን ፡ ዝርዝር ፡ በገጽ ፡ ፵፫ ፡ ቀጥር ፡ ፵ ፡ ባሴትረኔ ፡ በታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ትርጕሙን ፡ ገጽ ፡ ፱፻፴፪። ቀጥር ፡ ፳፬ ፡ ተመልከት።

አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በጵጵስና ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ አፄ ፡ አፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ ኣልፈው ፡ ባፄ ፡ ያግብኣ (አግብኣና ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ የግብፅ ፡ መንገድ ፡ ስለተከፈተና ፡ በካሊፋው ፡ ፈቃድ ፡ ከእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ተሾመው ፡ ኣባ ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለመጡ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የጵጵስና ፡ ሥራቸውን ፡ ላዲሱ ፡ ጳጳስ" ፡ ኣስረከቡ። ጳጳሱ ፡ ግን ፡ ኣብረን ፡ ጳጳስና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ሆነን ፡ ወይም ፡ ተካፍለን ፡ እንሥራ ፡ ብላዋቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል። እርሳቸው ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜያቸውም ፡ ስለሸመገለ ፡ የዚህን ፡ ሃሳብ ፡ ሳይቀበሉ ፡ የጵጵስናውን ፡ መሣሪያ ፡ መጽሐፈ ፡ ክህነቱን ፡ ቅብዓ ፡ ቅዱሱን ፡ ሚሮኑን ፡ ኣስረከበው ፡ ከጳጳሱ ፡ ተሰናብተው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ አስቦ (ደብረ ፡ ሊባኖስ-ግራርያ) ፡ መጥተው ፡ በራሳቸው ፡ ገዳም ፡ ሲኖሩ ፡ በነሐሴ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ በሺይ ፡ ፻፳፮ ፡ ዓም ፡ ዐረፉና ፡ በዚያው ፡ ተቀበሩ።

የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ታላቅነትና ፡ መንፈሳዊነት ፡ ከሚያስረዱት ፡ ከብዙዎቹ ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ አንባቢ ፡ ሊረዳላቸው ፡ የሚገባው ፡ በጳጳስነት ፡ ሲገዙ ፡ ኖረው ፡ በዚያው ፡ በዘመናቸው ፡ ጳጳስ ፡ እንዲመጣ ፡ መፍቀዳቸው ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ ለሥልጣኑ ፡ ሳይጓጉ ፡ ሳይቀኑም ፡ ጠብና ፡ ጦርነትም ፡ ሳያስነሡ ፡ በሰላም ፡ አስረከበው ፡ እርሳቸው ፡ ወደገዳማቸው ፡ መሄዳቸው ፡ ነው።

ይኸን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ታሪካቸውን ፡ ታላላቅ ፡ ተአምራትና ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ እየጨመረ ፡ የሚናገረው ፡ የራሳቸው ፡ ገድል ፡ መሆኑን ፡ ባለፈው ፡ ኣመልክተናል። እኔ ፡ ግን ፡ የዛሬ ፡ ኣንባቢ ፡ የማያምነውን ፡ ተኣምራት ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ እየተውሁ ፡ የታሪኩን ፡ ክፍል ፡ ከዚሁ ፡ ከገድሉና ፡ ከየታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ወይም ፡ ፈረንጆቹ ፡ ከየታሪኩ ፡ የላቀሙትን ፡ አጠራቅሜ ፡ ጽፌዋለሁ።

በየገድሉ ፡ በየታሪኩ ፡ ውስጥ ፡ እንደተገኘው! ፡ የተወለዱበት ፡ በ፩፻፵፪ ፡ ዓም ፡ የዐረፉት ፡ በሺ፪፻፲፮ ፡ ዓም ፡ሲሆን ፡ ዕድሜያቸው ፡ በሙሉ ፡ ፩፻፲ ፡ ዓመት ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው። ይኸም ፡ የዕድሜ ፡ ብዛት ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ላደለው ፡ ለብዙ ፡ ሰው ፡ የሚቻል ፡ ስላሆነ ፡ የሚያከራክር ፡ ነገር ፡ የለበትም። በገድለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በዜና ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደዚሁም ፡ በብዕለ ፡ ነገሥት ፡ በስንክሣር ፡ ውስጥ ፡ ስለርሳቸው ፡ በኣንዳንድ ፡ ነገር ፡ እየተለያየ ፡ ይነገራል። ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተጻፈው ፡ ኣብዛኛው ፡ ልደታቸውንና ፡ እድገታቸውን ፡ እቲሳ (ቡልጋ ፡ ውስጥ) ሲል ፡ ግማሹ ፡ «ሙላዱሰ ፡ ምድረ ፡ ኣምሓራ ፡ እንተ ፡ ትሰመይ ፡ ባሕረ ፡ ቀጋ ፡ ወዘመዱ ፡ ሐርብ ፡ ጋሴ ፡ ወእምህየ ፡ ፈለሰ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ይድላ ፡ ብሔረ ፡ ሴዋ (ሸዋ) ወበጽሐ ፡ ጽላልሽ ፡ ወነበረ ፡ ምድረ ፡ ዘረሬ ፡ ወወለደ ፡ ሕይወተነ ፡ በጽዮንሃ ፡ ...» ፡ ይልና ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ልደትና ፡ እድገት ፡ ዘረሬ ፡ በሚባል ፡ ሥፍራ ፡ ያደርገዋል። በዚያው ፡ በእቲሳ ፡ ዘረሬ ፡ የሚባል ፡ ክፍል ፡ እንዳለ ፡ አላውቅም። ጽላልሽ ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የቡልጋ ፡ ስም ፡ መሆኑ ፡ እርግጥ ፡ ነው። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይኸን ፡ በመሳሰላ ፡ በስም ፡ ኣጠራር ፡ ከመላያየቱ ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግባር ፡ ዙፋንን ፡ ከዛጕዬ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ዘር ፡ ለማስመለስ ፡ መድከማቸው ፡ ለዚሁም ፡ እንደ ፡ ውላታ ፡ ሆኖ ፡ ከአዲሱ ፡ ንጕሥ ፡ ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በእጨጌነት ፡ ሲያስተዳድሩ ፡ ለመነኰሳት ፡ ለቀሳ ፡ ውስት ፡ ለካህናት ፡ መተዳደሪያ ፡ እንዲሆን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሲሶ ፡ መንግሥት ፡ ማግኘቷቸውን ፡ ጽሑፉ ፡ ሁሉ ፡ በትክክል ፡ ተስማምቶ ፡ ይተርክልናል።

እናታቸውን ፡ ማርኮ ፡ የወሰደውን ፡ሞተለሜን ፡ ግን ፡ ግማሹ ፡ የወላሞ ፡ ንጕሥ ፡ ግማሹ ፡ የዳሞት ፡ ንጕሥ ፡ እያላ ፡ ጽሑፍ ፡ ሁሉ ፡ የአንባቢን ፡

ኣሳብ ፡ ሲያደናግር ፡ ይኖራል። ደንበኛውንና ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡ የተከተልን ፡ እንደሆነ ፡ የዳሞት ፡ ንጉሥ ፡ ብላን ፡ ልንጽፍም ፡ ልናነብም ፡ ይገባል። በዚህ ፡ ዘመን ፡ የነበሩ ፡ የዓረብ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እነ ፡ ኢብን ፡ ሐልዱን ፡ የግብፆቹም ፡ ሁሉ ፡ እንደሚገልጹት ፡ በዛጕዬ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ይልቍንም ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ግድም ፡ የዳሞት ፡ ባላባት ፡ አይሎ ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ፤ ግዛቱም ፡ በሸዋ ፡ ምዕራብ ፡ ከጐጃም ፡ ደቡብ ፡ ገርምሮ ፡ የዛሬውን ፡ የሊሙን ፡ የወለጋን ፡ የኖኖን ፡ የጨቦን ፡ የጕራጌን ፡ የሶዶን ፡ የወላሞን ፡ .... ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ሲገዛ ፡ ቆይቶ ፡ በመጨረሻም ፡ በተጕለትና ፡ በቡልጋ ፡ አልፎ ፡ የታወቀውን ፡ የይፋቱን ፡ ባላባት ፡ ሳይቀር ፡ አሸንፎ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ፡ የዚህም ፡ ገዥ ፡ ወላሞን ፡ ሌላውንም ፡ መደረቡ ፡ ስላልቀረ ፡ በጠቅላላው ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ የገዛው ፡ የዳሞት ፡ ባላባት ፡ ስለሆነ ፡ የአቡነ ፡ ተክላሃይማኖትን ፡ እናት ፡ እግዚእ ፡ ኀረያን ፡ የማረከውን ፡ ሞተለሚ (ሞቲላሜ) የዳሞት ፡ ንጉሥ ፡ ብሎ ፡ ማንበብ ፡ የሚገባ ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ የዳሞት ፡ ገዥ ፡ መሆኑን ፡ እንጂ ፡ ዘሩ ፡ ወላሞ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ዳሞት ፡ መሆኑን ፡ ማረጋገጥ ፡ አይቻልምና ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጕዳይ ፡ ኣልፈን ፡ ስላሲሶው ፡ መንግሥት ፡ በሚቀጥለው ፡ እንመልከት።

# ምዕራፍ ፡ ፫

## በአፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክና ፡ በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ሲሶ ፡ መንግሥት።

ብዕለ ፡ ነገሥት ፡ የሚባል ፡ ያገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ ኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክን ፡ ሲያነግሡ ፡ የተዋዋሉትን ፡ የሲሶ ፡ መንግሥት ፡ ውል ፡ ይገልጻል። ብዕለ ፡ ነገሥትን ፡ ሲመለከቱት ፡ እርሳቸው ፡ የጻፉት ፡ ወይም ፡ ያጻፉት ፡ ይመስላል። ነገር ፡ ግን ፡ ዝተረክበ ፡ በእደ ፡ አቡነ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ ስለሚል ፡ ራሳቸው ፡ ሳይጽፉት ፡ በርሳቸው ፡ ኣዛዥነት ፡ ተጽፎ ፡ ይሆናል።

ከመዠመሪያው ፡ ላይ ፡ ዐስመ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ናሁ ፡ ንጽሕፍ ፡ መጽሐፈ ፡ ዘስሙ ፡ ብዕለ ፡ ነገሥት ፡ ዘተረክበ ፡ በእደ ፡ ኣቡነ ፡ ክቡረስም ፡ ኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘውገ ፡ መላእክት ፡ ወትሩፈ ፡ ምግባራት ፤ ይላል ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ከዚያውም ፡ አባ ፡ ኵልቦ ፡ በ፪፻፳፩ ፡ ገጽ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ላይ ፡ አባ ፡ ሰላማና ፡ ንጉሡ ፡ ያግብኣ ፡ ጽዮን ፡ በ፲፱ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ነው ፡ ያጻፉት ፡ ይላሉ። ነገር ፡ ግን ፡ ያግብአ ፡ ጽዮንም ፡ ጳጳሱም ፡ የነበሩት ፡ በ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ እንጂ ፡ በ፲፬ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኣልነበሩም። በዚህም ፡ በ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻም ፡ በኣፄ ፡ ያግብአ ፡ ጽዮንና ፡ በጳጳሱ ፡ በአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘመን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በእጨጌነት ፡ ስለነበሩ ፡ እርሳቸው ፡ አጽፈውታል ፡ ማለት ፡ ይቀላል። ይልቍንም ፡ ጳጳሱ ፡ ግብፃዊ ፤ ቋንቋቸው ፡ ኣረብኛ ፡ ስለሆነ ፡ ለግእዙ ፡ ጽሑፍ ፡ ጳጳሱም ፡ ንጉሡም ፡ በቀጥታ ፡ አግባብና ፡ ችሎት ፡ ያላቸው ፡ ኣይመስልም። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ የዚህን ፡ ጕዳይ ፡ እንተውና ፡ ስለሲሶው ፡ መንግሥት ፡ በየዓይነቱ ፡ በየጊዜው ፡ የተጻፈው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ሁሉ ፡ ባጭሩ ፡ የሚለውን ፡ እንደሚከተለው ፡ እንመልከት።

ወእድም ፡ ሰገድ ፡ ወለዶ ፡ ለይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ ዘሜጠ ፡ ሎቱ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መንግሥተ ፡ እምነ ፡ ዛጔ ፡ እንዘ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃማይኖት ፡ ፵ወ፫ ፡ ዓመት ፡ ውእቱኒ ፡ አፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ ተካየደ ፡ ምስለ ፡ ኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወወሀቦ ፡ ሲሶ ፡ መንግሥት ፡ ወእምይእዜ ፡ ይሰመይ ፡ ዘመን ፡ ዘመነ ፡ —ኪዳን ፡ ትርጓሜ ፡ ——_እድም ፡ ሰገድ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክን ፡ ወለደ ፡ ለርሱም ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መንግሥትን ፡ ከዛጕዬ ፡ ኣስመለሱለት። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዕድሜ ፡ ፴፫ ፡ ዓመት ፡ ነበር። ይኸም ፡ ይከኖ ፡ አምላክ ፡ ሲሶ ፡ መንግሥትን ፡ ሰጣቸውና ፡ ከአባታችን ፡ ከአቡነ ፡ ተከላ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ። ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ዘመን ፡ ይባላል———

ከጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ኣሚድ ፡ የተገኘው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደጻፍነው ፡ ከዚህ ፡ ከላይኛው ፡ ለየት ፡ ያደርግና ፡ በዙፋን ፡ ማስመለሱ ፡ ሥራ ፡ ጳጳሱ ፡ አባ ፡ ጌርሎስ (ለተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሊቀ ፡

ዲቁና ፡ የሰጡት) የሐይቁ ፡ መምሕር ፡ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓ ፡ ከአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋር ፡ እንዳሉበት ፡ ለማመልከት ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ የገለጸውን ፡ ደግመን ፡ እንመልከተው ፡ «.... ፡ ለይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዘሜጠ ፡ መንግሥተ ፡ እምነ ፡ ዛጔ ፡ በጸሎት ፡ ጳጳስ ፡ ኣባ ፡ ጌርሎስ ፡ ወበጸሎተ ፡ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓ ፡ መምሕረ ፡ ሐይቅ፣ወበትንብልናሁ ፡ ለአብ ፡ ብፁዓዊ ፡ ክቡር ፡ ርእሰ ፡ ኣበው ፡ ኣቡነ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ መምሕር ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ። እስመ ፡ ነበሩ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ኵሎ ፡ ኖኅ ፡ መንግሥቱ ፡ ወበእንተዝ ፡ ወሀቦሙ ፡ ለውሉዱ ፡ ፩ደ ፡ እደ ፡ እም፫ቱ ፡ እድ ፡ መንግሥተ ፡ ወምናነ ፡ ወሥልጣነ ፡ ወሣመ ፡ እምውሉደ ፡ ኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እጨጌ ፡ በኪዳን ፡ ወመሐላ ፡ ወእምውሉደ ፡ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ከመ ፡ ይኵን ፡ ሎሙ ፡ ርስተ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡

እንግዴህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የምንመለከተው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገልጽልን ፡ በድልነዓድ ፡ ዘመን ፡ መራ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለዛጉዬ ፡ ዘር ፡ ወስዶ ፡ ለተከታዮቹ ፡ አውርሶ ፡ የነበረውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዘውድና ፡ ዙፋን ፡ ባዔ ፡ ነአኵቶ ፡ ለኣብ ፡ ዘመን ፡ ጳጳሱ ፡ ኣባ ፡ ጌርሎስ ፡ የሐይቁ ፡ መምሕር ፡ አባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓ ፡ ይልቁንም ፡ ከሁለቱ ፡ በበለጠ ፡ በታላቅ ፡ ትጋት ፡ በሰሜው ፡ በነኣነቶ ፡ "ላኣብና ፡ በተቀባዩ ፡ በይኵኖ ፡ አምላክ ፡ መካከል ፡ ሆነው ፡ በንግግርም ፡ በምክርም ፡ በመንፈሳዊነትም ፡ ተጭነው ፡ ለማስመለስ ፡ የቻሉት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መሆናቸውን ፡ ይገልጽልናል። ጸሐፊው ፡ ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ በ፲፬ኛውና ፡ በ፲፫ው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣውን ፡ ቃልና ፡ ጽሑፍ ፡ እየመረመረ ፡ ሲያዘጋጅ ፡ ጳጳሱን ፡ አባ ፡ ጌርሎስን ፡ ጨመራቸው ፡ እንጂ ፡ ዙፋን ፡ በተለዋወጡበት ፡ ሰዓት ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ በነገሠበት ፡ እንደ ፡ ኤው ቀ ፡ ፲፪፻፸ ፡ እንደ ፡ ኢት ፡ ሺ፪፻፷፪ ፡ ዓ.ም ፡ ዘመን ፡ አባ ፡ ጌርሎስ ፡ የሉም ፡ ከሞቱ ፡ ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ ይሆናቸዋል።

ነገር ፡ ግን ፡ ዙፋን ፡ ሸዋው ፡ ላለው ፡ ለነጋሢ ፡ ዘር ፡ እንዲመለስ ፡ በጊዜያቸው ፡ እንኳን ፡ እርሳቸው ፡ በቅርብ ፡ ያሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፡ የሆኑትና ፡ በሩቅ ፡ ያሉት ፡ የእስክንድርያው ፡ ፓትርያርክ ፡ ሳይቀሩ ፡

ከዛጒዬዎቹ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንዳይጣሉ ፡ ጥንቃቄን ፡ እየጨመሩ ፡ ውስጡን ፡ ዙፋኑ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ እንዲዛወር ፡ በኣሳብ ፡ ደግፈዋል።

ከሸዋም ፡ ድረስ ፡ መልክተኞች ፡ ካይሮ ፡ ድረስ ፡ እየሄዱ ፡ መነጋገራቸውን ፡ በቅዱስ ፡ ሐርቤ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ተመልክተናል።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ለነዚህ ፡ ለዙፋን ፡ አስመላሾችና ፡ ለታላላቅ ፡ የቤተክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እንደውለታ ፡ ተቆጥሮ ፡ ለአባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዓና ፡ በሐይቅ ፡ ገዳም ፡ በርሳቸው ፡ እግርለሚተካው ፡ መምህር ፡ የዓቃቤ ፡ ሰዓትነት ፡ ማዕርግ ፡ ተሰጣቸው። በኋላ ፡ የተነሡ ፡ ነገሥታት ፡ ግን ፡ የዓቃቤ ፡ ሰዓትን ፡ ማዕርግ ፡ ለሌላ ፡ ወገን ፡ መስጠታቸውን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ቀጥሎ ፡ ገልጿል ፡ ወዝኒ ፡ ሥርዓት ፡ ሀለወ ፡ ወኢፈለሰ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ለዓቃቤ ፡ ሰዓትሰ ፡ አፍለስዎ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ነገድ ፡ ነገሥት ፡ እለ ፡ እምድኅሬሁሥዒሮሙ ፡ ኪዳነ ፡ ዘመሐላ ፡ ሎመ ፡ ይኵኖአምላክ ፡ በስመ ፡ **እግዚአብሔር**……”

ይህ ፡ የዓቃቤ ፡ ሰዓትነት ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ ከአፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እስከ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ በምዕራፍ ፡ ፲፱ ፡ ገጽ ፡ ፸፬ ፡ እንደተገለጸው ፡ ንጕሡ ፡ በግብር ፡ ወይም ፡ በጉባዔ ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ በትረ ፡ ወርቅ ፡ ይዞ ፡ ቆሞ ፡ የሕግንና ፡ የወግን ፡ የሥርዓትን ፡ ነገር ፡ እያስተናበረ ፡ ያከናውናል። ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ታላቅ ፡ የተከበረ ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣን ፡ መሆኑን ፡ ወደፊት ፡ በነዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ በነ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ታሪክ ፡ እንመለከታለን።

ብዙ ፡ ለሠራ ፡ ዋጋው ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ በሥራቸው ፡ መጠን ፡ ለኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የተሰጠው ፡ ሲሶ ፡ መንግሥት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው። ይኸውም ፡ መደባቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ደብረ ፡ አስቦ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ ገዳም (ሸዋ) ፤ የማዕርግ ፡ ስማቸው ፡ እጨጌ. ፡ መምህር ፡ ዘደብረ ፡ ኣስቦ ፡ በኋላ ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ እየተባለ ፡ በሙሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ አግኝተው ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አገልጋዮች ፡ መነኮሳትን ፡ ቀሳውስትን ፡ ካህናትን ፡ ተማሪን ፡ የሚያስተዳድሩበት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሲሶ ፡

መንግሥት ፡ ከሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሦስቱ ፡ እጅ ፡ አንዱን ፡ እጅ ፡ ማግኘታቸው ፡ ትልቅ ፡ የአበል ፡ ውለታና ፡ ሥልጣን ፡ መቀበላቸውን ፡ ይገልጻል።

ይህ ፡ የሦስት ፡ እጅ ፡ ኣበሉና ፡ ሀብቱ ፡ በዛሬም ፡ በዚያን ፡ ዘመንም ፡ አእምሮ ፡ ሲገመት ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚሁ ፡ በተቀበለችው ፡ ኣበል ፡ ልክ ፡ የምትሠራ ፡ ከሆነ ፡ የአበሉ ፡ ብዛት ፡ በገማች ፡ ፊት ፡ ሊያሳጣም ፡ ሰጭውንና ፡ ተቀባዩንም ፡ ሊያስነቅፍ ፡ አይችልም።

ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚህ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ በመሐላ ፡ በሰጣት ፡ ሲሶ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ መብትና ፡ ሥልጣን ፡ ሲኖራት ፡ ልትፈጽመው ፡ የምትገደድበት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተግባር ፡ አለ። ይኸውም ፡ ተግባር ፡ ከመብቷ ፡ ጋር ፡ ትክክል ፡ እየሄደ ፡ ከክርስቶስ ፡ የተቀበለችውን ፡ ትእዛዝ ፡ በማክበር ፡ የሐዋርያትን ፡ ኣርአያ ፡ በመከተል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኣውራጃ ፡ ይልቁንም ፡ በአረመኔው ፡ ወይም ፡ በእስላሙ ፡ ክፍል ፡ ከአገር ፡ ወደ ፡ አገር ፡ እየተዘዋወረች ፡ ወንጌልን ፡ እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ በፈሊጥ ፡ እያስተማረች ፡ ብዙ ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ማምጣት ፤ ሕሙማንን ፤ እስረኛን፣እየዞሩ ፡ መጐብኘትና ፡ ማጽናናት ፡ መላውን ፡ ሕዝብ ፡ በአባትነትና ፡ በመንፈሳዊነት ፡ እየመከሩ ፡ ወደ ፡ በጎ ፡ ተግባር ፡ መምራት ፤ ከሕዝቡ ፡ ሥልጣኔ ፡ ከኣእምሮው ፡ እርምጃ ፡ ጋር ፡ ወደኋላ ፡ ሳይቀሩ ፡ አብረው ፡ እየተራመዱ ፡ <u>ረዓይኬ ፡ አባግዕየ ፡</u> እንዳለው ፡ የእረኝነትን ፡ የጠባቂነትን ፡ ተግባር ፡ መፈጸም ፤ ለቤተ ፡ ክህነትና ፡ ለድሆች ፡ ልጆች ፡ መንፈሳዊና ፡ ሥጋዊ ፡ የተደባለቀበት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለምሳሌ ፡ ወንጌልና ፡ አናጢነት ፡ ከመንግሥቱ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ እየተሻሙ ፡ መክፈትና ፡ ማስተማር ፡ ነበር ፡

ያለፈውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያናችንን ፡ ታሪክ ፡ የተመለከትን ፡ እንደሆነ ፡ በሙሉ ፡ እንደሚገባው ፡ አልተሠራም ፡ ለማለት ፡ አናፍርም ፡ በፍጹም ፡ ኣልተሠራም ፡ ለማለትም ፡ አንደፍርም። ነገር ፡ ግን ፡ የኛዎቹ ፡ ከሲሶ ፡ መንግሥት ፡ ኣበል ፡ ጋር ፡ ከሠሩት ፡ ይልቅ ፡ የመዠመሪያዎቹ ፡ ሐዋርያትና ፡ አርድእት ፡ ያለሲሶ ፡ ያለ ፡ ኣበል ፡ የሠሩት ፡ በሥራቸው ፡ ሁለቱም ፡ ያስገኙት ፡ ፍሬ ፡ ሲመዛዘን ፡ የነዚያ ፡ ከነዚህ ፡ በልጦ ፡ እንደሚገኝ ፡ ቅን ፡ ሕሊና ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ኣይስተውም።

በአክሱምም ፡ በላስታም ፡ በሸዋም ፡ በጐንደርም ፡ ዘመነመንግሥት ፡ የነበሩት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖቻችን ፡ ክርስትና ፡ ያልደረሰበትን ፡ አገር ፡ ኣሩሲን ፡ ወለጋን ፡ ባሌን ፡ ... ፡ ከማስተማር ፡ በበለጠ ፡ አሳባቸውንና ፡ ጊዜያቸውን ፡ ያጠፉት ፡ የነበረው ፡ ለክርስቶስ ፡ ባሕርይ ፡ ምርምርና ፡ ለክርክር ፡ ነበር። በዚህም ፡ የካራ ፡ የጸጋ ፡ የቅባት ፡ ወገን ፡ እየተባባሉ ፡ ጉባዔ ፡ እየተዘረጋ ፡ በረቂቁና ፡ በማይመረመረው ፡ በክርስቶስ ፡ ባሕርይ ፡ ሲከራከሩ ፡ ንጉሡም ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ እያከራከረ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ወዳንደኛው ፡ ወገን ፡ እየሆነእገሌ ፡ ተረታእገሌ ፡ ረታ ፡ እያሰኘ ፡ በዚሁም ፡ የተነሣ ፡ የማስተማሪያው ፡ የሐዋርያነቱ ፡ ጊዜ ፡ በከንቱ ፡ ከመጥፋቱ ፡ ይልቅ ፡ ጦርነት ፡ እየተነሣ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ሲፈስ ፡ ኖሯል።

ይኸን ፡ በመሰላ ፡ አሳዛኝሁኔታ ፡ የተገኘችውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ብቻ ፡ አይደለችም። ነገር ፡ ግን ፡ ኣርዮስን ፡ ከአስወገዱበት ፡ ከኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ ወዲህ ፡ ለክርስቶ ፡ ፪ ፡ ባሕርይና ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ ስለመኖሩ ፡ ክርስቶስ ፡ በረቂቅ ፡ ኣካል ፡ ወይም ፡ በጉልህ ፡ ኣካል ፡ ስለማረጉ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብና ፡ ከወልድ ፡ ስለመውጣቱ ፡ ወይም ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ ስለመስረፁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብና ፡ ከወልድ ፡ ጋር ፡ ትክክለኝነት (ዕሪና) ስለመኖሩ ፡ በየጊዜው ፡ ክርክር ፡ እየተነሣ ፡ በጉባዔ ፡ መታየቱ ፡ በጉባኤ ፡ ረቺና ፡ ተረቺ ፡ ተብለው ፡ የተላያዩት ፡ በመካከላቸው ፡ ቂምና ፡ በቀል ፡ አድሮ ፡ ሲጣሉ ፡ ሲዋጉ ፡ መኖራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው። በዚህ ፡ ጥልቅ ፡ በሆነው ፡ አምላካዊ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ወንድም ፡ ተከራክረው ፡ እንደወንድም ፡ ታርቀው ፡ ወይም ፡ የየራሳቸውን ፡ አሳብ ፡ ይዘው ፡ እንግዴህ ፡ ሁላችንም ፡ ወደ ፡ ሐዋርያነታችን ፡ እንሰማራ ፡ ማለት ፡ ኣልቻሉም። ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ቂሙ ፡ እየበሰለ ፡ ስለሔደ ፡ ላበቀል ፡ መመለሻ ፡ የንግግርም ፡ የጽሑፍም ፡ አሳብ ፡ በማሰላሰል ፡ ረዥም ፡ ጊዜ ፡ የፈጁ ፡ መሆናቸውን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተመልክተናል።

በዚህ ፡ በሁለቱ ፡ በሮማና ፡ በእስክንድርያ ፡ ክርክርና ፡ ጠበኛነት ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ የተጠቀመ ፡ የእስላም ፡ ሃይማኖትን ፡ መሥራቹ ፡ መሐመድ ፡ ነው። ባለፈው ፡ እንደተገነዘብነው ፡ የሁለቱ ፡ ጠብ ፡ እየጋላ ፡ በሄደበት ፡ በ፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ መሐመድ ፡ ተነሥቶ ፡ እነሱ ፡ በባሕርይ ፡ እየተከራከሩ

፡ ሲጣሉ ፡ ሲዋጉ ፡ እርሱ ፡ የእስላምን ፡ አዲስ ፡ ሃይማኖት ፡ በኣዲስ ፡ ሥርዓት ፡ ለተርታ ፡ ሕዝብ ፡ እንደሚገባ ፡ በቀላል ፡ መንገድ ፡ መሠረተና ፡ በንግግርም ፡ በጦርነትም ፡ በቶሎ ፡ እንዲስፋፋ ፡ አደረገ። ከጠባቸውና ፡ ከቂማቸው ፡ መብሰል ፡ የተነሣ ፡ የእስክንድርያ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የቍስጥንጥንያዎቹን ፡ ባለሥልጣኖች (ካቶሊኮቹን) ከግብፅ ፡ ለማስወጣት ፡ ሲሉ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ ተባበሩ ፡ ይባላል።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ አሳዛኝ ፡ መሆኑ ፡ ወደኋላም ፡ ተመልሶ ፡ ስሕተትን ፡ ማረም ፡ የማይቻል ፡ መሆኑ ፡ ታውቆ ፡ ከመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ወዲህ ፡ ያሉ ፡ የሮማም ፡ የምሥራቅም ፡ የምዕራብም ፡ ኣብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የቤተክርስቲያናቸውን ፡ ደንብና ፡ ሥርዓት ፡ እያደሱ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የሚያስነቅፈውን ፡ እያሻሻሉ ፡ ለማስተር ፡ በያገሩ ፡ በያውራጃው፣ ፡ ሚኪዮናዊ (መምህር) ፡ ሲልኩ ፡ እናያለን። ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ከአባ ፡ ሰላማ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ድረስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተወሰነ ፡ አበል ፡ ስለሌላት ፡ ባንዳንድ ፡ ነገሥታትና ፡ ታላላቅ ፡ ሰው ፡ ስጦታ ፡ እየተዳደረች ፡ የማስተማርን ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሳታስፋፋ ፡ የያዘችውንም ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ሳትለቅ ፡ ቆየች።

ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ለኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሲሶ ፡ መንግሥት ፡ ከሰጠ ፡ ወዲህ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ በዚህ ፡ ለመንግሥት ፡ በማትገብርበት ፡ ሲሶ ፡ መንግሥት ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ከየሀብታሙ ፡ በስለት ፡ በስጦታ ፡ በምታገኘው ፡ ሀብት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሀብታምሆነች። የገዳማት ፡ የአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የመነኮሳት ፡ የቀሳውስት ፡ የዲያቆናት ፡ ቀጥር ፡ እየበረከተ ፡ ሄደ። ከዚሁ ፡ ሀብት ፡ የተነሣ ፡ ቤተ ፡ ክህነትን ፡ የሚያገለግለው ፡ ወገን ፡ ቤተመንግሥትን ፡ ከሚያገለግለው ፡ የማያንስ ፡ ሆነ። በየገዳማቱ ፡ በየአብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ አጠገብ ፡ ከየአገሩ ፡ ከየመንደሩ ፡ የሚመጣላቸውን ፡ የሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ በረከቱ። የሀብቱ ፡ ኣሰባሰብና ፡ አያያዝ ፡ በደንብ ፡ ባይከናወንም ፡ በዚህ ፡ በሲሶ ፡ መንግሥት ፡ ቤተ ፡ ክህነትን ፡ የተጠጋ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ኣቅሙ ፡ ይተዳደርበት ፡ ዠመር። ነገር ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ያንኑ ፡ የያዘውን ፡ ከማጽናት ፡ ወይም ፡ መንፈሳዊ ፡ ትምህርቱን ፡ ዜማውን ፡ ቅኔውን ፡ ብሉይና ፡ ሐዲሱን ፡ ሁሉምእንደ ፡ ችሎቱ ፡ ከመማር ፡ ከማስተማር

፡ ከመመራመር ፡ በቀር ፡ ካለሁበት ፡ ከአክሱም ፡ ከላስታ ፡ ከሸዋ ፡ ከጐንደር ፡ ወይም ፡ ከደብረቢዘን ፡ ከደብረዳሞ ፡ ከደብረ ፡ ሐይቅ ፡ ከደብረሊባኖስ ፡ ከስፍራዬ ፡ ከበኣቴ ፡ ተነሥቼ ፡ ወለጋ ፡ አሩሲ ፡ ባሌ ፡ ሐረርጌ ፡ .... ሄጄ ፡ ሕዝቡን ፡ በክርስትና ፡ አሳምኜ ፡ ሐዋርያ ፡ ልሁን ፡ ብሎ ፡ የሚነሣ ፡ መምህርና ፡ ቄስ ፡ በልክ ፡ ነው። የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለሥልጣኖችም ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ከውስጣቸው ፡ እየመለመሉ ፡ ለመላክ ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ኣልጣሩበትም ፡ ነበር።

ያለዚያ ፡ እላይ ፡ ስማቸውን ፡ ያነሣናቸው ፡ ኣውራጃዎች ፡ ሁሉ ፡ ዛሬ ፡ ባሉበት ፡ ባረመኔነት ፡ ወይም ፡ በእስላምነት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ አይገኙም ፡ ነበር። ይኸም ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ በውጭ ፡ ኣገር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ እንደሚታየው ፡ በኛም ፡ እጨጌዎቹም ፡ የየገዳሙ ፡ መምህራን ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ መነቀፍ ፡ ኣይችሉም። አልፎ ፡ አልፎ ፡ በየዘመኑ ፡ ለክርስትና ፡ መስፋፋት ፡ በቀድሞው ፡ ጊዜ ፡ እንደነ ፡ አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ እንደነ ፡ አቡነ ፡ ጳንጠሌዎን ፡ እንደነ ፡ ኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያሉት ፡ እንደነበሩ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በ፲፬ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ እጨጌ ፡ ፊልጶስ ፡ መቀመጫቸውን ፡ ደብረሊባኖስ ፡ አድርገው ፡ እርሳቸው ፡ እንደ ፡ ሊቀ ፡ ሐዋርያ ፡ እንደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሆነው ፡ ሌሎች ፡ ፲፩ ፡ መምህራን ( ፡ የ፲፪ቱን ፡ ሐዋርያት ፡ ኣርአያ ፡ በመከተል) እየመረጡ ፡ በየአውራጃው ፡ እየተዘዋወራችሁ ፡ አስተምሩ ፡ እያሉ ፡ ይልኩ ፡ እንደነበረ ፡ የራሳቸው ፡ ገድል ፡ ገድለ ፡ ፊልጶስ ፡ ይገልጻልና ፡ ስለዚህ ፡ እርሳቸውንና ፡ እንደርሳቸው ፡ ያሉትን ፡ መምህራን ፡ አባቶችን ፡ ሳናመሰግን ፡ ማለፍ ፡ ኣይገባም።

አሁንም ፡ በዛሬ ፡ ዘመን ፡ ያሉት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ያለፈውን ፡ ሁሉ ፡ ተመልክተውየኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ይልቍንም ፡ የደቡቡን ፡ ክፍል ፡ ለማስተማር ፡ ሌላም ፡ የወጡኑት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ አስተዳደር ፡ ብዙ ፡ ደንብና ፡ ሥርዓት ፡ መኖሩን ፡ ስለምናውቅ ፡ አሳባቸው ፡ ሁሉ ፡ እየተቃና ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲደርስ ፡ ክልብ ፡ መመኘት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እኛም ፡ በሚቻላን ፡ ሁሉ ፡ የእርዳታ ፡ እጃችንን ፡ ልንዘረጋ ፡ ይገባል። ጉዳዩ ፡ በተላይ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝበት ፡ ሐተታ ፡ ብዙ ፡ ነው። የቤተ ፡ ክህነትናየቤተ ፡ መንግሥት

፡ የሃይማኖትና ፡ የፖለቲካ ፡ ኣንድነት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተያያዘ ፡ ስለሆነ ፡ ያንደኛው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መቅረት ፡ የሁለተኛውን ፡ እርምጃ ፡ ማበላሸቱ ፡ የታወቀ ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፬

## ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የነገሡበት ፡ ዘመን ፡ የነገሥታቱ ፡ ዝርዝርና ፡ የግዛታቸው ፡ ዘመን።

ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ የነገሡበት ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊው ፡ ሁሉ ፡ እየለያየ ፡ ስለሚጽፈው ፡ በዘመን ፡ ረገድ ፡ አንባቢን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከውልውል ፡ ለማዳን ፡ ችግር ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ምዕራፍ ፡ የሁሉንም ፡ ወገን ፡ አመዛዝኖ ፡ የሚቃረብ ፡ አሳብ ፡ ይሰጣል።

ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፉ ፡ በ፫፻፲፰ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ የይኵኖ ፡ አምላክን ፡ ንግሥ ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቀጥር ፡ ፲፪፻፸ ፡ ዓ.ም ፡ አድርጎታል። _ጀምስ ፡ ብሩስ፣ ዣን ፡ ባቲስት ፡ ኵልቦ ፣ ረኔ ፡ ባሴት ፣ ዡል ፡ ፔሩሾ_ ..... ፡ ፲፪፻፷፰ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ አድርገውታል። በነዚህ ፡ ጸሓፊዎችና ፡ በኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልተራራቅም። የኛና ፡ የፈረንጆቹ ፡ የዘመን ፡ አቆጣጠር ፡ በኀ ፡ ወይም ፡ በ፫ ፡ ዓመት ፡ ስለሚለያይ ፡ ፰ቱን ፡ ዓመት ፡ ከኮንቲሮሲኒ ፡ ፲፪፻፸ ፡ ላይ ፡ ቢቀነስ ፡ በኛ ፡ አቆጣጠር ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የነገሡበት ፡ ሺ፪፻፷፪ ፡ ከነዚያ ፡ ከነጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ከ፲፪፻፷፰ ፡ ላይ ፡ ቢቀነስ ፡ ደግሞ ፡ ሺ፪፻፷ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ እንደነገሡ ፡ ይታያል።

የቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከኮንቲሮሲኒ ፡ በቀር ፡ አብዛኞቹ ፡ ፲፪፻፷፰ ፡ የሚሉት ፡ የዓረቡን ፡ የአል ፡ ማክሪዚን ፡ የእስክንድርያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታሪክ ፡ በላቲን ፡ ቋንቋ ፡ የጻፈውን ፡ የረኖትን ፡ ጽሑፍ ፡ እየተከተሉ ፡ በተረፈ ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጣውን ፡ _የጀምስ ፡ ብሩስን_ ፡ መጽሐፍ ፡ መሠረት ፡ እያደረጉ ፡ ነው።

በአገራችን ፡ የተጻፈው ፡ የጐንደር ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ በተለይ ፡ አዛዥ ፡ ደልቦ ፡ ያዘጋጀው ፡ **ያፄ ፡ ሱስንዮስ** ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ሲመረመር ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ይገኛል። ዳሩ ፡ ግን ፡ የአዛዥ ፡ *ደልቦ* ፡ ጽሑፍ ፡ እርግጠኛ ፡ ለመሆኑ ፡ የሚያስተማምነን ፡ ጥብቅ ፡ ማስረጃ ፡ የለውም። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የሚለውን ፡ እንመልከት።

«.... ፡ ወነግሠ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ሰገድ ፡ ...በዳግም ፡ እምዘ ፡ ነግሠ ፡ እሑድ ፡ በ፩ ፡ ዕለት ፡ በሚያዝያ ፡ ፋሲካ ፡ እምይኵኖ ፡ አምላክእስከ ፡ ይእዜ ፡ ፻፶ወ፫ ፡ ዓመት ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ተፃብእ ፡ ምስለ ፡ ጋላ ፡ ዘውቅሮ ፡ ባጭሩ ፡ የጻሐፊው ፡ የኣዛዥ ፡ ደልቦ ፡ አሳብ ፡ ሱስንዮስ ፡ በነገሠ ፡ በ፯ኛው ፡ ዓመት ፡ ከጋለች ፡ ሲዋጋ ፡ ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዠምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያለፈው ፡ ዘመን ፡ ፻፶፫ ፡ ዓመት ፡ መሆኑን ፡ ለመግላጽ ፡ ነው። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ መሠረት ፡ ያደረግን ፡ እንደሆነ ፡ ከነኮንቲ ፡ ሮሲኒም ፡ ከነጀምስ ፡ ብሩስም ፡ እንዴት ፡ ወደኋላ ፡ ተመልሶ ፡ እንደሚርቅ ፡ እንመልከት።

ሱስንዮስ ፡ የነገሠው ፡ እንደፈረንጆቹ ፡ አቆጣጠር ፡ ሺ፮፻፯ ፡ ሲሆን ፡ በኛ ፡ ያው ፡ ሺ፮፻፰ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ ይሆናል ፡ በዚህ ፡ ስህተት ፡ ቢኖርም ፡ በ፩ናበይ ፡ ዓመት ፡ ይሆናልና ፡ ሁሉንም ፡ ትተን ፡ ሺ፮፻፰ ፡ ዓ.ም ፡ ሱስንዮስ ፡ የነገሠበትን ፡ እንያዝ። እንግዴህ ፡ ሱስንዮስ ፡ የነገሠው ፡ በሺ፮፻፰ ፡ ዓ.ም ፡ ሲሆን ፡ በነገሠ ፡ በ፯ኛው ፡ ዓመት ፡ ከውቅሮ ፡ ጋላ ፡ የተዋጋበት ፡ ዘመን ፡ ሺ፮፻፲፬ ፡ ዓ.ም ፡ መሆኑ ፡ ነው። ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ በሞተበትና ፡ በዚህ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከጋላ ፡ በተዋጋበት ፡ በሺ፮፻፲፬ ፡ ዓ.ም ፡ መካከል ፡ ያለፈው ፡ ጊዜ ፡ ፻፶፫ ፡ ዓመት ፡ ከሆነ ፡ ከሺ፮፻፲፬ ፡ ላይ ፡ ፻፶፫ ፡ ዓመት ፡ ሲቀነስ ፡ **ይኵኖ ፡ አምላክ** ፡ የሞተበት ፡ ዘመን ፡ ሺ፬፻፷፩ ፡ ዓ.ም ፡ ይገኛል። ከዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የነገሠበት (የገዛበት)ዘመን ፡ ፲፰ቱ ፡ ዓመት ፡ ቢቀነስ ፡ የነገሠበት ፡ ሺ፬፻፵፫ ፡ ዓ.ም ፡ መሆኑ ፡ ነው፥ ፡ ይህ ፡ ሲሆን ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ከሰጠው ፡ ጋር ፡ በ፲፩ ፡ ዓመት ፡ እነጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ከሰጡት ፡ ጋርበ ፡ ፲፱ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ርቆ ፡ ይለያያል። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ እምነት ፡ ለመስጠትና ፡ መሠረት ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም። ይኸን ፡ ትተን ፡ የሎንዶን ፡ ቤተ ፡

መጻሕፍት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የነበሩት ፡ ምስተር ፡ ዊሊያም ፡ ራይት ፡ የኢትዮጵያን ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ መጻሕፍት ፡ ባወጡበት ፡ የመጽሐፍ ፡ ዝርዝር (ካታሎግ) ፡ በመጀመሪያው ፡ ላይ ፡ ከዚያው ፡ ከኛው ፡ ጥንታዊ ፡ ጽሑፍ ፡ አግኝተው ፡ እንደቀዱት ፡ አፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ የሞተበት ፡ ጊዜ ፡ ያገራችን ፡ የቀድሞው ፡ ጸሐፊዎች ፡ እንዳለመዱት ፡ ኣጻጻፍ ፡ በፇሺ፯፻፸፪ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ነው። እንዳገራችን ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሊቃውንት ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡ ድረስ ፡ የነበረው ፡ ዘመን ፡ ፭ሺ፭፻ ፡ ዓመት ፡ ነው ፤ ከ**ክርስቶስ** ፡ ልደት ፡ ወዲህ ፡ **ይኵኖ ፡ ኣምላክ** ፡ የሞተበትን ፡ ሺ፪፻፸፯ ፡ ከዚያ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ከሚለው ፡ ፭ሺ ፡ ፭፻ ፡ ዓመት ፡ ጋር ፡ ደምሮ ፡ ፇሺ፯፻፸፯ ፡ ዓመት ፡ ማድረጉ ፡ ነው።

ስለዚህ ፡ አፄ ፡ **ይኵኖ ፡ ኣምላክ** ፡ የገዛበትን ፡ ዘመን ፡ ፲፭ቱን ፡ ዓመት ፡ ከሞተበት ፡ ዘመን ፡ ከሺ፪፻፸፯ ፡ ዓ. ምሕረት (፩ሺ፯፻፸፯ ፡ ዓመት ፡ ዓ. ዓለምና ፡ ዓ. ምሕረት) ላይ ፡ የቀነስን ፡ እንደሆነ ፡ የነገሡበትን ፡ ሺ፪፻፷፻ ፡ ዓ.ም ፡ እናገኛለን። ይኸውም ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ሺ፪፻፸ ፡ ካደረገው ፡ ጋር ፡ የኛን ፡ ለማግኘት ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ሲቀነስ ፡ ሺ፪፻፷፪ ፡ ጋር ፡ ተጋጥሞ ፡ ስለሚገኝ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የነገሡበትን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፪፻፷፪ ፡ የሞተበትን ፡ ሺ፪፻፸፯ ፡ ዓ. ምሕረት ፡ ላይ ፡ ማድረግ ፡ ከሁሉ ፡ የቀረበና ፡ መሠረት ፡ ሊሆን ፡ የሚገባው ፡ ይመስለኛል።

ስለዚህ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የነገሥታቱን ፡ ስምና ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ የገዙበትን ፡ ዘመን ፡ የሚያሳይ ፡ ጠቅላላ ፡ ዝርዝር ፡ እነሆ ፡ አዘጋጅቻለሁ ፤ ከርሱም ፡ ጋር ፡ ፈረንጆች ፡ የሚሰጡት ፡ ዝርዝርና ፡ ዘመን ፡ ለማስተያየት ፡ ያህል ፡ አብሮ ፡ ይገኛል።

ወደፊት ፡ በሚገኘው ፡ በየምዕራፉ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጒዳይ ፡ ለሆነው ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ትክክለኛ ፡ ዘመን ፡ ለመስጠት ፡ እስሕተት ፡ ላይ ፡ ከመውደቅ ፡ በቀር ፡ ችግር ፡ ነው። ለጊዜው ፡ የሚበቃን ፡ ነገሥታቱ ፡ የነገሡበትንና ፡ የሞቱበትን ፡ ጊዜ ፡ ማወቅ ፡ ነው። የቀረውን ፡ የታሪክ ፡ ዘመን ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ መካከል ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ መገንዘብ ፡ ለጊዜው ፡ ሳይበቃ ፡ አይቀርም። ይኸውም ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ላለው ፡ ነው

፡ እንጂ ፡ ከርሳቸው ፡ ዝምሮ ፡ ወደፊትያለው ፡ የተረጋገጠ ፡ ዘመን ፡ ይገኝበታል። የነገሥታቱን ፡ ዝርዝር ፡ በሚከተለው ፡ እንመልከት።

## ከዐፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የሚዝምረው ፡ የነገሥታት ፡ ዝርዝር ፡ በኢት ፡ ቍጥር

| ተርታ | መጠሪያ ፡ ስም | ስመ ፡ መንግሥት | የገዛበት ፡ ዘመን | ዓመተ ፡ ዓለም | ከ–ዓ. ም እስከ–ዓ. ም |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ተስፋ ፡ ኢየሱስ | ይኵኖ ፡ አምላክ | ፲፭ | ፭ሺ፯፻፷፪ | ሺ፪፻፷፪-ሺ፪፻፸፯.ዓም |
| ፪ | ያግብአ (እግብአ)ጽዮን | ሰሎሞን፡ | ፱ | ። | ሺ፪፻፸፯-ሺ፪፻፹፯.ዓም |
| ፫ | ባሕር ፡ ኣሰግድ (ሰብ ፡ ኣ ፡ ኣሰግድ) | | ፩ | ። | ሺ፪፻፹፯ |
| ፬ | ጽንፈ ኣሰግድ | | ፩ | ። | ሺ፪፻፹፰ |
| ፭ | ሕዝበ ፡ ኣርዕድ፡ | | ፩ | ። | ሺ፪፻፹፱ |
| ፮ | ቅድመ ፡ ኣሰግድ፡ | | ፩ | ። | ሺ፪፻፺ |
| ፯ | ዣን ፡ አሰግድ | | ፩ | ። | ሺ፪፻፺፩ |
| ፰ | ውድም ፡ ራኣድ (ኣርዕድ) | | ፲፭ | ። | ሺ፪፻፺፪-ሺ፫፻፯ |
| ፱ | ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ፩ኛ | ገብረ ፡ መስቀል | ፴ | ። | ሺ፫፻፯-ሺ፫፻፴፯ |
| ፲ | ንዋየ ፡ ክርስቶስ፡ | ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ቆስጠ | ፳፰ | ። | ሺ፫፻፴፯-ሺ፫፻፷፭ |
| ፲፩ | ንዋየ ማርያም | ውድም አስፈሬ | ፲ | ። | ሺ፫፻፷፭-ሺ፫፻፸፭ |
| ፲፪ | ዳዊት ፡ ፩ኛ | | ፳፱ | ። | ሺ፫፻፸፭-ሺ፬፻፬ |
| ፲፫ | ቴዎድሮስ ፡ ፩ኛ | | ፫/፬ | ። | ሺ፬፻፬-ሺ፬፻፯ |
| ፲፬ | ይስሐቅ | ገብረ ፡ መስቀል | ፲፭ | ። | ሺ፬፻፯-ሺ፬፻፳፪ |
| ፲፭ | እንድርያስ | እስክንድር? | ፮ ፡ ወር | ። | ሺ፬፻፳፪ |
| ፲፮ | ተክለ ፡ ማርያም | ሕዝበ ፡ ናኝ | ፬ | ። | ሺ፬፻፳፪-ሺ፬፻፳፮ |
| ፲፯ | ሥርወ ፡ ኢየሱስ | ምህርካ ፡ ናኝ | ፬ ፡ ወር፡ | ። | |
| ፲፰ | አምደ ፡ ኢየሱስ | በድል ፡ ናኝ | ፰ ፡ ወር፡ | ። | ሺ፬፻፳፮ |
| ፲፱ | ዘርዓ ፡ ያዕቆብ | ቆስጠንጢኖስ፡ | ፴፬ | ፭ሺ፱፻፷ | ሺ፬፻፳፮-ሺ፬፻፷ |
| ፳ | በእደማርያም (ሲ) (ሠርያቆስ?) | ዳዊት | ፲ | ። | ሺ፬፻፷-ሺ፬፻፸ |
| ፳፩ | እስክንድር | ቆስጠንጢኖስ | ፲፯ | ። | ሺ፬፻፸-ሺ፬፻፹፯ |
| ፳፪ | ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ፪ኛ | | ፮ ፡ ወር | ። | |

# የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ፪ተኛ፡ መጽሐፍ

ከዐፄ ይኵኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል ---- ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ

| ተርታ | መጠሪያ ፡ ስም | ስመ ፡ መንግሥት | የገዛበት ፡ ዘመን | ዓመተ ፡ ዓለም | ከ–ዓ. ም እስከ–ዓ. ም |
|---|---|---|---|---|---|
| ፹፫ | ናዖድ (ቀለዮጳ) | አንበሳ ፡ በፀር፡ | ፲፫ | ፯ሺ | ሺ፬፻፹፯-ሺ፭፻ |
| ፹፬ | ልብነድንግል (ዳዊት) | ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ፩ኛ | ፴፪ | ፯ሺ | ሺ፭፻-ሺ፭፻፴፪ |
| ፹፭ | ገላውዴዎስ | አጽናፍ ሰገድ፡ | ፲፱ | ፯ሺ ፡ ፵፩ | ሺ፭፻፴፪-ሺ፭፻፵፩ |
| ፹፮ | ሚናስ | ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ፪ኛ<br>አድማስ ፡ ሰገድ ፡ ፩ኛ | ፬ | ፯ሺ ፡ ፵፫ | ሺ፭፻፵፩-ሺ፭፻፵፫ |
| ፹፯ | ሠርፀ ፡ ድንግል | መለከ ፡ ሰገድ፡ | ፴፬ | ፯ሺ ፡ ፹፱ | ሺ፭፻፵፫-ሺ፭፻፹፱ |
| ፹፰ | ያዕቆብ | መለከ ፡ ሰገድ ፡ ፪ኛ፡ | ፯ | ። | ሺ፭፻፹፱-ሺ፭፻፺፯ |
| ፹፱ | ዘድንግል<br>ያዕቆብ ፡ እንደገና) | አጽናፍ ፡ ሰገድ።<br>መለከ ፡ ሰገድ። | ፩<br>፩ | ። | ሺ፭፻፺፯-ሺ፭፻፺፱<br>ሺ፭፻፺፱ |
| ፺ | ሱስንዮስ፡ | ሥልጣን ፡ ሰገድ | ፹፭ | ፯ሺ፺፱ | ሺ፭፻፺፱-ሺ፮፻፹፬ |
| ፺፩ | ፋሲለደስ | ዓለም ፡ ሰገድ፡ | ፴፮ | ። | ሺ፮፻፹፬-ሺ፮፻፳ |
| ፺፪ | ዮሐንስ፡ | አእላፍ ፡ ሰገድ፡ | ፲፬ | ። | ሺ፮፻፳-ሺ፮፻፸፬ |
| ፺፫ | ኢያሱ | ኣድያም ሰገድ፡ | ፹፬ | ። | ሺ፮፻፸፬-ሺ፮፻፺፱ |
| ፺፬ | ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ፩ኛ፡ | አብራክ ፡ ሰገድ፡ | ፪ | ። | ሺ፮፻፺፱-ሺ፯፻፩ |
| ፺፭ | ቴዎፍሎስ፡ | ኣጽራር ፡ ሰገድ | ፫ | ። | ሺ፯፻፩-ሺ፯፻፬ |
| ፺፮ | ዮስጦስ | ፀሐይ ፡ ሰገድ፡ | ፭ | ። | ሺ፯፻፬-ሺ፯፻፱ |
| ፺፯ | ዳዊት ፡ ፫ኛ፡ | ኣድባር ፡ ሰገድ፡ | ፭ | ። | ሺ፯፻፱-ሺ፯፻፲፬ |
| ፺፰ | በካፋ፡ | መሢሕ ፡ ሰገድ፡ | ፱ | ። | ሺ፯፻፲፬-ሺ፯፻፹፫ |
| ፺፱ | ኢያሱ ፡ ፪ኛ፡ | ብርሃን ፡ ሰገድ | ፹፭ | ። | ሺ፯፻፹፫-ሺ፯፻፵፰ |
| ፻ | ኢዮአስ፡ | ኣድያም ፡ ሰገድ ፡ ፪ኛ | ፲፬ | ። | ሺ፯፻፵፰-ሺ፯፻፳፪ |
| ፻፩ | ዮሐንስ ፪ኛ፡ | አድያም ፡ ሰገድ ፡ ፫ኛ | ፮ ፡ ወር | ። | ሺ፯፻፳፪ |
| ፻፪ | ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ፪ኛ | ኣድማስ ፡ ሰገድ ፡ ፪ኛ | | ። | ሺ፯፻፳፪ |
| | | ኃያል ፡ ሰገድ፡ | ፳ | ። | ሺ፯፻፳፪-ሺ፯፻፸ |
| | | ጥበብ ፡ ዕገድ፡ | | ። | |

# ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የሚዠምረው ፡ በአውሮፓ ፡ አቆጣጠርና ፡ በፈረንጆቹ ፡ ሂሣብ።

| ተርታ | መጠሪያ ፡ ስም | ስመ ፡ መንግሥት | የገዛበት፡ዘመን | ከ–እስከ–ከክርስቶስ ፡ ልደት በኋላ |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | ተስፋ ፡ ኢየሱስ ፡ | ይኵኖ ፡ አምላክ | ፲፭ | ሺ፪፻፷፰-ሺ፪፻፹፫ |
| ፪ | አግብእ (ግብአ) ጽዮን ፡ | ሰሎሞን ፡ | ፱ | ሺ፪፻፹፫-ሺ፪፻፺፬ |
| ፫ | ባሕር፡አስግድ ፡ ስብአ (አስግድ) | | ፩ | ሺ፪፻፺፬ |
| ፬ | ጽንፈ ፡ ኣሰግድ ፡ | | ፩ | ሺ፪፻፺፭ |
| ፭ | ሕዝበ ፡ አርዕድ ፡ | | ፩ | ሺ፪፻፺፮ |
| ፮ | ቅድመ ፡ ኣሰግድ ፡ | | ፩ | ሺ፪፻፺፯ |
| ፯ | ጃን ፡ አሰግድ ፡ | | ፩ | ሺ፪፻፺፰ |
| ፰ | ወድም ፡ ራዓድ (አርዕድ) | | ፲፭ | ሺ፪፻፺፰-ሺ፫፻፲፪ |
| ፱ | ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ፩ኛ | ገብረ ፡ መስቀል ፡ | ፴ | ሺ፫፻፲፪-ሺ፫፻፵፪ |
| ፲ | ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ | ሰይፈ ፡ አርእድ ፡ | ፳፰ | ሺ፫፻፵፪-ሺ፫፻፸፩ |
| ፲፩ | ንዋየ ፡ ማርያም ፡<br>» | ወድም ፡ አስፈሬ ፡<br>ግርማ ፡ ኣስፈሬ ፡ | ፲<br>» | ሺ፫፻፸፩-ሺ፫፻፹፩<br>» » |
| ፲፪ | ዳዊት ፡ _ ፩ኛ | | ፴/ ፳፱ | ሺ፫፻፹፩-ሺ፬፻፲ |
| ፲፫ | ቴዎድሮስ ፡ _ ፩ኛ | | ፬/ ፫ | ሺ፬፻፲-ሺ፬፻፲፬ |
| ፲፬ | ይስሐቅ ፡ | ገብረ መስቀል ፡ | ፲፭ | ሺ፬፻፲፬-ሺ፬፻፳፱ |
| ፲፭ | እንድርያስ ፡ | | ፮ ፡ ወር | ሺ፬፻፳፱ |
| ፲፮ | ተክለ ፡ ማርያም ፡ | ሕዝበ ናኝ ፡ | ፬ | ሺ፬፻፴፫ |
| ፲፯ | ሥርወ ፡ ኢየሱስ ፡ | ምህረካ ፡ ናኝ ፡ | .... | ሺ፬፻፴፫ |
| ፲፰ | አምደ ፡ ኢየሱስ ፡ | በድል ፡ ናኝ ፡ | ፩ | ሺ፬፻፴፬ |
| ፲፱ | ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ | ቆስጠንጢኖስ ፩ኛ | ፴፬ | ሺ፬፻፴፬-ሺ፬፻፷፰ |
| ፳ | በእደ ማርያም ፡ ፩ኛ | | ፲ | ሺ፬፻፷፰-ሺ፬፻፸፰ |
| ፳፩ | እስክንድር | ቆስጠንጢኖስ ፡ ፪ኛ | ፲፯ | ሺ፬፻፸፰-ሺ፬፻፺፭ |
| ፳፪ | አምደ ፡ ጽዮን ፡ ፪ኛ | | ፩/ ፮ ፡ ወር | |
| ፳፫ | ናዖድ ፡ | አንበሳ ፡ በፀር ፡ | ፲፫ | ሺ፬፻፺፭-ሺ፭፻፰ |
| ፳፬ | ልብነድንግል (ዳዊት)፪ኛ | ወናግ ፡ ሰገድ ፩ኛ | ፴፪/ ፴ | ሺ፭፻፰-ሺ፭፻፵ |
| ፳፭ | ገላውዴዎስ ፡ | አጽናፍ ፡ ሰገድ ፡ ፩ኛ | ፲፱ | ሺ፭፻፵-ሺ፭፻፰ |

| ተርታ | መጠሪያ ፡ ስም | ስመ ፡ መንግሥት | የገዛበት፡ዘመን | ከ—እስከ—ከክርስቶስ ፡ ልደት በኋላ |
|---|---|---|---|---|
| ፳፮ | ሚናስ ፡<br>» | ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ፪ኛ<br>አድማስ ፡ ሰገድ ፡ ፩ኛ | ፬<br>» | ሺ፭፻፷-ሺ፭፻፷፬<br>» |
| ፳፯ | ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ | መለክ ፡ ሰገድ ፡ ፩ኛ | ፴፬ | ሺ፭፻፷፬-ሺ፭፻፺፯ |
| ፳<br>፰ | ያዕቆብ ፡ | መለክ ፡ ሰገድ ፡ ፪ኛ | ፯ | ሺ፭፻፺፯-ሺ፮፻፯ |
| ፳፱ | ዘድንግል ፡ | አጽናፍ ፡ ሰገድ ፡ ፪ኛ | ፩ | » » |
| ፴ | ሱስንዮስ<br>» | መለክ ፡ ሰገድ ፡ ፫ኛ<br>ሥልጣን ሰገድ ፡ ፩ኛ | ፳፫<br>» | ሺ፮፻፯-ሺ፮፻፴፪<br>» » |
| ፴፩ | ፋሲለደስ ፡<br>» | ሥልጣን ፡ ስገድ ፡ ፪ኛ ፡<br>ዓለም ፡ ሰገድ ፡ | ፴፮<br>» | ሺ፮፻፴፪-ሺ፮፻፷፯<br>» » |
| ፴፪ | ዮሐንስ ፡ ፩ኛ ፡ | አዕላፍ ፡ ሰገድ ፡ | ፲፭ | ሺ፮፻፷፯-ሺ፮፻፹፪ |
| ፴፫ | ኢያሱ ፡ ፩ኛ ፡ | አድያም ፡ ሰገድ ፡ ፩ኛ | ፳፱ | ሺ፮፻፹፪-ሺ፯፻፮ |
| ፴፬ | ተክለ ሃይማኖት ፡ ፩ኛ ፡<br>»<br>» | ኣብራክ ፡ ሰገድ ፡<br>ልዑል ሰገድ ፡<br>ግሩም ፡ ሰገድ ፡ | ፪<br>»<br>» | ሺ፯፻፮-ሺ፯፻፰<br>» »<br>» » |
| ፴፭ | ቴዎፍሎስ ፡ | ኣጽራር ፡ ሰገድ ፡ | ፫/ ፭ | ሺ፯፻፰-ሺ፯፻፲፩ |
| ፴፮ | ዮስጦስ ፡ | ፀሐይ ፡ ሰገድ ፡ | ፭ | ሺ፯፻፲፩-ሺ፯፻፲፮ |
| ፴፯ | ዳዊት ፡ ፫ኛ ፡ | ኣድባር ሰገድ ፡ ፩ኛ | ፭ | ሺ፯፻፲፮-ሺ፯፻፳፩ |
| ፴<br>፰ | በካፋ (ዐፅመ ፡ ጊዮርጊስ)<br>» | አድባር ሰገድ ፡ ፪ኛ<br>መሲሕ ፡ ዕድ ፡ | ፱<br>» | ሺ፯፻፳፩-ሺ፯፻፴<br>» » |
| ፴፱ | ኢያሱ ፡ ፪ኛ ፡<br>» | ብርሃን ፡ ሰገድ ፡<br>ኣድያም ሰገድ ፡ ፪ኛ | ፳፭ | ሺ፯፻፴-ሺ፯፻፶፭<br>» » |
| ፵ | ኢዮአስ ፡ ፩ኛ ፡ | ኦድያም ፡ ስገድ ፡ ፫ኛ | ፲፬ | ሺ፯፻፶፭-ሺ፯፻፷፱ |
| ፵፩ | ዮሐንስ ፡ ፪ኛ ፡ | ኣድማስ ፡ ሰገድ ፡ ፩ | ፩ | |
| ፵፪ | ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ፪ኛ፡<br>» | ኃያል ፡ ሰገድ ፡<br>ጥበብ ፡ ሰገድ ፡ | ፯<br>» | |
| ፵፫ | ሰሎሞን ፡ ፪ኛ ፡ | | ፪ | |
| ፵፬ | ተክላ ፡ ጊዮርጊስ ፡ | ፍቅር ፡ ሰገድ ፡ | ፭ | |
| ፵፭ | ኢያሱ ፡ ፫ኛ ፡ | ብዕል ፡ ሰገድ ፡ | | |
| | በእደ ማርያም ፡ | | | |

| ተርታ | መጠሪያ ፡ ስም | ስመ ፡ መንግሥት | የገዛበት፡ዘመን | ከ–እስከ–ከክርስቶስ ፡ ልደት በኋላ |
|---|---|---|---|---|
| | ተክላ ፡ ጊዮርጊስ | | | |
| ፹፮ | ሕዝቅያስ ፡ | | | |
| | ተክለ ጊዮርጊስ | | | |
| ፹፯ | በእደ ፡ ማርያም ፡ ፪ኛ ፡ | | | |
| | ተክላ ፡ ጊዮርጊስ | | | |
| ፹<br>፰ | ሰሎሞን ፡ ፫ኛ ፡ | | | |
| ፹፱ | ዮናስ | | | |
| | ተክለጊዮርጊስ ፡ | | | |
| | ሰሎሞን ፡ ፫ኛ ፡ | | | |
| ፺ | ድሜጥሮስ ፡ | | | |
| | ተክላ ፡ ጊዮርጊስ ፡ | | | |
| | ድሜጥሮስ ፡ | | | |
| ፺፩ | ዕጓለ ፡ ጽዮን (ጓሉ) | ንዋይሰገድ | | |
| ፺፪ | ኢዮአስ (ዮአስ) ፪ኛ ፡ | | | |
| ፺፫ | ጂጋር ፡ | | | |
| ፺፬ | በእደ ፡ ማርያም ፡ | | | |
| | ጂጋር ፡ | | | |
| ፺፭ | ኢያሱ ፡ ፬ኛ ፡ | | | |
| ፺፮ | ገብረ ክርስቶስ ፡ | | | |
| ፺፯ | ሣህለ ፡ ድንግል ፡ ሣህሉ፡ | | | |
| ፺፰ | ዮሐንስ ፫ኛ ፡ | | | |
| | ሣህለ ፡ ድንግል ፡ | | | |
| ፺፱ | ቴዎድሮስ ፡ ፪ኛ ፡ | | | |
| ፻ | ዮሐንስ ፡ ፬ኛ ፡ | | | |

# ምዕራፍ ፡ ፳።

## ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ በዘመኑ ፡ የፈጸመው።

ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የክርስትና ፡ ስሙ ፡ ተስፋ ፡ **ኢየሱስ** ፡ ነበር ፡ በዚሁ ፡ በክርስትና ፡ ስሙ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሲጠራ ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ በዮዲት ፡ ጭካኔ ፡ ሲያልቅ ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ የተረፈ ፡ ነጋሢ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቀው ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዠምረው (እንደ ፡ ግማሾቹ ፡ የነገሠለት ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ (አምላክ ፡ ይሁነው) ብለው ፡ በሚጠሩት ፡ ይኸው ፡ ሠያሜ ፡ መጠሪያውም ፡ ስመ ፡ መ ፡ መንግሥቱምሆኖ ፡ ቀረ ፡ ይባላል።

ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ የመንግሥቱን ፡ መደብ ፡ በተጉለት ፡ አውራጃ (በኵልቦ ፡ መጽሐፍ ፡ በገጽ ፡ ፪፻፳፬ ፡ እንደሚገኘው ፡ እንደ ፡ ኢብን ፡ ኤል ፡ ዋርዲ ፡ አንኮበር) ኣደረገ። ወደ ፡ ኣባቶቹ ፡ ወደ ፡ ጥንታዊቱ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ኣክሱም ፡ ሳይመለስ ፡ የቀረበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ በሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዙፋን ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ለአፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ መሔዱ ፡ ቅር ፡ ያላቸው፣ ፡ የዛጕዬና ፡ የአገው ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ዙፋን ፡ ለመውሰድ ፡ የሚመኙ ፡ ፈላሾች ፡ እንዳሉ ፡ የነርሱን ፡ ሁኔታ ፡ በመፍራት ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ እኔንም ፡ አባቶቼንም ፡ በስደቱ ፡ ጊዜ ፡ ተቀብሎ ፡ ያስተናገደኝን ፡ ኣሁንም ፡ ያባቶቼን ፡ ዙፋን ፡ ለማግኘት ፡ ያበቃኝን ፡ የሸዋን ፡ አገር ፡ ለቅቄ ፡ አልሄድምብሎ ፡ እንደሆነ ፡ ኣይታወቅም።

በነገሡበት ፡ ዘመን ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ የሚገልጽ ፡ በዘመኑም ፡ ከዚያ ፡ ወዲህም ፡ የተጻፈ ፡ ታሪክም ፡ ዜና ፡ መዋዕልም ፡ የለውም። ነገር ፡ ግንከዓረብ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታሪክ ፡ እየለቃቀሙ ( ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ የሚጽፉ ፡ ፈረንጆች ፡ እነብሩስ ፡ እነኵልቦ ፡ እነረኔ ፡ ባሴት ፡ ከአዳሎች ፡ ጋር ፡ መዋጋቱን ፡ በዚሁም ፡ የተነሣ ፡ ከግብፁ ፡ ሱልጣን ፡ ጋር ፡ መቀያየሙን ፡ ጳጳስም ፡ ከግብፅ ፡ ማስመጣት ፡ የማይሆንለት ፡ ቢሆን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አባ ፡ ኢዮብ ፡ የሚባል ፡ ጳጳስማስመጣቱን፣ለቍስጥንጥንያ ፡ ንጉሥ ፡ ለሚካኤል ፡ ፓሌዎሎግ ፡ ደብዳቤ ፡ መላኩን ፡ ባጭሩበተለይ ፡ ኣባ ፡

ኵልቦ ፡ ጠቅሰውትይገኛል። እንደዚሁም ፡ በእነዚሁ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ማርኮፖሎ ፡ የሚባለው ፡ ስሙ ፡ ጥሩው ፡ የምሥራቅን ፡ መንገድ ፡ ለኤውሮፓ ፡ የከፈተው ፡ አገር ፡ መርማሪ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ስለአሉት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሲናገር ፡ « ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የተዋጊነት ፡ መንፈስ ፡ አላቸው ፡ ዘወትር ፡ ከአዳል ፡ ሡልጣን ፡ ጋር ፡ ይዋጋሉ" ብሎ ፡ መጥቀሱን ፡ ከዚያም ፡ እላይ ፡ እንደተባለው ፡ ጳጳስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣት ፡ ከቆመ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ስለአለፈ ፡ ጳጳስ ፡ ይላክልኝ ፡ ብሎ ፡ በሺ፩፻፸፱ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ ቢባርስ ፡ ለሚባለው ፡ ለግብፅ ፡ ሡልጣን ፡ ቢጽፍለት ፡ ሡልጣኑ ፡ አዳሎቹን (እስላሞቹን) እየወጋ ፡ ስላጠቃ ፡ አይላክላትም ፡ ብሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውላታ ፡ ጠይቆ ፡ የይኵኖ ፡ አምላክን ፡ ትሕትና ፡ የሞላበትን ፡ ጥያቄ ፡ ሡልጣኑ ፡ ሳይፈጽምላት ፡ እንደቀረ ፡ ማቅሪዝ ፡ የሚባለው ፡ ጸሐፊ ፡ እንደጻፈው ፡ በመጽሐፋቸው ፡ ከገጽ ፡ ፩፻፷፪ ፡ ጀምረው ፡ ይገልጹልናል።

ይኵኖ ፡ አምላክም ፡ እንደተለመደው ፡ ከግብፅ ፡ ጳጳስ ፡ ለማስመጣት ፡ ጠይቆ ፡ ሳይመጣለት ፡ ስለቀረ ፡ ያለጳጳስ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ መኖር ፡ አስቸጋሪ ፡ ስለሆነበት ፡ ኣሳቡን ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ ፓትርያርክ ፡ አዞረ ፤ በዚህም ፡ ዘመን ፡ በጌታችን ፡ መቃብር ፡ የተነሣ ፡ የመስቀል ፡ ጦርነት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተደርጎ ፡ የካቶሊኮቹ ፡ ነገሥታት ፡ ድል ፡ አግኝተው ፡ ማስተዳደር ፡ ዠምረው ፡ ስለነበረ ፡ በዚያ ፡ ያሉት ፡ የተዋሕዶ ፡ ያዕቆባውያን) ወገኖችና ፡ ካቶሊኮቹ ፡ ተባብረው ፡ መሥራት ፡ ዠምረውስለነበረ ፡ የዚህን ፡ ወሬ ፡ ሁሉ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የመጡ ፡ መነኮሳትና ፡ ምዕመናን ፡ ለይዙኖ ፡ አምላክ ፡ ገልጸውለት ፡ ነበር። በዚሁ ፡ መካከል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፡ አለመኖሩን ፡ ስላወቀ ፡ አባ ፡ ዳዊት ፡ አግናጥዩስዳቪድ ፡ ኢኞሲዩስ ፡ የሚባሉት ፡ ፓትርያርክ ፡ አባ ፡ ኢዮብ ፡ የሚባሉትን ፡ የሶርያ ፡ መነኵሴ ፡ የኤጲስቆጶስነት ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥተው ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ላኵዋቸው ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋር ፡ የዶሚኒካን ፡ የካቶሊክ ፡ ሚሲዮኖች ፡ አብረው ፡ መጥተው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ በትግሬ ፡ ያስተምሩ ፡ ዠመር። ወደሸዋ ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ ወዳለበት ፡ አልደረሱም። በዚያም ፡ ሆነው ፡ ሲያስተምሩ ፡ አንዳንዱ ፡ ሲከተላቸው ፡ የቀሩት ፡ የ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ወገኖች ፡ መሆናቸውን ፡ ተጠራጥረው ፡ በላያቸው ፡ ተነሡባቸው። በመካከሉም ፡ ይኵኖ

፡ አምላክ ፡ ሞቶ ፡ ልጁ ፡ ያግብአ ፡ ጽዮን ፡ ስለነገሠ ፡ እንደቀድሞው ፡ ከግብፅ ፡ ጳጳስ ፡ ኣስመጣ ፡ ሲሉ ፡ ጽፈዋል።

በፊተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ከግብፅ ፡ ጳጳስ ፡ ማስመጣት ፡ ችግር ፡ በመሆኑ ፡ ያለጳጳስ ፡ መኖርም ፡ ባለመቻሉ ፡ ምዕመናኑ ፡ ተሰብስበው ፡ አቡነ ፡ ተክለሃይማኖትን ፡ መምረጣቸውን ፡ ተመልክተናል ፡ እነዚህ ፡ የውጭ ፡ ኣገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ እንደገለጹት ፡ አባ ፡ ኢዮብ ፡ ከአባ ፡ ዳዊት ፡ አግናጥዩስ ፡ የኤጺስ ፡ ቆጶስነት ፡ ማዕርግ ፡ ተቀብለው ፡ መምጣታቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከመካከላቸው ፡ ጳጳስ ፡ አይሹሙ ፡ በሚለው ፡ በፍትሐነገሥት ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ ኣንደኛው ፡ ክፍል ፡ ኣጉረምርሞ ፡ እንደሆነ ፡ አባ ፡ ኢዮብ ፡ ንጉሡ ፡ ወደአሉበት ፡ ወደሸዋ ፡ ለመዝለቅ ፡ ያልቻሉበት ፡ ከኣቡነ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ ጋር ፡ ግጭት ፡ እንዳይሆን ፡ ተፈርቶ ፡ እንደሆነ ፡ ኣይታወቅም።

# ምዕራፍ ፡ ፯

## <u>የአፄ ፡ ያግብአ ፡ ጽዮንና ፡ የተከታዮቹ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።</u>

እፄ ፡ ያግብአ ፡ ጽዮን ፡ በነገሠበትና ፡ አፄ ፡ አምደጽዮን ፡ ፩ኛ ፡ በነገሠበት ፡ መካከል ፡ ለታሪክ ፡ አጻጻፍ ፡ የሚሞላ ፡ ጽሑፍ ፡ አልተገኘም። ታሪክ ፡ ነገሥቱም ፡ እገሌ ፡ ይኸን ፡ ያህል ፡ ዘመንነገሠ ፡ እያለ ፡ ስማቸውን ፡ ጠቅሶ ፡ ከማለፍ ፡ በቀር ፡ ዝርዝር ፡ ሥራቸውን ፡ ሊነግረን ፡ አልቻለም። በየፈረንጆቹ ፡ ታሪክ ፡ ግን ፡ እንደተገኘው ፡ አፄ ፡ ያግብኣ ፡ ጽዮን ፡ ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ሰሎሞን ፡ እንደነገሠ ፡ አባቱ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ከአዳሎችጋራ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተዋጋ ፡ ከግብፅም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጠበኛ ፡ ሆኖ ፡ የነበረውን ፡ ያባቱን ፡ ፖለቲካ ፡ ለውጦ ፡ እስላሞቹን ፡ በመልካም ፡ ዓይን ፡ ይመለከት ፡ ዠመር ፤ ከግብፅ ፡ ባለሥልጣኖችም ፡ ስምምነት ፡ ኣደረገ። ስለዚህ ፡ በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ለግብፁ ፡ ሡልጣን ፡ ለእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፡ እኰልኝ ፡ የሚል ፡ የልመና ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ላከ ፡ ሡልጣኑም ፡ ያግብኣ

፡ ጽዮን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላሉት ፡ እስላሞች ፡ ባደረገው ፡ መልካም ፡ ኣስተያየት ፡ ስለተደሰተ ፡ ጳጳስ ፡ በቶሎ ፡ እንዲላክለት ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ መፍቀዱን ፡ አስረዳ። በዚህም ፡ ዘመን ፡ የነበሩት ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ፤ እርሳቸውም ፡ በቶሎ ፡ ከመነኮሳቱ ፡ ኣንዱን ፡ ኣባ ፡ ሰላማ ፡ ብለው ፡ ሠይመው ፡ ጳጳስነት ፡ ሾመው ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ላኳቸው።

እንደመጀመሪያው ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ የተባሉበት ፡ ምክንያት ፡ በግብፆቹ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አለመፍቀድና ፡ በኋላም ፡ ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ ሳይገኝ ፡ ቀርቶ ፡ ጳጳስ ፡ ከእስክንድርያ ፡ መምጣት ፡ ከአቋረጠ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ስለሆነ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ካቶሊኮች ፡ እግራቸውን ፡ ሰደው ፡ የተዋሕዶን ፡ ሃይማኖት ፡ ሊያጠፏት ፡ የነበረውን ፡ ወይም ፡ ቅስና ፡ ዲቊና ፡ የሚሰጥ ፡ ጳጳስ ፡ ከመጥፋቱ ፡ የተነሣ ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሊጠፋ ፡ የነበረውን ፡ እኝህ ፡ ጳጳስ ፡ በመዠመሪያው ፡ ጳጳስ ፡ በኣባ ፡ ሰላማ ፡ መንገድ ፡ እንደገናኣድሰው ፡ መልሰው ፡ እንዲመሠርቱ ፡ ሲሉ ፡ ነው ፡ ይባላል።

እነሆ ፡ ባገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ ባፄ ፡ ያግብኣ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ ከእስክንድርያ ፡ ተልከው ፡ የመጡትን ፡ ኣባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሲል ፡ የውጭ ፡ ኣገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከዚያውም ፡ አባ ፡ ኵልቦ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ብለው ፡ ከነምክንያቱ ፡ ገልጸዋል። የኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ያቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በጳጳስነት ፡ እየሠሩ ፡ መቆየታቸውን ፡ ጳጳሱ ፡ ከመጡ ፡ በኋላ ፡ በሰላም ፡ የጵጵስናውን ፡ ሥልጣን ፡ ከነመሣሪያው ፡ አስረክበው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ አስቦ ፡ ገዳም ፡ ሄደው ፡ መቀመጣቸውን ፡ ሲገልጽ ፡ የነአባ ፡ ኵልቦ ፡ ጽሑፍ ፡ ይኸን ፡ ይዘልና ፡ በዚሁ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ባፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከግብፅ ፡ ሡልጣኖች ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ ማድረግና ፡ ጳጳስ ፡ ማግኘት ፡ ባለመቻሉ ፡ ንጉሡ ፡ ከቊስጥንጥንያ ፡ ንጉሥና ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ማድረጋቸውን ፡ ይገልጻል። ይኸም ፡ አገላለጥ ፡ በኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ስለሌለ ፡ የቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ጸሐፊዎቻችንም ፡ እነአለቃ ፡ ታዬ ፡ እነብላቴን ፡ ጌታም ፡ በዋዜማ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ጠቅሰውት ፡ አላገኘሁም ፤ ባፄ ፡ አግብኣ ፡ ዘመን ፡ የመጣውም ፡ ጳጳስ ፡ ስሙ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ወይም ፡ ኣባ ፡ ሰላማ ፡ መሆኑ ፡ ወደፊት ፡

የሚጣራ ፡ ነውና ፡ አሁን ፡ ወደኣፄ ፡ ያግብኣ (ወይም ፡ አግብአ) ጽዮን ፡ እንመለስ።

አፄ ፡ ያግብኣ ፡ ጽዮን ፡ በዘመኑ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሄዶ ፡ የጌታችንን ፡ መቃብር ፡ ለማሳለም ፡ ምኞት ፡ ነበረው ፡ ይባላል ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የመንግሥቱ ፡ ሥራና ፡ አስተዳደር ፡ ስለአልፈቀደለት ፡ ባንድ ፡ መነኵሴ ፡ እጅ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ መጋረጃና ፡ ጧፍ ፡ ዕጣን ፡ ጨምሮ ፡ በጸሎታችሁ ፡ ኣትርሱኝ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎልኮ ፡ እርሱ ፡ ቀረ ፡ ይባላል። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፱ኝ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ እንደገዛ ፡ ሞተ። ሲሞትም ፡ ፫ቱ ፡ ልጆቹ ፡ ጽንፈ ፡ አርእድ ፡ ሕዝበ ፡ ኣሰግድ ፡ ቅድመ ፡ ኣሰግድ ፡ ዣን ፡ አሰግድ ፡ ሰብኣ ፡ አሰግድ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በየተራ ፡ ይንገሡ ፡ ብሎ ፡ ተናዞ ፡ ኖሮ ፡ እነዚሁ ፡ ልጆቹ ፡ አንድ ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ በየተራ ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ የአፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ልጅ ፡ አጐታቸው ፡ ውድም ፡ አርእድ ፡ መንግሥትን ፡ ይዞ ፡ ያስተዳድር ፡ ዠመር። እርሱም ፡ በነገሠ ፡ በ ፡ ፲፬ኛው ፡ ዓመት ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይመኖት ፡ ዐረፉ። ውድም ፡ ኣርእድም ፡ ፲፫ ፡ ዓመት ፡ እንደገዛ ፡ በሺ፩፻፷፫ ፡ ዓ.ም ፡ ሞተ ፤ ውድም ፡ ረዓድ ፡ በዘመኑ ፡ ምን ፡ እንደሠራ ፡ የሚናገርለት ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ በግዕዝም ፡ በፈረንጆችም ፡ ኣልተገኘለትም። በዘመኑ ፡ የመንግሥቱን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ለመጻፍ ፡ ሞክሯል ፡ የሚሉ ፡ አሉ ፡ በዛን ፡ በቲስት ፡ ኵልቦ ፡ ፩ኛ ፡ ቮሊም ፡ በገጽ ፡ ፩፻፵፪ ፡ አማካይነት ፡ የኢኛሲዮ ፡ ጕይዲን ፡ ዲክሲዮሬር ፡ ተመልከት። እንደዚሁም ፡ በዘመኑ ፡ ሽህ ፡ መሐመድ (አቡ ፡ አብደላ ፡ የሚባለው ፡ ለውጊያ ፡ ከሰበሰባቸው ፡ ከአዳልና ፡ ከይፋት? ባላባቶች ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ እንዲገብር ፡ ኣስገድዶታል ፡ ብለው ፡ የጻፉ ፡ አሉ። ኤንሪኮ ፡ ቼሩሊ ፡ የደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በዓረብ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ዘንድ ፡ በሚባል ፡ መጽሐፉ ፡ አልሙፋዳል ፡ የሚባል ፡ የግብፅ ፡ ክርስቲያን ፡ መጻፉን ፡ ገልጿል ፤ ራሴኛ ፡ ዲ ፡ ስቱዲ ፡ ኤቲዮፒቺ ፡ በሚባል ፡ አርእስት ፡ ሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ያሳተሙትን ፡ ፩፻፷፲ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ተመልከት። በተረፈ ፡ ውድም ፡ ረዐድ ፡ ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ የሠራው ፡ ኣልታወቀም። ነገር ፡ ግን ፡ የርሱ ፡ ልጅ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ነግሦ ፡ የሠራውን ፡ ብዙ ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ እነሆ ፡ በሚቀጥለው ፡ እንመለከታለን።

# ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ ፯

## የታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ጽሑፍ።

ኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የአፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ያዬ ፡ ውድም ፡ ረዓድ (አርእድ) ልጅ ፡ ነው ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የወጣው ፡ በሺ፪፻፲፰ (፱?) ዓ.ም ፡ ላይ ፡ ነው። ይህ ፡ ንጉሥ ፡ በዘመኑ ፡ የጠፋውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ እንደገና ፡ በማደሱ ፡ በአዳሎች ፡ ላይ ፡ ድልን ፡ በማግኘቱ ፡ በጣም ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ነው።

የአክሱም ፡ መንግሥትና ፡ ሕዝብ ፡ በመዠመሪያው ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ጻፍነው ፡ ባባቶቻቸው ፡ በሳባውያን ፡ ኣናጋሪበሌለው ፡ ግዕዝኛ ፡ ፊደል ፡ ሲሠሩ ፡ ቆይተው ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ከሳባውያን ፡ ፊደል ፡ የመጣውን ፡ አሻሽለው ፡ ለግዕዙ ፡ ፊደል ፡ ኣናጋሪ ፡ ምልክት ፡ ኣበጅተው ፡ ይሠሩ ፡ ዠመር።

በዚህም ፡ ፊደልና ፡ ባልሠለጠነው ፡ የግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ሊፈርስ ፡ ባልቻለው ፡ ሐውልትላይ ፡ የጻፉትን ፡ በምዕራፉ ፡ ላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ እንደዚሁም ፡ በዚሁ ፡ ፊደል ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጽሐፍና ፡ ይልቁንም ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ እንደነበራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው።

ነገር ፡ ግን ፡ በመዠመሪያው ፡ መጽሐፍ (ቦሉም)እንደተጻፈው ፡ ዮዲት ፡ የምትባለዋ ፡ የፈላሻ ፡ ሴት ፡ ተነሥታ ፡ የአክሱምን ፡ ነገሥታትና ፡ ዘራቸውን ፡ ለማጥፋት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑንም ፡ ለማቃጠል ፡ ሐውልቱንም ፡ ለማፍረስ ፡ በሞከረችበት ፡ ጊዜ ፡ በቀላሉ ፡ ፈርሶ ፡ ለማለቅ ፡ ያልቻለው ፡ ሐውልትና ፡ የድልነዓድ ፡ ዘር ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሸሽቶ ፡ ሲተርፍ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ሁሉ ፡ በሁሉ ፡ አቃጥላው ፡ ስለነበረ ፡ የአክሱም ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ በፍጹም ፡ ጠፍቶ ፡ ነበር። ያን ፡ ጊዜ ፡ እንደዛሬ ፡ በማኅተም ፡ ተራብቶ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ የማይገኘውን ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ጨርሶ ፡ ለማጥፋት ፡ ብዙ ፡ ኣስቸጋሪ ፡ ኣልነበረም። ስለዚህ ፡ ከዮዲት ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ድረስ ፡ ታሪክ ፡ የሚጠቀሰውና ፡ የሚተረከው ፡ ከአዋቂዎች ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ የወረደው ፡ ብቻ ፡ ነበር። ይህ ፡ ብልህ ፡ ንጉሥ ፡ እዙፋን ፡ ከወጣ ፡ ወዲህ ፡ ይህ ፡ በቃል ፡ የሚነገረው ፡ ታሪክ

፡ በቶሎ ፡ ከብራና ፡ ላይ ፡ ሠፍሮ ፡ ለልጅልጅ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ከአልሆነ ፡ ወደፊት ፡ ጨርሶ ፡ ሊጠፋ ፡ እንደሚችል ፡ ተገነዘበ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ወይም ፡ በዘመ ፡ የነበረ ፡ ዛሬ ፡ ስሙ ፡ ያልታወቀ ፡ አንድ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ብልህ ፡ ሊቅ ፡ አሳስቦት ፡ እንደሆነ ፡ ኣይታወቅም።

ስለዚህ ፡ ያለፈ ፡ ታሪክ ፡ የሚያውቊትን ፡ ሊቃውንቱን ፡ ሰብስቦ ፡ ታሪክ ፡ እንዲጻፍ ፡ አዘዘ ፡ ይባላል። ብዙ ፡ የዳኝነት ፡ የጦር ፤ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሥራው ፡ የሚያከናውኑ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በየክፍሉ ፡ ሲደለድል ፡ እንደዚሁም ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡ ታሪክ ፡ ዜና ፡ መዋዕልን ፡ የሚያዘጋጅ ፡ የጸሐፌ ፡ ትእዛዝነት ፡ ማዕርግ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ሾመ።

ባለፈው ፡ እንዳመለከትነው ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዙም ፡ ሲጠራ ፡ “ ፡ አዛዥ ፡ እገሌ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዙ ፡ ለእገሌ ፡ የተባለ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህም ፡ ባሉት ፡ ነገሥታት ፡ ይሠየም ፡ ዠመር። ስለዚህ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የጸሐፌ ፡ ትእዛዝት ፡ የሥራ ፡ እንጂ ፡ እንደዛሬ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ አልተወሰነም ፡ ነበር ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ዛሬ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሲባል ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ሆኖተግባርንም ፡ ጭምር ፡ ሲያሳይ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ አዛዥ ፡ እገሌ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዙ ፡ እገሌ ፡ ሲል ፡ “አዛዥ ፡ የማዕርግስም ፡ “ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ተግባሩን (ሥራውን) የሚገልጽ ፡ ይመስላል።

የሆነሆኖ ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ የጸሐፌ ፡ ትእዛዝነት ፡ ተግባር ፡ ያለው ፡ አዛዥ ፡ በውስጡ ፡ ግዕዙ ፡ “ጸሐፍት ፡ ዘእምታሕቴሁ ፡ የሚላቸውን ፡ አበጅቶ ፡ ራሱም ፡ የሚያውቀውን ፡ የማያውቀውንም ፡ ከሊቃውንቱ ፡ እየጠየቀ ፡ ዛሬ ፡ ሙሉ ፡ ጐደሎም ፡ ቢሆን ፡ ክብረነገሥትና ፡ ታሪካ ፡ ነገሥት ፡ ዘኣክሱም ፡ እየተባለ ፡ የሚጠቀሰውን ፡ መጽሐፍ ፡ አዘጋጀ። እርሱና ፡ በየጊዜው ፡ የሚነሡት ፡ ጸሐፍተ ፡ ትእዛዘት ፡ ሲያዘጋጁም ፡ የሰሎሞንን ፡ ዘር ፡ ከላይ ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ አብርሃም ፡ ከአብርሃም ፡ እስከ ፡ ዳዊትና ፡ እስከ ፡ ልጁ ፡ እስከ ፡ ሰሎሞን ፡ ስማቸውን ፡ እየዘረዘሩ ፡ ከዚያ ፡ ከሰሎሞንና ፡ ከንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ተወለዶ ፡ የመዠመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ መሆኑን ፡ ከዚያም ፡ የሰሎሞንን ፡ ተከታዮች ፡ እየዘረዘሩ ፡ በመካከሉም ፡ እንደ ፡ አብርሃ ፡ እንደ ፡ ካሌብ ፡ እንደ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ላሉት ፡ የሚያውቊትን ፡ ታሪክ ፡

እያተቱ ፡ ከመንፈሳዊመጽሐፍም ፡ እየጨመሩ ፡ ዝርዝሩን ፡ እስከ ፡ ዘመኑ ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ አድርሰው ፡ አዘጋጁ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ያለውን ፡ ግን ፡ በየጊዜው ፡ በተነሡት ፡ ነገሥታት ፡ በነዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በነልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ እየተጨመረ ፡ ይዘጋጅ ፡ ዠመር።

ከእነዚህም ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንደ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ያሉት ፡ ከታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ውጭ ፡ የየራሳቸውን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በየጸሐፌ ፡ ትእዛዛቸው ፡ አማካይነት ፡ እንዲዘጋጅ ፡ አድርገዋል።

ባፄ ፡ ላሊበላ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የተጻፈው ፡ የክብረ ፡ ነገሥት ፡ ታሪክ ፡ የሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ጸሐፊው ፡ ይስሐቅ ፡ የተባለው ፡ እንደሚለው ፡ ባፄ ፡ ላሊበላ ፡ ዘመን ፡ ከእስክንድርያ ፡ ወጥቶ ፡ ከዓረብ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ሳይተረጐም ፡ እንደዚሁ ፡ ተቀምጦ ፡ ሲኖር ፡ የአክሱም ፡ ንቡረ ፡ ዕድ ፡ ይስሐቅ ፡ ከትግሬ ፡ ሹም ፡ ከያዕቢከ ፡ እግዚእ ፡ ጋር ፡ ተማክሮ ፡ ከጓደኞቹ ፡ ሊቃውንት ፡ ከነይምርሐነ ፡ አብ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ የተረጐመው ፡ በዚሁ ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ ነው።

ስለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒም ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴትም ፡ የግል ፡ አሳባቸውን ፡ ሲሰጡ ፡ ጸሐፊው ፡ ንቡረ ፡ ዕድ ፡ ይስሐቅ ፡ ለዚህ ፡ ለክብረ ፡ ነገሥት ፡ መጽሐፉ ፡ ቍም ፡ ነገርና ፡ ክብር ፡ ለመስጠት ፡ በህዝብም ፡ ዘንድ ፡ ለማስከበር ፡ ሲል ፡ በላሊበላ ፡ ዘመን ፡ ከግብፅ ፡ ከማርቆL ፡ ወንበር ፡ ወጥቶ ፡ ሲኖር ፡ በኋላ ፡ ወደግዕዝ ፡ ተረጐምነው ፡ ያለው ፡ እውነት ፡ አይመስልም ፤ ይኸንኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ባፄ ፡ አምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ ራሱ ፡ ንቡረ ፡ ዕድ ፡ ይስሐቅ ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ እየጻፈ ፡ አዘጋጀው ፡ ብለዋል። አኤቲዎፒካ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ የጻፈውን ፡ በ ፡ ፪ኛው ፡ ሴፊ ፡ ፴፩ ፡ ቍጥር ፡ ተመልከት። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ወልደ ፡ ጠቢብ ፡ በማለት ፡ እብነ ፡ ሐኪም (የብልህ ፡ ልጅ) እያለ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ አንዳንድ ፡ የዓረብኛ ፡ ቃል ፡ ስለሚገኝበት ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በፊት ፡ በዓረብኛ ፡ ተጽፎ ፡ እንደነበረና ፡ ተርጓሚው ፡ ይስሐቅ ፡ በቀጥታ ፡ ዐረብኛውን ፡ እንዳለ ፡ የወሰዱት ፡ ይመስላል።

የዛሬም ፡ ዘመን ፡ ሕዝብ ፡ ይልቁንም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብ ፡ የሚያውቀውና ፡ ወገኑ ፡ ያዘጋጀውን ፡ መጽሐፍ ፡ አክብሮ ፡ ኣድንቆ ፡ መቀበል ፡ ያዳግተዋል። ስለዚህ ፡ ሌሎች ፡ አረማውያንም ፡ እስላሞችም ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ብዙ ፡ የክርስቲያን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ገድልም ፡ ድርሳንም ፡ ጻፈው ፡ ከሰማይ ፡ ወረደ ፡ ወይም ፡ መልአክ ፡ እየነገረው ፡ ኣጻፈው ፡ እማለት ፡ ደርሰዋል። መሐመድ ፡ ቍራንን ፡ ገብርኤል ፡ ከሰማይ ፡ አውርዶ ፡ ሰጠኝ ፡ ሲል ፡ ከዚሁ"ጕዳይ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው። ስለዚህ ፡ እነንቡረ ፡ ዕድ ፡ ይስሐቅ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደ ፡ ማለት ፡ እንዳይበዛ ፡ ሕዝቡና ፡ ካህናቱ ፡ ከሚያከብሩት ፡ ከማርቆስ ፡ ወንበር ፡ ወጣ ፡ ብላው ፡ በዘዴ ፡ ሕዝቡ ፡ እንዲቀበል ፡ ኣድርገውት ፡ እንደሆነ ፡ ኣይታወቅም። ወይም ፡ ፩ ፡ ክርስቲያን ፡ ግብፃዊ ፡ በነላሊበላ ፡ ዘመን ፡ መጥቶ ፡ በዐረብኛ ፡ አዘጋጅቶት ፡ ሲኖር ፡ እነንቡረ ፡ ዕድ ፡ ይስሐቅ ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ ወደግዕዝ ፡ ተርጕመውት ፡ ይሆናል።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በጕብዝናውና ፡ በአስተዳዳሪነቱ ፡ መካከል ፡ የታሪክንና ፡ የጽሑፍን ፡ ጥቅም ፡ ተረድቶ ፡ ሊረሣ ፡ የነበረውን ፡ የአክሱሞቹን ፡ ታሪክ ፡ ጭምር ፡ በማጻፉ ፡ ከርሱ ፡ በኋላም ፡ የሚነሡት ፡ ነገሥታት ፡ በየጊዜው ፡ የሡሩትን ፡ የሚያሳይ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ እንዲያጽፉ ፡ ምሳሌ ፡ በመሆኑ ፡ ከጸሐፊዎቹ ፡ ከነንቡረ ፡ ዕድ ፡ ይስሐቅና ፡ ከነይምርሐነ ፡ ኣብ ፡ ጋር ፡ ምሥጋና ፡ ይገባዋል።

# ምዕራፍ ፡ ፰

## በኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንና ፡ በዘመኑ ፡ ሊቃውንት ፡ መካከል ፡ የተነሣው ፡ ጠብ

በኋላ ፡ ዘመን ፡ በዳግማዊ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድ ፡ ዘመነመንግሥት (፲፯፻፳፫-፲፯፻፵፭ ፡ ዓ.ም) በቀድሞ ፡ ላይ ፡ እየተሞላ ፡ በደጃች ፡ ኃይሉ ፡ እሸቱ ፡ ትጋት ፡ የተዘጋጀው ፡ ታሪክ ፡ እንደሚለውና ፡ ከገድለ ፡ ፊልጶስ ፡ አግኝተው ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ በዋዜማ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ያወጡት ፡

የቀሩትም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ብሩስ ፡ ኰልቦ ፡ ባሴት ፡ ረኔ ፡ ... ፡ የጻፉት ፡ እንደሚለው ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ባባቱ ፡ ዙፋን ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ ግማሾቹ ፡ የማትወልደውን ፡ ያባቱን ፡ የውድም ፡ ረዓድን ፡ ሚስት ፤ ግማሾቹ ፡ ከእኅቶቹ ፡ ውስጥ ፡ ዕቀባት ፡ ኣድርጎ ፡ አስቀመጠ ፤ የቀሩት ፡ በእኅትማማቾች ፡ ላይ ፡ አመነዘረ ፡ እያሉ ፡ ሐሜታ ፡ በዝቶ ፡ ነበር። ምንም ፡ እንኳን ፡ ይኸን ፡ የመሰለው ፡ ሁኔታ ፡ በምሥራቅና ፡ በኣፍሪካ ፡ ነገሥታትና ፡ መሣፍንት ፡ ዘንድ ፡ የተለመደ ፡ ቢሆን ፡ በክርስቲያኖች ፡ ዘንድ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ማስነቀፉ ፡ የታወቀ ፡ ነውና ፡ የዚህን ፡ ወሬ ፡ የሰሙ ፡ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፡ እየተገረሙ (ብዙ ፡ ሐሜት ፡ በዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ላይ ፡ ተነሣ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከግብፅ ፡ ተመርጠው ፡ የመጡት ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ይባላሉ ፤ እርሳቸውም ፡ ለሹመትና ፡ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ ሥልጣን ፡ የማይሰስቱ ፡ ለወንጌል ፡ መስፋፋት ፡ የሚጥሩ ፡ ጳጳስ ፡ ኖረው ፡ ሰፊውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ እየዞርሁ ፡ ለማስተማር ፡ ቅስናና ፡ ዲቍናም ፡ ብቻዬን ፡ ለመስጠት ፡ አልችልም ፡ ብለው ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሱን ፡ መምህር ፡ እጨጌ ፡ ፊልጶስን ፡ ጠርተው ፡ ከርሳቸው ፡ በታች ፡ የኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥተው ፡ በመላ ፡ ሸዋ ፡ ላይ ፡ ሾሟቸው። እጨጌ ፡ ፊልጶስለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ እጨጌነት ፡ ከኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዝምሮ ፡ ፫ኛ ፡ መሆናቸው ፡ ነው። እርሳቸውም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ እኔም ፡ በበኵሌ ፡ ሸዋን ፡ የሚያህል ፡ አገር ፡ ብቻዬን ፡ አስተምሬ ፡ አላደርሰውም ፡ ብለው ፡ እርሳቸው ፡ እንደጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ሐዋርያነቱን ፡ ይዘው ፡ ከርሳቸው ፡ በቀር ፡ ፲፩ ፡ መምህራን ፡ መርጠው ፡ አባ ፡ አኖሬዎስን ፡ ወረብ ፤ አባ ፡ አድኅነነ ፡ ዳሞት ፡ «ወላሞ» ፡ አባ ፡ ኢዮስያስን ፡ ወንጂ ፡ «አሩሲ» ፡ አባ ፡ ማትያስን ፡ ፈጠጋር ፡ ኣባ ፡ ዮሴፍን ፡ እናርያ ፡ «ሊሙ» ፡ ኣባ ፡ ታዴዎስን ፡ ጽላልሽ ፡ «ቡልጋ» ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስን ፡ ቦረና ፡ «ደብይ» ፡ ኣባ ፡ ቀውስጦስን ፡ መሐግል ፡ «ጥጥ ፡ አምባ» ፡ አባ ፡ ሳሙኤልን ፡ ወገግ ፡ «አሰቦት» ፡ አባ ፡ መርቆሬዎስን ፡ መራቤቴአባ ፡ ኣኖሬዎስን ፡ ወግዳና ፡ ሞረት ፡ ሾመው ፡ እንዲያስተምሩ ፡ አከፋፈሏቸው። ይኸን ፡ የመሰለው ፡ የሐዋርያነትና ፡ የመምሕራን ፡ ተግባር ፡ ጳጳሱን ፡ ኣባ ፡ ያዕቆብን ፡ እጨጌውንና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሱን ፡ ኣባ ፡ ፊልጶስን ፡ በጣም ፡ ያስመሰግናቸዋል።

እንግዴህ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ያባቱን ፡ ሚስት ፡ የማግባቱ ፡ ወሬ ፡ በአባ ፡ ፊልጶስና ፡ በነዚሁ ፡ መምህራን ፡ vሮ ፡ ደርሶ ፡ በጣም ፡ ኀዘንን ፡ ፈጠረባቸው። የግዕዙ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ግን ፡ ዕቅብተ ፡ አቡሁ (የአባቱ ፡ ዕቍባት) ይላል ፡ እንጂ ፡ ሚስት ፡ አይልም ፡ ፤ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዋናው ፡ መምህርናኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ አባ ፡ ፊልጶስ ፡ በገሀድ ፡ ንጉሡን ፡ ኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ በመንፈሳዊ ፡ አባትነት ፡ ወቅ ፡ ከዚህ ፡ ከማይገባ ፡ ሥራ ፡ ለማስጣል ፡ ብለው ፡ አባ ፡ አኖሬዎስን (ዘድጋጀ)ና ፡ ሌሎችም ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስን (የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ስሙ ፡ ደብረ ፡ አስቦ) መነኮሳትን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ ተጕለት ፡ መጡና ፡ ከንጉሡ ፡ ከአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ተገናኙ። ንጉሡም ፡ ከሰላምታ ፡ በኋላ ፡ የመጡበትን ፡ ጕዳይ ፡ ቢጠይቃቸው ፤ "ያባትህን ፡ ሚስት ፡ አግብተሃል" የሚሉ ፡ ወሬ ፡ ብንሰማ ፡ እውነትና ፡ ሐሰቱን ፡ ለመረዳት ፡ ነው ፡ የመጣነው ፡ ብለው ፡ መለሱለት። እርሱም ፡ «የማትወልደኝን ፡ ያባ ፡ ቴን ፡ ሚስት ፡ ባገባ ፡ ምን ፡ ኀጢአት ፡ አለበት ፡ ለዚያውም ፡ እንደናንተ ፡ የተማሩ ፡ ሊቃውንት ፡ የማትወልድህን ፡ ያባትህን ፡ ሚስት ፡ ብታገባ ፡ መንግሥትህ ፡ ይሰፋል ፡ ጠላትህ ፡ ይከፋል" ብለውኛል ፡ ሲል ፡ መለሰ። ንጉሡና ፡ እጨጌ ፡ ፊልጶስ ፡ የዚህኑ ፡ ጕዳይ ፡ እየተመላለሱ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ኣብረው ፡ ከእጨጌ ፡ ጋር ፡ የመጡት ፡ አባ ፡ አኖሬዎስ ፡ ግን ፡ በቍጣ ፡ ቃል ፡ ንጉሡን ፡ ስለተናገሩ ፡ ንጉሡ ፡ በዚሁ ፡ ተናደደና ፡ ግረፉት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ። የዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ሰዎች ፡ ገበያ ፡ ለገበያ ፡ እያዞሩ ፡ መነኵሴውን ፡ አባ ፡ አኖሬዎስን ፡ ሲገርፉ ፡ መነኵሴውም ፡ ሳይፈሩና ፡ ሳይጸጸቱ ፡ አፄ ፡ ዓምዶ ፡ ጽዮንን ፡ እየተሳደቡ ፡ ይገዝቱ ፡ ነበር ፡ ይባላል። ሲመሽም ፡ በከተማው ፤ ቃጠሎ ፡ ተነሥቶ ፡ ብዙ ፡ ቤት ፡ ተቃጠለ። የዚህም ፡ ቃጠሎ ፡ ወሬ ፡ በሁለት ፡ ዓይነት ፡ ተወራ። በንጉሡና ፡ በወገኖቹ ፡ ዘንድ ፡ የወንድማቸው፣ ፡ መገረፍ ፡ ያናደዳቸው ፡ መነኵሴዎች ፡ አቃጠሉት ፡ ተባለ። በመነኮሳቱ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በግፍ ፡ የአባ ፡ አኖሬዎስን ፡ ደም ፡ በከተማው ፡ አስገርፎ ፡ ስለአፈሰሰ ፡ ደሙ ፡ እሳት ፡ ሆኖ ፡ ከተማውን ፡ አቃጠለበት ፤ ተብሎ ፡ ተወራ። ይኸንኑ ፡ በመደገፍ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የተጻፈው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ በግዕዝ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ የሚለው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነው። መወኒ ፡ ዕበ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ኮነ ፡ ስደት ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ፡

እስመ ፡ አባ ፡ አኖሬዎስ ፡ ዘድጋጃ ፡ አውግዞ ፡ ለሐፄ ፡ ዓምደጽዮን ፡ ዕበ ፡ ነሥአ ፡ ዕቅብተ ፡ ኣቡሁ ፡ ቦ ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ ከመወ ፡ በእኀቱ ፡ ወዐ ፡ እላ ፡ ይቤሉ ፡ አበሰ ፡ በ፪ ፡ ኣሓት ፡ ወቀሠፈለኣባ ፡ ኣኖሬዎስ ፡ ዓቢየ ፡ ቅሥፈተ ፡ እስከ ፡ ኣንደደ ፡ በልዐ ፡ ከተማ ፡ ንጉሥ ፡ ነጠብጣበ ፡ ደሙ ፡ ለአባ ፡ አኖሬዎስ ፡ ከዊኖ ፡ ነበልባለ ፡ እሳት ፡ ታሪከ ፡ ነገሥታቱ ፡ የሚመሰክረው ፡ ለመነኮሳቱ ፡ ነው። ምክንያቱም ፡ ተገራፊው ፡ መነኰሴና ፡ ወቃሾቹ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ወገኖችታሪከ ፡ ነገሥቱንም ፡ ያዘጋጁት ፡ ጸሐፍተ ፡ ትእዛዛት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ወገኖች ፡ በመሆናቸው ፡ ይመስላል። የከተማውን ፡ መቃጠል ፡ እውነተኛውን ፡ ምክንያት ፡ የሚያውቀው ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ ለመለየት ፡ አይቻልም

እንደዚሁም ፡ በግዕዙ ፡ ላይ ፡ እንደምናነበው ፡ ያቄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንም ፡ ኀጢአት ፡ በትክክል ፡ ኣልተለየም ፡ ግማሹ ፡ ያባቱን ፡ ዕቍባት ፡ አገባ ፡ ሲል ፤ ግማሹ ፡ ከእኅቱ ፡ ጋር ፡ ተኛ ፡ የቀረው ፡ ደግሞ ፡ በሁለት ፡ እትማማቾች ፡ አመነዘረ ፡ ብለዋል። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ መነኰሳቱ ፡ ባባቱ ፡ ዕቍባትም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በእኅቱ ፡ አለበለዚያም ፡ በእኅትማማቾች ፡ ማመንዘሩን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ አሁንደግሞ ፡ በዚሁ ፡ ሊገሥጸው ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ድረስ ፡ የመጣውን ፡ መነኰሴ ፡ በመግረፉ ፡ የመነኰሴውን ፡ ዴም ፡ ወደ ፡ እሳተ ፡ ነበልባልነት ፡ ለውጦ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ከተማውን ፡ አቃጠለበት ፡ እያሉ ፡ እያወሩ ፡ ሕዝብንም ፡ የሚያስነሡበት ፡ ስለሆነ ፡ ከሹማማንቱ ፡ ጋር ፡ ተማከረና ፡ እጨጌ ፡ ፊልጶስንና ፡ መነኮሳቱን ፡ ከገዳማቸው ፡ ከደብረ ፡ አስቦ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ) እንዲሰደዱ ፡ አደረገ። እጨጌ ፡ ፊልጶስም ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ ግሼን ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ተሰደዱ ፤ በዚያም ፡ በተሰደዱበት ፡ አገር ፡ ማስተማራቸውን ፡ ቅስና ፡ ምንኵስና ፡ መስጠታቸውን ፡ አልተዉም። በዚያም ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘከብራንን ፡ አባ ፡ ተክላ ፡ አልፋ ፡ ዘዲማን፣ አባ ፡ ተከሥተ ፡ ብርሃንን ፡ ዘደብረ ፡ ፆታን ፡ ማመንኮሳቸው ፡ የቀሩትም ፡ ወደደንቢያ ፡ ወደ ፡ ቤገምድር ፡ እየተሰደዱ ፡ ማስተማራቸው ፡ በታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ይገኛል።

እንደ ፡ እጨጌ ፡ ፊልጶስ ፡ እንደ ፡ ኣባ ፡ አኖሬዎስ ፡ ያሉ ፡ የመንፈሳዊ ፡ አባቶች ፡ ኀጢአት ፡ ሲሠራ ፡ እያዩ ፡ ወይም ፡ እየሰሙ ፡ ችግርን ፡ ስደትን ፡ በመፍራት ፡ ዝም ፡ የማይሉ ፡ ሞልተዋል። በብሉይ ፡ በመጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ በምዕራፍ ፡ ፳፩ ፡ እንደሚገኘው ፡ አክአብ ፡ የ፳ኤል ፡ ንጉሥ ፡ የናቡቴን ፡ ለምለም ፡ መሬት ፡ በግፍ ፡ ቢቀማ ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንደምን ፡ በድፍረት ፡ እንደወቀሰው ፡ ዳዊት ፡ ጭፍራውን ፡ ኦርዮንን ፡ ወደ ፡ ወርነት ፡ ልኮ ፡ አስገድሎ ፡ ሚስቱን ፡ ቢቀማ ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ እንደምን ፡ እንደ ፡ ወቀሰው ፡ ስንመለከት ፡ በአቡነ ፡ ፊልጶስና ፡ በአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ - ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ጠብ ፡ ከነዚያ ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰል ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ የዳዊት ፡ ኀጢኣት ፡ ከዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የሚበልጥ ፡ ቢሆንም ፡ ዳዊት ፡ ዬናታንን ፡ ተግሣጽ ፡ ሰምቶ ፡ ንስሐ ፡ ሲገባ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንደ ፡ አክአብ ፡ አባ ፡ ፊልጶስንና ፡ አባ ፡ አኖሬዎስን ፡ ግርፋትና ፡ ስደት ፡ ስለአመጣባቸው ፡ ከሁሉም ፡ ኃጢኣቱን ፡ ተረድቶ ፡ የተጸጸተው ፡ ዳዊት ፡ ምሥጋና ፡ ይገባዋል።

፩ ፡ ኣንድ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አገር ፡ የሚያስተዳድር ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ኃጢኣት ፡ ሲሠራ ፡ በሕዝብም ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ ሲሠራ ፡ እያዩ ፡ ወይም ፡ እየሰሙ ፡ እንዳላዩ ፡ ኣይተው ፡ እንዳልሰሙ ፡ ሰምተው ፡ በስምምነት ፡ ኣብረው ፡ የሚኖሩ ፡ አይጠፉም። ይኸውም ፡ በዘመኑ ፡ ከነገሠው ፡ ሊሾም ፡ ሊሽር ፡ ሊያሥር ፡ ሊፈታ ፡ ከሚችል ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ መጣላት ፡ ከግርፋትም ፡ ወዲህ ፡ የዕለት ፡ ጥቅማቸውን ፡ የተቀመጡበትን ፡ የሥልጣን ፡ ደረጃ ፡ እንዳያፈናቅልባቸው ፡ ዘመናቸውን ፡ በደስታና ፡ በሰላም ፡ ለማሳለፍ ፡ የቆረጡ ፡ ያድር ፡ ባይነት ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው። እጨጌ ፡ ፊልጶስ ፡ ግን ፡ በሐዋርያነት ፡ ሥራቸው ፡ እንዳመሰገናቸው ፡ ኣሁን ፡ ደግሞ ፡ ለታላቀኍ ፡ ሹመትላእጨጌነት ፡ ሳይሳሱ ፡ ኃጢኣት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በተረዱበት ፡ ነገር ፡ ከኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጋር ፡ ሐሜታ ፡ ሳይሆን ፡ ፊትለፊት ፡ እንደ ፡ አባ ፡ ኣኖሬዎስ ፡ ወወጣላታቸው ፡ በዚሁ ፡ የደረሰባቸውን ፡ ስደት ፡ ታግሠው ፡ በተሰደዱበትም ፡ አገር ፡ የመምህርነትና ፡ ያባትነት ፡ ሥራቸውን ፡ አለማቋረጣቸው ፡ በምሥጋና ፡ ላይ ፡ ምሥጋና ፡ ይጨምርላቸዋል

# ምዕራፍ ፡ ፱

## የዘር ፡ ሐረግ።

ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ ከመዠመራችን ፡ በፊት ፡ የነገሥታቱን ፡ የይኵኖ ፡ አምላክን ፡ ተከታዮችና ፡ አንገዛም" ፡ እያሉ ፡ እየሸፈቱ ፡ የተዋጉትን ፡ የይፋት ፡ ወላስሞችን ፡ የዘር ፡ ግንድ ፡ ብንመለከት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለምናነበው ፡ ታሪክ ፡ ሁሉ ፡ ይጠቅመናል።

ከዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ ፩ኛው ፡ ቀጥር ፡ የይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ፪ኛው ፡ ቍጥር ፡ የወላስማ ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ ይገኛል። ይኸንንም ፡ ለመሥራት ፡ ያሳሰበን ፡ ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ድረስ ፡ የይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ተከታዮች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ እነአምደ ፡ ጽዮን ፡ እነዳዊት ፡ እነይስሐቅ ፡ እነዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሰፊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታቸው ፡ እንዳይከፈል ፡ ወይም ፡ እንዳይቀነስ ፡ ከሚሸፍቱባቸው ፡ ከይፋት ፡ ከሐድያ ፡ ከደዋሮ ፡ ከአዳል ፡ ባላባቶች ፡ ጋር ፡ ያደረጉት ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ ነው። እነዚያም ፡ የዛጕዬ ፡ መንግሥት ፡ ከግዛታቸው ፡ ርቆ ፡ በላስታ ፡ በሚገዛበት ፡ ጊዜ ፡ ምናልባት ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጦር ፡ ሲመጣ ፡ እየተዋጉ ፡ ወይም ፡ እየሸሹ ፡ አንድ ፡ ፩ ፡ ጊዜም ፡ እየገበሩ ፡ ኖረው ፡ እንደሆነ ፡ ዝርዝር ፡ ታሪኩ ፡ አይገኝም። ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ በሰላም ፡ ባገራቸው ፡ በየራሳቸው ፡ ባላባት ፡ እየተመሩ ፡ በነፃነት ፡ ኖረዋል። አሁን ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ መደበኛ ፡ ከተማ ፡ በሸዋ ፡ ሲሆን ፡ ለነዚህ ፡ አገሮች ፡ ቅርብ ፡ በመሆኑ ፡ በወሰናቸው ፡ የሚገኘው ፡ የይፋቱ ፡ የደዋሮው ፡ የአዳሉ ፡ ባላባቶች ፡ ልክ ፡ እንደትግሬው ፡ እንደ ፡ ጐጃሙ ፡ እንደ ፡ ሸዋው ፡ እንዳማራው ፡ እንዲገብርና ፡ እንዲገዛ ፡ ነገሥታቱ ፡ በቅርብ ፡ መቆጣጠር ፡ ስላበዙ ፡ እነዚያ ፡ ደግሞ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ እስላም ፡ ሆኖ ፡ የመሣሪያም ፡ የአሳብም ፡ እርዳታ ፡ ከዓረብ ፡ ከግብፅ ፡ በማግኘታቸው ፡ አንገዛም ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየሸፈቱ ፡ የተዋጉበት ፡ እየታረቁ ፡ የገቡበት ፡ ፩ዱ ፡ ሲሸፍት ፡ ወንድሙ ፡ ከነገሥታቱ ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ እየገበረ ፡ ሹመቱን ፡ ያጸደቀበት ፡ ታሪክ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በየምዕራፉ ፡ ውስጥ ፡ ታሪኩ ፡ ተተርኮ ፡ ይገኛል። ከቀሩትም ፡ ይበልጥ ፡ የይፋቱ

፡ የወላስማ ፡ ዘር ፡ ከነገሥታቱ ፡ የተዋጋበት ፡ ታሪክ ፡ ብዙ ፡ ነው። ስለዚህ ፡ በታሪክ ፡ እየተዘረዘረ ፡ ከሚነበበው ፡ ጋር ፡ የኢትዮጵያ ፡ የነገሥታቱ ፡ ሐረግና ፡ የወላስሞቹ ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ በሰሌዳ ፡ ተሠርቶ ፡ ሲገኝ ፡ የአንባቢን ፡ አሳብ ፡ ይበልጥ ፡ ያበራለታል። ይኸም ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ የተሠራው ፡ የነገሥታቱ ፡ ከታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ውስጥ ፡ የወላስሞቹ ፡ ኣል ፡ ማቅሪዝና ፡ አል ፡ ታሪቢርዲ ፡ የሚባሉ ፡ ዓረቦች ፡ ከጻፉትና ፡ እነባሴት ፡ ረኔ ፡ እነዡል ፡ ፔሩሾ ፡ እነኤንሪኮ ፡ ቼሩሊ ፡ ተርጕመው ፡ ከአሳተሙት ፡ ውስጥ ፡ የተገኘ ፡ ነው።

በይፋት ፡ ስለአሉት ፡ እስላሞች ፡ ይልቍንም ፡ ስለባላባቱ ፡ ስለወላስማ ፡ የምናገኘው ፡ የታሪክ ፡ ጽሑፍ ፡ በልክ ፡ ነው። መቼም ፡ ከመሐመድ ፡ ከነቢያቸው ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ እስላሞች ፡ ከዐረብ ፡ አገር ፡ በደቡብ ፡ ወደ ፡ ሬውሸዋ ፡ በሰሜንም ፡ ወደምጥዋ ፡ ወደ ፡ አርኪቆ ፡ በጠቅላላው ፡ ወደ ፡ ኤርትራ ፡ መግባታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው። በዚሁ ፡ በአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በ፯ኛው ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ከረሹት ፡ የሚባሉ ፡ እስላሞች ፡ መግባታቸው ፡ ይነገራል።

አሁን ፡ ግን ፡ በይፋት ፡ ስለገቡት ፡ እስላሞችና ፡ ስለወላስማ ፡ ዘር ፡ አለቃ ፡ ታየ ፡ በእጁ ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪካቸው ፡ የሚሉትን ፡ እንመልከት ፡ «በይፋት ፡ ያሉ ፡ እስላሞች ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ናቸው ፡ አርጎባ ፡ ዶባ ፡ ሻጕራ ፡ ቃጭኖ ፡ ይባላሉ። እነዚህም ፡ የአሊ ፡ ገዳዮች ፡ ናቸው። አሊ ፡ የመሐመድ (የነቢዩ) ፡ ኣማች ፡ የፋጢማ ፡ ባል ፡ ነው። ....መሐመድ ፡ ፷፫ ፡ ዓመት ፡ ገዝቶ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ኢሚር ፡ ኣቡበከር ፡ ሳዲቅ ፡ ፪ ፡ ዓመት ፡ ከርሱ ፡ ኡስማን ፡ ዕብነ ፡ ሓሩን ፡ ፲፬ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፡ በርሱም ፡ ጊዜ ፡ ግብፅና ፡ እስክንድርያ ፡ ተይዘው ፡ ሕዝቡ ፡ ሰለመ። ከኡስማንቀጥሎየመሐመድ ፡ ኣማች ፡ አሊ ፡ ነገሠ። በአሊ ፡ ዘመን ፡ ከነኸረዋን ፡ ሸዋርጅን ፡ የሚባ ፡ ሉ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ የማይጋጠሙ ፡ ሽፍቶች ፡ ነበሩና ፡ ከ፪ሺ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ፫ቱ ፡ ብቻ ፡ ሲያመልጡ ፡ የቀሩትን ፡ ኣሊ ፡ ፈጃቸው ፤ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ኣንዷት ፡ ቀጠሚት ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ ነበረች ፡ የርሷንም ፡ አባቷን ፡ ባልዋን ፡ ወንድሞቿን ፡ አሊ ፡ ከፈጃቸው ፡ በኋላ ፡ ከኣሊ ፡ ሰይፍ ፡ ከኣመለጡት ፡ ውስጥ ፡ አናግባሽ ፡ ቢሏት ፡ እኔን ፡ የሚያገባ ፡ ኣሊን ፡ መዓውያን ፡ መልአስን ፡ እነዚህን ፡ ፫ቱን ፡ የገደለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡

አለዚያ ፡ ወንድ ፡ አላ ፡ ብዬ ፡ አላገባም ፡ አለቻቸው። እነዚህም ፡ ከሞት ፡ የተረፉት ፡ ፫ቱን ፡ ለመግደል ፡ በእጣ ፡ ተካፍለው ፡ ፩ዱ ፡ ወደ ፡ መዓውያን ፡ ሄደ ፤ መዓውያን ፡ ረኽዮም ፡ ሰው ፡ ነበረና ፡ ጐልበቱን ፡ እንዳቆሰለው ፡ ሳይገድለው ፡ ተያዘና ፡ ተደብድቦ ፡ ሞተ። ወደ ፡ መልአስ ፡ የሄደው ፡ አሳስቶ ፡ ምስለኔውን ፡ ገደለና ፡ ተይዞ ፡ በካይሮ ፡ ተሰቀለ። ወደ ፡ አሊ ፡ የሄደው ፡ ግን ፡ በመስጊድ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ተደብቆ ፡ በመርዛም ፡ ጦር ፡ ወጋውና ፡ በ፫ኛው ፡ ቀን ፡ ሞተ። ገዳዩም ፡ አብዱረሕማን ፡ የሚባለው ፡ ተይዞ ፡ ተሰቀለ።

ስለዚህ ፡ አሊ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በዓረብ ፡ አገር ፡ መቀመጥ ፡ የማይሆንላቸሁ ፡ ስለሆነ ፡ የአሊ ፡ ገዳይ ፡ የአብዱረሕማን ፡ ወገኖች ፡ በቀልን ፡ ፈርተው ፡ የናረብን ፡ አገር ፡ ለቀው ፡ ወደይፋት ፡ በግልጥ ፡ መጡ ፤ ይፋት ፡ ማለትግልጥ ፡ ማለት ፡ ነው፣ ፡ የመጡበት ፡ አገርም ፡ ይፋት ፡ መባሉ ፡ ስለዚህ ፡ ነው። ዋና ፡ አበጋዛቸው (ሹማቸው) ወላስማ ፡ ይባላል ፤ ወላስማ ፡ ማላትም ፡ ወላ ፡ መስልም ፡ ወላ ፡ እስላም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ወላ ፡ እስላም ፡ ማለትም ፡ እስላም ፡ ያይደለ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ይኸንንም ፡ ስም ፡ የሰጡት ፡ አሊን ፡ ገድሎ ፡ ከእስላም ፡ ተለይቶ ፡ የወጣ ፡ መሆኑን ፡ ለማመልከት ፡ ነው ፡ እነዚህ ፡ የወላስማ ፡ ዘሮችም ፡ መልካቸው ፡ ቀያይ ፡ ቋንቋቸው ፡ ዓረብኛ ፡ ነው ፡ ግዕዝንም ፡ ይመስላል ፡

አለቃ ፡ ታዬ ፡ የዚህን ፡ የታሪክ ፡ ምንጭ ፡ ያገኙበትን ፡ ጽሑፍ ፡ አልጠቀሱትምና ፡ ታሪኩም ፡ እውነታ ፡ ቢሆን ፡ ለማመዛዘን ፡ ኣልቻልንም ፡ ፣ ይፋት ፡ የተባለው ፡ በይፋ (በግልጥ) መጡ ፡ ከተባለው ፡ ቃል ፡ ተወስዶ ፡ ት ፡ ተጨምሮ ፡ ይፋት ፡ ተባለ ፡ ያሉትንም ፡ እውነተኛ ፡ ትርጒሙ ፡ ከዐረብኛ ፡ ወይም ፡ ከአርጎባ ፡ ቋንቋ ፡ እስኪረጋገጥ ፡ ድረስ ፡ እንደዚሁ ፡ ማቆየት ፡ ይሻላል። እኛ ፡ ይፋት ፡ የምንለውን ፡ ዐረቦች ፡ አውፋት ፡ እንደሚሉት ፡ በጥንቱ ፡ በነማቅሪዝ ፡ ጽሑፍ ፡ መረጋገጡን ፡ የዐረብኛው ፡ ሊቅ ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ ገልጸዋል። እኝህ ፡ ሊቅ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥታችንን ፡ እተረጐሙበት ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፯–፩፻፳፰ ፡ ቍጥር ፡ ፳፯ ፡ ላይ ፡ በተለይ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ያደረገውን ፡ ጦርነት ፡ ሲጠቅሱ፣ ፡ ስለወላስማርና ፡ ስለይፋት ፡ እንደዚህ ፡ ይላሉ። “ከንጉሡ (ዓምደ ፡ ጽዮን) ፡ መላከተኞች ፡ አንዱ ፡ በይፋት (በዐረብኛ ፡ ኣውፋት) ፡ ተገደለ ፡ ስለዚህ ፡ በመዠመሪያ ፡ የተወጋው ፡ አገር ፡ ይፋት ፡

ነው። ማቅሪዝ ፡ እንደሚለው ፡ የዚህ ፡ አገር ፡ ሕዝቦች ፡ ሻፈይትና ፡ ሐነፊት ፡ ይባላሉ ፡ የዐረብኛና ፡ የኢትዮጵያ (ግዕዝ?) ቋንቋ ፡ ይናገራሉ። በአውራጃው ፡ የይፋት ፡ ከተማ ፡ ገበርታ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ የገዥዎቹ ( ፡ የባላባቶቹ) ፡ ዘር ፡ የመጣው ፡ ከአቡ ፡ ታሊብ ፡ ልጅ ፡ ከአቃኢል ፡ ከቆራይሽት ፡ ወገን ፡ ነው። በዚች ፡ የሐጼው (የሐበሻ ፡ ንጉሥ) ፡ ግዛት ፡ በሆነች ፡ አገር ፡ ወላስማ ፡ እስከ ፡ ተባለው ፡ እስከ ፡ ኡመር ፡ ድረስ ፡ እየተከታተሉ ፡ የኖሩት ፡ ሕዝቦች ፡ ታሪካቸው ፡ ጭለማ ፡ ነው። ወላስማ ፡ ግን ፡ በዚች ፡ በይፋት ፡ አገር ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ገዛ ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ልጆቹ ፡ በዙ ፤ ማንሱር ፤ ሐቅ ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ በየተራ ፡ ኣልጋውን ፡ ያዙ ፡ » ፡ በሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ደግሞ ፡ ወላስማ ፡ በሺ፪፻፪ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ የማህዙሚን ፡ ዘር ፡ አጥፍቶ ፡ በይፋት ፡ የራሱን ፡ ባላባትነት ፡ እንደተከለ ፡ ያረጋግጣሉ።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ በይፋት ፡ ያሉት ፡ በወላስማ ፡ የሚመሩት ፡ እስላሞች ፡ ዘመናቸው ፡ ብርታትን ፡ አግኝተው ፡ የገነኑ ፡ ሆነዋል። ከዚያ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ደህና ፡ ኣድርገው ፡ ባለመመሥረት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ዑመር ፡ ወላስማ ፡ ያላ ፡ መሪ ፡ ባላባት ፡ በማጣት ፡ ይሁን ፡ ብዙ ፡ የገነኑ ፡ አልነበሩም ፤ እነዚህም ፡ በላስታ ፡ ያለው ፡ የዛጉዌ ፡ መንግሥት ፡ ከሥፍራው ፡ ራቅ ፡ ስለኣላ ፡ በቅርብ ፡ ተቆጣጥሮ ፡ ሥልጣኑን ፡ ስለአልገለጠባቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በባላባታቸው ፡ እየተመሩ ፡ በነፃነት ፡ የቆዩ ፡ ይመስላል። መንግሥት ፡ ከነአኲቶ ፡ ለአብ ፡ ወደ ፡ ይኲኖ ፡ አምላክ ፡ ከላስታ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ በተዛወረ ፡ ጊዜ ፡ ሸዋ ፡ ላይፋት ፡ ቅርብ ፡ በመሆኑ ፡ ይፋትም ፡ የጥንት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ በመሆኑ ፡ ባለፈው ፡ በይኲኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ማርኮ ፡ ፖሎና ፡ ኣል ፡ ማክሪዚ ፡ እንዳሉት ፡ ይኲኖ ፡ ኣምላክ ፡ ይፋትንና ፡ ኣዳሎችን ፡ ለማስገበር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተዋግቷል። እነሱንም ፡ ለምን ፡ ወጋቸው ፡ በማለት ፡ የግብፁ ፡ ሱልጣን ፡ ቢባርስ ፡ የሚባለው ፡ ከይኲኖ ፡ አምላክ ፡ ዘንድ ፡ ጳጳስ ፡ ለማምጣት ፡ መላክተኛ ፡ ቢሄድ ፡ እምቢ ፡ ብሎ ፡ መልሷል።

ከአፄ ፡ ይኲኖ ፡ ኣምላክም ፡ ወዲህ ፡ እነዚሁ ፡ የይፋት ፡ እስላሞች ፡ አላቃታየ ፡ እንደ ፡ አሉት ፡ ከዓረብ ፡ አገር ፡ እስላሞች ፡ ጋር ፡ በጠብ ፡ ሳይተያዩ

፡ መሣሪያም ፡ ሽቀጥም ፡ እያገኙ ፡ እነርሱም ፡ ከይፋትና ፡ ከአዳል ፡ ወደ ፡ ዓረብ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ መካ ፡ መዲና ፡ ወደ ፡ ዘቢድ ፡ እየሄዱ ፡ ከነዚያም ፡ ወደዚህ ፡ እየመጡ ፡ የሃይማኖትና ፡ የዘር ፡ ኣንድነታቸውንናኣጥብቀው ፡ ነበር። በዚህም ፡ ዓይነት ፡ እየገነኑ ፡ ሄደው ፡ በዚሁ ፡ በዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ የዚሁ ፡ የወላስማ ፡ ተከታይ ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ ተነሥቶ ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ብርታት ፡ መውደቁን ፡ እንመለከታለን።

ስለዚህ ፡ የወላስማ ፡ ተከታዮች ፡ ሐቅ ፡ አድ ፡ ዲንና ፡ ሳብር ፡ አድዲን ፡ የነዚህም ፡ ተከታዮች ፡ ሁሉ ፡ በየጊዜው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ የተዋጉበትን ፡ በምናነብበት ፡ መካከል ፡ ስማቸውን ፡ በትክክል ፡ ለመረዳት ፡ የዘራቸውንም ፡ ግንኙነት ፡ ለመገንዘብ ፡ እንዲመቸን ፡ የወላስማን ፡ ዘርና ፡ የይኵኖ ፡ አምላክን ፡ ዘር ፡ የሚያሳይ ፡ ሁለት ፡ የዘር ፡ ሐረግ ፡ እነሆ ፡ ኣዘጋጅተናል። በዘሩ ፡ ሐረግ ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ሙሉውና ፡ እውነተኛው ፡ የወላስሞቹ ፡ ስም ፡ እንዳያሳስት ፡ ቀጥር ፡ እየሰጠን ፡ በሐረጉ ፡ ግርጌ ፡ ገልጠነዋል። ለምሳሌ ፡ የዘሩ ፡ ረግ ፡ ሐቅ ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ የሚለውን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ሐቅ ፡ ዲን ፡ የሚለውን ፡ ማለት ፡ ነው። በታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የገደለው ፡ ደራደር ፡ የሐቀ ፡ ዲን ፡ ወንድም ፡ መሆኑን ፡ መሬ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ ሲያረጋግጡ ፡ ቼሩሊ ፡ በራሱ ፡ ጸሑፍ ፡ ትቶታል። የዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሐቅ ፡ አድ ፡ ዲንና ፡ ደራደር ፡ በእናት ፡ እንጂ ፡ በአባት ፡ ኣይገናኙም ፡ ይሆናል ፡ ደግሞ ፡ ባንዳንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራደርን ፡ የሐቀ ፡ ዲን ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ያደርገዋል። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በሙሴ ፡ ኮረኔ ፡ ባሴት ፡ ጽሑፍ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ በኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በግዕዝኛው ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ ስለተገኘ ፡ ደራደርን ፡ እንደ ፡ ወላስማ ፡ ልጅ ፡ አድርጌ ፡ ጽፌዋለሁ።

የዘሩ ፡ ሐረግ ፡ የይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዘር ፡ የነገሥታቱ ፡ ፩ ፡ ቀጥር ፡ የወላስሞቹ ፡ ፪ ፡ ቍጥር ፡ ተብሎ ፡ ተመልክቷልና ፡ አንባቢ ፡ ታሪኮን ፡ በሚያነብበት ፡ ስማቸውን ፡ በጽሑፍ ፡ በሚያገኝበት ፡ ጊዜ ፡ የሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ ሥርወ ፡ ወመንግሥትና ፡ ቅርንጫፋቸውን ፡ ለመለየት ፡ ወደ ፡ ዘሩ ፡ ሐረግ ፡ ዓይኑን ፡ ይጣል።

# ምዕራፍ ፡ ፲

## የይፋትና ፡ የአዳል ፡ ባላባቶች ፡ በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ሸፍተው ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንደተዋጋቸው።

በኢትዮጵያ ፡ ሰፊው ፡ ግዛት ፡ በደቡብና ፡ በምሥራቅ ፡ የሚገኙ ፡ የአዳል ፡ የይፋትና ፡ የደዋሮ ፡ የባሌ ፡ የሐድያ ፡ ነገዶች ፡ ቀድሞ ፡ በየራሳቸው ፡ ባላባት ፡ እየተገዙ ፡ የራሳቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጣዖትና ፡ የመናፍስት ፡ አምልኮ ፡ ይዘው ፡ ይኖራሉ። የአክሱምና ፡ የላስታ ፡ መንግሥት ፡ በሩቅ ፡ ስላሚገኝ ፡ በቅርብ ፡ እየተቆጣጠረ ፡ ገዥነቱን ፡ ያጸናባቸው ፡ አይመስልም። ነገር ፡ ግን ፡ ግብር ፡ ከለከሉ ፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በዘመኑ ፡ የነበረው ፡ ንጉሥ ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደሩ ፡ ሰላም ፡ አግኝቶ ፡ ኃይል ፡ ሲሰማው ፡ በነዚሁ ፡ ሩቅ ፡ በሚገኙት ፡ ግዛቶቹ ፡ ጦር ፡ እየላከ ፡ ሲያሳምናቸው ፡ ይኖራል። የእስላሞች ፡ ኃይል ፡ በምሥራቧ ፡ በኵል ፡ በየመንና ፡ በዓረቢያ ፡ ሳውዲት ፡ በሰሜን ፡ በኵል ፡ በግብፅና ፡ በመካከል ፡ ምሥራቅ ፡ በገነነበት ፡ ዘመን ፡ ከነርሱ ፡ የመጣ ፡ የእስላም ፡ ቄስ ፡ እየሰበከ ፡ ባላባቶቹን ፡ ወደ ፡ እስልምና ፡ ስላመጣቸው ፡ በዚሁ ፡ በሃይማኖት ፡ ረገድ ፡ ተዛምደው ፡ ከእስላሞቹ ፡ በሚያገኙት ፡ እርዳታ ፡ የመጣባቸውን ፡ የንጉሥ ፡ ሠራዊት ፡ እየተዋጉ ፡ ፩ ፡ ኣንድ ፡ ጊዜም ፡ እያሸነፉ ፡ መመለሳቸው ፡ የተወቀ ፡ ነው። እነዋህም ፡ አገሮች ፡ በሸዋ ፡ ምሥራቅና ፡ ደቡብ ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕርና ፡ እስካ ፡ ሕንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ጠረፍ ፡ ድረስ ፡ የሚገኙ ፡ በዚያን ፡ ጊዜው ፡ ኣጠራር ፡ የይፋት ፡ የደዋሮ ፡ የባሌ ፡ የፈጠጋር ፡ የደንካሊ ፡ የኣጻል ፡ ባላባትና ፡ ነገዶች ፡ ናቸው። ከነዚሁ ፡ መካከል ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ የተጻፈው ፡ የይፋቱ ፡ የወላስማ ፡ ነገድ ፡ ራሱ ፡ የዓረብ ፡ ቅልቅል ፡ በመሆኑ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የበረታ ፡ ሆኖአል። ከዚያ ፡ በፊት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ መደቡ ፡ በሸዋ ፡ በተጕለት ፡ ከተዛወረ ፡ ወዲህ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የዘመኑ ፡ ሊቃውንት ፡ በጽሑፍ ፡ ባያስቀሩት ፡ ይዘኖ ፡ አምላክ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልገብር ፡ ያሉትን ፡ ይልቊንም ፡ ኣጻሎቹን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተዋግቷል። አገብአ ፡ ጽዮን ፡ ደግሞ ፡ ውጊያውንና ፡ ጠቡን ፡ ትቶ ፡ በሰላም ፡ ተስማምቶ ፡ ጊዜውን ፡ አሳልፋል። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ አገሮች ፡

አንድ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ መሸፈታቸውና ፡ መነጠላቸው ፡ ባይቀርም ፡ ሁሉም ፡ የኢትዮጵያ ፡ አውራጃዎች ፡ ስለሆኑ ፡ በየዘመኑ ፡ የነበሩ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሁሉ ፡ ካርታም ፡ ሲሠሩ ፡ ታሪኵንም ፡ ሲተርኩ ፡ እንደኢትዮጵያ ፡ ኣውራጃዎች ፡ እየቀጠሩ ፡ ነው። ከሃይማኖት ፡ ልዩነት ፡ በቀር ፡ በውነትም ፡ በመሬቱ ፡ አቀማመጥም ፡ በጥቅምም ፡ በታሪክም ፡ በዘርም ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ አገሮች ፡ በደቡብና ፡ በምሥራቅ ፡ ከሚገኘው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ ልዩነት ፡ የላቸውም።

አሁን ፡ ግን ፡ ከያግብኣ ፡ ጽዮን ፡ ወዲህ ፡ የተነሡት ፡ ልጆቹ ፡ እንዳባታቸው ፡ ኑዛዜ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የገዙት ፡ እነ ፡ ጽንፈ ፡ አርዕድ ፡ እነሕዝበ ፡ አሰግድ ፡ ...ደካሞች ፡ ስለሆኑ ፡ እነዚሁ ፡ የይፋትና ፡ የአዳል ፡ ባላባቶች ፡ እያደር ፡ ኃይል ፡ እያበጁ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ መገበራቸውንም ፡ አቋርጠው ፡ በነፃነት ፡ ይኖሩ ፡ ዠመር። ከሁሉም ፡ በበለጠ ፡ የይፋቱ ፡ ባላባት ፡ እየገነነ ፡ ሌሎቹንም ፡ ባላባቶች ፡ በውስጡ ፡ እያደረገ ፡ ባገሩና ፡ በግዛቱ ፡ በይፋት ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ እየተቆጠረ ፡ ይገዛ ፡ ዠመር። የርሱም ፡ ባላባት ፡ የይፋት ፡ ወላስማ ፡ የሚባለው ፡ በኋላ ፡ ወደሐረርጌ ፡ ከመዞሩ ፡ በፊት ፡ በዚያው ፡ በይፋት ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፡ አንባቢ ፡ በዘሩ ፡ ሐረግ ፡ ላይ ፡ እንደሚመለከተው ፡ ተከታትለው ፡ የገዙት ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ናቸው ፡ የመዠመሪያው ፡ ባላባት ፡ ኡመር ፡ ወላስማ ፡ አራት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡ እነሱም ፡ በዚዩIሐቅአድ ፡ ዲን ፡ ሁሳይንናስር ፡ አድ ፡ ዲን ፡ ደራደር ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው። ባዚዩ ፡ ማንሱርንና ፡ ጋማል ፡ አድ ፡ ዲንን ፡ ይወልዳል ፡ ማንሱር ፡ ጻልሁይን ፡ ይወልዳል ፡ ዳልሁይ ፡ ሳብር ፡ ኣድ ፡ ዲንን ፡ ይወልኣል ፡ እርሱም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጋር ፡ የተዋጋነው ፡ ዝርዝሩን ፡ ታሪክ ፡ በሚቀጥለው ፡ እንመለከታለን። ለሐቅ ፡ አዲን ፡ ደግሞ ፡ ደራደር ፡ የሚባል ፡ ወንድም ፡ እንደሌሎቹ (የወንድም ፡ ልጅ) ነበረው። እርሱም ፡ በመዠመሪያው ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ከኣፄ ፡ ዓምደጽዮን ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተውነው።

አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ አባቶቹዙፋን ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በተባለ ፡ ጊዜ ፡ እንደአባቱ ፡ እንደውድም ፡ ረዓድ ፡ እንደ ፡ ኣጐቱ ፡ እንደ ፡ አግብአ ፡ ጽዮን ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ ተስማምቶ ፡ መኖርንም ፡ አንገብርም

፡ ያሉትንም ፡ የይፋትና ፡ የአዳል ፡ ባላባቶችንም ፡ ችላ ፡ ብሉ ፡ በሰላም ፡ መተው ፡ አልሆነለትም። ራሱ ፡ ዠግንነት ፡ የተመላ ፡ ኃይለኛ ፡ ንጉሥ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ የገናናዎቹን ፡ ነገሥታት ፡ የነአብርሃን ፡ የነካሌብን ፡ የነላሊበላን ፡ የነይኵኖ ፡ አምላክን ፡ ዙፋን ፡ ወርሶ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥትነቱን ፡ ሥፍራ ፡ በመያዙ ፡ የነዚጋ ፡ አውራጆች ፡ በነፃነት ፡ ተነጥሎ ፡ መኖር ፡ ለልቡ ፡ ሰላም ፡ ሊሰጠው ፡ አላቻለም። እንኳን ፡ አጠገቡ ፡ ያሉትን ፡ የራሱ ፡ ተገዥ ፡ የሆኑትን ፡ የይፋትና ፡ የአዳል ፡ ባላባቶች ፡ በሩቅ ፡ አገር ፡ በግብፅ ፡ ያሉት ፡ የእስላም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ኣጠቋቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸውንም ፡ አፈረሱት ፡ የሚሉ ፡ ወሬ ፡ ሲሰማ ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ማጥቃት ፡ ያልተዋችሁ ፡ ያፈረሳችሁትንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልሳችሁ ፡ ያልሠራችሁት ፡ እንደሆነ ፡ እኔም ፡ የናንተን ፡ መስጊድ ፡ አመድ ፡ ነው ፡ የማደርገው ፡ የዐባይንም ፡ ወሀ ፡ አስገድቤ ፡ ወደግብፅ ፡ እንዳይወርድ ፡ ኣደርገዋለሁ» ፡ እያለ ፡ በደብዳቤ ፡ ያስፈራራቸው ፡ ነበር።

ስለዚህ ፡ በዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ በእስላሞቹና ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ መካከል ፡ የግዛቱም ፡ የሃይማኖቱም ፡ ጠብ ፡ እየከረረ ፡ ሄደ ፤ እነዚህም ፡ ባላባቶች ፡ የግብፅንና ፡ የዐረብን ፡ ነገር ፡ ድጋፍ ፡ በማግኘታቸው ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ላይ ፡ እምቢታቸውንና ፡ ጠባቸውን ፡ ኣበረከቱ። ከንጉሡም ፡ ዘንድ ፡ ወደግብፅም ፡ ወደኢየሩሳሌምም ፡ እየተላኩ ፡ የሚሄዱትን ፡ ሲያገኙ ፡ እየያዙ ፡ ያጉላሉዋቸው ፡ ዠመር። ፩ኛው ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ መላክተኛ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ በዘይላ ፡ በኵል ፡ አድርጎ ፡ ለማለፍ ፡ ሲሞክር ፡ የአዳሉ ፡ ባላባት ፡ ይዞ ፡ ኣቆይቶ ፡ በኋላም ፡ አሥሮ ፡ ላይፋቱ ፡ ባላባት ፡ ለሐቅ ፡ አድዲን ፡ ላከለት ፤ እርሱም ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ ለማናደድ ፡ እየሰደበም ፡ እያንገላታም ፡ በብዙ ፡ ሥቃይ ፡ ሲያሰቃየው ፡ ቆይቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ሰለቡት ፡ ይባላል። ምናልባት ፡ ይህ ፡ መልክተኛ ፡ "ትእይንተይ" ብሎ ፡ የዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የግዕዙ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ የሚጠራው ፡ ይሆናል።

የዚህን ፡ ሁሉ ፡ ወሬ ፡ ሲሰማ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ተናደደ። ስለዚህ ፡ በያገሩ ፡ ያለው ፡ ዋናው ፡ ጦር ፡ ሳይሰበሰብ ፡ ለጊዜው ፡ ያገኘውን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ በ፲፫፻፳፪ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ ከተጉለት ፡ ወደይፋት ፡ ጉዞ ፡ ዠመረ። በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ ጦሩን ፡ በያለበት ፡ ልኮ ፡ ከአጋጠማቸው ፡ ጦር ፡ ጋር ፡

እየተዋጉ ፡ ዘረፋም ፡ ቃጠሎም ፡ ዝመሩ ፡ ፤ በመጨረሻም ፡ የአዳልና ፡ የይፋት ፡ ጦር ፡ ባንድነት ፡ በባላባቱ ፡ በሐቅ ፡ አድ ፡ ዲንና ፡ በወንድሙ ፡ ልጅ (እንደሌሎቹ ፡ ወንድሙ) በደራደር ፡ እየተመራ ፡ ተሰብስቦ ፡ በንጉሡ ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ ሌሊት ፡ ሊነጋ ፡ አቅራቢያ ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ ለመፍጀት ፡ ገሥግሦ ፡ በንጉሡ ፡ ሠፈር ፡ ደረሰ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ያለበት ፡ እንኳን ፡ የንጉሥ ፡ ሠፈርና ፡ ያንድ ፡ ከፍል ፡ ጦርም ፡ ቢሆን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ በሚያስፈራ ፡ የጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ያለሰላይና ፡ ያለቃፊር ፡ አይተኛምና ፡ የእስላሞቹ ፡ መምጣት ፡ በንጉሡ ፡ ሠፈር ፡ ሲሰማሁሉም ፡ ለጦርነት ፡ ተቀስቅሶ ፡ ተሰልፎ ፡ ጠብቆ ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር። ንጉሡ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንም ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ ሲያዋጋ ፡ ደራደር ፡ የሚባለው ፡ የነዚያ ፡ የጦር ፡ አላቃ ፡ ተዋጊዎቹን ፡ እስላሞቹን ፡ ለማነቃቃት ፡ እየመራ ፡ እፊት ፡ ቀድሞ ፡ ሲያዋጋ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በሩቅ ፡ ዓይቶ ፡ ጦሩን ፡ ሰብቆ ፡ ወረወረና ፡ ጣለውወዲያው ፡ ደራደር ፡ ወድቆ ፡ ሊሞት ፡ ሲያቃስት ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ ሠራዊት ፡ ሲመለከት ፡ በፈረሱ ፡ አጐዳ ፡ እየረጋገጠ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ሄደበት ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጦሩም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እየሮጠ ፡ እነዚያን ፡ እያባረረ ፡ ይፈጅ ፡ ዠመር። የቀረውም ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ እየሸሸ ፡ ሲያመልጥ ፡ የቀረው ፡ በግድም ፡ በውድም ፡ ምሕረት ፡ እየለመነ ፡ እጁን ፡ ሰጠ። ዋናው ፡ መሪና ፡ ባላባት ፡ ሐቅ ፡ አድዲንም ፡ ተማረከና ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጣ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግድያውና ፡ ዘረፋው ፡ ቆሞ ፡ መልስ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ሐቅ ፡ አድዲን ፡ ታሠረ! በእርሱም ፡ እግር ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ለይፋትና ፡ ለፈጠጋር ፡ ግዛት ፡ የወንድሙን ፡ ልጅ ፡ ሰበን ፡ ኢድ ፡ የሚባለውን ፡ ሾመው። ይኸውም ፡ ሰበን ፡ ኢድን ፡ ምናልባትወገኖቹ ፡ ሸፍተው ፡ በሚዋጉበት ፡ 5ዓት ፡ እርሱ ፡ ለንጉሡ ፡ ታማኝነቱን ፡ ሳይተው ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ የነበረ ፡ ስለሆነ ፡ የይፋትና ፡ የፈጠጋር ፡ ሕዝብም ፡ ገዢያቸው ፡ ከዚያው ፡ ከባላባታቸው ፡ ከዑመር ፡ ወላስማ ፡ ውስጥ ፡ አለመውጣቱን ፡ ተመልክተው ፡ ለወደፊቱ ፡ በሰላም ፡ እንዲገዙ ፡ የታሰበ ፡ በመሐሪነት ፡ የተሸፈነ ፡ የፖለቲካ ፡ ዘዴ ፡ ሳይሆን ፡ ኣይቀርም። ንጉሡም ፡ እንደዚህ ፡ ኣድርጎ ፡ የሸፈተውን ፡ ኣገር ፡ በጦር ፡ አሳምኖ ፡ ሰበን ፡ ኢድንበሹሙቱ ፡ አደላድሎ ፡ ሲጨርስ ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ወደ ፡ ቲጉለት ፡ ተመለሰ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተጻፈው ፡ የደራደርና ፡ ያዬ ፡ ዓደ ፡ ጽዮን ፡ የመዠመሪያው ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ ከጀምስ ፡ ብሩስ፣ከረኔ ፡ ባሴት፣ ፡ ከኰልቦ ፡ ከሌሎቹም ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወደፊት ፡ በምናገኘው ፡ ባሄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የጦርነት ፡ ታሪከ ፡ በግዕዝኛ ፡ እተጻፈው ፡ ውስጥ ፡ የለም። ምናልባት ፡ እኔ ፡ ያላገኘሁት ፡ የዚሁ ፡ ታሪክ ፡ ለብቻው ፡ በግዕዝ ፡ እንዳለ ፡ አላረጋግጥም።

# ምዕራፍ ፡ ፲፩።

## አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከይፋትና ፡ ከአዳል ፡ ባላባቶች ፡ ጋር ፡ ያደረገውን ፡ ጦርነት ፡ የሚተርከው ፡ ጽሑፍ።

የመዠመሪያው ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ የነበረው ፡ ሐቅ ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ ከተማረከ ፡ ወዲህ ፡ ፍጻሜው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ በታሪክ ፡ ኣላገኘሁም።

በወህኒ ፡ ቤት ፡ እንዳለ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ሞቶ ፡ ይሁንአይታወቅም። ባሁን ፡ ሰዓት ፡ ደግሞ ፡ ሌሎቹን ፡ ባላባቶች ፡ ሁሉ ፡ በበታቹ ፡ ሰብስቦ ፡ ያለፈውን ፡ ብድራት ፡ ለመመለስ ፡ የተነሣው ፡ ሳብር ፡ አድ ፡ ዲንመሐመድ ፡ የሚባለው ፡ ነው። ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በግዕዝ ፡ የተጻፈውዜናመዋዕል ፡ ግን ፡ ባጭሩ ፡ «ንጉሠ ፡ ዕልዋን ፡ ዘስሙ ፡ ሰብረዲን ፡ ንይለዋል። ወደፊት ፡ የምናነበውን ፡ የጦርነት ፡ ሁኔታ ፡ በሰፊው ፡ የሚልገልጽልን ፡ ይኸው ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ነው ፤ እርሱንም ፡ ቀድሞ ፡ ዳልሜይዳ ፡ የሚባለው ፡ የፖርቱጋል ፡ ቄስ ፡ ወደቋንቋው ፡ ተርጕሞ ፡ በታሪኩ ፡ ጽፎት ፡ ሳላ ፡ የእጁን ፡ ጽሑፍ ፡ ከሎንዶን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ አግኝተው ፡ ሙሴ ፡ ዝል ፡ ፔሩሾ (Jules ፡ Perruchon) የሚባሉት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጽሑፍ ፡ ምርመራ ፡ የደከሙት ፡ የፈረንሳዊ ፡ ሊቅ ፡ ወደፈረንሳዊ ፡ ቋንቋ ፡ ተርጕመው ፡ ከግዕዙ ፡ ጋር ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ አድርገው ፡ በ፩፻፰፻፺፩ ፡ ዓ.ም ፡ አሳትመው ፡ አራብተውታል። ይህ ፡ የጦርነት ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ብዙ ፡ ሰዎችና ፡ ራሳቸው ፡ ሙሴ ፡ ፔሩሾ ፡ በዚያው ፡ በዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ የተጻፈ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለማመን ፡ ሞክረው ፡

ነበር። ነገርግን ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ግድም (ገጽ ፡ ፱፻፲፰) ሚካኤል ፡ ወሀቦ ፡ ሰይፈ ፡ ለቴዎድሮስ ፡ ወገብርኤል ፡ ላገላውዴዎስ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ስላለበት ፡ ከዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ወዲህ ፡ የነገሡትን ፡ ነገሥታትቴዎድሮስ ፡ ፩ኛንና ፡ ኣፄ ፡ ገላውዴዎስን ፡ ማንሣቱ ፡ ነውና ፡ የተጻፈው ፡ ሙሴ ፡ ፔሩሽም ፡ እንዳሰቡት ፡ በኋለኛው ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ያሰኛል። ይኸውም ፡ ቃሉ ፡ ቴዎድሮስና ፡ ገላውዴዎስ ፡ ለሚባሉ ፡ ለሰማዕታት ፡ ወይም ፡ ስማቸው ፡ በገድልና ፡ በድርሳን ፡ ለሚገኝ ፡ ለሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሳይሆን ፡ በእርግጥ ፡ ለነዚሁ ፡ ለነገሥታቱ ፡ መሆኑ ፡ ተጣርቶ ፡ የታወቀ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ ጻሩ ፡ ግን ፡ ቃሉ ፡ በአጭር ፡ ስለሚያልቅ ፡ ለማጣራት ፡ መንገድ ፡ አይሰጥም። ደግሞ ፡ ኣፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ከፓርቱጊዞች ፡ ጋር ፡ ግራኝን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ ያጠፉ ፡ ስለሆኑገብርኤል ፡ ወሀቦ ፡ ሰይፈ ፡ ለገላውዴዎስ ፡ ቢል ፡ መንገድ ፡ አለው። ቴዎድሮስ ፡ የሚባሉት ፡ ሺ፫፻፳፫–፲፪ ፡ ላይ ፡ የነገሡት ፡ ንጉሥ ፡ ግን ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ ያደረጉት ፡ ጦርነት ፡ በታሪኩ ፡ ውስጥ ፡ ስለሌለ ፡ ሚካኤል ፡ ሰይፍ ፡ ሰጣቸው ፡ የተባለው ፡ ለርሳቸው ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ይሁን ፡ አልተረጋገጠምና ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ይህ ፡ ወደፊት ፡ የምናነበው ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በትክክል ፡ የተጻፈበት ፡ ጊዜ ፡ አይታወቅም።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ ዠግንነት ፡ የየለቱን ፡ ድል ፡ ኣድራጊነቱን ፡ ኣሳምሮ ፡ ይገልጻል። ጸሐፊው ፡ ጽሑፉን ፡ ለማሳመርከብሉይ ፡ ከሐዲስ ፡ ጥቅስ ፡ እያመጣ ፡ እየጨመረ ፡ በደንብ ፡ አሳክቶታል። ለአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ደገኛውን ፡ የምስጋና ፡ ቅጽል ፡ እየሰጠ ፡ ለሰብር ፡ አድ ፡ ዲን ፡ ለይፋቱ ፡ ባላባት ፡ «ንጉሠ ፡ ዕልዋን ፡ ዕቡይ ፡ ወመምዕላይ ፡ ርጉም ፡ ወዐማፂ ፡ ወልዱ ፡ ላሰይጣን ፡ ፀራ ፡ ለጽድቅ" ፡ እያለ ፡ ይሰድበዋል። ጦርነቱ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜና ፡ በየጦሩ ፡ ግምባር ፡ ሁሉ ፡ ዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ አሸናፊ ፡ እነዚያን ፡ ተሸናፊ ፡ እነዚህን ፡ ኣባራሪ ፡ እነዚያን ፡ በራሪ ፡ ከማድረግ ፡ በቀር ፡ የነዚህንና ፡ የነዚያን ፡ የጦርነት ፡ ሁኔታ ፡ የዠግንነታቸውንም ፡ ዓይነት ፡ በፍርድ ፡ መንገድ ፡ እየለየ ፡ ያለድልወት ፡ ሊጽፈው ፡ አልቻለም። በትም ፡ አገር ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ይልቊንም ፡ በዚያን

፡ ዘመን ፡ ጸሐፊ ፡ ሁሉ ፡ የጦርነትን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ሲጽፍ ፡ ላለበት ፡ ወገን ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ እያደላ ፡ መጻፍ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው።

በዚህም ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ የኛ ፡ ጸሐፍተ ፡ ትእዛዞች ፡ ወይም ፡ አዛዦች ፡ የነገሥታቶቻቸውን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ የዓምደ ፡ ጽዮንንም ፡ የልብነ ፡ ድንግልንም ፡ የሌሎቹንም ፡ በግዕዝ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሲጽፉ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ወገን ፡ የሚጻፈውን ፡ ብንመለከት ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተገለባብጦ ፡ እናገኘዋለን። የወላስሞቹን ፡ ታሪክ ፡ እነአል ፡ ማክሪዚ ፡ እነአል ፡ ታግሬቢርዲ ፡ በኋላም ፡ እነአራብ ፡ ፋቂህ ፡ የጻፉትን ፡ እነሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ እነቼሩሊ ፡ እነባሴት ፡ ወደፈረንሳዊና ፡ ወደኢጣልያን ፡ የተረጐሙትን ፡ ብንመለከት ፡ ዠግንነትም ፡ ሃይማኖትም ፡ የሌላቸው ፡ እነዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ናቸው ፡ በዐራብ ፡ ፋቂህ ፡ ጽሑፍም ፡ ውስጥ ፡ የግራኝን ፡ ታሪክ ፡ ወደፊት ፡ ስናነብ፤ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ እየተመሰገነ ፡ አፄ ፡ ልብነድንግል ፡ ሲሰደቡ ፡ እንመለከታለን። ስላዚህ ፡ አሁን ፡ በአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንና ፡ በሰብር ፡ አድ ፡ ዲን ፡ መካከል ፡ የሚደረገውን ፡ ጦርነት ፡ ከዚሁ ፡ ከግዕዙ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ እየወሰድን ፡ ስንመለከት ፡ ኣስቀድመን ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ የድልወት ፡ አጻጻፍ ፡ እንደማይጠፋ ፡ ያሰብን ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉንም ፡ በሕሊናችን ፡ ለማመዛዘን ፡ ይረዳናል። መቼም ፡ አፄ ፡ ዓምደጽዮን ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሆኑ ፡ ሳብር ፡ አድዲን ፡ በኽዮግራፊም ፡ በታሪክም ፡ የኢትዮጵያ ፡ አውራጃ ፡ በሆነው ፡ በይፋት ፡ በደዋሮ ፡ ላይ ፡ ባላባትና ፡ ገዥ ፡ የነበረ ፡ መሆኑ ፡ አይሳትም።

እርሱ ፡ እንደ ፡ ሽፍታ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንደደምሳሽ ፡ እርሱ ፡ ልለይ ፡ ባይ ፡ አልገብርም ፡ ባይ ፡ ዓምደጽዮን ፡ ከታላቂቱ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አትለይምናላባቶቼ ፡ የምትገብረውንም ፡ ግብር ፡ መቀጠል ፡ አለብህ ፡ ባይ ፡ ናቸውና ፡ እነዚህን ፡ በመሰሉ ፡ መካከል ፡ ጦርነት ፡ ሲደረግና ፡ የጦርነቱን ፡ ታሪክ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ባዕድ ፡ እንኳን ፡ ሲጽፈው ፡ የታላቀኙን ፡ ማጋነን ፡ የታናሹን ፡ ማቃለል ፡ የተለመደ ፡ ስለሆነ ፡ አሁንም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በይፋትና ፡ በአዳሎች ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ጦርነት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎችም ፡ እያጋነኑ ፡ ጽፈውለታል።

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የላስቶቹም ፡ ነገሥታት ፡ ከመራቃቸው ፡ ይልቊንም ፡ ከአግብኦ ፡ ጽዮን ፡ ወዲህ ፡ ያሉት ፡ ነገሥታት ፡ ደካሞች ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ የይፋቱ ፡ ባላባት ፡ ወላስማ ፡ ኡመር ፡ በግብፅና ፡ ይልቊንም ፡ በዐረብ ፡ አገር ፡ ሡልጣኖች ፡ እየተረዳ ፡ ኃይል ፡ አበጅቶ ፡ እንደ ፡ ነፃ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ እርሱና ፡ ተከታዮቹ ፡ የኛ ፡ ዘር ፡ ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዘር ፡ አያንስም ፡ እያሉ ፡ ራሳቸውን ፡ እንደ ፡ ሥታት ፡ ቆጥረው ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ነገሥታት ፡ ከነዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ፉክክር ፡ ዠምረው ፡ ነበር ፤ አሁንም ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ሳይቀር ፡ እንደ ፡ ሚገልጸው ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በይፋት ፡ ወላስማ ፡ ላይ ፡ ነግሻለሁ ፡ ብሎ ፡ የተነሣው ፡ ሳብር ፡ አድ ፡ ዲን ፡ በቀላሉ ፡ ከአፄዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ለመሸፈትና ፡ ነፃ ፡ ለመሆን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከዚህም ፡ አልፎ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ ጥሎ ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመንገሥ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ተነሣ። ከርሱም ፡ ጋር ፡ የደዋሮው ፡ የአዳሉ ፡ የሓድያው ፡ ባላባቶች ፡ ሌሎችም ፡ የደራ ፡ የሞራ ፡ የሻርቃላ ፡ የእስቲ ፡ የበስላ ፡ የሀገራ ፡ የፈድሴ ፡

.....ባላባቶች ፡ የሚባሉት ፡ ሁሉ ፡ አብረውለት ፡ ነበር። የነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ያብዛኞቹን ፡ ግዛታቸውን ፡ ዛሬ ፡ እየለዩ ፡ ለአንባቢ ፡ ለማስረዳት ፡ ችግር ፡ ነው። አገሩን ፡ ሁሉ ፡ በእግር ፡ እያደረሱ ፡ ሽማግሌዎቹን ፡ እየጠየቊ ፡ ስሙንና ፡ ስፍራውን ፡ እያጣሩ ፡ ማጋጠም ፡ ያስፈልጋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በጠቅላላው ፡ ሁሉም ፡ የሚገኙት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ ከሸዋ ፡ በምሥራቅና ፡ በደቡብ ፡ እስከ ፡ አደን ፡ እስከ ፡ ሕንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ የሚገኙ ፡ በዛሬው ፡ ደንከል ፡ በኣውሳ ፡ በአዳል ፡ በውጋዴን ፡ በሱማሌ ፡ በባሌና ፡ በአሩሲም ፡ በሲዳሞና ፡ በቦረና ፡ በኵል ፡ የሚገኙ ፡ ነገዶች ፡ ናቸው። ባሊ ፡ ደዋሮ ፡ ይፋት ፡ ፈጠጋር ፡ ደንካሊን ፡ ከዥዎግራፊው ፡ ላይ ፡ ለይቶ ፡ መመልከት ፡ ይቻላል። ስለዚህ ፡ ኣሁን ፡ ሁሉንም ፡ ትተን ፡ የጦርነቱን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በሚቀጥሉት ፡ ምዕራፎች ፡ እንመልከት። ሁሉ ፡ ሰው ፡ ሊያነበው ፡ እንደሚችል ፡ ከግዕዝ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ተርጒሜዋለሁ። ኣንዳንድ ፡ ቦታ ፡ የተሠወረ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ የተሳሳተ ፡ መሆኑን ፡ የምረዳውን ፡ ስሕተት ፡ የሆነውን ፡ ቃል ፡ በጐኑ ፡ መጻፌ ፡ ሳይቀር ፡ እዚያው ፡ አጠገቡ ፡ በቅንፍ ፡ ውስጥ ፡ እርሙኝ ፡ ቃል ፡ ጨምሬዋለሁ። ትርፍና ፡ የማይጠቅም ፡ ቃል ፡ የሆነውን ፡ መተዌን ፡ ለማስረዳት ፡ ...ብዙ ፡ የመሰለ ፡ ጠቃጠ ፡ ወይም ፡ የነቊጣ ፡ ምልክት ፡

አድርጌያለሁ። የሹማምንቱ ፡ ስም ፡ በግዕዝኛ ፡ ስለሆነ ፡ ሲተረጐም ፡ እንዳይጠፋ ፡ በማለት ፡ እንደዚሁም ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ግዕዝኛው ፡ ቃል ፡ ከአማርኛው ፡ ይበልጥ ፡ ለሚያውቁት ፡ ሰዎች ፡ ሊያብራራላቸው ፡ ስለሚችል ፡ አልፎአልፎ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ የግዕዝኛው ፡ ቃል ፡ በቅንፍ ፡ ታጥሮ ፡ በዚያው ፡ ባማርኛው ፡ ጐን ፡ ይገኛል።

# ምዕራፍ ፡ ፲፪

## ዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከሰብር ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ ጦርነት።

ዜና ፡ መዋዕሉን ፡ ጸሐፊው ፡ "ንጽሕፍ ፡ በረድኤተ ፡ እግዚእነ ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ኃይላ ፡ ወመዊዓ ፡ ዘገብረ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ በእደዊሁ ፡ ለዓም ፡ ጽዮን ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ገብረመስቀል" …ብሎ ፡ ይዠምርና ፡ ከግዕዝ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ እንደ ፡ መለስሁት ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ደንበኛው ፡ ታሪክ ፡ ይቀጥላል።

<<ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በነገሠ ፡ በ፳ኛው ፡ ዓመት ፡ ሰብረዚን ( ፡ ሰብር ፡ አድ ፡ ዲን) ኢትዮጵያን ፡ እገዛለሁ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ አፍርሼ ፡ መስጊድ ፡ አቆማለሁ ፡ ክርስቲያኑንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እስልምና ፡ መልሼ ፡ በቍራን ፡ ሕግ ፡ ኣስተዳድረዋለሁ ፡ ብሉ ፡ ተነሣና ፡ ወደክርስቲያኖቹ ፡ ሄዶ ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ መግደል ፡ የተረፉትንም ፡ ወንዱንም ፡ ሴቱንም ፡ መማረክ ፡ ዠመረ። ከዚያም ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ የጽዮን (የኢትዮጵያ) ነገሥታት ፡ እንደሚያደርጉት ፡ በዳሞት ፤ በሐጌ ፤ በፈጠጋር ፤ በተጕለት ፤ በጐዣም ፤ በአምሐራ ፡ ….ኣገር ፡ ሁሉ ፡ መሳፍንት ፤ መኳንንት ፡ እየደለደለ ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ ያደርግ ፡ ዠመር። የዚህን ፡ ወሬ ፡ ንጉሡ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ተናደደ ፤ እንደዚህም ፡ ሲል ፡ ላከበት! ፡ «ይህ ፡ የምሰማው ፡ እውነት ፡ ነውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ እያቃጠልህ ፡ ክርስቲያኑን ፡ መግደልህና ፡ መማረክህስ ፡ እውነት ፡ ነውን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ወንድምህ ፡ ሐቀዲን ፡ ትዕይንተይ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ታናሽ ፡

አገልጋይ ፡ ማርኮ ፡ ቢወስድ ፡ ያደረግሁትን ፡ .....የወንድምህን ፡ ልጅ ፡ ደራደርን ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ መግደሌን ፡ አታውቅምን ፡ ....አሁንም ፡ ፲ ክርስቲያን ፡ ገድለህ ፡ እንደሆነ ፡ እኔ ፡ ያንተን ፡ ሺ ፡ ፪ ፡ ገድለህ ፡ እንደሆነ ፡ እኔ ፡ ያንተን ፡ ፲ ሺ ፡ እገድልብሃለሁ....”

ሰብረዲን ፡ ከመላከተኛው ፡ ይኸን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ወደ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ላከ ፡ “አንተ ፡ ዘንድ ፡ መጥቼ ፡ እፊትህ ፡ አልቆምም። አንተ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ ብትመጣ ፡ ግን ፡ አልፈራህም። በጦር ፡ በጐራዴ ፡ በሰይፍ ፡ በቀስት ፡ የሚዋጋ ፡ ካንተ ፡ የሚበልጥ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አለኝ። ስለዚህ ፡ መንገዱ ፡ ክፍት ፡ ነውና ፡ ናና ፡ ጦርነት ፡ እንግጠም። አንተ ፡ ያልመጣህ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ እመጣለሁ፥ ፡ ሰብረዲን ፡ ይኸን ፡ ቃል ፡ ከመለሰ ፡ ወዲህ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱንና ፡ ሹማምንቱን ፡ እያደላደለ ፡ ለጦርነት ፡ ያዘጋጅ ፡ ዠመረ... ፡ ከዚያም ፡ በውስጡ ፡ የሚገኙትን ፡ ጠንቋዮችና ፡ አዋቂዎች ፡ ሰበሰበና ፡ ሄደን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ እንዋጋ ፡ ወይስ ፡ እንቅር ፡ እስኪ ፡ ንገሩኝ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አመኖ ፡ የሚባለውን ፡ የሐድያን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ጽዮን (ዓምደ ፡ ጽዮን) አትሂድ ፡ ገጸ ፡ በረከትም ፡ ኣታቅርብለት ፡ እሱ ፡ መጥቶ ፡ የተዋጋህ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ በእጅህ ፡ ይወድቅና ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ትጨርሰዋለህ” ብሎ ፡ መክሮት ፡ በዚሁ ፡ እንደ ፡ ሶምሶን ፡ ኃይለኛ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ተጋዳይ (ኃያል ፡ ከመ ፡ ሶምሶን ፡ ወመስተቃትል ፡ ከመ ፡ ዳዊት) የሆነው ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ተቆጥቶ ፡ ሐድያ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ንጉሡንም ፡ ሠራዊቱንም ፡ አጥፍቶ ፡ እንደነበረው ፡ አሁንም ፡ ይኸው ፡ ኣሳሳች ፡ ጠንቋይ ፡ ለሰብረዲን ፡ ‹ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ መንግሥታቸው ፡ ኣልቆ ፡ ለኛ ፡ ተሰጥቷል። ስለዚህ ፡ ውጣና ፡ ከክርስቲያኑ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ተዋጋ ፡ ታሸንፈዋለህ ፡ ከነሕዝቡም ፡ ትገዛዋለህ ፡ አንተም ፡ በጽዮን (ኢትዮጵያ) ትነግሣለህ› ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፤ የቀሩትም ፡ ጠንቋዮች ፡ ይኸንኑ ፡ ቃል ፡ አጸደቀ።

ስለዚህ ፡ ሰብረዲን ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ እሦስት ፡ ላይ ፡ ከፍሎ ፡ ፩ዱን ፡ ወደ ፡ ኣማራ ፡ ፩ዱን ፡ ወደ ፡ ኣንጐት ፡ ልኮ ፡ ራሱ ፡ ግን ፡ ንጉሥ ፡ ዓምደ ፡

ጽዮን ፡ ወደሚገኝበት ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ አመራ። ይኸን ፡ ሁሉ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሸዋ ፡ ረዓድ ፤ የንዝአ ፡ አይገባ ፡ አንጐትይ ፡ ወትእይንተይ ፡ ሐግተ ፡ ጐነይ ፡ አምላክ ፡ ጽናሕ ፡ አውራ ፡ መንዝል ፡ ሊቀ ፡ አፍራስ ፡ ዘየማን ፡ የአክል ፡ ጋዳ (ድግና?) ሊቀ ፡ አፍራስ ፡ ዘፀጋም ፡ ውድሞዓላ ፡ የሚባሉትን ፡ የጦር ፡ ሹማምንቱን (ሊቃውንተ ፡ ሐራሁ) ለጦርነት ፡ ተዘጋጁ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው። ከዚያ ፡ ከግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ወርቁንና ፡ ብሩን ፡ ሽልማቱን ፡ ሁሉ ፡ አስወጥቶ ፡ ሁሉንም ፡ ከታናሽ ፡ እስካ ፡ ታላቁ ፡ በሽልማትም ፡ በስጦታም ፡ አስደሰታቸው። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በ፳፱ ፡ የካቲት ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ድልን ፡ ሰጥቶ ፡ ይርዳችሁ ፡ ብሎ ፡ አሰናብቶ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ( ፡ ላካቸው ፡ " ፡ እነሱም ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ በደስታ ፡ ሄደው ፡ ተኰላ ፡ የሚባሉት ፡ ትንሽ ፡ የጦር ፡ ክፍሎች (ጎዳጣን ፡ እምነሠራዊት ፡ ለ ፡ ይብልዎሙ ፡ ተኰላ) ወደ ፡ ሰብረዲን ፡ አገር ፡ ደረሱ። መንገዱ ፡ ጠማማና ፡ መጥፎ ፡ ስለነበረ ፡ ከትንሾቹ ፡ ከግንባር ፡ ቀደሞቹ ፡ በቀር ፡ የቀረው ፡ ዋናው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ባንድነት ፡ አልደረሰም። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚያው ፡ ትንሾቹ ፡ ወደሰብረዲን ፡ መኖሪያ ፡ ከተማ ፡ ደርሰው ፡ ውጊያውን ፡ ዠምረው ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ አሸነፉት ፡ "በኋላም ፡ ዋናው ፡ ጦርመጥቶ ፡ ፀሐይ ፡ እስኪጠልቅ ፡ ድረስ ፡ ወታደሮች ፡ እየተካታተሉ ፡ ሲዋጉት ፡ በመጨረሻ ፡ ሰብረዲን ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ አምልጧቸው ፡ ሸሸ።

ከተማዉንም ፡ አፈራርሰው ፡ ሰዉንም ፡ ሁሉ ፡ ገደሉበት ፡ ከቤተመንግሥቱም ፡ ብዙ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ በያይነቱ ፡ የከበረ ፡ ደንጊያና ፡ ልብስ ፡ ሁሉ ፡ ዘርፈው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወደ ፡ ንጉሣቸው ፡ እንደዚህ ፡ ብለው ፡ የደስታ ፡ ቃል ፡ ላኩ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ደስ ፡ ይበልህ ፡ በመንግሥትህና ፡ በሠራዊትህ ፡ ላይ ፡ የተሣነውን ፡ ጠላትህን ፡ አሸነፍነው። ከሸሸው፣ ፡ በቀር ፡ የቀረውን ፡ ግማሹንም ፡ ገደልነው ፡ የተረፈውንም ፡ ዕቁባቱንና ፡ ሴቱን ፡ ምንም ፡ ሳናስተርፍ ፡ ማረክናቸው። በቤቱ ፡ የተገኘውን ፡ የከበረ ፡ ደንጊያ (ዕንቀና ፡ አልማዝ) ወርቅና ፡ ብር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጌጥና ፡ የሽልማት ፡ ልብስ ፡ ብዙ ፡ የጦርመሣሪያ ፡ ሰንናብርት ፡ ሌላም ፡ መቁጠር ፡ የማይቻል ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፤ ዘርፈን ፡ መሸከም ፡ እስከሚችሉ ፡ ድረስ ፡ ላሽጐራ (ሽጉራ) ለዘብርአ ፡ ለጊጋ ፡

አገር (ምድረ ፡ ዝጋ) ፡ ሰጠናቸው። እርሱ ፡ ግን ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ አምልጦን ፡ ሸሸ። »

ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የሰብረዲንን ፡ ማምለጥ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ታቦቱ ፡ ወዳለበት ፡ ድንኳን (ደብተራ ፡ መርጡል ፡ ኀበ ፡ ታቦት) ገብቶ ፡ የመሠዊያውን ፡ መንበር ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ **ክርስቶስ** ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ጸላየ። የልቤን ፡ ልመና ፡ ስማኝ ፡ ባንደበቴ ፡ የምለምንህንም ፡ አትከልክለኝ ፡ በኃጢአቴ ፡ ምክንያት ፡ የምሕረትህን ፡ በር ፡ አትዝጋብኝ።

ነገር ፡ ግን ፡ በስምህና ፡ በበጐችህ (በክርስቲያኖቼ) ፡ ላይ ፡ የተነሣውን ፡ ይኸን ፡ ጠላቴን ፡ እወጋው ፡ ዘንድ ፡ መንገድ ፡ የሚመራኝን ፡ ደጉን ፡ መልአክህን ፡ ላክልኝ። ይኸን ፡ ጸልዮ ፡ ሲጨርስ ፡ የታቦት ፡ ልብስ ፡ ስለቱን ፡ ለቤተ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ሰጠና ፡ ወደውጭ ፡ ወጣ። ከዚያ ፡ ዳሞት ፡ ሰቀልት ፤ ጎንደር ፤ ሐድያ ፡ የሚባሉትን ፡ የፈረሰኛና ፡ የእግረኛ ፡ ወታደሮች ፡ በጠብና ፡ በውጊያ ፡ ጊዜ ፡ ለዝግንነታቸው ፡ ምሳሌ ፡ የሌላቸውን ፡ ኣለቃቸውን ፡ ጺጋ ፡ **ክርስቶስን** ፡ መሪ ፡ አድርጎ ፡ ወደቤገምድር ፡ ሄደው ፡ ከሰሜን ፡ ከወገራ ፤ ከጸለምት ፤ ከጸገዴ ፤ ሰዎች ፡ ጋር ፡ እንዲዋጉ ፡ ላካቸው። እነዚህ ፡ አገሮች ፡ ቀድሞ ፡ ክርስቲያን ፡ የነበሩ ፡ **ክርስቶስን** ፡ እንደሰቀሉት ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ የሸፈቱ ፡ ስለሆኑ ፡ እነሱን ፡ እንዲወጉ ፡ ላካቸው። ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ንድኃን ፡ የሚባል ፡ ከሐዲ ፡ ስለሸፈተ ፡ የቀን ፡ ጸልባ ፡ መኳንንት ፤ የዋግ ፡ ሹም ፤ የዳኅና ፡ ሹም ፡ የሰሐርት ፡ ሹም ፡ ከበብማእከለ ፡ ተዋዝት ፡ ማእከለ ፡ ባሕር ፡ የሚባሉትን ፡ ተዋጉ ፡ ብሎ ፡ ላካቸው። እርሱም ፡ ንጉሡ ፡ ራሱ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያሉትን ፡ ሠራዊቱን ፡ ይዞ ፡ በመጋቢት ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ተጉዞ ፡ ደዋሮ ፡ ደረሰ። የዚች ፡ አገር ፡ ገዥ (መኰንን) ፡ ስሙ ፡ ሐይደራ ፡ ይባላል። እርሱም ፡ እንደ ፡ ይሁዳ ፡ አፉን ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ አድርጎ ፡ ልቡን ፡ ከጠላቶቹ ፡ ከነሰብረዲን ፡ ጋር ፡ ያደረገ ፡ ነው። ኣስቀድሞ ፡ ንጉሡ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ወደኔ ፡ ቢመጣ ፡ አንተ ፡ ከነሠራዊትህ ፡ መጥተህ ፡ ወዳንተ ፡ ቢመጣ ፡ ከነሠራዊቴ ፡ መጥቼ ፡ አብረን ፡ ሆነን ፡ ወግተን ፡ እናጠፋዋለን ፡ ብሎ ፡ ከሰብረዲን ፡ ጋር ፡ ተስማምቶ ፡ ነበር።

ንጉሡ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ግን ፡ ከዚያ (ከደዋሮ) ፡ አልፎ ፡ ጋላ ፡ ወደሚባለው ፡ አገር (ገላን ፡ ወይም ፡ ጋላ ፡ ኣገር ፡ ነው) ፡ ሄደ ፡ በዚያም ፡ በሚያዝያ ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ በሰላምና ፡ በደስታ ፡ የፋሲካን ፡ በዓል ፡ ኣክብሮ ፡ ዋለ። በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ድንኳኑን (ሠፈሩን)ና ፡ ንግሥቲቱን ፡ መንገሻን) ፡ ባለቤቱን ( ፡ ትቶ ፡ ወደሰማርያ) ፡ ይኸን ፡ አገር ፡ ብሩስ ፡ ሰምሐር ፡ ዳልሜዳ ፡ ዛማርያ ፡ ይለዋል) ሄዶ ፡ ተዋጋ። ቀጥሎም ፡ ፳፫ ፡ ፈረሰኛ ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ተሰውሮ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሲዋጋ ፡ በሌላ ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ ሠራዊቱ ፡ ብቻቸውን ፡ ሲዋጉ ፡ ቆዩ። ሠራዊቱም ፡ ንጉሣቸውን ፡ አጥተው ፡ የት ፡ ሄዶ ፡ ይሆን ፡ ንጉሣችን ፡ እንግዴህ ፡ ምን ፡ ይሻለናል ፡ እያሉ ፡ ሲጨነቁ ፡ ንጉሡ ፡ ሲዋጋ ፡ ውሎ ፡ የማረከውን ፡ ምርኮ ፡ እንደያዘ ፡ ወደ ፡ ሠፈሩ ፡ ተመለሰ ፡ " ፡ ሠራዊቱም ፡ በየሄዱበት ፡ ሲዋጉ ፡ ውለው ፡ ወደሠፈር ፡ ገብተው ፡ ከንጉሣቸው ፡ ተገናኝተው ፡ እንደምን ፡ እንደተዋጉ ፡ እንደምን ፡ እንዳሸነፉ ፡ ተረኰለት ፡ ..... ፡ ከሀዲው (ሰብረዲን) የንጉሡንና ፡ የሠራዊቱን ፡ መገናኘት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ተጨነቀ ፡ .... ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ንግሥቲቱ (ወደ ፡ እቴጌይቱ)እንደዚህ ፡ ብለ ፡ ላከ ፡ በጌታዬ ፡ በንጉሥ ፡ ላይ ፡ በደልሁ ፡ ከፉ ፡ ሠራሁ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በሌላ ፡ በባዕድ ፡ እጅ ፡ ከምወድቅ ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ ብወድቅ ፡ ይሻለኛልና ፡ የፈቀደውን ፡ ያድርግብኝ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ መምጣቴ ፡ ነው ፡ ንግሥቲቱ ፡ ሰብረዲን ፡ የላከውን ፡ ቃል ፡ ሄዳ ፡ ለንጉሡ ፡ ነገረችው። ንጉሡ ፡ ግን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከቍጣው ፡ አልበረደምና ፡ እንደዚህ ፡ ብለሽ ፡ ላኪበት ፡ ብሎ ፡ ነገራት ፡ ብትመጣም ፡ ብትቀርም ፡ ኣያሳዝነንም ፡ ሩቅ ፡ ኣገርም ፡ ብትሄድ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ እከተልሃለሁ ፡ ወደ ፡ ጒድጓድም ፡ ብትገባ ፡ ብትሸሽም ፡ አገኘሁህ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ አልመለስም ፡ ይኸንመልእክት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሰብረዲን ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ መጣና ፡ በፊቱ ፡ ቆመ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ወቀሳውን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ዠመረ ፡ ለምንድነው ፡ እንደዚህ ፡ ያለሥራ ፡ መሥራትህ ፡ ለኔ ፡ ያወጣኸውን ፡ ግብርና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ለባሮችህ ፡ አደልኸው ፡ የኔንም ፡ የራሴን ፡ ገንዘብ ፡ ለድሆች ፡ የሰጠሁትን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ቀማህ ፡ ! ፡ ከኔ ፡ ጋር (ከመንግሥቴ ፡ የሚነግዱትን ፡ ኣሠርህ ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ደግሞ ፡ ዲያብሎስ ፡ ጌታውን ፡ ፈጣሪውን ፡ ለመሆን ፡ እንደተመኘዞፋኔን ፡ ተመኘሁ ፡ ከሐዲው ፡ ይኸን ፡ ቃል

፡ ከንጉሡ ፡ ሲሰማ ፡ ከፍርሀቱ ፡ የተነሣ ፡ መልስ ፡ አጣ ፡ ...ከዚያ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ደስ ፡ የሚልህን ፡ አድርግብኝአለ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በንጉሡ ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ ያሉት ፡ እየተነሡ ፡ «ይህ ፡ ሊሞት ፡ ይገባዋል (ኢይደልዎ ፡ ሕይወት)ኣብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ አቃጠለ ፤ ክርስቲያኖችን ፡ ገደለ ፡ የተረፉትንም ፡ ማርኮ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ አገባቸው (አሰላማቸው) ከዚያም ፡ ወደከፍተኛው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ መውጣት (ሊነግሥ) አሰበ ፡ እያሉ ፡ ግማሾቹ ፡ በሰይፍ ፡ ተመትቶ ፡ ግማሾቹ ፡ በደንጊያ ፡ ተወግሮ ፡ ግማሾቹ ፡ በእሳት ፡ ተቃጥሎ ፡ ይሙት ፡ ኣሁንም ፡ የመጣው ፡ በሥራዬ ፡ ሊያፌዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ለደኅንነትና ፡ ለመገዛት ፡ የመጣ ፡ አይምሰልህ ፡ እያሉ ፡ ተናገሩ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከወገቡ ፡ መቀነቱ ፡ ቢፈተሽ ፡ ብዙ ፡ ሥራሥር ፡ መድኀኒት ፡ ተገኘ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ በውነት ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ከእጄ ፡ ያድነኀልን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀውና ፡ ሁለት ፡ እጁን ፡ በሰንሰለት ፡ እሠሩት ፡ እንጂ ፡ ኣይገደል ፡ ብሉ ፡ አዘዘ። በዚሁም ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስሙን ፡ ያነሣነው ፡ ሐይደራ ፡ የሚባለው ፡ የደዋሮ ፡ ገዢ ፡ በዚህ ፡ በክፉ ፡ ሥራ ፡ ከሰብረ ፡ ዲን ፡ ጋር ፡ ተባብሮ ፡ ስለነበረ ፡ ኣብሮ ፡ ታሠረ። የሰብረዲን ፡ ግዛት ፡ የነበረው ፡ ሁሉ ፡ ለወንድሙ (ያባቱ ፡ የዳልሁዶ ፡ ኣጐት ፡ እንጂ ፡ ወንድሙ ፡ ኣይደለም) ላግማልዲን (ጋማል ፡ ኣድዲን) ከሽልማት ፡ ጋር ፡ ተሰጠው። »

ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳልነው ፡ የጦርነቱን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ የጻፈው ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ የንጉሥ ፡ ኣሽከርና ፡ ባለሟል ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ክርስቲያን ፡ በመሆኑ ፡ ተዘጋጅተው ፡ የመጡት ፡ የይፋትና ፡ የደዋሮ ፡ ባላባቶችና ፡ ወታደሮች ፡ ከመሸነፋቸውና ፡ ከመማረካቸው ፡ በፊት ፡ የውጊያቸውን ፡ ዝርዝር ፡ ሳይሰጠን ፡ በቀላል ፡ መሸነፋቸውን ፡ ፺፫ ፡ ፈረሰኛ ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ንጉሡ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ እንደማረከ ፡ ሲገልጽን ፡ ታሪኵ ፡ በመሠረቱ ፡ እውነት ፡ መሆኑም ፡ ባይቀር ፡ በጸሐፊው ፡ ላይ ፡ እንደዘመኑ ፡ አጻጻፍና ፡ ልማድ ፡ በኣነጋገሩ ፡ ለወገኑ ፡ ማድላቱ ፡ ይታያል።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ደዋሮን ፡ አልፎ ፡ ወደጋላ ፡ አገር ፡ ሄደ ፡ ስለሚል ፡ በዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ ጋሎች ፡ በደዋሮ ፡ አጠገብ ፡ መኖራቸውን ፡ ያስረዳል ፡ ከዚያም ፡ አፄ ፡ ዓምደጽዮን ፡ ከነዚሁ ፡ ከይፋትና ፡ ከደዋሮ ፡ በላባቶች ፡ ጋር

፡ ለጦርነት ፡ በተሠለፈበት ፡ ሰዓት ፡ በስሜንና ፡ በወገራ ፡ በጸለምት ፡ ያሉ ፡ ፈላሾችና ፡ እስላሞች ፡ ከነዚህ ፡ ጋር ፡ ውስጡን ፡ ተላልከው ፡ ወይም ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ከንጉሣቸው ፡ ጋር ፡ ማጥቃት ፡ የምንችልበት ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ ነው ፡ በማለት ፡ መነሣታቸውን ፡ የሚያስረዳው ፡ ኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጻጋ ፡ **ክርስቶስ** ፡ በሚባለው ፡ መሪነት ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ወደነዚሁ ፡ አገሮች ፡ መላኩ ፡ ነው።

ለኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲያስቸግሩ ፡ በየ ፡ ጊዜው ፡ የምንመለከተው ፡ በስሜንና ፡ በወገራ ፡ ፈላሾች ፤ በዚህ ፡ በደቡብ ፡ በኵል ፡ የይፋትና ፡ የአዳል ፡ እስላሞች ፡ ናቸው። እነዚህንም ፡ በየጊዜው ፡ ነገሥታቱ ፡ መውጋታቸውም ፡ ማስገበራቸውም ፡ ባይቀር ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ልዩነት ፡ የተነሣ ፡ ከቀረው ፡ የክርስቲያን ፡ ሕዝብ ፡ ዜጋ ፡ ጋር ፡ መዋሐዱ ፡ ኣስቸጋሪ ፡ ሆኖ ፡ ወደፊት ፡ ባለው ፡ በሸዋና ፡ በጐንደር ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ እነሱን ፡ ለማሳመን ፡ የተደረገው ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ ነው። ስለዚህ ፡ ኣሁን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትተን ፡ ወደይፋቱና ፡ ወደዳሉ ፡ ጦርነት ፡ እንመለስ።

አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከይፋቱ ፡ ባላባት ፡ ከወላስማ ፡ ዘር ፡ ከሰብረዲን (ሳብር ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ መሐመድ) ጋር ፡ ያደረገበትን ፡ የጦርነት ፡ ዘመን ፡ ለማግኘት ፡ በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ላይ ፡ የተጻፈው ፡ ይገልጽልናል። በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በነገሠ ፡ በ፲፰ኛው ፡ ዓመት ፡ ሰብረዲን ፡ ኢትዮጵያን ፡ እገዛለሁ ፡ ብሎ ፡ ተነሣስለሚል ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የነገሠበት ፡ ጊዜ ፡ ሺ፫፻፪ ፡ ዓ.ምሕረት ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ አሥራ ፡ ስምንቱ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ሲጨመርሺ፫፻፳፪ ፡ ዓ.ምሕረት ፡ ስለሆነ ፡ ጦርነቱ ፡ የተደረገው ፡ በዚሁ ፡ በሺ፫፻፳፪ ፡ ዓ.ም ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው። ወሩም ፡ በየካቲት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ጦሩን ፡ አስቀድሞ ፡ ልኮ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ በመጋቢት ፡ ጌ ፡ ቀን ፡ ደዋሮ ፡ ሄዶ ፡ ከዚያ ፡ በሚያዝያ ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ጋላ ፡ ወደ ፡ ሚባለው ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ የፋሲካን ፡ በዓል ፡ አክብሮ ፡ ወዲያው ፡ ሰማርያ። ወደሚባለው ፡ ቦታ ፡ ሄዶ ፡ መዋጋቱን ፡ ዜናመዋዕሉ ፡ በትክክል ፡ ይገልጻል።

# ምዕራፍ ፡ ፲፫

## ዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከኣዳሉ ፡ ንጉሥና ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ የመዠመሪያው ፡ ጦርነት።

ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደተመለከተው ፡ የይፋትና ፡ የደዋሮው ፡ ባላባቶች ፡ ሸፍትነት ፡ አልቆ ፡ ዋናዎቹ ፡ ባላባቶች ፡ ሰብር ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ የይፋቱ ፡ ሐይዛራ ፡ የደዋሮው ፡ ከታሠሩ ፡ ወዲህ ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የጦርነት ፡ ግዕዝኛ ፡ ታሪክ ፡ የአዳልና ፡ የሞራ ፡ ባላባቶች ፡ ያደረጉትን ፡ ታላቀኑን ፡ ጦርነት ፡ መደዳውን ፡ ከመተረክ ፡ በቀር ፡ የይፋቱን ፡ ጨርሶ ፡ የአዳሎቹን ፡ በሚዠምርበት ፡ መካከል ፡ ምዕራፍ ፡ አላደረገበትም። እኔ ፡ ግን ፡ ያለፈውን ፡ የይፋቱን ፡ ባንድ ፡ ምዕራፍ ፡ አቀኍሜ ፡ ላንባቢ ፡ እንዲመች ፡ ላሁኑ ፡ ላዳሎቹ ፡ ጦርነት ፡ ለሌሳውም ፡ ወደፊት ፡ ለሚገኘው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ምዕራፍ ፡ አድርጌለታለሁ። ይኸም ፡ ወደፊት ፡ የምንመለከተው ፡ የኣዳል ፡ ጦርነት ፡ ከይፋቱ ፡ የበለጠ ፡ አስቸጋሪ ፡ የነበረ ፡ ነው ፡ " ፡ ይፋትና ፡ ደዋሮ ፡ ለሸዋ ፡ የሚቀርቡ ፡ ኣገሮች ፡ በመሆናቸው ፡ የሕዝቡንም ፡ አመልና ፡ ልማድ ፡ የአገሩንም ፡ ውጫና ፡ መግቢያውን ፡ በማወቅ ፡ ለክርስቲያኖቹ ፡ የአባሉን ፡ ያህል ፡ አላስቸገረም ፡ አዳልና ፡ ሞራ ፡ የሚባሉት ፡ አገሮች ፡ ከደዋሮና ፡ ከፈጠጋር ፡ ዠምሮ ፡ እስካ ፡ ሕንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ድረስ ፡ የሚደርስ ፡ ሰፊው ፡ የዛሬው ፡ የአዳል ፡ የኢሳ ፡ የውጋዴን ፡ የሱማሌ ፡ አገር ፡ ስለሆነ ፡ በሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ ባገሩ ፡ ስፋትና ፡ በረሃነት ፡ የተነሣ ፡ ይህን ፡ ጦርነት ፡ በእንዴት ፡ ያለችግርና ፡ መሥዋዕትነት ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ድል ፡ ለማድረግ ፡ እንደቻለ ፡ እንመለከታለን ፤ በዚህም ፡ ታሪክ ፡ ውስጥስናነበው ፡ ደስ ፡ የሚለን ፡ ሕዝቡ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጦ ፡ እንመለስ ፡ ሲል ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የወታደሩንና ፡ የሹማምንቱን ፡ ልብ ፡ ለማነቃቃት ፡ የተናገረው ፡ ዲስኩር ፡ ፣ ፡ በሕመሙ ፡ ጊዜ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ቍጭትና ፡ ቆራጥነት ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባላቤቱ ፡ እቴጌዪቱ ፡ በእንዴት ፡ ያላ ፡ ሐዘንና ፡ ለቅሶው ፡ ሸኝታ ፡ ስለ ፡ ባለቤቷ ፡ ያደረገችው ፡ ጸሎት ፡ ነው። ምንም ፡ እንኳን ፡ ጸሐፊው ፡ ፩ ፡ ኣንድ ፡ የማጋነን ፡ ቃል ፡ እየጨመረ ፡ የታሪኩን ፡ መልክ ፡ ማሳመሩ ፡ ባይቀር ፡ ጸሐፊው ፡ ደግሞ ፡ ጫፍና

፡ መሠረት ፡ ሳያገኝ ፡ አልጻፈውምና ፡ ታሪኩ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው። እንግዲህ ፡ ከዚሁ ፡ ቀጥሎ ፡ ግዕዙ ፡ የሚለውንና ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ የመለስሁት ፡ የሚለውን ፡ በቀጥታ ፡ እንመልከት።

"ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አዳልና ፡ ሞራ ፡ የሚባሉ ፡ ብዙ ፡ ሕዝቦች ፡ ተባብረው ፡ እንደዚህ ፡ ብለው ፡ መጡ ፡ ፤ የክርስቲያኑን ፡ ንጉሥ ፡ እርሱ ፡ አገራችን ፡ ሳይመጣ ፡ እኛ ፡ ሄደን ፡ እንውጋው። አለበት ፡ ሄደን ፡ የወጋነው ፡ እንደሆነ ፡ በፍርሐት ፡ ደንግጦ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይመለሳል። ዝም ፡ ያልነው ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ወዳገራችን ፡ መጥቶ ፡ ያጠፋናል። » ፡ ይኸን ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ አዳሎቹ ፡ ወደ ፡ ይፋት ፡ መጥተው ፡ የንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ በተኙበት ፡ ሌሊት ደርሰው ፡ ቲንሽ ፡ ሰዎች ፡ ገድለው ፡ ተመለሱ። እነዚህም ፡ የንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ ብቻቸውን ፡ ነበሩ ፤ ብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ግን ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ነበሩ። ስለዚህ ፡ ባልጠረጠሩበት ፡ ሰዓት ፡ በሰላም ፡ እተኙበት ፡ ድረስ ፡ ሌሊት ፡ መጥተው ፡ ገድለው ፡ ተመለሱ። ቀጥሎም ፡ በሌላው ፡ ቀን ፡ ፪ኛ ፡ መጥተው ፡ የንጉሡን ፡ ጦር ፡ ገጥመው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ፈጅ፤ብዙ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ከብትም ፡ ዘርፈው ፡ ሄዱ ፤ ከዚያም ፡ ፫ኛ ፡ ጊዜ ፡ ከፊተኛው ፡ የበለጠ ፡ በርክተው ፡ ሌሊት ፡ መጥተው ፡ ከንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ ጋር ፡ ገጥመው ፡ ድንኳኑን ፡ ገለባብጠው ፡ ብዙ ፡ ዕቃ ፡ ዘረፉ ፡ ....ሲነጋ ፡ የንጉሡ ፡ የዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ወታደሮች ፡ ተከታትለው ፡ በአዳሎቹ ፡ ደረሱባቸውና ፡ ተዋግተው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ጨረሱባቸው ፤ የተማረከውን ፡ ዕቃና ፡ ድንኳን ፡ ሁሉ ፡ አስመልሰው ፡ በደስታ ፡ ወደንጉሣቸው ፡ ተመለሱ ......።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በማግስቱ ፡ ሹማምንቱና ፡ የጦር ፡ አለቆቹ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ መጡና ፡ እንግዴህ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ጠላቶችህን ፡ ከእግርህ (ከድኳህ) በታች ፡ ከአስገዛህ ፡ አሁን ፡ ወዳገራችን ፡ እንመለስ ፡ የክረምት ፡ ጊዜውም ፡ እነሆ ፡ መግባቱ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ በባዕድ ፡ አገር ፡ እንዳንጠፋ ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ እንመለስ ፡ »አሉት ፤ ንጉሡም ፡ ከሰማቸው ፡ በኋላ ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው። ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ንግግር ፡ ሁለተኛ ፡ በፊቴ ፡ እንዳትናገሩ ፡ እኔ ፡ የመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ሆኜ ፡ እነዚህ ፡ ባላባቶች ፡ የተዋጉኝ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ወዳገሬ ፡ አልመለስም። »

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ግማልዲን (ጋማል ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ በሳብር ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ እግር ፡ የተሾመው) ብዙ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ መጣና ፡ «ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እንግዴህ ፡ ወደ ፡ አገርህ ፡ ተመለስ ፤ እኔን ፡ ለዚህ ፡ አገር ፡ ከሾምኸኝ ፡ ፈቃድህን ፡ ሁሉ ፡ እፈጽማለሁ ፡ እንግዴህ ፡ ኣገሩ ፡ ሁሉ ፡ ጠፍቷል ፡ የተረፈውን ፡ አታጥፋው... ፡ እስላሞቹ ፡ ሁሉ ፡ እኔም ፡ ጭምር ፡ አሁን ፡ ያንተ ፡ ባሮች ፡ ነን'' አለው። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ በቍጣ! መለሰለት ፡ እነዚህ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ልጅ ፡ የማያምኑ ፡ የውሻና ፡ የዕባብ ፡ ልጆች ፡ እየወጉኝ ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ አልመለስም። ኣዳል ፡ አገር ፡ ሳልገባ ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ ብመለስ ፡ እዚህ ፡ ያለውም ፡ የሌለውም ፡ እንደወለደችኝ ፡ እናቴ ፡ ሴት ፡ ይበለኝ'' ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሰኔ ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ንጉሡ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋር ፡ ከጋላ ፡ ኣገር ፡ ተነሥቶ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ተጓዘ ፡ '' ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከሠራዊቱ ፡ ብቻውን ፡ ተላይቶ ፡ መጥቶበት ፡ ወደነበረው ፡ ሥፍራ ፡ ደረሰ። የሰባት ፡ አገር ፡ ባላባቶችም ፡ ተሰብስበው ፡ ሌሊት ፡ ሊዋጉ ፡ መጡ። እነዚህም ፡ የአዳል ፡ የሞራ ፡ የሚቆ ፡ የጳጉማ ፡ የበከላ ፡ የወርገር ፡ የገበላ ፡ ናቸው። የጦራቸውም ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ኣሸዋ ፡ ነው። አመጣጣቸውም ፡ ሌሊት ፡ ንጉሡ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ እተኛበት ፡ ደርሰን ፡ አንድም ፡ ሳናስቀር ፡ እንጨርሰዋለን ፡ ብለው ፡ ነው። እንዳሉትም ፡ ሌሊት ፡ ደርሰው ፡ የንጉሡን ፡ ሠፈር ፡ ሲከቡ ፡ የንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ ንጉሣችን ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ እስላሞቹ ፡ መጥተዋልና ፡ መጥቶ ፡ ያድነን'' ፡ ብለው ፡ ጮሁ ፡ ''ንጉሡም ፡ የወታደሮቹን ፡ ጩኸት ፡ ሰምቶ ፡ ከተኛበት ፡ ተነሣ ፤ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ ታጥቆ ፡ ሰይፉን ፡ ይዞ ፡ ከድንኳኑ ፡ ወጣና ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ ጦርነት ፡ ገጠማቸው። እነዚያም ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ተሸንፈው ፡ ከፊቱ ፡ ሸሹ፡...እንደዚህም ፡ እያደረጉ ፡ ....በ፪ኛውም ፡ በ፫ኛውም ፡ ቀን ፡ እየመጡ ፡ ቢዋጉት ፡ በፈረሱ ፡ ላይ ፡ እየወጣ ፡ ተዋጋቸው። በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ከሌላው ፡ ቀን ፡ በርክተው ፡ ሊዋጉ ፡ መጡ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንደለመደው ፡ እፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ «ጌታዬ ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ሆይ ፡ ባሪያህን ፡ ዳዊትን ፡ ከጦር ፡ እንዳዳንኸው ፡ እኔንም ፡ ከእጃቸው ፡ አድነኝ ፡ ብሎ ፡ ጸለየና ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከነዚያ ፡ ወገን ፡ ኣንድ ፡ ወታደር ፡ የንጉሡ ፡ ወታደር ፡ መስሎ ፡ ከወደ ፡

ኋላው ፡ መጣና ፡ በሰይፍ ፡ መትቶ ፡ ንጉሡ ፡ የታጠቀውን ፡ ቀበቶና ፡ የጦር ፡ ልብሱን (ወመተረ ፡ ቅናተ ፡ ሐቃሁ ፡ ወልብሰ ፡ ፀብእሂ) በጥሶ ፡ ሲቀድ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ንጉሡን ፡ አዳነው። ንጉሡ ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ግንባሩን ፡ በጦር ፡ ወጋና ፡ እመሬት ፡ ጣለው.... በሌላ ፡ ግንባር ፡ ያሉትም ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ወደ ፡ መሸነፍ ፡ አዘንብለው ፡ ንጉሣችን ፡ ወዴት ፡ ሄደ ፡ ምነው ፡ ደርሶ ፡ ባዳነን ፡ እያሉ ፡ ሲሉ ፡ ከወደ ፡ ኋላ ፡ በፈረስ ፡ ደርሶ ፡ እስላሞቹን ፡ ተዋጋቸው.... በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ ጦርነቱን ፡ መቀጠል ፡ አልቻሉምና ፡ ወደኋላቸው ፡ ሸሹ። ንጉሡም ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ጦርነት ፡ ያልተዋጉትን ፡ አዲስ ፡ ወታደሮች ፡ በራሪዎቹን ፡ ተከታትላችሁ ፡ ውጉ ፡ ብሎ ፡ ኣዘዛቸውና ፡ ያባርሩ ፡ ዠመር። ሌሊቱንሙሉ ፡ ሲሄዱ ፡ ኣድረውሲነጋ ፡ ደረሱባቸውና ፡ ውጊያ ፡ ገጥመው ፡ ብዙዎችን ፡ ፈጅተው ፡ ሲጨርሱ ፡ የማረኰትን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሰይፍ ፡ ጦር ፡ ቀስት ፡ ብዙ ፡ ልብስ ፡ ይዘው ፡ ሲመጡ ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ኣለው።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ሄደና ፡ በሰኔ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ የጦርሠራዊቱን ፡ ሰብስቦ (ሰልፍ ፡ አደረገ) እንደዚህ ፡ እያለ (በዲስኵር)ነገራቸው። « ፡ ስምዑኒ ፡ እንግርክሙ ፡ ምሥራቀ ፡ ወምዕራበ ፡ ደቡበሂ ፡ ሰሜነሂ ፡ ትግሬሂ ፡ ወጐዣምሂ፣ ፡ ወገራሂ ፤ ወዳሞትሂ ፤ ወሐድያሂ ፡ ወእንተ ፡ ኵሎሄ ፡ ፀባዕነ ፡ አኮኑ ፡ በኃይላ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ሞፅናሆሙ ፡ ወቀተልናሆሙ። ወእለ ፡ ተርፉ ፡ ጼወውናሆሙ ፡ ዓቢዮሙ ፡ ወንኡሰሙ ፡ ለነገሥቶሙኒ ፡ ጼወውናሆሙ። ወይእዜኒ ፡ ኢትፍርሁ ፡ እምቅድሜሆሙ ፡ ለዕልዋን ፡ ጥብዑ ፡ ወኢትናፍቁ ፡ እስመ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ይፀብእ ፡ ለነ ፡ ወለእመመጽኡ ፡ ኀቤክሙ ፡ በሰይፍ ፡ ብክሙ ፡ ሰይፍ ፤ ወለእመ ፡ መጽኡ ፡ በቀስት ፡ ወኲናት ፡ ብክሙ ፡ ቀስት ፡ ወኲናት። ኢሰማዕክሙኑ ፡ በከመ ፡ ይቤሉ ፡ እሉ ፡ ተንባላት ፡ ዕልዋነ ፡ መሢሑ ፡ ለ**እግዚአብሔር**። ወእለ ፡ ኢየአምርዎ ፡ ለ**ክርስቶስ** ፡ ሶበ ፡ ይቀትሉነ ፡ ክርስቲያን ፡ ንከውን ፡ ሰማዕተ ፡ ወሶበ ፡ ንቀትሎሙ ፡ ለክርስቲያን ፡ ንረክብ ፡ ገነተ። ከመዝ ፡ ይቤሉ ፡ ዕልዋነ ፡ ተንባላት ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ተስፋ ፡ ለድኅን ፡ ወያጠብኡ ፡ ለመዊት። እፎኬ ፡ ኣንትሙ ፡ እለ ፡ ተአምርዎ ፡ **ለአብ** ፡ ምስለ ፡ **ወልዱ** ፡ **ወመንፈስ ፡ ቅዱስ** ፡ እለ ፡

ተጠመቅክሙ ፡ በስሙ ፡ ወተቀደስክሙ ፡ በደሙ ፡ ለምንት ፡ ትፈርህዎሙ ፡ ለዕልዋን ፡ ትካትሰ ፡ ታጠብዑ ፡ ተቃትሎ ፡ በእንቲአየ።

ወይእዜኒ ፡ አጥብዑ ፡ ተቃትሎ ፡ በእንተ ፡ **ክርስቶስ** ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፈ ፡ ቀኖና ፡ ተቃተል ፡ ዕልዋነ ፡ ወከሀድያነ ፡ በሰይፈ ፡ ኀፂን ፡ ወምላሕ ፡ ሰይፈከ ፡ በላዕለ ፡ ሃይማኖት ፡ ፍጽምት ፡ ወአንትሙሂ ፡ ቅንቱ ፡ ሰይፈክሙ ፡ ወአጥብዑ ፡ ልበክሙ ፡ ወኢታደንግፁ ፡ ነፍሰክሙ። አላ ፡ ፅንዑወተወከሉ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፈ ፡ መዝሙር ፡ በቧወቹ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ተወከልኩ ፡ ኢይፈርህ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ምንትይሬስየኒ። **እግዚአብሔር** ፡ ይረድኣኒ ፡ ወአነ ፡ እሬእዮሙ ፡ ለጸላዕትየ ፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ኵሎሙ ፡ ኣሕዛብ ፡ አገቱኒ ፡ ወበስመ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ሞዕክዎሙ" ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ በቍጣ ፡ ል ፡ ታነብሩ ፡ ልበክሙ ፡ ድኅረ ፡ ዘባንክሙ። ኣላ ፡ አግብኡ ፡ ልበክሙ ፡ እንተ ፡ ቅድሜክሙ ፡ ኀበ ፡ ያዘቀዳሚ ፡ ንብረቱ ፡ ወአእትቱ ፡ ፍርሐተ ፡ እምላዕሌክሙ ፡ አንሰኬ ፡ መሐልኩ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ሕያው ፡ ፈጣሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ወለእመ ፡ ኮነክረምት ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሐጋይ ፡ ከመ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ውስተ ፡ ሀገርየ ፡ እስከ ፡ አሐልቆሙ ፡ ላዕልዋን ፡ በኃይላ ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ አምላኪየ ፡ ወልደ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ወለእመኒ ፡ ሞት ፡ ወለእመኒ ፡ ሐየውነ ፡ ለ**እግዚአብሔር** ፡ ንሕነ። ኣነኒ ፡ አጽናእኩ ፡ ልብየ ፡ በ**ክርስቶስ** ፡ » ፡ ትርጕሙ ፡ ከመዠመሪው ፡ አንሥቶ ፡ ምሥራቅም ፡ ምዕራብም ፡ ደቡብም ፡ ሰሜንም ፡ ትግሬም ፡ ጐጃምም ፡ ወገራም ፡ ዳሞትም ፡ ሐድያም ፡ የምነግራችሁን ፡ ስሙኝ ፡ እነሆ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እየተዋጋን ፡ ብዙዎቹን ፡ ገደልናቸው ፡ የተረፉትንም ፡ ቲንሾቹንም ፡ ትልቆቹንም ፡ ነገሥታቶቻቸውንም ፡ ማረክናቸው ፡ ይኸንን ፡ ሁሉ ፡ ድል ፡ ያገኘነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ አይደለምን ፡ አሁንም ፡ በነዚህ ፡ በከሐዲዎች ፡ ፊት ፡ አትፍሩ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ስለኛ ፡ ይዋጋልናል ፡ ጽኑ ፡ እንጂ ፡ አትጠራጠሩ። በሰይፍ ፡ ቢመጡባችሁ ፡ ሰይፍአላችሁ ፡ " ፡ በቀስትና ፡ በጦር ፡ ቢመጡባችሁም ፡ ቀስትና ፡ ጦር ፡ አላችሁ። እነዚህ ፡ የ**እግዚአብሔር**ን ፡ መላከተኛው (መሢሑን) የሚክዱ ፡ **ክርስቶስን** ፡ የማያውቍ ፡ አረመኔዎች ፡ የሚሉትን ፡ አልሰማችሁምን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ቢገድሉን ፡ ሰማዕት ፡ እንሆናላን፣እኛ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ የገደልን

፡ እንደሆነ ፡ ህግን ፡ ገነትን ፡ እናገኛለን ፡ ነው ፡ የሚሉት። እነዚህ ፡ ለሞት ፡ እንጂ ፡ ለድኅነት ፡ ተስፋ ፡ የሌላቸው ፡ አረማውያን ፡ ከሐዲዎች ፡ ናቸው። እናንተስ ፡ **አብን ፡** ከ**ወልድ** ፡ ጋር ፡ **መንፈስ ፡ ቅዱስን**ም ፡ የምታውቀኍት ፡ በስሙ ፡ ተጠምቃችሁ ፡ በደሙ ፡ የተቀደሳችሁት ፡ እነዚህን ፡ ከሐዲዎች ፡ ለምን ፡ ትፈሩዋቸዋላችሁ። ቀድሞ ፡ ስለኔ ፡ ለመዋጋት ፡ ልባችሁን ፡ አጽንታችኋል ፡ ኣሁን ፡ ግን ፡ መጽሐፈ ፡ ቀኖና ፡ ለእውነተኛዪቱ ፡ ሃይማኖት ፡ ሰይፍህን ፡ ምዘዝናከከሐዲና ፡ ከአረመኔ ፡ ጋር ፡ ተጋደል ፡ እንዳለ ፡ እናንተም ፡ አሁን ፡ ለ**ክርስቶስ** ፡ ስትሉ ፡ ለውጊያ ፡ ጽኑ። ሰይፋችሁን ፡ ታጠቍ ፡ ልባችሁን ፡ አጽኑ ፡ ነፍሳችሁን ፡ አታስደንግጡ። ነገር ፡ ግን ፡ የመዝሙር (የዳዊት) መጽሐፍ ፡ በ፲፫ኛው ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ታምኛለሁና ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፡ ብዬ ፡ አልፈራም ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ስለሚረዳኝ ፡ ጠላቶቼን ፡ እመለከታቸዋለሁ (ሲወድቍ?) እንዳለው ፡ እናንተም ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ታምናችሁ ፡ ጽኑ። ደግሞም ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ከበቡኝ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ስም ፡ አሸነፍኋቸው ፡ ብሏል ፡ ከዚህ ፡ አያይዞ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በቍጣ ፡ ቃል ፡ ለሠራዊቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ «ልባችሁን ፡ ቀድሞ ፡ እነበረበት ፡ እፊታችሁ ፡ አድርጉት ፡ እንጂ ፡ ወደኋላ ፡ ወደ ፡ ዠርባችሁ ፡ አታድርጉት (ወደ ፡ ፊት ፡ ቅደሙ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አትሽሹ ፡ ወይም ፡ ለጠላት ፡ ዠርባችሁን ፡ አትስጡ ፡ ለማለት ፡ ይሆናል) ። ፍርሐትን ፡ ከልባችሁ ፡ አስወግዱ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ በአምላኪየ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ልጅ ፡ በ**ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ኃይል ፡ እነዚህን ፡ ከሐዲዎች ፡ ሳልጨርስ ፡ በጋም ፡ ቢሆን ፡ ክረምትም ፡ ቢሆን ፡ ወዳገሬ ፡ እንዳልመለስ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በፈጠረ ፡ በሕያው ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ምያለሁ ፡ ልቤንም ፡ በ**ክርስቶስ** ፡ አፅንቻለሁ። »

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ አሁንም ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ የወታደሩን ፡ ልብ ፡ ለማጽናት ፡ ሲል ፡ ቀጥሎ ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፡ ደግ ፡ አማኑኤል ፡ የሚባል ፡ መነኰሴ ፡ የ**እግዚአብሔር** ፡ ሰው ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ የላከብኝን ፡ ስሙ! ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ይኸ ፡ የምነግርህ ፡ ሕልም ፡ ያልሆነ ፡ ወይም ፡ አሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ሐሰት ፡ ትንቢት ፡ የምነግርህ ፡ እንዳይመስልህ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ያወቅሁትን ፡ ነው።

የእስላሞቹ ፡ መንግሥት ፡ ተፈጽሟል። እስካሁን ፡ ለሚያልፍ ፡ መንግሥትና ፡ ለወርቅ ፡ ለብርና ፡ ለሽልማት (ኣልባሳት ፡ ክቡራት) ትዋጋ ፡ ነበር። አሁን ፡ ግን ፡ የሐዋርያት ፡ መጽሐፈ ፡ ቀኖና ፡ በሰይፍህ ፡ ጫፍ ፡ ከከሐዲዎች ፡ ጋር ፡ ተጋደል ፡ እንዳለው ፡ አንተም ፡ ለ**ክርስቶስ** ፡ ስትል ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገሥግሥ ፡ ከሐዲዎችንም ፡ ውጋቸው ፡ የምታሸንፋቸው ፡ አንተ ፡ ነህና ፡ አትፍራቸው) ብለው ፡ መነኰሴው ፡ ላኵብኝ ፡ ስለዚህ ፡ እናንተም ፡ የምነግራችሁን ፡ ስሙኝ ፡ እነዚህን ፡ ከሐዲዎች ፡ ለምን ፡ ትፈሩዋቸዋላችሁ ፡ ልባችሁን ፡ በማጽናት ፡ እንጂ ፡ በፍርሐት ፡ የምታመልጡ ፡ ኣይምሰላችሁ። ደግሞ ፡ የምነግራችሁን ፡ ምሳሌ ፡ ስሙ። ማልከግራ ፡ ማል ፡ ጋራ ፡ ቢጣሉ ፡ ጐንደረት ፡ ያስታርቋቸዋል። የላዕዳት ፡ ከጊዓ ፡ ጋራ ፡ ቢጣሉ ፡ ዋልሳ ፡ ያስታርቋቸዋል። እናንተ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ዳጅ ፡ በዘይት ፡ ሐመወክሙ ፡ አላችሁ ፡ ወይም ፡ በናንተና ፡ በእስላሞቹ ፡ መካከል ፡ የሚያስታርቅ ፡ ወዳጅ ፡ አላችሁ? በፊትስ ፡ በኋላስ ፡ የአዋሽን ፡ ወንዝ ፡ ከተሻገርን ፡ ወዲህ ፡ የሠራነው ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ ኣይደለምን ፡ እስኪ ፡ እናንተው ፡ ንገሩኝ ፡ ይኸንንም ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ በቍጣ ፡ ቃል ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረከእንግዴህ ፡ ወዲያ ፡ እናንተ ፡ የምትሉትን ፡ በሉ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ እስላሞቹን ፡ ሳልጨርስ ፡ ወዳገሬ ፡ እንዳልመለስ ፡ በሰማይ ፡ አምላክ ፡ ምያለሁ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሠራዊቱ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ አወን ፡ እንዳዘዝኸን ፡ እንሠራለን ፡ ነገርግን ፡ ሁሉም ፡ እንዲቀናን ፡ ባርከን ፡ ሲሉ ፡ መለሱለት። እርሱም ፡ በቃሉ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ባረካቸው ፡ የከሐዲዎቹ ፡ ሰይፋቸውም ፡ ጦራቸውም ፡ ፍላፃቸውም ፡ በላያችሁ ፡ ላይ ፡ አይውደቅ። የናንተ ፡ ግን ፡ ሰይፋችሁም ፡ ወደ ፡ ልባቸው ፡ ይግባ ፡ ጦርና ፡ ፍላፃቸውም ፡ ወደልባቸው ፡ ይመለስ ፡ ፤ ጐራዲያችሁና ፡ ጦራችሁም ፡ እነሱን ፡ ይምታ። እናንተን ፡ **እግዚአብሔር** ፡ በጋሻው ፡ ከልሎ ፡ እየሠወረ ፡ ኃይልንና ፡ አሸናፊነትን ፡ ይስጣችሁ ፡ ሕዝቡም ፡ አሜን ፡ ወአሜን ፡ ለይዙን ፡ ለይተን» ፡ ብሎ ፡ ተፈጸመ።

ዲስኵሩ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ተፈጸመ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስማቸውን ፡ ያነሣኋቸው ፡ ሙሴ ፡ ዡል ፡ ፔሩሾ ፡ ይኸን ፡ ያምደ ፡ ጽዮንን ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ

፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ተርጒመውታል። በትርጒማቸውም ፡ ውስጥ ፡ ኣልፎ ፡ ኣልፎ ፡ አንዳንድ ፡ ቲናንሽ ፡ ስሕተት ፡ አይጠፋበትም።

ይኸንንም ፡ ያፄ ፡ ዓምደጽዮንን ፡ ዲስኩር ፡ ሲተረጒሙ ፡ እመዠመሪያው ፡ ላይስምዑኒ ፡ እንግርክሙ ፡ ምሥራቀ ፡ ወምዕራበ ፡ ደቡበሂ ፡ ሰሜነሂ ፡ ትግሬሂ ፡ ወጐዣምሂ ፡ ወገራሂ ፡ ወዳሞትሂ ፤ ወሐድያሂ ፡ ወእንተ ፡ ኵለሄ ፡ ፀባዕነ ፡ ኣኮኑ ፡ በኃይለ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ሞዕናሆሙ...” ፡ የሚለውን ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ሲተረጒሙ ፡ » *Ecoutez-moi! Lcrsque nous avons fait la guerre de tous cötés dans l’ Est et dans l Ouest dans le Nord et dans le MidiLorsque nous avons combattu les gens des Tigres, du Godjam ፥ ....*

ኣድምጠኝ ፡ በምሥራቅም ፡ በምዕራብም ፡ በደቡብም ፡ በሰሜንም ፡ ጦርነት ፡ ያደረግን ፡ ጊዜ ፡ ከትግሬም ፡ ከጐጃምም... ፡ የተዋጋን ፡ ጊዜ ፡ ... ፡ ብለው ፡ ተርጒመውታል። ምንም ፡ እኻህ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ታሪክና ፡ ጽሑፍ ፡ እንደነ ፡ ሉደልፍ ፡ እንደነ ፡ ብሩስ ፡ እንደነ ፡ ዲልማን ፤ እንደነ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ እንደነ ፡ ኢኛሲዮ ፡ ጉዪዲ ፡ እንደነ ፡ ኮንቲሮሲኒ ፡ የደከሙ ፡ በዚህም ፡ ሙሉ ፡ ምሥጋና ፡ የሚገባቸውን ፡ ይህ ፡ ከዝንጋታ ፡ እንጂ ፡ ከስህተት ፡ የማይቆጠረው ፡ ትርጓሜ ፡ ሊያስቀርባቸው ፡ ኣይችልም። የውጭ ፡ ኣገር ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ ጠንቅቀን ፡ አወቅን ፡ ቢሉ ፡ የግዕዝና ፡ የአማርኛ ፡ ነገር ፡ ፩ ፡ ኣንድ ፡ ጊዜ ፡ ይሳሳታቸዋል ፡ ከኤውሮፓ ፡ ልዩ ፡ የሆነውን ፡ የግዕዝና ፡ የአማርኛ ፡ መንፈሱን ፡ አሳቡን ፡ ለመረዳት ፡ ከዚያው ፡ ከደንበኛው ፡ ኣማራና ፡ ከግዕዝ ፡ ኣዋቂው ፡ በቀር ፡ የውጭ ፡ አገርን ፡ ዐዋቂ ፡ ያሳስታል።

ነገር ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ባፄ ፡ ዓደ ፡ ጽዮንና ፡ በይፋትና ፡ በአዳል ፡ ባላባቶች ፡ መካከል ፡ የተደረገውን ፡ ጦርነት ፡ በትክክል ፡ ስንመለከተው ፡ የትግሬ ፡ የጐጃም ፡ የዳሞት ፡ ያማራ ፡ የሸዋ ፡ ሕዝብ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ አዳሎቹንና ፡ የይፋቱንና ፡ የደዋሮን ፡ እስላሞችወታደርም ፡ አጃቢም ፡ ካህንም ፡ ሆኖ ፡ አብሮ ፡ ከመውጋት ፡ በቀር ፡ ትግሬም ፡ ጐጃምም ፡ ሸፍቶ ፡ አልተዋጋቸውም። የነዚህም ፡ አገር ፡ ሕዝቦች ፡ ከርሳቸው ፡ ወገን ፡ ለመሆን ፡ የሚያስገድደው ፡ የዘር ፡ የቋንቋ

፡ ይልቍንም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ የሚከበረው ፡ የሃይማኖት ፡ ኣንድነት ፡ ነው። አዳሎቹንና ፡ ይፋቶቹን ፡ እመሸፈት ፡ የሚያደርሳቸው ፡ የዘሩ ፡ ኣንድነት ፡ ሳይጠፋ ፡ የእስላምን ፡ ሃይማኖት ፡ በመያዛቸውና ፡ ክርስቲያንና ፡ እስላም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ እየተያየ ፡ አንዱ ፡ ያንዱን ፡ ሃይማኖት ፡ ለመደምሰስ ፡ ባለው ፡ ፍላጎት ፡ የተነሣ ፡ ነው።

፪ኛ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ዲስኵሩ ፡ መጨረሻ ፡ «... ፡ ስምዑ ፡ አምሳለ ፡ ዘእሜስል ፡ ለክሙ ፡ ሶበ ፡ ይትበኣሶ ፡ ማል ፡ ምስለ ፡ ግራ ፡ ማል ፡ የዓርቆሙ ፡ ጐንደረት ፡ ወሶበ ፡ ይትበኣሱ ፡ የላዕዳት ፡ ምስለ ፡ ጊአ ፡ የዓርቅዎሙ ፡ ዋልሳ ፡ አንትሙሂ ፡ ብክሙ ፡ በዝየ ፡ ዐርክ ፡ በዘይትሐመወክሙ ፡ ኣው ፡ ፍቍር ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ዕር ፡ ማዕከሌክሙ ፡ ወማዕከላ ፡ ተንባላት.... ያለውን ፡ እኹሁ ፡ ሊቅ ፡ አሳቡ ፡ በፍጹም ፡ አልገባኝም ፡ ብለው ፡ ራሳቸው ፡ ገልጸው ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ሳይተረጕሙ ፡ ዘለውታል። እኔም ፡ ራሴ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ግዕዙ ፡ የሚለውን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ለመተርጐም ፡ ከመሞከር ፡ በቀር ፡ ኣሳቡ ፡ በትክክል ፡ ስላልገባኝ ፡ ለአንባቢ ፡ ለማብራራት ፡ አልቻልሁም። ይኸም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በሊቃውንትና ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የተለመደ ፡ ተረትና ፡ ምሳሌ ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ ተረስቶ ፡ ለዛሬው ፡ ዘመን ፡ የማይገባ ፡ ይሆናል። ወይም ፡ ዛሬ ፡ የሚገባቸው ፡ ወገኖች ፡ ይኖሩ ፡ ይሆናል። እኔ ፡ ግን ፡ ለጊዜው ፡ የመሰለኝ ፡ ምናልባት ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ማል ፤ ግራ ፡ ማል ፤ ጐንደረት፣የላዕዳት፣ ፡ ጊዓ ፡ ዋልሳ ፤ የሚባሉ ፡ የጦር ፡ ወይም ፡ የነገድ ፡ ክፍሎች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚጣሉና ፡ የሚተራረቁ ፡ ወገኖችና ፡ ዘመዳሞች ፡ ይኖሩ ፡ ይሆናል። ከእነዚህም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ካደንደኛው ፡ ሲጣላ ፡ ሦስተኛው ፡ ያስታርቀዋል። እኔም ፡ ዜጎቼ ፡ ከሆናችሁት ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ዜጎቼ ፡ የነበሩት ፡ ከናንተ ፡ ቢጣሉ ፡ ድል ፡ ኣድርጌ ፡ አስታርቃችኋለሁ (አገናኝቼ ፡ አንድ ፡ ኣደርጋችኋለሁ) ማለቱ ፡ ይሆን? እናንተ ፡ ግን ፡ እናስ ፡ በእርሳችሁ ፡ ግማሻችሁ ፡ አገራችን ፡ እንመላስ ፡ ግማሻችሁ ፡ እንዋጋ ፡ ብላችሁ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ብትለያዩ ፡ «ብትጣሉ» ፡ ማስታረቍ ፡ ችግር ፡ ነውና ፡ አሳባችሁ ፡ አንድ ፡ ይሁን ፡ ማለቱ ፡ ይሆን? ወይስ ፡ ክርስቲያን ፡ ከክርስቲያን ፡ ቢጣላ ፡ ክርስቲያን ፡ ያስታርቀዋል ፡ ካላሸነፋችሁ ፡ በቀር ፡ ከእስላም ፡ ስትጣሉማነው ፡

ኣስታራቂያችሁ ፡ ማለቱ ፡ ይሆን? አይታወቅም። አሁን ፡ ግን ፡ ወደፊት ፡ ያለውን ፡ ጦርነት ፡ ከሚቀጥለው ፡ ምዕራፍ ፡ በቀጥታ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የሚለውን ፡ እንመልከት።

# ምዕራፍ ፡ ፲

## አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከአዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ ፪ተኛው ፡ ትልቅ ፡ ጦርንት።

«ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በሐምሌ ፡ በመዝመሪያው ፡ ቀን ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ከሠፈሩ ፡ ተነሥቶ ፡ ያስ ፡ የሚባለውን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሮ ፡ በሞራ ፡ ገሞራ ፡ አገር ፡ ደርሶ ፡ ሠፈር ፡ ኣደረገ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከክርስቲያን ፡ ወገን ፡ የነበረችና ፡ ወደነዚያ ፡ ተሸጣ ፡ ሄዳ ፡ የነበረች ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሠፈር ፡ መጣችና ፡ ‹እስላሞቹ ፡ ሰማይ ፡ ቀልቶ ፡ ኃይለኛ ፡ ዝናም ፡ ከነፋስ ፡ ጋራ ፡ ሲዘንም ፡ ክርስቲያኖችን ፡ እንጨርሳለን ፡ ብለው ፡ ኣስበዋል ፡ አለችው። በዚሁ ፡ ቀን ፡ የንጉሡ ፡ ድንኳንና ፡ ሠፈር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡ እስኪወድቅና ፡ እስኪበታተን ፡ ድረስ ፡ ኃይለኛ ፡ ዝናም ፡ ዘንሞ ፡ ነፋሱም ፡ ነፈሰ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ በፍርሐት ፡ ልቡ ፡ ታወከ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡ ፡ ኣዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ በሠፈር ፡ እየዞረ ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፡ « ፡ የክርስቲያን ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፡ ዝናምንና ፡ ነፋስን ፡ ብታዩ ፡ አትደንግጡ ፡ ይህ ፡ እስላሞችን ፡ ኣሸንፈን ፡ የምናባርርበት ፡ ከ**እግዚአብሔር** ፡ ዘንድ ፡ የመጣልን ፡ ምልክት ፡ ነው›ይኸንንም ፡ አዋጅ ፡ ማስነገሩ ፡ የሕዝቡን ፡ ልብ ፡ ለማጽናትና ፡ ፍርሐትን ፡ ከልባቸው ፡ ለማስወገድ ፡ ሲል ፡ ነው።

በዚችም ፡ ሌሊት ፡ በሐምሌ ፡ ፷ ፡ ቀን ፡ የሐዋርያት ፡ በዓል ፡ በዋለበት ፡ ቀን ፡ እስላሞቹ ፡ "ዕልዋን ፡ በሌሊት ፡ ወጥተው ፡ የንጉሡን ፡ ሠፈር ፡ ከበቡ ፡ የንጉሡ ፡ ዘበኞችም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ጮሁ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ከድንኳኑ ፡ ወጥቶ ፡ ጥሩንባ ፡ ኣስነፋ ፤ ሠራዊቱም ፡ እየተጫጫኸ ፡ ወደነሱ ፡ ሄደና ፡ ተዋግቶ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ መለሳቸው። በሌላ ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ንጉሥ

፡ ከዋናው ፡ ሠፈር ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ርቆ ፡ በሠፈረበት ፡ ቀን ፡ እስላሞቹ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ወዳለበት ፡ ሌሊት ፡ መጥተው ፡ ጦርነት ፡ ዠመሩ ፡ ሠራዊቱም ፡ ንጉሣችን ፡ መጥቶ ፡ እንዳያድነን ፡ ወዴት ፡ ሄደ ፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ዠመር ፤ ንጉሡ ፡ ይኸን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ «ጸንታችሁ ፡ ተዋጉ ፡ ብዬ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ነገርኋችሁ ፡ አሁንም ፡ እነዚህን ፡ ከሐዲዎች ፡ ጸንታችሁ ፡ ተዋጉዋቸው ፡ ንጉሡ ፡ ሠራዊቱን ፡ እየጠራ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ መላክ ፡ ልማድ ፡ ነበር ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ወደጦርነት ፡ ለመላክ ፡ ትጠሩኝ ፡ ዠመር ፡ ያለኔ ፡ መዋጋት ፡ አይቻላችሁምን ፡ ብሎ ፡ ተቆጣቸውና ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ገባ ፡ ተዋግቶም ፡ ጠላቶቹን ፡ አባረራቸው ፡ **እግዚአብሔር**ንም ፡ እያመሰገነ ፡ ወደድንኳኑ ፡ ገባ።

እንግዴህ ፡ በንጉሡና ፡ በሠራዊቱ ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ጦርነት ፡ የምነግራችሁን ፡ ስሙኝ (የዘመኑ ፡ ጸሐፊ ፡ ነው ፡ የሚገልጸው) ፡ ከግንቦት ፡ ወር ፡ እስከ ፡ ሐምሌ ፡ ወር ፡ ሌትም ፡ ቀንም ፡ ዕረፍት ፡ ኣልነበረም ፡ ከወገቡም ፡ ትጥቁን ፡ የፈታ ፡ የለም። ንጉሡም ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንደሌሎች ፡ ነገሥታት ፡ ሠራዊቱን ፡ ብቻ ፡ ወደጦርነት ፡ ሳይሰድ ፡ ራሱ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ሳይተኛ ፡ ትጥቁንም ፡ ሳይፈታ ፡ ጠንክሮ ፡ እየተዋጋ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ ኣሸንፎ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ወደአልደረሱበት ፡ አዳል ፡ ወደ ፡ ሚባለው ፡ አገር ፡ ይኸን ፡ በመሰለ ፡ ብርታት ፡ ደረሰ። በዚህ ፡ አገር ፡ ምሥራቁና ፡ ምዕራቡ ፡ አይታወቅም ፡ አገሩ (በተለይ) ደስ ፡ ወሀው ፡ ፋር ፡ ይባላል። በዚህም ፡ ሳሉ ፡ የታቦቱ ፡ ድንኳን ፡ በተተከለበት ፡ ዙሪያ ፡ ምሥራቁ ፡ በዚህ ፡ ነው ፡ የለም ፡ ምዕራቡ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምሥራቁ ፡ በዚህ ፡ በዙል ፡ ኣይደለም ፡ እየተባባሉ ፡ ካህናቱ ፡ ይጣሉ ፡ ነበር። በዚሁ ፡ በክረምቱ ፡ መካከል ፡ በረሃው ፡ እንደሳት ፡ ሰውንም ፡ እንስሳውንም ፡ ያቃጥል ፡ ነበር። ወሀም ፡ የለም ፡ ቢኖርም ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ የተቆፈረ ፡ በጉድጓድ ፡ የሚገኝ ፡ የቆሸሸ ፡ ወሀ ፡ ነው ፡ እንጅየጠራ ፡ የሚወርድ ፡ ምንጭ ፡ የለም ፡ ይኸውም ፡ ሆኖ ፡ ያው ፡ የሚጠጣው ፡ እንደድርጎ ፡ በልክ ፡ እየተሰጠ ፡ ነው። ድንጋዩም ፡ እንደሾህ ፡ ይዋጋል። የዚህም ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እግራቸውን ፡ ወደላይ ፡ ራሳቸውን ፡ ወደታች ፡ ዘቅዝቀው ፡ እንደ ፡ እግር ፡ በእጃቸው ፡ ይሮጣሉ። እንደዚህም ፡ እየሆነሁልጊዜ ፡ ሌሊት ፡ እየመጡ ፡ የንጉሡን ፡ ጦር ፡ ይወጉ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡

በ**እግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ እየተሸነፉ ፡ ይመለሳሉ። ... ፡ ደግሞ ፡ ንጉሥ ፡ ዓምደጽዮንን ፡ የወጉትን ፡ የነዚህን ፡ ሃይማኖት ፡ የሌላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ጦርነት ፡ የምነግራችሁን ፡ ስሙኝ። የነርሱንም ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ ሠራዊትን ፡ ባንድነት ፡ አሳድሞ ፡ የተነሣው ፡ ነገሥታቱም ፡ መኳንንቱም ፡ በሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ አምሳል ፡ እንደ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ የሚያከብሩት ፡ መጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ስልሕ ፡ የሹመት ፡ ስሙ ፡ ቃዚ (ሳልህ ፡ ቃዲ ፡ ማለቱ ፡ ነው) ፡ ይባላል። ከርሱም ፡ ጋር ፡ ለዚህ ፡ ጦርነት ፡ አብረው ፡ የተሠለፉት።

| | |
|---|---|
| የአዳል ፡ | ንጉሥ፡ |
| የሞራ ፡ | » |
| የበከላ ፡ | » |
| የሀገራ ፡ | » |
| የፈድሴ ፡ | » |
| የግዳድ ፡ | » |
| የነገብ ፡ | » |
| የኰባ ፡ | » |
| የሐርላ ፡ | » |
| የሆባት ፡ | » |
| የተርሣ | » |
| የእይሞ ፡ | » |
| የእልብሮ ፡ | » |
| የዜልኣ ፡ | » |
| የእስቲ ፡ | » |
| የደዋሮ ፡ | ከገበረና ፡ በንጉሡ ፡ ፈቃድ ፡ ከተሾመ ፡ በኋላ ፡ የሸፈተውን ፡ ገማልዲንን ፡ ማለቱ ፡ ይሆናል፡ |
| ፱ ፡ የድልሆነ ፡ | መኳንንት |

፰ ፡ የወርጋር ፡ »
፲፪ ፡ የጋሳ ፡ »
፯ ፡ የሐርጎል ፡ »
፬ ፡ የከሶ ፡ »
፫ ፡ የስሶጌ ፡ መኳንንት
፭ ፡ የተአረካ ፡ »
፫ ፡ የእድርገል ፡ »
፫ ፡ የወደኣና፡ »
፬ ፡ የኮሶ ፡ »
፭ ፡ የሚታሎት »
፫ ፡ የጢርከቱ ፡ »
፫ ፡ የሀገራ ፡ »
፱ ፡ የአዳል ፡ »
፻፲ ፡ የልሕን ፡ »
፫ ፡ የዝቡራ ፡ »
፲፮ ፡ የዘፈጊ ፡ »
፫ ፡ የስልጠጊ ፡ »
፫ ፡ የወርጡጥ ፡ »
፭ ፡ የዝርዋስጌ ፡ »
፲ ፡ የትማኬ ፡ »
፲፪ ፡ የተከው ፡ »
፭ ፡ የጐዓት ፡ »
፫ ፡ የጣይዲካ ፡ »
፭ ፡ የእፎልኣይ ፡ »
፲፪ ፡ የዝዳ ፡ »
፭ ፡ የመገረት ፡ »

| | |
|---|---|
| ፫ ፡ የኵምግዳይ ፡ | » |
| ፩ሺ ፡ የከሮሮ ፡ | » |
| ፰ ፡ የጊቶ ፡ | » |
| ፬ ፡ የአጥቂጥ ፡ | » |
| ፩ ፡ የግሙሕጋር ፡ | መኰንን ፡ |
| ፩ ፡ የጕሪ ፡ | » |
| ፩ ፡ የጋቱር ፡ | » |
| ፩ ፡ የኣዘዞ ፡ | » |
| ፩ ፡ የስሐና ፡ | » |
| ፩ ፡ የገዝኣ ፡ | » |
| ፩ ፡ የላዕላይ ፡ ዋዝ | መኰንን ፡ |
| ፩ ፡ የታሕታይ ፡ ዋዝ | » |
| ፩ ፡ የሐርያ ፡ | » |
| ፩ ፡ የሕድጕኤል ፡ | » |
| ፩ ፡ የወገረጸላ ፡ | » |
| ፩ ፡ የውርሳግ ፡ | » |
| ፩ ፡ የድን ፡ | » |
| ፩ ፡ የገመራር ፡ | » |
| ፩ ፡ የሚላዕ ፡ | » |
| ፩ ፡ የለግ ፡ | » |
| ፩ ፡ የታሕታይ ፡ ሐስያ፡ | » |
| ፩ ፡ የላዕላይ ፡ ሐስያ ፡ | » |
| ፩ ፡ የዞት ፡ | » |
| ፩ ፡ የሐዶቂር ፡ | » |
| ፩ ፡ የክርክር ፡ | » |
| ፀ ፡ የመከይ ፡ | » |

፩ ፡ የርግሬን ፡ »
፩ ፡ የመግዳሬ ፡ »
፩ ፡ የእድርስኰ ፡ »
፩ ፡ የሆበት ፡ »
፩ ፡ የሕትፊ ፡ »
፩ ፡ የኣተርሖ ፡ »
፩ ፡ የሊት ፡ »
፩ ፡ የሶት ፡ »
፩ ፡ የድጕ ፡ »
፩ ፡ የኰርሆ »
፩ ፡ የዝገማ ፡ »
፩ ፡ የዘተራ ፡ »
፩ ፡ የመየግብ ፡ »
፩ ፡ የጋዛከ ፡ »
፩ ፡ የዛሑየ ፡ »
፩ ፡ የገልጣት ፡ »
፩ ፡ የይግዓመድ ፡ »
፩ ፡ የዢጐርም ፡ »
፩ ፡ የነጋኤን ፡ »
፩ ፡ የአትጕት ፡ »
፩ ፡ የወሪ ፡ »
፩ ፡ የወረሶ ፡ »
፩ ፡ የሂግራ ፡ መኳንንት
፫ ፡ የስረር ፡ »
፰ ፡ የጠርነቦ ፡ »
፬ ፡ የአደራ »

፪ ፡ የኪያሪ ፡ »
፩ ፡ የሞራ ፡ መኰንን ፡
፳ ፡ የላዕላይ ፡ በከላ ፡ መኳንንት
፪ ፡ የታሕታይ ፡ በከላ ፡ »
፫ ፡ የገበላ ፡ »
፫ ፡ የግደፊም ፡ ጋድ ፡ »
፯ ፡ የቀረሞሌ ፡ »
፱ ፡ የጋስኵር ፡ »
፩ ፡ የማሉኬ ፡ መኰንን ፡
፩ ፡ የዘጋሚካስ ፡ »
፩ ፡ የይደጎል ፡ ኣርጊ ፡ »
፩ ፡ የአዊላ ፡ »
፩ ፡ የደቢሆርመይ ፡ »
፩ ፡ የደቢሐዳላ ፡ »
፩ ፡ የጠይቢት ፡ »
፩ ፡ የዚባ ፡ »
፩ ፡ የጠባ ፡ »
፩ ፡ የገመኣላጕባ ፡ »
፩ ፡ የአርጊ ፡ »
፫ ፡ የመርመራ ፡ መኳንንት
፫ ፡ የከልሴር ፡ »
፩ ፡ የጕሬ ፡ መኰንን ፡
፩ ፡ የሰንዲዘሐዘር ፡ »
፪ ፡ የተለግ ፡ መኳንንት
፲ ፡ የእረጠ ፡ »
፩ ፡ የማሎ ፡ መኰንን ፡
፫ ፡ የእሩብ ፡ መኳንንት

፫ ፡ የመኳ ፡ ተልፋል ፡ »
፱ ፡ የኣግዩር ፡ »
፲ ፡ የብላሳ ፡ »
፯ ፡ የሔዊ ፡ »
፲ ፡ የአፈር ፡ ዳቦ ፡ »
፬ ፡ የአገቦት ፡ »
፰ ፡ የኣድቢጊ ፡ »
፩ ፡ የዘረብኪ ፡ መኰንን ፡
፩ ፡ የዘርውስጊ ፡ »
፩ ፡ የቈሕብር ፡ »
፩ ፡ የይጦሮቅጊ ፡ »
፩ ፡ የዝጕዕ ፡ »
፩ ፡ የዝውቀይ ፡ »
፩ ፡ የዝዊ ፡ »
፩ ፡ የአውሶ ፡ »
፩ ፡ የሐርገየ ፡ »
፩ ፡ የኣያዝ ፡ »
፩ ፡ የመቀር ፡ »
፩ ፡ የስሪ ፡ »
፩ ፡ የመቆዝ ፡ »
፫ ፡ የእስጌር ፡ መኳንንት
፩ ፡ የየከባይጊ ፡ መኰንን ፡
፩ ፡ የኣይቲን ፡ »
፩ ፡ የእስላል ፡ »
፩ ፡ የጕርዛልጊ ፡ »
፲፪ ፡ የግራጊ ፡ መኳንንት
፲ ፡ የጋልፍኣኪ ፡ »

፫ ፡ የነጌቤሄ ፡ ጌራ ፡ »
፩ ፡ የመካይጋር ፡ መኰንን ፡
፩ ፡ የነገብደሐላ ፡ »
፩ ፡ የተርሳ ፡ »
፬ ፡ የከንመነጋ ፡ መኳንንት
፫ ፡ የዝእሙልጊ ፡ »
፩ ፡ የዘአብረስጊ ፡ መኰንን ፡
፩ ፡ የዱልጊ ፡ »
፩ ፡ የመርጦላት ፡ »
፩ ፡ የስየ ፡ »
፩ ፡ የጻፍረታ »
፫ ፡ የትሙዝ ፡ መኳንንት
፩ ፡ የተቦኪ ፡ መኰንን ፡
፩ ፡ የታሕታይ ፡ ጦሳ ፡ »
፩ ፡ የእኬላ ፡ »
፩ ፡ የጠርሐሳብ ፡ »
፫ ፡ የዝፍግጊ ፡ መኳንንት
፬ ፡ የስኮት ፡ »
፲ ፡ የሐረር ፡ »
፫ ፡ የዘቢልጊ ፡ »
፩ ፡ የመዳየት ፡ መኰንን ፡
፩ ፡ የብር ፡ »
፩ ፡ የሜትራ ፡ »
፩ ፡ የፍጹስፋራ ፡ »
፩ ፡ የስጣ »
፪ ፡ የበረጣ ፡ መኳንንት
፲ ፡ የጠሰና ፡ »

፪ ፡ የጐሶት ፡ »

፪ ፡ የአቴርገረዝ ፡ »

፫ ፡ የሚኮስ ፡ »

፪ ፡ የስርወዴ ፡ »

፰ ፡ የወጣ ፡ »

፯ ፡ የእገላ ፡ ፤ »

፫ ፡ የኤልሳዕ ፡ »

፩ ፡ የምጋ ፡ መኰንን ፡

፩ ፡ የጋሶር »

፩ ፡ የዘላብ ፡ »

፩ ፡ የግፌ ፡ »

፫ ፡ የሰበከ ፡ መኳንንት

፩ ፡ የወኪል ፡ መኰንን ፡

፩ ፡ የዱለም ፡ »

፩ ፡ የእላልቆባ ፡ »

፩ ፡ የጕላን ፡ »

፩ ፡ የንፊላ ፡ »

፩ ፡ የዘን ፡ »

፩ ፡ የሐፊ ፡ »

፩ ፡ የኤላት ፡ »

<u>የዘላን ፡ መኳንንት ፥</u>

፩ ፡ የእጕርባ መኰንን ፡

፩ ፡ የምጥሐና ፡ »

፩ ፡ የፍቅራሚራ ፡ »

፩ ፡ የደላን ፡ »

፩ ፡ የአይፍሎ ፡ »

፩ ፡ የግወልጥወልጥ ፡ »
፩ ፡ የወተልጣ ፡ »
፩ ፡ የድንኰዕሉ ፡ »
፩ ፡ የኣከርሶ ፡ »

## የገበል ፡ መኳንንት ፥

፩ ፡ የብልእምባ ፡ መኰንን ፡
፩ ፡ የመይረባስ ፡ »
፩ ፡ የሔርባ ፡ »
፩ ፡ የአይዶም ፡ »
፩ ፡ የዘርሕ ፡ »
፩ ፡ የሐዙማ ፡ »
፩ ፡ የኣዌሳ ፡ »
፩ ፡ የሀበንዘገል ፡ »
፩ ፡ የበልሐከ ፡ »
፩ ፡ የአላጦር ፡ »
፩ ፡ የኣሉላ ፡ »
፩ ፡ የገር ፡ በአዶ ፡ »

የነዚህ ፡ ነገሥታትና ፡ የመኳንንት ፡ ቍጥር ፡ ዘላንና ፡ ገበል ፡ ሳይጨመር ፡ ፪ሺ፫፻፳፪ ፡ ነው። መስጊዳቸው ፡ የዘላንና ፡ የገበል ፡ ሳይጨመር ፡ ፲፪ሺ፰ ፡ ነው።

ከነዚህም ፡ ጋር ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ ንጉሡ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከእሥራት ፡ ፈትቶ ፡ በወንድሙ ፡ በሰብረዲን ፡ እግር ፡ የሾመው ፡ ግማለዲን (ገማል ፡ አድ ፡ ዲን) ከነዚሁ ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ ጋር ፡ በምክር ፡ ተባብሮ ፡ ከንጉሡ ፡ ሸፈተ። ወዲያውም ፡ ለኣዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ላከበት ፡ ሰላም ፡ ላንተ ፡ ይሁን ፡ ላታላቅነትህም (ለዕበይከካ ፡ ምክሬን ፡ ስማ ፡ ነገሬንም ፡ አድምጥ

፤ እነሆ ፡ የክርስቲያኑ ፡ ንጉሥ ፡ ሊወጣባት ፡ በማይቻለው ፡ በጠባብ ፡ መንገድ ፡ መጣ። አንተ ፡ ግን ፡ ለራስህ ፡ ከነዚህ ፡ ከሁለቱ ፡ መንገዶች ፡ አንደኛውን ፡ ምረጥ። ግብርና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ትሰጠው ፡ እንደሆነ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ለመስጠት ፡ ወደዚህ ፡ የምትሰጠው ፡ ነገር ፡ ያለህ ፡ እንደሆነ ፡ ሚስትህንና ፡ ልጆችህን ፡ ያለህን ፡ ሁሉ ፡ ስጠው። ከአንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ አባቶችህ ፡ ያላደረጉትን ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ያደረግህ ፡ እንደሆነ ፡ ከኣንተና ፡ ከዘር ፡ ዘርህ ፡ ለዘላለም ፡ ባርነት ፡ አይወጣም።

አሁን ፡ ግን ፡ የምትሠራውን ፡ በጥበብ ፡ አስተውል። በሰይፍ ፤ በቀስት ፡ በጋሻበጦር ፤ ባንካሴ ፤ (ኣርማህ) በብረትና ፡ በዱላ ፡ የሚዋጉትን ፡ ሠራዊትህን ፡ ሰብስብ። እኔም ፡ የእግረኛና ፡ የፈረሰኛው ፡ ወታደሬን ፡ ይዤ ፡ እመጣና ፡ ዙሪያውን ፡ ከበን ፡ ኣንድም ፡ ሳናስተርፍ ፡ እንጨርሰዋለን። »

የአዳል ፡ ንጉሥ ፡ ይኸን ፡ ሰምቶ ፡ ነው ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ ከነሕዝባቸው ፡ የሰበሰባቸው። እነዚህንም ፡ ለመሰብሰብ ፡ ኣራት ፡ ወር ፡ ፈጀበት ፤ **እግዚአብሔር** ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ሊቆጥረው ፡ የማይቻለውን ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሠራዊቱን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በነፍሱ ፡ ኰራ ፡ ፈርያን ፡ የግብፁ ፡ ንጉሥ ፡ በሙሴ ፡ ላይ ፡ በሰይፍ ፡ እገድላለሁ ፡ በእጄ ፡ እፈርድበታለሁ ፡ ነፍሴንም ፡ በምርኮ ፡ አጸግባታለሁ ፡ እንዳላው ፡ ሰናክሬምም ፡ በውኑ ፡ ከእጄ ፡ የሚያድን ፡ አምላክ ፡ አለህን ፡ ብሎ ፡ በሕዝቅያስ ፡ ላይ ፡ እንደኰራበት ፡ ይኸም ፡ የሰይጣን ፡ ወዳጅ ፡ የሆነው ፡ ከሐዲ ፡ በ**ክርስቶስ** ፡ ስም ፡ ላይ ፡ ኰራ (ታበየ) የ**እግዚአብሔር** ፡ ልጅ ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ያላበትን ፡ የድንኳን ፡ መቅደስ (ደብተራ ፡ መርጡል?) ለራሴ ፡ መስጊድ ፡ ኣደርገዋለሁ። በውስጡ ፡ የሚገኘውንም ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ የተቀደሱትንም ፡ አልባሳት ፡ ለቤቴ ፡ አደርገዋለሁ ፡ ክርስቲያኖቹንም ፡ ከነንጉሣቸው ፡ አጥፍቼ ፡ ያጠራቀሙትን ፡ ገንዘብ ፡ ግመልና ፡ ከብት ፡ ለሠራዊቴ ፡ ኣካፍለዋለሁ። ንግሥት (እቴጌ) ዣን ፡ መንሣንና ፡ ዕቍባቶቹን ፡ ሴቶቹንም ፡ ልጆቹንም ፡ እህል ፡ ፈጭ ፡ አደርጋቸዋለሁ ፡ ኣለ።

ይኽንን ፡ ካላ ፡ በኋላ ፡ ተነሡ ፡ የምርኮው ፡ ገንዘብ ፡ ለክፍያ ፡ እንዳያንሰን ፡ የይፋቱ ፡ ንጉሥ (ገማልዲንቃ ፡ ሳይመጣ ፡ ብቻችንን ፡ የክርስቲያኑን ፡ ንጉሥ ፡ እንውጋው ፡ ብሎ ፡ ለነገሥታቱና ፡ ለመኳንንቱ ፡ ለሠራዊቱም ፡ ሁሉ ፡ ነገራቸው…ስለዚህ ፡ በዚሁ ፡ ተስማምተው ፡ የአዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ እነዚያን ፡ ሁሉ ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ ይዞ ፡ መጥቶ ፡ ሐምሌ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ዓርብ ፡ ሠራዊቱ ፡ በሌለበት ፡ ሰዓት ፡ የዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ ሠፈር ፡ ከበቡ።

የንጉሡ ፡ የዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ሠራዊት ፡

ቀስተ ፡ ንህብ ፡ አለቃቸው ፡ ሰመይሸሐል ፡

ተኵላ (ትርጒሙ ፡ ጽኑዓን) አለቃቸው ፡ ሽዋ ፡ ረዓድ ፡

ኮረም ፡ የሚባሉት ፡ የግራና ፡ የቀኝ ፡ ፈረሰኞች ፡ ኣለቆቻቸው ፡ ድምአላና ፡ ድግና።

ባርያ ፡ ኣለቃቸው ፡ አንጎታይ ፡

ሐረብ ፡ ጎንዳ ፡ አለቃቸው ፡ አወፌ ፡ ወገዝል ፡

ፀዋርያነ ፡ ወርመት ፡ ዓቢያን ፡ አለቃቸው ፡ ዘአዶናዊ ፡

ፀዋርያነ ፡ ንገሬ (አንግሬ) አለቃቸው ፡ ኣምላክ ፡ ጽንሐ ፡

የቀኝና ፡ የግራ ፡ ፀዋርያነ ፡ ወርመት ፡ አለቆቻቸው ፡ ትዕይንተይ ፡ ና ፡ ሐግተጐነይ።

ጐዣም ፡ (ጐጃም)፡የግራና፡የቀኝ፡አለቆቻቸው፡ዋድላይ ፡ ና ፡ ሐርበ ፡ ኢገራ ፡ (ሐርበኢገራ)።

ዳሞት ፡ አለቃቸው ፡ ማርከሰወይ (ማርከስወይ)

ፀዋርያነ ፡ ኣስይፍት (ሰይፈ ፡ ዣግሬ) አለቃቸው ፡ ሐርብ ፡ ኣስምዓ ፡

ፀዋርያነ ፡ መንበር (ወምበር ፡ ተሸካሚ) ፡ አለቃቸው ፡ እኪንዕዱ ፡ አኪንኢዱ።

ፀዋርያነ ፡ መነሳንስት ፡(ጭራ፡ያዥ፡) ፡ ኣለቃቸው ፡ ብሕት ፡ ኣከለ (ብሕት፡ ለክላ)።

ጐጃም ፡ ፈረሰኛ ፡ አለቃቸው ፡ ወድም ፡

እለ፡ይፀውሩ፡ወልታ ፡ (ሠራዊት፡ፀሊማን) (ድንኳን ፡ ተሸካሚ) አለቃቸው ፡ ጉድፈይ።

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የንጉሥ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የቀኝና ፡ የግራ ፡ የፊትና ፡ የኋላ ፡ ጦር ፡ የአምሐራ ፡ የሸዋ ፡ የጐጃም ፡ የዳሞት ፡ ሠራዊት ፡ ለውጊያ ፡ የተዘጋጁ ፡ በብርና ፡ በወርቅ ፡ በሸልማት ፡ ያስጌጣቸው ፡ ቀስተኛና ፡ ጦረኛ ፡ የእግረኛና ፡ የፈረሰኛ ፡ ወታደሮች ፡ ናቸው። እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ ወታደሮች ፡ ወደጦርነት ፡ በገቡጊዜ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ነቢይ ፡ የመላእክትን ፡ ድምፅና ፡ ጩኸታቸውን ፡ ሰማሁ ፡ እንዳለውእንደአሞራ ፡ የሚበሩእንደ ፡ ሚዳቋ ፡ የሚርጡ ፤ እግራቸው ፡ እንደናዳ ፡ ድንጋይ ፡ የሚሽከረከርናቸው። እነርሱም ፡ ለዚህ ፡ ጦርነት ፡ ንጉሡ ፡ እምነቱን ፡ የጣላባቸው ፡ ስለሆነ ፡ በሌላ ፡ ክፍል ፡ እንዲዋጉ ፡ ልኳቸው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በአጠገቡ ፡ ኣልነበሩም። በዚያው ፡ በየሄዱበት ፡ አገር ፡ ከሌሎች ፡ አረማያውን ፡ ጋር ፡ ይዋጉ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በንጉሡ ፡ በኵል ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ አያውቀኊም ፡ ነበር። ግን ፡ ንጉሡ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አሞት ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ አልጋው ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር። ከሰባት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ኣልበላም ፡ አልጠጣም። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በአጠገቡ ፡ ያለውን ፡ ዘና ፡ የማኑ ፡ የሚባለውን ፡ ሊቀ ፡ ንዑሳን (የልፍኝ ፡ አሽከር ፡ አለቃ) ሂድና ፡ ለውሾች ፡ የሚሰጥ ፡ ሥጋ ፡ አውሬ ፡ ኣድነህ ፡ አምጣ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ፡ እርሱም ፡ አውሬ ፡ ፍለጋ ፡ ሲጓዝ ፡ የአዳሎቹ ፡ ጦር ፡ ሲመጣ ፡ አየ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኣደኑን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ «ከመላው ፡ ሠራዊትህ ፡ የሚበልጥ ፡ ጦርእነሆ ፡ መጣ ፤ ስለዚህ ፡ ወዳንተ ፡ ተመልሰን ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ብንሞት ፡ ይሻላል” ብሎ ፡ ላከ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ይኸንኑ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሌሎች ፡ ፈረሰኞች ፡ ሄደው ፡ አይተው ፡ የነዚያን ፡ የጦር ፡ ብዛት ፡ ሰልለው ፡ እንዲመለሱ ፡ ላካቸው ፡ እነርሱም ፡ ሄደው ፡ ሰማይን ፡ እንደሚሸፍን ፡ ጉም ፡ መሬትን ፡ ሁሉ ፡ እንደሚያለብስ ፡ አንበጣ ፡ የመሰለውን ፡ የነዚያን ፡ ጦር ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ዓይናቸው ፡ ጨለመ ፡ ልባቸውም ፡ ጠፋ (ደነገጡ) ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ተመልሰው ፡ እንደዚህ ፡ አሉት ፡ የነዚህን ፡ ሠራዊት ፡ ብዛት ፡ መሬት ፡ ሁሉሊሸከመው ፡ አይችልም ፡ ከወሰን ፡ እስከ ፡ ወሰን ፡ ዝምሮ ፡ የመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሠራዊት ፡ ትልቁኊም ፡ ቲንሹም ፡ ተሰብስቦ ፡ ቢመጣ ፡ እነዚህን ፡ ተዋግተን ፡ መመለስ ፡ አንችልም። »

ይኸን ፡ ንግግር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከመኝታው ፡ ተነሥቶ ፡ እንደታመመና ፡ እንደደከመ ፡ ወደውጭ ፡ ሊወጣ ፡ ፈለገ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከሕመሙ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ እግሩም ፡ መቆም ፡ ወገቡንም ፡ መታጠቅ ፡ ኣቃተውና ፡ ወደቀ ፡ ከዚያ ፡ አሽከሮቹ ፡ ኣንሥተው ፡ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ አስታጠቍትና ፡ እየተንገደገደ ፡ ከሠፈሩ ፡ ወጣ። ሁለቱ ፡ ንግሥቶች (ሁለቱ ፡ ሚስቶች ፡ ማለቱ ፡ ነው) በዕንባ ፡ እየተላቀሱ ፡ እየተከተሉ ፡ እንደዚህ ፡ አሉት ፡ እንደቀድሞ ፡ የሚሮጥ ፡ እግር ፤ ቀስት ፡ ደግኖ ፡ የሚወረውርና ፡ ጦርና ፡ ጋሻ ፡ የሚይዝ ፡ እጅ ፡ አለህን? ፈረስ ፡ ለመውጣትስ ፡ ነፍስህ (ሰውነትህ) ደክማ ፡ የለምን? » ፡ ንጉሡም ፡ እኔ ፡ እንደሴት (እድንኳን ፡ ውስጥ?) ኣልሞትም ፡ እንደ ፡ ተጋዳይ ፡ አርበኛ ፡ አማሚትን ፡ አውቃለሁ ፡ ብሎ ፡ መንገዱን ፡ ይቀጥል ፡ ዝመር። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ታናሽቱ ፡ ንግሥት ፡ ለታላቂቱ ፡ ንግሥት (እቴጌ) ስለ**ክርስቶስ** ፡ ብለሽ ፡ ያዥው ፡ እንጂ ፡ አትልቀቂው ፡ ብትላት ፡ ታላቂቱ ፡ "አረመኔዎቹ ፡ እመኝታው ፡ ሊገድሉት ፡ ሲመጡ ፡ እይዘዋለሁን? አላደርገውም ፡ ነገርግን ፡ ይሂድና ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ ይሙት" እያለቻት ፡ ሁለቱም ፡ ንጉሡን ፡ ሁለተኛ ፡ እንደማያገኙት ፡ ተስፋ ፡ ቆርጠው ፡ ሲላቀሱ ፡ ንጉሡ ፡ ፊቱን ፡ ወደነሱ ፡ አዞሮ« ፡ ሂዱ ፡ ግቡ ፡ አትከተሉኝ ፡ አላቸውና ፡ እምነቱን ፡ በሚገድልና ፡ በሚያድን ፡ በሚቀጣና ፡ ይቅር ፡ በሚል.... በ**እግዚአብሔር** ፡ አድርጎ ፡ ሄደ.... ሕመሙንም ፡ ድካሙንም ፡ ረሳው። ሁለት ፡ አፍ ፡ ጸሎትና ፡ ስለት» ፡ የሆነውን ፡ ሰይፍ ፡ ታጠቀ......ካህናቱን ፡ ወደ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ጸልዩ ፡ እኔንም ፡ በጸሎታችሁ ፡ ኣትርሱኝ ፡ ኣለና ፡ ከሠፈር ፡ ወደውጭ ፡ ወጣ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ታላቂቱ ፡ ንግሥት ፡ ተከትላ ፡ ስትወጣ ፡ የቀሩትም ፡ ንግሥትና ፡ ዕቍባት ፡ ተከታትለው ፡ እየተመለከቱ ፡ ሲያዩ ፡ ትንሷንግሥት ፡ ለትልቂቱ ፡ ልጆቼን ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ላድርጋቸው ፡ ታቦቱ ፡ ወዳላበት ፡ ድንኳን ፡ እያየ ፡ እንዲጠብቃቸው ፡ ልተዋቸውን ፡ ወይስ ፡ ወደ ፡ ማኅፀኔ ፡ መልሼ ፡ ልዋጣቸውን ፡ ወይስ ፡ ከነሕይወታቸው ፡ መልሼ ፡ እመሬት ፡ ልቅበራቸውን? .... ወይስ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ እንዲሞቱ ፡ ላምጣቸውን? » ፡ ብትላት ፡ ታላቂቱ ፡ እዚህ ፡ ብታመጪቸው ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ይልቅስ ፡ የ**እግዚአብሔር** ፡ ልጅ ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ውሰጃቸውና ፡ በዚያ ፡ እነዚሁ ፡ ኣረማውያኑ ፡

ይግደሉዋቸው ፡ ብትላት ፡ ወደዚያ ፡ ወሰደቻቸውና ፡ በታቦቱ ፡ እግር ፡ አስቀመጠቻቸው።

ንግሥቶችና ፡ ዕቀባቶች ፡ ንጉሥ ፡ ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ መጥፋቱ ፡ ነው ፡ እንግዴህ ፡ ወዮልን” እያሉ ፡ መራራ ፡ ለቅሶ ፡ አላቀሱ። ንግሥት ፡ ዣን ፡ መንገሣም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጣ ፡ እንደዚህ ፡ ብላ ፡ ጸለየች ፡ አእግዚእየ ፡ አምላከ ፡ ፩ኤል ፡ ቅዱሳን ፡ ገባሬ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ….20ኤልን ፡ ከፈርዖን ፡ ሶስናን ፡ ከዳኞች ፡ እጅ ፡ ዳንኤልን ፡ ከአንበሳ ፡ አፍ ፡ የአዳንካቸው ፡ ሁሉን ፡ ማድረግ ፡ ይቻልሃል ፡ ኣሁንም ፡ የባሪያዪቱን ፡ ለቅሶና ፡ ጩኸት ፡ ስማ። ይኸን ፡ ባርያህን ፡ ያነገሥኸው ፡ ኣንተ ፡ አይደለህምን ፡ ሁሉን ፡ ሰጭ ፡ ሁሉን ፡ ነሺ ፡ አንተ ፡ አይደለህምን ፡ ለሩሜ ፡ የሰጠኸው ፡ እግር ፡ ለመዳሰሻ ፡ የሰጠኸው ፡ እጅ ፡ በበሽታው ፡ ተቀጠቀጠ። ሞቱን ፡ እንኳን ፡ እንዳያዩ ፡ በፊቱና ፡ በኋላው ፡ የሚሰለፉት ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ የሉም። በኃጢኣቱ ፡ ዛሬ ፡ ልትቀጣው ፡ ነውን ፡ የሰውን ፡ ኃጢኣት ፡ ከተቆጣጠርህ ፡ አንድም ፡ የሚድን ፡ አይገኝም ፡ " ፡ ስለዚህ ፡ በፊያህን ፡ ከነዚህ ፡ ከአረማውያኑ ፡ አድነው ፡ ልትገድለውፈልገህ ፡ እንዴuነ ፡ አንተው ፡ በእጅህ ፡ ግደለው ፡ እንጂ ፡ በነዚህ ፡ ስምህን ፡ በማያውቁት ፡ በኣረማውያኑ ፡ እጅ ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጠው ፡ ሥጋህንና ፡ ደምህን ፡ አስብ ፡ እንጂ ፡ የርሱን ፡ ኃጢአትና ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ አትመልከት ፡ የሰውን (የኃጢአተኛውን) ድኅነቱን (መመለሱን) እንጂ ፡ ሞቱን ፡ ኣትፈልግም። »

ይኸን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጣ ፡ ከጸለየች ፡ በኋላ ፡ ፊቷን ፡ እርሱ ፡ ወዳለበት ፡ አዙራ ፡ እርሱን ፡ እያየች ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ አለች ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ፍላፃ ፡ ይሆን ፡ በላይህ ፡ የሚወድቀው ፡ እንዴት ፡ ያለው ፡ ጦር ፡ ነው ፡ የሚወጋህ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰይፍ ፡ ይሆን ፡ የሚመታህ ፡ ሞትህ ፡ ከመኳንንቶችህና ፡ ከሠራዊትህ ፡ ጋር ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ስላንተ ፡ ምንም ፡ አላዝንም ፡ ነበር።

ኣሁን ፡ ግን ፡ ስላንተ ፡ የማዝነውና ፡ የማለቅሰው ፡ የሚረዳህ ፡ ሳይኖር ፡ ብቻህን ፡ በመሆንህ ፡ ነው። ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ስትሄድ ፡ ሁለመናህን ፡

እስም ፡ ነበር ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ እጅህንም ፡ እግርህንም... ፡ ዓይንህንም ፡ አልሳምሁም ፡ ወየው ፡ ለኔ ፡ ሞትህን ፡ ሳላይ ፡ እንድሞት ፡ ዛሬ ፡ ለኔ ፡ ሞትን ፡ ማን ፡ በሰጠኝ ፡ › ፡ እያለች ፡ ዕንባዋን ፡ በጉንጫ ፡ ላይ ፡ እያወረደ። ስታለቅስ ፡ ሴቱም ፡ ሽማግሌውም ፡ ሕፃኑም ፡ ወጣቱም ፡ ከርሷ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ኣመድ ፡ እየበተኑ ፡ አለቀሱ ፡ .... ንጉሡም ፡ ባለበት ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጦ ፡ እጆቹን ፡ ዘርግቶ ፡ መሐፊው ፡ ኃያሉ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ሆይ...ሕዝብህን ፡ በኃጢአቱ ፡ ምክንያት ፡ አታጥፋው) ነገር ፡ ግን ፡ በምሕረትህ ፡ ማረው......እኔን ፡ ግን ፡ ደስ ፡ የሚልህን ፡ አድርግብኝ ፡ አለ። ይኸንንም ፡ ሁሉ ፡ የጸለየው ፡ ወንጌል ፡ መልካም ፡ እረኛ ፡ ስላ ፡ በጐቹ ፡ ራሱን ፡ ይለውጣል ፡ እንዳለው ፡ ለሕዝቡ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለራሱ ፡ ኣይደለም።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የአረመኔዎቹ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ሰይፋቸውን ፡ እንደመብረቅ ፡ እያብለጨለጩ ፡ ቀስታቸውን ፡ ደግነው ፡ ጦርና ፡ የብረት ፡ አንካሴያቸውን ፡ በእጃቸው ፡ እንደያዙ ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ በርክተው ፡ በክረምት ፡ ሰማይን ፡ እንደ ፡ ሚሸፍን ፡ ደመና ፡ መስለው ፡ ድምጻቸው ፡ ነፋስ ፡ እንዳወከው ፡ የባሕርን ፡ ማዕበል ፡ ቃላቸው ፡ በዝናም ፡ ጊዜ ፡ እንደሚጮህ ፡ መብረቅና ፡ ነጐድጓድ ፡ ሆኖ ፡ በጩኸታቸው ፡ መሬትን ፡ ተራራን ፡ እያነቃነቁ ፡ መጡ። አንባቢ ፡ ሆይ ፡ የምነግርህን ፡ ሁሉከንቱ (ተረት) ሳታስመስልብኝ ፡ ስማኝ ፤ ለኔ ፡ እንደ ፡ መሰለኝ ፡ እነሱ ፡ ሲሮጡ ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ዛፉም ፡ ተራራውም ፡ ጨረቃውም ፡ ኮከቡዎ ፡ አብሮ ፡ የሚሮጥ ፡ ነው ፡ የሚመስለው ፡ ...... ፡ የብዛታቸውን ፡ ነገር ፡ የሰው ፡ አንደበት ፡ ተናግሮ ፡ ሊጨርሰው ፡ አይችልም.... ፡ እንኳን ፡ ሰው ፡ አራዊት ፡ የሚሸሹበት ፡ ቦታ ፡ አጥተው ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ሠፈርመጡ። እስላሞቹ ፡ ሲመጡ ፡ ንግሥቲቱ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የእስላም ፡ ሰው ፡ ለንጉሡ ፡ «ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እስላሞቹ ፡ ለጦርነት ፡ ወዳንተ ፡ ሲመጡ ፡ በሠፈርህና ፡ አንተና ፡ ሠራዊትህ ፡ በምትጠጡት ፡ ውሀ ፡ ሥራይ (መርዝ) ያደርጉበታል" ሲል ፡ የነገረውን ፡ አሰበችና ፡ «የጐልጐታን ፡ እመትና ፡ የዮርዳኖስን ፡ ጠበል ፡ ኣንተም ፡ ተጠመቀው ፡ በሠራዊትህም ፡ ላይ ፡ እርጨው ፡ ብላ ፡ ላከችለት። መላክተኛውም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ተክለጽዮን ፡ የሚባለውን ፡ ቄስ ፡

ጠራና ፡ አጥምቀኝ ፡ አለው ፤ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ እንደታጠቀ ፡ ቁሱ ፡ በዚሁ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ውሀ ፡ አጠመቀው። በተጠመቀም ፡ ጊዜ ፡ ሕመሙም ፡ ድካሙም ፡ ከላዩ ፡ ላይ ፡ ተወገደለት። **የእግዚአብሔርን** ፡ ኃይል ፡ ለበሰ ፤ እንዲህም ፡ አለ ፡ «ይህ ፡ የዮርዳኖስ ፡ ጠበል ፡ ብሞት ፡ ስንቅ ፡ ይሁነኝ ፡ ሕያው ፡ ብሆን ፡ ኃይል ፡ ይስጠኝ ፡ አለ ፡ ከዚያም ፡ በሠራዊቱና ፡ በፈረሶቹ ፡ ላይ ፡ ረጨው ፡ ሠራዊቱ ፡ ስላችሁም ፡ ዳቦ ፡ ጋጋሪዎችን ፡ እረኞችን ፡ ለጊዜው ፡ ባጠገቡ ፡ የተገኙትን ፡ የፈረሰኛ ፡ ወታደሮችን ፡ ማለቴ ፡ ነው ፤ (ብዙዎቹ ፡ የሉም ፡ ለማለት ፡ ነው) .... ፡ ወዲያው ፡ ባጠገቡ ፡ ላለው ፡ ተዋጊ ፡ ሕዝብንገሡ ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፡ «አይዟችሁ ፡ እነዚህን ፡ የእስላሞቹን ፡ የጦር ፡ ሰዎች ፡ ብዛታቸውን ፡ አይታችሁ ፡ አትፍሩ ፡ **የእግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ ካልተጨመረ ፡ በቀር ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ በብዛቱ ፡ ማሸነፍ ፡ ቲንሹም ፡ ጦር ፡ በማነሱ ፡ ሊሸነፍ ፡ አይችልም» ፡ ይኸን ፡ ሲል ፡ የእስላሞቹ ፡ የጦር ፡ ወታደሮች ፡ በፊታቸውሲቶች ፡ ሥራይ ፡ እየበተኑላቸው ፡ መጡ ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡ ንጉሡም ፡ ዩዮርዳኖስን ፡ ጠበል ፡ ኣስነዛና ፡ ሥራቸውን ፡ ከንቱ ፡ እንዲሆን ፡ አደረገው። ወዲያው ፡ ፈረሰኞችንና ፡ ቲንሽ ፡ የእግር ፡ ወታደሮችን ፡ አስቀደመና ፡ ውጊያው ፡ እንደተዠመረ ፡ አንቶ ፡ እሠፈራችን ፡ ምሽግ ፡ ውስጥ ፡ ተመልሰን ፡ ገብተን ፡ በዚያ ፡ ሆነን ፡ ብንዋጋ ፡ ይሻላል ፡ " ፡ ብሎ ፡ ለንጉሡ ፡ ቢያማክረው ፡ «እንደ ፡ ወንድ ፡ እጦርነቱ ፡ ላይ ፡ እሞታለሁ ፡ እንጂ ፡ እሚስቴ ፡ ክንድ (ሕፅነ ፡ ብእሲትየ) ፡ ላይ ፡ ሆኜ ፡ አልሞትም ፡ ብሎ ፡ እምቢ ፡ አለው። ሌላው ፡ ደግሞ ፡ «በፈረሶቻችንላይ ፡ እንውጣና ፡ በግልቢያ ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጦር ፡ ሠፈራችን ፡ ሸሽተን ፡ እንደባለቅና ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ሆነን ፡ ተመልሰን ፡ እንውጋቸው" ሲል ፡ አብ ፡ ቢያቀርብ ፡ ሚስቴን ፡ ልጆቼን ፡ አምላኪየ ፡ ኢየሱስየሰጠኝን ፡ ሕዝብ ፡ ትቼለመሸሽ ፡ አላደርገውም ፡ **የእግዚአብሔር** ፡ ልጅ ፡ ሊገድለኝ ፡ ፈልጎ ፡ እንደሆነ ፡ ይግደለኝ ፡ ሊያኖረኝ ፡ ፈልጎ ፡ እንደሆነ ፡ ያኑረኝ" ብሎ ፡ መለሰ።

ይኸን ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ወዳጆቹ ፡ እጁንና ፡ እግሩን ፡ ዓይኑንና ፡ ትከሻውን ፡ ስመው ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ለቀቀኍትና ፡ ሁሉም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሸሹ ፡ ንጉው ፡ ግን ፡ እንደማይነቃነቅ ፡ ምሰሶ ፡ እንደ ፡ ጽኑ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ቆመለ ፡ ሚሸሹት ፡ ትንሽ ፡ ቆማችሁ ፡ እንደምን ፡ እየተጋደልሁ ፡ እንደምሞት ፡

ተመልከቱ ፡ **እግዚአብሔርም** ፡ በእጄ ፡ የሚሠራውን ፡ ተመልከቱ» ፡ አላቸው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ሸሽታቸውን ፡ በቀጠሉ ፡ ጊዜ ፡ ለወታደሮቹ ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ጮኸ ፡ « ፡ ወዴት ፡ ትሸሻላችሁ ፡ ዛሬ ፡ አገራችሁ ፡ በሽሽት ፡ የምትደርሱ ፡ ይመስላችኋልን? እኔን ፡ በጠጅና ፡ በጮማ (በስብሐ ፡ አስዋር ፡ ወበሜስ) ያሳደግኋችሁን ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ በሽልማት ፡ ያከበርኃችሁን ፡ እኔን ፡ አታስቡምን» ፡ ይኸን ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ነብር ፡ ተወርውሮ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ዘሎ ፡ ዓረብ ፡ ኣስፈሬ ፡ እሚባለው ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ ወዲያው ፡ ዘነአስፈሬ ፡ የሚባሉትን ፡ የጐልማሶችን ፡ ፈረሰኞች ፡ ኣለቃ ፡ በቀኝ ፡ በኵል ፡ በእስላሞቹ ፡ ጦር ፡ መካከል ፡ ግባ ፡ አለው ፡ ዘነአስፈሬም ፡ እንደታዘዘ ፡ ተክለ ፤ ወናግረዓድ፣ሳፍ ፡ ሰገድ (የንጉሥ ፡ ልጅ፣በድል ፡ ወበዝ ፤ ቅድመይ ፡ የሚባሉትን ፡ ፫ ፡ ፈረሰኞች ፡ አስከትሎ ፡ በቀኝ ፡ ወደ ፡ ጥሩ ፡ መካከል ፡ ገባ። ንጉሡ ፡ ደግሞ ፡ የጠላት ፡ ሠራዊት ፡ በበረከተበት ፡ በኵል ፡ ገብቶ ፡ ፍላጻና ፡ ጦር ፡ እንደ ፡ ዝናም ፡ እየወረደበት ፡ ይዋጋ ፡ ዠመር። እነርሱም ፡ በሰይፍ ፡ ሊከቡት ፡ መጡ ፤ እርሱ ፡ ግን ፡ ለሞት ፡ ቆርጦ ፡ ፊቱን ፡ እንደ ፡ ቋጥኝ ፡ ደንጊያ ፡ አጠጥሮ ፡ ሰልፋቸውን ፡ እሁላት ፡ ሰነጠቀው። ወዲያውም ፡ **በእግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ በአንድ ፡ ጦር ፡ በትር ፡ ሁለቱን ፡ አጣምሮ ፡ ጣላቸው። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስላሞችሸሽት ፡ ዠመሩ። እነዚያም ፡ በቀኝ ፡ በኵል ፡ የገቡት ፡ ፈረሰኞች ፡ እንደዚሁ ፡ ብዙ ፡ ጨረሱ። ንጉሡም ፡ እስላሞቹን ፡ እያባረረ ፡ ሲመታ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ በፊት ፡ የሸሹት ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ እየመጡ ፡ አብረው ፡ ይዋጉ ፡ ዝመር... ፡ ንጉሡም ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ ጋሻና ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ቀኝ ፡ እጁ ፡ ሲደክም ፡ በግራው ፡ ግራው ፡ ሲደክም ፡ በቀኙ ፡ እያፈራረቀ ፡ ተዋጋ።

የእስላሞቹ ፡ ቊመታቸው ፡ ረዣዥም ፡ መልካቸው ፡ የማያምር ፡ ነው። ጠጕራቸው ፡ እንደ ፡ ሴት ፡ ጠጕር ፡ የተጐነጐነ ፡ ሆኖ ፡ እስከ ፡ ሽንጣቸው ፡ ይወርዳል። ዠግኖች ፡ ስለሆኑ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ቦታ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ አንዱን ፡ ሌላው ፡ ጥሎት ፡ እንዳይሸሽ ፡ የልብሳቸውን ፡ ጫፍና ፡ ማፍ ፡ ያስሩታል።

ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ልጅ ፡ **በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ኃይል ፡ የዓለም ፡ ሁሉ ፡ መመኪያ ፡ በሆነችው ፡ በሰማይ ፡ ባለቤት (መርዓተ ፡ ሰማይ) በጽዮን ፡ እርዳታ ፡ በካህናት ፡ በዲያቆናት ፡ በመነኮሳት ፡

በወንድና ፡ በሴቱ ፡ ጸሎት ፡ ይልቍንም ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ሰራሱ ፡ በእምነቱና ፡ በሃይማኖቱ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ አሸንፎ ፡ ጨረሳቸው። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ እንደገና ፡ እፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣና ፡ የሸሹትን ፡ ያባርር ፡ ዠመር። ለወታደሩም ፡ « ፡ የሞቱትን ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ምርኮና ፡ ላባ ፡ ሴቶቹ ፡ ይውሰዱ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ያልሞቱትን ፡ የጠላትን ፡ ወታደሮች ፡ ኣባሩ ፡ ብሎ ፡ አዘዘና ፡ ወደፊት ፡ ይጋልበ ፡ ዠመር ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እመንገዱ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ የሞተውን ፡ የሬሣ ፡ ልብስ ፡ ሲገፍ ፡ ከኋላው ፡ ደረሰበትና ፡ በጦር ፡ ወጋው። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወታደሩ ፡ ሁሉ ፡ የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈርተው ፡ እንደ ፡ ቃሉ ፡ ይፈጽሙ ፡ ዠመር። ሴቱም ፡ ሁሉ ፡ ከሬሣ ፡ ላይ ፡ ልብስ ፡ ጦር ፡ ቀስት ፡ ሰይፍ ፡ ጋሻ ፡ እየሰበሰቡ ፡ መሸከም ፡ እስኪሳናቸው ፡ ድረስ ፡ እየተሸከሙ ፡ ወደ ፡ ሠፈር ፡ ወሰዱ። ይኸን ፡ የመሰለው ፡ ሥራ ፡ በሌሎች ፡ ነገሥታት ፡ ዘንድ ፡ ተደርጓል ፡ ወይም ፡ ሰምተናል ፡ ብለው ፡ ከኛ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ አባቶቻችን ፡ ኣልነገሩንም ፡ .... ፡ ጦርነቱም ፡ ከ፪ ፡ ሰዓት ፡ የዠመረ ፡ ፀሐይ ፡ እስከትጠልቅ ፡ ድረስ ፡ ቆየ ፡ ...ሲዋጋ ፡ የዋለበትም ፡ እጁ ፡ በደም ፡ ከጦሩ ፡ ጋር ፡ ተጣብቆ ፡ በግድተላቀቀ.... ፡ **የእግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ሙሉው ፡ ሠራዊቱ ፡ በሌለበት ፡ ሰዓት ፡ እነዚህ ፡ አረማውያን ፡ መጥተው ፡ ቢወጉት ፡ መጽሐፍ ፡ ፪ቱ ፡ ሺውን ፡ ያባርሯቸዋል ፡ እንዳለ ፡ እነዚህንም ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ **በእግዚአብሔር** ፡ ኃይልና ፡ እርዳታ ፡ ቲንሽ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ኣሸንፎ ፡ አባረራቸው ፡ ......ዓምደጽዮን ፡ በእጁ ፡ የገደለውን ፡ ብዘረዝርላችሁ ፡ ይህ ፡ የማይቻል ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ ነገሬን ፡ እንደ ፡ ተረት ፡ እንዳትቆጥሩብኝትቼዋለሁ......ጦርነቱ ፡ የተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ንግሥቲቱ ፡ ከቀሩት ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ሲዋጋ ፡ በሩቅ ፡ ይመለከቱት ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ እያባረረሲዋጋ ፡ ካይናቸው ፡ ጠፍቶ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ሳያውቍ ፡ ልባቸው ፡ በጭንቀት ፡ ተይዞ ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ ንጉሥ ፡ ጦርነቱ ፡ ሲያልቅ ፡ ለንግሥቲቱ (ለዣን ፡ መንገሣ ፡ "ብስራትኪኣ ፡ ኢትኅዝኒኣ ፡ እስመ ፡ ሀሎኩ ፡ ሕያወአ) የምስራች ፡ በሕይወት ፡ ነውና ፡ ያለሁት ፡ አትዘኚ» ፡ ብሎ ፡ ላከባት።

ይኸን ፡ የምሥራች ፡ ንግሥቲቱ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ተነሥታ ፡ ታቦቱ ፡ ወዳለበት ፡ ድንኳን ፡ ገባች ፡ ልብሷን ፡ ቀዳ ፡ በግንባሯ ፡ ተደፍታ ፡ መራራ ፡

ልቅሶ ፡ አለቀሰች ፡ ከዚያም ፡ ተነሣችና ፡ እምሰሶው ፡ አጠገብ ፡ ቆማ ፡ «ስብሐት ፡ ከ ፡ **ክርስቶስ** ፡ ወልደ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ሕያው ፡ ዘታቀልል ፡ ዕጹበወትገብር ፡ መንክረ ፡ ወታስተፌሥሕ ፡ ትኩዘዘትቀትል ፡ ሕያወ ፡ ወታነሥእ ፡ ምውተ ፡ ኦእግዚኦ ፡ ርኁቅኒ ፡ ቅሩብ ፡ ላከ ፡ ዕጹብኒ ፡ ቀሊል ፡ በኀቤከ ፡ አኰቴት ፡ ለከ ፡ ምስለ ፡ አቡከ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስሌከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን" ብላ ፡ ጸለየች ፤ ሌሎቹም ፡ ሴቶች ፡ ከርሷ ፡ ጋር ፡ እያለቀሱ ፡ ጸለዩ።

በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ኃይል ፡ በብዙ ፡ ሞገስ ፡ ወዶ ፡ ሠፈሩ ፡ ተመለሰ። ወዲያው ፡ ታቦቱ ፡ ወዳለበት ፡ ድንኳን ፡ ገብቶ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ በኢየሱስ ፡ **ክርስቶስ** ፡ እግር ፡ ወድቆ ፡ በግንባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ስብሐት ፡ ለከ ፡ **ክርስቶስ** ፡ ምስለ ፡ ኣቡከ ፡ መሓፊ ፡ **ወመንፈስ ፡ ቅዱስ** ፡ ማሕየዊ ፡ ዘወሀብከነ ፡ መዊዓ ፡ ወኣድኃንከነ ፡ እምእዴሆሙ ፡ ለዕልዋን ፡ ወስላተ ፡ ጸላኢ ፡ ኣረሰይከነ» ፡ ብሎ ፡ ጸለየ። ካህናቱም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ላዩ .... በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተሳልሞ ፡ ወጣና ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ገባ ፤ ንግሥቲቱም ፡ ተከትላው ፡ ገባችና ፡ እጁንና ፡ እግሩን ፡ ሳመችው ፤ ወገቡንም ፡ ይዛ ፡ «ንጉሥ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ደህና ፡ ነህን፡? ለኔ ፡ ግን ፡ የተኛ ፡ ሰው ፡ በሕልሙ ፡ አልሞ ፡ ሲነቃ ፡ ሕልሙ ፡ እንደሚጠፋበት ፡ ሕልም ፡ ነው ፡ የመሰለኝ ፡ እያለች ፡ ስታለቅስ ፡ ቆየችና ፡ አቧራ ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ እየተንሰቀሰቀች ፡ ስታለቅስ ፡ ቢያይ ፡ ንጉሥ ፡ በጦርነት ፡ ሰውነቱ ፡ ደክሞ ፡ መናገር ፡ እንኳን ፡ ስለተሣነው ፡ ኣሽከሮቹን ፡ ጠቀሳቸውና ፡ እነሱ ፡ ኣንሥተው ፡ ኣስቀመጧት። ንጉሡ ፡ በፍጹም ፡ የሞተ ፡ መስሏቸው ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሴቱም ፡ ወንዱም ፡ ሽማግሌውም ፡ ሕፃኑም ፡ ከርሷ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ አብሮ ፡ ይላቀስ ፡ ነበር። ከመሸም ፡ በኋላ ፡ እነዚያ ፡ ሠራዊቱ ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ ሲዋጉ ፡ ውለው ፡ የነበሩት ፡ መጡና ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ትልቅ ፡ ኃዘንና ፡ ደስታ ፡ ተደረገ ፤ በቀን ፡ ኃዘንና ፡ ጩኸት ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ደስታ ፡ ሆኖ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ተፈጸመ።

.... እነሆ ፡ ሁለተኛው ፡ ጦርነት ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ መፈጸሙን ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ያመለክተናል። አሁንም ፡ ይህ ፡ ጦርነት ፡ የተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ በዚያው ፡ የፊተኛው ፡ የይፋቱ ፡ የሰብረዲን ፡ በተፈጸመበት ፡ በሺ፫፻፳፫ ፡ ዓመተ

፡ ምሕረት ፡ በሐምሌ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ነው። በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ነፋሱ ፡ ሲነፍስ ፡ ሰማዩ ፡ ሲቀላ ፡ የክርስቲያኑን ፡ ንጉሥ ፡ እናሸንፈዋለን ፡ እያሉ ፡ ሸኮቹ ፡ ዝብን ፡ ላማነቃቃት ፡ ያመጡትን ፡ ካንዲት ፡ ሴት ፡ ሰምቶ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የዚህን ፡ የነፋስንና ፡ የዝናም ፡ ምልክት ፡ «ለኛ ፡ ማሸነፊያ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ያደረገው ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የራሱን ፡ ወታደር ፡ አጽናንቶበታል። ነገር ፡ ግን ፡ ወሩ ፡ ደንበኛው ፡ የክረምት ፡ ወር ፡ ሐምሌ ፡ ሆኖ ፡ የነፋሱንና ፡ የዝናሙን ፡ ምልክት ፡ ክርስቲያኖቹና ፡ እስላሞቹ ፡ መሻማታቸው ፡ ከዛሬ ፡ የበለጠ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ይኸን ፡ ለመሳሰላ ፡ ምልክት ፡ ቍም ፡ ነገር ፡ ይሰጥ ፡ እንደነበረ ፡ ያስረዳል። ምናልባት ፡ የአዳል ፡ አገር ፡ በረሃ ፡ ስለሆነ ፡ በወዲህኛው ፡ በሸዋ ፡ ግዛት ፡ እንደሚያደርገው ፡ በዚያ ፡ ኣይዘንምምና ፡ በዚህ ፡ ጊዜና ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ መዝነሙን ፡ እንደ ፡ ተአምራት ፡ ቆጥረውት ፡ ይሆናል።

በዚሁ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ወታደሮቹ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ በተጋጠሙ ፡ ቍጥር ፡ "ንጉሣችን ፡ እንዳያድነን ፡ ወደት ፡ ሄደ ፡ እያሉ ፡ በመጮህ ፡ በኋላ ፡ ሆኖ ፡ ጦር ፡ ለማዘጋጀት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ንግግር ፡ ሆኖ ፡ ለመዋጋት ፡ ያሰበውን ፡ ንጉሡን ፡ ቅደምልን ፡ ወይም ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ሁን ፡ እያሉ ፡ በየጦሩ ፡ ግንባር ፡ ያሉት ፡ ወታደሮች ፡ እንዳስቸገሩት ፡ ይታያል። እርሱም ፡ «ንጉሥ ፡ ጦር ፡ እየላከ ፡ ያዋጋል ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ የተገላቢጦሽ ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ልትልኩኝ ፡ ትፈልጋላችሁ ፡ ሲላቸው ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ተዋጊ ፡ ዠግና ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የንግግር ፡ ስልትና ፡ ዕውቀት ፡ እንደነበረው ፡ ያስረዳል።

ጸሐፊው ፡ የመጨረሻውን ፡ ጦርነት ፡ ንጉሡ ፡ ፩ኛ ፡ በታመመበት ፡ ፪ኛ ፡ ጦሩ ፡ በተበተነበት ፡ ሰዓት ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ቆራጥነት ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ የበረከተውን ፡ ጦር ፡ መመለሱን ፡ ይገልጽልናል። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በእስላሞቹም ፡ በክርስቲያኖቹም ፡ ዘንድ ፡ ጦርነት ፡ በሆነ ፡ ቍጥር ፡ የጦርነቱ ፡ ታሪክ ፡ በየወገኑ ፡ ሲተረክ ፡ የመሪውን ፡ ዠግንነት ፡ የአምላኩን ፡ ተራዳኢነት ፡ የሃይማኖቱን ፡ ጽናት ፡ ለማመልከት ፡ ብቲንኹ ፡ ጦር ፡ ብዙውን ፡ መለሰው ፡ ማለትን ፡ ኣዘውትረው ፡ ይጽፉታል። ስለዚህ ፡ የዚህ ፡ ሕመም ፡ የአፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንንም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጸሐፊ ፡ ሳያገኘው ፡ ኣይቀርም ፤ ጸሐፊው ፡ ግን ፡ የጦርነቱን ፡ ሁኔታ ፡ የንጉሡን ፡ ዠግንነት ፡

በኣድንቆት ፡ ሲጽፍ ፡ መቼም ፡ አታምኑኝ ፡ እያለ ፡ የዛሬኣንባቢና ፡ ጸሐፊ ፡ ነገሩን ፡ እንዳይጠራጠሩበት ፡ አጥብቆ ፡ አሳስቧል።

ከዚህም ፡ ጋር ፡ ከእስላሞቹ ፡ ውስጥ ፡ ጭንቅላታቸውን ፡ ቍልቍል ፡ ዘቅዝቀው ፡ እግራቸውን ፡ ወደላይ ፡ ሰቅለው ፡ በእጃቸውየሚሮጡ ፡ ኣሉባቸው ፡ ሲል ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነገድ ፡ መኖሩን ፡ ከአዳሎቹ ፡ ውስጥ ፡ በጥያቄ ፡ ማጣራት ፡ ይሻላልና ፡ ስለዚህ ፡ ጕዳይ ፡ ሐተታ ፡ መስጠት ፡ ችግር ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፲፫

## የመመለስና ፡ ጦርነቱን ፡ የመቀጠል ፡ ምክር—ያዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ገብተው ፡ ምሕረት ፡ መለመን—የመጨረሻው ፡ ጦርነት።

ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የቀረውን ፡ የጦርነት ፡ ሁኔታ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይቀጥላል ፡ ይህ ፡ ጦርነት ፡ በተደረገበማግሥቱ ፡ ንጉሡ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ጦርነት ፡ ወደተደረገበት ፡ ቦታ ፡ ወጣ ፡ ሴቱም ፡ ወንዱም ፡ ቲንሹም ፡ ትልቍም ፡ ካህናትም ፡ ዲያቆናትም ፡ መነኮሳትም ፡ **እግዚአብሔር** ፡ በገብረ ፡ መስቀል ፡ እጅ (ዓምደ ፡ ጽዮን) ፡ የሠራውን ፡ አስደናቂ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ አጭዶ ፡ የከመረውን ፡ ሬሳ ፡ ይመለከቱ ፡ ዘንድ ፡ አብረው ፡ ወጡ።

እንደ ፡ አምላክ ፡ የሚመለከቱት ፡ ስልሕ ፡ የሞራ ፡ ንጉሥ ፡ ንጉሣቸውም ፡ ንጉሡ (ዓምደ ፡ ጽዮን) ገድሎት ፡ በዚያው ፡ ነበር። በሬሳውም ፡ አንገት ፡ ዙሪያ ፡ ምልክት (ክታብ ፡ ወይም ፡ ንቅሳት?) ነበረው። እርሱንም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲያየው ፡ ንጉሡ ፡ ከዚያ ፡ አስነሥቶ ፡ በዋናው ፡ ሠፈር ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ በእንጨት ፡ ላይ ፡ አሰቀለው። ዳግም ፡ በእስላሞቹ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ እየሄደች ፡ አመድና ፡ አፈር ፡ እየበተነች ፡ ታሟርት ፡ የነበረችው ፡ ተገኘችና ፡ ተገደለች። እርሷም ፡ ቍመቷ ፡ ረጅም ፡ ራሷ ፡ በራ ፡ ያካሏ ፡ ጠጕር ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ነጭ ፡ ሆኖ ፡ እንደፈረስ ፡ ጋማ ፡ ረዥም ፡ ነበር።

**እግዚአብሔር** ፡ ለገብረ ፡ መስቀል (ዓምደ ፡ ጽዮን) ፡ የሠራለት ፡ ተአምራት ፡ ለሙሴ ፡ ከሠራለት ፡ ጋር ፡ የሚገናኝ ፡ ነው ፡ …በንጉሡ ፡ ብርታትና ፡ ጽናት ፡ ከዚህ ፡ ዕለት ፡ ጥፋት ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ኣወጣቸው…. ይኸንንም ፡ ሁሉ ፡ የምንጽፈው ፡ የ**እግዚአብሔርን** ፡ ቸርነት ፡ ለመናገር ፡ የ**እግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ ተደብቆ ፡ እንዳይቀር ፡ ብለን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለትምክህት ፡ አይደለም። …

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ሠራዊቱን ፡ ሰብስቦ ፡ "እስኪ ፡ እንግዲህ ፡ ሳትፈሩ ፡ ንገሩኝ ፡ እስካሁን ፡ ያገለግሉን ፡ የነበሩትን ፡ ሴቶቻችንን ፡ ልጆቻችንን ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ ባሮቻችንን ፡ እንተዋቸውና ፡ ወደፊት ፡ እንሂድን?" ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከመካከላቸው ፡ ፩ድም ፡ የመለሰለት ፡ ኣልተገኘም። ስለዚህ ፡ መልሶ ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ፤ «እውነቱን ፡ ነው ፡ የምጠይቃችሁ ፡ የሚጠቅመውንና ፡ የሚበጀውን ፡ እንድትነግሩኝ ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ መመለስ ፡ የወደዳችሁ ፡ እንደሆነ ፡ በወደዳችሁት ፡ ጊዜ ፡ ሌትም ፡ ቢሆን ፡ ቀንም ፡ ጧትም ፡ ቢሆን ፡ ማታም ፡ ቢሆን ፡ ደስ ፡ በሚያሰኛችሁ ፡ ጊዜ ፡ እንመለስ። ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ በመኳንንቱ ፡ ፈቃድ ፡ መመራት ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መኳንንት ፡ በንጉሥ ፡ ፈቃድ ፡ መመራት ፡ የተገባ ፡ ነው። ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ያለምክር ፡ የተደረገ ፡ እንደሆነ ፡ ሥንፍና ፡ ነው (ኣያምርም) ። ስለዚህ ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ሴቶችና ፡ ልጆቻችንን ፡ አገልጋዮቻችንንም ፡ ገንዘባችንንም ፡ ትተን ፡ ወደፊት ፡ እንሂድ ፡ ፈረስና ፡ በቅሉ ፡ ላይ ፡ ብትወጡ ፡ እኔም ፡ ከናንተ ፡ የተሻለ ፡ ፈረስና ፡ በቅሎ ፡ አለኝ ፤ ዋና ፡ ብትዋኙ ፡ እኔም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሚያድነኝ ፡ እናንተም ፡ በሌላችሁበት ፡ ጊዜ (በትናንትናው ፡ ጦርነት) ከአረመኔዎቹ ፡ እጅ ፡ ባዳነኝ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ እዋኛለሁ ፡ እኔ ፡ ተስፋዬና ፡ የምታመንበት ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ እንግዴህ ፡ የምትሉትን ፡ በሉ»

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ከደብተሮቹ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ትልቅ ፡ ካህን ፡ ሕዝበ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ የሚባል ፡ ተነሥቶ ፡ ላንጉሡ ፡ እንደዚህ ፡ ኣለ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ከእስላሞቹ ፡ እጅ ፡ አድኖሃል ፡ የ**እግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ ሁላችንም ፡ አንድንም ፡ ነበር ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ስማኝ ፡ ከዚህ ፡ ጦርነት ፡ ያድነነን ፡ ዘንድ ፡ ራሱን ፡ ልጁን ፡ ላከልን ፡ እንጂ ፡ ሚካኤልንና ፡

ገብርኤልን ፡ መላእክተ ፡ ኃይሉን ፡ አልላከም» ፡ ይህ ፡ ካህን ፡ ይኸን ፡ ማለቱ ፡ የእስላሞቹን ፡ ብዛት ፡ ለመግለጽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሃይማኖት ፡ ጐድሎት ፡ አይደለም። ብዛታቸው ፡ ለዓይንም ፡ ግሩም ፡ ነው ፡ ለመስማትም ፡ ድንቅ ፡ ነው። ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ በእውነት ፡ በመላእክቱ ፡ እጅ ፡ የሚሠራውን ፡ ተአምራት ፡ ልንገርህ። በሚካኤል ፡ እጅይል ፡ ሰጥቶ ፡ ፈርዖንን ፡ ከነሠራዊቱ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ አሰጠማቸው። በሚካኤል ፡ እጅ ፡ ጴጥሮስን ፡ ከታሠረበት ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ አወጣው። የኛም ፡ በገብርኤል ፡ እጅ ፡ በባቢሎን ፡ አገር ፡ ፫ቱ ፡ ደቂቅን ፡ ነበልባሉን ፡ እሳት ፡ አጥፍቶ ፡ አዳናቸው። በጦርነቱም ፡ ላይ ፡ በመላእክቱ ፡ እጅ ፡ ኃይሉን ፡ ይገልጻል። ሚካኤል ፡ ለቴዎድሮስ (የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሺ፫፻ዥ፰ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ የነገሠው ፡ ይሆን?) ገብርኤል ፡ ለገላውዴዎስ (ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ ማለቱ ፡ ይሆን?) ሰይፍን ፡ ሰጡዋቸውና ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ ድል ፡ አደረጉ። **እግዚአብሔር** ፡ በመላእክቱ ፡ እጅ ፡ በየወገኑ ፡ የሠራው ፡ ብዙ ፡ ሲሆን ፡ እኛ ፡ ጥቂቱን ፡ ኣስታወስን።

አሁን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ነገ ፡ እንመለስ ፡ ንጉሡ ፡ የካህኑን ፡ ቃል ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ ለኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሠራዊት ፡ በሙሉ ፡ መጥተው ፡ እነዚህን ፡ እስላሞቹን ፡ ያላ ፡ ሰይፍና ፡ ያለ ፡ ጦር ፡ ያለ ፡ ቀስት ፡ ቢያገኙዋቸው ፡ ፯ ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ በጦርቢወጉዋቸው ፡ ኣያልቁም ፡ ነበር ፡ ሁሉን ፡ ማድረግ ፡ የማይሳነው ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ግን ፡ ሁሉንም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ደመሰሳቸው። መሓሪና ፡ ሰውንLወዳጅ (መፍቀሬ ፡ ሰብእ) በመሆኑ ፡ የኔንም ፡ ኃጢአት ፡ አላሰበብኝም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከጦር ፡ አለቆቹ ፡ አንዱ ፡ ለንጉሡ ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡ እንዳልከው ፡ በዚህ ፡ ሜዳ (እርሻ) እስላሞቹ ፡ በሰይፍ ፡ ሊወጉኝ ፡ መጡ ፡ እኛ ፡ ግን ፡ በፈረስ ፡ እያበረርን ፡ ስንወጋቸው ፡ እንዴት ፡ ይገርማል ፡ ትል፣ነበር። ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ የንጉሡ ፡ አማች ፡ የንግሥቲቱ ፡ ወንድም ፡ ታላቁ ፡ መኰንን ፡ እንደዚህ ፡ ለማለት ፡ ተነሣ ፡ ፤ ምድር ፡ የማትችለው ፡ ተራራና ፡ ዛፍ ፡ የሚያንቀጠቅጠው ፡ የኢሎፍሊ (ፍልስጥዔም) ሠራዊት ፡ ወደኛ ፡ መጡ ፡ ብሎ ፡ ንጉሡ ፡ አልተናገረም ፡ ያለው ፡ የሐድያና ፡ የዳሞት ፡ የጐጃምና ፡ የትግሬ ፡ ጦር ፡

ቢዋጉዋቸው ፡ ኖሮ ፡ ያሸንፉዋቸው ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ የመሰለው ፡ አለ ፡ ለኔም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፡ የመሰለኝ ፡ አለ። (የ፪ቱ ፡ ጦር ፡ መኰንኖች ፡ ንግግር ፡ በውስጡ ፡ የጐደለው ፡ ነገር ፡ ያለቀስ ፡ ለሚመስል ፡ ሐሳቡ ፡ ሊገባን ፡ አይችልም)

አሁንም ፡ ንጉሡ ፡ የጦርሠራዊቱን ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ እንደገና ፡ ጠየቃቸው ፡ በመጣንበት ፡ መንገድ ፡ እንመለስን? ወይስ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ አድርገን ፡ ወደአገራችን ፡ እንመለስ ፡ በዝምታ ፡ ነገር ፡ አይፈጸምምና ፡ እስቲ ፡ የምትሉትን ፡ ንገሩኝ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ክረምት ፡ ደመና ፡ በርክተው ፡ እስላሞቹ ፡ ሲመጡባችሁ ፡ ብትፈሩ ፡ እውነት ፡ አላችሁ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ምሕረቱን ፡ በላያችን ፡ ገልጾ ፡ ከጠላቶቻችን ፡ አድኖናልና ፡ አትፍሩ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሠራዊቱአንተ ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ተዋግተህ ፡ ከእስላሞቹ ፡ እጅ ፡ አድነኸናል ፡ አሁንም ፡ አንተው ፡ በምክርህ (በፈቃድህ) አገራችን ፡ አግባን ፡ »ቢሉት ፡ በወጣበት ፡ የሚመለስ ፡ እንስሳ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ተለግ ፡ የምትባለዋን ፡ የአጻልን ፡ አገር ፡ ተሻግረን ፡ የተረፉትን ፡ አረመኔዎች ፡ ገድለን ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ተመልሰን ፡ ወዳገራችን ፡ እንግባ ፡ እላለሁ ፡ ብሎ ፡ መለሰ። ሠራዊቱም ፡ እንደፈቃድህ ፡ ይሁን> ፡ ብለው ፡ መለሱ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ ባ ፡ ወደምትባል ፡ አገር ፡ ወረደና ፡ በዚያ ፡ ሠፈሩን ፡ አደረገ። በማግስቱ ፡ ተኣረከ ፡ ወደምትባለው ፡ አገር ፡ ፤ ጦር ፡ ላከ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱም ፡ ሰዎቹን ፡ ገድለው ፡ ሴቱንና ፡ ወንዱን ፡ ከብቱን ፡ ማርከው ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተመለሱ። ከዚያ ፡ በሐምሌ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ የቂርቆስ ፡ ለት ፡ ዶቢ? ወደሚባለው ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ ሰፈረ። በማግስቱም ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እየከፈለ ፡ ላከ ፡ ሠራዊቱም ፡ ዘሰይ ፡ ዘሶይ) ፡ የምትባለውን ፡ አገር ፡ አጥፍተው ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ ማረኩ ፡ አብደላ ፡ የሚባለውንም ፡ እንደ ፡ ጳጳሳቸው ፡ የሆነውንም ፡ ገድለው ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ንጉሣቸው ፡ መጡ። መራዳ ፡ የሚባሉትም ፡ አበልጊ ፡ ወደ ፡ ሚባለው ፡ ኣገር ፡ ተልከው ፡ የነበሩት ፡ እንደዚሁ ፡ አገሪቱን ፡ አጥፍተው ፡ ብዙ ፡ የሰውና ፡ የከብት ፡ ምርኮ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ንጉሣቸው ፡ መጡ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ካላበት ፡ ቦታ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ተለግ (ሐገረ ፡ ተለግ) ሄዶ ፡ ይችም ፡ አገር ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ ለመውጋት ፡

ነገሥታትንና ፡ መኳንንትን ፡ የሰበሰበው ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ያሸነፈው ፡ የአዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ አገር ፡ ናት። በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ ከጦርነት ፡ ያመለጡት ፡ የአዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ ወንድምና ፡ ፫ቱ ፡ ልጆቹ ፡ ከእግራቸው ፡ ላይ ፡ ጫማቸውን ፡ አውልቀው ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ አድርገው ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ተገዛንልህ ፡ ተገዛንልህ ፡ እያሉ ፡ እጅ ፡ እየነሡ ፡ መጡና ፡ ባገር ፡ ከቲንሽ ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ የተረፈ ፡ የለምና ፡ ማረን ፡ ሁለተኛ ፡ አታጥፋን> ፡ ብለው ፡ ለመኑት። ንጉሡም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ወቀሳቸው ፡ እናንተም ፡ አባታችሁም ፡ ሰው ፡ የማይበድለውን ፡ በደል ፡ በደላችሁኝ ፡ ተገዥ ፡ የሀነሰው ፡ ከንጉሥ ፡ ሲሸፍት ፡ ወደተራራ ፡ ወደ ፡ ጫካ ፡ እየሸሸ ፡ እስከቻለ ፡ ድረስ ፡ ይዋጋል ፡ ወይም ፡ ተገዥነቱን ፡ ያመነ ፡ ግብሩን ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ፡ ለግዥው ፡ ይዞ ፡ ይመጣል ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ሁለቱንም ፡ ሽሽቱንም ፡ መገዛቱንም ፡ ኣልፈጸማችሁም ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ እኔን-የመላውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ልትወጉኝ ፡ መጣችሁ። **እግዚአብሔር** ፡ ግን ፡ የልባችሁን ፡ ኵራት ፡ ተመልክቶ ፡ በጄ ፡ ላይ ፡ ጣላችሁ ፡ እንደልባችሁ ፡ ክፋት ፡ ከፈላችሁ ፡ ክፋታችሁም ፡ በራሳችሁ ፡ ላይ ፡ ተመልሶ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ የኃይለኞችና ፡ የምውታን ፡ የትሑታን ፡ አምላክ ፡ ስለሆነ ፡ ከክብራችሁ ፡ አዋረዳችሁ ፡ " ፡ ቀድሞውኑ ፡ ከአባታችሁ ፡ ጋር ፡ ግብራችሁን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ የከበረ ፡ ልብስ ፡ ይዛችሁ ፡ መጥታችሁ ፡ ተገዝታችሁልኝ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በናንተና ፡ በኔ ፡ መካከል ፡ ፍቅር ፡ በተመሠረተ ፡ ነበር።

ልጆቹ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ መለሱ ፤ "ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ባገራችን ፡ ከ**እግዚአብሔር** ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ የሚገዛ ፡ የለም ፡ ማንም ፡ የሚችላን ፡ አልነበረም። አንተ ፡ በመጣህ ፡ ጊዜ ፡ ደስታ ፡ ተድላ ፡ የለመደ ፡ እንጂ ፡ የሚዋጋ ፡ ጦር ፡ አለ ፡ ብለን ፡ አልጠረጠርንም ፡ ነበር። ቍጥራችን ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ከመብዛቱ ፡ የተነሣ ፡ የክርስቲያኖች ፡ ገንዘብ (ለምርኮ) ይበቃን ፡ ይሆን ፡ እንባባል ፡ ነበር። እንተና ፡ ሠራዊትህ ፡ በእጃችን ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ወደቃችሁአምነን ፡ ነበር። አንተን ፡ ብቻ ፡ የማንፈራ ፡ አልነበርንም። ነገርግን ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ተሰብስበው ፡ ቢመጡ ፡ እንዋጋቸው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ኣንፈራቸው ፡ ነበር ፡ አንተ ፡ አሁን ፡ ከአሸነፍኸን ፡ በቀር ፡ በፊታችን ፡ የሚቆም ፡ ኣልነበረም። አሁን ፡ ግን ፡ ንጉሥ

፡ ሆይ ፡ ቊጣህን ፡ ተው ፡ ፈጽመህም ፡ አታጥፋን ፡ ያዘዝኸንን ፡ ሁሉ ፡ እንፈጽማለን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ መልሶእንደዚህ ፡ አላቸው ፤ "እስኪ ፡ እናንተው ፡ ራሳችሁ ፡ ነገሥታቶቻቸውን ፡ የሚወጉ ፡ ተገዥ ፡ ሕዝቦች ፡ ወዴት ፡ እንዳሉ ፡ ንገሩኝ። ይልቅስ ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ተገዥው ፡ ሕዝብ ፡ ለንጉሣቸው ፡ ገጸ ፡ በረከትና ፡ መታያ ፡ ይዘው ፡ ይመጣሉ፣እናንተ ፡ ግን ፡ ልትወጉኝ ፡ መጣችሁ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ረዳቴ ፡ ሆነ ፤ ቅጽራችሁንና ፡ ምሽጋችሁንም ፡ ኣፈረሰ። በእጄ ፡ ደመሰሳችሁ። አሁንም ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ ታላቊንም ፡ ታናሹን ፡ ከብታችሁንም ፡ አገራችሁንም ፡ በረሃና ፡ ባዶ ፡ ኣድርጌ ፡ ሳላጠፋ ፡ ኣልተዋችሁም። ልጆቹም ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ "ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ይኸን ፡ አትሥራ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ ቀሩት ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ እንዲገቡልህና ፡ የፈቀድኸውን ፡ እንድታደርግባቸው ፡ እንልክባቸዋለን ፡ ኣሉት ፡ እርሱም ፡ «ቢመጡ ፡ ይምጡ ፡ ባይመጡ ፡ በአምላኬ ፡ ኃይል ፡ የማደርገውን ፡ ያያሉ፥ አላቸው።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚሁ ፡ የአዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ ልጆች ፡ «ከሚስቶቻችሁና ፡ ከልጆቻችሁ ፡ ከከብታችሁም ፡ ጋር ፡ ሳይጨርሳችሁ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ገብታችሁ ፡ ተገዙ ፡ ብለው ፡ ለነገሥታቱና ፡ ለመኳንንቱ ፡ ጻፉ። የነዚህን ፡ የልጆቹን ፡ መልእክት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የሀገሩ (የአዳሉ) ንጉሥ ፡ የሀገሩን ፡ ሕዝብ ፡ ሰብስቦ ፡ «የነዚህን ፡ የልጆች ፡ ቃል ፡ አትስሙ ፡ ነገራቸውንም ፡ አትቀበሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያውን ፡ ንጉሥ ፡ እንድንገድለው ፡ ልባችሁን ፡ አጽኑ። ክርስቲያኖች ፡ ቢገድሉን ፡ ሰማዕት ፡ እንሆናለን ፡ እኛ ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ብንገድላቸው ፡ ግን ፡ ዝትን ፡ እናገኛለን" ብሎ ፡ ሰበከና ፡ በዚሁ ፡ ለውጊያ ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ ቲንኹም ፡ ትልቊም ፡ ሁሉም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብቶ ፡ ተስማማ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይኸው ፡ ዓመጸኛ ፡ አባታቸው) ፡ የአዳሉ ፡ ንጉሥ) «ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ አንመጣም ፡ ፤ እርሱ ፡ ወደኛ ፡ ቢመጣ ፡ ግን ፡ አንፈራውም ፤ ባገራችን ፡ ላይ ፡ ተዋግተን ፡ እንሞታለን" ብሎ ፡ ለልጆቹ ፡ ላከባቸው። ልጆቹም ፡ ፱ ፡ መኳንንት ፡ የሚገዛው ፡ የሀገራ (አዳል?) ንጉሥ ፡ ቆርጦ ፡ የላከውን ፡ ለንጉሡ ፡ አስታወቊት።

ይኸን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ በቍጣ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ እኳ ፡ የሚባለውን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሮ ፡ መርመጉብ ፡ እሚባለው ፡ አገር ፡ ደርሶ ፡ ሠፈር ፡ ኣደረገ። በማግስቱም ፡ «ይህ ፡ ዓመጸኛ ፡ እንዳያመልጣችሁ ፡ ለነፍሳችሁ ፡ ዕወቍ» ፡ ብሎ ፡ አስጠንቅቆ ፡ ጦሩን ፡ ከፋፍሎ ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ላካቸው። ንጉሡ ፡ ራሱ ፡ ግን ፡ በመካከል ፡ አድርጎ ፡ ቲንሽ ፡ ወታደሮች ፡ ይዞ ፡ ሲሄድ ፡ ይኸው ፡ ክፉ ፡ ሰውዬ (የአዳሉ ፡ ንጉሥ) ወንዱንም ፡ ሴቱንም ፡ ቲንሹንም ፡ ትልቍንም ፡ ለጦርነት ፡ ይዞ ፡ ሲጠብቀው ፡ ተገናኙና ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ተደረገ። የእስላሞቹም ፡ ጦር ፡ በርትቶ ፡ ተዋጋ ፡ ፤ ከነእርሱም ፡ ውስጥ ፡ በፍላጻ ( ፡ በጦር ፡ መሣሪያ) ሲዋጉ ፡ ግማሾቹ ፡ ጋሻ ፡ ይዘውይከልሏቸው ፡ ነበር ፡ ሴቶቹም ፡ በዱላ ፡ በደንጊያ ፡ እንደ ፡ ኃይለኛ ፡ ወጣት ፡ በርትተው ፡ ይዋጉ ፡ ነበር። የጦርነቱን ፡ መበርታት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ራሱ (ዓምደ ፡ ጽዮን) እንደ ፡ ነብር ፡ እየተወረወረ ፡ እንደ ፡ አንበሳእያገሣ ፡ ቀስቱን ፡ ደግኖ ፡ የአገራን (አዳል)ንጉሥ ፡ አንገቱን ፡ ወጋውና ፡ ወስፈንጠሩ ፡ በኣንገቱ ፡ መካከል ፡ ሾልኮ ፡ በረረ። ክፉውም ፡ ሰውዬ ፡ ወዲያው ፡ በዠርባው ፡ ወደቀ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስላምቹ ፡ ሸሽት ፡ ዠመሩ ፡ የንጉሡም ፡ ጦር ፡ ከቦ ፡ እስኪያልቍ ፡ ድረስ ፡ ወጋቸው፣ ፡ የሚሸሹትንም ፡ የፈረሰኛ ፡ ወታደር ፡ እያባረረ ፡ ከ፫ ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ ሁሉንም ፡ ፈጃቸው።

ንጉሡ ፡ ከጦርነቱ ፡ ሲመለስ ፡ ወእንዘኣይገብ ፡ ና ፡ ስምይሸሐል ፡ የሚባሉትን ፡ ሁለት ፡ ወታደሮቹን ፡ ፈለገ ፤ ባጣቸውም ፡ ጊዜ ፡ የሞቱመስሎት ፡ በጣም ፡ እያዘነ ፡ ሲሄድ ፡ ከሐዘኑ ፡ የተነሣ ፡ የባዕድ ፡ የጠላት ፡ ወገን ፡ መሆኑን ፡ ሳያውቅ ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ ኣገኘናሁለቱን ፡ ወታደሮቹን ፡ ኣላየህምን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው። ጠላት ፡ መሆኑን ፡ በተረዳ ፡ ጊዜ ፡ ገደለውና ፡ ከዚያ ፡ እንዳለፈ ፡ ሁለቱን ፡ የሚወዳቸውን (ወታደሮቹን)ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለው። ነገር ፡ ግን ፡ እስላሞቹ ፡ ራሳቸውን ፡ ያቆሰሉዋቸውን ፡ ተመለከተና ፡ በጣም ፡ ይወዳቸው ፡ ነበርና ፡ ኣዘነ። ከዚያ ፡ በራሱ ፡ በቅሎዎች ፡ ተቀምጠው ፡ ፀሐይም ፡ ብርድም ፡ እንዳይመታቸው ፡ ድባብ (ዣንጥላ) ተይዞላቸው ፡ እንዲሄዱ ፡ ኣዘዘ። ምክንያቱም ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ ሰኖ ፡ ዘንድ (ሸዋ)ክረምትሆኖ ፡ በዚህ ፡ ኣገር

(አዳል) ግን ፡ በጋ ፡ ስለሆነ ፡ ነው። ከጦርነቱ ፡ በታ ፡ ንጉሡ ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ ሞያ ፡ ተጉዞ ፡ እሠፈሩ ፡ ደረሳ...።

በማግስቱ ፡ ንጉሡ ፡ ሰሶጌ (ሣዕጌ) ወደ ፡ ሚባለው ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ የመጥምቁን ፡ የዮሐንስን ፡ በዓል ፡ አክብሮ ፡ ዋለ። የእስላሞቹ ፡ መስጊድ ፡ እንዲፈርስ ፡ አገራቸው ፡ እንዲቃጠል ፡ ኣዘዘ ፡ ...። ከዚያም ፡ በነሐሴ ፡ ፲፩ቀን ፡ ዘርአት ፡ የሚባለውን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሮ ፡ አራቲ ፡ እሚባለው ፡ አገር ፡ ደረሰና ፡ ሠፈሩን ፡ አደረገ። የዚህም ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ሰውን ፡ ከነሕይወቱ ፡ ዥሮውን ፡ እንደውምላጭ ፡ በጥርሳቸው ፡ ይቆርጣሉ። የሞተውንም ፡ ሰው ፡ ከመቃብር ፡ እያወጡ ፡ ዥሮውን ፡ ቆርጠው ፡ ብልቱን ፡ ይሰልባሉ ፡ በዚህምሥራ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ የከፉ ፡ ናቸው። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ዥሮዋቸውን ፡ የተቆረጡ ፡ ከንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ ውስጥ ፡ መጥተው ፡ በፊቱ ፡ ቆሙ ፡ ንጉሡም ፡ በቍስላቸው ፡ ሲታመሙ ፡ ኣይቶ ፡ በጣም ፡ አዘነ ፡ ወዲያውም ፡ «ምን ፡ ጊዜ ፡ አግኝተው ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ ያደረግዋችሁ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ግማሾቹ ፡ ወሀ ፡ ስንቀዳግማሾቹ ፡ እንጨት ፡ ስንሰብር...ነው ፡ ብለው ፡ መለሱ። ይኸን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሚያደርገውን ፡ አስቦ ፡ የጦር ፡ አለቆቹን ፡ ጠራና ፡ ነገ ፡ ጧት ፡ እኔ ፡ ጥሩምባ ፡ እያስነፋሁ ፡ ሠፈር ፡ ለቅቄ ፡ እወጣለሁ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ እስላሞቹ ፡ እንዳያዩዋችሁ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በጫካ ፡ ተደብቃችሁ ፡ ተቀመጡ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸውና ፡ በጧት ፡ ጥሩምባውን ፡ እያስነፋ ፡ ሠራዊቱን ፡ አስከትሎ ፡ ጉዞውን ፡ ዠመረ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስላሞቹ ፡ ወደ ፡ ሠፈር ፡ ሲመጡ ፡ የንጉሡ ፡ ወታደሮች (የተደበቁት) ወጥተው ፡ ፈጅዋቸው። ንጉሡም ፡ ይኸንኑ ፡ በኋላ ፡ ሰምቶ ፡ ደስ ፡ አለው። ከዚያ ፡ ሐዝዮ ፡ ወደ ፡ ሚባለው ፡ አገር ፡ ሄዶ ፡ የመስቀልን ፡ በዓል ፡ አክብሮ ፡ ፳ቀን ፡ በዚያ ፡ ሰነበተ። በዚያም ፡ ትልቅ ፡ ምሽግ (ቅጥር) ሥሩ ፡ ብሎ ፡ አዘዘና ፡ ተሠርቶ ፡ ሲያልቅ ፡ ወታደሮቹን ፡ በቅጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ትቶ ፡ እንደዚያው ፡ ጥሩምባውን ፡ እያስነፋ ፡ መንገዱን ፡ ሲጓዝ ፡ አረመኔዎቹ ፡ ወደ ፡ ሠፈሩ ፡ መጡ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮቹ ፡ ከቅጥሩ ፡ ውስጥ ፡ እየወጡ ፡ ፈጅዋቸው ፡ ብዙ ፡ መሣሪያና ፡ ልብስ ፡ ይልቁንም ፡ የሰለቡትን ፡ ባገልግል ፡ እንዳስቀመጡት ፡ ማርከው.... ለንጉሡ ፡ ቢያሳዩት ፡ በጣም ፡ ኣዘነ ፤ ቢሆንም ፡ እነዚያ ፡ በመገደላቸው ፡ ደስ ፡ ተሰኘ።

ከዚያ ፡ የ፯ ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ተጕዞ ፡ ብቍልዛር ፡ እሚባለው ፡ አገር ፡ ደርሶ ፡ ሠፈረ ፤ በዚያም ፡ ሳላ ፡ የእስላሞቹን ፡ ንጕሥ? ጠራና ፡ «በል ፡ ከሾምሁህ ፡ ዠምሮ ፡ ባንተ ፡ ጊዜ ፡ **ክርስቶስን** ፡ የካዱትን ፡ ክርስቲያኖች ፡ እያወጣህ ፡ ስጠኝ ፡ እምቢ ፡ ያልህ ፡ እንደሆነ ፡ አንተን ፡ በሰንሰለት ፡ አሥሬ ፡ ሰውህንም ፡ ልጆችህንም ፡ ጨርሼ ፡ አገርህን ፡ ሁሉ ፡ አጠፋዋለሁ ፡ አለው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የእስላሞቹ ፡ ንጕሥ ፡ በፍርሐት ፡ ተንቀጥቅጦ ፡ በያገሩ ፡ ልኮ ፡ እነዚያን ፡ ከሐዲዎች ፡ ዲያቆናትን ፡ ቀሳውስትን ፡ አስመጣ ፡ በመጡም ፡ ጊዜ ፡ የንጕሡ ፡ ወታደሮች ፡ ተቀብለው ፡ እፊቱ ፡ አቆሚቸው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጕሡ ፡ የሰማይንና ፡ የምድርን ፡ ፈጣሪ ፡ **የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡** በውነት ፡ ካዳችሁትን? አባቶቻችሁ ፡ በቀደሷችሁ ፡ ቀን ፡ **ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** ያገኛችሁትን ፡ ጥምቀት ፡ ለውጣችሁ ፡ በዲያብሎስ ፡ በእስላም) ሕግ ፡ ገባችሁን? »ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ የሚመልሱት ፡ አጡ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የንጕሡ ፡ ልብ ፡ በቍጣ ፡ ነደደ ፡ ሠላሳ ፡ ፴ ፡ ዥራፍ ፡ አስገረፋቸውና ፡ በዠርባቸው.... ላይ ፡ ሥራቸው ፡ እንዲጻፍ ፡ ኣደረገ ፡ ወዲያው ፡ ለ**ክርስቶስ** ፡ ሕግ ፡ በመቅናት ፡ አንገትና ፡ እጃቸው ፡ በብረት ፡ እንዲታሠር ፡ አደረገ። ከዚህም ፡ ቀጥሉ ፡ አሁንም ፡ የተረፉትን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ስጠኝ» ፡ ብሎ ፡ እንደገና ፡ የእስላሞቹን ፡ ንጕሥ ፡ ቢያዘው ፡ የንጕሤ ፡ ልጅ ፡ ከለከለኝ ፡ ብሎ ፡ አመካኘ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጕሡ ፡ ተቆጣና ፡ የወንድሙን ፡ ልጅ ፡ ያዘና ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ ኣሥሮ ፡ አስቀመጠው ፡ አገሩንም ፡ ኣስጠፋና ፡ ሹመቱን ፡ ነስረዲን (ናስር ፡ ኤዲን) ለሚባለው ፡ ለወንድሙ ፡ ሰጠበት። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጕሡ ፡ ዋዝ ፡ ወደሚባል ፡ አገር.... ለመሄድ ፡ ያምስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ተጕዞ ፡ ድልሆያ ፡ ወደሚባለው ፡ አገር ፡ ደረሰ ፡ የዚያችም ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ንጕሡ ፡ የሾመውን ፡ መኰንን ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ በዚች ፡ አገር ፡ የተዋቸውን ፡ ወታደሮች ፡ ወንዱንም ፡ ሴቱንም ፡ ክርስቲያኖችን ፡ በሙሉ ፡ ገድለው ፡ በእሳት ፡ ስላቃጠሉዋቸው ፡ በጣም ፡ ተናዶ ፡ ነበርና ፡ እንደደረሰ ፡ ...። ሁሉንም ፡ አንድም ፡ ሳያስቀር ፡ አስጠፋቸው ፡ ከዚያ ፡ የ፫ ፡ ቀን ፡ ጕዞ ፡ አድርጎ ፡ ደጕ (ሀገረ ፡ ደጕ) ደረሰ ፡ በዚያም ፡ የዘላኖቹን ፡ አገር ፡ አጥፍቶ ፡ ፬ት ፡ ቀን ፡ ተጕዞ ፡ ወደ ፡ ደዋሮ ፡ ደረሰ ፡ የዚህም ፡ አገር ፡ ሹም ፡ ሀይደራ ፡ የሚባለው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡

ከዚያ ፡ ከክፉ (ዓማፂ) ከሰብረዲን ፡ ጋር ፡ በኣድማ ፡ ተባብሮ ፡ የነበረው ፡ አገር ፡ ስለሆነ ፡ ከወሰን ፡ እስካ ፡ ወሰን ፡ ድረስ ፡ ኣስጠፋት ፡ " ፡ ይልቍንም ፡ ንጉሡ ፡ በፊት ፡ በዚች ፡ አገር ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ (ከተጕለት) የተላከውን ፡ የንጉሡንና ፡ የንግሥቲቱን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ብዙ ፡ ልብስና ፡ ዕቃ ፡ መላከተኞቹን ፡ ኣዘንግተው ፡ ገድለው ፡ ቀምተዋቸው ፡ ስለነበረ ፡ ተናዶ ፡ ነበርና ፡ አዝመራቸውን ፡ ሳይቀር ፡ አስጠፋው። በዚያም ፡ ሳለ ፡ ኃጢኣትን ፡ ለማስተሥረይ ፡ **ክርስቶስ** ፡ ከድንግል ፡ የተወለደበትን ፡ የልደትን (የገናን) በዓል ፡ አከበረ። በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ዮሴፍ ፡ የሚባለውን ፡ የሳርካ ፡ ሹም (መኰንነ ፡ ሳርካ) ከደዋሮ ፡ ሰዎች ፡ በክፋት ፡ ተባብሮ ፡ ስለነበረ ፡ እርሱን ፡ አሠረና ፡ በአገሩ ፡ የሚገኘውንም ፡ ከብቱንም ፡ ፈረሱን ፡ በቅሎውንም ፡ አዘረፈው። ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የኢትዮጵያው ፡ ንጉሥ ፡ በታላቅ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ በብዙ ፡ ሞገስ ፡ ተመልሶ ፡ በሰላም ፡ በደስታ ፡ ድልን ፡ የሰጠውን ፡ ኣምላክ ፡ እያመሰገነ ፡ ወደሀገሩ ፡ ገባ።

# ምዕራፍ ፡ ፲፪

## የጦርነቱ ፡ ታሪክና ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ አንደኛ ፡ ፍጻሜ።

ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በግዕዝ ፡ የተጻፈው ፡ የጦርነቱ ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ይፈጸማል። እመጨረሻው ፡ ላይ ፡ ብዙኅ ፡ እምዘተጽሕፈ ፡ ዘኮነ ፡ ፀብእ ፡ ላዕለ ፡ ንጉሥ ፡ ወሠራዊቱ ፡ በኵሉ ፡ ምድረ ፡ ተንባላት ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ኅዳጠ ፡ ኢነገርነ ፡ ወኢወሰክነ ፡ ከመ ፡ ኢይኑኅ ፡ ነገር ፡ ወኢይኵን ፡ ድንጋጼ ፡ ለዘይሰምዖ ፡ .... ሰሚ ፡ እንዳይደነግጥ (እንዳይሰለች? ነገር ፡ እንዳይበዛ ፡ ብለን ፡ ብዙ ፡ ከመናገርና ፡ ከመጨመር ፡ ባንታገድ ፡ ኖሮ ፡ በእስላሞቹ ፡ አገር ፡ በንጉሡና ፡ በሠራዊቱ ፡ ላይ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ የተደረገውን ፡ ጦርነት ፡ በብዙ ፡ ሊጻፍ ፡ በተቻለ ፡ ነበር ፡ ሲል ፡ ጸሐፊው ፡ ኣንባቢን ፡ ላለማሰልቸት ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ መተዉን ፡ ይገልጻል።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳልነው ፡ ይህ ፡ ጦርነት ፡ የተደረገበት ፡ ዘመን ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በነገሠ ፡ በ፲፰ኛው ፡ ዓመት ፡ መሆኑን ፡ ታሪኩ ፡ ይገልጻል። ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የነገሠው ፡ በዝርዝሩ ፡ ላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ በሺ፫፻፯ ዓ. ምሕረት ፡ ሲሆን ፡ ጦርነቱ ፡ የተደረገው ፡ በሺ፫፻፳፭ ፡ ዓ. ምሕረት ፡ ላይ ፡ ይሆናል። የፈረንጆቹ ፡ ጸሐፊዎችም ፡ ጊዜውን ፡ ግማሹ ፡ ፩ሺ፫፻፴ ፡ የቀረው ፡ ፩ሺ፫፻፴፪-፴፬ ፡ እያሉ ፡ ጽፈውታልና ፡ ከኛው ፡ ከግዕዙ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ጋር ፡ አልተራራቀም። ጦርነቱ ፡ ያለቀው ፡ ግን ፡ በሺ፫፻፳፱ ፡ ዓ.ም ፡ በታኅሣሥና ፡ በጥር ፡ ወር ፡ መሆኑ ፡ ነው።

ይህ ፡ የዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ የተጻፈበት ፡ ጊዜና ፡ የጻፈው ፡ ሰው ፡ ማን ፡ መሆኑ ፡ ከነስሙ ፡ አይታወቅም ፡ ታሪኩን ፡ ሲያነቡት ፡ ጸሐፊው ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ሳይለይ ፡ እየተከተለ ፡ ባይኑ ፡ እያየ ፡ የጻፈው ፡ ይመስላል ፡ የዚችን ፡ ቀን ፡ ጦርነት ፡ ለመተረክ ፡ ቃልና ፡ ቋንቋ ፡ ያንሣል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ እንደዚሁም ፡ "ይሰላቻል ፡ ብዬ ፡ ባልተወው ፡ የምተርክላችሁ ፡ ብዙ ፡ ነበር ፡ ሲል ፡ ራሱ ፡ ጸሐፊው ፡ በዘመኑ ፡ ተገኝቶ ፡ የጻፈው ፡ ይመስላል። ደግሞ ፡ ዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንኳን ፡ በዘመኑ ፡ የራሱንና ፡ ያለፉትን ፡ ያባቶቹን ፡ የአክሱሞቹን ፡ ታሪክ ፡ እያዋጣችሁ ፡ ታሪክ ፡ ኣዘጋጁ ፡ ብሎ ፡ ሊቃውንትን ፡ ያዘዘ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ የራሱን ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ እንዲዘጋጅለት ፡ ማዘዙ ፡ የታወቀ ፡ ነው።

የታሪክንና ፡ የጽሑፍን ፡ ጣዕምና ፡ ጥቅም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ተረድቶ ፡ ያለፈውን ፡ ሲያጽፍ ፡ የራሱን ፡ እደምን ፡ ችላ ፡ ይላል ፡ ለማለት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አለ። በምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ ላይ ፡ እንዳስታወስነው ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ከ፻ ፡ ዓመት ፡ የሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ኣልፎ ፡ የነገሡትን ፡ አፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ፩ኛ ፡ ከ፪፻ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የነበሩትን ፡ ዓፄ ፡ ገላውዴ ፡ ዎስንም ፡ ስላነሣ ፡ በርሱ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሆን ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ የተጻፈው ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል። ነገር ፡ ግን ፡ ቴዎድሮስና ፡ ገላውዴዎስ ፡ ሲል ፡ ነገሥታቱን ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ መሆኑ ፡ በትክክል ፡ አይታወቅም። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሚመስለው ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ በዚያው ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ከአሁኑ ፡ ባነሰ ፡ የግዕዝ ፡ አስካክ ፡ ተጽፎ ፡ በብራና ፡ ሲኖር ፤ በኋላ ፡ ባፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፩ኛ ፡

ባፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ወይም ፡ በሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ ፡ ይሁን ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ የሚያውቅ ፡ ሊቅ ፡ የቀድሞውን ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ አድርጎከሽማግሌዎችና ፡ ከሊቃውንት ፡ አፍቃል ፡ በቃል ፡ እየተነገረ ፡ የመጣውን ፡ ቃል ፡ እየጨመረ ፡ በአዲስ ፡ ዓይነት ፡ ኣነጋገር ፡ አሟልቶ ፡ ጽፎት ፡ ወይም ፡ ኣጽፎት ፡ ይሆናል።

እርሱም ፡ ስሙን ፡ ሳይገልጽ ፡ ሊተኒ ፡ ለኃጥእ ፡ ወአባሲ ፡ ዘአጽሐፍክዋ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ኢትርስዑኒ ፡ በጸሎትክሙ.... እኔንም ፡ ይህቺን ፡ መጽሐፍ ፡ ያጻፍኅዋትን ፡ ኃጢአተኛና ፡ በደለኛ ፡ ሰው ፡ በጸሎታችሁ ፡ ኣትርሱኝ.... » ሲል ፡ የዋናው ፡ የጸሐፊነቱን ፡ ተግባር ፡ ለዚያው ፡ ለገለበጠበት ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ ለነበረው ፡ ትቶ ፡ ራሱን ፡ እንደገና ፡ እንዳስጻፈው ፡ ያደርጋል።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቃለ ፡ ውዳሴና ፡ ማግነን ፡ ቢኖርበትም ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ ሳይጻፍ ፡ ቀርቶ ፡ የተገኘው ፡ እንደ ፡ ብርቅ ፡ የሚታይ ፡ ስለሆነ ፡ ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ መስጠት ፡ ይገባል። በውስጡ ፡ የንጉሡን ፡ ያምደ ፡ ጽዮንን ፡ ስም ፡ ከስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ከገብረመስቀል ፡ ጋር ፡ በትክክል ፡ ይሰጣል ፤ የዋናውን ፡ የሚስቱን ፡ ስም (የእቴጌዪቱን)ዣን ፡ መንገሣ ፡ እያለ ፡ እንደዘመኑ ፡ የአፍሪቃና ፡ የእስያ ፡ ነገሥታት ፡ ልማድ ፡ ሌሎች ፡ ንግሥቶችና ፡ ዕቍባቶች ፡ መኖራቸውን ፡ ያስረዳል። እንደዚሁም ፡ የጦር ፡ አለቆቹን ፡ ስምና ፡ የማዕርግ ፡ ስማቸውን ፡ ከአዳሎቹም ፡ ወገን ፡ የነገሥታቱንና ፡ የመኳንንቱን ፡ ነገር ፡ በተርታ ፡ ሳይሰለች ፡ ይዘረዝራል። ደግሞ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ለሠራዊቱ ፡ ያደረገውን ፡ ዲስኵር ፡ ስንመለከት ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ ነገሥታትና ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ንግግራቸውን ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሚቀርጹት ፡ ያሳየናል።

ዲስኵሩን ፡ ሲያደርግ ፡ ስምዑኒ ፡ እንግርክሙ ፡ .... ፡ ትግሬሂ ፡ ጐዣምሂ ፡ ወገራሂ ፡ ዳሞትሂ ፤ ሐድያሂ ፡ ሲል ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ደግሞ ፡ ጸሐፊው ፡ «የሸዋ ፡ የአማራና ፡ የትግሬ ፡ የጐጃም ፡ የዳሞት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ የሚበሩ ፡ እንደናዳ ፡ ድንጋይ ፡ የሚሽከረከሩ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ በሽልማት ፡ በክብር ፡ ያሳደጋቸውን ፡ ሲል ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ አገሮች ፡ የውስጥ ፡ አንድነታቸው ፡ በዘር ፡ በሃይማኖት ፡ በልማድ ፡

በቋንቋ ፡ የጠበቀ ፡ ንጉሣቸውን ፡ በዚህ ፡ በሚያስፈራና ፡ በረዥም ፡ ጦርነት ፡ ያልተለዩ ፡ መሆናቸውን ፡ ያስረዳል። ወገራ ፡ ሰሜን ፡ ጻገደ ፡ ሽፍተውበት ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳስረዳነው ፡ በሃይማኖታቸው ፡ የተነሣ ፡ ፈላሾች ፡ ወይም ፡ በዚያ ፡ በዙል ፡ ያሉ ፡ የአገው ፡ የበለውና ፡ የበጅያ ፡ እስልምናን ፡ የተቀበሉ ፡ ዘሮች ፡ ናቸው። ስለነርሱ ፡ ጦርነት ፡ ፍጻሜ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ አልገለጸልንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደተለመደ ፡ ድርጅት ፡ ያላቸው ፡ የንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ መደምሰሳቸው ፡ ኣይቀርም።

ዋናው ፡ የአዳል ፡ ጦርነት ፡ የተደረገ ፡ ዕለት ፡ “.... ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንደ ፡ ነብር ፡ ተወርውሮ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ጩሆ ፡ ኣረብ ፡ አስፈሬ ፡ እሚባለው ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ ሲል ፡ የፈረሱን ፡ ስም ፡ ዐረብ ፡ አስፈሬ ፡ ብሎ ፡ መሠየሙ ፡ ለነዚህ ፡ ተገዥዎቹ ፡ ለሆኑት ፡ ለደዋሮ ፡ ለኣዳል ፡ ባላባቶች ፡ የአረብ ፡ አገር ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በሃይማኖትም ፡ እየሰበኩ ፡ መሣሪያ ፡ እየሰጡ ፡ ጥግም ፡ እየሆኑ ፡ ያስቸገሩትን ፡ አረቦች ፡ መጥቀሱን ፡ ወይም ፡ መንካቱን ፡ ያስገነዝበናል።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ትልቅና ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ንጉሥ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ታላቅና ፡ የማይከፈል (የማይነጠል) ለማድረግ ፡ ባደረገው ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ መድከሙ ፡ አባቶቹ ፡ ያልደረሱበትን ፡ ያዳል ፡ በረሃ ፡ ዞሮ ፡ ማዳረሱ ፡ አርበኛ ፡ ንጉሥነቱን ፡ ይገልጻል። ይኸን ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ በብርታትና ፡ በዠግንነት ፡ ባይደመስሰው ፡ ኖሮ ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ የተፈጸመውን ፡ የግራኝን ፡ ወረራ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ስብር ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ የይፋቱ ፡ ባላባት ፡ ወይም ፡ የአዳሉ ፡ ሊፈጽሙት ፡ ይችሉ ፡ ነበር ፡ ድካሙን ፡ ጀግንነቱን ፡ ክርስቲያናዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሊያውቀኦለት ፡ ይገባል።

ደግሞ ፡ የደጃዝማች ፡ እሸቴ ፡ ልጅ ፡ ደጃዝማችኃይሉ ፡ አፄ ፡ ኢያሱ (ብርሃን፡ሰገድ) በነገሡበት ፡ ዘመን ፡ በ፲፯፻፹፯ ፡ ዓ.ም ፡ ሰበሰቡት ፡ በሚባለው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥ ፡ በዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ስም ፡ የተደረገ ፡ ግጥም ፡ ይገኝበታል ፡ እርሱም ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ነው።

ሐርበኛ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን።
መላላሽ ፡ የወሰን ፡

ወሀ ፡ እንደመስን ፡ መላላሽ ፡ የወሰን ፡
ከወጅ ፡ ዜብደናን ፡ ከገንዝ ፡ ጠጠን ፡
ምን ፡ ቀረህ ፡ በወሰን ፡ ከድያ ፡ ኣመኖን ፡
ምን ፡ ቀረህ ፡ በወሰን ፡ ከባሊ ፡ አሊን ፡
ከደዋሮ ፡ ሄደራን ፡ ከፈጠጋር ፡ ዜላርድን ፡
ከኢፋት ፡ ኣምበል ፡ አቦከርን ፡
ከግድም ፡ የዊሰይን ፡
ከኣንጎት ፡ ዣን ፡ አሞራን ፡
ከአገው ፡ ቤት ፡ አዢርን ፡
ከትግሬ ፡ ነገደ ፡ **ክርስቶስ** ፡ ይውረድ ፡
ኣደረግኸው ፡ ገንዙን ፡
እንዲሠራ ፡ ደውጀውን ፡
ማን ፡ ቀረህ ፡ በወሰን ፡
ኣላጸፋኸው ፡ ፊቱን ፡
አልአስማረክኸው ፡ ልጅ ፡ ሚስቱን ፡
ከጐጃም ፡ ጀን ፡ ክምርን ፡
ከጋፋት ፡ አወላሞን ፡
በዳሞት ፡ ሞት ፡ ለሚን ፡
ማን ፡ ቀረህ ፡ ከወሰን ፡
ያላጸፋኸው ፡ ፊቱን ፡
ያላስማረክኸው ፡ ልጅ ፡ ሚስቱን ፡
ሐርበኛ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡
መላላሽ ፡ የወሰን።
ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ስም ፡ የዘራ ፡
በወጅ ፡ እስከ ፡ በጥርአሞራ (በተርአሞራ)
ቃራ ፡ ይነስንስ ፡ ቃራ ፡ እንደ ፡ ጭራ ፡
በወንዶች ፡ ገራገራ ፡
በሐድያ ፡ እስከ ፡ ጉዴላ ፡
በባሕር ፡ እስከ ፡ ኤርትራ ፡

ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ስም ፡ የዘራ።

ይህ ፡ ግጥም ፡ የዚህን ፡ ታላቅ ፡ ንጉሥ ፡ ጀግንነትና ፡ አርበኝነት ፡ ከመግለጹ ፡ በቀር።

**ሀ|** በ "**ን** ፡ ,, **በ** ፤ "ራ,, ቤት ፡ እየመታ ፡ የሚሰጠን ፡ ግጥም ፡ በዘመኑ ፡ ሕዝብ ፡ ይነጋገርበት ፡ የነበረውን ፡ ግዕዝና ፡ አማርኛ ፡ የተደባለቀበትን ፡ ቋንቋ ፡ ያሳየናል። ከዚህም ፡ ጋር።

**ለ|** ሐርበኛ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ መላላስ (ሽ) የወሰን... ፡ ምን ፡ ቀረህ ፡ በወሰን ፡ ከባሊ ፡ አሊን ፡ ከደዋሮ ፡ ሃዳራን ፤ (ሐይደራ) ከኢፋት ፡ አምበል ፡ ኣቦከር (አቡበከር) ከዳሞት ፡ ሞት ፡ ለሚን (ሞተለሚ) እያለ ፡ የኣውራጆቹንና ፡ የባላባቶቹን ፡ ወይም ፡ የጥንቶቹን ፡ ባላባትነት ፡ የመሠረቱትን ፡ ስም ፡ ስለሚያነሣ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የታሪክ ፡ አስታዋሽነት ፡ አለው። በነዚህ ፡ መካከል ፡ "በዳሞት ፡ ሞት ፡ ለሚን ፡ ያለው ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ እናት ፡ ማርኮ ፡ ወሰደ ፡ የተባለውን ፡ የዳሞቱን ፡ ንጉሥ ፡ ሞተለሚን ፡ ሲያነሣ ፡ ነው። ካፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ሞተለሚን ፡ የዳሞቱን ፡ ንጉሥ ፡ በዛሬው ፡ ባምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ እንደምን ፡ ያነሣል ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ በአንባቢ ፡ ኣእምሮ ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ መልሱ ፡ ቅርብ ፡ ነው።

የይፋት ፡ የመዠመሪያው ፡ ባላባት ፡ ወላስማ ፡ ሲባል ፡ በርሱ ፡ ስም ፡ የልጅልጆቹ (ተከታዮቹ) ሁሉ ፡ ይጠሩበታል። እንደዚሁም ፡ ከመቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ የዳሞቱን ፡ ንጉሥ ፡ ስም ፡ ሞተ ፡ ለሚን ፡ ዛሬም ፡ በዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ ተከታዩ ፡ ይጠራበታል ፡ ማለት ፡ ነው።

በተረፈ ፡ የደጃዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ይኸን ፡ ግጥም ፡ ሲሰጥ ፡ የተገጠመው ፡ ለዚሁ ፡ ላምደ ፡ ጽዮን ፡ ፩ኛ ፡ ወይም ፡ በሺ፱፻፹፯ ፡ ዓ.ም ፡ መካከል ፡ ፯ ፡ ወር ፡ ለነገሠው ፡ ላምደ ፡ ጽዮን ፡ ፪ኛ ፡ መሆኑን ፡ አይለይም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፪ኛው ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በሕፃንነቱ ፡ ነግሦ ፡ በ፯ ፡ ወሩ ፡ ቢበዛ ፡ ባመቱ ፡ መንግሥቱን ፡ የለቀቀ ፡ ስለሆነ ፡ በዘመኑም ፡ እርሱም ፡ የጦር ፡ አለቆቹም ፡ የታወቀ ፡ ጦርነት ፡ ማድረጋቸው ፡ ስለአልተጻፈ ፡ ይህ ፡ ግጥም ፡ የዚሁ ፡ የዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ፩ኛ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም።

“ሐርበኛ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ መላላስ ፡ የወሰን ፡ ወሀ ፡ እንደመስን ፡ እያለ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በነበረው ፡ ከግዕዝ ፡ በተደባለቀና ፡ ባልተጣራ ፡ አማርኛ ፡ የሚናገረው ፡ በዛሬ ፡ አማርኛ ፡ ቢሆን ፡ አርበኛው ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንደ ፡ መስኖ ፡ ወሀወሰን ፡ የሚያስመልሰው ፡ ማለቱ ፡ ነበር። ይኸውም ፡ ባለፈው ፡ የተመለከትነውን ፡ የአዳልን ፡ አገር ፡ የማስገበሩን ፡ ጦርነት ፡ መጥቀሱ ፡ ይሆናል።

አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ ዠግንነቱን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ይህ ፡ ያለፈው ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ አንዳንድ ፡ መልካም ፡ ጠባዩን ፡ ይገልጽልናል።

**፩ኛ**—በሃይማኖት ፡ ረገድ ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ሲሄድ ፡ ከጦርነትም ፡ ሲመለስ ፡ መጸለዩ ፤ ድልን ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ በዠግንነቱ ፡ ሳይመካ ፡ “**እግዚአብሔር** ፡ ኃጢአቴን ፡ ሳያስብብኝ ፡ ድልን ፡ ሰጠኝ ፡ ሲል ፡ ራሱን ፡ በትሕትና ፡ **ከእግዚአብሔር** ፡ ጸጋ ፡ በታች ፡ ማድረጉ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል። ኃጢአቴን ፡ ሳያስብብኝ ፡ ያለው ፡ ምናልባት ፡ ያባቱን ፡ ዕቍባት ፡ ሚስት ፡ ኣድርጎ ፡ በማስቀመጡ ፡ ከእጨጌ ፡ ፊልጶስ ፡ ተጣልቶ ፡ ከነመነኮሳቱ ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ በማሳደዱ ፡ አባ ፡ አኖሬዎስን ፡ በማስገረፉ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ እርሱና ፡ አምላኩ ፡ የሚያውቍት ፡ ሌላ ፡ በደል ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቀም።

**፪ኛ**—የደዋሮውንና ፡ የይፋቱን ፡ የአዳሉንም ፡ ባላባቶች ፡ ከአሸነፈ ፡ በኋላ ፡ የአዳሉ ፡ ባላባት ፡ ወታደሩን ፡ ሌሎቹንም ፡ ተባባሪዎቹን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ኣፈግፍጎ ፡ መቀመጡን ፡ በተረዳ ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ በኣዳል ፡ አገር ፡ ሳለ ፡ ወታደሩንና ፡ ሹማምንቱን ፡ ወደፊት ፡ አልፈን ፡ እንዋጋ ፡ ወይስ ፡ እንመለስ ፡ እስኪንገሩኝ ፡ ቢል ፡ እንመለስ ፡ ማለት ፡ ቅር ፡ እንደሚለው ፡ የሚያውቍት ፡ ሹማምንቱ ፡ ዝም ፡ ቢሉ ፡ «የምታስቡትንሳትፈሩ ፡ ንገሩኝ ፡ ፩ ፡ ኣንድ ፡ ጊዜ ፡ መኳንንት ፡ በንጉሥ ፡ ምክር ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ በመኳንንት ፡ ምክር ፡ ሊመራ ፡ ይገባዋል ፡ ያለ ፡ ምክር ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ኣይጠቅምም ፡ ሲል ፡ መምከርና ፡ መመከር ፡ ከመውደዱ ፡ በቀር ፡ በቂ ፡ ኣሳብ ፡ ካመጡለት ፡ እርሱ ፡ የበላዩ ፡ በበታቾቹ ፡ በመኳንንቱ ፡ ምክር ፡ መመራትን ፡ እንደመረጠ ፡ ለመኳንንቱም ፡ እንደልባቸውአሳብ ፡ የመስጠት ፡ መብት ፡ እንደሰጣቸው ፡ ይታያል። በዚህ ፡ ሁኔታውን ፡ እዛዝ ፡ ናዛዝ ፡ የበላዩ ፡ መሪው ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡

ነኝና ፡ የማዛችሁን ፡ በቀጥታና ፡ በግዴታ ፡ ፈጽሙ ፡ ከሚሉ ፡ አስገዳጅ ፡ መሪዎች (ዲክታተሮች ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ ማለት ፡ ነው።

**፫ኛ**— በጦር ፡ መሪነቱ ፡ ልበ ፡ ሙሉ ፡ ዠግንነት ፡ ያለው ፡ ደንበኛ ፡ መሪና ፡ ንጉሥ ፡ መሆኑን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሡ ፡ ነጋሥታዊ ፡ ሰፊ ፡ ግዛት ፡ ሳይቀነስና ፡ ሳይከፈል ፡ ከዳር ፡ ዳር ፡ ሁሉም ፡ በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ተባብሮእንዲኖር ፡ ሙሉ ፡ ጥረት ፡ ያለውና ፡ ጥረቱ ፡ በሥራ ፡ የተገለጸ ፡ ንጉሥ ፡ ነው። ይኸንንም ፡ የአዳልን ፡ ሰፊ ፡ በረሀዘልቆ ፡ ያደረገው ፡ ጦርነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከአዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ሲነጋገር ፡ እናንተም ፡ አባታችሁም ፡ ሰው ፡ የማይበድለውን ፡ በደል ፡ በደላችሁኝ። በመገበር ፡ ፈንታ ፡ እኔን ፡ የመላውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ወጋችሁኝ ፡ እያላ ፡ ያቀረበው ፡ ወቀሳ ፡ ያስረዳል።

**፬ኛ**— የጦር ፡ መሪነትና ፡ ልበ ፡ ሙሉ ፡ ዠግንነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የጦር ፡ ኣመራርና ፡ ጠላትን ፡ የሚያጠቃበትን ፡ ዘዴ ፡ መፍጠር ፡ ያውቅ ፡ ነበር። አራቲ ፡ እሚባለው ፡ ኣገር ፡ ሠፈር ፡ ኣድርጎ ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ምላጭ ፡ በጥርሳቸው ፡ የወታደሮቹን ፡ ሞሮ ፡ ቆርጠው ፡ በሰለቧቸው ፡ ጊዜ ፡ ይኸንኑ ፡ ለመበቀል ፡ ሲል ፡ እርሱ ፡ ሠፈሩን ፡ ሲለቅ ፡ እነዚያ ፡ ሠፍሮበት ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ቦታ ፡ መምጣታቸው ፡ እንደማይቀር ፡ ኣስቦ ፡ እኔ ፡ ጥሩምባ ፡ እያስነፋሁ ፡ ፈሬን ፡ ለቅቄ ፡ ስሄድ ፡ እናንተ ፡ በጫካ ፡ ተደብቃችሁ ፡ ዐይታችሁ ፡ ሲመጡ ፡ ግደሏቸው ፡ ብሎ ፡ በብልሃት ፡ የኣሽከሮቹን ፡ ደም ፡ ተበቀላ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በሃይማኖትም ፡ በዠግንነትም ፡ በኣስተዳዳሪነቱም ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ላይ ፡ በዘመኑ ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ የተነሣ ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ የጻፈለትን ፡ ብቻ ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ ጕድለት ፡ የሌለበት ፡ ንጉሥ ፡ አድርገን ፡ ልንመለከተው ፡ አንችልም። ጸሐፊው ፡ የሚያሳየን ፡ የደጉን ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ወደጦርነት ፡ ሲሄድወይም ፡ ሲመለስ ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ጸለየ ፡ ያለውም ፡ ራሱ ፡ ያዘጋጀው ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም። በዚህ ፡ በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ላይም ፡ ያልተገለጸ ፡ የአስተዳደርም ፡ የጭካኔም ፡ የአድልዎም ፡ ስሕተትበዘመኑ ፡ እንደቀሩት ፡ ነገሥታት ፡ እንደሰው ፡ ሁሉ ፡ መሥራቱ ፡ ኣይቀርም።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይኸ ፡ - ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ንጉሥ ፡ ከአዳል ፡ ጦርት ፡ ተመልሶ ፡ የሠራውን ፡ ሳይገልጽልን ፡ ዜና ፡ መዋዕሉና ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ሁሉ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ነግሦ ፡ መሞቱን ፡ ከርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ልጁ ፡ ንዋየ ፡ **ክርስቶስ** (ሰይፈ ፡ አርእድ) መንገሡን ፡ ብቻ ፡ ይገልጽልናል። ነገር ፡ ግን ፡ በሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ የሠራውንስንፈላለግ ፡ ሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ "የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ የወርቅ ፡ ወንጌል ፡ ብሎ ፡ በአወጣው ፡ መጽሐፍ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንና ፡ ባለቤቱ ፡ ለኣባ ፡ ማጣ (መጣዕ) ገዳም ፡ የሰጡትን ፡ ርስተ ፡ ጉልት ፡ እንመለከታለን።

# ምዕራፍ ፡ ፲፯።

## ለአባ ፡ መጣዕ (ሊባኖስ)ገዳም ፡ ኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የሰጠው ፡ ጉልት።

ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ አረመኔም ፡ ቢሆን ፡ እስላም ፡ ይሁዲም ፡ ቢሆን ፡ ክርስቲያን ፡ ለሚያመልክበት ፡ ለአምላኩ ፡ እንዲሁም ፡ ለቅዱሳኑ ፡ ለሰማዕታቱ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ መሥራትና ፡ ቤተ ፡ መቅደሱን ፡ በስጦታ ፡ ማከበር ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ የቆየ ፡ ነው። የቀሩትን ፡ እንለፋቸውና ፡ የካቶሊክም ፡ የተዋሕዶም ፡ አገሮች ፡ ነገሥታት ፡ በዚሁ ፡ ይዞታ ፡ በሚወዱት ፡ ቅዱስና ፡ ሰማዕት ፡ ስም ፡ ብዙ ፡ ገዳማት ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኣሠርተዋል። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ በየጊዜው ፡ የተነሡት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ በየጊዜው ፡ በየአውራጃው ፡ የሠሩት ፡ ብዙ ፡ ነው። ወደፊት ፡ ባሉት ፡ ነገሥታት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ሲሠራ ፡ የምንመለከተው ፡ የበረከተ ፡ ነው።

ደግሞ ፡ አንድ ፡ ገዳም ፡ እንደ ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ እንደ ፡ ደብረ ፡ ቢዘን ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ በሸዋ ፡ እንዳለው ፡ እንደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ያለው ፡ ባንድ ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ ተተክሎ ፡ ጻድቁ ፡ ጸሎትና ፡ ስለት ፡ ሰሚ ፡ ነው ፡ ጠበሉ ፡ ድውይ ፡ ይፈውሳል ፡ ተብሎ ፡ እጅግ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በየጊዜው ፡ የሚነሡት ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ለዚህ ፡ ገዳም ፡ ወይም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

ከርስታቸው ፡ ከሀብታቸው ፡ እየከፈሉ ፡ ለነፍሳቸው ፡ ድኅነት ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ ስጦታ ፡ መስጠት ፡ ልማዳቸው ፡ ነው።

በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ለአክሱም ፡ ጽዮን ፡ ለቀሩትም ፡ ገዳማትና ፡ አድባራት ፡ የሚገባውን ፡ እንለፍና ፡ ለአባ ፡ መጣዕ ፡ ከአፄ ፡ ላሊበላ ፡ ካሄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ የተሰጠውን ፡ ርስተ ፡ ጕልት ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተመልክተናል። በዚያው ፡ በላሊበላ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ ኣባ ፡ መጣዕ ፡ ወይም ፡ ሊባኖስ ፡ የሚባሉት ፡ መነኰሴ ፡ ባፄ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት (፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ላይ) ከአንጾኪያ ፡ መጥተው ፡ በትግሬ ፡ አውራጃ ፡ በሠራዌ ፡ ወንጌል ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር። ቀጥሎም ፡ በስማቸው ፡ የሚጠሩትን ፡ ሁለት ፡ ገዳማት ፡ ኣንዱን ፡ በራሳቸው ፡ ስም ፡ እንዳ ፡ አባ ፡ መጣዕ ፡ የሚባለውን ፡ በከሣድ ፡ ዳሮ (ዳዓሮ)በሠራዌ ፡ ገድመው ፡ ነበር ፤ በዚህም ፡ ገዳም ፡ ኣጠገብ ፡ ድውይ ፡ የሚፈውስ ፡ ጠበል ፡ አለ ፡ እየተባለ ፡ ከየአገሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ስለሚሰበሰቡ ፡ አፄ ፡ ሠይፈ ፡ አርዕድ (ሺ፫፻፴፮ - ሺ፫፻፷፮ ፡ ዓ.ም)የሚባለው ፡ ንጉሥ ፡ የዚሁ ፡ የዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ልጅ ፡ አክሱም ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፡ ጦሩን ፡ በሽታ ፡ ቢፈጅበት ፡ ወደዚህ ፡ ጠበል ፡ አምጥቶ ፡ እንዲፈወስ ፡ ኣድርጎታል ፡ ሲል ፡ ተአምረ ፡ ሊባኖስ ፡ የሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሚያረጋግጥ ፡ ሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ገለጿል።

ሌላው ፡ ፪ኛው ፡ ገዳም ፡ ደግሞ ፡ በሠናፌ ፡ ውስጥ ፡ አጋሜ ፡ ግዛት ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተብሎ ፡ አሁንም ፡ በስማቸው ፡ የሚጠራውን ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ገዳም ፡ የመሠረቱት ፡ እኒሁ ፡ አባ ፡ መጣዕ ፡ ወይም ፡ ሊባኖስ ፡ የሚባሉት ፡ መነኰሴ ፡ ናቸው። ስለዚህ ፡ መነኰሴውና ፡ ገዳሙ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ ላሊበላ ፡ ፲፩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ባሠራ ፡ ጊዜ ፡ ኣንዱን ፡ ቤተ ፡ ሊባኖስ ፡ ብሎ ፡ ሠይሞታል። ወደፊት ፡ ባላው ፡ ጊዜ ፡ አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ (ሺ፬፻፳፮–ሺ፬፻፷ ፡ ዓ.ም) የዛሬውን (የፍቼውን ፡ ገዳም) ከዚያ ፡ በፊት ፡ ደብረ ፡ አስቦ ፡ ይባል ፡ የነበረውን ፡ ስሙን ፡ ለውጠው ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ብለው ፡ የሠየሙት ፡ በእኝሁ ፡ መነኰሴና ፡ በገዳማቸው ፡ ስም ፡ መሆኑ ፡ ነው።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ለአባ ፡ መጣዕ (ደብረ ፡ ሊባኖስ) ገዳም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ዓፄ ፡ ገብረ ፡ መስቀል፣አፄ ፡ ላሊበላ ፤ አፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ እንደሰጡት ፡ ርስትና ፡ ጒልት ፡ የዚህ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንና ፡ ባለቤቱ ፡ ለዚሁ ፡ ገዳም ፡ ርስትና ፡ ጒልት ፡ ሰጥተዋል። የስጦታቸውም ፡ ጽሑፍ ፡ በዚሁበኣባ ፡ መጣዕ ፡ ገዳም ፡ ባለው ፡ ወንጌል ፡ ወደመጨረሻው ፡ ከቀሩት ፡ ነገሥታት ፡ ስጦታ ፡ ጋር ፡ ተዘርዝሮ ፡ ይገኛል።

ኢጣሊያኖች ፡ አስመራን ፡ በሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ከአስመራ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ መሪና ፡ አጃቢ ፡ ተቀብሎ ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ መጥቶ ፡ ጐብኝቶታል ፤ ቀጥሎም ፡ የገዳሙን ፡ መምህር ፡ መምህር ፡ ገብረ ፡ ሕይወትን ፡ አግኝቶ ፡ በትውስት ፡ ለምኖ ፡ መቀበሉንና ፡ የስጦታዎቹን ፡ ጽሑፍ ፡ ማግኘቱን ፡ ይገልጻል። ስለዚህ ፡ በሙሴ ፡ ኮንቲሮሲኒ ፡ ታትሞ ፡ የተራባው

መጽሐፍ ፡ ያፄ ፡ ዓምደጽዮንን ፡ ስጦታ ፡ የሚገልጸው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው።

«በአኰቴተ ፡ **አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** በ፳፻ወ፳ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ወሀብኩ ፡ ኣነ ፡ ዐምደ ፡ ጽዮን ፡ ንጉሥ ፡ ለአባ ፡ መጣዕ ፡ ዘአሃምከመ ፡ ይትወሐሰኒ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወርቅ ፡ ፻፹ወ፪ ፡ ወ፪ ፡ መስቀል ፡ ዘወርቅ ፡ ወ፩ ፡ ጻሕል ፡ ዘወርቅ ፡ ወ፩ ፡ ጽዋዕ ፡ ዘወርቅ ፡ ወ፩ዱ ፡ ጻሕል ፡ ዘብሩር ፡ ወ፩ ፡ ጽዋዕ ፡ ዘብሩር ፡ ወአልባስ ፡ ክብር ፡ ፻፫ ፡ ለቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ዘመጣዕ ፡ ወለቅዱሳንሂ ፡ ፵ ፡ ብዙት ፡ ወለካልኣንሂ ፡ ኣብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ፡ ዘመጣዕ ፡ ፴ ፡ ልብስ ፡ ክቡራት ፡ ወአልሕምትሂ ፡ ፲ወ፪ ፡ ወእምድኅረ ፡ ኵሎን ፡ ወሀብኩ ፡ ልብሰ ፡ ወርቅ ፡ ዘላዕሌየ ፡ ወዕጣቅየ ፡ ወ፪ ፡ ሰራዌልየ ፡ አውጺእየ ፡ እምውስተ ፡ ሐቃየ ፡ ወ፪ተ ፡ አሳንየ (አሳዕንየ?) እምእገርየ ፡ ወዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ዘወሀብኩ ፡ አእሚርየ ፡ ከመ ፡ የሐልፍ ፡ ንብረተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ይትወሐሰኒ ፡ ፍቅኀርየ ፡ መጣዕ ፡ በመንግሥት ፡ ሰማያት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ፡ ወለንጉሥነ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘስዕበዮ ፡ እምነገሥተ ፡ ምድር ፡ ያኑኅ ፡ መዋዕሊሁ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ወይረስዮ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ሥሩዓ ፡ ከመ ፡ ወርኅ ፡ ወብሩሃ ፡ ከመ ፡ ፀሐይ ፡ ወይዕቀብ ፡ አንስቲያሁ ፡

ወደቂቆ ፡ ወደቂቀ ፡ ደቂቆ ፤ ወዓዲ ፡ ያድኅኖሙ ፡ ለሠራዊቱ ፡ እምስረተ ፡ ሐጽ ፡ ወውግረተ ፡ እብን ፤ ወያግርር ፡ ፀሮ ፡ ወጸላዕቶ ፡ ወበዕለተ ፡ ሞቱሂ ፡ ይኍልቆ ፡ ምስለ ፡ ቅዱሳን ፡ ወሰማዕት ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ኣስመርዎ ፡ **ለእግዚአብሔር** ፡ ምስለ ፡ ዳዊት ፡ ወቆስጠንጢኖስ ፡ ወአኖርዮስ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን። ወአንትሙሂ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ ሀለውክሙ ፡ ውስተ ፡ መካነመጣዕ ፡ ጸልዩ ፡ ለንጉሥነ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ሠርካ ፡ ወነግሀ ፡ ሌሊተ ፡ ወመዓልተ ፡ ቀትረ ፡ ወሰዓተ ፡ በውስተ ፡ ቍርባንሂ ፡ ወበውስተ ፡ ማኅበርሂ ፡ ወኀበ ፡ ተጋባእክሙሂ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን። »

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ ባለቤቱ ፡ በራሷና ፡ በባለቤቷ ፡ በዔ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ስም ፡ የሰጠችውን ፡ እንመልከት።

“በአኰቴተ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በ፳፻ወ፯ ፡ ዓመትምሕረት ፡ ወሀብኩ ፡ አነ ፡ ብሌን ፡ ሳባ ፡ በዓልተ ፡ ቢሐት ፡ ብእሲቱ ፡ ለዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ንጉሥ ፡ በእንተ ፡ ፍቅሩ ፡ ለመጣዕ ፡ ከመ ፡ ይትወሐሰኒ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አመ ፡ እቀውም ፡ እራቅየ ፡ ቅድመ ፡ ሰማያዊ ፡ ንጉሥ ፡ ገላባ ፡ ወሰንቅርያ ፡ ወሀብኩ ፡ ዘንተ ፡ ጒልተ ፡ ለብፁዕ ፡ መጣዕ ፡ ፍቍርየ ፡ ዘኢይበውኦ ፡ ፈረስ ፡ ወኢአንበሳ ፡ ወኢሥዩመ ፡ ደብረ ፡ ማዕያ ፡ ወኢሥዩመ ፡ ዘሬዳ ፡ ኢዘተሠይመ ፡ ወኢዘተስእረ ፡ ወዘኢተነግሡ ፡ ወኢዘኣንሥገሡ ፡ ዘኢያበውኦ ፡ ቃለ ፡ ነጋሲ (ሢ) ወኢደቀ ፡ ጽርሕ ፡ ወለእመቦ ፡ ዘተፀገለ ፡ ወዘተዓየለ ፡ ዘንተ ፡ ጒልተ ፡ ዘወሀብኩ ፡ ለአባ ፡ መጣዕ ፡ ዘአሀም ፡ እንዘ ፡ ንጉሥ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ወእንዘ ፡ ሠየምተ ፡ እንትርታ ፡ ብሌን ፡ ሳባበዓልተ ፡ ቢሐት ፡ ወእንዘ ፡ ማዕከለ ፡ ባሕር ፡ ሰማይ ፡ ወእንዘሥዩመ ፡ ደብረ ፡ ማፅያ ፡ መጥሬ ፡ እግዚእ ፡ ወእንዘ ፡ ሥዩመ ፡ ዘሬዳ ፡ ዘርዐ ፡ ዳዊት ፡ ወእንዘ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓተ ፡ መጣዕ ፡ ገብረ**ክርስቶስ** ፡ ወዘንተ ፡ ዘወሀብኩኣእሚርየ ፡ ከመ ፡ የሐልፍ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ወሰማዕኩ ፡ ዘይቤ ፡ ቃል ፡ መክብብ ፡ ከንቱ ፡ ዙሉከንቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘአቅደመ ፡ ስንቆ (በሒወቱ) በሕይወቱ ፡ ወአነሂ ፡ ወሀብኩ ፡ ለመጣዕ ፡ ወለቅዱሳን ፡ ፬ወ፶ ፡ አልህምት ፡ ወአልባስ ፡ ሰንዱናት ፡ ወመ ፡ ባእዚ ፡ ጽዒንየ ፡ ዘአውረድኩ ፡ በአምሐራ ፡ ወእመቦ ፡ ዘተኀየለ ፡ በንተ ፡ ጒልተ ፡ ዘወሀብኩ ፡ አነ ፡ ለመጣዕ ፡ ፍቀኍርየ ፡ ውጉዝ ፡ ለይኩን ፡ በአፈ ፡ ፲ወ፰ ፡ ነቢያት ፡ ወበአፈ

: ፲ወ፪ : ሐዋርያት : በአፈ : ፫፻፲ወ፰ : ርቱዐነ : ሃይማኖት : ወበአፈ : ጴጥሮስ : ሊቀ : ጳጳሳት : ወበጸሎቱ : ለብፁዕ : መጣዕ : ወበአፈ : **ኣብ : ወወልድ : ወመንፈስ : ቅዱስ :** ውጉዘ : ለይኩን : በዝ : ዓለም : ወበዘይመጽእ : ዓለም : ዘኢይትፈታሕ : በጾም : ወበጸሎት : በስኣል : ወበሰጊድ : ለዓለመ : ዓለም : አሜን።

ወዘአግባእኩ : ዘንተ : ጉልተ : ወዘንተ : ኵሉ : ዘገበርኩ : ዘአዘዘኒ : እግዚእነ : ንጉሥ : ዓምደ : ጽዮን : ወይቤለኒ : ሑሪ : ብጽሒ : ኀበ : መጣኣ : ዘአሀም : ወግበሪ : ፈቃዶ : ለብፁዕ : መጣዕ : ፍቍርየ : ወበሊ : ኢትንሥኡ : እግዚኦ : በመዋዕለ : ውርዙቱ : ለእግዚእየ : ዓምደ : ጽዮን። ወበጻሕኩ : አነኒ : ወበከይኩ : ወለሐውኩ : ወአንገርገርኩ : ኀበ : መቃብሩ : ለመጣዕ : በከመ : አዘዘኒ : እግዚእየ : ዓምደ : ጽዮን : ግበር : ሎቱ : እግዚኦ : በከመ : ፈቃደ : ልቡ : ወይቤለኒ : ሀቢ : እንቀርዖ : ወገለበ : ከመ : የሀበኒ : **እግዚአብሔር** : በመንግሥተ : ሰማያት : ህየንተ : ኀዳጥ : ብዙኀ : አሜን : የሀቦ : **እግዚአብሔር** : ሕየንተ : ዘበምድር : ዘበሰማያት : ኣሜን። ህየንተ : ዘይበሊ : ዘኢይበሊ : አሜን። ወህየንተ : ዘይማስን : ዘኢይማስን : አሜን። ወያኑኀ : መዋዕሊሁ : በዲበ : ምድር : አሜን። ወያግርር : ፀሮ : ወጸላእቶ : አሜን። ወይስረይ : ኃጢአቶ : ወይደምስስ : መጽሐፈ : ዕዳሁ : አሜን። የሀቦ : **እግዚአብሔር** : ጥበበ : በከመ : ሰሎሞን : አሜን። የሀቦ : **እግዚአብሔር** : ሞገሰ : በከመ : ዳዊት : አሜን። የሀቦ : **እግዚአብሔር :** ትእግሥተበከመ : ኢዮብ : አሜን። የሀቦ : **እግዚአብሔር** : መዊዓ : ከመ : ኢያሱ : ኣሜን።

ወለይእቲኒ : ብሌን : ሳባ : በዐልተ : ቢሐት : የሀባ : **እግዚአብሔር** : ፍቅረ : ምስለ : ምታ : ዓምደ : ጽዮን : ዘገብረ (ት) ፈቃዶ : በመልእክናሃ : በከመ : ገብርብፁዕ : ጌር : ዘያስተፌሥሕ : እግዚኡ : በመልእክቱ : ከማሁ : ሠናየ : ገብረት : በመልእክት : የሀባ : **እግዚአብሔር** : ዕሤተ : አሜን። <u>የሀባ</u> : **እግዚአብሔር** : መዋዕላ : ብዙኀ : በፍሥሐ : ዘአልቦ : ሐዘን : ምስለ : ምታ : ዓምደ : ጽዮን : አሜን። ወአመ : ዕለተ : ጽዋዐሆሙ : ያስምዖሙ : **እግዚአብሔር** : ቃለ : ፍሥሐ : ዘይበል : ንፁ : ኀቤየ : ቡሩካኑ : ለአቡየ : ትረሱ : መንግሥተ : ዘአስተዳለወ : ለክሙ : እምቅድመ : ዓለም : ኣሜን።

ወይባርክ ፡ ውሉዶሙ ፡ አሜን። ወያብዝኅ ፡ ዘርዖሙ ፡ ከመ ፡ ኮከበ ፡ ሰማይ ፡ ወከመ ፡ ኆፃ ፡ ባሕር ፡ አሜን። ወአሜን። ወይበል ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ አሜን ፡ ወአሜን። ወኵልክሙ ፡ እላ ፡ ኣንበብክሙ ፡ ጸልዩ ፡ ለንጉሥ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ወለንግሥት ፡ ብሌን ፡ ሳባ ፡ ከመ ፡ ይምሐሮሙ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ በሰማይ ፡ ወበምድር ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ኣሜን ፡ ወአሜን።

ከዚህ ፡ ውስጥ ፡ እንደምንመለከተው ፡ ሄደሽ ፡ በልጅነቱ ፡ ዘመን ፡ ኣትውሰደው (አትግደለው) ብለሽ ፡ ጸልየሽ ፡ ይኸን ፡ ጒልት ፡ ለአባ ፡ መጣዕ ፡ ስጭልኝ ፡ ብሎ ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሡ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ኣዘዘኝ ፡ የምትለው ፡ ባለቤቱ ፡ ነች ፡ እርሷም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በሚስትነቷ ፡ ላይ ፡ የእንትርታን ፡ ሹመት ፡ ይዛለች። ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የጦርነት ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የጦርሠራዊት ፡ የሹመት ፡ ማዕርግና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ አንብበናል ፡ በዚህ ፡ ስለጒልቱ ፡ በሚናገረው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ ባለቤቱ ፡ ብሌን ፡ ሳባ ፡ በዓልተ ፡ ቢሐት ፡ ተብላ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ሥይምተ ፡ እንትርታ ፡ ስትባል ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ በስሜን ፡ በትግሬ ፡ ውስጥ ፡ የቤተ ፡ ክህነትና ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሹመት ፡ የያዙ ፡ ማዕከለ ፡ ባሕር (ሹሙ ፡ ሰማይ) ሥዩመ ፡ ደብረ ፡ ማዕዖ (ሹሙ ፡ መጥሬ ፡ እግዚእ) ሥዩመ ፡ ዘሬዳ (ሹሙ ፡ ዘርዐ ፡ ዳዊት) ዓቃቤ ፡ ሰዓተ ፡ መጣዕ (ሹሙ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ) ይባላሉ።

ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደአመለከትነው ፡ እንደክርስቲያን ፡ ነገሥታት ፡ ደንብ ፡ ባንድ ፡ ሚስት ፡ አለመወሰኑን ፡ የጦርነቱ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በግልጽ ፡ እንዳስረዳን ፡ የዚህም ፡ የስጦታውና ፡ የጒልቱ ፡ ጽሑፍ ፡ «ወያኑኅ ፡ መዋዕሊሁ.... ወይዕቀብ ፡ ኣንስቲያሁ (ሚስቶቹ) ፡ ብሎ ፡ አብዝቶ ፡ ገልጾልናል።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህቺ ፡ ስለ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዕድሜና ፡ ሕይወት ፡ ለአባ ፡ መጣዕ ፡ ገዳም ፡ ጒልት ፡ የሰጠችው ፡ በጦርነቱ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ ካየናቸው ፡ ከሁለቱ ፡ የትኛዋ ፡ መሆኗን ፡ በግልጽ ፡ ማወቅ ፡ ይቸግራል። በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ላይ ፡ ታሞ ፡ ሊዋጋ ፡ ሲሄድ ፡ ያኸው ፡ አትልቀቂው ፡ ብላ ፡ ታናሽቱ ፡ ለታላቂቱ ፡ ነገረቻት ፡ ይላል ፡ ታላቂቱ ፡ የተባለችው ፡ በዚያው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ

፡ እንደሚታየው ፡ ስሟ ፡ ዣን ፡ መንገሣ ፡ ይባላል ፡ እርሷም ፡ ታላቂቱ ፡ እንጂ ፡ ታናሽቱ ፡ አይደለችም።

ስለዚህ ፡ ጉልቱን ፡ ያገባችው ፡ ምናልባት ፡ ቲንሿ ፡ ንግሥት ፡ ስሟ ፡ በዚህኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ብሌን ፡ ሳባ ፡ ተብሎ ፡ የተገለጸው ፡ ይሆናል። ነገር ፡ ግን ፡ ወደፊት ፡ በነ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ እንደምንመለከተው ፡ ንግሥቶቹ ፡ እንደነገሥታቱ ፡ በመጠሪያና ፡ በስመ ፡ መንግሥት ፡ የተለየ ፡ ሁለት ፡ ስም ፡ ስለ ፡ አላቸው ፡ የዋናይቱ ፡ የታላቂቱ ፡ ንግሥት ፡ ስም ፡ መጠሪያ ፡ ስሟ ፡ ብሌን ፡ ሳባ ፤ ስመ ፡ መንግሥቷ ፡ ዣን ፡ መንገሣ ፡ ይሆናል ፡ ይልቁንም ፡ "ዣን" የሚባለው ፡ ቃል ፡ የተጨመረበት ፡ ለንግሥት ፡ ሲሆን ፡ እንደስመ ፡ መንግሥት ፡ ዣን ፡ በለው ፤ ዣን ፡ ቀንጠፋ ፤ ዣን ፡ ገደብ ፤ ዣን ፡ ገዳብ ፡ ዣን ፡ ደረባ ፡ ....እየተባለ ፡ ለሹም ፡ ለወታደር ፡ ለቤት ፡ ጠባቂ ፡ ሲሰጥ ፡ የንጉሥ ፡ ኣሽከር ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል። ይኸንንም ፡ ወደ ፡ ነገሥታቱ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ስንገባ ፡ ይበልጥ ፡ ያስረዳናል።

ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ በዘመኑ ፡ ለኝሁ ፡ ለአባ ፡ መጣዕ ፡ ራሱም ፡ በቀጥታ ፡ በሚስቱ ፡ በብሌን ፡ ሳባ (ሳብአ) በሹማምንቱ ፡ **በክርስቶስ** ፡ ኣቡሁ ፡ በዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ገብረክርስቶስ-አማካይነት ፡ የሰጠው ፡ ስጦታና ፡ ርስት ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ሁሉንም ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ብንዘረዝረው ፡ አንባቢን ፡ ከማድከም ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ ከተጻፈው ፡ ውጭ ፡ አዲስ ፡ ለታሪክ ፡ የሚያገለግል ፡ ጽሑፍ ፡ እምብዛም ፡ አናገኝበትም። ባንደኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ባሕር ፡ ኣሰግድ ፡ የሚባለው ፡ ያምደ ፡ ጽዮን ፡ ፫ኛ ፡ ልጁ ፡ የ<u>ሐስጓና</u> ፡ <u>የአቃንጻን ፡ ሹመት ፡</u> ይዞ ፡ እንደነበረ ፡ ይገልጻል።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ንጉሥ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲገዛ ፡ ብዙ ፡ የሠራው ፡ ያስተዳደር ፡ የጦርነት ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ መኖሩ ፡ ሳይቀር ፡ የተጻፈ ፡ ባለመገኘቱ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ሁሉ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ገዝቶ ፡ መሞቱን ፡ በመንግሥቱም ፡ ልጁ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ (ሰይፈ ፡ አርእድ) መተካቱ ፡ ብቻ ፡ ይገልጽልናል።

# ምዕራፍ ፡ ፲፰።

## ያፄ ፡ ዓምደጽዮን ፡ ተከታይ ፡ አፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ።

ዓፄ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ይባላል ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ የሚሉም ፡ ኣሉ። ከመጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ይበልጥ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘው ፡ ግን ፡ በስመ ፡ መንግሥቱ ፡ በሰይፈ ፡ ኣርዕድ ፡ ነው። እርሱም ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ፩ኛ ፡ ልጅ ፡ ነው። ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ የገዛበትን ፡ ዘመን ፡ ፳፰ ፡ ዓመት ፡ መሆኑን ፡ ሲገልጽ ፡ በዚህ ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ የሠራው ፡ ነገር ፡ ተዘርዝሮ ፡ አይገኝም። በዚሁ ፡ በታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ባጭሩ ፡ የሚገኘው ፡ እንደዚህ ፡ ይላል። ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘውእቱ ፡ ሰይፈ ፡ ኣርዕድ ፡ ወልዱ ፡ ለሐፄዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ነግሠ ፡ ፳ወ፰ተ ፡ ዓመት ፡ ወውእቱ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ዘሖረ ፡ እስከ ፡ ትግሬ ፡ ወዐርገ ፡ ደብረ ፡ በንኰል ፡ ወረከቦ ፡ ለአባ ፡ መድኃኒነ ፡ እግዚእ ፡ ከዊኖ ፡ ድቀቀ ፡ አረጋዌ ፡ ወተባሪኮ ፡ እምኔሁ ፡ ሖረ ፡ ወጸብዖ ፡ ለላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ሶበ ፡ ሞቅሖመስፍነ ፡ ምስር ፡ ላኣባ ፡ ማርቆስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡ ፩ ፡ እም ፻ወ፬ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በምክንያተ ፡ ጸባሕት። ወእምዝ ፡ ፈትሖ ፡ ዝንቱ ፡ መስፍን ፡ ለውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወሜጦ ፡ ውስተ ፡ ሢመቱ ፡ ወዝንቱ ፡ ዜና ፡ ሀሎ ፡ በስንክሳር ፡ አመ ፡ ፲ወ፱ ፡ ለጥቅምት ፡ ወበ፳ወ፩ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ኮነ ፡ ፍልሰተ ፡ ዐፅሙ ፡ ላአቡነተክለ ፡ ሃይማኖትይልና ፡ ከዚያ ፡ ልጁ ፡ ንዋየ ፡ ማርያም ፡ ነገሠ ፡ ወደማለት ፡ ይሻገራል። በዚህ ፡ ኣጭር ፡ የግዕዝ ፡ ታሪከ ፡ ውስጥ ፡ የምናገኘው ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ እስካ ፡ ትግሬ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ በደብረ ፡ በንኰል (ገዳም)ገብቶ ፡ በሽምግልና ፡ የወደቁትን ፡ አባ ፡ መድኃኒነ ፡ እግዚእ ፡ የሚባሉትን ፡ መምህር ፡ አግኝቶ ፡ ከርሳቸው ፡ ቡራኬ (ምረቃከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ሄዶ ፡ ፳፬ኛውን ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በግብር ፡ ምክንያት ፡ ከኣሠረው ፡ ከግብፁ ፡ መስፍን ፡ ጋር ፡ መዋጋቱንና ፡ በዚሁ ፡ መስፍኑ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱን ፡ ከእሥራታቸው ፡ ፈትቶ ፡ እሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሹመታቸው ፡ መመለሱን ፡ ብቻ ፡ ነው።

ባላፈው ፡ ታሪክ ፡ ሁሉበየምዕራፉ ፡ እንዳስታወስነው ፡ የግብፅ ፡ ነገሥታት (ሱልጣን ፤ ወይም ፡ ከሊፋ) የሚባሉት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቱን ፡ ከኑብያም ፡ ከኢትዮጵያም ፡ ከእስክንድርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችሁ ፡ የምታገኘው ፡ ጥቅም ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ ግብር ፡ ክፈሉ ፡ እያሉ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቱን ፡ ማጕላላታቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ የተነሣ ፡ አፄ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ (ሰይፈ ፡ አርዕድ) ለውጊያ ፡ ወደ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ቢሄድ ፡ ፈርቶ ፡ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ተሸንፎ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱን ፡ ፈትቶ ፡ እቀድሞ ፡ ሥልጣናቸው ፡ መመለሱ ፡ የሚያጠራጥር ፡ ነገር ፡ አለበት። ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ግብፅን ፡ የሚያስተዳድሩት ፡ ማመሉክ ፡ የግዛታቸው ፡ ስፋት ፡ እንኳ ፡ ባይሆን ፡ የኃይላቸው ፡ ብዛት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የበለጠ ፡ ነው። በዚህም ፡ ላይ ፡ የቱርክና ፡ የዐረቦችን ፡ ኣገር ፡ ዝምድና ፡ ተደግፏል። ምናልባት ፡ ዓፄ ፡ ሠይፈ ፡ አርዕድ ፡ ለውጊያም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሱን ፡ እስራት ፡ ሁኔታ ፡ ለማወቅ ፡ ወደ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ወሰን ፡ ወደ ፡ ሚሆን ፡ ወደ ፡ ኑብያ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ሳለ ፡ በዚያው ፡ እንዳለ ፡ ከግብፆቹ ፡ ተገናኝተው ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ወይም ፡ ሳይዋጉ ፡ ግብፆቹም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱን ፡ እንዲፈቱ ፡ ንጉሡም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባሉት ፡ እስላሞች ፡ ላይ ፡ ኣገዛዝ ፡ እንዳያጸና ፡ ተነጋግረው ፡ ተስማምተው ፡ ተመልሰው ፡ ይሆናል።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ያሎት ፡ የግብፅ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሱልጣን ፡ መሊክ ፡ ኤስሳሊሕና ፡ ይልቍንምሞግዚቱ ፡ ኤሚር ፡ ሼኵም ፡ ተድላና ፡ ፍስታድልወት ፡ ተሰማችሁ ፡ ብለው ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በክርስቲያኖቹም ፡ በይሁዲዎቹም ፡ ላይ ፡ ቀረጥና ፡ ግብርን ፡ ምክንያት ፡ እያደረጉ ፡ ያለምክንያትበሺ፲፻፶፫–፶፯ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ ስደት ፡ እስራት ፡ አምጥተውባቸው ፡ እንደነበረ ፡ የዐረቦችም ፡ የፈረንጆቹ ፡ ጸፊዎች ፡ ጠቅሰውታል።

በተረፈ ፡ አፄ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ (ሰይፈ ፡ አርዕድ) እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከይፋት ፡ ወላስሞች ፡ ጋር ፡ ተዋግቷል። ሰብር ፡ ኣድ ፡ ዲን (ሰብረዲን)ከኣፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ከርሱ ፡ ወዲህ ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ልጁ ፡ አሊ ፡ ተቀምጦ ፡ በይፋት ፡ ይገዛ ፡ ነበርና ፡ እርሱም ፡ እንዳባቱ ፡ ባፄ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ ላይ ፡ ሸፍቶ ፡ ሲዋጋ ፡ ተሸንፎ ፡

በምርኮ ፡ ተያዘና ፡ ግዛቱ ፡ ላልጁ ፡ ለአሕመድ ፡ ሐርብ ፡ አራድ ፡ ተሰጠበት። በኋላደግሞ ፡ አሊ ፡ በግዞት ፡ ባፄ ፡ ንዋየክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ ምሕረት ፡ አግኝቶ ፡ ሹመቱንአስመልሶ ፡ ወደ ፡ ይፋት ፡ ቢሄድ ፡ ከልጁ ፡ ጋር ፡ ሳይስማሙ ፡ ቀርተው ፡ ተዋጉና ፡ ልጁ ፡ አሕመድ ፡ ሐርብ ፡ አራድ ፡ ወደ ፡ አፄ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ መጣ። ንጉሡም ፡ የይፋቱን ፡ ግዛት ፡ ለአሊ ፡ ስለ ፡ ኣጸደቀለት ፡ ላኣሕመድ ፡ ሰገበርት ፡ አንድ ፡ ቲንሽ ፡ ግዛት ፡ ሰጥቶ ፡ አስቀመጠው። በዚህ ፡ መካከል ፡ አህመድ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ የይፋቱ ፡ ገዥ ፡ ዓሊ ፡ የአሕመድን ፡ ግዛት ፡ አቡበከርቤን ዓሊ ፡ ለሚባለው ፡ ሰጠበት። ነገር ፡ ግን ፡ የልጅ ፡ ልጁ (የአሕመድ ፡ ልጅ) ሓቅ ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ በዚሁ ፡ ተናዶ ፡ አጐቱን ፡ ኣቡበከርን ፡ አባረረው። ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ ይኸው ፡ ወጣቱ ፡ ሐቅ ፡ አድ—ዲን ፡ ማውላ ፡ ኣስፋሕ ፡ የሚባለውን ፡ ሌላውን ፡ አጐቱን ፡ ጦርነት ፡ ገጠመው። ማውላ ፡ ኣስፋሕ ፡ ሐቅአድዲንን ፡ መመለስ ፡ ስላቃተው ፡ ወደ ፡ አፄ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ እርዳታ ፡ እንዲላክለት ፡ መላከተኛ ፡ ሰደደ። ከንጉሡም ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ቢላክለት ፡ እነሱንም ፡ ድል ፡ ኣድርጎ ፡ አሸነፋቸው ፡ ቀጥሎም ፡ ቢላክ ፡ ሐቅ ኣድዲን ፡ እየተዋጋ ፡ መለሳቸው። ማውላ ፡ አስፋሕም ፡ በጦርነቱ ፡ ሞተ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐቅ ፡ አድ ፡ ዲን ፡ ወደ ፡ ይፋት ፡ ገሥግሥና ፡ ሥልጣኑን ፡ ያዘ። ሽማግሌውን ፡ አያቱን ፡ አሊን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አላጉላላውም።

የዚህ ፡ ሁሉ ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ ባለፈው ፡ እንደተመለከትነው ፡ እንደ ፡ አፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጦርነት ፡ በዝርዝር ፡ የሚናገር ፡ የግዕዝም ፡ የአማርኛም ፡ ታሪክ ፡ የለንም ፡ ይኸም ፡ የተገኘው ፡ ሙሴ ፡ ኮረኔ ፡ ባሴት ፡ በ፩፻፴፩ ፡ ገጽ ፡ በቍጥር ፡ ፹፱ ፡ ላይ ፡ አል ፡ ማቅሪዚ ፡ የሚባለው ፡ የዐረብ ፡ ጸሐፊ ፡ ከጻፈው ፡ ላይ ፡ አግኝተው ፡ የጻፉት ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፲፱።

## ባፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ፈቃድ ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ — ያፄ ፡ ንዋየ ፡ ማርያም ፡ ዘመን።

ዓፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ የግዛቱ ፡ ዘመን ፡ ፳፰ ፡ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ በየታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲገለጥ ፡ በዚህ ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በዘመኑ ፡ ወይም ፡ ዘመኑ ፡ ባለፈበት ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የተገኙ ፡ ሊቃውንት ፡ በጽሑፍ ፡ ስለአላስቀሩት ፡ ብዙ ፡ ታሪክ ፡ እንደተዘጋ ፡ ቀርቷል። ነገር ፡ ግን ፡ ፈረንጆች ፡ የራሳቸውን ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ መርምረው ፡ አበጥረው ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ ጽፈው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ኣዲስ ፡ ታሪክ ፡ ለማግኘት ፡ ብዙዎቹ ፡ ስለሚመኙ ፡ ታሪኩ ፡ እየባከነ ፡ የቀረውን ፡ የእስያንና ፡ የአፍሪካን ፡ መንግሥታት ፡ ታሪክ ፡ ወደመመርመር ፡ በአዘነበሉበት ፡ ጊዜ ፡ ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ ጊዜያቸውን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያጠፉ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው። ሉዶልፍ ፡ ዲልማን፣ ሊትማን ፤ ጕይዲ ፤ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ፣ ፡ ባሴት ፡ ረኔ፣ ዝል ፡ ፔሩሾ ፡ ...መሆናቸውን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኣስታውሰናል።

ከነዚህ ፡ ከተጠሩት ፡ ውስጥ ፡ ሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ (ኣባ ፡ መጣዕ) ገዳም ፡ በውሰት ፡ ከአገኘው ፡ ወንጌል ፡ ውስጥ ፡ ባፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድፈቃድ ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ አሳትሞት ፡ ይገኛል። ይኸም ፡ ሕግ ፡ በኣባ ፡ መጣዕ ፡ ገዳም ፡ ሴት ፡ እንዳትገባ ፡ የሚከለክል ፡ መንፈሳዊነት ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የፖለቲካና ፡ ያስተዳደር ፡ ሕግ ፡ ያለበት ፡ አይደለም። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በውስጡ ፡ አንዳንድ ፡ የዘመኑን ፡ ሹማምንት ፡ ስም ፡ ስለሚጠቅስ ፡ የታሪክ ፡ ጽሑፍ ፡ ውድ ፡ ለሆነበት ፡ ለዚህ ፡ ዘመን ፡ ያገለግላል ፡ በማለት ፡ እነሆ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ገልብጬዋለሁ።

“አውሎግሶን ፡ ጽደቍ ፡ ዘኣዘዙ ፡ ንጉሥነ ፡ ርቱዐ ፡ ሃይማኖት ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ወስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ወጳጳስነ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ መጋቤ ፡ ሃይማኖት ፡ ወመላኬ ፡ ባሕር ፡ ብሌን ፡ ሰገድ ፡ መፍቀሬ ፡ ጽድቅ ፡ ትሑት ፡ ሥርዑነ ፡ ለኵሎሙ ፡ መነኮሳት ፡ እለ ፡ ብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከመ ፡ ንንበር ፡

በሥርዓት ፡ ዘእንበለ ፡ ተሐውዕ ፡ ምስለ ፡ መበለታት ፤ ወመበለታትሂ ፡ ከመ ፡ ኢይትዓወሳ ፡ ምስለ ፡ መነኮሳት ፡ ዘንተ ፡ ሠርዐ ፡ ጳጳስሂ ፡ ወንጉሥኒ ፡ ኀቢሮሙ ፡ በርትዕት ፡ ሃይማኖት ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ዐበይት ፡ ኖሎት ፡ ወዐቃብያነ ፡ መርዔት ፡ እስመ ፡ ጽሕቀ ፡ ለአድኅኖ ፡ ኵሉ ፡ ነፍሳት ፡ " ፡ ወይእዜኒ ፡ ስምዑ ፡ ኣንትሙ ፡ አኃው ፡ እላ ፡ መካነ ፡ መጣዕ ፡ ቅድስት ፡ ከመዘሠራዕናክሙ ፡ ተጋቢኦሙ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወመላኬ ፡ ባሕርሂ ፡ ነቢሮ ፡ ማዕከለ ፡ እንዘ ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ይትሐረም ፡ መካነ ፡ መጣዕ ፡ ከመ ፡ ኢይባኣ ፡ አንከት ፡ ወኢይግስሳ ፡ ጥቀ ፡ በእደዊሆን ፡ ዘእንበለቀዲሆሙ ፡ በከራ ፡ ወእመሂ ፡ በማኀየብ ፡ ወእመሂ ፡ በጐይብ ፡ " ፡ እስመ ፡ ዘንተሂ ፡ ዘሠራዕናከሙ ፡ ከመ ፡ ትድኑ ፡ እምኃጢኣት ፡ ወትንጽሑ ፡ እምርስሐት ፡ ወከመ ፡ ትኵኑ ፡ ምስምዐ ፡ ጸሎት ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ይነግር ፡ እስመ ፡ ለፈራኄ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ይሰምዖ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ወለኃጥእሰ ፡ ኢይሰምዖ ፡ **እግዚአብሔር**። ወይእዜኒ ፡ እመቦ ፡ ዘአብኣ ፡ ኣንስተ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መካነ ፡ መጣዕ ፡ እመሂ ፡ መነኰስ ፡ ወእመሂ ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ፡ እመሂ ፡ ሥዩም ፡ አው ፡ ሕዝባዊ ፡ እመሂ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ወቀሲስ ፡ ገበዝ ፡ እመቦ ፡ ዘአብኣ ፡ አንስተ ፡ እምበዓልቲት ፡ እስከ ፡ አመት ፡ አው ፡ ወለቶ ፡ ኣው ፡ እኅቶ ፡ አው ፡ እሞ ፡ ኣው ፡ አእርክቶ ፡ ኣው ፡ ብእሲቶ። እመጊ ፡ ዘአበኣ ፡ እመድረከ ፡ ኖኅት ፡ ወእም ፡ አንፈ ፡ ቀያፍ ፡ ለፌ ፡ ወእምነ ፡ ጻዕሮ ፡ ላዕሉ ፡ እመቦ ፡ እምዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘተኣደወ ፡ እመሂ ፡ ነጺሮ ፡ ወእመሂ ፡ ሰሚዖ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፡ በኣፈ ፡ ወ፪ ፡ አርድእት፣ ፡ በአፈ ፡ ፫፻፲ወ፰ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ በኣፈ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ውጉዘ ፡ ለይኹን ፡ እምዝንቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘተዐደወ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን። ወ**እግዚአብሔር** ፡ ይዕቀብ ፡ መንግሥቶ ፡ ለንጉሥነ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ለዘጸውዓነ ፡ እምኃጢኣት ፡ ከመ ፡ ንትገሐሥ። »

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ የምንመለከተው ፡ ፩ኛ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ የሚባለውን ፡ ስም ፡ ነው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ሁሉ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ሲል ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድን ፡ መጠሪያ ፡ ስም ፡ አድርጎ ፡ ስመ ፡ መንግሥቱን ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ሲል ፡ ይገኛል። ምናልባት ፡ በነገሠበት ፡ ቀን ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ወገኖች ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ይባል ፡ ሲሉ ፡ የቀሩትና ፡ የነዚህ ፡ የአባ ፡ መጣዕ ፡ ገዳም ፡ ወገኖች ፡

ቆስጠንጢኖስ ፡ ይባል ፡ ብለው ፡ በዚሁ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ጸንተውበት ፡ ይሆናል።

**፪ኛ** ፡ ይኸን ፡ ሕግ ፡ በኅብረት ፡ ተባብረው ፡ ኣወጡት ፡ ከሚለው ፡ ከንጉሡና ፡ ከጳጳሱ ፡ ጋር ፡ ፫ኛ ፡ መላኬ ፡ ባሕር ፡ ብሌን ፡ ሰገድ ፡ የሚባለውን ፡ ይጠቅሳል ፡ ንጉሡን ፡ ርቱዐ ፡ ሃይማኖት ፡ ጳጳሱን ፡ መጋቤ ፡ ሃይማኖት ፡ ሲል ፡ እርሱን ፡ መፍቀሬ ፡ ጽድቅ ፡ ትሑት ፡ ይለዋል። ይህ ፡ መላኬ ፡ ባሕር ፡ የተባለው ፡ ለብሌን ፡ ሰገድ ፡ የተሰጠው ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ እየተባሉ ፡ የኤርትራን ፡ የምጥዋን ፡ የደሆኖን ፡ ወደብ ፡ ከንጉሡ ፡ እየተሾሙ ፡ የሚያስተዳድሩትን ፡ መሆኑ ፡ ነው።

**፫ኛ** ፡ ከንጉሡ ፡ ከሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ጋር ፡ ስማቸው ፡ የተጠቀሰውን ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ የሚባሉትን ፡ ጳጳስ ፡ ሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ኣባ ፡ ሰላማ ፡ ከሞቱ ፡ ፶ ፡ ዓመት ፡ አልፏል ፡ ስለዚህ ፡ ጳጳሱ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ የሚለው ፡ የአክሱሙን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ለዚሁ ፡ እንደምስክር ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ስለአባ ፡ ገሪማ ፡ የጻፉትን ፡ ገድል ፡ ጠቅሷል። ነገር ፡ ግን ፡ በብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ዋዜማ ፡ መጽሐፍ ፡ የጳጳሳት ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ ባፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ፊቅጦር ፡ የሚባሉ ፡ መኖራቸውን ፡ እንጂ ፡ ሰላማ ፡ የሚሉ ፡ ጳጳስ ፡ መኖሩ ፡ አልተጻፈም። እርሱን ፡ ትተን ፡ ሙሴ ፡ ውሊያምራይት ፡ የሎንዶን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መሪ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መጻሕፍት ፡ ባዘጋጁበት ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ፫፻፳ ፡ ገጽ ፡ የጳጳሳት ፡ ዝርዝር ፡ ሲዘረዝር ፡ ኣባ ፡ ፊቅጦር ፡ ፴ወ፭ (፴፭ኛ፡) ዘውእቱ ፡ ሣልሳይ ፡ ሰላማ ፡ ስለሚል። ከዚህም ፡ ጋር ፡ ግዕዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ሕጉን ፡ ባወጣበት ፡ ውስጥ ፡ ወጳጳስነ ፡ ሰላማ ፡ ሲል ፡ በእርግጥ ፡ በዓፄ ፡ ሰይፈ ፡ ኣርዕድ ፡ ጊዜ ፡ የነበሩትን ፡ ጳጳሱን ፡ እንጂ ፡ የአኵስሙን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ሊሆን ፡ አይችልምና ፡ የሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒን ፡ አሳብ ፡ መሠረት ፡ ማድረግ ፡ አይቻልም። አሁን ፡ ወደታሪኩ ፡ እንመለስ።

አፄ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ግማሾቹ ፡ ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ እንደ ፡ ቀሩት ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ፳፰ ፡ ዓመት ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ ንዋየ ፡ ማርያም ፡ ነገሠ። የርሱም ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ ውድም ፡ ኣስፈሪ ፡ ይባላል። አንዳንዱ ፡ ጽሑፍ ፡ ደግሞ ፡ ግርማ ፡ ኣስፈሬ ፡ ይለዋል። ስለርሱ ፡

ግዕዙ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥታችን (ንዋየ ፡ ማርያም ፡ ዘውእቱ ፡ ውድምአስፈሬ ፡ ወልዱ ፡ ለሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ነግሠ ፡ ፲ተ ፡ ዓመተ ፡ ጠፍ ፡ ውእቱ፡) ብሎ ፡ ዓሥር ፡ ዓመት ፡ መግዛቱንና ፡ የርሱ ፡ ዘመን ፡ ጠፍ (ታሪክ ፡ የሌለበት) ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የተጻፈለት ፡ ነገር ፡ የለም። ይኸም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንዳልነው ፡ የጸሐፊ ፡ እጦት ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ባሥር ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ንጉሥ ፡ ባስተዳደርም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ግንኙነትም ፡ ዐረብ ፡ ግብፅ (እስክንድርያ) (ኑብያ) ወይም ፡ ከአዳሎች ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ ጦርነት ፡ እንደማይጠፋ ፡ አይጠረጠርም። ዝል ፡ ፔሩሾረኒ ፡ ባሴት ፡ ማቅሪዝ ፡ የሚባለው ፡ ጸሐፊ ፡ በስሕተት ፡ ባዔ ፡ ዳዊት ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጋ ፡ ሞተ ፡ ያለውን ፡ ሐቀ ፡ ዲንን ፡ ባዔ ፡ ንዋየ ፡ ማርያም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት (ከሺየ፳፫ሺ፫የሮ፰ ፡ ዓ.ም) በትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ሲዋጋ ፡ መሞቱን ፡ ገልጸዋል ፤ የሞተበትም ፡ ጊዜ ፡ በእስላሞቹ ፡ ቍጥር ፡ ፺የሮ፺ ፡ የሂጂራ ፡ ዓመት ፡ በኢትዮጵያ ፡ አቆጣጠር ፡ ሺ፫የ፳ጌ-፳ጊ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ ይሆናል ፡ የባሴት ፡ ረኔ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ምርመራ ፡ የሚባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ፻ ፡ ፲፫ ፡ ቍጥር ፡ ፺ ፡ ተመልከት።

# ያፄ ፡ ዳዊት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ ፳።

## ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከግብፅ ፡ ሱልጣን ፡ ጋር ፡ የተደ ፡ ረገው ፡ ስምምነትና ፡ የግማደ ፡ መስቀል ፡ መምጣት።

ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ ከወንድሙ ፡ ከዓፄ ፡ ንዋየ ፡ ማርያም (ውድም ፡ አስፈሬ ፡ ቀጥሎ ፡ በሺ፫፻፸፫ ፡ ዓ.ም ፡ ነገሠ ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ አለው ፡ የሚል ፡ እንድም ፡ የውጭ ፡ አገርም ፡ ያገራችንም ፡ ጽሑፍ ፡ አላየሁም። ምናልባት ፡ ስሜም ፡ ስመ ፡ መንግሥቴም ፡ በዚሁ ፡ በዳዊት ፡ ይርጋ ፡ ብሎ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ እስኪነግሥ ፡ ድረስ ፡ በሌላ ፡ ሳይጻፍ ፡ በቀረ ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፡ ኖሮ ፡ ሲነግሥ ፡ ዳዊት ፡ ተብሎ ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ስለ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ የሚናገረው ፡ ያገራችን ፡ ታሪክ ፡ አሁንም ፡ አጭር ፡ ነው። እርሱም ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ፡ ዳዊት ፡ ካልእ ፡ ወል ፡ ለሰይፈ ፡ ኣርዕድ ፡ ነግሠ ፡ ፳ወ፬ተ ፡ ዓመተ። ወበመዋዕሊሁ ፡ መጽአ ፡ ዕፀ ፡ መስቀሉ ፡ ለክርስቶስ ፡ `ወገብረ ፡ ፍሥሐ ፡ ወአሠርገዎሙ ፡ ለካህናት ፡ ካፓ ፡ በአጽገዩ። ወለውእቱ ፡ ዳዊት ፡ ንጉሥ ፡ ይቤሉ ፡ ቀተለቶ ፡ ባዝራ ፡ ረጊፃ ፡ ወሀሉ ፡ ትእምርተ ፡ ስብረት ፡ ውስተ ፡ ግምባሩ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ በደሌተ ፡ ዳጋ። ዕረፍቱኒ ፡ ኮነ ፡ አመ ፡ ፱ ፡ ለጥቅምት። ይህ ፡ የሚያስረዳን ፡ ዳዊት ፡ ያ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ ፳፱ ፡ ዓመት ፡ መንገሡን ፡ በዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ የጌታችን ፡ ዕፀ ፡ መስቀል (ግማደ ፡ መስቀል)ስለመጣላት ፡ ደስታ ፡ ሆኖ ፡ ካህናቱን ፡ ካባ ፡ እንደ ፡ ሸለመ ፡ ከዚያም ፡ ባዝራ (ፈረስ) ረግጣው ፡ እንደ ፡ ሞተና ፡ በግምባሩ ፡ ላይ ፡ የስብራቱ ፡ ምልክት (፩)እስከ ፡ ዚህ ፡ ጊዜ?ድረስ ፡ በዳጋ ፡ ደሴት ፡ መኖሩን ፡ ነው ፡ በተረፈ ፡ በነማክሪዝ ፡ መጽሐፍ ፡ በነረኔ ፡ ባሴት ፡ በነኰልቦ ፡ ትርጒም ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘው ፡ ግብፁ ፡ ማመሉክ ፡ መላላኩ ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ መዋጋቱ ፡ በግዕዙ ፡ አልተጻፈም። ዕፀ ፡ መስቀሉም ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ የመጣበትንም ፡ ምክንያት ፡ በመጠኑ ፡ ኣይዘረዝርም።

ምናልባት ፡ እኔ ፡ ያላገኘሁት ፡ የታሪክ ፡ የገድል ፡ የድርሳን ፡ ጽሑፍ ፡ እንዳለው ፡ አላረጋግጥም።

ስለዚህ ፡ ማክሪዚ ፡ የሚባለው ፡ ግብፃዊ ፡ ጸሐፊ (ሃይማኖቱ ፡ ክርስቲያን?) Historia Rerum Isl amiticarumin Abissinia-በአበሻ ፡ የእስላም ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ከጻፈው ፡ ውስጥ ፡ እያገኙ ፡ ብዙ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እነባሴት ፡ ረኔ ፡ እነ ፡ ኲልቢ. የጻፉትን ፡ እንመልከት።

## ከግብፅ ፡ ሱልጣን ፡ ጋር ፡ የተደረገው ፡ ስምምነት።

ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ የግብፆቹ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ በግብርና ፡ በቀረጥ ፡ በሌላውምእያመካኙ ፡ ባጕላሉዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ዓፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድም ፡ ይኸንኑ ፡ ለመቀበል ፡ እስከ ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅ ፡ ወሰን ፡ ድረስ ፡ መዝለቊን ፡ ተመልክተናል ፡

እርሱም ፡ ሄዶ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ የሚሄዱትን ፡ ነጋዴዎች ፡ አቊሞ ፡ ግብፆቹን ፡ እመቸገር ፡ ላይ ፡ አድርሷቸው ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያሉትን ፡ እስላሞች ፡ ክርስቲያን ፡ ካልሆናችሁ ፡ ብሎ ፡ አጕላልቷቸው ፡ ኖሯል። ስለዚህ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ መካከል ፡ የሚቸገሩት ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱና ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ስለሆኑ ፡ ተስማምተው ፡ ወደዓፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ መላክተኛ ፡ ላኩ። በዚህም ፡ አሳብ ፡ ውስጥ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚገኙት ፡ ፓትረያርክ ፡ ዮሐንስም ፡ ስለገቡበት ፡ እንዲያውም ፡ የመልክተኞቹ ፡ መሪ ፡ እንዲሆኑ ፡ ተወሰነ። ስለዚህ ፡ እንደ ፡ ስንክሳር ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡ እንደማቅሪዚ ፡ አባ ፡ ማቴዎስ ፡ የሚባሉት ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በነበሩበት ፡ ዘመን ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ፓትርያርክ ፡ መሪ ፡ ሆነው ፡ የእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡

---

(፩) ሙሴ፡ ባሴት፡ ረኔ፡ ወደ፡ ፈረንሳዊ፡ ሲተረጕሙ፡ <<በዳጋ፡ ደሴት፡ ግንባሩ፡ በሚባለው፡(ሥፍራ) ለስብራቱ፡ ምልክት፡ መታሰቢያ፡ እንዲሆን፡ የቆመለት፡ ሐውልት፡ እስከዛሬ፡ ይታያል>> ብለው፡ ግምባርን፡ የአገር፡ ወይም፡ የቦታ፡ ስም፡ አድርገውታል፡ ገጽ፡ ፶፫። ነገር፡ ግን፡ እስከ፡ ዛሬ፡ በግምባራቸው፡ ይታያል፡ ሲል፡ ለማንም፡ ያሳስታል።

ክርስቲያን ፡ ታላላቅ ፡ ሊቃውንት ፡ አባ ፡ ማዕምርና (ኢትዮጵያዊ ፡ ይሆኑን) አባ ፡ ቂርሎስ (የአሕናስ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ) ሆነው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጡ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ዓፄ ፡ ሰይፈአርዕድም ፡ ዓፄ ፡ ንዋየ ፡ ማርያምም ፡ ኣልፈው ፡ በዙፋን ፡ የነበረው ፡ ንጉሥ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ ስለነበረ ፡ እስከ ፡ ወሰን ፡ ድረስ ፡ ተቀባይ ፡ ልኮ ፡ በኋላም ፡ ራሱ ፡ እስከ ፡ ኣክሱም ፡ ድረስ ፡ ሄዶ (?)ተገናኛቸውና ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ የመጣበትን ፡ ጉዳይ ፡ ፈጽሞ ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ንግዱም ፡ እንዳይዘጋ ፡ እስላሞቹም ፡ እንዳይጉላሉ ፡ በበኩሉ ፡ የግብፁም ፡ ባለሥልጣን ፡ በእስክንድርያ ፡ ባሉት ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስና ፡ ክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ እንዳይፈጥር ፡ ተነጋግሮ ፡ በዚሁ ፡ ስምምነት ፡ ተለያዩ። ከዚያም ፡ ማክሪዚና ፡ አል ፡ ታሪግርቢርዲ ፡ የሚባሉት ፡ እንደጻፉት ፡ በ፲፻፸፯ ፡ ሄጂራእንደ ፡ ኤው ፡ ቍ ፡ ፩ሺ፫፻፹፲ላይ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ የራሱን ፡ መልክተኞች ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ ላከ። መልክተኞቹም ፡ ለሡልጣኑ ፡ የሚሰጥ ፡ በ፳ ፡ ግመል ፡ የተጫነ ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ ነበር ፡ ለገጸበረከት ፡ ከተያዘውም ፡ ውስጥ ፡ እንደሸምብራ ፡ ዓይነት ፡ የተሠሩ ፡ ወርቆች ፡ የተመሉባቸው ፡ በወርቅ ፡ የተሠሩ ፡ ማሰሮዎች ፡ ነበሩና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ መላከተኞች ፡ ወስደው ፡ ተገናኝተው ፡ አስረከቡ። በአፄ ፡ ዳዊትና ፡ በግብፁ ፡ ሱልጣን ፡ መካከል ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ ስምምነት ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ሱልጣኑም ፡ በዚሁ ፡ ተደስቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ግብፅም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ሲሄዱ ፡ በመንገድ ፡ ችግር ፡ እንዳያገኛቸው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚገኙት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መነኮሳትና ፡ ምዕመናንም ፡ ያለችግር ፡ እንዲኖሩ ፡ አዘዘ ፡ ይባላል።

ስለዚህ ፡ አፄ ፡ ዳዊት ፡ የሱልጣኑን ፡ ድጋፍ ፡ ካገኘ ፡ ወዲህ ፡ የኢየሩሳሌሙ ፡ ፓትሪያርክ ፡ መጥተው ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ የተሰቀለበትንና ፡ ዕሌኒ ፡ ንግሥት ፡ አገኘችው ፡ ከሚባለው ፡ ከእውነተኛው ፡ የመስቀል ፡ እንጨት ፡ ፩ ፡ ቍራጭ ፡ እንዲላክለት ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ብዙ ፡ የሚሰጥ ፡ ወርቅ ፡ ጨምሮ ፡ መላክተኛ ፡ ላከ። እነዚያም ፡ በደረሳቸው ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡን ፡ መላክተኞች ፡ በደስታ ፡ ተቀብለው ፡ ከዓፄ ፡ ዳዊት ፡ የተላከውን ፡ የወርቅ ፡ ስጦታ፡ግማሹን ፡ የጌታችን ፡ መቃብር ፡ በሚገኝበት ፡ በጐልጎታ ፡ አስቀምጠው ፤ በግማሹ ፡ ቅዱስ ፡ ሉቃስ ፡ ሳለው ፡ የሚባለውን ፡

የእመቤታችንንና ፡ የጌታችንን ፡ ስዕል ፡ ባንድነት ፡ ያለበትን ፡ ስዕል (ምስለ ፡ ፍቍር ፡ ወልዳ) ሌላ ፡ ደግሞ ፡ የጌታችን ፡ ስዕል ፡ አክሊለ ፡ ሦክ ፡ እንዳደረገ ፡ ያለበትን (ዘርዓተ ፡ ርእሱ ፡ የሚባለውን) ገዝተው ፡ ከግማደ ፡ መስቀሉ ፡ ጋር ፡ ጨምረው ፡ ሰጥተው ፡ አስደሰቷቸው። ያፄ ፡ ዳዊት ፡ መላክተኞችም ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ስዕልና ፡ ግማደ ፡ መስቀል ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ይዘው ፡

በስምምነቱ ፡ መሠረት ፡ እንደልባቸው ፡ እስላሞቹን ፡ ሳይፈሩ ፡ በስናር ፡ በኰላ ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ደረሱ ፤ ንጉሡ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊትም ፡ በፍጥነት ፡ ሩቅ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ተቀበላቸውና ፡ ሕዝቡም ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ በሆታና ፡ በእልልታ ፡ በዘፈን ፡ ካህናቱም ፡ በዜማ ፡ በማኅሌት ፡ በታላቅ ፡ ክብረ ፡ በዓል ፡ ተቀብለዋቸው ፡ በመስከረም ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ተጕለት ፡ ገቡና ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ኣጠገብ ፡ ንጉሡ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሳንፆ ፡ ግማደ ፡ መስቀሉን ፡ በክብር ፡ አስቀመጠው። በኋላ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ግሼን ፡ ተዛወረ ፡ ይባላል። ስለዚህ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ሊቃውንቱ ፡ እንደ ፡ ወሰኑት ፡ በመስከረም ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ በያመቱ ፡ የምናከብረው ፡ ያፄ ፡ መስቀል ፡ በዓል ፡ የዚሁ ፡ መታሰቢያ ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፳፩።

## የውስጥ ፡ ጦርነት።

ባፄ ፡ ዳዊት ፡ ዘመን ፡ በውስጥ ፡ አስተዳደርና ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የይፋቶችና ፡ የኣዳሎች ፡ ጦርነት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ነገሥታቱና ፡ የሚልኳት ፡ ጦር ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ አሸናፊነቱ ፡ ባይቀር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የእስላሞቹ ፡ መሪዎች ፡ ጊዜ ፡ ሲመች ፡ እየጠበቊ ፡ መሸፈታቸው ፡ እንደልማድ ፡ ሆኗል። ምንም ፡ እንኳንበስሜንና ፡ በወገራ ፡ ፈላሾችና ፡ የበላው ፡ ዘሮች ፡ ፩፩ ፡ ጊዜ ፡ መነሣታቸው ፡ ባይቀር ፡ ሌላው ፡ ኣውራጃ ፡ ባንድ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በንጕሥዋ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሲተዳደር ፡ እነርሱን ፡ ለዘለቄታ ፡ አስገብሮ ፡ ማሳመን ፡ የማይቻል ፡ ነገር ፡ ሆነ። ለዚህም ፡ ዋና ፡ እንቅፋት ፡ የሆ ፡ ው ፡ የእስላም ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በዠርባቸው ፡ ያለው ፡ የየመን ፡ መንግሥት

: ነው። ይልቍንም : በዚህ : ዘመን : የተነሣው : ኣደንን : ቀይ : ባሕርን : እየገዛ : ሥልጣኑን : እስከ : ዘይላ : ድረስ : የአሰፋው : የዘቢዱ : ሹም : ለነዚሁ : በኢትዮጵያ : ነገሥታት : ላይ : ለሚሸፍቱት : የሀድያና : የይፋት : የአዳል : ባላባቶች : ሲዋጉ : መሣሪያም : ወታደርም : ዕርዳታ : እየላከ : ሲሸነፉ : መሸሻና : መጠጊያ : ሥፍራ : እየሰጠ : ዋና : ደጋፊ : ስለሆናቸው : ከእርሱ : ዝርባ : ደግሞ : የአውሮፓን : ነገሥታት : ሁሉ : ያሸነፈው : የግብፁ : ማመሉክ : የቱርኩ : ሱልጣን : ስላሉ : የይፋትና : የአዳል : ሁኔታ : ከቀን : ፀደቀን : አሰጊ : ሆነ : የኢትዮጵያ : ነገሥታት : ለነዚህ : ለተገኙዎቹ : መሣሪያ : እየሰጠ : ድጋፍ : የሆነውን : የየመኑንና : የዘቢዱን : ገዥዎች : ለመምታት : የበቃ : አቅም : የባሕር : ላይ : ኃይል : ስለኣልነበረው : ዘመኑን : ሁሉ : እነዚህኑ : የሚሸፍቱበትን : ተገዥዎቹን : ብቻ : ሲዋጋ : ሲያሳምን : ሲሾም : ሲሽር : ሲያስር : ሲፈታ : ፩ : ፩ : ጊዜም : ወታደሮቹን : በነዚያ : ሲያስፈጅ : ኖረ።

በዚሁ : አያያዝ : ባፄ : ንዋየ : ማርያም (ውድም : አስፈሬ) ጊዜ : ሐቅ : ኣድ : ዲን : ሲዋጋ : ከሞተ : በኋላ : ባሁኑ : ባፄ : ዳዊት : ዘመነ : መንግሥት : ዘመን : በዘሩ : ሐረግ : ላይ : አንባቢ : ሊመለከተው : የሚችለው : መሐመድ : ኣቡል : ባራከት : ሳድአድ : ዲን : የሚባለው : በወንድሙ : እግር : ተተክቶ : እስላሞቹን : እየመራ : ባፄ : ዳዊት : ላይ : ሸፈተ። ሙሴ : ባሴት : ረኔ : ከማክሪዝ : መጽሐፍ : ከገጽ : ፳፩-፳፫ : አግኝተው : በ፩፱፵ዩ : ገጽ : መጽሐፋቸው : ቍጥር፵፫ : እንደዚህ : ሲሉ : ጽፈዋል። «ሳአድ : ኣድ : ዲን : አህባዛህ : እሚባል : አገር : ላይ : ሲዋጋ : የንጉሡ : ወታደሮች : ማርከውበት : ነበር : በኋላ : ግን : የራሱ : ወታደሮች : አስጥለውት : ከዚያ : ጦርነቱን : ቀጥሎ : የንጉሡን : ያፄ : ዳዊትን : ሹም : አማን : ሞርፋ : የሚባለውን : በጦርነት : ኣሸነፈና : የዘላንን : ኣገር : ወሰደ : ብዙም : ምርኮ : ኣገኘ። ነገር : ግን : በዚያው : ሰሞን : ሳሊም : ቤን : አያድ : የሚባለው : ኣማቹ : በኢትዮጵያውያን : እጅ : ተገድሎበታል።

ይሁን : እንጂ : የኢትዮጵያውያን : ጦር : ዛንሐቅ : በሚባል : እየተመራ : መጥቶ : ኣሳድ : የሚባለው : እስላም : ተዋግቶ : ከመለሳቸው : በኋላ : እንደዚሁም : ባንደኛው : ክፍል : ክርስቲያኖቹ : ኤሚር : መሐመድ :

የሚባለውን ፡ ፩ ፡ ፈረሰኛ (ለወሬ ፡ ነጋሪ?) ብቻ ፡ ሲያመልጥ ፡ አግኝተው ፡ ከነጦሩ ፡ ፈጁት። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባኑአ ፡ የሚባል ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ መቾ ፡ ከሳአድ ፡ ዲን ፡ ጋር ፡ ተጋጠመና ፡ አሸነፈው። ሳኣድ ፡ ዲንም ፡ ከጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ ሸሽቶ ፡ ዘይላ ፡ ከተማ ፡ ቢገባ ፡ በዚያም ፡ ተከታትሎ ፡ ሄዶ ፡ ከተማይቱን ፡ ከቦ ፡ እስላሞቹን ፡ በውሃ ፡ ጥምም ፡ በጦርነትም ፡ ፈጅቶ ፡ ተመለሰ። ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ሳኣድ ፡ ዲን ፡ ከሞተ ፡ ወዲህ ፡ የእስላሞቹ ፡ ኃይል ፡ ተዋረደ ፡ በመስጊዶቹም ፡ ፈንታ ፡ በያለበት ፡ ኣብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተተከሉ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዓፄ ፡ ሰይፈ ፡ ኣርዕድ ፡ የተላኩት ፡ የግብፅ ፡ መልክተኞች ፡ ወደ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ መጥተው ፡ ተገናኙ ፡ ብሎ ፡ » ፡ ይጨርሳል።

ስለዚህ ፡ በነ ፡ አምደ ፡ ጽዮን ፡ በነ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘመን ፡ የነበረው ፡ የእስላሞቹ ፡ ሽፍትነት ፡ በዓፄ ፡ ዳዊት ፡ ጊዜም ፡ አላቋረጠም ፡ ማለት ፡ ነው። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ ዝንባሌው ፡ ከጦርነት ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ መንፈሳዊ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ መጽሐፍ ፡ ምርመራ ፡ ያቀና ፡ ይመስላል። በጽሑፉም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ጦርነቱን ፡ ያደረጉት ፡ ከርሱ ፡ የተላኩ ፡ የጦር ፡ ኣላቆቹ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ራሱ ፡ ጦሩን ፡ እየመራ ፡ ሄዶ ፡ የተዋጋ ፡ አይመስልም። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የእስላሞቹም ፡ ባላባቶች ፡ ባምደ ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ እንዳደረጉት ፡ ያለ ፡ ሕብረትና ፡ ድርጅት ፡ በርሱ ፡ ጊዜ ፡ ስላላደረጉ ፡ የሳአድ ፡ ዲን ፡ ኃይል ፡ በተላከ ፡ ጦር ፡ ብቻ ፡ ሊሸነፍ ፡ እንደ ፡ ቻለ ፡ ይታያል።

ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ ፳፱ ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከገዛ ፡ በኋላ ፡ በሺ፬፻፱ ፡ ዓ.ምሕረት ፡ ጥቅምት ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ሞቶ ፡ በደሴተ ፡ ዳጋ (ደቀ ፡ እስጢፋኖስ) ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጣና ፡ ተቀበረ። በዘመኑ ፡ የአረመኔ ፡ ስፌድ ፡ የኣልማዝ ፡ ግድግዳ ፡ የሚባል ፡ ሥያሜ ፡ ሰጥተውታል ፡ ይባላል። ስለ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ በስንክሳር ፡ በያመቱ ፡ በሞተበት ፡ በጥቅምት ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ የሚነበብ ፡ ስንክሣር ፡ አለው።

ስለ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ በዘመኑ ፡ የተገጠመ ፡ የሚመስለውን ፡ ግጥም ፡ ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ እሸቴ ፡ አዘጋጁት ፡ ከሚባለው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥ ፡ ያገኘነውን ፡ ላፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንዳደረግነው ፡ ያፄ ፡ ዳዊትንም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ጽፈነዋል።

## ላፄ ፡ ዳዊት

አንት ፡ ልጅ ፡ የብስማር ፡
ለምን ፡ ጸላህ ፡ የኛን ፡ ፍቅር ፡
ምሽት ፡ ሰጥተነህ ፡ ወይዘር ፡
አከል ፡ ሰጥተነህ ፡ ሐመር ፡
ሰፊ ፡ ሰጥተነህ ፡ ሀገር ፡
ለምን ፡ ጸላኸው ፡ የኛን ፡ ፍቅር ፡
ጽላ ፡ ተመተር ፡
ሐአባትህ ፡ አገር ፡
ቢጸባ ፡ መስቀል ፡
ይስሐቅ ፡ ድረስ ፡ ስትል (ይህ ፡ በተለይ ፡ ያፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ይመስላል)
እንደ ፡ ኣግአዘን ፡ ደምበር ፡
እንደ ፡ ብር ፡ ቀርር ፡
ኅልቆኸንቀጸር ፡
ልጅ ፡ ምሽትህን ፡ ዘርዝር
ጽላ ፡ ተመተር ፡
ሐአባትህ ፡ አገር ፡
ዣን ፡ እንግዴ ፡ የሰማ ፡ ነበር ፡
ኣንበሳ ፡ ዳዊት ፡ ተኳር
ይበላ ፡ አልጻፈጠው ፡ እህል ፡
ይጻጻ ፡ አልጻፈጠው ፡ ቅምብር ፡
ገነነ ፡ ቢሉ ፡ ገባር ፡
በሽ ፡ ንቿ ፡ አሉ ፡ ሰፈር ፡
ስንቱን ፡ እቈጽር ፡
የዴላ ፡ ገባር ፡
ሲፈክር ፡ ነበር ፡
ስንኳ ፡ ለአምሐራ ፡ ጅር ፡
ሰማይ ፡ ቢከነበል ፡
እናቆም ፡ ሲሉ ፡ ነበር ፡ በጾር ፡

ሲፈክሩ ፡ ነበር ፡
ኣጠፉዋቾ ፡ ለዝክር ፡
ደርሶ ፡ በሳንፎ ፡ ሠፈር ፡
ኣጠፉዋቾ ፡ ለዝክር ፡
እራሳቸው ፡ በእሳት ፡ ኣረር ፡
አንበሳ ፡ ትኵር ፡
ኣሉህ ፡ እንገብር ፡ በአባትህ ፡ ነበር ፡
ፈረስህን ፡ ናቀብል ፡
በቅሎህን ፡ ናቀብል ፡
አንጥፉ ፡ ለዘር ፡ ኣንበሳ ፡ ዳዊት ፡ ተኳር ፡
በዳበናኾ ፡ መገን ፡ በፈረስህ ፡ መገን ፡
በሪምሕ ፡ መገን ፡ በሕፃናትህ ፡ መገን
አማስለህ ፡ አትፍጀን ፡
እኛስ ፡ ፈቃደኛህ ፡ ነን ፡
እንስጥ ፡ መንግሥትህን ፡
ፈረስኽ ፡ የተፈተን ፡ ወርቅ ፡ የተመዘን ፡
ሐበጥ ፡ ቂራጥ ፡ ብለን ፡
ናድርስ ፡ መንግሥትህን ፡
አማስለህ ፡ አትፍጀን ፡
ዣን ፡ በደል ፡ እሳት ፡
ጽርሐ ፡ ንግሥት ፡ ታቦት ፡
እንደተከስዋት ፡ በእሳት ፡
ኣስሐረርዋቾእርሱም ፡ በእሳት ፡
አንበሳ ፡ ዳዊት ፡ ሐስ ፡ ተሸንጕርት ፡
መለኵሴ ፡ እንዳያንስ ፡ በሰዓት ፡
ደርሶ ፡ ወረደባቸው ፡ ዮሴፍ ፡ መዓት
ተጋየሱ ፡ የጊስት ፡ ተከለለት ፡ አበቤት ፡
ሐመል ፡ ወፍራ ፡ የዳዊት ፡
የግራ ፡ የቀኝ ፡ ባልታት ፡

በደብር ፡ ያላችሁ ፡ መላኮሳት ፡
በከተማ ፡ ያላችሁ ፡ ሕፃናት ፡
ማን ፡ ተዋጋችሁ ፡ አቂት ፡
ንጉሥ ፡ በክረምት ፡ ሲዘምት ፡
ወርኀ ፡ የሌለ ፡ ሲሉአለሁለት
አላሰኄና ፡ ግንቦት ፡
አንቲ ፡ ገቡ ፡ የወጁበት ፡
አንበሳ ፡ በደል ፡ እሳት ፡
አለ ፡ መለስ ፡ አለዋት ፡ ድላ ፡ ዝመት ፡
ትሁን ፡ እናት ፡
ሚካኤል ፡ ይሁንህ ፡ ኣባት ፡
ይከተሉህ ፡ ሠራዊተ ፡ መላእከት ፡
ተነሣ ፡ በሰዓት ፡ ሰዓት ፡
ጫማ ፡ ሳይል ፡ በቍልቍለት ፡
ሐርቡን ፡ ሳይል ፡ ከተት ፡
በቅሎሳይል ፡ ላቀበት ፡
ፃርማን ፡ ሲወርዱ ፡ ቍልቍለት
የጎሽ ፡ ተገኝ ፡ በረት ፡ "
ናኛቸው ፡ ላኣቂት ፡
ላም ፡ ኣስመስሎ ፡ የተጉበት ፡
የገድ ፡ መዠመሪያችነት ፡
ጻርማን ፡ በተሳት ፡
ሐዋሽ ፡ መርማን ፡ በጸዋት ፡
ለዚያች ፡ ላውብራ ፡ አገዊት ፡
ስታዝን ፡ የተውናት ፡
ድላ ፡ መለስ ፡ ብስራት ፡
ስታዝን ፡ የተውናት ፡
የሐዋሽነት ፡ ምልኣት (ምላት)
አላስረገፈንም ፡ አባቍልት

ኣላስፈታንም (ወገረት ፡
ጽላ ፡ ጊታንገር ፡ መኾት ፡
ምንም ፡ ኣልኾንም ፡ በልዋት
አንበሳ ፡ ዳዊት ፡ ጽርሐ ፡ ንግሥትነ ፡ ታቦት ፡
እንደተኰስዋት ፡ በእሳት ፡
አሳረርዋቸው ፡ በእሳት ፡
እርሱም ፡ ደርሶአወረደባቸው ፡ ዮሴፍ ፡ መዓት
ሓስ ፡ ተስንኍርት ፡
መለኵሴ ፡ እንድያንስ ፡ በሰዓት
አወረደባቸው ፡ ዮሴፍመዓት
ኣንበሳ ፡ ዳዊት ፡

## ላዔ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡

ዠን ፡ በድል ፡ እማም ፡
ኣባት ፡ የበእደ ፡ ማርያም ፡
አባት ፡ የፀበለ ፡ ማርያም ፡
ዓመፁ ፡ እለያ ፡ ፀረ ፡ ማርያም (ስለደቀ ፡ እስጢፋዎች?)
ጸበባቸው ፡ ዓለም ፡ ሲፈቀዋቸው ፡ ኣጋም ፡
ሲሉ ፡ በእንተ ፡ ማርያም ፡
ሐረድዋቸው ፡ እንደስላም ፡
ዦን ፡ በድል ፡ ዘለቅ ፡
አቤታቾየአዳል ፡ መብረቅ ፡
ጓዥብ ፡ እንደ ፡ በላ ፡ ጭምቅቅ ፡
ባዶል ፡ ቢልባቸው ፡ ብቅ ፡ -
አማፀውቶች ፡ ዝቅ ፡
አሞራ ፡ የጻዊት ፡ አሞራ ፡
ተኸተለኝ ፡ በኋላ ፡ ሥጋ ፡ ኣበሳህ ፡ ኣበላ ፡
የደም ፡ ኣጠጣህ ፡ ነተራ ፡ ፤

ተኸተለኝ ፡ በኋላ ፡ ወግዕቼ ፡ በቃራ
ሰከቼ ፡ በደምራ ፡ እኛስ ፡ ባንበዓኸ ፡ መሀላ ፡
ለጾር ፡ ይስጠን ፡ ለወርወር ፡
የክንፍ ፡ ብናደርግ ፡ ጽላ ፡
ለቀስት ፡ ይስጠን ፡ ለቀፈራ ፡
ምንከባሰኸ ፡ ንብላኸ ፡ መሐላ ፡
ገላቹን ፡ ከመሰል ፡ የፈጠጋር ፡ እምብላ ፡
አፈቹን ፡ ከመሰል ፡ ባልቴት ፡ የገባችእንሶስላ
ፀአታችን ፡ ይመስል ፡ በደም ፡ የዘራ ፡ ጭራ ፡
ስማችን ፡ ዣን ፡ ተኸላ ፡
አንበልዓም ፡ መሐላ።

ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ እሸቴ ፡ ሰበሰቡት ፡ በሚባለው ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ግጥሙ ፡ ለማን ፡ መሆኑ ፡ ሳይለይ ፡ በየዘመኑም ፡ ሳይከፈል ፡ መደዳውን ፡ የተጻፈውን ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ መሰለኝ ፡ እንደ ፡ ታሪኩ ፡ አቀራረብ ፡ እየተመለከትሁ ፡ ይልቍንም ፡ ስማቸውን ፡ በሚጠቅሰው ፡ እየተመራሁ ፡ ለዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፤ ላፄ ፡ ዳዊት ፤ ላፄ ፡ ይስሐቅ ፤ ላፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፤ ላፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ከፋፍዬዋለሁ። ምናልባት ፡ በአከፋፈሉ ፡ ውስጥ ፡ ላንዶኛው ፡ የተገጠመው ፡ ወደሌላው ፡ ቢሄድም ፡ ወደፊት ፡ በምርምር ፡ ሳይተካከል ፡ ኣይቀርም። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ይህ ፡ ግጥም ፡ የዘመኑን ፡ ግጥም ፡ በሚያሳይበት ፡ ጐን ፡ የዘመኑን ፡ ግዕዝኛ ፡ የተደባለቀበትን ፡ የዘመኑን ፡ አማርኛ ፡ አነጋገርና ፡ ጽሑፍ ፡ ያሳየናል።

# ምዕራፍ ፡ ፳፪።

# የኣፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፩ኛ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።

ከኣፄ ፡ ዳዊት ፡ ቀጥሎ ፡ የነገሠ ፡ ልጁ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ነው። ስለ ፡ እርሱም ፡ በታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ በግዕዝ ፡ የተጻፈ ፡ የለም። ስለርሱ ፡ በብሩስ ፡ መጽሐፍና ፡ በስንክሳር ፡ እንደሚገኘው ፡ ዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፡ ባፄ ፡ ይኵኖ ፡

አምላክና ፡ በኣቡነ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ መካከል ፡ የተደረገውን ፡ የሲሶ ፡ መንግሥት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፍርሶ ፡ በዚህ ፡ በትልቅ ፡ ሀብት ፡ ሕዝብ ፡ ይጠቀምበት ፡ ብሎ ፡ የቤተክህነቱን ፡ ርስትና ፡ ጉልት ፡ ለሕዝብ ፡ ማካፈል ፡ ዝምሮ ፡ ነበር ፡ ይባላል። ከአባቶቹም ፡ ከተከታዮቹም ፡ የተለየ ፡ አሳብ ፡ አምጥቶ ፡ የሲሶውን ፡ መንግሥት ፡ በዘመኑ ፡ ለማፍረስ ፡ መሞከር ፡ ለሥልጣንና ፡ ለምስጋና ፡ የማይጓጓ ፡ የቤተ ፡ ክህነትንም ፡ ሐታና ፡ ወቀሣ-የማይፈራ ፡ ደፋር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መሆኑን ፡ ያስረዳል። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ይኸንንም ፡ ሠርቶ ፡ ሳለ ፡ ዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ ንጉሥ ፡ አልነበረም ፡ ለዚሁም ፡ ምስክሩ ፡ ከልጅነቱ ፡ ዝምሮ ፡ **እግዚአብሔርን** ፡ የሚፈራ ፡ ባንዲት ፡ ሚስት ፡ የተወሰነ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ እያለ ፡ ስንክሣሩ ፡ ማመስገኑ ፡ ነው። በዚህም ፡ ላይ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ተክሏል። ከገዛ ፡ ሀብቱም ፡ እያወጣ ፡ ለድሆች ፡ ያድል ፡ ነበር ፡ ፤ ፍካሬ ፡ **ኢየሱስም** ፡ በርሱ ፡ ጊዜ ፡ ተጻፈ ፡ ይባላል። ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ሔዶ ፡ የጌታችንን ፡ መቃብር ፡ ለመሳላም ፡ ምኞት ፡ ነበረው ፡ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በጳጳሱ ፡ በኣቡነ ፡ ማርቆስ ፡ ምክር ፡ ሳይሔድ ፡ ቀረ ፡ ይባላል። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ በግዛት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሳይቆይ ፡ ፫ዓመት ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ገዛ ፡ ሞተና ፡ በተድባበ ፡ ማርያም (አማራ ፡ ሳይንት) ተቀበረ። ወንድሙ ፡ ዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ በመንግሥቱ ፡ ተተካ። በስንክሣር ፡ በሞተበት ፡ በሰኔ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የሚነበበውን ፡ ተመልከት።

የዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ግዛቱ ፡ ከሺ፬፻፬ ፡ እከ ፡ ሺ፬፻፯ ፡ ዓ. ምሕረት ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፳፫።

# የዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።

ዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ያፄ ፡ ዳዊት ፡ ልጅ ፡ ያፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ወንድም ፡ ነው ፡ ያገራችን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ኣንዳንዶቹ ፡ አጫጭር ፡ ታሪክ ፡ እየጨመረ ፡ ለቀሩት ፡ ስማቸውንና ፡ የነገሡበትን ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እየጠቀሰ ፡ መጥቶ ፡ ዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል። “ይስሐቅ ፡ ካልዕ ፡ ወልዱ ፡ ለዳዊት

፡ ነግሠ ፡ ፲ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ ወውእቱ ፡ ዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ዘመጽአ ፡ እስከ ፡ ወገራ ፡ ወፀብዖ ፡ ለቤተ ፡ ኣሹር (አጅር) ፈላሻ ፡ ዘመረባ ፡ ወሠርዖ (ወሠዖሮሙ) ለ፳ወ፬ ፡ በላዋምባ (በለው ፡ ኣምባ) እስመ ፡ ቆሙ ፡ ሎቱ (ቦቱ?) በዕለተ ፡ ፀብኡ። ወበመዋዕሊሁ ፡ ተሐንፃ ፡ ብዙኃት ፡ ኣብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በምድረ ፡ ደምቢያ ፡ ወወገራ ፡ በኮሶጌዚ ፡ ሀሎ ፡ ዘይሰመይ ፡ ይስሐቅ ፡ ደብር ፡ ወበ፪ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ተፈጸመ ፡ ፲ወ፫ ፡ ቀመር ፡ ዘ» በዚህ ፡ ላይ ፡ የምንረዳው ፡ ዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ መንገሡን ፡ እስከ ፡ ወገራ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ቤተ ፡ አሹር ፡ ፈላሻ ፡ ዘመረባ ፡ ከሚለው (ከፈላሾች) ጋር ፡ መዋጋቱን ፡ ፳፬ ፡ በለዋምባ (ወንበሮችን ፡ ዳኞችን?)በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ስለኣልረዱት (ወይም ፡ ከጠላቶቹ ፡ ወገን ፡ ስለሆኑ) እንደሻራቸው ፡ በርሱ ፡ ዘመን ፡ በደምቢያ ፡ በወገራ ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መሠራታቸውንና ፡ በከሶጌ? በስሙ ፡ የተሠየመ ፡ ደብረ ፡ ይስሐቅ ፡ የሚባል ፡ መኖሩን ፡ እርሱም ፡ በነገሠ ፡ በ፪ኛው ፡ ዓመት ፡ ፲፫ ፡ የዘመን ፡ ቀመር (ሲክል) መፈጸሙን ፡ ብቻ ፡ ነው።

ለኢትዮጵያ ፡ ለክርስቲያኑ ፡ መንግሥት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እየሸፈቱ ፡ እንቅፋት ፡ የሚፈጥሩበት ፡ የይፋት ፡ የሐድያ ፡ የአዳል ፡ እስላሞች ፡ ብቻ ፡ አልነበሩም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ በስሜን ፡ በወገራ ፡ ያሉ ፡ ፈላሾች ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ዕብራዊ ፡ኦሪታዊ) ሆኖ ፡ እንደ ፡ እስላሞቹ ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ የተለየ ፡ ስለሆነ ፡ በክርስቲያኖቹና ፡ በነርሱ ፡ መካከል ፡ መናናቅ ፡ የሃይማኖት ፡ ማበላለጥና ፡ ጥላቻ ፡ ስለነበረ ፡ የእስላሞቹን ፡ ያህል ፡ እንኳን ፡ ባይበዛ ፡ አልፎአልፎ ፡ ጊዜ ፡ ሲመቻቸው ፡ ወይም ፡ ከመካከላቸው ፡ ትልቅ ፡ ሰው (ቀንደኛ ፡ ሲነሣ ፡ እየሸፈቱ ፡ ከመንግሥቱ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ይዋጉ ፡ ነበር። የድልነዓድንና ፡ የዮዲትን ፡ ጦርነት ፡ ባለፈው ፡ ያነበብነው ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ትዝ ፡ ይለናል። በቅርቡ ፡ ዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ተሰብስበው ፡ የመጡበትን ፡ የደዋሮ ፡ የይፋት ፡ የአዳል ፡ እስላሞች ፡ ሊዋጋ ፡ በሚዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ የወገራ ፡ የጸገዴ ፡ የስሜን ፡ ፈላሾች ፡ ሸፍተውበት ፡ ጸጋ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚባለው ፡ የጦር ፡ አለቃው ፡ ኣዝማችነት ፡ ጦሩን ፡ ከፍሎ ፡ የላከው ፡ የሸፈቱበትን ፡ እነዚህኑ ፡ ፈላሾች ፡ ለመውጋት ፡ ነው።

ስለዚህ ፡ እነዚሁ ፡ ፈላሾች ፡ አሁንም ፡ ባፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ጊዜ ፡ ስለሸፈቱ ፡ እስከ ፡ ወገራ ፡ ድረስ ፡ ራሱ ፡ ሄዶ ፡ ተዋግቷል ፡ ማለት ፡ ነው። ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ባጭሩ ፡ ይኸን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ወርውሮ ፡ ወደሚከተለው ፡ ንጉሥ ፡ ስለሚያልፍ ፡ ስለዚህ ፡ ጦርነት ፡ ዝርዝርሐተታ ፡ መስጠት ፡ ችግር ፡ ነው።

ለቤተ-ኣሹር ፡ ፈላሻ ፡ ዘመረባ ፡ የሚለው ፡ ቤተ ፡ አሹር ፡ ያምናልባት ፡ ቤተ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቤተ ፡ ኤዎስጣቴዎስ ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ የኤዎስጣቴዎስ ፡ ወገን ፡ እንደዚሁም ፡ የሞጃ ፡ ቤት (ወገን) እንደሚባለው ፡ ከፈላሾቹ ፡ ውስጥ ፡ አጅር ፡ የሚባለው ፡ ወገን ፡ መረባ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ የሚገኙት ፡ መሸፈታቸውን ፡ ለመስረዳት ፡ ይሆናል። እንደዚሁም ፡ የ፷፬ ፡ ዳኞቹ ፡ መሻር ፡ ምክንያቱ ፡ የተጨፈነ ፡ ነው። ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ፲፪ ፡ በትግሬ ፡ ፲፪ ፡ በሸዋየነበሩ ፡ ዳኞች ፡ በድምሩ ፡ ፳፬ ፡ የሚሆኑ ፡ በፈላሾች ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ግፍ ፡ ስለተቃወሙት ፡ ነው ፡ ብሏል ፡ ይህ ፡ እርሱ ፡ የሰጠውን ፡ ምክንያት ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ ከኛ ፡ ወገን ፡ በፍጹም ፡ ሳይኖር ፡ የእንግሊዙ ፡ ጸሐፊ ፡ ከምን ፡ እንዳመጣው ፡ ወይም ፡ በይመስላል ፡ ጽፎት ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም። ቢሆንምየኢትዮጵያን ፡ መንግሥትየሚመራው ፡ ንጉሥ ፡ ከነሹማምንቱ ፡ ከነመኳንንቱ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ስለሆኑ ፡ እስላሙን ፡ እንደ ፡ ፈላሻ ፡ ፈላሻውን ፡ እንደ ፡ እስላም ፡ መናቃቸው ፡ መጸየፋቸው ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ማጥቃታቸው ፡ ማጒላላታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው። በብልሃትና ፡ በስብከት ፡ በጋብቻ ፡ ሥልጣን ፡ በማካፈልና ፡ በማቅረብ ፡ ፈንታውያን ፡ ጊዜ ፡ በኃይል ፡ ብቻ ፡ እነዚህን ፡ ከክርስትና ፡ ውጭ ፡ ሌላ ፡ ሃይማኖት ፡ የያዙትን ፡ ፈላሾችና ፡ እስላሞች ፡ ለማጥፋት ፡ የክርስቲያኑ ፡ ክፍል ፡ ይጣጣር ፡ ነበር።

ይሁን ፡ እንጂ*በ፳፬ቱ ፡ ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ ቍጥር ፡ በሸዋና ፡ በትግሬ ፡ ለዳኝነት ፡ የተሾሙት ፡ ሰዎች ፡ ኣብዛኞቹ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰዎች ፡ መሆናቸው ፡ ሲታወቅ ፡ የቤተ ፡ ክህነቱም ፡ ወገኖች ፡ ሳሙኤል ፡ ሳአልን ፡ ፍልስጥኤሙን ፡ ፍጀው ፡ ጨርሰው ፡ እያለ ፡ ያዝ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እነሱም ፡ ፈላሻውን ፡ እስላሙን (ተንባላቱን)በለው ፡ ፍጀው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ፈላሾቹ ፡ ሲሉ ፡ በንጉሡ ፡ ባፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ በዚሁ ፡ የተነሣ ፡ ሻራቸው ፡ ብሎ ፡ ለማመን ፡ ይቸግራል። እኔ ፡ ግን ፡ የሚመስለኝ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ፳፬ቱን

፡ በለው ፡ አምባ (በለዋምባ) ሻራቸው ፡ የሚለው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፈላሾቹና ፡ እንደ ፡ አባሎቹ ፡ እስላሞች ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ የሚያምጹትን ፡ የበለውን ፡ ዘሮች ፡ ይሆናል። እነርሱም ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ከፈላሾች ፡ ወይም ፡ ከአዳል ፡ እስላሞች ፡ ጋር ፡ በሚዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ ኣንድነታቸውን ፡ ከነዚያ ፡ ጋር ፡ ያደርጉ ፡ ነበር። በኋላም ፡ ከነዚሁ ፡ ከበለው ፡ ወገኖች ፡ ተከፍለው ፡ ከአገራቸው ፡ ከትግሬ ፡ ወደ ፡ ኣዳል ፡ ኣገር ፡ ተዛውረዋል። ይኸንንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እናገኛለን።

# ምዕራፍ ፡ ፳፬

## በዐረብና ፡ በግብፃውያን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ዘንድ ፡ የሚገኘው ፡ ያፄ ፡ ይስሐቅ ፡ የውስጥ ፡ ጦርነት ፡ ያፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ፍጻሜና ፡ የተደረገላቸው ፡ ግጥም ፡

ከታሪክ ፡ ነገሥታችን ፡ ሌላ ፡ የግብፃውያንና ፡ የዐረብ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እነ ፡ ማቅሪዚ ፡ እነ ፡ አል ፡ ታግሪቢርዲ ፡ ባፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የተፈጸመ ፡ ፩ ፡ ኣንድ ፡ ታሪኮ ፡ የጻፉትን ፡ ፈረንጆቹ ፡ እነ ፡ ሙሴ ፡ ባሴት ፡ ረኔ ፡ ያቀርቡልናል።

በታግሪቢርዲ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፰፻፳፪ ፡ ዓመተ ፡ ሄጂራ ፡ በጉማዳኣል ፡ ኡልራ (ሰኔ)ሰባት ፡ ቀን ፡ የግብፁ ፡ ሱልጣን ፡ ሌሎቹን ፡ ቃዲዎቹንና ፡ ሹማምንቱን ፡ ሰብስቦ ፡ በተቀመጠበት ፡ አዳራሽ ፡ የክርስቲያኖቹን ፡ ፓትርያርክ (ሊቀጳጳሳት) ጠርቶ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እስላሞቹ ፡ ሲጠቁ ፡ ለምን ፡ ዝም ፡ ኣልህ ፡ ብሎ ፡ ኣጉላልቶ ፡ እስከ ፡ መግደል ፡ ድረስ ፡ ኣስፈራራው ፡ .... የሚል ፡ ይገኛል። የዚህም ፡ ምክንያት ፡ ዓፄ ፡ ይስሐቅ (እንደግማሾቹ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ በእስላሞቹ ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ ጦርነት ፡ ሱልጣኑ ፡ ሰምቶ ፡ ነው።

በኣል ፡ ማቅሪዚ ፡ መጽሐፍ ፡ ደግሞ ፡ የተጻው ፡ እንደዚህይላል። «ባፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ዘመን ፡ ኣልቱም ፡ ቦጋ ፡ የሚባል ፡ የሳይድ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ የነበረ ፡

የጦር ፡ መኰንን (ማመሉክ) ከግብፅ ፡ ሱልጣን ፡ ተጣልቶ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሔዶ ፡ ለዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ኣደረ። ይኸም ፡ መኰንን ፡ የነፍጥ ፡ ሥራ ፡ ስለሚያውቅ ፡ ለዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ እየሠራ ፡ ወታደሩንም ፡ ሰልፍና ፡ የወታደርነት ፡ ሥልጣኔ ፡ አስተማራቸው። እንዲሁም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ሁለት ፡ ግብፃውያን ፡ አንዱ ፡ ለወታደርነት ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጌጥና ፡ የልብስ ፡ ሸቀጥ ፡ እያመጣ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ አጥግቦት ፡ ነበር። እንደዚሁም ፡ ፋክር ፡ ኤል ፡ ዳውሌት ፡ የሚባል ፡ የግብፅ ፡ መነኰሴ ፡ አስተዳደርና ፡ ሕግ ፡ የሚያውቅ ፡ መጥቶ ፡ ለዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ያገለግል ፡ ነበር። ዓፄ ፡ ይስሐቅም ፡ እስላምን ፡ ለማጥፋት ፡ ወደ ፡ ፍራንኮች ፡ ንጉሥ ፡ ደብዳቤ ፡ መላላክ ፡ ዠምሮ ፡ ነበር። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰኣድ ፡ ዲን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ አሥሩ ፡ ልጆቹ (በዘሩ ፡ ሐረግ ፡ ላይ ፡ በየታሪኩ ፡ የሚገኙት ፡ ፫ ፡ ብቻ ፡ ናቸው) ወደ ፡ ዐረብ ፡ ኣገር ፡ ሸሽተው ፡ በናስር ፡ ኣሕመድ ፡ ብን ፡ ኣሽራፍ ፡ ኢስማኤል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሲኖሩ ፡ ከርሱ ፡ ርዳታ ፡ ይዘው ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ኣፍሪካ (ኢትዮጵያ) ተሻገሩ ፤ ከመካከላቸውም ፡ ታላቁን ፡ ወንድማቸውን ፡ ሳብር ፡ አድ-ዲንን (በዘሩ ፡ ሐረግ ፡ ላይ ፡ ተመልከት) አዝማች ፡ አደረጉት። እርሱን ፡ መሪ ፡ እናድርገው ፡ በሳያራህ ፡ ሲቀመጡ ፡ የጥንት ፡ ያባታቸው (የመሐመድ ፡ አቡል ፡ ባራካት ፡ ማለቱ ፡ ነው) ወታደርና ፡ ተከታይ ፡ እየመጣ ፡ ገባላቸው።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ ኣነሡና ፡ መዠመሪያ ፡ በድዚቅር ፡ አህማራህ ፡ ቀጥሎ ፡ በሳርጋ (ጀ)ን ፡ ወረራ ፡ ኣደረጉ። ነገር ፡ ግን ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ እንደገና ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ በናጅት ፡ ባቃል ፡ መሪነት ፡ መጥተው ፡ እስላሞቹን ፡ ከገቡበት ፡ አገር ፡ መልሰው ፡ አባረሯቸው። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ የክርስቲያኖቹን ፡ መሪ ፡ የኤሚሩ (ሳብር ፡ አድ ፡ ዲን) ፡ ወንድም ፡ መሐመድ (አህመድ?) አሸነፈውና ፡ ገደለው። ሌላው ፡ ወንድሙ ፡ ኡመር ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ ተሸንፎ ፡ እሱም ፡ ከሞት ፡ ለጥቂት ፡ አምልጦ ፡ ሸሸ። ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ሰላም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ሳብርኣድ ፡ ዲን (፰፻፳፭ ፡ ዓመት ፡ ሄጅር) ፡ ስለሞተ ፡ በርሱ ፡ ምትክ ፡ ወንድሙ ፡ መንሱር ፡ ሳአድ ፡ ዲን ፡ ተተካና ፡ ጦርነቱን ፡ ይቀጥል ፡ ዠመር። ማንሱርም ፡

እስከ ፡ ንጉሡ ፡ መቀመጫ ፡ እስከ ፡ ጀዳያሀ" እስከ ፡ ሞካ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ በመዠመሪያው ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ አሸናፊ ፡ ሆኖ ፡ ነበር። ዳሩ ፡ ግን ፡ በመጨረሻ ፡ ይስሐቅ ፡ ድል ፡ መታና ፡ እርሱን ፡ ከነወንድሙ (መሐመድ) ማርኮ ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ በርሱ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ እስረኛ ፡ ሆነው ፡ ኖሩ። ከማንሱር ፡ ቀጥሎ ፡ አሁንም ፡ ወንድሙ ፡ ጀማል ፡ ኣድ ፡ ዲን (ጋማልዲን) በሥፍራው ፡ ተተክቶ ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ለመውጋት ፡ ተነሣ። የርሱ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ሀርብ ፡ ጃውሽ ፡ በያጅዛህ ፡ በጀዳያሀ ፡ በባሊ ፡ እየተዋጋ ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ከነመሣሪያቸው ፡ ሲማርክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሲያቃጥል ፡ ደዋሮንም ፡ ሲዘርፍ ፡ ማርኮ ፡ ያመጣቸውንም ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ (በየገበያው) ሲሸጥ ፡ ራሱ ፡ ጋማል ፡ ኤዲን ፡ ደግሞ ፡ ከዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ጋር ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ፡ እርሱንም ፡ እየወጋ ፡ እስካ ፡ ዓባይ ፡ ወንዝ ፡ አደረሰው። »

ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ማክሪዚ ፡ የሚባለው ፡ የዓረቡ፣ ጸሐፊ ፡ የተረከው ፡ ስለሆነ ፡ ትልቁን ፡ የይስሐቅን ፡ ጦር ፡ አሸንፎ ፡ አድ ፡ ዲን ፡ ንጉሡን ፡ እስከ ፡ ዓባይ ፡ ድረስ ፡ ማሸነፉን ፡ እየተጠራጠሩ ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ እንዲያውም ፡ ዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ሳአድ ፡ ዲንን ፡ ሀራጃህ ፡ ላይ ፡ በኃይል ፡ ወግቶ ፡ አባርሮታል ፡ ብላው ፡ እነሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ጥናት (ምርመራ) ከሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ በገጽ ፡ ፫፻፫ ፡ ቀጥር ፡ ፱ ፡ ተመልከት።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ከዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እስከ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ድረስ ፡ ካሉት ፡ ነገሥታት ፡ በጦርነትም ፡ ባስተዳደርም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የሚገመት ፡ ንጉሥ ፡ ነው። ደጃዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ሰበሰቡት ፡ ከሚባለው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ ለዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ላፄ ፡ ዳዊት ፡ ለዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እተደረሰው ፡ ግጥም ፡ ውስጥ ፡ ስለዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ በረዥሙ ፡ የተገጠመ ፡ አለ። ግጥሙ ፡ እንደሌሎቹ ፡ ኣማርኛና ፡ ግዕዝ ፡ የተደባለቀበት ፡ ለዛሬው ፡ ዘመን ፡ በግልጽ ፡ የማይገባና ፡ የማያምር ፡ ቢሆንም ፡ በታሪክነቱ ፡ ውድና ፡ ብርቅ ፡ ስለሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሱ ፡ ጽፈነዋል። ግጥሙ ፡ በዘመናቸው ፡ የተገጠመ ፡ ወይም ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ በተከታዮቻቸው ፡ ዘመን ፡ የተደረሰላቸው ፡ መሆኑን ፡ ማረጋገጥ ፡ ኣይቻልም።

ቢሆንም ፡ የግጥሙ ፡ አካሄድና ፡ አለማማር ፡ አማርኛና ፡ ግዕዝ ፡ የተደባለቀበት ፡ በመሆኑ ፡ በዚያው ፡ በ፲፭ኛው ፡ ቢበዛ ፡ በ፲፮ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ውስጥ ፡ የተገጠመ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም።

## የግጥሙን ፡ ዓይነት ፡ እንመልከት።

ገጽ ፡ ዠን ፡ ይስሐቄ ፡ ገጽ ፡
በአርያም ፡ ይመስል ፡ አንቀጽ ፡
እሳት ፡ ይመስል ፡ ብቍጽ ፡
ከመ ፡ መዳልው ፡ ልጽሉጽ ፡
ገጹ ፡ እንዲያስደነግጽ ፡
እስራኤላዊ ፡ መደንግጽ ፡
ዓይነ ፡ ቀራንብቱን ፡ ቢገልጽ ፡
ማን ፡ አየህ ፡ ገጽ ፡ በገጽ
ዓይን ፡ እንደሎሚ ፡ ይፍረጽ ፡
ገላው ፡ እንደሸንኰርት ፡ ይላጽ ፡
ያየህ ፡ ገጽ ፡ በገጽ ፡
እሳት ፡ ይመስል ፡ ዣን ፡ ተራራ ፡ እኂዞ ፡ ሲልጽ
ማዕበሉ ፡ ሲቆረፅ ፡
እንዲያስደነግጽ ፡
ኣንበሳ ፡ ይመስልን ፡ ዣን ፡ ፍሪዳ ፡ እኂዞ ፡ ሲጋየጽ
ማዕከለ ፡ ኣገዳውን ፡ ሲፈጸፍጽ ፡
እንዲያስደነግጽ ፡
እንዴት ፡ ታስደነግጽ ፡
ጎሽ ፡ ከፊላው ፡ ሲወጽ (ሲወጣ)
ዱር ፡ በቀንድ ፡ ሲገልጽ ፡
እስትንፋሱ ፡ ሲቆረጽ ፡
ደንጊያ ፡ በእግሩ ፡ ሲፈልጽ ፡
እንዲ (ያ)ስደነግፅ ፡

እንዴት ፡ ታስደነግጽ ፡
ደንጊያ ፡ በቍልቍለት ፡ ሲሮጽ ፡
እርስ ፡ በርሱ ፡ ሲፋለጽ ፡
እንዲ (ያ)ስደነግጽ ፡
እንዴት ፡ ታስደነግጽ ፡
ኮከብ ፡ ትመስል ፡ ዣን ፡ በጽሩ ፡ ሰማይ ፡ ሲሮጽ ፡
ወደምዕራብ ፡ ሲሠርጽ ፡
ገጽኹ ፡ እንዲያስደነግጽ ፡
ሲሬ ፡ ሲራዊ ፡ ይመስል ፡ ዣን ፡
ሐምበል ፡ አልብሶ ፡ ረመጽ ፡
ጐድን ፡ በፊም ፡ ሲፈጸፍጽ ፡
ሐንገት ፡ በሰይፍ ፡ ሲቆርጽ ፡
ገጽኹ ፡ እንዲያስደነግጽ ፡
ዣን ፡ ይስሐቂ ፡ ገጽ ፡
ምልአት ፡ ይመስል ፡ ዢን ፡
ሳፍ ፡ ለሳፍ ፡ ከንፈርዓጽ ፡
ወርካ ፡ ከሥሩ ፡ ነቅሎ ፡ ሲያሮጽ ፡
እንዲያስደነግጽ ፡
ገጽኹ ፡ የዣን ፡ ይስሐቄ ፡ እንዲያስደነግጽ ፡
ዣን ፡ ይስ (ሐ)ቄ ፡ ገጽ ፡
ፈረስ ፡ ሲያሮጽ ፡ ሲጋየጽ ፡
ስለጢን ፡ እኂዞ ፡ የግብፅ ፡
ዛብያው ፡ ያይታወቅ ፡ ዕፅ ፡
ማን ፡ ያአየህ ፡ ገጽ ፡ በገጽ ፡
ወምበዴ ፡ ጠፋ ፡ ለድምጽ ፡
ዓይን ፡ በፍል ፡ ስታፈርፅ ፡
እጅ ፡ በብልሕ ፡ ስትቈርፅ ፡
ጥበብህ ፡ የግብፅ ፡
ኃይልህ ፡ የሕንፅ ፡

ዣን ፡ ይስሐቁ ፡ ትኵር ፡
ትኵረቱም ፡ ተምክር ፡
የዣን ፡ ይስሐቁ ፡ ነገር ፡
በሐብል ፡ በቃላ ፡ ጐዣም ፡ ይንግር ፡
አፍሶ ፡ አይፈጁ ፡ አፈር ፡
መትሮ ፡ አይፈጁ ፡ ግራር ፡
እስኩ ፡ ይንግር ፡ የእሳታዊ ፡ ዱር ፡
ለበቅሉ ፡ ያልበቃው ፡ መተከል።
ለፈረስ ፡ አልበቃው ፡ ጨንገር ፡
በኀብልም ፡ በቃል ፡ ይንግር ፡
ብዝ (ዛ)ቱን ፡ የሚቆፅር ፡
ሻንቅላ ፡ ይንግር ፡
ፍየሉን ፡ የሚያቈፅር ፡
ቢዛማ ፡ ይንግር ፡
ብዝት ፡ የሚያቊፅር ፡
ዕቢ ፡ ይንግር ፡
ብዛት ፡ የሚያቈፅር ፡
በረድ ፡ ይንግር
ጕቱን ፡ የሚይነግር ፡
ጕቱን ፡ የሚቊፅር ፡
በጥ ፡ ይንግር ፡
ገቿን ፡ የሚያቈፅር ፡
ማለጕ ፡ ይንግር ፡
ገቹን ፡ የሚያቈፅር ፡
አበድራይ ፡ ይንግር ፡
ገቹን ፡ የሚቈፅር ፡
ገምቦ ፡ ይንግር ፡
ግብሩን ፡ የሚገብር ፡
ኣብስሎ ፡ ተብቅል ፡

ግምጃ ፡ ቤት ፡ የሚጀጐል ፡
ሸት ፡ ይንገር ፡
ገቹን ፡ የሚገብር ፡
ድጋዕት ፡ ይንግር ፡
ዋማ ፡ ይንግር ፡
ዜት ፡ ይንግር ፡
ወርቀ‍ን ፡ የሚገብር ፡
ዝንጀሮ (ጃንጀሮ) ይንገር ፡
ከምበት (ከምባታ) ይንገር ፡
ፈረሱን ፡ የሚያቈጽር ፡
ኣነሞር (እነሞር) ይንግር ፡
ተረቀር ፡ ይንግር ፡
ሓውዘኛ ፡ ይንግር ፡
ፈረስ ፡ የሚገብር ፡
ቈጪ ፡ ይንግር ፡
ዝርጎ ፡ ይንገር ፡
የአንበሳ ፡ መትከል ፡ ብሶ ፡ ደንጊያ ፡ ያኖር ፡
ኳራ (ቋራ)ይንግር ፡ ፈረሱን ፡ የሚገብር ፡
ዛቶ ፡ ይንግር ፡ ወለም ፡ ይንገር ፡
ባሕር ፡ ገሞ ፡ ይንገር ፡ ሱፍ ፡ ገሞ ፡ ይንገር
ፈረስ ፡ የሚገብር ፡ ሐለባ ፡ ይንገር ፡
ቆቤን ፡ ይንገር ፡ ባደብ ፡ ይንገር ፡
ጉዴላ ፡ ይንገር ፡ ባሊሾች ፡ ይንግር ፡
ማና ፡ ይንገር ፡ ደሽላ ፡ ይንገር ፡
ዝቡራ ፡ ይንገር ፡ ዣን ፡ ይስሐቄ ፡ ትኵር ፡
እንደ ፡ ሀበልሁስ ፡ በቃል ፡
ሱማሌ ፡ ይንግር። ጽሙር ፡ ይንገር ፡
ዘንካር ፡ ይንገር ፤ አዳል ፡ ይንገር ፡
ባሕር ፡ ማተባ ፡ ይንገር ፡

በሰው ፡ ባለ ፡ ሀገር ፡
አብርሃም ፡ የሚሉ ፡ ታቦት ፡ ተከል ፡
ለቅዱሳን ፡ ናኝ ፡ ምድር ፡
በብረት ፡ አስጀጐል ፡ በሪም ፡ ኣስማገር ፡
ዣን ፡ ይስሐቄ ፡ ትኰር ፡
ትኰረቱም ፡ ተምክር ፡
እንደሐበልሁ ፡ በቃል ፡ ምጽዋ ፡ ይንገር ፡
በምጽዋ ፡ ምድር ፡
ጠረስምባው ፡ የነበር ፡
እንጀራ ፡ በምኵር ፡ ጻላው ፡ በስፍር ፡
አብ ፡ ከልጁ ፡ ሲጨመር ፡
ጻፋዋቾ ፡ ሲናሰር ፡
ዣን ፡ ይስሐቄ ፡ ከዘመት ፡ ሀገር ፡
ተንቀሳቀሰች ፡ ሀገር ፡
ጎማ ፡ አዘነች ፡ በዱር ፡
ኣሣም ፡ ኣዘነ ፡ በባሕር ፡
ባሕሩም ፡ ኣዘነ ፡ በጅባር
ዣን ፡ ይስሐቄ ፡ ሐወረወር
ግድ ፡ የዣን ፡ ሐርብይ ፡ ወልድ ፡
ዓለሙን ፡ ገዝዋቾ ፡ በግድ ፡
አልገዙዋቸውም ፡ በውድ ፡
ረጅም ፡ ዋርካ ፡ ከተነሐድ ፡
ባለምሳር ፡ ከወረድ ፡ ረዥም ፡ ለዓምድ
ሐጭሩን ፡ ለገደራድ ፡
አስመስሎ ፡ ገባሬ ፡ ሐርድ ፡
ዣን ፡ ይስሐቄ ፡ የግድ
መላሳይ ፡ አለ ፡ ኑ ፡ እንሂድ ፡
ከዚሁ ፡ ማን ፡ ይፃመድ ፡
ከእምሰማይ ፡ ወረድ ፡

ከመላእክታት ፡ የተፈረድ ፡
ሲይፈጀን ፡ በስላውን ፡ ሲሰጕድ ፡
እንደ ፡ አሣ ፡ ሲላጭድ ፡
መለሳይ ፡ ኣሉ ፡ እንሂድ ፡
ዢብ ፡ የየኀዝ ፡ ክበድ ፡
ሐተን ፡ ጠበጠበ ፡ ብርንድ ፡
አስመሰሉ ፡ ገባሬ ፡ ሐርድ ፡
ዣን ፡ ይስሐቄ ፡ የግድ ፡
የዣን ፡ ሐርቤይ ፡ ወልድ ፡
ኢያማዢን ፡ ይስሐቄ ፡ ኢያማ ፡
አሁንም ፡ ወዴትማ ፡
ተመታእ ፡ በገናኾማ ፡
ወደል ፡ ሐደሰማ ፡
ጋጃ ፡ ነፋሳማ ፡
ምሥራቅ ፡ ኾነች ፡ ጨማሪ
ምዕራብ ፡ ኾነች ፡ ማማ ፡
ተተከል ፡ ቃራሁማ ፡ መስቀል ፡ ደባማ
እንግዴህ ፡ ወዴትማ ፡ ዣን ፡ ይስሐቅ ፡ ኢያማ፡

# ምዕራፍ ፡ ፳፫

## እንድርያስ--ተክለ ፡ ማርያም–ሠርዌ ፡ ኢየሱስ--ዓምደ ፡ ኢየሱስ።

አግብኣ ፡ ጽዮን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እንደሆነው ፡ አሁንም ፡ ዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ድረስ ፡ ዘመኑ ፡ የረዘመ ፡ በሥልጣኑ ፡ የቆየ ፡ ትልቅና ፡ ኃይለኛ ፡ ንጉሥ ፡ በዙፋን ፡ አልተቀመጠም። ስለዚህ ፡ ታሪክ ፡ ነገሥቱም ፡ «እንድርያስ ፡ ወልዱ ፡ ለይስሐቅ ፡ ነግሠ ፡ ፮ተ ፡ ኣውራኃ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ ዘውእቱ ፡ ሕዝበ ፡ ናኝ ፡ ሣልሳይ ፡ ወልዱ ፡ ለዳዊት ፡ ነግሠ ፡ ፬ተ ፡ ዓመተ ፡ ሠርዌ ፡ **ኢየሱስ** ፡ ዘስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ምህርካ ፡ ናኝ ፡ ወውእቱ ፡ ወልዱ ፡ ለሕዝበ ፡ ናኝ ፡ ነግሠ ፡ ፬ተ ፡ አውራኃ ፡ ዓምደ ፡ **ኢየሱስ** ፡ ዘውእቱ ፡ በድል ፡ ናኝ ፡ ካልዕ ፡ ወልዱ ፡ ለሕዝበ ፡ ናኝ ፡ ነግሠ ፡ ፰ተ ፡ ኣውራኃ ፡ ጠፍ ፡ ናቸው ፡ ሠለስቲሆሙ ፡ እያለ ፡ ከማለፍ ፡ በቀር ፡ ከአምስቱ ፡ ላንዳቸውም ፡ ኣጭር ፡ ታሪክ ፡ አልሰጣቸውም። ሁል ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ኃይለኛ ፡ ንጉሥ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ አብዛኛው ፡ ጊዜ ፡ ደካሞች ፡ ንጉሦች ፡ ይከተሉታል። ከደካሞቹ ፡ ነገሥታት ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ መልሶ ፡ ኃይለኛ ፡ ንጉሥ ፡ ይመጣል። ፫ቱ ፡ የያግብአ ፡ ጽዮን ፡ ልጆችና ፡ ውድም ፡ ረዓድ ፡ ካላፉ ፡ በኋላ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ የመሰለ ፡ ኃይለኛና ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከነዚህ ፡ ከአምስቱ ፡ አንዱ ፡ ፬ ፡ ዓመት ፡ የቀሩት ፡ ፬ ፡ ወር ፡ ፮ ፡ ወር ፡ ሁለቱ ፡ ፰ ፡ ወር ፡ ነግሠው ፡ የበቃ ፡ ጊዜ ፡ ሳያገኙ ፡ የጐላ ፡ ሥራ ፡ ሳይሠሩ ፡ ሲያልፉ ፡ ከነርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ በጦርነት ፡ በውስጥ ፡ ኣስተዳደር ፡ ገናና ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ንጉሥ ፡ ያለ ፡ ተነሣ። እርሱም ፡ በደካሞቹ ፡ ምክንያት ፡ ሲያንቀላፋ ፡ የነበረውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኃይል ፡ እንደገና ፡ ቀሰቀሰው። የክርስትናው ፡ ሃይማኖት ፡ በእስላም ፡ ወይም ፡ በኣረመኔ ፡ ሃይማኖት ፡ ሊወረር ፡ ሲል ፡ እንደገና ፡ ኣደሰው። በዚህ ፡ መካከል ፡ ከወንጌል ፡ ቃል ፡ ውጭ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ግፍ ፡ መሥራቱ ፡ ባይዘነጋም ፡ ታላላቅ ፡ ነገሥታት ፡ የሆኑት ፡ ሁሉ ፡ ይኸን ፡ ከመሰለ ፡ ግፍ ፡ ሥራ ፡ ሊርቊ ፡ ኣልቻሉምና ፡ በርሱ ፡ ብቻ ፡ አይፈረድም ፡ ደግሞ ፡ ታላላቅ ፡

ነገሥታት ፡ መንግሥታቸውን ፡ የሚያጸኑበት ፡ ወይም ፡ የሚያገኙበት ፡ ከጭካኔና ፡ ከኃል ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ የላቸውም። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ወደፊት ፡ የዚህን ፡ የስመ ፡ ጥር ፡ ንጉሥ ፡ ታሪክ ፡ እናነባለን። እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ለአሉት ፡ ነገሥታት ፡ እርስዎታ ፡ ያልሰጠነውን ፡ አሁን ፡ ከኺህ ፡ ታላቅ ፡ ንጉሥ ፡ ዠምረን ፡ የሚቀጥሉትንም ፡ እርሱ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ እርሳቸው ፡ እያልን ፡ እንጽፋለን።

ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ኣምስቱ ፡ ነገሥታት ፡ በነ ፡ ማቅሪዝ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ኣጭር ፡ ጥቅስ ፡ እንመልከት።

ጋማል ፡ አድ ፡ ዲን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሽሀብ ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ ኣሕመድ (ኣርዊ ፡ በድላይ) በወንድሙ ፡ ሥፍራ ፡ ተተክቶ ፡ የወንድሙን ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ውጊያ ፡ ዠመረ። የባሊንም ፡ አገር ፡ ወረረ ፡ ፺ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አቃጠለ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ በድልናኘ (ዓምደ ፡ **ኢየሱስ**) እስላሞቹን ፡ ወግቶ ፡ አገራቸውን ፡ ሁሉ ፡ ወረረው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሺሃብ ፡ አድ ፡ ዲን ፡ ታርቆ ፡ ወደ ፡ በድልናኝ ፡ ሊገባ ፡ ሲል ፡ በዚያን ፡ ሰዓት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ትልቅ ፡ በሽታ ፡ ገብቶ ፡ ነበርና ፡ ንጉሡ ፡ በዚሁ ፡ በሽታ ፡ ሞተ ፡ ቢሆንም ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ በበሽታው ፡ ምክንያት ፡ በእስላሞቹም ፡ በክርስቲያኖቹም ፡ መካከል ፡ ጦርነቱ ፡ ቆመ ፡ እያለ ፡ ተርኮ ፡ ያቆማል።

# ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ ፳፪።

## ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸው።

ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ከኣብርሃ ፡ ከካሌብ ፡ ከላሊበላ ፡ ከዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ፲፰ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ያለ ፡ ስመጥር ፡ ንጉሥ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አልተነሣም። ከርሳቸው ፡ ወዲህ ፡ ያሉት ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፤ ፋሲል ፤ ኢያሱ ፤ ኣድያም ፡ ሰገድ ፡ እንዳለፉት ፡ ሁሉ ፡ ስመ ፡ ጥርነታቸው ፡ ገናናነታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው። የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ ላማስፋት ፡ የውስጡን ፡ ኣንድነት ፡ ለማጥበቅ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በማናቸውም ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ እንድትሆን ፡ በመጣር ፡ ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ ከዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሲመሳሰል ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ከነርሱ ፡ የሚበልጠው ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ከመፈጸማቸው ፡ ጋር ፡ የቤተ ፡ ክህነትና ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ደንብና ፡ ሕግ ፡ ጽኑ ፡ እንዲሆን ፡ ራሳቸው ፡ መጽሐፍ ፡ እያወጡ ፡ በማሻሻል ፡ የንጉሥ ፡ ደራሲ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው። ለኘህ ፡ ለስመጥር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክና ፡ ቋንቋ ፡ በጥብቅ ፡ የሚከታተሉት ፡ ታላላቅ ፡ ጸሐፊዎች ፡ እነዲልማን ፡ እነኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደራቸውን ፡ ክርስትና ፡ ለማስፋት ፡ አምልኮ ፡ ጣዖትን ፡ ለማስወገድ ፡ ያደረጉትን ፡ ትግል ፡ ተመልክተው ፡ የጻፏቸውንም ፡ መጻሕፍት ፡ ወደየቋንቋቸው ፡ እየተረጐሙ ፡ በመመርመር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ሰጥተዋቸዋል። ሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ተዓቅቦ ፡ ምሥጢር ፡ የሚባለውን ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ መጽሐፍ ፡ ግዕዙን ፡ ወደ ፡ ጣልያንኛ ፡ ተርጒመው ፡ እመረመሩበት ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ከነበሩት ፡ ዡምሮ ፡ እስከ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ድረስ ፡ ካሉት ፡ ነገሥታት ፡ ዋነኛው ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ » ፡ ይላሉ።

እርሳቸውም ፡ በዘር ፡ ሐረጉ ፡ ላይ ፡ እንደምንመለከተው ፡ ያፄ ፡ ዳዊት ፡ ፬ኛው ፡ ልጅ ፡ ያፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ያፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ያፄ ፡ ተክላ ፡ ማርያም (ምሕርካ ፡ ናኘ) ወንድም ፡ ናቸው። እናታቸው ፡ እግዚእ ፡ ክብራ ፡ ይባላሉ። የተወለዱበት ፡ ሥፍራ ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ ጥልቅ ፡ ውስተ ፡ ምድረ ፡ ፈጠጋር ፡ እንደሚለው

፡ በፈጠጋር ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡ ከሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ነው። ፈጠጋር ፡ የሚባለው ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ዝምሮ ፡ የታወቀ ፡ እንደአንድ ፡ የንጉሥ ፡ አውራጃ ፡ የሚቆጠር ፡ ከተጉለት ፡ ዝምሮ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ያለው ፡ የቡልጋ ፡ የሸንኮራ ፡ የምንጃር ፡ ያዳማ (ናዝሬት) ፡ ግዛት ፡ እስከ ፡ ባሌና ፡ እስከ ፡ ኣሩሲ ፡ ድንበር ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ አገር ፡ ነው ፡ በዚዎግራፊው ፡ ካርታ ፡ ላይ ፡ አንባቢ ፡ ሊመለከተው ፡ እንደሚችል (የአውራጃ ፡ የግዛት ፡ ዓደኞቹ ፡ ይፋት ፡ ደዋሮ ፡ አዳል ፤ ዳሞት ፡ ጐዝም ፡ .....ናቸው።

ኣሁን ፡ ለምንጽፈው ፡ ታሪካቸው ፡ መሠረት ፡ ኣድርገን ፡ የምንጠቀምበት ፡ በግዕዝ ፡ የተጻፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ አላቸው። ጽሑፉ ፡ ለታሪክ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚነት ፡ ያለውነው። ያፄ ፡ አምደጽዮን ፡ ፩ኛ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጦርነት ፡ ብቻ ፡ ሲተርክልን ፡ ይኸኛው ፡ ጦርነትም ፡ አስተዳደርም ፡ አምልኮም ፡ ድርጅት ፡ እንደመጠኑ ፡ አሟልቶ ፡ ያሳየናል። በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቀድሞ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነበሩ ፡ ዳልሜይዳ (፩፻፺፻፸፫ ፡ ዓ.ም) ጀምስ ፡ ብሩስ (፩፻ ፡ ፯፻፷፱–፩፻፺፻፸፫ ፡ ዓ.ም) የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ በየቋንቋቸው ፡ በፓርቱጋልና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ሲጽፉ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ተጠቅመውበታል ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በ፻፷፻፷ ፡ ዓ.ም ፡ አፄ ፡ ቲዎድሮስን ፡ ሊወጋ ፡ <u>በዠኔራል ፡ ናፒየር ፡</u> እየተመራ ፡ የመጣው ፡ የእንግሊዝ ፡ ጦር ፡ የንጉሡ ፡ ዕቃና ፡ መዛሪያ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ተሰብስበው ፡ ከተቀመጡበት ፡ ከመቅደላ ፡ ኣግኝቶ ፡ ሁሉንም ፡ ሰብስቦ ፡ ፷፱ ፡ የሚሆኑ ፡ በእጅ ፡ የተጻፉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍቶቻችንን ፡ ይዞ ፡ ወዳገሩ ፡ ወደ ፡ ሎንዶን ፡ ሲመለስ ፡ ይህ ፡ ያዔዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ የልጃቸው ፡ የበእደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ አብሮ ፡ ነበር። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንግሊዞች ፡ እነዚህን ፡ መጻሕፍቶቻችንን ፡ ወስደው ፡ መኳንንቶቻቸውና ፡ ሊቃውንቶቻቸው ፡ ለየራሳቸው ፡ ኣልተካፈሉትም። ነገር ፡ ግን ፡ ዝርዝሩ ፡ በመጽሐፍ ፡ ወጥቶ ፡ ብሪቲሽ ፡ ሙዜውም ፡ በሚባለው ፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍታቸው ፡ በደምብና ፡ በክብር ፡ ተቀመጠ። ከዚያ ፡ መጽሐፉን ፡ እመረምራለሁ ፡ የሚል ፡ እየገባ ፡ እየተመለከተ ፡ እንዲመረምረው ፡ እንዲቀዳው ፡ እንዲያራባው ፡ ተደረገ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ *ሙሴ ፡ አጉስት ፡ ዲልማን ፡* ጀርመኑ ፤ *ሙሴ ፡ ዋሊያም ፡ ራይት ፡* እንግሊዙ ፤ *ሙሴ ፡ ዥል ፡ ፒሩሾ ፡* ፈረንሳዊው ፡ እየተመለከቱ ፡ ዝርዝር ፡

እያወጡ ፡ ወደየቋንቋቸው ፡ እየተረጐሙ ፡ በማኅተም ፡ እያተሙ ፡ ለጻሐፊና ፡ ለአንባቢ ፡ እንዲራባና ፡ እንዲጠቅም ፡ አደረጉት። የነርሱንም ፡ መሠረት ፡ እያደረገ ፡ ጸሐፊው ፡ ሁሉ ፡ *ባሴት ፡ ረኔ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡* ኵልዐ ፡ በመጠኑ ፡ ተጠቀሙበት። ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ ታሪክ ፡ ቀድሞ ፡ በትንሹ ፡ እየተጠቀሰ ፡ ይታለፍ ፡ የነበረው ፡ ቀረና ፡ እየሰፋ ፡ ይጻፍላቸው ፡ ዠመር።

ይህ ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በዘመናቸው ፡ ለመጻፉ ፡ ዕምነት ፡ የሚሰጥ ፡ ማስረጃ ፡ የለም። በየአረፍተ ፡ ነገሩ (በየምዕራፉ) መጨረሻ ፡ የርሳቸውን ፡ ስም ፡ «ለዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ያውርሶ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ... ፡ ይልና ፡ ከዚያው ፡ ቀጥሎ ፡ ወለወልዱ ፡ ልብነድንግል ፡ የሀቦ ፡ ኃይለ ፡ ወይባርከ ፡ ንግሦ ፡ የሚል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ስለሚናገር ፡ አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ በልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ባፄ ፡ ናዖድ ፡ ልጅ ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጊዜ (፩ሺ፫፻ ፡ ፩ሺ፮፻፴፪ ፡ ዓ.ም) ነው ፡ የተጻፈው ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል። በዚህም ፡ አሳብ ፡ ብዙ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ተስማምተውበታል። ነገር ፡ ግን ፡ ነገሥታትና ፡ መሣፍንት ፡ ከነርሱ ፡ በፊት ፡ ከተጻፈ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ የሆነውን ፡ መጽሐፍ ፡ ሲያገኙና ፡ በዘመናቸው ፡ ሲያስገለብጡ ፡ በየምዕራፉ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ «ዕቀቦ ፡ ለእገሌ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ዕቀበኒ ፡ ሊተ ፡ ለገብርካ ፡ እያሉ ፡ መጨመራቸው ፡ የተለመደ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ውስጥ ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ስም ፡ ተጠቅሶ ፡ መገኘቱ ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ለመጻፉ ፡ በቂና ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን ፡ አይችልም። ምናልባት ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዛቸው ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሰዓታቸ ፡ ጽፎት ፡ ሲኖር ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ካለፈው ፡ በኋላ ፡ አሮጌውን ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጸሐፊ ፡ አግኝቶ ፡ የዚያን ፡ ስም ፡ ሳያነሣ ፡ አድሶ ፡ ባዲስ ፡ ብራና ፡ ገልብጦት ፡ ይሆናል። አዲስ ፡ የተገለበጠውን ፡ የቀድሞ ፡ አያታቸውን ፡ ታሪክ ፡ ንጉሡ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በሚመለከቱበት ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ እንዲላቸው ፡ የርሳቸውን ፡ ስም ፡ ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እየቀጠለ ፡ ጽፎት ፡ ይሆናል። በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ፩ዱን ፡ ጉዳይ ፡ ሥፍራና ፡ ጊዜ ፡ እየለየ ፡ ለየብቻ ፡ በሁለት ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ሚተርከው ፡ ጽሑፉ ፡ ምናልባት ፡ የሁለት ፡ ሰው ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ያሰኛል። ወደ ፡ ፊት ፡ እንደ

፡ ምናገኘው ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተርኮ ፡ የቆረጠውን ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ከፊተኛው ፡ አጉድሎ ፡ ወይም ፡ ጨምሮ ፡ ይጽፈዋል።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ውስጥ ፡ ንጉሡ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ ከነገሡ ፡ ዠምሮ ፡ ጣዖታትን ፡ ለማጥፋት ፡ ይኸውም ፡ ማለት ፡ ከክርስትናና ፡ ከእውነተኛው ፡ አምላክ ፡ ውጭ ፡ ሕዝቡ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የዛፍ ፡ የአድባር ፡ የመናፍስት ፡ አምልኮ ፡ ይዞ ፡ የነበረውን ፡ ለማስቀረት ፡ ባዋጅም ፡ በቅጣትም ፡ የፈጸሙት ፡ ይገኛል። ቀጥሎ ፡ ሹም ፡ ሽርና ፡ የግዛት ፡ ድርጅት ፡ የሐድያው ፡ ገራድ ፡ የማሂኮ-ሽፍትነት ፤ ጨዋ ፡ የሚባለው ፡ በያገሩ ፡ በድልድል ፡ እንደተሾመ ፡ ንጉሡ ፡ ኣክሱም ፡ ጽዮን ፡ ሄደው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ መፈጸማቸው ፡ ከዚያ ፡ መልስ ፡ በየመንገዱ ፡ በኣማራው ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ኣብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ እየተከሉ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተመልሰው ፡ ከአርዌ ፡ በድላይ ፡ መዋጋታቸው ፤ የደብረ ፡ ብርሃን ፡ የደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ የቂርቆስ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሥራ ፤ በውስጡ ፡ የሚስቶቻቸውና ፡ የልጆቻቸው ፡ የሹማምንቶቻቸው ፡ ስም ፡ ይገኛል። ጸሐፊው ፡ ይኸን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ሲያዘጋጅ ፡ የቀን ፡ የቀኑን ፡ ይኸም ፡ ቢቀር ፡ ያመት ፡ ያመቱን ፡ ተግባራቸውን ፡ እየተከተላ ፡ መደዳውን ፡ በሕግና ፡ በሥርዓት ፡ መሥራቱና ፡ አለመሥራቱ ፡ አይታወቅም። የመረው ፡ የጣዖት ፡ አምልኮን ፡ ለማጥፋት ፡ ባደረጉት ፡ አዋጅና ፡ ቅጣት ፡ ነው። አክሱም ፡ ሔደው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ማከበራቸውን ፡ የሚጽፈው ፡ ወደ ፡ መካከሉ ፡ ላይ ፡ ነው። ይኸም ፡ በእርግጥበሥራ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይተው ፡ ሔደው ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ጸሐፊው ፡ የፊቱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ኣዘዋውሮት ፡ ይሁን ፡ በግልጽ ፡ አይታወቅም። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዋናው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ የጽሑፉ ፡ መገኘት ፡ እንጂ ፡ የጽሑፉ ፡ መዘዋወር ፡ ቍም ፡ ነገር ፡ የለውምና ፡ ኣሁን ፡ ወደ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጽሑፍ ፡ ከመግባታችን ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ታሪክ ፡ ገብተን ፡ በምናነብበት ፡ ጊዜ ፡ የግራ ፡ ባልቲሐት ፡ የቀኝ ፡ ባልቲሐት (የቀኝ ፡ ባለ ፡ ቤት ፡ የግራ ፡ ባለ ፡ ቤት፱) ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ጽራግ ፡ ማሰሬ ፡ የሚላው ፡ ቃል ፡ ሲገጥመን ፡ ጉዳዩ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ እንዲታይ ፡ ከዚህ ፡ በሚቀጥለው ፡ ምዕራፍ ፡ በሥርዓተ ፡ መንግሥታችን ፡ በታሪክ ፡ ነገሥታችንና ፡ ከዚያምናምንጭ ፡ እያገኙ ፡ የጻፉትን ፡ የአላቃ ፡ ታዬን ፡ .......መጽሐፍ ፡ መሠረት ፡ ኣድርገን ፡ ስለሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ከዚያም ፡

ተከታትሎ ፡ ስለ ፡ ቤተመንግሥት ፡ ሥርዓትና ፡ ወግ ፡ የተጻፈውን ፡ በሚቀጥለው ፡ እንመልከት።

# ምዕራፍ ፡ ፳፲

## ሥርዓተ ፡ ንግሥ––የሹማምንት ፡ የማዕርግ ፡ ስምና ፡ ደረጃ።

በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚያገለግሉትን ፡ የቤተ ፡ ክህነትና ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የደረጃቸውንና ፡ የተግባራቸውን ፡ ዓይነት ፡ በመጠኑ ፡ የሚገልጽልን ፡ ያገራችን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ነው። ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ እንዳላ ፡ ግዕዝኛው ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ኣማርኛ ፡ ተተርጉሞ ፡ ባገራችን ፡ ያልታተመና ፡ የቀኍም ፡ ነገሩመጠን ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ያልታወቀና ፡ ያልተገመተ ፡ ስለሆነ ፡ በየሥፍራው ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ በገዳም ፡ የሚገኘው ፡ በየጊዜው ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ በብራና ፡ ወይም ፡ በወረቀት ፡ የተቀዳው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው።

ከዚያ ፡ ፈረንጆቹ ፡ እነዲልማን ፡ እነባሴት ፡ ረኔ ፡ ግዕዙን ፡ ወደ ፡ ጀርመንና ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ እየተረጐሙ ፡ በምልክት ፡ ለማብራራት ፡ ሞክረዋል። ፈረንጅ ፡ ምንም ፡ ግዕዝና ፡ አማርኛ ፡ ተምሮ ፡ ቢያውቅ ፡ እንደ ፡ ኣንድ ፡ ግዕዝና ፡ አማርኛ ፡ ኣዋቂ ፡ ኢትዮጵያዊያህል ፡ የቃሉን ፡ ድምፅ ፡ የንግግሩንም ፡ ስሜት ፡ መረዳት ፡ ያዳግተዋል። እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ላኢትዮጵያዊ ፡ ጸሐፊ ፡ የተጨፈነውን ፡ የአገር ፡ ካርታን ፡ የውጭን ፡ ግንኙነት ፡ ጕዳይ ፡ ማብራራት ፡ ይሆንላቸዋል። ስለዚህ ፡ ባሁኑም ፡ በሚቀጥለውም ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ እስከተቻለኝ፤ላገናዝብ ፡ የሞከርሁት ፡ ከሁለቱ ፡ የጽሑፍ ፡ አውድማ ፡ ለዛሬው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኝ ፡ የታሪክ ፡ ጽሑፍ ፡ ለማስገኘት ፡ ሲሆን ፡ ለዚህ ፡ ለሥርዓተ ፡ ንግሥና ፡ ለቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡ መርጨዋ ፡ መሠረት ፡ የማዳርገው ፡ ያገራችን ፡ ሥርዓተ ፡ መንግሥት ፡ የሚባለውና ፡ ከዚያም ፡ <u>ደጃዝማች ፡ ኃይሉ ፡ እሸቴ ፡ ግራኝ ፡ ከአጠፋው ፡ ወዲህ ፡ ከየደሴቱ</u>

፡ አጠራቅመው ፡ ያዘጋጁትን ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ቀጥሎ ፡ አለቃ ፡ ታዬ ፡ የጻፉትን ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው። በነዚህና ፡ በሌላው ፡ ሁሉ ፡ በየመጠኑ ፡ የተጻፈው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ እንደሚለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ (፮፻ኛ ፡ ዓ.ም) ሥርዓተ ፡ ንግው ፡ ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ባመጣው ፡ በኦሪት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ነበር። በኋላ ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ ዓፄ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ የኦሪቱን ፡ ሥርዓት ፡ ለውጦ ፡ በአክሱም ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ክርስትና ፡ ሥርዓት ፡ ሕዝብ (ወይስ ፡ ሕፃናት) የሰሌን ፡ ቅጠል ፡ ይዘው ፡ ካህናቱ (ቀሳውስቱ ፡ መስቀልና ፡ ጥና ፡ ይዘው ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙር ፡ የ፲፯ኛውን ፡ ቊጥር ፡ ቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡ **እግዚአብሔር**... የሚለውን ፡ እየዘመሩ ፡ ይዞራሉ። ሌላም ፡ ስለንግሥና ፡ ስለ ፡ ክህነት ፡ የሚናገረውንቃል ፡ ከኦሪትም ፡ ከነቢያትም ፡ ከሐዲስም ፡ እየመረጡ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ በድግምትም ፡ በዜማም ፡ ይጸልያሉ። የንጉሡ ፡ ዝፋን ፡ ከቅኔ ፡ ማኅሌት ፡ ገብቶ ፡ ይዘረጋል ፡ ሽቱ ፤ ኣበባ ፡ ይነሰነሳል። ከንጉሡም ፡ ፊት ፡ ኣንበሳና ፡ ጐሽ ፡ ይታሠሩና ፡ አንበሳው ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ ይገደላል ፤ የቀሩት ፡ እንስሶች ፡ ግን ፡ ኣይገደሉም። ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሲገባ ፡ ወርቅ ፡ ዘግኖ ፡ ይበትናል ፡ ምንጣፍ ፡ ተነጥፎ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ይቀመጥና ፡ ሁለት ፡ የወርቅ ፡ ፪ ፡ የብር ፡ ጻሕል ፡ ባንዱ ፡ ወተት ፡ ባንዱ ፡ ጠጅ ፡ ባንደኛው ፡ ወይን ፡ አምጥተው ፡ የንጉሡን ፡ ራስ ፡ እየቀቡ ፡ የዮርዳኖስንም ፡ ጠበል ፡ ይረጩታል። የራሱን ፡ ጠጉር ፡ ቆርጠው ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ ከጥና ፡ ጋር ፡ ወስደው ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ታቦቱን ፡ ይዞሩና ፡ መልሰው ፡ አምጥተው ፡ የነገሥታት ፡ መማፀኛ ፡ ደንጊያ ፡ በሚባለው ፡ ላይ ፡ ያስቀምጡና ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ከጽናው ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የሳት ፡ ፍሕም ፡ አፍስሰው ፡ ንጉሡን ፡ **እግዚአብሔር** ፡ አይለይህ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ትርዳህ .... ትርዳህ ፡ ብለው ፡ አማፅነው ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ያንግሥህ ፡ ብለው ፡ ሲመርቊትና ፡ ከዚያ ፡ እምቢልታ ፡ ነጋሪት ፡ መመታት ፡ ሲዝምር ፡ ግርግሩና ፡ እልልታው ፡ ይቀልጣል። ቀጥሎ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፡ ሰውነቱን ፡ ያማጽናል።

ከዚያ ፡ ይወጣና ፡ ዛሬም ፡ ግማሾቹበአክሱም ፡ እንደሚታዩት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች (ዳኞች) በሚቀመጡበት ፡ ፲፪ ፡ የደንጊያ ፡ ወንበር ፡ በሚባለው ፡ ፮ቱን ፡ በቀኝ ፡ ፮ቱን ፡ በግራ ፡ አድርጎ ፡ በመካከል ፡ ይቆማል ፡ በዚያ ፡ ሳለ ፡ ጳጳስ ፡ ቀሳውስት ፡ ካህናት ፡ ዲያቆናት ፡ እፊቱ ፡ እየመጡ ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ ያንግሥህ ፡ ይሉታል ፡ ፤

የተተከለ ፡ ደንጊያ ፡ ባለበት (ምዕራፍ)በምሥራቅ ፡ በኵል ፡ ወደ ፡ ኣክሱም ፡ ሲመጣ ፡ ሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ሹማምንት ፡ ሠራዊት ፡ በየወገናቸው ፡ ሆነው ፡ ይቀበሉታል። ደናግል ፡ ሴቶች ፡ የቀይ ፡ ሐር ፡ መጋረጃ ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ይዘው ፡ መንገዱን ፡ ይዘጉበታል። ከልጃገረዶቹ ፡ አንዲቱ ፡ አንተ ፡ ማነህብላ ፡ ትጠይቀዋለች። እሱም ፡ ንጉሥ ፡ ነኝይላታል ፡ «አይደለህምትልና ፡ እንደገና ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ ብላ ፡ ስትጠይቀው ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡ ይላታል ፡ ጥያቄውና ፡ መልሱ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ከተደጋገመ ፡ በኋላ ፡ በ፫ኛው ፡ ኣንተ ፡ ማነህ ፡ ስትለው ፡ ሰይፉን ፡ መዞ ፡ የሐሩን ፡ መጋረጃ ፡ ይቆርጠውና ፡ የጽዮን ፡ ንጉሥ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ይላታል። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የጽዮን ፡ ንጉሥ ፡ እውነት ፡ በእውነት (አማን ፡ በአማን) ስትለው ፡ ሕዝቡም ፡ እርሷን ፡ ተከትሎ ፡ የጽዮን ፡ ንጉሥ.... ይለዋል።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ወርቅ ፡ ዘግኖ ፡ ይበትናል ፡ በዕቃ ፡ ቤት ፡ ያሉ ፡ ባለሕጎች ፡ | ፡ ወርቊን ፡ ከወሰዱና ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ላቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ የሚሆን ፡ እንደገና ፡ ዘግኖ ፡ ይበትናል።

ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ ዓፄ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ በዘመናቸው ፡ የደነገጉት ፡ ነው ፡ ይባላል። ደግሞ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በዘመናቸው ፡ ኣሻሽለውና ፡ የአወጡትና ፡ ባፄ ፡ ኢያሱ ፡ ኣድያም ፡ ሰገድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ታደሰ ፡ የሚባለው ፡ ቅብዓ ፡ ቅዱስን ፡ ሌላም ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡ ይጨምራል።

፲፯ ፡ ኣፈዋተ ፡ መንግሥት ፡ የተባሉትን ፡ በሎሚ ፡ ወሀ ፡ ለውሰው ፡ ቅባ ፡ ቅዱስ ፡ ጨምረው ፡ ያኖሩታል። ፲፯ ፡ ኣፈዋተ ፡ መንግሥት ፡ የሚባሉትም ፡ በአለቃ ፡ ታዬ ፡ መጽሐፍ ፡ በእጁ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተዘረዘረው

## ፲፯ ፡ ኣፈዋተ ፡ መንግሥት

| | በግዕዝ ፡ | በአማርኛ ፡ |
|---|---|---|
| ፩ | ከርቤ ፡ | ከርቤ ፡ |
| ፪ | ጵስጥቂስ | ኮረሪማ ፡ |
| ፫ | ርኄ ፡ | ኣሸቲ ፡ ጥቍር ፡ አርያን ፡ |
| ፬ | ቀጺመት ፡ | ናትሪ ፡ ነጭ ፡ አርያን ፡ |
| ፭ | ቀንዓት ፡ | ቀርንፉል ፡ |
| ፮ | ሰሊሆት ፡ | ሰንደል ፡ |
| ፯ | ሰሊክ ፡ | ሰንቡል ፡ |
| ፰ | ቀንሞስ ፡ | የጠንበለል ፡ ኣበባ ፡ |
| ፱ | ቀናንሞስ ፡ | የቀጋ ፡ ኣበባ ፡ |
| ፲ | መጽርይ ፡ | ጽጌ ፡ ረዳ |
| ፲፩ | ኣለው ፡ | የወይራ ፡ አበባ ፡ |
| ፲፪ | ዕንጕታት ፡ | የትርንጎ ፡ አበባ ፡ |
| ፲፫ | ናርዶስ ፡ | የዶግ ፡ ኣበባ |
| ፲፬ | ሱቃጢስ ፡ ሳጡቃጢስ ፡ | የደንጋ ፡ አበባ ፡ |
| ፲፭ | ኮል | የንኮይ ፡ ኣበባ |
| ፲፮ | ሚገ ፡ | ሎሚ ፡ |
| ፲፯ | ማየ ፡ ልብን ፡ | የሎሚ ፡ ወሀ ፡ |

እነዚህን፡፲፯ቱን፡ቅብዓ፡መንግሥት፡የሚባሉትን፡ሽቶዎች (ኣፈዋተ፡ መንግሥት) የሚገኙትን ፡ ያህል ፡ ሰባቱንም ፡ አሥሩንም ፡ ቢያደርጉ ፡ ይሆናል ፡ ይባላል።

ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ከሚፈስ ፡ ወሀ ፡ በመንቀል ፡ አምጥቶ ፡ ፯ ፡ ቆቀር (ስባሪ) ዕጣን ፡ ጨምሮ ፡ ሲሆን ፡ ፲፪ ፡ ሳይሆን ፡ ፯ ፡ መነኰሳት ፡ ፳፩ኛውን ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር-ከነቢያት ፡ ፯ቱን ፤ መሐልየ ፡ ሰሎሞንን ፡ ፭ቱን ፤ ውዳሴ ፡ ማርያም ፡ ከነ ፡ ኣንቀጸ ፡ ብርሃኑ ፡ ከመልክዓ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋር ፡ ፯ ፡ ሱባዔ (ሳምንት) ይጸልዩበታል። በፊተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በወሀ ፡ ይታጠባልንው?) በ፪ኛው ፡ ሱባዔ ፡ ዕጣን ፡ ያጥናል፣በ፫ኛው ፡ ይቀባል።

ንጉሥ ፡ የሚነግሠው ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ነው። ካህናቱ ፡ መወድስ ፡ እያደረሱ ፡ ጐሥዓ ፡ ልብየ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ይሔዳሉ...ንጉሡም ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ንዑስ ፡ አነ ፡ እምአኀውየ ፡ ከሚለው ፡ ጀምሮ ፡ ወቀብዓኒ ፡ ቅብዓ ፡ ቅዱሰ ፡ እስከሚለው ፡ ድረስ ፡ ይደግማል ፡ ካህናቱም ፡ ተክአወ ፡ ሞገስ ፡ እምከናፍሪከ ፡ ይሉና ፡ ቅንት ፡ ሰይፈከ ፡ ኃያል ፡ ውስተ ፡ ሐቌከ ፡ እያሉ ፡ ባለወርቅ ፡ ሰገባ ፡ ሰይፍ ፡ ያስታጥቍታል። ንጉሡም ፡ ሲነሣ ፡ አርትዕ ፡ ተሠራህ ፡ ወንገሥ ፡ ይሉና ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያ ፡ ይገባሉ። ንጉሡም ፡ በዝሆን ፡ ጥርስ ፡ ወንበር ፡ ይቀመጣል ፤ የወርቅ ፡ ውይም ፡ የብር ፡ ዘንግ ፡ ይመረኰዛል። የአራቱን ፡ እንስሳ ፡ ልብስ ፡ ይለብሳል። ካህናቱ ፡ መንበርከ ፡ እግዚኦ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ከርቤ ፡ ወቀዓት። .... እሚሰው ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ ዲያቆኑ ፡ ወዐልዐልኩ ፡ ኅሩይየ ፡ እምህዝብየ ፡ ይላል ፡ እጨጌው ፡ ከሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ ብእሲ ፡ ክቡር ፡ የሚለውን ፡ ሲያነቡ ፡ ጳጳሱ ፡ በእንተዝ ፡ ቀብዓከ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ኣምላክከ ፡ ብለው ፡ ቅባዓ ፡ መንግሥት ፡ ይቀቡታል።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቅዳሴ ፡ ይገቡና ፡ በወንጌል ፡ ጊዜ ፡ ምስባክ ፡ እስመ ፡ ጻሕኮ ፡ በበረከት ፡ ሠናይ.... ይባላል። ከሉቃስ ፡ ወይም ፡ ከማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ይነበባል ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዕራቅ ፡ ማሠሬ (ጽራግ- ፡ ጽራጅ ፡ ማሰሪያ ፡ ዘውዱን ፡ በንጉሡ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያስቀምጣል። ምልጣን ፡ በመንፈስ ፡ የጸውር ፤ መዝሙር ፡ ምፅዋድ ፡ ኣልቦ ፡ ዘየዓቢ ፡ ይባላል።

ከቅዳሴ ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጥቶ ፡ ከግቢው ፡ ይመጣል። ዕራቅ ፡ ማሠሬው ፡ ተፈሥሑ ፡ ሲል ፤ ካህናት ፡ ተፈሣሕነ ፡ ወተፈሠይነ ፡ ይላሉ። የብቡ ፡ ለአምላከ ፡ እገሌ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱ ፡ ንሴብሖ ፡ ይላሉ። ቀጥሎ ፡ እጨጌው ፡ ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ጸሎት ፡ ያደርጋሉ ፡ ጳጳሱም ፡ በረከተ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ወቴዎዶስዮስ ፡ ይደርብህ ፡ ሲሉ ፡ እጨጌው ፡ ባገራቸው (በኢትዮጵያ)ጻድቃን ፡ ነገሥታት ፡ ስም ፡ ይባርኵትና ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ንጉሥ ፡ ሕያው ፡ ሁን ፡ እያሉ ፡ ይመርቁኋታል።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያዋጅ ፡ ነጋሪው ፡ ቃል ፡ ንሥኡ ፡ መዝሙረ ፡ ወሀቡ ፡ ከበረ ፡ እስመ ፡ ሥርዓቱ ፡ ለእስራኤል ፡ ውእቱ ፡ እስከሚለው ፡ ድረስ ፡ ያንብቡ ፡ ይላል። ንጉሡ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ በበቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደቤቱ ፡ ይሔዳል ፡ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ በየሥፍራቸው ፡ ተሰልፈው ፡ ደስታቸውን ፡ በዘፈንና ፡ በጩኸት ፡ በእልልታ ፡ ይገልጹለታል። ሊጋባ ፡ በፊቱ ፡ እየሔደ ፡ ይመራል ፡ ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ነጋሪት ፡ መችዎች ፡ ከነርሱ ፡ ኋላ ፡ ፴ቱ ፡ ኣዛዦች ፡ እየተጓዙ ፡ ታላቅ ፡ የከበረ ፡ በዓል ፡ ይደረጋል... ባራተኛው ፡ ቀን ፡ ሊቀ ፡ ማእምራኑ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ወንጌል ፡ እየተረጐመ ፡ ያሰማል።

ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈው ፡ እንደሚያመለክተን ፡ ንጉሡ ፡ በነገሡበት ፡ ቀን ፡ ጳጳሱም ፡ ንጉሡምዕራቅ ፡ ማሰሬውም ፡ እየተቀባበሉ ፡ የሚደግሙት ፡ ወይም ፡ የሚጸልዩበት ፡ ቃል ፡ በዳዊት ፡ መዝሙር ፡ በሌላውም ፡ ቅዱስመጽሐፍ ፡ ውስጥበየሥፍራው ፡ የሚገኘውን ፡ ስለንጉሥና ፡ ስለ ፡ ኣነጋገሥ ፡ የሚናገረውን ፡ ቃል ፡ እየመረጡ ፡ የየዘመኑ ፡ ሊቃውንት ፡ የመደቡትን ፡ ነው። ከዚህም ፡ ጋር ፡ የምንመለከተው ፡ ዕራቅ ፡ ማሰሬ ፡ እንደግማሾቹ ፡ ጽራግ ፡ ወይም ፡ ጽራጅ ፡ ማሰሬ ፡ በንግሥ ፡ ቀን ፡ ዘውዱን ፡ በንጉሡ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የመድፋት ፡ መብት ፡ የነበረውን ፡ ነው። ስለዚህም ፡ ይህ ፡ መብቱ ፡ የተከበረና ፡ ባለማዕርግ ፡ እንዳደረገው ፡ እንረዳለን።

ወደ ፡ ፊት ፡ በምናነባቸው ፡ ምዕራፎች ፡ ውስጥ ፡ በዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፤ ባፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ በሌሎቹም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ውስጥ ፡ የንጉሡን ፡ አነጋገሥ ፤ በየጒዳዩ ፡ እየገቡ ፡ የሚጠሩትንም ፡ ያንዳንድ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ስም ፡ እናገኛለን። የንጉሡ ፡ አነጋገሥ ፡ የቀድሞው ፡ ባፄ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ከዚያም

፡ ወዲህ ፡ በዛጕዬዎችም ፡ ባዬ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንም ፡ ባዬ ፡ ዳዊትና ፡ ባዬ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ ጊዜ ፡ ወጕና ፡ ሥርዓቱ ፡ እየተጨመረ ፡ እንደተሻሻለ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱና ፡ የቤተክህነቱም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የማዕርግ ፡ ስማቸው ፡ በየጊዜው ፡ አዳዲስ ፡ እየተጨመረ ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ አኳኋን ፡ ተሟልቷል።

<u>በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጡትና ፡ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ተጠሩበት ፡ የሚባለው ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ቀጥሎ ፡ እንዳለው ፡ ነው።</u>

**፩ኛ ፡** –<u>ራቅ ፡ ማሰሬ</u>–የርሱም ፡ ዋና ፡ ተግባር ፡ ባለፈው ፡ እንደተመለከትነው ፡ ንጉሡ ፡ በነገሠ ፡ ቀን ፡ ዘውድ ፡ ደፊ ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ በሌላው ፡ ቀን ፡ ያገረ ፡ ገዥነት ፡ የግብር ፡ ማስገባት ፡ የመፍረድም ፡ ነዋሪ ፡ ሥራ ፡ እንዳለው ፡ የታወቀ ፡ ነው።

**፪ኛ ፡** –<u>ቀለብሳ</u>–የሚያቀርብ ፡ ደረባ ፡ ቤት ፡ የሥራ ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ አዛዥ ፡ እንደማለት ፡ ነው።

**፫ኛ ፡** –<u>ሊቀ. ሳፍ</u> ፡ (ባልደራስ)

**፬ኛ** ፡ —-<u>ሠርጓይ ፡ ዳርስጌ</u> (ቢት ፡ ወደድ)

**፭ኛ ፡** –<u>በስተግራ</u> (የእስር ፡ ቤት ፡ አለቃ)

**፮ኛ ፡** –<u>ደቀ ፡ ሠርጓይ</u> ፡ ባለምሥር ፡ ቃና ፡ የእምቢልተኞችና ፡ የመለከተኞች ፡ አለቃ።

**፯ኛ ፡** –<u>ሊቀ ፡ ዲያቆናት</u> ፡ (የታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ጠባቂ)

**፰ኛ ፡** –ሊቀ ፡ መጣኒ ፡ (የሚፈርድ ፡ ዳኛ) ኣንዳንዱ ፡ ጽሑፍ ፡ ሊቀ ፡ መጫኒ-ሊቀ ፡ መጽአኒ-ሊቀ ፡ መጣን-ሊቀ ፡ መጣኖች ፡ እያለ ፡ እየለያየ ፡ ግማሹ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ግማሹ ፡ ወደግዕዝ ፡ እየወሰደ ፡ ይጠራዋል።

**፱ነኛ ፡** –ንጕሥ ፡ ሕዝባይ ፡ ሥጋ ፡ መልከኛ ፡ ነጋሪት ፡ አስሞች)

**፲ኛ ፡** –ደልከሚ ፡ ደጃዝማች)

**፲፩ኛ ፡** –ምጓ (ወንጀለኛ ፡ የሚቀጣ ፡ የሚቆርጥ ፡ የሚሰቅል ፡ ...)

**፲፪ኛ ፡** –ሐስጓ (ቢት ፡ ወደድ ፡ ዙፋን ፡ ቤት?)

ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ ታሪካቸውን ፡ ባለፈው ፡ በምዕራፍ ፡ ፳ና ፡ ፳፩ ባነበብነው ፡ ባፄ ፡ ዳዊት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በዘመናቸው ፡ እስላም ፡ በረታ ፡ ክርስቲያን ፡ ደከመ ፡ ሃይማኖት ፡ ጠፋ ፡ የሚል ፡ መልእክት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ቢመጣባቸው ፡ ለጉዞ ፡ መንገድ ፡ሲዝምሩ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ አዲስ ፡ ሹመት ፡ ጨመሩ።

**፩ኛ ፡** –ፊት ፡ አውራሪ (ቀድሞ ፡ የሚጓዝ)

**፪ኛ ፡** –ቀኛዝማች (በቀኝ ፡ ለሚዘምተው ፡ ወይም ፡ ለሚጓዘው ፡ ጦር ፡ አለቃ)

**፫ኛ ፡** –ግራዝማች (በግራ ፡ በኵል)

**፬ኛ ፡** -ደጃዝማች (ደጃን ፡ አዝማች ፡ እኋላ ፡ ላለው ፡ ለደጃን ፡ ጦር ፡ መሪ)

**፭ኛ ፡** –በጅሮንድ (በጅሮ ፡ ወእድ-በጅሮና ፡ በእጅ?) የመንግሥትን ፡ ምስጢር ፡ በጅሮ ፡ ነጋሪ ፡ የግምጃ ፡ ቤት ፡ ቍልፍ ፡ መክፈቻ ፡ ያዥ ፡ ስለሆነ ፡ በጅሮ ፡ ወእድ ፡ ተብሎ ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ ቃሉ ፡ ወደ ፡ በጅሮንድነት ፡ የተለወጠ።

**፮ኛ ፡** –ባላምባራስ (ባለኣምበል ፡ ራስ—ኣምባ ፡ ጠባቂ)

**፯ኛ ፡** –ከንቲባ (ካንት ፡ ይባዕ?)

**፰ኛ ፡** –ነጋድራስ (ነጋ ፡ ድረስ?)

**፱ነኛ ፡** –ባልደራስ (ባለህ ፡ ድረስ?)

ከዓፄ ፡ ዳዊት ፡ ወዲህ ፡ በኣሁኑ ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ ተጨመሩ።

**፩ኛ ፡** –ሊቀ ፡ መኳስ (ልቀም ፡ ኳሱሊቀ ፡ መነኵስ) ይኸ ፡ ሥያሜ ፡ በዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ ላይ ፡ የለም።

**፪ኛ ፡** –ብላቴን ፡ ጌታ (የብላቴኖች-የቤት ፡ ልጆች ፡ ኣለቃ)

**፫ኛ ፡** –አጋፋሪ (ኣደግ (የኵሬ ፡ ወሀ) አይፈሪ?)

**፬ኛ ፡** –ሊጋባ (ንጉሥ ፡ ሊገባ-ወይም ፡ ሊያገባ)

**፭ኛ ፡** –ብሕት ፡ ወደድ (በንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ብቻውን ፡ የሚወደድ ፡ የካበረ ፡ ባለሟል)

**፮ኛ ፡** –ኳደሪ (ከዳሪ ፡ ተገኝ?)

**፯ኛ ፡** –<u>ጭቃ</u> (ምድር ፡ የሚለይ)

**፰ኛ ፡** –<u>ገበዝ (</u>ጐበዝ))

**፱ነኛ ፡** –<u>መኰንነ</u> ፡ <u>፲፻</u> (የሺ ፡ አለቃ)

**፲ኛ ፡** –መኰንነ ፡ ፶ (የ፶ ፡ አለቃ)

**፲፩ኛ ፡** –መኰንነ ፡ ፻ (የመቶ ፡ አለቃ)

ነገር ፡ ግን ፡ ሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ "የወርቅ ፡ ወንጌል ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ባሳተሙት ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ባፄ ፡ ላሊበላ ፡ ባፄ ፡ ይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ ባፄ ፡ ዓምደጽዮን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉት ፡ እንደነበሩ ፡ ይገልጻሉ።

ማዕከለ ፡ ባሕር (በኋላ ፡ መልአከ ፡ ባሕር ፡ ወይም ፡ ባሕር ፡ ነጋሢ (ነጋሽ)
ሥዩመ ፡ እንተርታ (የእንደርታ ፡ ሹም?)

ሐስጓ ፡

ኣቃንጻን (አቃጽን ፡ ኣቃጸን)

ማዕከለ ፡ ትዋዛት ፡

ሕዱግ ፡ ኣምባ ፡

ሊቀ ፡ ኅዳር ፡

ሊቀ ፡ አቀይታት።

*ዡፊል፣ ፡ ፔሩሾ ፡* በማኅተም ፡ ያሳተሙትን ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ስናነብ ፡ ከነዚህ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ የማዕርግ ፡ ስሞች ፡ ግማሾቹን ፡ ሲጠራ ፡ ግማሾቹን ፡ ሲተው ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ የሌሉ ፡ ቀይስ ፡ ሐፄ ፡ ሊቀ ፡ ቃቄታት ፤ ሊቀ ፡ ደብተራ፣ ፡ ኅበርት ፡ ቤትቃለ ፡ ሐፄ፡…. የሚባሉት ፡ ይገኛሉ። በዚህ ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ የተመለከቱት ፡ ግራዝማችና ፡ ቀኛዝማች ፤ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ኣጋፋሪ ፡ ሊጋባ ፡ ኣይገኙምና ፡ በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የሚገኙትን ፡ የሹመት ፡ ደረጃዎች ፡ ወደፊት ፡ ከዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ላይ ፡ እንመለከታለን። ዜና ፡ መዋዕሉም ፡ የሚጽፈው ፡ ከሙሉው ፡ በከፊል ፡ ከከፊልም ፡ ያነሰ ፡ ስለሆነ ፡ ስማቸው ፡ በዜና ፡ መዋዕል ፡ ከሌለ ፡ የሹመቱ ፡ ደረጃ ፡ ባይኖር ፡ ነው ፡ ሊያሰኝ ፡ አይችልም። በሌላ ፡ ቦታ ፡ ደግሞ ፡ ደረጃቸው

፡ ይኸውም ፡ ቅደም ፡ ተከተላቸውን ፡ በሚዘረዝርበት ፡ ክፍል ፡ ስማቸውን ፡ እየሞላ ፡ ያመጣዋል። ነገር ፡ ግን ፡ ይኸንኑ ፡ የሚናገረው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ የሰበሰቡትም ፡ ሌላውም ፡ በጐንደር ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ የተጻፈ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም።

እርሱም ፡ ሲዠምር ፡ ከእገሌ ፡ ቀጥሎ ፡ እገሌ ፡ ይመከራል ፡ ስለሚል ፡ ይመከራል ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ በፍርድም ፡ በጒዞም ፡ በግብርም ፡ ጊዜ ፡ ደረጃቸውን ፡ ለማሣየት ፡ ሲሞክር ፡ ነውና ፡ ቃሉን ፡ እነሆ ፡ እንስማ።

ከሁሉ ፡ በፊት ፡ የአዳል ፡ ጭፍራ ፡ የሻለቃ ፡ ይመከራል ፡ ከርሱ ፡ በላይ ፡

፩ኛ ፡ ደጅ ፡ አማካሪ ፡ ይመከራል (ይፈርዳል)
፪ኛ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ፡ » » »
፫ኛ ፡ ባላምባራስ፡ » » »
፬ኛ ፡ በጅሮንድ ፡ ዘዙፋን ፡ ቤት ፡ » » »
፭ኛ ፡ ዙፋን ፡ መከዳ ፡ የሚገባው ፡ ነጋድራስ » »
፮ኛ ፡ ፊታውራሪ፡ » » »
፯ኛ ፡ ግራዝማች፡ » » »
፰ኛ ፡ ቀኛዝማች፡ » »
፱ነኛ ፡ ጥቃቅን ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ » » »
፲ኛ ፡ ዣንደረባ ፡ አዛዥ፡ » » »
፲፩ኛ ፡ ጠረስምባ ፡ አዛዥ፡ » » »
፲፪ኛ ፡ አራቱ ፡ አዛገሮቹ፡ » » »
፲፫ኛ ፡ ሁለቱ ፡ ጸሐፍተ ፡ ትእዛዝ፡ » » »
፲፬ኛ ፡ ውስጥ ፡ አዛዥ » » »
፲፭ኛ ፡ አዛዥ » » »
፲፮ኛ ፡ ባሻ (ደጃዝማች ፡ ነውና) » » »
፲፯ኛ ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ የዳሞት ፡ በጨዋነት ፡ ከሁሉ ፡ ስለሚቀድም» »
፲፰ኛ ፡ ጐዣም ፡ ነጋሽ ፡ ያለቆች ፡ አለቃ ፡ ስለሆነ » »

፲፱ነኛ ፡ ቤገምድር ፡ ላዝማች ፡ እሱ ፡ የወርወር ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ስለሆነ፡ »
፳ኛ ፡ ስሜን ፡ አጋፋሪ ፡ ላድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ከመንግሥታቸው ፡ በፊት ፡ ይኸን ፡ ሹመት ፡ ይዘውት ፡ ስለነበረ ፡
፳፩ኛ ፡ ትግሬ ፡ መኰንን ፡ ያነሱም ፡ ንቡረ ፡ ዕድ ፡ ስለሆነ። » »
፳፪ኛ ፡ ታላቅ ፡ ብላቴን ፡ ጌታ። » » »
፳፫ኛ ፡ ራስ ፡ ቢትወደድ። » » »
፳፬ኛ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት። » » »
፳፭ኛ ፡ በመጨረሻ ፡ ንጉሥ ፡ በሚወስነው ፡ ፍጻሜ ፡ ይሆናል፡» » »

በነዚህ ፡ መካከል ፡ ጽራጅ (ጽራግ)ወይም ፡ ዕራቅ ፡ ማሰሬው ፡ አለመግባቱን ፡ እንመለከታለን። በ፲፪ኛው ፡ ቍጥር ፡ አራቱ ፡ አዛዦች ፡ የሚላቸው ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፤ ቄስ ፡ ሐፄ ፤ ሊቀ ፡ ደብተራ ፤ ሊቀ ፡ ማዕምራን ፡ መሆናቸውን ፡ ይገልጻል። በሌላ ፡ ቦታ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ አራት ፡ አዛዦች ፡ ሊቀ ፡ መጣኒዎች ፡ ወይም ፡ ቃቤታቶች ፡ ሲላቸው ፡ ይገኛል። እነዚህም ፡ ሁሉ ፡ በአደባባይ ፡ ተቀምጠው ፡ ፍርድ ፡ የሚሰጡ ፡ ናቸው።

ከዓፄ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ በፊት (፯ኛ ፡ መቶ ፡ ዓ.ም) ከሌዋውያን ፡ ዘር ፡ ፈራጅ ፡ የነበሩት ፡ ፪ ፡ ሊቃውንት ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ፡ ይባላል። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ ፲፬ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ.ም) ሁለት ፡ ሊቃውንት ፡ ተጨመሩ ፤ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን ፡ በአራቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በሮማ ፡ በእስክንድርያ ፤ በአንጾኪያ፣ ፡ በቍስጥንጥንያ) ላምሳል ፡ ላራት ፡ ሊኮ ፡ መጣኖች (ዳኞች)በአራት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ አምሳል ፡ አራት ፡ አዛዦች ፡ ተጨምረው ፡ በድምሩ ፡ ስምንት ፡ ፈራጆችና ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ እንደ ፡ ተመደቡ ፡ የነርሱም ፡ ምርጫ ፡ ከዚያው ፡ ከነገደ ፡ ሌዊ (እስራኤል)ውስጥ ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ በግዝት ፡ እንዳጸኑላቸው ፤ ገበታቸውም ፡ ከመንበሩ ፡ ከንጉሡ ፡ መቀመጫ)ግርጌ ፡ እንደሆነ ፡ ከነርሱም ፡ በላይ ፡ የግራና ፡ የቀኙ ፡ ሁለቱ ፡ ቢትወደዶች ፡ ብቻ ፡ መሆናቸውን ፡ ይገልጻል። ነገር ፡ ግን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ይኸንን ፡ ሲል ፡ ከጳጳሱ ፡ ከእጨጌው ፡ ከዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ በቀር ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከንጉሡ ፡ ከንግሥቲቱ ፡ ከጳጳሱ ፡ ቀጥሎ ፡ የማዕርጉ ፡ ተራ ፡

ለእጨጌው ፡ ከዚያም ፡ ለዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ መሆኑ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ወደፊት ፡ እናገኛለን። የቀረው ፡ ስለጕዞ ፤ ስለማዕርግ ፡ ልብስ ፤ በታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ቀድሞውንም ፡ ባይፋ ፡ አብዛኛው ፡ በታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚገኘው ፡ በጐንደር ፡ መንግሥት ፡ ግማሹ ፡ በነዓፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ ግማሹ ፡ ባፄ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ጊዜ ፡ የተዘጋጀ ፡ ስለሆነ ፡ በኣሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ለመጻፍ ፡ የፊቱን ፡ ወደ ፡ ኋል። ምጣት ፡ እንዳይሆን ፡ ትተነዋል።

# ምዕራፍ ፡ ፳፫።

## ስለ ፡ እቴጌዪቱ ፡ ሥርዓተን ፡ ግሥ።

ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ሁለት ፡ የግራና ፡ የቀኝ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ሁለት ፡ ጸሐፍተ ፡ ትእዛዛት ፤ ኣራት ፡ አዛዦች (ፈራጆች) መኖራቸውን ፡ ሲገልጹልን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ነገሥታቱ ፡ ሁለት ፡ ሚስቶች ፡ በይፋ ፡ ያገቡ ፡ ደነበረ ፡ አይገልጽልንም። ምናልባት ፡ እኔ ፡ ያልተመለከትሁት ፡ ሌላ ፡ ገዳምና ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ይገኝ ፡ እንደሆነ ፡ አላረጋግጥም። በአከሱሞች ፡ ዘንድ ፡ ስለሚስት ፡ ወይም ፡ ስለእቴጌዪቱ ፡ አንዲት ፡ ብቻ ፡ መሆኗ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ መሆናቸውን ፡ የሚናገር ፡ ታሪከ ፡ የለም። እንኳን ፡ የሚስቶቻውን ፡ ከዒዛና (አብርሃ)ከካሌብ ፡ በቀር ፡ የነገሥታቱን ፡ የራሳቸውን ፡ ታሪከ ፡ እንንኳን ፡ ማግኘት ፡ አልተቻለም። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ በዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ታሪከ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ታላቂቱ ፡ ንግሥት ፡ ታናሺቱ ፡ ንግሥት ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ ሚስቶች ፡ ላፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንደነበሩት ፡ አንብበናል። ወደ ፡ ፊት ፡ እንደምንመለከተው ፡ የግራ ፡ ባለቤት ፡ የቀኝ ፡ ባለቤት ፡ የሚባሉ ፡ ደግሞ ፡ ላዔ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ ለልጃቸው ፡ ለዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምም ፡ ፪ ፡ ሚስቶች ፡ እንደነበሩዋቸው ፡ ግልጽ ፡ ነው።

ስለዚህ ፡ የዚህን ፡ ጕዳይ ፡ ኣልፈን ፡ አሁን ፡ እነዚሁ ፡ ንግሥታት ፡ የሚነግሡበትን ፡ የሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ አኳኋን ፡ ከታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ ባጭሩ ፡ እንመልከት።

ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ የሚሰቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ይከበራል። ባለፈው ፡ እንደተመለከትነው ፡ በየዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ቀኝ ፡ ወይም ፡ ግራ ፡ በዓልቴሐት ፡ ወይም ፡ ንግሥት ፡ ሲል ፡ በብርቅ ፡ ባንዳንድ ፡ ቦታ ፡ እቴ ፡ ወይም ፡ እቴጌ ፡ ሲል ፡ ይገኛል። እቴጌ ፡ ማለት ፡ እግዝእተጌ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እግዝእተጌ ፡ ማለትም ፡ ያገር ፡ ወይም ፡ የምድር ፡ እመቤት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ይላሉ። ነገር ፡ ግን ፡ ኣጠራሩ ፡ እተጌ ፡ እንጂ ፡ እግዝእተጌ ፡ ብሎ ፡ የንጉሡን ፡ ባለቤት ፡ የሚጠራ ፡ ጽሑፍ ፡ ስለሌለ ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ነገሩን ፡ ማስታረቅ ፡ ችገር ፡ ይላል ፡ **ጌ** ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ምድር ፡ መሆኑ ፡ በብዙ ፡ አኳኋን ፡ ማስረጃ ፡ አለ ፡ ይኸውም ፡ ሐረር ፡ በሚለው ፡ ስም ፡ ላይ ፡ ጌ ፡ ተጨምሮ ፡ ሐረርጌ ፡ ሲባል ፡ ጕርዓ ፡ በሚለው ፡ ላይ ፡ ጌ ፡ ተጨምሮ ፡ ጕርዓጌ ፡ ሲባል ፡ የሐረር ፡ ምድር ፡ የጕርዓ ምድር ፡ ለማለት ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እቴጌዪቱ ፡ በነገሡበት ፡ ቀን ፡ የአማረ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጌጥ ፡ ኣጊጠው ፡ ንጉሡ ፡ በታላቅ ፡ ዙፋናቸው ፡ ተቀምጠው ፡ በሚጠብቍበት ፡ ኣዳራሽ ፡ መጥተው ፡ በንጉሡ ፡ ቀኝ ፡ ከንጉሡ ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ። ካህናትም ፡ ወትቀውም ፡ ንግሥት ፡ በየማንከ ፡ ሲሉ ፡ ሕዝቡ ፡ ወይዘከሩ ፡ ስመኪ ፡ በኵሉ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ወትሰይምይዮሙ (ወትሰምይዮሙ?) መላእክተ ፡ እስኩ ፡ ፍጻሜሁ ፡ ብለው ፡ ይቀበላሉ። ከዚያው ፡ ሊቀ ፡ ማዕምራን ፡ ቄስ ፡ ሐፄ ፡ ሊቀ ፡ ደብተራ ፡ ይባርኰዋቸዋል። ራቅ ፡ ማሰሬውም ፡ ዘውዱን ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ይደፋል። ንግሥቲቱ ፡ የተማሩ ፡ እንደሆነ ፡ ከመ ፡ ኃይል ፡ ወልድ ፡ እኑየ ፡ ፀዓዳ ፡ ወቀይህ ፡ እስከ ፡ ሚለው ፡ ይጸልያሉ ፡ ያልተማሩ ፡ ሲሆኑ ፡ ስለርሳቸው ፡ የተማረ ፡ ይጸልይላቸዋል። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እልልታ ፡ ደስታ ፡ ይሆናል ፡ "እቴ ፡ አግሮድ? » እየተባለም ፡ ይዘፈናል። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እምቢልታ፣ ፡ መለከት ፡ እየተነፋ ፡ በሴቶች ፡ መውጫ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ይሄዳሉ።

እቴጌዪቱም ፡ በተከሰሱም ፡ በከሰሱም ፡ ጊዜ ፡ ዳኞቹ ፡ ተጠርተው ፡ በቤታቸው ፡ ሔደው ፡ ዳኝነት ፡ እንደሚሰሙ ፡ እንጂ ፡ እቴጌዪቱ ፡ ወደ ፡ ኣደባባይ ፡ ለሙግት ፡ እንደማይወጡ ፡ በዚሁ ፡ በታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ተጽፏል። በተረፈ ፡ ስለ ፡ ንጉሡም ፡ ስለ ፡ እቴጌዪቱም ፡ ስለ ፡ እጨጌውና ፡ ስለዓቃቤ ፡

ሰዓቱ ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡ በጐንደር ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ እየተሻሻለ ፡ የተጨመረውን ፡ በዚያው ፡ በዘመኑና ፡ በሥፍራው ፡ ላይ ፡ ለማንሣት ፡ አልፈነዋልና ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ በታሪክ ፡ ነገሥት ፡ የተጻፈውን ፡ የተለመደውንና ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያውቀውን ፡ ትተን ፡ ስለ ፡ ንጉሡና ፡ ስለ ፡ እቴጌዩቱ ፡ ስያሜ ፡ በሐውልትና ፡ በጽሑፍ ፡ በየዜና ፡ መዋዕላቸውም ፡ የሚገኘውን ፡ ከሚቀጥለው ፡ ምዕራፍ ፡ እንመልከት።

# ምዕራፍ ፡ ፳፱።

## ስለ ፡ ንጉሡና ፡ ስለ ፡ ንግሥቶች ፡ የማዕርግ ፡ ስም።

በየታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ በየክብረ ፡ ነገሥቱ ፡ «ጃንሆይ ፡ ስለሚባለው ፡ ቃል ፡ የተጻፈውን ፡ ቃልና ፡ ሐተታ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ከሌላም ፡ በመመራመር ፡ አለቃ ፡ ታዬ ፡ በታሪክ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ትርጉም ፡ ሰጥተዋል።

**፩ኛ** ፡ ከነገደ ፡ ኦሪ ፡ ወገኖች ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ጃን ፡ አንደኛ ፡ ጃን ፡ ሁለተኛ ፡ የሚባሉ ፡ ነገሥታት ፡ ስለነበሩ ፡ ከነርሱ ፡ ወዲህ ፡ ጃን ፡ ሆይ ፡ የሚባለው ፡ ቃል ፡ እንደተፈጠረ ፡ ጃን ፡ ማለትም ፡ ትርጓሜው ፡ በዕውቀት ፡ የበለጠ ፡ ክቡር ፡ ማለት ፡ መሆኑን።

**፪ኛ** ፡ በዐረብ ፡ ቋንቋ ፡ ጃን (ዣን) ማለት ፡ ባለግርማ ፡ የሚያስፈራ ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ ገልጸዋል።

**፫ኛ** ፡ ከዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ባፄ ፡ ሠርፀ ፡ " ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ ዓፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ባላገሮች ፡ ጃንሆይ ፡ ጃንሆይ ፡ እያሉ ፡ ሲጮሁ ፡ ሰምተው ፡ ምንድነው ፡ ምክንያቱ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቊ ፡ በደምቢያ ፡ ቋንቋ ፡ ጃን ፡ ማለት ፡ ዝሆን ፡ ማለት ፡ ስለሆነዝሆኑ ፡ አዝመራቸውን ፡ ሊያበላሽ ፡ ሲመጣባቸው ፡ ጃንሆይ ፡ ጃንሆይ ፡ እያሉ ፡ ሲጮሁበት ፡ ትቶላቸው ፡ ይሄዳል ፡ ብለው ፡ ቢያስረዱዋቸው ፡ ለወደፊቱ ፡ ኣዘንና ፡ ችግር ፡ የገጠመው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እኔንም ፡ ጃንሆይ ፡ ጃንሆይ ፡ እያለ ፡ ቢለምነኝ ፡ ፈጥኜ ፡

ደርሼ•ችግሩን ፡ እፈጽምለታለሁ ፡ ስላሉ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ነገሥታቱ ፡ ጃንሆይ ፡ እየተባሉ ፡ ይጠሩበት ፡ ዝመር ፡ የሚሉ ፡ አሉ። ነገር ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ የመሰለው ፡ አተራረክ ፡ አፈታሪክ ፡ ስለሚመስል ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በፍጹም ፡ ልብ ፡ መቀበል ፡ ያዳግታልና ፡ እውነተኛው ፡ ማስረጃ ፡ እስቲገኝ ፡ በዚሁ ፡ መቆየት ፡ ግዴታ ፡ ነው። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዓፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ የነበሩበት ፡ ዘመን ፡ ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ዣን ፡ የሚባለው ፡ ቃል ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ተጠርቶ ፡ ይገኛል። ለጊዜው ፡ እንኳን ፡ በኣሳቤ ፡ ትዝ ፡ የሚለኝ ፡ ያዊዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ፲፬ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ.ም ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ) ባለቤት ፡ ስማቸው ፡ ዣን ፡ መንግሣ (መንገሻ) ነበር ፡ ላፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ.ም) የተገጠመላቸው ፡ ግጥም።

ገጽ ፡ ዣን ፡ ይስሐቄ ፡ ገጽ ፡

በአርያም ፡ ይመስል ፡ አንቀጽ ፡

ዣን ፡ ይስሐቄ ፡ ትኵር ፡

ትኵረቱም ፡ ተምክር ፡

እያለ ፡ ዣን ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ ከመጠሪያ ፡ ስማቸው ፡ እንደ ፡ ማዕርግ ፡ ስም ፡ እያስቀደመ ፡ ይጠራቸዋል። ባሁኑ ፡ ባፄ ፡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን (ሺ፬፻፵ ፡ ላይ) የንጉሡ ፡ ሚስት ፡ ዣን ፡ ኃይላ ፡ 1 ፡ የንጉሡ ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ዣን ፡ ሰበር ፡ ራስ ፡ ዣን ፡ ቀንጠፋ! ፡ ዣን ፡ ቤት ፡ ጠባቂ ፤ ዣን ፡ ደረባ ፡ ዣን ፡ በለው.... እየተባሉ ፡ ይጠሩ ፡ ነበር። ይኸም ፡ የንጉሡ ፡ ሹማምንት ፡ መሆናቸውን ፡ አጥብቆ ፡ የሚያስረዳው ፡ ዣን ፡ የሚባለው ፡ ቃል ፡ ሲጨመር ፡ ስለሆነ ፡ ባይሆን ፡ ሆይ ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ ባፄ ፡ ሠርፀድንግል ፡ ዘመን ፡ ተጨምሮ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዣን ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ የንጉሡን ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ የሚመለከት ፡ ሆኖ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ኖሩን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የገለጽነው ፡ ያስረዳል።

እንደዚሁም ፡ ዓፄ ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ ምንጩና ፡ ትርጓሜው ፡ የተዘ'መረበት ፡ ጊዜ ፡ ስለጠፋ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የተነሣ ፡ ፡ የግዕዝ ፡ ሊቅ ፡ እንደመሰለው ፡ ለመተርጐም ፡ ሞክሯል።

ዓፄ ፡ ማለት ፡ ዓጻዌ ፡ ፀር (ጠላትን ፡ የሚዘጋ) ፡ ወይም ፡ ሐጽየ ፡ ፍላላየ ፡ የጠላት ፡ መውጊያዬ) ማለት ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ ግማሾቹ ፡ ከሐጸየ ፡ ግሥ ፡ ሐፄ ፡ ተባለ ፡ የሚሉ ፡ ግማሾቹ ፡ ከአጸየ ፡ ዕፄ ፡ የነበረው ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ ዓፄ ፡ ተባለ ፡ የሚሉ ፡ ግማሾቹ ፡ በቀድሞ ፡ የአማራ ፡ ቋንቋ ፡ ዓፄ ፡ ማለት ፡ ሹም ፡ ማለት ፡ ነውና ፡ ከዚያ ፡ ተያይዞ ፡ የወረደ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ይኹን ፡ በመሰለ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ መሰላቸው ፡ እየለያዩ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አድርሰውታል ፤ እውነተኛውና ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጓሜው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አለመገኘቱ ፡ ያሳዝናል።

በአክሱሞች ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የነገሥታትና ፡ የእቴጌዎች ፡ የሹማምንት ፡ የማዕርግ ፡ ስማቸውን ፡ ዝርዝር ፡ ማግኘት ፡ ችግር ፡ ነው። ወደፊት ፡ ከመሬት ፡ ተቆፍሮ ፡ ከሚገኘው ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ባለው ፡ ጽሑፍ ፡ ሠፍሮ ፡ የሚገኘው ፡ የጳጳሳቱ ፡ የእጨጌዎች ፡ አልፎአልፎ ፡ በየድርሳኑና ፡ ገድል ፡ ላይ ፡ የንቡረ ፡ ዕድ ፡ ያቃቤ ፡ ሰዓት ፡ እንጂ ፡ የነገሥታቱ ፡ የእቴጌዎቹና ፡ የሹማምንቱ ፡ ስምና ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ የሚገኘው ፡ በብርቅ ፡ ነው። የነዚህም ፡ ፩ ፡ አንዱ ፡ የሚገኘው ፡ ከክርስትና ፡ ወዲህ ፡ ያለው ፡ ብቻ ፡ ነው። አብርሐ (ኢዛና ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ዓሠርዊ ፡ መሀዛ ፡ ሠርዌ ፡ መቲ ፤ ዳቍን ፡ ሠርዊ ፡ › ፡ የሚል ፡ አለ ፡ ይኸም ፡ የሠራዊት (ሠርዊ) ፡ ጠቅላላ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ አላቃው ፡ ስም ፡ መሆኑ ፡ በትክክል ፡ አይታወቅም። በየሐውልቱም ፡ ላይ ፡ ባላፈው ፡ በአክሱም ፡ ታሪክ ፡ እንደተመለከትነው ፡ « ፡ ዒዛና ፡ ወልደ ፡ እላዓሜዳ ፡ ብእስየ ፡ ሐሌን ፡ ንጉሠ ፡ አክሱም.... ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ » ፡ ሲል ፡ የአክሱምና ፡ በዙሪያው ፡ የሚገኙት ፡ አገሮች ፡ ንጉሥ ፡ መሆኑን ፡ ሲገልጽልን ፡ ከዛጕዬ ፡ ዘር ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ላሉት ፡ ነገሥታት ፡ የሚናገረው ፡ ጽሑፍ ፡ የተወልን ፡ እንደሚለው ፡ ሐፃኒ ፡ ሐፄ ፡ ዓፄ ፡ የሚል ፡ ጭማሪ ፡ የለበትም። ነገር ፡ ግን ፡ እነ ፡ *ሙሴ ፡ ሊትማን ፡* አክሱምንና ፡ የአክሱምን ፡ ሐውልት ፡ ዙሪያ ፡ መርምረው ፡ ያወጡት ፡ መጽሐፍ ፡ ወደ ፡ ፯፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ ሐፃኒ ፡ የሚባለው ፡ የንጉሥ ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡

መዝመሩን ፡ ይነግሩናል። ሙሴ ፡ ኤንሪኮ ፡ ቼሩሊ ፡ የመረመረው ፡ የኢብን ፡ ሐውቃል ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ አበሻን ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝምሮ ፡ ፩ ፡ ሴት (ዮዲት ፡ ማለቱ ፡ ነው) ትገዛዋለች። እርሷም ፡ ሐፃኒ ፡ ይባሉ ፡ የነበሩትን ፡ የአበሾቹን ፡ ንጉሥ ፡ ገድላ ፡ ነው» ፡ ስለሚል ፡ እነድልነዓድ ፡ ሁሉ ፡ ሐፃኒ ፡ ይባሉ ፡ እንደነበረ ፡ ይታወቃል። ሐዋኒ ፡ ዳንኤል ፡ የሚባል ፡ ንጉሥ ፡ በ፲ረኛው ፡ መቶ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ መኖሩን ፡ ባለፈው ፡ ተመልከተናል።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በዛጕዬ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ላሊበላ ፡ ለደብረሊባኖስ (ለአባ ፡ ማጣ) ገዳም ፡ ርስትና ፡ ጕልት ፡ ሲሰጥ ፡ አጕለትኰአነ ፡ ሐፃኒ ፡ ላሊበላ ፡ ወስመ ፡ መንግሥትየ ፡ ገብረ ፡ መስቀል" እያለ ፡ በትክክል ፡ ይገልጣል። ላሊበላም ፡ አባቶቹም ፡ ተከታዮቹም ፡ ምንም ፡ ከሌላ ፡ ነገድ ፡ ቢሆኑ ፡ የማዕርግ ፡ ስማቸው ፡ የመንግሥታቸው ፡ ወጕም ፡ ምርዓቱም ፡ ከኣክሱም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የተወረሰ ፡ ስለሆነ ፡ ባይጻፍ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ እውነተኛው ፡ ትርጕም ፡ ባይገኝም ፡ ሐፄ ፡ ሐፄጌ ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ ከጥንት ፡ ዝምሮ ፡ ለኣክሱም ፡ ነገሥታት ፡ ሲሰጥ ፡ የኖረው ፡ የማዕርግና ፡ የአክብሮት ፡ ስም ፡ ይሆናል።

እንደዚሁም ፡ የላሊበላ ፡ ባለቤት ፡ መጠሪያ ፡ ስሟ ፡ መስቀል ፡ ክብራ ፡ ሲሆን ፡ ተጨማሪው ፡ ስምነ ፡ ብዓልተቢሓት ፡ ይላል ፡ ይኸም ፡ በተራ ፡ ኣነጋገር ፡ ባለቤት ፡ ማለቱ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ቢሐት ፡ የሚባል ፡ አገር ፡ ኖሮ ፡ የቢሐት ፡ እመቤት ፡ ማለቱ ፡ ይሁን ፡ ሳይታወቅ ፡ የይኵኖ ፡ ኣምላክ ፡ ተከታዮች ፡ ባለፈው ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንና ፡ ኣሁንም ፡ የነዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ባለቤቶች ፡ ስለተጠሩበት ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ይመስላል። ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ ባፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ጊዜ ፡ ፩ዲቱ ፡ የግራ ፡ በዓልቲሐት ፡ ፩ዲቱ ፡ የቀኝ ፡ ባልቲሐት ፡ እየተባሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ እየተደረገላቸው ፡ መኖራቸውን ፡ እንመለከታለን።

ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የጦርነት ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከዕቍባቶቹ ፡ በቀር ፡ ታላቂቱ ፡ ንፃሥት ፡ ታናሺቱ ፡ ንግሥት ፡ እየተባሉ ፡ የሚለዩ ፡ ሁለት ፡ ሚስቶች ፡ ነበሩት ፡ የታላቂቱ ፡ ስም ፡ ዣን ፡ መንግሣ

(መንገሳ)ነው። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ንግሥት ፡ የሚል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ላሊበላ ፡ »በዓልተ ፡ ቢሐት ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ኣልነበረበትም። ለኣባ ፡ መጣዕ ፡ እሰጠው ፡ ጒልት ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ብሌን ፡ ሳባ ፡ በዓልተ ፡ ቢሐት ፡ ማለቱን ፡ ያመለክተናል። የራሱም ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ቀድሞ ፡ ሐፃኒሲባል ፡ እንደ ፡ ነበረቂ ፡ የሚባለው ፡ ፊደል ፡ ቀርቶ ፡ ሐፄ ፡ እየተባሉ ፡ እርሱም ፡ ተከታዮቹም ፡ ይጠሩበት ፡ ዠመር። በኋላም ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ ሐ ፡ በ ፡ ዓ ፡ ተላወጠና ፡ ዓፄ ፡ እገሌ ፡ ይባል ፡ መር ፡ ማለት ፡ ነው።

ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ የሚባለው ፡ ደግሞ ፡ ከኣክሱሞች ፡ ዠምሮ ፡ የነበረ ፡ መሆኑ ፡ እርግጥ ፡ ነው። ለዚሁም ፡ ማስረጃው ፡ «በኃይለ ፡ እግዚኣ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ መዋዒ ፡ ለዘኮነ ፡ ዒዛና ፡ ወልደ ፡ እለ ፡ ዓሜዳ ፡ ......ንጉሠ ፡ ኣክሱም.... ወዘሕሜር ፡ ወዘረይዳን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢይትመዋዕ ፡ ለፀር ፡ የሚለው ፡ የዒዛና (የአብርሃ) ፡ የታወቀው ፡ የአክሱም ፡ ሐውልቱ ፡ ነው። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የሮማ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳባት ፡ አራተኛው ፡ ኒኮላዎስ ፡ ፩ሺ፪፻፹፱ ፤ ዮሐንስ ፡ ጂዎቫኒ ፡ ፳፪ኛ (፩ሺ፫፻፳፱) ከዚያ ፡ ወዲህም ፡ ያሉት ፡ ለዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ ለገላውዴዎስም ፡ ለሱስንዮስም ፡ በላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ሲጽፉ ፡ አንድ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ « Roi » ፡ ንጉሥ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ «Imperatortum» ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ይሉ ፡ ነበር። የዐረብ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ኣብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ያበሻ ፡ ሐፄ ፡ የኛዎቹ ፡ በግዕዝ ፡ እንዳጋጠማቸው ፡ ሐፄ ፡ እገሌ ፡ ወይም ፡ ንጉሥ ፡ እገሌ ፤ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ይላሉ።

በዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የጦርነት ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ እንደተገነዘብነው ፡ ነገሥታቱ ፡ ሁለት ፡ ሚስቶችና ፡ ብዙ ፡ ዕቍባቶች ፡ ነበሩዋቸው። ባንድ ፡ ሚስት ፡ መኖሩን ፡ ታሪክ ፡ የመሰከረለት ፡ ባቡነ ፡ ተክለሃይማኖትና ፡ በዓፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ መካከል ፡ የተደረገውን ፡ የሲሶውን ፡ መንግሥት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በዘመኑ ፡ ለማፍረስ ፡ የሞከረው ፡ ቴዎድሮስ ፡ አንደኛ ፡ ብቻ ፡ ነው። አሁን ፡ ታሪካቸውን ፡ የምንመለከተው ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም (ስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ ቆስጠንጢኖስ) ሁለት ፡ ሚስቶች ፡ ነበሯቸው። አንደኛይቱ (ዋናይቱ) ቀኝዕ (ቀኝ)በዓልቲሐት ፤ ሁለተኛዪቱ ፡ ግራ ፡ በዓልቲሐት ፡ ይባላሉ።

መጽሐፉ ፡ የሐድያውን ፡ የገራድ ፡ መሐመድን ፡ ልጅ ፡ ንግሥት ፡ ዕሌኒ ፡ ቀኝዕ ፡ በዓልቲሐት ፡ የልጅነት ፡ ሚስታቸውን ፡ ዣን ፡ ኃይላን ፡ ግራ ፡ በዓልቲሐት ፡ ይላቸዋል። ባለፈው ፡ እንዳመለከትነው ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ እንደምንመለከተው ፡ ለበእደ ፡ ማርያምም ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ የሆኑ ፡ በዚሁ ፡ ሥያሜ ፡ ሁለት ፡ ሚስቶች ፡ ነበሩዋቸው። አንደኛይቱ ፡ ቀኝዕ ፡ በዓልቲሐት ፡ ዕሌኒ ፡ አድማስ ፡ ሞገሳ ፡ ፪ተኛዪቱ ፡ ግራ ፡ በዓልቲሐት ፡ ዣን ፡ ሰይፋ ፡ የሚባሉነበሩዋቸው። ፩ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለቱ ፡ በማዕርግ ፡ ከቀኟ ፡ የግራዋ ፡ የምትበልጥ ፡ ይመስላል። ስለዚህ ፡ ነገሥታቱ ፡ የቀኝ ፡ ባለቤት ፡ የግራ ፡ ባለቤት ፡ የሚባሉ ፡ ደረጃና ፡ ሥልጣናቸው ፡ የተወሰነ ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ የበላጡ ፡ ሚስቶች ፡ እንደነበሩዋቸው ፡ እንረዳለን። ይኸም ፡ የቀኝ ፡ ቢትወደድ፣የግራ ፡ ቢትወደድ ፡ የቀኝ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ የግራ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ እያሉ ፡ ከሚሾሙት ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም።

የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታትና ፡ ሕዝብ ፡ ክርስቲያኖች ፡ መሆናቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ በእስላሞች ፡ የተከበቡ ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንጂ ፡ በክርስቲያኖች ፡ የተከበቡ ፡ ከክርስቲያን ፡ ነገሥታትና ፡ ጳጳሳት ፡ ቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ ክርስቲያኖች ፡ አይደሉም። ስለዚህ ፡ የእስላም ፡ ነገሥታትና ፡ ባላባቶች ፡ ፬ ፡ ወይም ፡ ከአራት ፡ የበለጡ ፡ ሲያገቡ ፡ የዚህ ፡ ልማድ ፡ የኛንም ፡ ነገሥታት ፡ ሊይዛቸው ፡ ይችላል። ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ደግሞ ፡ ለሥጋ ፡ ፍትወታቸውና ፡ ለአምሮታቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ አገዛዝንና ፡ ፖለቲካን ፡ የሚያቃናው ፡ የጋብቻ ፡ ብዛት ፡ ነበር። አንዱ ፡ የአዳል ፡ ወይም ፡ የደዋሮ ፡ ኣለዚያም ፡ የሐድያ ፡ ባላባት ፡ ልጁን ፡ ለንጉሡ ፡ የዳረ ፡ እንደሆነ ፡ ያለፈ ፡ ቂሙን ፡ ወደ ፡ መርሳት ፡ የሽፍትነት ፡ ሥራውን ፡ ወደ ፡ መተው ፡ ይቀርባል። ከሁለቱ ፡ መካከል ፡ ልጅ ፡ የተወለደም ፡ እንደሆነ ፡ ዝምድናው ፡ እየጠበቀ ፡ ይሔዳል ፡ የጠብና ፡ የጦርነት ፡ ለት ፡ ወንድማችንን ፡ እንዴት ፡ እንወጋዋለን ፡ ያሰኛል። ስለዚህ ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ተነሣንበት ፡ እንመለስ።

የዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ተከታይ ፡ ልጅ ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ እናት ፡ ጽዮን ፡ ሞገሳ ፡ ቀኝዕ ፡ በዓልቴሐት ፡ ይሁኑ ፡ ወይም ፡ ግራ ፡ ባልቲሐት ፡ ይሁኑ ፡ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ አይታወቅም። ደግሞ ፡ «ጽዮን ፡ ሞገሳ ፡ » ከስም ፡ ጋር ፡

ተጨምሮ ፡ የሚሰጥ ፡ ስም ፡ እንጂ ፡ ዕሌኒ ፤ ማርያም ፡ ስና ፤ ሰብላ ፡ ወንጌል ፡ እንደሚባል ፡ መጠሪያ ፡ ስም ፡ አይደለም። ይኸንንም ፡ ወደፊት ፡ ከዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ቀጥሎ ፡ የምንመለከተው ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይገልጽልናል ፡ "...ወለብእሲተ ፡ ንእሱ ፡ ግራ ፡ በዓልቲሐት ፡ ሠመይዋ ፡ ዣን ፡ ሰይፉ ፡ ወለቀኝዕ ፡ ባልቲሐት ፡ ዕሌኒ ፡ ሠመይዋ ፡ አድማስ ፡ ሞገሳ ፡ -ቲንሿን ፡ ሚስቱን ፡ የግራዋን ፡ ባላቤት ፡ ዣን ፡ ሰይፉ ፡ የቀኙዋን ፡ ባለቤት ፡ ዕሌኒን ፡ አድማስ ፡ ሞገሳ ፡ ብለው ፡ ሠየሚት።

ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንደምንመለከተው ፡ በምድረ ፡ ደጎ (ተጕለት) የመካነ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኣሠርቶ ፡ ሲጨርስ ፡ ፍሬ ፡ ማርያም ፡ ለምትባለው ፡ ለግራ ፡ ባልቲሐት ፡ ሚስቱ ፡ ለመታሰቢያም ፡ ለመቃብሯም ፡ ይሆናት ፡ ዘንድ ፡ ሰጣት ፡ ይላል። በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ደግሞ ፡ በምድረ ፡ ደጎ (ተጕለት) የመካነ ፡ ማርያምን ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ አሠርቶ ፡ ሲጨርስ ፡ ለልጅነት ፡ ሚስቱ ፡ ለዣን ፡ ኃይላ ፡ ግራ ፡ ባልቲሐት ፡ ለምትባለው ፡ ሰጣት ፡ ይላል። እንግዴህ ፡ በዚያው ፡ ባንድ ፡ ሥፍራ ፡ በምድረ ፡ ደጎ ፡ ፪ ፡ መካነ ፡ ማርያም ፡ አሠራ ፡ አይልም ፤ የተሠራው ፡ ፩ ፡ መካነ ፡ ማርያም ፡ ተብሎ ፡ የተሠየመ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ባንደኛው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ፍሬ ፡ ማርያም ፡ ብሎ ፡ በመጠሪያ ፡ ወይም ፡ በክርስትና ፡ ስም ፡ በሌላው ፡ ቦታ ፡ ለስመ ፡ መንግሥት ፡ በተሠጣት ፡ በዣን ፡ ኃይላ ፡ ስለጻፈው ፡ ኣንዲቱ ፡ የግራ ፡ ባልቲሐት ፡ ሁለት ፡ ንግሥቶች ፡ መስለው ፡ ይታያሉ።

ስለዚህ ፡ የታሪኩ ፡ የሥያሜው ፡ አካሔድ ፡ እንደ ፡ ሚመራው ፡ ንጕሡ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ተፈጽሞለት ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ በቀድሞ ፡ ስሙ ፡ ላይ ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ እንደሚወጣላት ፡ የንጕሡ ፡ ሚስቶችም ፡ ንጕሥ ፡ ከዓቃቤ ፡ ሰዓቱና ፡ ከጽራግ ፡ ማሰሬው ፡ እየተማከረ ፡ በምርጫ ፡ እንደፈቀደላቸው ፡ አንዲቱ ፡ የግራ ፡ አንዲቱ ፡ የቀኝ ፡ በኣልቲሐት ፡ ተብለው ፡ እንደዚያን ፡ ጊዜው ፡ የእቴ ፡ እንደዛሬው ፡ የእቴጌነት ፡ ደረጃ ፡ ሲሰጣቸውና ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ለነርሱም ፡ የሚገባው ፡ የእቴጌነት ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ሲፈጸም ፡ «ዣን ፡ ሞገሳ ፤ አድማስ ፡ ሞገሳ ፡ ጽዮን ፡ ሞገሳ ፡ ዣን ፡ ኃይላ ፡ ዣን ፡ ሰይፉ ፡ የሚባል ፡

ስመ ፡ መንግሥት ፡ ይሰጣቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ ባለቤት ፡ እቴ ፡ ዣን ፡ ዛላ ፡ የሚላቸውና ፡ በሌላ ፡ ምዕራፍ ፡ ደግሞ ፡ ዕሌኒ ፡ ቀኝዕ ፡ በዓልቲሐት ፡ የሚላቸው ፡ አንዲቷን ፡ ሴት ፡ ነው። እንደ ፡ ወንዶቹነገሥታት ፡ የሴቶቹም ፡ አንዱ ፡ መጽሐፍ ፡ በስሟ ፡ አንደኛው ፡ በስመ ፡ መንግሥቷ ፡ ብቻ ፡ እየጻፈው ፡ ሲገኝ ፡ አንዲቱ ፡ ሁለት ፡ እየመሰሉ ፡ ጸሐፊንም ፡ አንባቢንም ፡ ሲያሳስት ፡ ይኖራል። እንኳን ፡ የንጉሡና ፡ የባለቤቱ ፡ የሹማምንቱም ፡ ስም ፡ ለማይጠነቅቅ ፡ ጸሐፊና ፡ አንባቢ ፡ እንደዚሁ ፡ ያሳስታል ፡ ስሕተትም ፡ ቢቀር ፡ ያደናግራል።

ለምሳሌ ፡ ኣንዱ ፡ ሹም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የተከበረውን ፡ የአዛዥነት ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ በዚያው ፡ ላይ ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝነትን ፡ ይይዛል ፡ እሱው ፡ ራሱ ፡ ባንድ ፡ ደብር ፡ ላይ ፡ መሪነትን ፡ የጨመረ ፡ እንደሆነ ፡ የአለቅነትን ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ ይወስዳል።

ስለዚህ ፡ ስሙንና ፡ የማዕርግ ፡ ስሙን ፡ አሟልቶ ፡ የሚጽፈው ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ኣዛዥ ፡ እገሌ ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዙ ፡ ለእገሌ (የንጉሡ ፡ ስም ፡ ይጨመራል) ፡ የእገሌ (የደብሩ ፡ ስም ፡ ተጠቅሶ) አለቃ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል። በሥራውም ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱንና ፡ የቤተ ፡ ክህነቱን ፡ ደርቦ ፡ ያካሄዳል። እንደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለቃ ፡ ቅኔ ፡ ማኅሌት ፡ ገብቶ ፡ እካህናቱ ፡ መካከል ፡ እልቅናው ፡ ቦታ ፡ ሆኖ ፡ ቅኔ ፡ እየሰጠ ፡ ምራት ፡ እየመራ ፡ ያስተዳድራል ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ ያስተላልፋል ፡ የንጉሡን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ያጽፋል። የንጉሡን ፡ ሀብት ፡ በመዝገብ ፡ ይይዛል። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በአዛዥነቱ ፡ የዳኝነት ፡ ደረጃ ፡ ከንጉሡ ፡ የተሰጠው ፡ ሲሆን ፡ በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ ከሊቀ ፡ መጣን (ሊቀ ፡ መጣኒ ፡ ሊቀ ፡ መጽአኒ ፡ ሊቀ ፡ መጫኒ) ፡ ጋር ፡ ተቀምጦ ፡ ይፈርዳል። ደግሞ ፡ በበእደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ውስጥ ፡ ፩ ፡ ታላቅ ፡ ሹም ፡ የብሕት ፡ ወደድነትና ፡ የባሊ ፡ ገራድነት ፡ ሹመት ፡ ፩ኛው ፡ ሊቀ ፡ መጣኒ ፡ በተሳለበት ፡ ላይ ፡ ቃለ ፡ ሐፄነትን ፡ ደርቦ ፡ ሲይዝ ፡ እንመለከታለን።

የዚህም ፡ ሁሉ ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ የመነጨው ፡ ከዚያው ፡ ከአክሱም ፡ ሆኖ ፡ ከዛጉዬ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ኣልፎ ፡ ምልክቱ ፡ እስከ ፡

ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ደርሷል። የዓፄ ፡ ምኒልክ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ በእልቅና ፡ የራጕኤልን ፡ ደብር ፡ እየመሩ ፡ የጸሐፌ ፡ ትእዛዝነቱን ፡ ሥራ ፡ ያስኬዱ ፡ ስለነበረ ፡ «አለቃ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ዘውእቱ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዙ ፡ ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ይባሉ ፡ ነበር። በዚህ ፡ መካከል ፡ የሚያሳስተው ፡ አንዱ ፡ መጽሐፍ ፡ አለቃ ፡ እገሌ ፡ ሌላው ፡ ኣዛዥ ፡ እገሌ ፡ ፫ኛው ፡ ደግሞ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ እገሌ ፡ ሲለው ፡ ነው።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ለማስታወስ ፡ የደረስነው ፡ ባለፈውም ፡ ባሁኑም ፡ ለወደፊቱም ፡ የነገሥታቱም ፡ የእቴጌዎቹም ፡ የሹማምንቱም ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ከመጠሪያ ፡ ስማቸው ፡ ጋር ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ባንድነት ፡ እየሆነ ፡ በየዜና ፡ መዋዕሉ ፡ በግልጽ ፡ ሳይጻፍ ፡ አንዱ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በመጠሪያ ፡ እሌላው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ በስመ ፡ መንግሥት ፡ ሲጻፍ ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ በመጠሪያው ፡ ስም ፡ ገብቶ ፡ ያንን ፡ አስረስቶ ፡ መጠሪያ ፡ ሲሆን ፡ ኣንባቢን ፡ እንዳያሳስት ፡ ለማስገንዘብ ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፴።

## ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኣምልኮን ፡ ለማጥፋት ፡ ያደረጉት ፡ ቅጣትና ፡ ያወጡት ፡ አዋጅ።

ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ለክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ በጣም ፡ ቀናዒ ፡ እንደነበሩ ፡ ይህ ፡ ምዕራፍ ፡ ያስረዳል። ይኸም ፡ ሁኔታ ፡ ከልብ ፡ እውነተኛውን ፡ ኣምላክና ፡ የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ ለማገልገል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ምናልባት ፡ ሕዝቡ ፡ ከኣረመኔ ፡ አምልኮ ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ሲመለስና ፡ ከሌላው ፡ ክርስቲያናዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ በሃይማኖት ፡ ሲዋሐድ ፡ በኑሮውም ፡ በአሳቡም ፡ ያንድነትና ፡ የወንድማማችነት ፡ መንፈስ ፡ ሲያድርበት ፡ ለአገዛዝም ፡ እንደሚመች ፡ ገምተው ፡ ይሆናል።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ በመዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ እንደዚህ ፡ ይላል፣ደስክ ፡ የሚባል (ጣዖት ፡ ምስል ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ጋኔን ፡ ይሁን ፡

ኣይታወቅም) ነበረ ፡ ለርሱና ፡ ለዲያብሎስ ፡ ሰገድን ፡ ብለው ፡ ራሳቸው ፡ አምነው ፡ ሌሎቹንም ፡ ሰዎች ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ሰግደዋል ፡ ብለው ፡ በሐሰት ፡ እየመሰከሩ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አስገደሉ። ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ መስካሪዎቹን ፡ በሐሰት ፡ መስክራችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ደማቸው ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ይውደቅ ፡ ብለው ፡ ኣስጠንቅቀው ፡ ባደረጉት ፡ ቅጣት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በድንጋጤና ፡ በፍርሐት ፡ ተንቀጠቀጠ ፡ ለገዛ ፡ <u>ልጆቻቸው ፡ ለወንዶቹ ፡ ለገላውዴዎስና ፡ ለዓምደ ፡ ማርያም ፡ ለዘርዓ ፡ አብርሃም ፡ ለበትረ ፡ ጽዮን ፡ ለሴቶቹ ፡ ለድል ፡ ሠምራ ፡ ለሮም ፡ ገነዬላ ፡ ለዓዳል ፡ መንገሣም ፡</u> አልራሩላቸውም። .... በዚህ ፡ ቀን ፡ በተደረገው ፡ ቅጣት ፡ የሞቱት ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ሞተው ፡ እነርሱ ፡ የዳኑ ፡ ብዙ ፡ አሉ ፡ ...። ቅጣቱ ፡ ከአለቀ ፡ በኋላ ፡ የንጉሡ ፡ አዋጅ ፡ እንደዚህ ፡ ተብሎ ፡ በሰቀላ (ዓደባባይ?) ተነገረ። የክርስቲያን ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፡ ብዙዎቹን ፡ ሰዎች ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ለደስክና ፡ ላዲኖ ፡ ከመስገድ ፡ ካስጣልናቸው ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ሰይጣን ፡ እቤታችን ፡ ድረስ ፡ ገብቶ ፡ ልጆቻችንንም ፡ አስቶ ፡ ገዛቸው። » ሕዝቡም ፡ የተገረፉትን ፡ ሰዎች ፡ ቊስላቸውን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በነርሱም ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አለቀሰ ፡ ተጨነቀ። ቀጥሎም ፡ በየሕዝቡ ፡ ግንባር ፡ ላይ (**በኣብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ**) የሚል ፡ ክህድክዎ ፡ ለዲያብሎስ ፡ በ**ክርስቶስ** ፡ አምላክ ፡ የሚል ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ ላይ ፡ ክህድክዎ ፡ ለደስክ ፡ ርጉም ፡ አነ ፡ ገብራ ፡ ለ**ማርያም** ፡ እሙ ፡ ለፈጣሬ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ የሚል ፡ እግራ ፡ ክንዳቸው ፡ ላይ ፡ እንዲጻፍ ፡ ታዘዘ።

ይኸንንም ፡ ሳይፈጽም ፡ የተገኘ ፡ ቤቱ ፡ እንዲበረበር ፡ በሥጋው ፡ እንዲቀጣ ፡ ከንጉሡ ፡ መታዘዙ ፡ ለሁሉም ፡ ተነገረ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በክፉ ፡ ሥራው ፡ ዘርዓ ፡ ሰይጣን ፡ ተብሎ ፡ የተሠየመ ፡ ዘርዓ ፡ ጽዮን ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ነበር። እርሱም ፡ በሐሰት ፡ እየመሰከረ ፡ ብዙ ፡ መነኮሳትና ፡ ደባትር ፡ ብዙ ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ ከአስገደለ ፡ በኋላ ፡ ኃጢኣቱ ፡ ስለተገለጸበት ፡ በግዞት ፡ ወደሐይቅ ፡ ሄደ ፡ ሲል ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ይጨርሳል።

መቸም ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ የሚመለከት ፡ ሰው ፡ የቀድሞ ፡ ነገሥታትና ፡ ጳጳሳት ፡ የሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ከወንጌል ፡ ቃል ፡ ውጭና ፡ የማይገባ ፡ ሆኖ ፡ ያገኘዋል። **ክርስቶስ** ፡ ሐዋርያቶቹ ፡ ክርስትናን ፡ በዓለም ፡ እየዞሩ ፡

እንዲያስተምሩለት ፡ ሲያዝ ፡ «ሂዱ ፡ አስተምሩ ፡ **በአብና በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ** ፡ ስም ፡ አጥምቍ ፡ ነገራችሁን ፡ የሚቀበል ፡ ነፍሱን ፡ ያድናል ፡ እምቢ ፡ ያላችሁ ፡ ቢኖር ፡ የእግራችሁን ፡ አቧራ ፡ ምስክር ፡ እንዲሆንበት ፡ አራገፉችሁን ፡ ትታችሁ ፡ ወደሌላ ፡ ሄዳችሁ ፡ አስተምሩ ፡ ነው ፡ ያለው ፡ የእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ በስብከቱ ፡ ላይ ፡ እንደተጨማሪ ፡ በሆነው ፡ በጦርነት ፡ሲመሠረት ፡ ክርስትና ፡ ግን ፡ ከመዠመሪያ ፡ ዝምሮ ፡ በጌታችንና ፡ በሐገርዋሪያቱ ፡ የተመሠረተው ፡ ሰማስረዳት ፡ ብቻ ፡ ነው። በግዴታና ፡ በውዴታ ፡ በጦርነትና ፡ በማስረዳት ፡ መካከል ፡ ያለውም ፡ ልዩነቱ ፡ ብዙ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ለመዘርዘር ፡ ጊዜ ፡ የላንም። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሕዝባቸውን ፡ ከአረመኔ ፡ ኣምልኮ ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ለመመለስ ፡ በስብከት ፡ ፈንታ ፡ ግርፋትንና ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ ሲፈጽሙ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ረገድ ፡ **እግዚአብሔርን**ና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በፖለቲካ ፡ በኵል ፡ ኢትዮጵያን ፡ በቅን ፡ ለማገልገል ፡ እንጂ ፡ ለክፋት ፡ አላደረጉትም ፡ ነበር ፡ ያውም ፡ ቢሆን ፡ ነገሥታቱ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ከጳጳስና ፡ ከእጨጌ ፡ ከሊቃውንት ፡ ምክር ፡ ኣይወጡምና ፡ ግማሹን ፡ በሞት ፡ ግማሹን ፡ በግርፋት ፡ ሲቀጡ ፡ እነዚሁ ፡ አባቶች ፡ ጠጋ ፡ ብለው ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ኣይገባም ፡ ክርስትና ፡ በማስተማር ፡ እንጂ ፡ በቅጣት ፡ አይመሠረትም። ይኸም ፡ የኛ ፡ የግል ፡ ተግባራችን ፡ ነውና ፡ እናስተምራለን" ፡ ቢሏቸው ፡ ከዚህ ፡ ግፈኛ ፡ ሥራ ፡ ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሳይመለሱ ፡ ኣይቀሩም ፡ ነበር። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ በማድረግ ፡ ፈንታ ፡ እንዲያውም ፡ ለቅጣቱ ፡ ሊቃውንቱ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ አባሪ ፡ ተነባባሪ ፡ መሆናቸው ፡ አይጠረጠርም። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ እኛ ፡ ይኸን ፡ የምናስብበት ፡ ጊዜና ፡ እነርሱ ፡ ያሉበት ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ እኛ ፡ ወደነርሱ ፡ ጊዜ ፡ ብንሄድ ፡ የነርሱን ፡ ለመሥራት ፡ እነርሱም ፡ እኛ ፡ አለንበት ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ ቢገኙኖሮ ፡ ዛሬ ፡ እኛ ፡ እንደምናስበው ፡ እንደሚያስቡ ፡ የታወቀ ፡ መሆኑን ፡ ሳንዘነጋ ፡ ወደሌላው ፡ ጉዳይ ፡ እንተላለፍ።

ይኸን ፡ ቅጣት ፡ የፈጠሩትን ፡ የዘመኑን ፡ ጣዖታት ፡ ሁኔታ ፡ ሙሉ ፡ ዝርዝርና ፡ ሐተታ ፡ ከዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ላይ ፡ አናገኝም። ስማቸውን ፡ ያንደኛውን ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ደስክ ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ደስክ ፡ ና ፡ ዲኖ ፡ መሆናቸውን ፡ ይገልጻል። ደጋግሞ ፡ ስሙን ፡ ስለሚጠራው ፡ ከዲኖ ፡ ይበልጥ ፡ ደስክ ፡

የተመለከበት ፡ ይመስላል። የርሱም ፡ አምልኮ ፡ ባዔ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ ሳይበርድ ፡ ባዔ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ጊዜ ፡ ለደስክ ፡ ሰግደዋል ፡ ተብለው ፡ ሲቀጡ ፡ ገና ፡ ወደፊት ፡ እንመለከታለን። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ደስክ ፡ የተባለው ፡ ጣዖት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ከዐረብ ፡ ከግብፅ ፡ የመነጨ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ከአገር ፡ ተወላጁ ፡ ከአማራው ፡ ወይም ፡ ከጋላው ፡ አለዚያም ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ነገድ ፡ ከአንዱ ፡ የተፈጠረ ፡ ይሁን ፡ ኣይታወቅም። የሚመለከውም ፡ በመንፈስና ፡ በአእምሮ ፡ ብቻ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ እንደሌላው ፡ አገር ፡ የእንጨት ፡ የብረት ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፡ ምስል ፡ ሠርተው ፡ ይሰግዱለት ፡ እንደሆነ ፡ በትክክል ፡ አልተገለጸም። ነገር ፡ ግን ፡ በኣለቃ ፡ ታዬ ፡ የእጁ ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈው ፡ እንደዚህ ፡ ይላል።

“ሸዋ ፡ ቅንብቢት ፡ አጠገብ ፡ ሰንጋ ፡ ቦካ ፡ በላይ ፡ ብለት ፡ የምትባል ፡ ትንሽ ፡ ኮረብታ ፡ አለች ፡ ዛሬ ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ታቦት ፡ ተተክሎበታል። ጥንት ፡ በዚያ ፡ ሥፍራ ፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ቤተ ፡ ደስክ ፡ የሚባል ፡ የዛር ፡ መቅደስ ፡ ነበረ። የክርስቲያን ፡ ነገሥታት ፡ መኳንንቱም ፡ ዘመቻ ፡ ሲነሡ ፡ ከርሱ ፡ ይሠፍሩና ፡ ከዛሩ ፡ አለቃ ፡ ምክር ፡ ተቀብለው ፡ ይዘምቱ ፡ ነበር። በሀገሩም ፡ የነበሩ ፡ የጋፋት ፡ ሕዝብ ፡ ኣምልኳቸው ፡ በዚህ ፡ በቤተ ፡ ደስክ ፡ ነበረ ፤ ይኸንንም ፡ ቤተ ፡ ደስክ ፡ በኋላ ፡ ኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ኣፈረሱት ፡ ይላሉ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ የምንመለከተው ፡ የደስክ ፡ አምልኮ ፡ ከኣቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከሺ፪፻፷ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ መሆኑን ፡ ከዚያ ፡ ለክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ቀናዒና ፡ የታወቊ ፡ ሐዋርያ ፡ የሆኑት ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ማፍረሳቸውን ፡ ነው።

ዳሩ ፡ ግን ፡ እርሳቸው ፡ ከአለፉ ፡ በኋላ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ሥሩን ፡ የሰደደው ፡ የደስክ ፡ ኣምልኮ ፡ እንደገና ፡ ተስፋፍቶ ፡ እስከዚህ ፡ እስከ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ድረስ ፡ ደርሷል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በመካከሉም ፡ የአለፉት ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፡ ነገሩን ፡ ችላ ፡ ብለው ፡ እንዲያውም ፡ ራሳቸው ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡

ሲሄዱ ፡ ድልን ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ባጠገቡ ፡ ሠፍረው ፡ ደጅ ፡ ይጠኑ ፡ እንደነበረ ፡ ተመልክተናል።

ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ከአባቶቻቸው ፡ የተላየ ፡ የሥራ ፡ ትጋት ፡ ጥብቅ ፡ መንፈስ ፡ ያላቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ ፍጹም ፡ ክርስቲያንነት ፡ ስለሚሰማቸው ፡ የደስክን ፡ አምልኮ ፡ ለዘለቄታ ፡ ከሕዝብ ፡ ላይ ፡ ለመንቀል ፡ ተነሡ ፡ ማለትነው። በዚህም ፡ ኣምልኮ ፡ የውጭው ፡ ሕዝብ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከልጆቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ስለነበሩበት ፡ “ ኦ » ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘከመ ፡ ይገብር ፡ ሰይጣን ፡ ሶበ ፡ ኣሕደግናሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ እምአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወእምሰጊድ ፡ ላደስክ ፡ ወላዲዋ ፡ ይእዜሰ ፡ በአ ፡ ውስተ ፡ ቤትነ ፡ ወአስሐተ ፡ ውሉደነ ፡ ብለው ፡ በገሀድ ፡ በኣዋጅ ፡ ገልጸው ፡ በዚህ ፡ አምልኮ ፡ ተገኝተዋል ፡ የተባሉትን ፡ ሁሉ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ እንደሚለው ፡ እገሌ ፡ ሰግዷል ፡ ብሎ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ሲመሰክር ፡ «በሐሰት ፡ መስክረህ ፡ እንደሆነ ፡ ደሙ ፡ በላይህ ፡ ይሁን ፡ እያሉ ፡ ያመለከውን ፡ ሁሉ ፡ በግርፋትና ፡ በሞት ፡ ቀጡ። በሕዝብ ፡ ላይ ፡ የጣሉትንም ፡ ሕግና ፡ ቅጣት ፡ በልጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ለመፈጸም ፡ እነሆ ፡ የተገረፉትንና ፡ የሞቱትንም ፡ ልጆቻቸውን ፡ ስም ፡ ገልጸናል።

# ምዕራፍ ፡ ፴፩።

## ሹም ፡ ሽርና ፡ ባለሟልነት።

ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ አጻጻፉ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የፊቱ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ የዞረ ፡ ወይም ፡ የኋለኛው ፡ የቀደመ ፡ ባይጠፋም ፡ እንደዚሁም ፡ ኣንዱ ፡ ጕዳይ ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ ሳያልቅ ፡ ተቋርጦ ፡ እሌላ ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ እየተደባለቀ ፡ ለአጻጻፍ ፡ ባይመችም ፡ በውስጡ ፡ አዳዲስ ፡ የዘመኑን ፡ ሥርዓትና ፡ ደንብቦ ፡ ይገልጻል። እኛም ፡ ስንጽፍ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ታሪኩ ፡ እንዳይፋለስ ፡ መደዳውን ፡ እንደተጻፈ ፡ እየተረጐምን ፡ መግለጻችን ፡ ባይቀር ፡ የተነጣጠለውን ፡ ባንድነት ፡ ለመሰብሰብ ፡ እንሞክራለን።

ከሹም ፡ ሽሩ ፡ በፊት ፡ የራሳቸውን ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ሰምተናል ፡ "ይኸው ፡ ሐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ » ነው። ስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ እንዲሆን ፡ እንደዘመኑ ፡ ደንብ ፡ ከብዙ ፡ ስም ፡ ጋር ፡ ቀርቦ ፡ በእጣ ፡ የወጣው ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ስለሆነ ፡ ይኸው ፡ የትልቁ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ስም ፡ የነበረው ፡ ለርሳቸው ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ እንዲሆን ፡ ተወስኗል። ከርሳቸውም ፡ ጋር ፡ የሚስቶቻቸው ፡ ስምና ፡ የማዕርግ ፡ ስማቸው ፡ ያንደኛዪቱ ፡ ንግሥት ፡ ዕሌኒ ፡ ቀኝዕ ፡ በዓልቴሐት (ዣን ፡ ዛላ?) የሁለተኛዪቱ ፡ ንግሥት ፡ ፍሬ ፡ ማርያም ፡ ዣን ፡ ኃይላ ፡ ግራ ፡ በዓልቴሐት ፡ ነው። በዚህ ፡ ውስጥ ፡ የምንመላከተው ፡ ጒድለት ፡ የንግሥት ፡ ዕሌኒ ፡ ስማቸው ፡ ሲገኝ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ የለም። ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንዳሳሰብነው ፡ ኢቴ ፡ ዣን ፡ ዛላ ፡ ብሎ ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ የሚጠቅሰው ፡ የርሳቸው ፡ ይመስላል ፡ ለማለት ፡ ሲያስደፍር ፡ ለማረጋገጥ ፡ አይቻልም።

ያንደኛዪቱ (የ፪ተኛዪቱ) ስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ ዣን ፡ ኃይላ ፡ ባንድ ፡ ሥፍራ ፡ ሲገኝ ፡ መጠሪያ ፡ ስማቸው ፡ ፍሬ ፡ ማርያም ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ይገኛል። በላሊበላም ፡ ገድል ፡ በዓምደ ፡ ጽዮንም ፡ የጦርነት ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ውስጥ ፡ "**ኢቴ**" የሚል ፡ ቃል ፡ በነገሥታቱ ፡ ሚስቶች ፡ ስም ፡ ኣጠገብ ፡ አላገኘሁም። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ በዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ውስጥ ፡ ኢቴ ፡ ዣን ፡ ዛላ ፡ ሲል ፡ ይገኛል። ስለዚህ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ጌ ፡ የሚባለው ፡ ፊደል ፡ ተጨምሮ ፡ እቴጌ ፡ ይባል ፡ ዠመር ፡ ማለት ፡ ነው። በዓልት ፡ ቢሐት ፡ የሚባለው ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ገና ፡ በፊት ፡ በላሊበላ ፡ ከዚያም ፡ በዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ መኖሩ ፡ ባለፈው ፡ የጻፍነው ፡ ያስረዳልያፄ ፡ ላሊበላ ፡ ባለቤት ፡ መስቀል ፡ ክብራ ፡ ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ብሌን ፡ ሳባ ፡ በዓልተ ፡ ቢሐት ፡ ይባላሉ። በዓልታ ፡ ቢሐት ፡ የነበረው ፡ ቃል ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ በቲንሹ ፡ ተለውጦ ፡ ባሁነ ፡ ጊዜ ፡ በዓልቴሐት ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው።

ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ስለጣዖት ፡ አምልኮና ፡ ስለ ፡ ቅጣቱ ፡ የሆነውን ፡ ከገለጸ ፡ በኋላ ፡ የሹም ፡ ሽር ፡ ነገር ፡ ከመዠመሩ ፡ በፊት ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምደ ፡ መስቀል ፡ የሚባል ፡ በኋላ ፡ ዓምደ ፡ ሰይጣን ፡ ተብሎ ፡ የተሠየመ ፡ የንጒሡ ፡ አማች ፡ የልጃቸው ፡ የብርሃን ፡ ዘመዳ ፡ ባል ፡ እንደነበረ

፡ እርሱም ፡ ከንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ከሚስቱ ፡ አልፎ ፡ በስርቆሽ ፡ ከአንዲት ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ የሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ሲያደርግ ፡ ኖሮ ፡ በኋላም ፡ ይህቺኑ ፡ ሴት ፡ ለአምኃ ፡ ኢየሱስ ፡ ጻሰርጓ ፡ አሳልፎ ፡ የሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ እንዲያደርግ ፡ መስጠቱን ፡ ሚስቱ ፡ ብርሃን ፡ ዘመዳ ፡ ላባቷ ፡ ለንጉሡ ፡ መንገሯን ፡ አባቱዋም ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምደ ፡ መስቀልን ፡ ቢጠይቀኣት ፡ በቃሉ ፡ ስለኣመነ ፡ በዚሁ ፡ ጥፋትና ፡ በሌላም ፡ ባልተገለጸ ፡ በብዙ ፡ ኃጢአቱ (በፖለቲካ?)የተነሣ ፡ ከጥፋት ፡ ጓደኞቹ ፡ ከአምኃ ፡ ኢየሱስ ፡ ጻዕርጓና ፡ ከደብረ ፡ ዳሞው ፡ ንቡረ ፡ ዕድ ፡ ከኖብ (በኋላ ፡ ከበሮ ፡ ሰይጣን ፡ ተብሎ ፡ የተሠየመው)ጋር ፡ እንደተቀጡ ፡ ይገልጻል። ከተቀጡ ፡ በኋላ ፡ በግዞት ፡ የሄዱበት ፡ አገር ፡ የዓምደ ፡ መስቀል ፡ አውራጃው ፡ አምሐራ ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ በተለይ ፡ ሥፍራው ፡ ከንጉሡ ፡ ከራሱ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ የሚያውቅ ፡ እንደሌለው ፡ አምኃየስና ፡ ንቡረ ፡ ዕድ ፡ ኖብ ፡ ግን ፡ በጐሰአሮ፡? እንደተጋዙ ፡ ከዓምደ ፡ መስቀል ፡ በፊት ፡ የብሕት ፡ ወደድነቱን ፡ ሹመት ፡ የያዘው ፡ ኢሳይያስ ፡ ንጉሡ ፡ አምሐራ ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ግዞት ፡ እንዳገኘው ፡ ከዚሁ ፡ ኣያይዞ ፡ ዓምደ ፡ መስቀል ፡ ከተወገደ ፡ ወዲህ ፡ የንጉሡ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ መድኅን ፡ ዘመዳ ፡ የቀኝ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፤ ብርሃን ፡ ዘመዳ (ያምደ ፡ መስቀል ፡ ሚስት) የግራ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ተብለው ፡ መሾማቸውን ፡ ይገልጻል።

ስለዚህ ፡ በዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ባለቤታቸው ፡ ብሌን ፡ ሳባ ፡ ወይም (ሰብአ) ፡ የሚባሉት ፡ ሥይምተ ፡ እንትርታ (እንደርታ) ፡ እየተባሉ ፡ የእንደርታን ፡ አውራጃ ፡ ይገዙ ፡ እንደነበረ ፡ አቱን ፡ ደግሞ ፡ በዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸው ፡ የግራና ፡ የቀኝ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ እየተባሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሥልጣን ፡ ደረጃ ፡ መያዛቸውን ፡ እንረዳለን።

የብሕት ፡ ወደድነት ፡ ሥልጣን ፡ በመጠኑ ፡ በየጊዜው ፡ ሳይለዋወጥ ፡ የቀረ ፡ አይመስልም። ታሪከ ፡ •ነገሥቱ ፡ ትርጓሜውን ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ማለት ፡ ብቻውን ፡ የሚወደድ ፡ ባለሟል ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ ከገለጸ ፡ በኋላ ፡ ሥራውን ፡ አልፎ ፡ ሲናገር ፡ አንዱ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ በውጭ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ሄዶ ፡ ከንጉሡ ፡ በታች ፡ ሙሉ ፡ የጦር ፡ አዝማች ፡ ሆኖ ፡ ሲያዘምት ፡ አንደኛው ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ አገርና ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ጠባቂ ፡ እንደራሴ ፡ መሆኑን ፡

ይገልጽና ፡ ከዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ከእጨጌ ፡ ከጳጳስ ፡ በቀር ፡ በማዕርግ ፡ የሚቀድመው ፡ እንደሌለ ፡ ያስረዳል።

በሸዋ ፡ በነዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ጊዜ ፡ እነ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ በጎንደር ፤ በዓፄ ፡ "ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ ዘመን ፡ እነ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ መልክአ ፡ ክርስቶስ ፤ በዓፄ ፡ በካፋ ፡ ዘመን ፡ እነ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ኤራቅሊስ ፡ እነ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ኣምኃየስ ፡ እንደ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትርነት ፡ የመሰለ ፡ የእንደራሴነት ፡ ሥልጣን ፡ ነበራቸው። አሁን ፡ ግን ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወንዶቹን ፡ እነ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምደ ፡ መስቀልን ፡ ሽረው ፡ ለሴቶች ፡ ልጆቻቸው ፡ መስጠታቸው ፡ በልጆቻቸው ፡ እየተረዱ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣንን ፡ በእጃቸው ፡ ለማድረግ ፡ የፈለጉ ፡ ይመስላል። ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ ባምደ ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ የተረከው ፡ የምንዝርና ፡ ኃጢአት ፡ ለሰበብ ፡ እንጂ ፡ በውስጡ ፡ የፖለቲካ ፡ ጠብ ፡ እንዳለበት ፡ ሲያስረዳ ፡ "በብዙ ፡ ኃጢአትና ፡ በሌላም ፡ ባልተገለጠ ፡ ነገር ፡ ብሎት ፡ ያልፋል። አብዛኛውን ፡ እላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ የብሕት ፡ ወደድነቱን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በአብዛኛውም ፡ አውራጃ ፡ ላይ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ ሲሾሙ ፡ በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ላይና ፡ በታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ላይ ፡ በዝርዝር ፡ ያልተገለጸ ፡ የወንዶቹን ፡ ሹማምንት ፡ የጠረጠሩበት ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ምክንያት ፡ አይጠፋም። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ እንመልከት።

መድኅን ፡ ዘመዳ ፡ ቀኝዕ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡

ብርሃን ፡ ዘመዳ (ያምደ ፡ መስቀል ፡ ሚስት) ግራ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡

በትግራይ (አገር ፡ ግዛት) ድል ፡ ሠምራ፥

በአንጎት ፡ ባሕር ፡ መንግሣ ፡

በግድም ፡ ሶፍያ ፡

በይፋት ፡ ኣመተ ፡ ጊዮርጊስ ፡

በሸዋ ፡ ሮም ፡ ነዬላ ፡

በዳሞት ፡ መድኅን ፡ ዘመዳ ፡ (የማዕረግ ፡ ስም ፡ ቀኝ ፡ ብሕት ፡ ወደድነት ፡ ከተሰጣት ፡ በኋላ ፡ አገር ፡ ግዛት ፡ ደግሞ ፡ የዳሞትን ፡ ኣገር ፡ የተሾመች ፡ የመዠመሪያዪቱ ፡ ትመስላለች።)

በቤገምድር ፡ ፀበላ (ዓባለ?) ማርያም፡
በገኝ? አጽናፍ ፡ ሰገዱ ፡

ከዚች ፡ ከመጨረሻዋ ፡ ከአጽናፍ ፡ ሰገዱ ፡ በቀር ፡ የቀሩት ፡ ሁሉም ፡ ያዔ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ፡ልጆች ፡ መሆናቸውን ፡ አጽናፍ ፡ ሰገዱ ፡ የእኅት ፡ ልጅ ፡ መሆኗን ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸወ ፡ ያረጋግጣል።

ይኸን ፡ ከጻፈ ፡ በኋላ ፡ ወደመጨረሻ ፡ ግድም ፡ ነገር ፡ በእንተ ፡ ሥርዓተ ፡ ሢመታት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ብሎ ፡ በሚጽፈው ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ካለው ፡ ትንሽ ፡ ልዩነት ፡ እያደረገ ፡ ይጽፋል።

ብርሃን ፡ ዘመዳ ፡ የግራ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡
መድኅን ፡ ዘመዳ ፡ የቀኝ ፡
ድል ፡ ሠምራ ፡ በትግሬ ፡
ባሕር ፡ መንግሣ ፡ በኣንጎት ፡
ፀበለ ፡ ማርያም (በፊት ፡ ዓባለ ፡ ማርያም ፡ ብሎ ፡ ነበር) በቤገምድር፡
ኣመተ ፡ መሢሕ (በፊት ፡ አልነበረችም) በአምሐራ ፡
ሶፍያ፡ በግድም፡
ሮም፡ገነዬሳ፡ በሸዋ፡
ኣጽናፍ፡ሰምራ፡ (ኣልነበረችም) በጐዣም፡
ቴዎድሮስ ፡ የዣን፡ ሰበር ፡ ራስነት ፡

ይኸን ፡ ዝርዝር ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ኣስቀድሞ ፡ በያውራጃው ፡ የንጉሡ ፡ ቃለ ፡ ሐፄ (ምስለኔ ፡ ዳኛ?) እንደነበረ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ራሳቸው ፡ ንጉሡ ፡ እንደቃለ ፡ ሐፄ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ ገድ ፡ ይስጣናቸው ፡ የሚባሉት ፡ አገሩን ፡ አጥፍተው ፡ እንደዘረፉትና ፡ ክርስቲያንነታቸውን ፡ ትተው ፡ አይሁድ ፡ እንደሆኑ ፡ ብዙ ፡ ያማራ ፡ ሰው ፡ እንደገደሉ ፡ ንጉሡም ፡ ሊዋጉዋቸው ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ አይለው ፡ እንደመለሱዋቸው ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ እንዳቃጠሉ ፡ ይገልጻል። ይኸን ፡ ከገለጸበት ፡ ቀጥሎ ፡ እነሱ ፡ ቀርተው ፡ በነርሱ ፡ የተተካውን ፡ የሚተርከው ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ነው። በዚያም ፡ ላይ ፡ የሰጠው ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ እንደሰጠው ፡ ያለ ፡ የሴቶቹ ፡ ኣገረ ፡ ገዥዎች ፡ ወይም ፡ የነርስ ፡ ገድ ፡

ይስጣን? አገር ፡ በማጥፋታቸው ፡ ሳይሆን ፡ ለጣዖት ፡ በመስገድና ፡ በሌላም ፡ ይልታወቀ ፡ ምክንያት (ዙረን ፡ ተቀናቅነው ፡ ወይም ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ አድመው ፡ ይሆናል) ከተቀጡ ፡ በኋላ ፡ የየአውራጃውን ፡ ጠቅላላ ፡ ሥልጣን ፡ የቤተ ፡ ክህነቱን ፡ ሳይቀር ፡ ንጉሡ ፡ በእጃቸው ፡ አድርገው ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ እንደሾሙ ፡ ያስረዳል።

የአዲሱ፡ሹመት፡እንደዚህ፡ነው።

በሸዋ ፡ የራቅ፡ማሰሬ ፡ (ጽራግ–ጽራጅ፡ማሰሬ)

በፈጠጋር ፡ አዛዥ፡ በፈጠጋር ፡ በመላው ፡ መልከኛ ፡ ዓምደ ፡ ሚካኤል፡

ፈረገለ ፡ አዳምነት?

በደዋሮ ፡ አዋራሪ ፡

በጅርና ፡ በግብር ፡ ምድር ፡ ሄገኖ (የእስላም ፡ ነክ ፡ በሆነው ፡ አገር ፡ የሚሰጥ ፡ ሹመት ፡ ነው።)

| | |
|---|---|
| በወጅ ፡ | ሄገኖ ፡ |
| በዳሞት ፡ | ዕራቅ ፡ ማሰሬ ፡ |
| በጐዣም ፡ | ዕራቅ ፡ ማዕሬ ፡ |
| በቤገምድር ፡ | ዕራቅ ፡ ማሰሬ ፡ |
| በትግሬ ፡ | ዕራቅ ፡ ማሰሬ ፡ |
| በቅዳ? | ዕራቅ ፡ ማዕሬ ፡ |
| በኣንጎት ፡ | ራቅ ፡ ተማስሬ ፡ |
| በአምሐራ ፡ | ጻሕፈ ፡ ላም ፡ |

በገኝ፣ በግድም ፡ በይፋት፣ ራቅ ፡ ማሰሬ።

በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ደግሞ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ዓምኃ ፡ ጽዮን ፡ የሚባል ፡ የንጉሡ ፡ ፍጹም ፡ ወዳጅ (ባለሟል) እንደነበረ ፡ እርሱም ፡ ወደቤቱ ፡ ሲገባ ፡ ከቤቱም ፡ ሲወጣ ፡ ማንም ፡ የሚያየው ፡ እንዳልነበረ ፡ ወደቤቱ ፡ ዩ ፡ ወይም ፡

፫ ፡ ወጣቶች ፡ ብቻ ፡ ገብተው ፡ ያገለግሉት ፡ እንደነበሩ ፡ ይኸም ፡ ሁሉ ፡ መሆኑ ፡ ወደንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይገባ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ መንግሥቱን ፡ ለማክበር ፡ እንደሆነ ፡ ይገልጻል። ከዚሁም ፡ አያይዞ ፡ እንደርሱ ፡ ውስጥ ፡ ብላቴኖች ፡ የሚባሉት ፡ ከሰው ፡ እንደማይገናኙ ፡ በንጉሡ ፡ ሴት ፡ ለዘወትር ፡ እንደሚኖሩ ፡ ወደውጭ ፡ ሲወጡም ፡ ሲገቡም ፡ መልከኛ ፡ እንደሚከተላቸው ፡ በኑሯቸውም ፡ ንጉሡ (ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ ከሴት ፡ እንደማይገናኙ ፡ የራሳቸውንም ፡ ጠጕር ፡ እንደማይላጩ ፡ ያደፈ ፡ ልብስ ፡ እንደማይለብሱ ፡ ድንገት ፡ እሰው ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ በሉ ፡ ጠጡ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረባቸው ፡ እንደሆነ ፡ እነሱም ፡ ተቀባዩም ፡ እንደሚገደሉ ፡ ይገልጻል።

በሥር ፡ ዝምረን ፡ የዚህን ፡ የሹመት ፡ ሁኔታ ፡ እንመርምር። ናፖሌዎን ፡ የፈረንሳዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ኤስፖኝንና ፡ ቤልክን ፡ ሆላንድንና ፡ የጣልያንን ፡ አውራጃዎች ፡ ሁሉ ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ በያገሩ ፡ ወንድሞቹንና ፡ የእህቶቹን ፡ ባሎች ፡ እንደሾመ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የየአውራጃው ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ በልጆቻቸው ፡ እጅ ፡ እንዲገባ ፡ እንዳሰቡ ፡ ይታያል። ከተሿሚዎቹም ፡ ብዙዎቹ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸው ፡ ስለሆኑ ፡ ወንዶቹን ፡ ልጆቻቸውን ፡ የጠረጠሯቸው ፡ ይመስላል። ወንጆቹ ፡ ቀርቶ ፡ ሴቶቹም ፡ እነሆ ፡ ሸፍተው ፡ እንዳወኩ ፡ ተገለጸ። ገድይስጣን ፡ የሚባለው ፡ የሴቶቹ ፡ ሹም ፡ አገር ፡ ያጠፋው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ሊግባኝ ፡ ኣልቻለም።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸው ፡ ከሸፈቱባቸው ፡ በኋላ ፡ ሥልጣኑን ፡ ሁሉ ፡ እንደገና ፡ በእጃቸው ፡ አግብተው ፡ በርሳቸው ፡ ስም ፡ ለጊዜው ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ ዕራቅ ፡ ማሠሬ ፡ ወይም ፡ ጻሕፈ ፡ ላህም ፡ የሚባለውን ፡ ማዕርግ ፡ እየሰጡ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ልከዋል ፡ ማለት ፡ ነው።

የንጉሡ ፡ ባለሟል ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓቱና ፡ የውስጥ ፡ ብላቴኖች (የልፍኝ ፡ አሽከሮች) ከሴት ፡ እንዳይገናኙ ፡ እሰው ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ እንዳይበሉ ፡ እንዳይጠጡ ፡ የተደረገው ፡ ከሴት ፡ ከተገናኙ ፡ ወይም ፡ እሰው ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ከበሉ ፡ ከጠጡ ፡ ከሰው ፡ መወዳጀትና ፡ መፋቀር ፡ ከሰውም ፡ ከተወዳጁ ፡ ዘንድ ፡ ምሥጢራዊ ፡ ወሬ ፡ እያዋጡ ፡ መጨዋወት ፡ የማይቀር ፡ ስለሆነ ፡ እነዚህ ፡ የልፍኝ ፡ አሽከሮች ፡ በምድረ ፡ ግቢው ፡ የተደረገውን ፡ ንጉሡ ፡

የሚያደርገውን ፡ አየን ፡ ወይም ፡ የተናገረውን ፡ ሰማን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እንዳያወጡና ፡ ምስጢር ፡ መባከንና ፡ መናቅ፣ መደፈር ፡ እንዳይደርስ ፡ የተደረገ ፡ ዘዴ ፡ ነው። እንኳን ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ ፩ ፡ አንዶቹ ፡ የዛሬም ፡ ዘመን ፡ ነገሥታትና ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የቅርብ ፡ ሠራተኞቻቸውና ፡ ባለሟላቸው ፡ ከሰው ፡ ግንኙነት ፡ የሚያበዛውንቱ ፡ እንደሚጠሉት ፡ እንደሚያስወግዱት ፡ ስብስብና ፡ ጭምት ፡ የሆነውን ፡ አጥብቀው ፡ እየወደዱ ፡ በሹመት ፡ ከፍ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ የታወቀ ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፴፪።

## የማሂኮ ፡ ሽፍትነትና ፡ ፍጻሜው።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሹምሽር ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ከግርማ ፡ መንግሥታቸውና ፡ ይላቸው ፡ ታላቅነትየተነሣ ፡ ሰውሁሉ ፡ እንደተንቀጠቀጠላቸው ፡ ለመግለጽ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጸሐፊው ፡ «ወርዕዱ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ እምግርማ ፡ መንግሥቱ ፡ ወእምዕበየ ፡ ኃይሉ ፡ ይላል። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከዚሁ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደሚተርከው (የሐድያው ፡ ገራድ ፡ ለመንግሥቱ ፡ የሚገባውን ፡ ግብር ፡ ይዘህ ፡ ና ፡ ተብሎ ፡ ቢጠራ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትህም ፡ አልመጣ ፡ ከአገሬም ፡ አልወጣ ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ላከ። ይኸም ፡ የሐድያ ፡ ገራድ ፡ ስሙ ፡ ማሂኮ ፡ ይበላል። እርሱም ፡ የንግሥት ፡ ዣን ፡ ዛላ (ዕሌኒ?) የቀኝዕ ፡ በዓልቲሐት ፡ ወንድም ፡ የገራድ ፡ መሐመድ ፡ ልጅ ፡ ነው። ከሐድያ ፡ ሹማምንት ፡ አንዱ ፡ ገንይቾ ፡ ገራድ ፡ የሚባለው ፡ የማሂኮን ፡ እምቢታ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በችኮላ ፡ ከኣገሩ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ መጣና ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ፡ «ማሂኮ ፡ ለጦርነት ፡ በጣም ፡ ተዘጋጅቷል። ደዋሮንና ፡ ባሊን ፡ ለማጥፋት ፡ መጥቶ ፡ ይረዳው ፡ ዘንድ ፡ ከአዳሎችም ፡ ባላባት ፡ ጋር ፡ ተላልኳል። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ መልሰው ፡ የሐድያ ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ኣብሯልን ፡ ወይስ ፡ ግማሹ ፡ ነውን ፡ እስኪ ፡ የሚሻለውን ፡ ምክር ፡ አምጣ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት። እርሱም ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ፡ ጉደላ ፡ ገራድና ፡ ዲሆ ፡ ገራድም ፤ ሐደቦ ፡ ገራድም ፡ ነህ ፡ ገራድም ፡ ሰጋገራድሥ ፡ ገብ ፡ ገራድም፣ ፡ ቀብኤን ፡ ገራድም ፡ ጎገላ ፡ ገራድም

፡ ሀለብ ፡ ገራድም ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ተባብረዋል። ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ አሁን ፡ የሚሻለው ፡ ያባቱን ፡ ወንድም ፡ ገራድ ፡ ባሞን ፡ ከዴገን ፡ ጥራና ፡ በሐድያ ፡ ሹመው። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የገራድ ፡ ማሂኮ ፡ ምክሩም ፡ ኃይሉም ፡ ይበላሸበታል።

ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ገራድ ፡ ባሞን ፡ ካኣለበት ፡ ከዴገን ፡ ምድር ፡ ድረስ ፡ ዘፍጥነት ፡ ልከው ፡ ኣስመጡትና ፡ በደብረብርን ፡ ሳሉ ፡ የሐድያ ፡ ገራድ ፡ ብለው ፡ ሾሙት። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለርሱና ፡ ለገንይቾ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩሽልማት ፡ ሸልመው ፡ በፀር ፡ ሾተል ፡ የሚባሉትን ፡ የዳሞት ፡ ኣገር ፡ የጦር ፡ ክፍሎችን ፡ ጨምረው ፡ ወደ ፡ ሐድያ ፡ ላኰዋቸው። ለባሌና ፡ ለደዋሮ ፡ ሕዝብ ፡ ገራድ ፡ ማሂኮ ፡ አምልጧችሁ ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ እንዳይሸሽ ፡ ተጠንቀቊ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተላለፈ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጥሩምባ ፡ ተነፋ። ብዙዎችም ፡ መነኮሳትና ፡ ካህናት ፡ ተሰበሰቡ ፡ በየቤተክርስቲያናቸውም ፡ ጸሎትና ፡ ምሕላ ፡ እንዲይዙ ፡ ለየአብያተክርስቲያናቱም ፡ ዕጣን ፡ ልብስም ፡ ለድሆች ፡ እንዲሰጥ ፡ ታዘዘ። ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ «ይኸን ፡ ከሐዲ ፡ አስረው ፡ አምጥተው ፡ እፊቴ ፡ ሲያቆሙት ፡ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ በሕልሜ ፡ እመቤቴ ፡ እግዝእትነ» ፡ ማርያም ፡ አሳየችኝ ፡ ይህ ፡ ሕልሜ ፡ እንዲፈጸምልኝ ፡ ወደ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ጸልዩልኝ ፡ ብለው ፡ ለቅዱሳኑ ፡ ነገሩ።

ገራድ ፡ ባሞ ፡ ከንጉሡ ፡ የተሰጠውን ፡ ሠራዊት ፡ ይዞ ፡ ሐድያ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ ሸፍተው ፡ የነበሩት ፡ ሹማምንት ፡ ሁሉ ፡ እየመጡ ፡ ገቡለት ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሰምቶ ፡ ማሂኮ ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ አገር ፡ ለመሸሽ ፡ ሲጓዝ ፡ ቀዳሞት ፡ ደሀፊ ፡ የሚባሉት ፡ ተከታትለው ፡ እስከ ፡ ገባበት ፡ አምባ ፡ እስከ ፡ ስጋ ( ፡ ምድር ፡ ዘልቀው ፡ ደረሱበት። እርሱም ፡ ልብሱንና ፡ ገንዘቡን ፡ ሲሻሙ ፡ የሚመለሱለት ፡ መስሎት ፡ በየመንገዱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልብስና ፡ ግምጃ ፡ ገንዘብ ፡ በተነላቸው። ነገር ፡ ግን ፡ እነርሱ ፡ በዚህ ፡ ሳይመለሱ ፡ እገባበት ፡ አምባ ፡ ድረስ ፡ ገብተው ፡ በጽኑ ፡ ወግተው ፡ ገደሉት ፡ ከዚያም ፡ እራሱን ፡ እጁንና ፡ እግሩን ፡ ቆረጡት። የዚህም ፡ ወሬ ፡ በንጉሡ ፡ በዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘንድ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ እንደፋሲካ ፡ ሰሞን ፡ በማኅሌት ፡ በዘፈን ፡ ደስታ ፡ ተደረገ ፡ ......ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሐድያው ፡ ገራድ ፡ ባሞና ፡ እነዚህ ፡ ዳሞት ፡ ሀዳሪ ፡

የሚባሉት ፡ የማሂኮን ፡ የተቆረጠ ፡ ራሱን ፡ እግሩንና ፡ እጁን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ መጡና ፡ እፊታቸው ፡ ቆመው ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ተናገሩ (የጦርነቱን ፡ ሁኔታ ፡ ተረኩ) ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ገራድ ፡ ባሞን ፤ ገንይቾ ፡ ገራድን ፡ ዳሞት ፡ ሀዳሪን ፡ አመሰገኗቸው። መብልና ፡ መጠጥም ፡ እንደአሰኛቸው ፡ ለየአንዳንዳቸው ፡ አዘዙላቸው። የከሐዲው ፡ ጭንቅላቱ ፡ እግሩና ፡ እጁ ፡ በቀንዕ ፡ ደጅ ፤ በግራ ፡ ደጅ ፡ በሥርጉን? ደጅተሰቀለ። ...ከቲንሽ ፡ ጊዜም ፡ በኋላ ፡ ሁሉንም ፡ ሽልማት ፡ እየሸለሙ ፡ በየአገራቸው ፡ ሰደዱዋቸው። የገንይች ፡ ገራድን ፡ ግዛት ፡ እስከ ፡ ልጅ ፡ ልጁ ፡ ድረስ ፡ የሐድያ ፡ ገራድ ፡ አይግዛው ፡ ብለው ፡ አዘዙለት። ማሂኮን ፡ በፀር ፡ በሾተል ፡ ጦርና ፡ ጐራዴ) ለገደለው ፡ ለባሞ ፡ ገራድ ፡ ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ ጉልት ፡ ሰጡት።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ በገለጸልን ፡ ታሪክ ፡ የምንረዳው ፡ የይፋቱና ፡ የዓዳሉ ፡ ባላባቶች ፡ ዓፄ ፡ አምደ ፡ ጽዮንንና ፡ ተከታዮቻቸውን ፡ እየሸፈቱ ፡ ያውኩ ፡ እንደነበሩ ፡ አሁን ፡ ደግ ፡ ሥ ፡ የሐድያው ፡ ገራድ ፡ ከዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ለመነጠል ፡ ማሰቡን ፡ ነው። እርሱም ፡ ሃይማኖቱ ፡ እስላም ፡ በመሆኑ ፡ ባለፈውም ፡ ወደፊትም ፡ በምናገኘው ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የሐድያ ፡ ገራዶች (ባላባቶች) ከሃይማኖት ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ከይፋትና ፡ ከአዳል ፡ ባላባቶች ፡ ጋር ፡ እየተባበሩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥትን ፡ ሲያውኩ ፡ ኖረዋል።

ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ይኸን ፡ ማሂኮ ፡ የሚባለውን ፡ የሐድያ ፡ ባላባት ፡ በዝምድና ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ እንዲደባለቅና ፡ ታማኝ ፡ ዜጋ ፡ ለማድረግ ፡ አስበው ፡ እህቱን ፡ አግብተው ፡ ቀኝዕ ፡ በኣልቲሐት ፡ ብለው ፡ ሠይመው ፡ ደንበኛ ፡ ሚስት ፡ አድርገዋል። ዳሩ ፡ ግን ፡ የግዛትና ፡ የሥልጣን ፡ ምኞት ፡ ያጠቃውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የጋብቻና ፡ የዝምድና ፡ ገመድ ፡ አሥሮ ፡ ሊያኖረው ፡ አይችልምና ፡ እነሆ ፡ ሸፍቶ ፡ አልገብርም ፡ አልገዛም ፡ ሲል ፡ እንመለከታለን። ዝምድናው ፡ ፈርሶ ፡ አልገብርም ፡ ብሎ ፡ ሲሸፍት ፡ የማጥቂያ ፡ መንገድ ፡ በሚፈልጉበት ፡ ጊዜ ፡ የገዛ ፡ ወገኑ ፡ መካር ፡ የገዛ ፡ ዘመዱ ፡ አገሩን ፡ ተሾሞ ፡ ሸፍታውን ፡ በዘመዱ ፡ እንዳስጠቀኈት ፡ ስንመለከት ፡ «አለያይተህ ፡ ግዛ ፡

የሚባለው ፡ የሮማውያን ፡ ዘዴ ፡ «የሰው ፡ ጠላቱ ፡ ቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ የጌታችን ፡ ንግግር ፡ ትዝ ፡ ሳይለን ፡ ኣያልፍም።

# ምዕራፍ ፡ ፴፫።

## የቤት ፡ ሥራና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዓትና ፡ ደንብ።

የዚህን ፡ የጦርነት ፡ ሁኔታ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉን ፡ ጸሐፊው ፡ የደብረ ፡ ብርሃንን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሥራ ፡ ይቀጥላል። የደብረብርሃንን ፡ ከተማና ፡ የሥላሴን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የመሠረቱም ፡ በዘመናቸው ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ናቸው ፡ በዚሁም ፡ የተነሣ ፡ ዛሬም ፡ ካህናቱ.... ወካህናቲሃ ፡ ለደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ እንተ ፡ ይእቲሀገሩ ፡ ለዘርዓ ፡ ያዕቆብ ( ፡ ይላሉ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የምናነበው ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ በዚያው ፡ በተሠራው ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ኣዲስ ፡ የሚሠራ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ አዳራሽ ፡ ይመስላል ፡ ጸሐፊው (...ኣዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ከመ ፡ ይጽናዕ ፡ ጀጉል ፡ .... » ብሎ ፡ ይዠምራል ፡ ጀጉል ፡ ምናልባት ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ አጠራር ፡ የቤተመንግሥት ፡ ወይም ፡ የአዳራሽ ፡ ቅጥር ፡ ስም ፡ ይሆናል ፡ ቃሉን ፡ እንመልከት። (ማገሩ ፡ በ፲ ፡ በ፲ ፡ ሆኖ ፡ ጽኑ ፡ ቍመቱም ፡ ረዥም ፡ መልኩ ፡ ነጭ ፡ ፀዓዳ ፡ እንዲሆን ፡ የዚህ ፡ ግብረ ፡ ጀጉላ (የዚህ ፡ የቤት ፡ ሥራ) ሳያልቅየቀኝ ፡ ራቅ ፡ ማሰሮችም ፡ የግራራቅ ፡ ማሰሮችምየዚህን ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩት ፡ ዣን ፡ ማሰሬዎችም ፡ የሹመት ፡ ቀሚሳቸውን ፡ እንዳይለብሱ። በቤተ ፡ አንበሳ ፡ ደጅ ፡ አጠገብ ፡ ሌላ ፡ ንጉሡ ፡ በፈረሱ ፡ እንደተቀመጠ ፡ ሊወጣና ፡ ሊገባበት ፡ የሚችል ፡ ኣዳራሽ ፡ በሸልማት ፡ ደጅ ፡ ቲንሽ ፡ ሰቀላ ፡ ቤት ፡ በመብልዕ ፡ ደጅም ፡ እንደዚሁ ፡ ኣንዲት ፡ ሰቀላ ፡ እንዲሠራ ፡ ታዘዘ ፡ በፀርዋጀት (እልፍኝ?) ደጅ ፡ ግን ፡ ሰቀላ ፡ የለውም ፡ በፀርዋጀት ፡ ውስጥ ፡ ከዓቃቤ ፡ ሰዓትና ፡ ከሕፃናት (የልፍኝ ፡ ኣሽከሮች?) ከማዕድ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይገባበትም። ሌላ ፡ ለመግባት ፡ ቢጠጋ ፡ በጦር ፡ ይወጋል።

የንጉሡ ፡ መቀመጫ ፡ ቤትም ፡ እንደዚሁ ፡ በሚያምር ፡ ተሠርቶ ፡ ሲያልቅ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ የወርቅ ፡ መስቀል ፡ ተደረገበት። በንጉሡ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ወርቅ ፡ ማድረግም ፡ የተዠመረው ፡ በዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ ነው። ከንጉሡ ፡ ቤት ፡ በታች ፡ በኵል ፡ ፫ ፡ ደበና (ድንኳን) ተተከለ። የመካከለኛው ፡ ደበና ፡ ዱለት ፡ ቤት ፡ በቀኝ ፡ በኵል ፡ ያለው ፡ በዓለ ፡ ግምጃ ፡ ደባና ፤ በግራ ፡ በኵል ፡ ያለውን ፡ ኣቂት ፡ ደመና ፡ ብለው ፡ ሠየሙት። .....ለቤቱ ፡ ሥራ ፡ ዕንጨት ፡ የሚመጣበት ፡ አገር ፡ ዜጋ (ምድረ ፡ ዜጋ)ይባላል ፡ ከክብደቱና ፡ ከውፍረቱ ፡ የተነሣ ፡ አንዱን ፡ ዕንጨት ፡ ፪ ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ተሸክሞ ፡ የሚመጣው። ዙሪያውን ፡ ኣንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ግንድ ፡ ተጠጋግቶ ፡ በታጠረው ፡ ላይ ፡ የሰው ፡ ዓይን ፡ የሚያልፍበት ፡ ቀዳዳ ፡ የለም ፡ ነበር። ልጡም ፡ ከላዩ ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ ስለተላጠ ፡ መልኵ ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ነጭሆኖ ፡ ይታይ ፡ ነበር። ቍመቱ ፡ ፳ ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ ፲፫ ፡ ነው ፡ የሚሉም ፡ አሉ (ጸሐፊው ፡ እንዳልከነዳው ፡ ይገልጻል) ።

ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደጃፍ ፡ የሚደርስ ፡ ግራና ፡ ቀኝትልቅ ፡ አጥር ፡ ተሠራ ፡ ይኸም ፡ የተሠራበት ፡ ምክንያት ፡ ንጉሡ ፡ ሲወጣና ፡ ሲገባ ፡ ሰው ፡ እንዳያየው ፡ ነው። በዚት ፡ መንገድ ፡ ከራሱ ፡ ከንጉሙ ፡ ከዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ ከውስጥ ፡ ብላቴኖች ፡ ንዑሳን (የውስጥ ፡ ታናናሽ ፡ የልፍኝ፡አሽከሮች) በቀር ፡ የሚያልፍ ፡ የለም። በቍርባንም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲገባ ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፤ ከደብረ ፡ ማርያም ፤ ከቢዘን ፤ ከደብረ ፡ ገሊላ ፡ የሃሎሄ ፤ ከቀየዳ ፤ ከመለጎ ፤ ከደረባ ፡ ዓባይ ፤ ከፀዓዳ ፡ አምባ፣ ከዋልድባ ፤ ከደብረ ፡ ማርያም ፤ ገርዓልታ ፤ ከሕንፃ ፡ ማርያም ፡ መምህራንና ፡ መነኰሳት ፡ መዘምራን ፡ በቀር ፡ ደብተሮች ፡ አይገቡም። ......መምህራኑና ፡ መነኰሳቱ ፡ ሥጋ ፡ የማይበሉ ፡ ጠጅ ፡ የማይጠጡ ፡ ናቸው። በበዓል ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ደብተሮቹ ፡ ሁሉ ፡ ከደብረ ፡ ብርሃንም ፡ ከደብረ ፡ ነጐድጓድ ፤ ከየለባሽ ፤ ከጋርማ ፤ ከ**ኢየሱስ** ፡ ደብተራ ፤ ከግምጃ ፡ ቤት ፡ ማርያም ፤ ከመስቀል ፡ መጥተው ፡ ውስት (ቅኔ?) ይውላሉ ፡ የቍርባን ፡ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ሁሉንም ፡ በየሥፍራቸው ፡ ይልኳቸዋል። እገባሬ ፡ ሠናዩ ፡ ውስጥ ፡ ከዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ ገብረ ፡ አልፋና ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡

ከሚባሉት ፡ ከሁለቱ ፡ ልጆቹ ፤ ከሊቀ ፡ ደብተራ ፡ ገብረ ፡ **ኢየሱስ** ፡ ይስሐቅ ፡ ከሚባል ፡ ከአንድ ፡ ድሀ ፡ በቀር ፡ የሚገባ ፡ የለም። ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ቁርባን ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የሚያገለግሉት (የሚቀድሱት?) እነዚህ ፡ ፫ቱ ፡ ናቸው።

ንጉሡ ፡ ከቍርባን ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ በ (ቅኔ)ማኅሌት ፡ የነበሩት ፡ ደብተሮች ፡ ይጠሩና ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አዳራሽ ፡ መካበቢያ ፡ ያስገቡዋቸዋል። ከዚያ ፡ ከ፫ቱ ፡ ደበና ፡ አንዱን ፡ ላዕላይ ፡ ፊት ፤ የታችኛውን ፡ ለዣን ፡ ቤት ፡ ጠባቂ ፡ የተመደበውን ፡ ታሕታይ ፡ ፊት ፡ ይሉታል ፤ ካህናቱ ፡ የሚጋበዙት ፡ በላዕላይ ፡ ፊት ፡ ነው። ምግቡና ፡ መጠጡ ፡ እየመጣ ፡ የሚዘጋጀው ፡ ከቤተ ፡ ፈጠጋርና ፡ ከግራ ፡ በዓልቲሐት ፡ ዘንድ ፡ ነው። ካህናቱ ፡ የተዘጋጀውን ፡ ግብር ፡ እፈቀዳቸው ፡ ድረስ ፡ በልተው ፡ የሞቀና ፡ የቀዘቀዘውንም ፡ መጠጥ ፡ ጠጥተው ፡ ሲጠግቡ ፡ የተረፋቸውን ፡ ተሸከመው ፡ ወደ ፡ መኖሪያቸው ፡ ይሔዳሉ። የማዕዱን ፡ ሥርዓት ፡ ከንጉሡበቀር ፡ ማንም ፡ ቆጥሮ ፡ ሊያዳርሰው ፡ ኣይችልም። የጠላው ፡ ዓይነት ፡ አንዱ ፡ ጽሩይ (የጠራ) ፪ተኛው "ኢታርፍድ ፡ ሦስተኛው ፡ ጸላ ፡ ሐፄ (የንጉሥ ፡ ጠላ) ይባላል። ጸላ ፡ ሐፄ ፡ የተባለውን ፡ በንጉሡ ፡ ቃል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለማንም ፡ አይሰጥም። ጸጅ (ጠጅ)የሐዣ ፡ የሚባለውን ፡ ጸጅ ፡ አበዛ ፡ ይሉታል።

በፀርዋጀት ፡ በድል ፡ ደመና ፡ በድል ፡ ሾተል ፡ የሚባሉትን ፡ የጨዋ ፡ ወገኖች ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ግብር ፡ ያበሉዋቸዋል። ሁለተኛ ፡ ደግሞ ፡ በፀር ፡ ሾተል ፤ ድብ ፡ ምልዓት ፡ ዣን ፡ ምልዓት ፤ በድል ፡ መብረቅ ፡ በድል ፡ መስቀል ፡ በአዳል ፡ ዣን ፡ አቂት ፡ በአምባ ፡ በአዳል ፡ ዋዢት ፡ ደመና ፡ አምባ ፡ በባሕር ፡ ዋገት ፡ በአዳል ፡ መብረቅ ፡ የሚባሉት ፡ የንጉሡን ፡ ምድረ ፡ ግቢ (አጥር) ከበው ፡ የሚያድሩት ፡ የጨዋ ፡ ወገኖች ፡ በዚሁ ፡ በላዕላይ ፡ ፊት ፡ ግብር ፡ ይበላሉ።

ከደበና ፡ ዠምሮ ፡ በግራ ፡ በኰል ፡ እስከ ፡ አለው ፡ እስከ ፡ ንጉሡ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ ቍመቱ ፡ ፻፶ ፡ ወይም ፡ ፻፴ ፡ ክንድ ፡ የሚሆን ፡ መጋረጃ ፡ ይጋረዳል። የሚገረፍም ፡ የሚወቀስም ፡ ሰው ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ነው። ዣን ፡ ቤት ፡ ጠባቂ ፡ ታሕይ ፡ ፊት ፡ በሚባለው ፡ ቤት ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ሥፍራ ፡ አይቆሙም። በዚህ ፡ በላዕላይ ፡ ፊት ፡ የሚገቡና ፡ የሚሠሩ ፡ ጽራግ ፡ ጠባቂ ፤

ዣን ፡ ደረባ ፡ ናቸውአዛዦችም ፡ ከመልከኛና ፡ ከመነኰሳት ፡ ከደጋግ ፡ ከትግሬ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በዚሁ ፡ ይሠራሉ። ወደታችኛው ፡ ቤት (ታሕታይ ፡ ፊት) በወረዱ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ያዛሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዋናው ፡ ሥልጣናቸው ፡ በላይኛው ፡ ቤት (ላዕላይ ፡ ፊት) ነው።

እነዚህ ፡ አዛዦች ፡ ሁሉ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመቀበል ፡ ንጉሡ ፡ ወዳለበት ፡ ሲገቡ ፡ በፍርሐትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ በጕልበታቸው ፡ ተንበርከው ፡ መሬት ፡ ይስማሉ ፤ ትእዛዙንም ፤ (ቃሉን) በሰሙ ፡ ቍጥር ፡ እንደዚሁ ፡ ነው። ቀላሚ ፡ ኳፍሬ ፤ ሾቀጤ? ፡ የሚባለውን ፡ እንጂ ፡ አዛዦቹም ፡ ጌቶቹም ፡ ሊቀ ፡ መጣኒም ፤ ዣን ፡ ማሰሮችም ፡ ኢ.ቃቂታችም ፤ ዣን ፡ ሐፀናም ፡ ዣን ፡ ቤት ፡ ጣባቅያንም ፡ ልብሳቸው ፡ የተለየ ፡ ነው። እነሱም ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ በየሥፍራቸው ፡ ቆመው ፡ ሌትም ፡ ቀንም ፡ ሳያጓድሉ ፡ በታሕታይ ፡ ፊት (በታችኛው ፡ ቤት) ሌሊት ፡ ፋና ፡ ያበራሉ። በላዕላይ ፡ ፊት (ላይኛው ፡ ቤት) ጵራን ፡ ጠባቂና ፡ ዣንደረቦች ፡ ከሰም ፡ የተሠራ ፡ ጧፍ ፡ ይዘው ፡ ይቆማሉ። ፋና (ፓናተፋኖስ) በታሕታይ ፡ ፊት ፡ እንጂ ፡ በላይኛው ፡ አይገባም። ..... ዣን ፡ ቤት ፡ ጠባቂ ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ይሠራል። እረፍትም ፡ ከቲንሽ ፡ ጊዜ ፡ በቀር ፡ የለውም.... ንጉሡ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲሄድ ፡ ማንም ፡ አያየውም። ንጉሡበስውር ፡ ማንም ፡ ሳያውቀው ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ብላቴና ፡ ይወጣና ፡ በድል ፡ ሾተል ፡ በፀር ፡ ሾተል ፡ በድል ፡ ደመና ፡ በፀር ፡ ዋጀት ፤ በደመና ፡ ኣምባ ፤ በአዳል ፡ ዋጀት ፤ በድል ፡ መብረቅ ፤ በድል ፡ መስቀል ፡ ለሚባሉት ፡ ለጨዋ ፡ ክፍሎች (ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጦር ፡ ሹማምንት) ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለፉ ፡ ብሎ ፡ ይነግሯቸዋል። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጥሩምባ (ኣቅርንት) ነጋሪት (ቀንደ ፡ ከበሮ) እየመቱ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሄዱና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ደጃፍ ፡ ይቆማሉ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ አይችሉም። የቢዘን ፡ መነኮሳት ፡ ሰይፍና ፡ ገለብ (አፎት) ይዘው ፡ የአዳል ፡ መብረቅ ፡ ቀስትና ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ ይጠብቃሉ። የቍርባኑ ፡ ሥርዓት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ለጨዋዎች ፡ እስኪጠግቡ ፡ ድረስ ፡ ሕብስትና ፡ መጠጥ ፡ ይሰጧቸዋል።

ንጉሡ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለርሱ ፡ በተለየው ፡ መንገድ (ስርቆሽ ፡ በር) እንደዚያው ፡ ከዓቃቤ ፡ ሰዓቱና ፡ ከውስጥ ፡ ብላቴኖች ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሳያየውና ፡ ሳያውቀው ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ይመለሳል። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብላቴናም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ ይልና ፡ ለነዚያ ፡ ጨዋ ፡ ለሚባሉት ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ወታደሮችና ፡ አለቆች ፡ ንጉሡ ፡ ከቤተክርስቲያን ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ መግባቱን ፡ ለማስረዳት ፡ በእጁ ፡ እየጠቀሰ ፡ ያመለክታቸዋል። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጥሩምባ ፡ እየተነፋ ፡ ነጋሪቱ ፡ እየተጐሸመ ፡ ግማሹ ፡ ሆ ፡ እያለ ፡ ግማሹ ፡ እንዳገሩ ፡ እና ፡ እንደየቋንቋው ፡ እየዘፈነ ፡ ታላቅ ፡ ጩኸትና ፡ ድምፅ ፡ ግርማው ፡ የሚያስፈራ ፡ የዘፈን ፡ የደስታ ፡ ሁካታ ፡ ይደረጋል። ከዚያ ፡ ሁሉም ፡ ወደየሥፍራው ፡ በሰላም ፡ እንዲሄድ ፡ ከየአለቃው ፡ ትእዛዝ ፡ ይቀበላል።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በምድረ ፡ ግቢውአጥር ፡ ውስጥ ፡ ናዝሬት ፡ የሚባለው ፡ ትልቍ ፡ ድንኳን ፡ ይተከላል። በርሱም ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ በየ፸ ፡ ከዚህም ፡ የሚበዛ ፡ ድንኳን (ትርሽ?) ይተከላል። በዚያም ፡ ውስጥ ፡ ከመላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለ ፡ ግብርና ፡ ስለመታያ ፡ የመጣው ፡ ገንዘብ ፡ ማለፊያ ፡ ማለፊያው ፡ የሚጠቅመው ፡ እየተመረጠ ፡ እየገባ ፡ ይቀመጣል ፤ የተረፈው ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ በረከት ፡ ቤት ፡ ወደሚባለው ፡ ክፍል ፡ እየሄደ ፡ ይቀመጣል። ከዚያ ፡ ለሽልማትም ፡ ለሌላም ፡ ጒዳይ ፡ የሚሆነው! ፡ ዕቃና ፡ መሣሪያ ፡ ልብስ ፡ ከናዝሬት ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ቤትና ፡ ወደ ፡ በረከት ፡ ቤት ፡ በትእዛዝ ፡ እየሄደ ፡ ለሽልማት ፡ የሚሆነውንና ፡ ለቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ አዋቂዎቹ ፡ እየሰፉ ፡ ጌጥ ፡ እየጨመሩ ፡ ያዘጋጃሉ። ለማዕድ (ገበታ) የሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ ከግብር ፡ ቤትና ፡ ከግራ ፡ በዓልቲሐት ፡ ዘንድ ፡ ይመጣል። በተረፈ ፡ ቀኝ ፡ በዓልቲሐት ፡ በዓልተ ፡ ሽሕና ፡ የገላግል ፡ ገዜት ፤ ወሰርበት ፡ ቤት ፡ ቀይስ ፡ ሐፄ ፡ ሊቀደብተራ ፡ ጽራግ ፡ ማሰሬ ፡ ሊቀ ፡ መጫኒ፣ ፡ ሊቀ ፡ ቃቂታች ፤ አልጅሆ ፡ በዓልዳሞ ፡ ማርያም ፡ ወልታ ፡ ሐፄም ፡ የሚሰጡት ፡ በናዝሬት ፡ ቤት ፡ በግራና ፡ በቀኙይገባና ፡ ከዚያ ፡ እየወጣ ፡ ለደብተራ (ካህናት) ለጨዋ (ለወታደር ፡ ንጉሡ ፡ ላዘዘለት ፡ ሁሉ ፡ ከመብሉም ፡ ከጠላውም ፡ ከጠጁም ፡ ጸላ ፡ ሜስ ፡ ወይዳት1 ፡ ሻናሜ ፡ ሞገርያ ፡ ከሚባለው ፡ ከመጠጥና ፡ ከመብል ፡ ዓይነት ፡ ይሰጣል ፡

"የነበረው (ለካህንና ፡ ለወታደር)ሲሰጥ ፡ አዲስ ፡ የመጣው ፡ ወደ ፡ ናዝሬት ፡ ቤት ፡ ይገባል።

በደበና (ድንኳን) ላይኛው ፡ መንገድ ፡ ከንጉሡቤት ፡ በታች ፡ ኣጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ለፈረሶች ፡ ሰቀላ ፡ ቤት ፡ ተሠርቶ ፡ ሰው ፡ እንዳያያቸው ፡ በዚያ ፡ ያቆሟቸዋል።

ከነርሱም ፡ መካከል ፡ ኮርቻ ፡ ተጭነው ፡ ልጓም ፡ እንደተላጐሙ ፡ ተዘጋጅተው ፡ የሚቆሙ ፡ አሉባቸው (ለድንገተኛ ፡ ለሚያፋጥን ፡ ትእዛዝ) ዝንበር ፡ ከጠለቀች ፡ ዝምሮ ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስካህናት (ቀሳውስት?) የንጉሡን ፡ ቤት ፡ ዙሪያ ፡ እየዞሩ ፡ ማየ ፡ ጸሎት (ጠበል) ይረጫሉ። ከካህናቱ ፡ ውስጥ ፡ ወንጌል ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ፤ ክህደተ ፡ ሰይጣን ፤ **እግዚአብሔር** ፡ ነግሥን ፤ ለመድገም ፡ ችሎትና ፡ ሥርዓት ፡ ያላቸውን ፡ መርጠው ፡ ከአምሐራ ፡ ከአንጎት ፡ ያመጧቸዋል። በፍርዱ ፡ በጽድቀ ፡ በሃይማኖቱ ፡ የቀኑ ፡ ሰዎች ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ሥራይ ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስቡ ፡ ሰዎች ፡ ስለአሉ ፡ ካህናቱ ፡ የጸሎቱን ፡ ወሀ ፡ ከመርጨት ፡ ቀንም ፡ ሌሊትም ፡ ኣያርፉም ፡ ነበር። ንጉሡ ፡ ራሱ ፡ በመንገድም ፡ ሲሔድ ፡ በቤትም ፡ ሳለ ፡ ሥራይ ፡ እንደጣሉበት ፡ በቃሉም ፡ ተናግሯል ፡ በመጽሐፉም ፡ ጽፎታል......።

ንጉሡ ፡ ለጉዞ ፡ ከደበና ፡ ቤቱ (ከቤተ ፡ መንግሥቱ) ሲወጣ ፡ ትልቅ ፡ ግርግርታ ፡ ይሆናል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከፊቱ ፡ እየፈራ ፡ ይሸሻል። ታላላቅ ፡ ድባብ ፡ የሚይዙለት ፡ ፫ ፡ ሰዎችና ፡ ጭራ ፡ የሚይዙ ፡ ብቻ ፡ ይጠጉታል"ሽማ (ሰንደቅ ፡ ዓላማ?) ተሸካሚዎችም ፡ በሩቀ ፡ በርሱ ፡ ዙሪያ ፡ እያጀቡ ፡ ይጓዛሉ ፡ በጉዞ ፡ ቀን ፡ በፈረስ ፡ እንጂ ፡ በበቅሎ ፡ አይቀመጥም። ምስርቃና (ባለጥሩምባ)ድብ ፡ አንበሳ (ባለነጋሪት)ከፊትና ፡ ከኋላ ፡ በሩቅ ፡ ሆነው ፡ እየነፉና ፡ እየመቱ ፡ ንጉሠ ፡ ሲጓዝም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ሲገባም ፡ ይከተላሉብሎ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ይጨርሳል።

ምንም ፡ እንኳን ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ የየክፍሉስም ፡ የሹማምንቶቹ ፡ የማዕርግና ፡ የክፍል ፡ ስማቸው ፡ በትክክልና ፡ በግልጽ ፡ የማይገባ ፡ ቢሆን ፡

ይህ ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ አብዛኛው ፡ ጊዜ ፡ ጦርነትን ፡ ብቻ ፡ ከሚተርኩት ፡ እርሱ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ሥርዓትና ፡ ደንብ ፡ የብዙ ፡ ክፍሎችና ፡ የሹማምንት ፡ ስም ፡ እየጨመረ ፡ መጻፉ ፡ ቍም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ነው። የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ የቤተ ፡ ክህነቱ ፡ የሹማምንቱ ፡ ስማቸው ፡ ሥርዓትና ፡ ደንባቸው ፡ ከዛሬው ፡ ጋር ፡ የሚጋጠምም ፡ የሚለያይም ፡ አለ። ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ የነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ ካላንበት ፡ ፭፻ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ርቆ ፡ ሲገኝ ፡ በ፭፻ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ቋንቋም ፡ እንደ ፡ ሥርዓትና ፡ እንደ ፡ ደንብ ፡ እየተለዋወጠ ፡ ይሔዳል። አማርኛ ፡ በዚያን ፡ ሰዓት ፡ ሠልጥኖ ፡ የሕዝብ ፡ ቋንቋ ፤ ግዕዝ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የምንችልበት ፡ መንገድ ፡ ዝግ ፡ ነው። በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ ንግግሩ ፡ በግዕዝ ፡ ሆኖ ፡ የነገሩ ፡ የዕቃው ፡ የሥርዓቱ ፡ የደንቡ ፡ የሹመቱ ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ ከግዕዝ ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ስለሆነ፣በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ የአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ምልክት ፡ የሚገኘው ፡ በልክ ፡ ነው። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አማርኛ ፡ ከዛጕዬ ፡ መንግሥት ፡ ወዲህ ፡ ተዠመረ ፡ የሚሉ ፡ አሉ። ብዙዎች ፡ ከግዕዝ ፡ ተወለደ ፡ የሚሉ ፡ አንዳንዶች ፡ ከግዕዝ ፡ ጋር ፡ ጓደኛ ፡ ሆኖ ፡ አብሮ ፡ ተፈጥሮ ፡ ቋንቋ ፡ አድርጎ ፡ የያዘው ፡ ነገድ ፡ ኣለው ፡ የሚሉ ፡ ኣሉ። ምናልባት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከግዕዝና ፡ ከዛሬው ፡ አማርኛ ፡ ተከልሶ ፡ የሚናገሩበት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ቋንቋ ፡ ይኖራል። ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈ ፡ ጽሑፍ ፡ በፍጹም ፡ አላየሁምና ፡ ዓይነቱን ፡ በትክክል ፡ ለማመልከት ፡ አልችልም። ምልክት ፡ የሚሰጠን ፡ ለነዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ለነዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ለኀሁ ፡ ላፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያቆብም ፡ የተገጠመው ፡ ግጥም ፡ ብቻ ፡ ነው።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ከመዠመሪያው ፡ ላይ ፡ ጀጕል ፤ በፀርዋጀት ፡ ደበና ፡ ቤተ ፡ ኣንበሳ ፤ ቤተ ፡ ዱለት ፤ በዓላ ፡ ግምጃ ፡ ደበና ፤ አቄት ፡ ደመና ፡ ላዕላይ ፡ ፊታሕታይ ፡ ፊት ፡ የሚለው ፡ በዛሬ ፡ አነጋገራችን ፡ ቤተመንግሥት፣ ኣዳራሽ ፡ እልፍኝ፣ራስጌው ፡ ቤት ፤ ዕንግዳ ፡ መቀበያ ፡ ግብር ፡ ቤት ፤ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ማድ ፡ ቤት .... እንደሚባለው ፡ ነው። በፀር ፡ ዋጀት ፤ በድል ፡ ደመና ፡ በድል ፡ ሾተል ፤ በፀር ፡ ሾተል ፤ ድብ ፡ ምልዓት ፤ ዣን ፡ ምልዓት፣በድል ፡ መብረቅ.... የሚባሉት ፡ መድፈኛ ፡ ጠበንጃ ፡ ያዥ ፡ ሰይፈ ፡ ዣግሬ ፡ መሐል ፡ ሰፋሪ ፡ ወርዋሪ ፡ እንደሚባሉት ፡ ዓይነት ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ያሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡

የንጉሡ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ አለቆች ፡ ናቸው። ባነጋገሩ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሹም ፡ ስም ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ ስም ፡ ይመስላል። በፀርዋጀት ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ የቤት ፡ ስም ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ኣለቃ ፡ መስሎ ፡ ይታያል። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አለቃውን ፤ ጭፍራውን ፡ የተመደበበትን ፡ ሥፍራ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ስም ፡ ይጠሩታል። ይኸም ፡ ኣዳል ፡ መጣ ፡ ሲሉ ፡ ሰዎቹን ፡ ወይም ፡ ሹሙን ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ አገር ፡ ሄደ ፡ ሲሉ ፡ አገሩን ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ዓይነት ፡ ነው።

በተረፈ ፡ በውስጡ ፡ የሚጠራቸውን ፡ ሹማምንት ፡ የዓቃቤ ፡ ሰዓቱን ፡ የቀይስ ፡ ሐፄውን ፡ የሊቀ ፡ ደብተራውን ፡ የሊቀ ፡ መጫኒ (መጣኒ ፡ መጽዐኒውን) ተግባርባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ የገለጽነው ፡ ያመለክታል ፡ " ፡ በዚህላይ ፡ የምንመለከተው ፡ ባፄ ፡ ላሊ ፡ በላ ፤ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡን ፡ ባለቤት ፡ በዓልተ ፡ ቢሐት ፡ ይል ፡ የነበረው ፡ አሁን ፡ የዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በዓልቲሐት ፡ ሲለው ፡ ይገኛል። ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ባልቲሐት ፡ የሚል ፡ ይገኛል ፤ ምናልባት ፡ የፊተኛው ፡ የግዕዝኛውን ፡ ቃል ፡ የጠበቀ ፡ ያሁኑ ፡ ወደዘመኑ ፡ አማርኛ ፡ የተጠጋ ፡ ይሆናል። በየዘመኑ ፡ የቦታም ፡ የማዕርግም ፡ ስም ፡ በመጠኑ ፡ ይለዋወጣል። በኋላ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፡ የተባለው ፡ ቀድሞ ፡ መልአከ ፡ ወይም ፡ መላኬ ፡ ባሕር ፡ ይባል ፡ እንደነበረ ፡ ተመልክተናል። ከዚህም ፡ የበለጠ ፡ የአንዱን ፡ ባለሥልጣን (ዳኛ)ስም ፡ ሊቀ ፡ መጽኣኒ ፡ ሊቀ ፡ መጣኒ ፡ ሊቀ ፡ መጫኒ ፡ ሊቀ ፡ መጣን .... እያለ ፡ መጽሐፍ ፡ ሁሉ ፡ ግማሹ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ግማሹ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ እየሳበ ፡ ይጠራዋል።

፪ኛ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ የምንረዳው ፡ ቀኝ ፡ በዓልቲሐት ፡ ግራበ ፡ ዓልቲሐት ፡ ከሚባሉት ፡ ከሁለቱ ፡ ከንጉሡ ፡ ባለቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ለግብር ፡ ለመብልና ፡ ለመጠጥ ፡ የሚሆነውን ፡ በሥልጣኗ ፡ የምታዘጋጅ ፡ የግራዋ ፡ ባለቤት ፡ ግራ ፡ ባልቲሐት ፡ የምትባለዋ ፡ ናት። ጽሑፉ ፡ ወውእቱ ፡ ማዕደ ፡ ኀብስት ፡ ወሜስ ፡ ይበውእ ፡ እምነ ፡ ቤተ ፡ ፈጠጋር ፡ ወእምቤተ ፡ ግራ ፡ በዓልቲሐት ፡ ይላል። ነግር ፡ ግን ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ በንጉሡ ፡ ሥልጣን ፡ በየጊዜው ፡ የሚለዋወጥ ፡ ስለሆነ ፡ ኣንዱ ፡ ንጉሥ ፡ ያቆመውን ፡ ተከታዩ ፡ ብዙ

፡ ጊዜ ፡ ስለሚያፈርሰው ፡ ይኸንንም ፡ የጸና ፡ ደንብ ፡ አድርገን ፡ ልንመለከተው ፡ አንችልም።

# ምዕራፍ ፡ ፴፬።

## የጨዋ ፡ ድልድልና ፡ በአክሱም ፡ ጽዮን ፡ የተደረገ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ።

ጨዋ ፡ በታወቀው ፡ የአማርኛ ፡ ንግግር ፡ በሥርዓት ፡ ያደገ ፡ ከብልግና ፡ የራቀ) ማለት ፡ ነው። እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስም ፡ ወደፊት ፡ ሹመትና ፡ ደረጃ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱለማግኘት ፡ አስቀድመው ፡ ባሽከርነት ፡ ለማገልገል ፡ የሚገቡት ፡ የመኳንንትና ፡ የሹማምንት ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ጨዋ ፡ እየተባሉ ፡ አለቃ ፡ እየተደረገላቸው ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር። በዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ (ምናልባትም ፡ ከዚያ ፡ በፊት) ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ በሹመትም ፡ በብዛትም ፡ የሚኖሩ ፡ ይመስላል። እነርሱም ፡ በያለበት ፡ ተከፋፍለው ፡ የሚኖሩ ፡ የወታደር ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው። ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ ከመሔዳቸው ፡ በፊት ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጨዋ ፡ የሚባሉትን ፡ በያገሩ ፡ እንደደለደሉና ፡ እንደላኩ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይገልጻል።

«የቀድሞዎቹ ፡ ጨዋ ፡ ዣን ፡ ጸገና ፡ የሚባሉት ፡ ከዓመጹበት (ትዝኀሩ) ወዲህ ፡ አርቋይ ፡ በጹር ፡ ዋጀት ፤ በድል ፡ ጸገና ፡ በአዳል ፡ አምባ፣ በድል ፡ ድብ ፤ በድል ፡ ነድ ፤ በኣዳል ፡ መብረቅ ፤ ደረቆ ፡ በፀር ፡ ዋጅት ፤ ዣን ፡ ገደብ ፡ ሌሎችም ፡ ስማቸው ፡ ያልታወቀውን ፡ በደዋሮ ፡ አገር ፡ ደልድለው ፡ ላኩ።

የቀድሞዎቹ ፡ ጥፋት ፡ አጥፍተው ፡ ወቀሳና ፡ ቍጣ ፡ እየፈሩ ፡ ወደአዳል ፡ ይሸሹ ፡ ነበር። ስለዚህ (ንጉሡ?) እንደዚህ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው። «የሰጠናችሁ ፡ አዝማች ፡ እየገረፈ ፡ ቢያሰላጥናችሁ ፡ እየተቆጣችሁ ፡ ወደ ፡ እስላም ፡ አገር ፡ ሔዳችሁ ፡ በኛና ፡ በአዝማቹ ፡ ላይ ፡ ትመኩበት ፡ ነበር። አሁን ፡ ግን ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ ሌሎች ፡ አዲሶች ፡ ጨዋ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ እንዳዘዘን ፡ ልከንላችኋል። የቀድሞውን ፡ ክፉታችሁን ፡ ትታችሁ ፡ በሥርዓትና ፡ በሕግ ፡ ኑሩ። እምቢ ፡

ያላችሁ ፡ እንደሆነ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ እንደአሰብነው ፡ ቅጣት ፡ እንፈርድባችኋለን። ከደዋሮም ፡ ሌላ ፡ በሐድያ ፤ በባሊ ፤ በቤገ ፡ ምድር ፤ በጐዣም፤በፈጠጋር ፤ በይፋት ፤ በግድምበበኝ ፤ በአንጎት ፤ በቅጻ ፤ በትግሬ ፡ ባሕር ፡ አምባ፤ በሳራዋ (ሠራዩ?) በፀር ፡ ዋጅት ፡ በእነዚህ ፡ ሁሉ ፡ አገሮች ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ በያገራቸው ፡ ክፍልና ፡ ስም ፡ እየሰጡ ፡ ጨዋን ፡ ደልድለው ፡ ላኳቸው።

ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽን ፡ ከሁሉም ፡ ሹማምንት ፡ ከፍ ፡ ያለሹመትና ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥተው ፡ በጣም ፡ ኣሳደጉት። በውስጡ ፡ የሺሬን ፡ ሹም (ሥዩመ ፡ ሲሬ) የሠራዬን ፡ ሹም (ሥዩመ ፡ ሰራዌ) ሁለቱን ፡ የሐማሴን ፡ ከንቲቦች ፡ የቡርንም ፡ ሹም (ሥዩመ ፡ ቡር?) በበላይ ፡ እንዲገዛቸው ፡ ሥልጣን ፡ ሰጡት ፡ ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ በሙሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሥርዓትን ፡ እያሳመሩ ፡ አደሱት። ይኸውም ፡ አዲስ ፡ ሥርዓት ፡ ብርሃን ፡ ሆኖ ፡ በጨለማው ፡ ላይ ፡ ኣበራ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሣችን ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እንደ ፡ አባቶቻቸው ፡ ነገሥታት ፡ የንግሥን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓትን ፡ ለመፈጸም ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ በወረዱ ፡ ጊዜ ፡ የአገሩ ፡ ሕዝብና ፡ ካህናት ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተቀበልዋቸው። የትግሬ ፡ ሹማምንቱና ፡ ጨዋው (ወታደሩ) በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ጋሻና ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ሴቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደቀድሞ ፡ ልማዳቸው ፡ ዘፈን ፡ እየዘፈኑ ፡ ወደበሩ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜም ፡ የትግሬ ፡ መኰንንና ፡ የአክሱም ፡ ንቡረ ፡ ዕድ (ነብር ፡ እድ) ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ሆነው ፡ የወይራ ፡ ዝንጣፊ ፡ እንደ ፡ ሕጋቸው ፡ ይዘው ፡ ተቀበልዋቸው። ስለዚህ ፡ ትግሬ ፡ መኰንን ፡ ዓቃቤ ፡ ጽንጽንያ ፡ ይባላል። ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ ቅጽር ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እየረገጡ ፡ እንዲያልፉበት ፡ በተዘረጋው ፡ ሥጋጃ ፡ ላይ (ላዕለ ፡ ብሳጥ ፡ ወማኪ?) ያመጡትን ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ በተኑት። የበተኑት ፡ ወርቅ ፡ ፻ (መቶ) ወቄት (ኅልቅ) ይሆናል። ከዚያ ፡ የተረፈው ፡ ፶ ፡ ወይም ፡ ፴ ፡ ይሁን ፡ አይታወቅም። ንጉሡ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ማድረጋቸውና ፡ እንደቀድሞ ፡ ኣባቶቻቸው ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ መስጠታቸው ፡ ስለ ፡ ጽዮን ፡ ክብር ፡ ሲሉ ፡ ነው። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የእመቤታችን ፡ የማርያም ፡ ዕረፍቷ ፡ በዋለበት ፡ በጥር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ እድንጋዩ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሡን ፡ ፈጸሙ። የዚህም ፡ የደንጊያው ፡ ዙፋንና ፡ የሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ሥፍራ ፡ ቅጥር ፡ ተበጅቶለት ፡ ለብቻው ፡ ይኖራል። ከዚያ

፡ ደግሞ ፡ ንጉሡ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ የሚባረኩበት ፡ ደንጊያ (ዙፋን") ለብቻው ፡ አለ። በተረፈ ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ፲፪ቱ ፡ ዳኞች (በዓለ ፡ ሕግ) የሚቀመጡበት ፡ የደንጊያ ፡ ወንበር ፡ ይገኛል ፡ የጳጳሱም ፡ መቀመጫ ፡ በዚሁ ፡ ስፍራ ፡ ነው። ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በዚያው ፡ ሳሉ ፡ የቤተክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ አቋቋሙ። ቀድሞ ፡ ያልነበረውን ፡ የሳታት ፡ ጸሎት ፡ በየጊዜው ፡ እንዲያደርጉ ፡ ኣዘዙ ፡ ብዙ ፡ መነኮሳትንም ፡ ሰብስበው ፡ ማኅበር (ገዳምን) ፡ ኣበጁ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ኣክሱም ፡ የሚል ፡ ሥያሜ ፡ ጨምረው ፡ ሹም ፡ ሾሙ። ለዚሁም ፡ ማኅበር (ገዳም?) በናዕዴር ፡ ምድር ፡ የሚገኝ ፡ መሬት ፡ ሰጡ። ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ማድረጋቸው ፡ ስለእመቤታችን ፡ ስለ ፡ ማርያም ፡ ፍቅርና ፡ ለልጃቸው ፡ ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲሆን ፡ ብለው ፡ ነው። መምህራንንም ፡ እያስመጡ ፡ በዚሁ ፡ እየተከሉ ፡ አስቀመጧቸው። ለቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ብዙ ፡ ልብስና ፡ የወርቅ ፡ ሰን (ኵስ ፡ ኵስት) ሰጡ። እንደዚህ ፡ ኣድርገው ፡ አሮጌውን ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ኣድሰው ፡ በደስታ ፡ አክሱምን ፡ ከሞሏት ፡ በኋላ ፡ በሰላም ፡ ተመለሱ። በሚመለሱበት ፡ ጊዜ ፡ አምሐራ ፡ አገር ፡ በተለይ ፡ ፀሐያ ፡ እሚባለው ፡ ምድር ፡ ሲደርሱ ፡ አንድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ያማረ ፡ ለደብር ፡ የሚመች ፡ ሥፍራ ፡ ኣገኙና ፡ ደስ ፡ አላቸው። በዚህም ፡ ሥፍራ ፡ በምሥራቅ ፡ በኵል ፡ አባታቸው ፡ ዳዊት ፡ ቤተ ፡ መቅደስ (ቤተ ፡ ክርስቲያን) ለማሠራት ፡ አስቦ ፡ ያስዠመረውን ፡ ትንሽ ፡ ግንብ ፡ አዩ። ዳዊት (የ፳ኤል ፡ ንጉሥ) የ**እግዚአብሔር**ን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በዘመኑ ፡ ለመሥራት ፡ አስቦ ፡ ሳይሆንለት ፡ ቀርቶ ፡ ልጁ ፡ ሰሎሞን ፡ በኋላ ፡ ምኞቱን ፡ እንደፈጸመ ፡ አሁንም ፡ ለአባታቸው ፡ ሳይቻል ፡ የቀረውን ፡ ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በዚሁ ፡ ደብር (ተራራ) በምዕራብ ፡ በኵል ፡ ለማሠራት ፡ በቶሎ ፡ ደሀውም ፡ ጌታውም ፡ ሹማምንቱ ፡ ሁሉ ፡ ደንጊያ ፡ እንዲያግዙ ፡ ኣዘዙና ፡ ሥራው ፡ በቶሎ ፡ ተዠምሮ ፡ በቶሎ ፡ ኣለቀ። ኣምረው ፡ የተሠሩትን ፡ ሁለት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ አንዱን ፡ መካነ ፡ ጎል ፤ አንደኛውን ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ብለው ፡ ሰየሙት። ብዙ ፡ ካህናትና ፡ ደብተራም ፡ ተተከሉ ፡ ርስትም ፡ ተሰጣቸው። ለደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኮሳትም ፡ እንደዚሁ ፡ ርስት ፡ ጨምረው ፡ በማኅበር (ገዳም) እንዲሠሩ ፡ አሰማሩዋቸው። የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ሥራና ፡ የካህናቱን ፡ ድልድል

፡ ሥርዓቱን ፡ ሁሉ ፡ አከናውነው ፡ የእመቤታችን ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲከበር ፡ አልባሳትም ፡ ሰጥተው ፡ ሥራውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ሲጓዙ ፡ መዠመሪያ ፡ ወደነገሡበት ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ደጎ ፡ ደረሱ። በዚያም ፡ የእመቤታችንን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አሠሩና ፡ ከሌላው ፡ አገር ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሥራው ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፡ መካነ ፡ ማርያም ፡ ብለው ፡ ሠየሙትና ፡ ብዙ ፡ ጒልት ፡ ሰጥተው ፡ በውስጡ ፡ **እግዚአብሔር**ን ፡ እያመሰገኑ ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ካህናት ፡ ተከሉ። ይህቺንም ፡ የመካነ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፍሬ ፡ ማርያም (ዣን ፡ ኃይላ) ለምትባለው ፡ ለግራ ፡ ባልቲሐት (የግራ ፡ ሚስቱ)

መታሰቢያም ፡ መቀበሪያም ፡ እንዲሆናት ፡ ሰጧት። ግራ ፡ ባልቲሐት ፡ ፍሬ ፡ ማርያምም ፡ የብርሃን ፡ ዘመዳ ፡ የመድኅን ፡ ዘመዳ ፡ የፀበለ ፡ ማርያም ፡ የድል ፡ ድባባ ፡ እናት ፡ ነች። እንዳሰበውም ፡ ፍሬ ፡ ማርያም ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ተቀበረች።

በነገሡ ፡ በ፰ኛው ፡ ዓመት ፡ ከአምሐራ ፡ ተመልሰው ፡ ተጒለት ፡ በተለይ ፡ እጉባ ፡ እሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ደርሰው ፡ የጥምቀትን ፡ ሕግ ፡ ሠርተው ፡ ይህንኑ ፡ ሥፍራ ፡ ስለ ፡ ወደዱት ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ተቀመጡ። በዚህም ፡ ሳሉ ፡ በምስር (ግብፅ) አገር ፡ እመቤታችን ፡ በገሀድ ፡ እየታየችው ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ስላሳመነች ፡ እስላሞቹ ፡ የደብረ ፡ ምጥማቅን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አቃጥለው ፡ ኣፈረሱት ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ከአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘንድ ፡ መጣ። ይኸንንም ፡ ንጒሡ ፡ ሲሰሙ ፡ ከሠራዊታቸውም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ኣስቀድሞ ፡ ከመጡት ፡ ነጋድያን ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ አዝነው ፡ ኣለቀሱ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የራሳቸውንም ፡ ልብ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ ያዘኑትንም ፡ ሁሉ ፡ የሚያጽናኑበትን ፡ ሲያስቡ ፡ ቆዩና ፡ ቀጥሎ ፡ እንደዚህ ፡ ኣሉ። «የክርስቲያን ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፡ በምስር (በግብፅ) ደብረ ፡ ምጥማቅን ፡ አፈረሷት ፡ ብላችሁ ፡ አትዘኑ ፡ አታልቅሱ ፡ እኛ ፡ እዚህ ፡ የቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠርተን ፡ ስሙንም ፡ ደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ ብለን ፡ እንሠይመዋለን። »

ይኸን ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሥራ ፡ እንዲዠመር ፡ ኣዘዙ። ሥራውም ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ ከተጕለት ፡ ጕልት ፡ ሰጥተው ፡ ካህናቱንም ፡ ደልድለው ፡ ሥርዓቱን ፡ ሁሉ ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ እንደዚያው ፡ እንደተናገሩትና ፡ ልባቸው ፡ እንደተመኘው ፡ ስሙን ፡ ደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ ብለው ፡ ሠየሙት። »

ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ባለፈው ፡ እንደተመለከትነው ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ እንደነገሡ ፡ መዠመሪያ ፡ ስለ ፡ ጣዖትና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አምልኮ ፡ አዋጅ ፡ ማወጃቸው ፡ ቅጣት ፡ መፈጸማቸወ ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ ማድረጋቸው ፡ ማሂኮን ፡ ማስወጋታቸው ፡ የደብረብርሃንን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ማሠራታቸው ፡ ተጽፏል። እንደዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ወደአክሱም ፡ ሄደው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ የፈጸሙት ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ከአደረጉ ፡ በኋላ ፡ መሆኑ ፡ ነው። ጸሐፊው ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የፊቱን ፡ ወደኋላ ፡ የኋለኛውን ፡ ወደፊት ፡ እያደረገ ፡ መደዳውን ፡ በመጻፍ ፡ በሙሉ ፡ የተጠነቀቀ ፡ አይመስልም። ስለዚህም ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ ከቀረው ፡ ሁሉ ፡ በፊት ፡ የአክሱምን ፡ ጕዞና ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ ያስቀድማሉ። የዣን ፡ ባቲስት ፡ ኰልቦ ፡ መጽሐፍም ፡ የሚዠምረው ፡ በሥርዓተ ፡ ንግሡ ፡ ነው። ይኸውም ፡ ፩ ፡ ንጉሥ ፡ ከሁሉ ፡ ኣስቀድሞ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሡን ፡ የመፈጸሙን ፡ የተለመደውን ፡ ጕዳና ፡ በመከተልነው። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ ምናልባት ፡ መንግሥትን ፡ በያዙበት ፡ ዘመን ፡ በምድረ ፡ ደኅ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ማድረጋቸውን ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ይጠቅሣል።

ነገር ፡ ግን ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ከአክሱሙ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸው ፡ በፊት ፡ ሌሎቹን ፡ ሥራዎች ፡ በማስቀደሙ ፡ የተሳሳተ ፡ አይመስልም። ምክንያቱም ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ከወንድማቸው ፡ ልጅ ፡ ከዓምደ ፡ ኢየሱስ ፡ መንግሥትን ፡ እንደተቀበሉ ፡ ወደ ፡ ኣክሱም ፡ ለመሄድ ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደሩ ፡ ጕዳይ ፡ የፈቀደላቸው ፡ አይመስልም። መንግሥትን ፡ እንደተቀበሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ ለማክበር ፡ ሲሉ ፡ በቶሎ ፡ በዚያው ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ኣክሱም ፡ ሄደው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ምናልባት ፡ እግራቸው ፡ ራቅ ፡ ሲል ፡ በመንግሥታቸው

፡ ላይ ፡ የሚነሣ ፡ የነጋሢ ፡ ዘር ፡ ወይም ፡ አልገዛም ፡ ብሎ ፡ የሚሸፍት ፡ ቀንደኛ ፡ ለመንግሥታቸው ፡ ሁከት ፡ ሊፈጥር ፡ ይችል ፡ ነበር። የነቢትወደድ ፡ ዓምደ ፡ መስቀል ፡ ሁከት ፡ ባምልኮ ፡ ቢመካኝም ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም። ስለዚህ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሡን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ እደርስበታለሁ ፡ ለጊዜውም ፡ በምድረ ፡ ደጎ ፡ ኣድርጌያለሁ ፡ ብለው ፡ ኣስቀድሞ ፡ ያመጹትን ፡ በቅጣት ፤ ደስ ፡ ያሰኙዋቸውን ፡ በሹመት ፡ ኣስደስተው ፡ ከአረጋጉ ፡ በኋላ ፡ ደንበኛውን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ለመፈጸም ፡ ወደ ፡ ኣክሱም ፡ ሄደዋል ፡ ማለት ፡ ነው። የሄዱበትም ፡ ጊዜ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ «በነገሡ ፡ በ፯ኛው ፡ ዓመት ፡ ከአምሐራ ፡ ተመልሰው ፡ ተጕለት ፡ ገቡ ፡ » ካለ ፡ ምናልባት ፡ ለሥርዓተ ፡ ንግሡ ፡ በአክሱም ፤ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ ሥራ ፡ በአማራ ፡ አገር ፡ የ፩ ፡ ዓመት ፡ ቢበዛም ፡ የ፪ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ቢወስዱ ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ የሄዱት ፡ በነገሡ ፡ በ፭ኛው ፡ ወይም ፡ በ፮ኛ ፡ ዓመት ፡ በሺ፬፻፲፮ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ ይሆናል። ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዝምሮ ፡ እስከርሳቸው ፡ ድረስ ፡ ከነገሡት ፡ ከ፲፰ቱ ፡ ነገሥታት ፡ አንዱንም ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ ሄዶ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሡን ፡ ኣከበረ ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ የለም። ዓፄ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ደንጐሎ ፡ የሄደ ፡ ጊዜ ፡ አክሱም ፡ ደርሶ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ማክበሩን ፡ ታሪኩ ፡ ኣይገልጽም። ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ግን ፡ ከተጕለት ፡ ተነሥተው ፡ ረዥሙን ፡ ጕዞ ፡ ፈጽመው ፡ አክሱም ፡ "ሄደው ፡ ሥርዓት ፡ ንግሣቸውን ፡ ማክበራቸው ፡ አንድ ፡ ፩ ፡ ያረጀ ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ማደሳቸው ፡ ሲመለሱም ፡ በያገሩ ፡ አንድ ፡ ፩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እየተከሉ ፡ የሕዝቡን ፡ ፍላጎት ፡ መሙላታቸው ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደርንና ፡ ኣንድነትን ፡ ያጸናል።

ኣባቶቻቸው ፡ ያላደረጉትን ፡ አክሱም ፡ ድረስ ፡ ሔደው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ ማክበራቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በጥንታዊነቷና ፡ በታሪኳ ፡ የምታኰራዋን ፡ የአክሱምን ፡ ከተማ ፡ ማየታቸው ፡ ደስ ፡ ያሰኛል። በዚህም ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ይበልጥ ፡ ለዚች ፡ ለታወቀች ፡ ጥንታዊት ፡ ከተማ ፡ ስሟና ፡ ገናንነቷ ፡ እንዳይዘነጋ ፡ እንደገና ፡ ባዲስ ፡ ኃይል ፡ እንዲቀሰቀስ ፡ ማድረጋቸው ፡ ሁሉ ፡ ለታሪክ ፡ ጠቃሚነት ፡ አለው። የርሳቸውንም ፡ ዝና ፡ ያደምቀዋል።

ጸሐፊው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥን ፡ እተረከበት ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ የነገሥበት ፡ የደንጊያ ፡ ዙፋን ፡ ፩ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ የሚባረኩበት ፡ ፲፪ቱ ፡ ዳኞች (በዓለ ፡ ሕግ) የሚቀመጡበት ፡ ፲፪ ፡ የድንጋይ ፡ ወምበር ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ አለ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ከእውነተኛው ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ የተጋጠመ ፡ ነው። እነኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ እነ ፡ ሊትማን ፡ በዚሁ ፡ ሥፍራው ፡ እየዞሩ ፡ ሐውል ፡ ሲመረምሩ ፡ በጠባቂና ፡ በተከባካቢ ፡ እጦት ፡ ግማሾቹ ፡ እየወደቁ ፡ ቢሰባበሩም ፡ ግማሾቹን ፡ በዓይናቸው ፡ እያዩ ፡ ፎቶግራፍ ፡ እያነሡ ፡ በየመጽሐፋቸው ፡ ገልጸውታል። እኔም ፡ ራሴ ፡ በሺ፱፻፵፱ ፡ ዓ.ም ፡ ከፓሪስ ፡ ስመለስ ፡ ዓይቼዋለሁ።

በተረፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ከአክሱም ፡ በአምሐራ ፡ በኵል ፡ አድርገው ፡ ሲመለሱ ፡ የመካነ (ጐልጐልጐታ)ን ፡ የደብረ ፡ ነጐድጓድን ፡ አብያተክርስቲያናት ፡ ሥራ ፡ ኣስፈጽመው ፡ በሚመለሱበት ፡ ጊዜ ፡ በአባታቸው ፡ ዐፅም ፡ የተነሣ ፡ ከሙዋዓል (ሙዋል)ሰዎች ፡ ጋር ፡ ያደረጉትን ፡ ጠብ ፡ በመዠመሪያ ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ የተወውን ፡ ወደመጨረሻው ፡ ባለው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ኣርእስት ፡ አበጅቶ ፡ እንደገና ፡ ይተርከዋል ፡ ይኸም ፡ እንደዚህ ፡ ነው።

"ከአክሱም ፡ ተመልሰው ፡ ያባታቸውንያፄ ፡ ዳዊትን ፡ ዐፅም ፡ ከጽዮን? አስመጥተው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ለማድረግ ፡ መልክተኞች ፡ ወደ ፡ ሙዋል? ሰዎች (ካህናት?) ቢልኩ ፡ አብረ ፡ ዳኢ ፧ ገብሩ ፧ ምጡስ ፡ የሚባሉ ፡ ፃስርጐች (ጸሐሥርጓ ፡ ማለት ፡ ባለወርቅ ፡ ቀለበት ፡ ዳኛ ፡ ነው፡?) የንጉሥም ፡ የጳጳስም ፡ ቃል ፡ ቢመጣባችሁ ፡ የንጉሣችንን ፡ የዳዊትን ፡ ዐፅም ፡ እንዳትሰጡ ፡ ብለዋቸው ፡ ኖሮ ፡ ካህናቱ ፡ እምቢ ፡ ብለው ፡ የንጉሡን ፡ መላክተኞች ፡ መለሱ። ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ተቆጡና ፡ በአዳል ፡ ዣን ፡ የሚባሉትን ፡ ወታደሮች (ጨዋ)ልከው ፡ የእምቢተኞቹን ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ከነሚስቶቻቸው ፡ ከነልጆቻቸው ፡ ማርከው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አመጡዋቸውና ፡ ለምን ፡ የንጉሥ ፡ ቃል ፡ እምቢ ፡ አላችሁ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቋቸው ፡ ፃዕርጓ (ዳኞቹ)አትስጡ ፡ አሉን ፡ ብለው ፡ ኣመካኙ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፫ቱ ፡ ፃስርጓ ፡ ተጠርተው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ቀድሞ ፡ ያባቴን ፡ የዳዊትን ፡ ዐፅም ፡ ከዚህ (ከናንተ ፡ ዘንድ) ለማውጣት ፡ ማሰቤን ፡ ባማከራችሁ ፡ ይሁን ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡

መለሳችሁልኝ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ለማስወሰድ ፡ መልክተኛ ፡ ብልክ ፡ አትስጡ ፡ ብላችሁ ፡ ላገሩ ፡ ሰው ፡ ላካችሁ ፡ ብለው ፡ ወቀሱና ፡ ኣጋዙዋቸው። እነሱም ፡ ዘር ፡ ዘራቸውም ፡ የደብተራነትና ፡ የፃስርኳነት ፡ ደረጃ ፡ እንዳያገኙ ፡ በጽሕፈት ፡ ለኋለኛው ፡ ትውልድ ፡ አስተላለፉባቸው። ያገሩን ፡ ሰዎች (ሙዋል)ግን ፡ ምሕረት ፡ ኣድርገው ፡ ሁሉንም ፡ ወደየአገራቸው ፡ አሰናበቱዋቸው። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዳዊትን ፡ ዐፅም ፡ አስመጡና ፡ ባሠሩት ፡ በደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስቀመጡት።

ጸሐፊው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ላለው ፡ ታሪክ ፡ ምስክር ፡ የሚቆጥረው ፡ ራቅ ፡ ማሠሬ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚባለውን ፡ ነው። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ እነዚህ ፡ ፃስርኳ ፡ የሚባሉት ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ የዳኝነትና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ የሚመሩት ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ባፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሡ ፡ ተጣልተው፣፳፬ቱንም ፡ ሻራቸው ፡ የሚላቸው ፡ እነዚህኑ ፡ ወይም ፡ አባቶቻቸውን ፡ ሳይሆን ፡ ኣይቀርም። እዚያ ፡ ላይ ፡ ስማቸውን ፡ ለ፳ወ፬ቱ ፡ በለዋምባ ፡ ይላቸዋል። ባሁኑ ፡ ላይ ፡ ዋነኞቹን ፡ አዛዦች ፡ ፃስርኳ ፡ ያገሩን ፡ ሰዎች ፡ ሰብአ ፡ ሙዋዓል ፡ ይላቸዋል። ስርኳ ፡ እንደ ፡ ቢትወደድ ፡ ያለ ፡ ሹመት ፡ ያለው ፡ ነው። ፃስርኳ ፡ ሲል ፡ ግን ፡ ዳኞቹን ፡ ወይም ፡ ኣገረ ፡ ገዥዎቹን ፡ ማለቱ ፡ ይሆናል። የንጉው ፡ ዐፅም ፡ እንዳይሔድ ፡ የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ እምቢ ፡ ለማለት ፡ የደፈሩበትን ፡ ምክንያት ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ አይገልጽም። ይሁን ፡ እንጅ ፡ እንደዛሬ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ፩ ፡ ንጉሥ ፡ የነገሠበት ፡ ደብር ፡ የተቀበረበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክብርና ፡ ደረጃ ፡ ኣለው። በዚሁም ፡ ርስተ ፡ ጒልት ፡ ገንዘብና ፡ ልብስ ፡ በየጊዜው ፡ ከወራሲው ፡ ንጉሥ ፡ ይሰጣልና ፡ የስመ ፡ ጥሩው ፡ ንጉሥ ፡ ያፄ ፡ ዳዊት ፡ ዐፅም ፡ ከዚያ ፡ ሲሔድባቸው ፡ የአገሩ ፡ የደብሩ ፡ ክብሩም ፡ ጥቅሙም ፡ እንዳይነካ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ላፄ ፡ ዳዊት ፡ ክብርና ፡ ጥቅም ፡ ከወራሲውና ፡ ከልጃቸው ፡ ከአፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ይበልጥ ፡ አስበው ፡ አይደለም።

በተረፈ ፡ በመዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ዜናመዋዕል ፡ ጸሐፊው ፡ የመካነ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርቶ ፡ መታሰቢያ ፡ መቀበሪያም ፡ እንዲሆናት ፡ ለሚስቱ ፡ ለግራ ፡ ባልቲሐት ፡ ለፍሬ ፡ ማርያም ፡ ሰጣት ፡ ብሎ ፡ የነበረውን ፡ ወደመጨረሻ ፡ ግድም ፡ ባለወ ፡ ላይ ፡ እንደገና ፡ ጒዳዩን ፡ አንስቶ

፡ ሲጽፍ ፡ የመካነ ፡ ማርያምን ፡ ሥራ ፡ ኣሠርቶ ፡ ሲጨርስ ፡ ዣን ፡ ኃይላ ፡ ለምትባለው ፡ ለልጅነት ፡ ሚስቱ ፡ ሰጣት ፡ ይላል። ይኸም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳልነው ፡ እፊተኛው ፡ ላይ ፡ በክርስትና ፡ ስሟ ፡ በፍሬ ፡ ማርያም ፡ እዚህኛው ፡ እሁለተኛው ፡ ላይ ፡ በስመ ፡ መንግሥቷ ፡ ዣን ፡ ኃይላ ፡ ብሎ ፡ የጻፈው ፡ አንዷቷን ፡ ሚስቱን ፡ የመድኅን ፡ ዘመዳንና ፡ የብርሃን ፡ ዘመዳን ፡ እናት ፡ ግራ ፡ ባልቲሐትን ፡ መሆኑን ፡ አንባቢን ፡ እንዳያሳስት ፡ እናስገነዝባለን።

ሙሴ ፡ ዊልያም ፡ ራይት ፡ የሚባሉት ፡ የሎንዶን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መሪ ፡ እንደ ፡ ኤው ፡ ቀጥር ፡ በ፲፰፻ኞቹ ፡ ዓ.ም ፡ የኢትዮጵያን ፡ መጽሐፍ ፡ አወጡበት ፡ ዝርዝር (ካታሎግ) ላይ ፡ ለነዚህ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በዘመናቸው ፡ ላሠሩዋቸው ፡ ኣብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተአምረ ፡ ማርያም ፡ ለማርያም ፡ ገድለ ፡ ላሊበላ ፡ ለመካነ ፡ ጎልጎታ ፡ መስጠታቸውን ፡ በገጽ ፡ ፹፯ና ፡ ፩፻፺፫ ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ያስረዳል ፡ "ወሀብኩ ፡ ኣነ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወስመ ፡ መንግሥትየ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፈ ፡ ገድለ ፡ ላሊበላ ፡ ከመ ፡ ይኲነኒ ፡ መርሐ ፡ ለብሔረ ፡ ተድላ ፡ አመ ፡ ይትጋብኡ ፡ ኣንስርተ ፡ ቆላ ፡ ምስላ ፡ እሊአየ ፡ ያርፍቀኒ ፡ በሣህሉ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘገሊላ ፡ ዘይመልክ ፡ ኲላ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም። ወዓዲ ፡ ዘአውጽኣ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ በተመንግኖ ፡ እመካነ ፡ ጎልጎታ ፡ ቅዱስ ፡ እመሂ ፡ ቀሲስ ፡ ወእመሂርኡስ ፡ ውጉዘ ፡ ፡ ለይኩን ፡ በአፈ ፡ **አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ** ፡ እስከ ፡ ደኃሪት ፡ እስትንፋስ" ። ለማርያም ፡ የተሰጠው ፡ ባንተ ፡ ተኣምረ ፡ ማርያም ፡ ዘአጽሐፈ ፡ ንጉሥነ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወዘወሀበሂ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ለማርያም ፡ ወኢያውጽኡ ፡ እምኔሃ ፡ ...»

ዳሩ ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡ መጻሕፍት ፡ ዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በመቅደላ ፡ ሰብስበዋቸው ፡ ሳለ ፡ ንጉሡ ፡ ራሳቸውን ፡ በሽጉጥ ፡ ገድለው ፡ ሲሞቱ ፡ እንግሊዞቹ ፡ ከመቅደላ ፡ እነዚህኑ ፡ መጻሕፍት ፡ አግኝተው ፡ ከሌሎቹ ፡ መጻሕፍት ፡ ጋር ፡ ሎንዶን ፡ ወስደውታል ፡ ማለት ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፴፫።

## የአሕመድ ፡ በድላይ ፡ ስሙና ፡ የዘሩ ፡ ሐረግ - ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጋር ፡ ተዋግቶ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በርሱ ፡ ሞት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳምና ፡ ሌሎቹም ፡ ኣድባራት ፡ ያገኙት ፡ ስጦታ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ በመካከሉ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የይፋትና ፡ የአዳል ፡ ባላባቶች ፡ ግብር ፡ እየከፈሉ ፡ እየተገዙ ፡ ሰላም ፡ ቢሆንም ፡ ንጉሡም ፡ በሰላማዊው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኣክሱም ፡ ሂደው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ሲያከብሩ ፡ በየመንገዳቸው ፡ ልባቸው ፡ እመረጠው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ካገርና ፡ ከባላባት ፡ ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖችም ፡ እየተማከሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ሲተክሉ ፡ ገዳም ፡ ሲገድሙ ፡ ለገዳማቱና ፡ ለአብያተክርስቲያናቱ ፡ መነኮሳትና ፡ ካህናት ፡ ለመነኮሳቱና ፡ ለካህናቱ ፡ መተዳደሪያ ፡ ርስት ፡ ጕልት ፡ እየደለደሉ ፡ እየሰጡ ፡ ወደተጕለትም ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ይኸንኑ ፡ የመሳሰለውንና ፡ ሌላም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሚያስገድደውን ፡ ያስተዳደር ፡ ሥራ ፡ ሲፈጽሙ ፡ በዚሁ ፡ መካከል ፡ ያ ፡ ባባት ፡ ባያት ፡ በቅድመ ፡ አያታቸው ፡ ጊዜ ፡ ያላቋረጠው ፡ የይፋትና ፡ የአዳል ፡ እስላሞች ፡ ጦርነት ፡ አሁንም ፡ በርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ አለማቋረጡን ፡ እነሆ ፡ ልንመለከት ፡ ነው። የሐድያው ፡ ገራድ ፡ የማሂኮ ፡ ጦርነት ፡ ያሁኑን ፡ ያህል ፡ ስለማያሰጋ ፡ የራሳቸውን ፡ ጦርጬ ፡ ምረው ፡ ለማሂኮ ፡ አጐት ፡ ከነአገሩ ፡ ሰጥተው ፡ ሽፍታውን ፡ ባጐቱ ፡ ያለ ፡ ብዙ ፡ ድካም ፡ እንዳሸነፉት ፡ ባለፈው ፡ ተመልክተናል።

ያሁኑ ፡ ከመሐመድ ፡ በድላይ ፡ ጋር ፡ የሚያደርጉት ፡ ጦርነት ፡ ከዚያ ፡ የበለጠ ፡ አስጊ ፡ በመሆኑ ፡ በመልእክተኛ ፡ ጦር ፡ የማይደፈር ፡ ስለሆነ ፡ ራሳቸው ፡ መዝመታቸውን ፡ እንመለከታለን። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በይፋት ፡ ወላስሞች ፡ አልጋ ፡ የተቀመጠው ፡ ሙሴኮረኔ ፡ ባሴት ፡ ከነማክሪዝ ፡ እንደተረጐሙት ፡ ሙሉ ፡ ስሙ ፡ ሼሃብ ፡ ኤዲን ፡ አህመድ ፡ በድላይ ፡ ነው። *ሔንሪኮ ፡ ቺሩሊ* ፡ ደግሞ ፡ *ከታግሪብርዲ* ፡ እንዳገኘው ፡ በድላይ ፡ ሺሃብ ፡ አድዲን ፡ መሐመድ ፡


ሲል ፡ ከባሴት ፡ የስፍራ ፡ ማዘዋወር ፡ እንጂ ፡ የስም ፡ ልዩነት ፡ የለውም። የማዕርግ ፡ ስሙም ፡ የኣውፋት ፡ ንጉሥ ፡ ነው። የዓረቦቹ ፡ ጽሑፍ ፡ አውፋት ፡ የሚለው ፡ እኛ ፡ በግዕዝና ፡ በአማርኛ ፡ ይፋት ፡ የምንለውን ፡ አገር ፡ ነው። ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ የግዕዙ ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ ግን ፡ ባጭሩ ፡ አርዌ ፡ በድላይ ፡ እያለ ፡ ከማለፍ ፡ በቀር ፡ ሙሉ ፡ ስሙን ፡ አይጠራም። ከሙሉው ፡ ስሙ ፡ ውስጥ ፡ በድላይ ፡ ያለው ፡ ከደንበኛ ፡ ስሙ ፡ የተወሰደው ፡ ትክክል ፡ ነው።

አርዌ ፡ በድላይ ፡ እያለ ፡ ከበድላይ ፡ በፊት ፡ አርዌ ፡ ማለቱ ፡ እባብነቱን (ተንኮለኛነቱን) ለመግለጽ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እመጠሪያ ፡ ስሙ ፡ ውስጥ ፡ ኣርዌ ፡ የሚሉ ፡ ሥያሜ ፡ በፍጹም ፡ የለም። ግዛቱንም ፡ የይፋት ፡ ንጉሥ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ የአዳል ፡ ንጉሥ ፡ ይለዋል። ይኸን ፡ ያለበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ ይፋት ፡ ለሸዋ ፡ ይልቁንም ፡ ለነገሥታቱ ፡ መቀመጫ ፡ ለተጉለት ፡ ቅርብ ፡ ስለሆነ ፡ መልከኛ ፡ ጨዋ ፡ እየሾሙበት ፡ በቅርብ ፡ ሀንው ፡ ስለተቆጣጠሩትና ፡ አሕመድ ፡ በድላይ ፡ ጦር ፡ የሰበሰበውና ፡ የተነሣው ፡ ከይፋት ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ከሚገኘው ፡ ከአዳል ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ የይፋቱ ፡ የወላስማ ፡ ዘር ፡ አይሎ ፡ የአዳሉንም ፡ ደርቦ ፡ ስለሚገዛው ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም።

የዘሩን ፡ ሐረግ ፡ የተመለከትን ፡ እንደሆነ ፡ አሕመድ ፡ በድላይ ፡ የይፋትን ፡ የወላስማ ፡ ዘር ፡ ለመሠረተው ፡ ለዑመር ፡ ወላስማ ፡ ዓሥረኛ ፡ ትውልድ ፡ ነው። ከዑመር ፡ ወላስማ ፡ ወዲህ ፡ የቅድም ፡ አያቱ ፡ አባት (ቅም ፡ አያቱ?) ሳብር ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ መሐመድ (ሰብረዲን)ከዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጋር ፡ ቅድም ፡ አያቱ ፡ አሊ ፡ ካፄ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ (ሰይፈ ፡ አርዕድ) ጋር ፡ አያቱ ፡ ያፄ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ አጐቱ ፡ ሐቅ ፡ አድዲን ፡ ካፄ ፡ ንዋየ ፡ ማርያም (ውድም ፡ አስፈሬ) ጋር፣ ፡ አባቱ ፡ ሰአድ ፡ ዲን ፡ ካዔ ፡ ዳዊትና ፡ ካፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ጋር ፡ ሲዋጉ ፡ ኑረዋል። እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ የዐረቦቹም ፡ የፈረንጆቹም ፡ ጸሐፊዎች ፡ የይፋት ፡ ነገሥታት ፡ ነው ፡ የሚሏቸው ፡ የዘራቸውም ፡ ግንድ ፡ በዘሩ ፡ ሐረግ ፡ እንደምንመለከተው ፡ ያው ፡ የይፋቱ ፡ ወላስማ ፡ ዑመር ፡ ነው።

ከግራኝ አህመድ ኢብን ኢብራአሂም በፊት ሳይመቻቸው እየተገዙ ሲመቻቸው እየሸፈቱ ከኢትዮጵያ ነገስታት ጋር ሲዋጉ የኖሩት የሱልጣን ወላስማ ተከታዮች የሚያሳይ እነ አል ማከኔዚ፤ እነታሃረበርዲ፤ እነ አራብ ፡ ፍቄህ ፡ ጽፈውት ፡ እነ ፡ ባሴት................ እነ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ እነ ኤንሪኮ ፡ ቼሩሊ ፡ ተርጉመው ፡ ካዘጋጁትና ፡ ከኛ ፡ ታሪክ ፡ ነገስት ፡ ውስጥ ፡ ተለቅሞ ፡ ባዲስ ፡ አይነት ፡ የተሠራ ፡ የወላስማ ፡ የዘር ፡ ሐረግ። ከወላስማ ፡ በፊት ፡ አቡ ፡ ታሌካና ፡ አቃዴስ ፡ የሚባሉ ፡ ተርፍው ፡ የዘሩ ፡ መነሻ....... ስልጣን ፡ ከወላስማ ፡ ይጀምራል ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከማንኛው ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ እንደተዋጉ ፡ ለመለየት ፡ በስማቻው ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ቁጥር ፡ በግርጌ ፡ ከሚገኘው ፡ ቁጥር ፡ ጋር ፡ እያገናኙ ፡ መመልከት ፡ ነው

## የወላስሞች ፡ የዘር ፡ ሐረግ።




ደራሲው ፡ ከየመጽሐፉ ፡ ለቅሞ ፡ ያሰናዳው ፡ የወላስሞች ፡ የዘር ፡ ሐረግ።

ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በታላቅነቱ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የአዳሉንም ፡ የደዋሮውንም ፡ ወደራሱ ፡ ሥልጣን ፡ እየያዘ ፡ እያሳደመ ፡ ቢመራቸው ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ነገሥታቱ ፡ ከይፋት ፡ እያባረሩት ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ ወደ ፡ ዘይላ ፡ እየሔደ ፡ መቀመጡ ፡ ባይቀር ፡ ደንበኛው ፡ መደቡና ፡ መጠሪያው ፡ ይፋት ፡ ስለሆነ ፡ የይፋት ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ባላባት ፡ ማለት ፡ ከታሪኩ ፡ ጋር ፡ ይስማማል።

ባላባት ፡ የምንለውም ፡ በዛሬ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የኛም ፡ የግዕዝኛ ፡ ጽሑፍ ፡ የይፋት ፡ ንጉሥ ፡ የአዳል ፡ ንጉሥ ፡ እንደሚለው ፡ ኣሕመድ ፡ በድላይም ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ የይፋት ፡ ንጉሥ ፡ እያለነው። የሚጠራው። የግብፅና ፡ የዐረብ ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ የገበርት ፡ ጌታ ፡ የይፋት ፡ መስፍን ፡ ፩ ፡ ኣንድ ፡ ጊዜም ፡ የይፋት ፡ ንጉሥ ፡ ይሉታል። የኛን ፡ የክርስቲያኖቹንም ፡ ነገሥታትአንድ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ የግብፅና ፡ የዐረብ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከኛ ፡ ወስደው ፡ ሐፄ ፡ ወይም ፡ «የአማራ ፡ መስፍን ፡ ሲሉ ፡ ንጉሥ ፡ ለማለት ፡ ነው። የይፋቱን ፡ ባላባትና ፡ የኢትዮጵያውንም ፡ ንጉሥ ፡ ባጻጻፋቸው ፡ ሁለት ፡ የሚያዋጉና ፡ የሚጣሉ ፡ ጐረቤት ፡ ነገሥታት ፡ እንጂ ፡ የይፋቱን ፡ ተገዥ ፡ የኢትዮጵያውን ፡ ንጉሥ ፡ ገዥ ፡ አድርገው ፡ ኣያሳዩትም ፡ ቢያሳዩም ፡ መጠን ፡ ያለው ፡ ነው።

በሌሎች ፡ በክርስቲያን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ወሰንና ፡ መጠን ፡ ቢኖረውም ፡ ለነጻነታቸው ፡ መጋደላቸውን ፡ ሳይተዉ ፡ እነሱን ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ተገዥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የክርስቲያኖቹን ፡ ነገሥታት ፡ እንደገዥ ፡ እያደረጉ ፡ ይጽፉቸዋል። የኛ ፡ ነገሥታት ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ሕንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ድረስ ፡ ይፋትንም ፡ አዳልንም ፡ በሙሉ ፡ የግዛት ፡ ክፍል ፡ አድርገው ፡ በሚገባ ፡ መመልከታቸውን ፡ የምንረዳው ፡ ዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ አዳል ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ ሊዋጋ ፡ ሔዶ ፡ ኣባትዮውን ፡ አባርሮ ፡ ልጆቹ ፡ ጫማቸውን ፡ ከእግራቸው ፡ አውልቀው ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ይዘው ፡ ማረን ፡ ተገዛንልህ ፡ የቀሩትንም ፡ እናስገባለን ፡ ብለው ፡ ከፊቱ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ «ተገዥ

፡ ለገኘሁው ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ እያቀረበ ፡ ግብር ፡ እየከፈለ ፡ የሚገዛውን ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ የመላዋን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ንጉሥ ፡ ወጋችሁኝ ፡ .....**እግዚአብሔር** ፡ ግን ፡ ተንኮላችሁን ፡ አይቶ ፡ በእጄ ፡ ላይ ፡ ጣላችሁ ፡ ብሎ ፡ የመለሰላቸው ፡ ወቀሳ ፡ ያስረዳል።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በየጊዜውበነገሥታቱና ፡ በነዚህ ፡ በይፋትናበአዳል ፡ ባላባቶች ፡ መካከል ፡ የሆነውን ፡ የጦርነት ፡ ምክንያት ፡ ስንፈልግ ፡ ኣብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ባላባቶቹ ፡ ራሳቸው ፡ መጥተው ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ ልከው ፡ ግብር ፡ ከመክፈልና ፡ ተገዥነታቸውን ፡ ከመግለጽ ፡ ሲያቋርጡ ፡ መሆኑን ፡ እንረዳለን። ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ከነዚያ ፡ ውስጥ ፡ ኃይል ፡ የተሰማው ፡ የሚበቃ ፡ እርዳታ ፡ ከየመንና ፡ ከዘቢድ ፤ ከግብፅ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ያገኘው ፡ መገበር ፡ ቀርቶ ፡ ቢቻል ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባይቻል ፡ የእስላም ፡ አገር ፡ ነክነት ፡ ያለውን ፡ ደዋሮን ፡ ሐድያን ፡ ባሊን ፡ ለመጠቅለልና ፡ አንድ ፡ የእስላም ፡ መንግሥት ፡ ለማቆም ፡ እንደጣረ ፡ ነው። ሳብር ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ መሐመድ ፡ ካፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጋር ፡ ከመዋጋቱ ፡ በፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ አውራጃ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ እንደሚያደርጉት ፡ የጻሕፈ ፡ ላምነት ፡ የመስፍንነት ፡ ደረጃ ፡ እየሰጠ ፡ በአንጎት ፡ በአምሐራ ፡ በጐጃም ፡ ሳይቀር ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ አደረገበት ፡ እያለ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ እንደገለጸልን ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ተመልክተናል።

አሁንም ፡ በዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ በኣሕመድ ፡ በድላይ ፡ መካከል ፡ የሆነውን ፡ ጦርነት ፡ የሚተርክልን ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ የደብረ ፡ ምጥማቅን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠራርና ፡ ፍጻሜ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ወሰሚዖ ፤ ካዕበ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ምድር ፡ ከመ ፡ መጽአ ፡ አርዌ ፡ በድላይ ፡ ተንሥኣ ፡ እምይእቲ ፡ መካን ፡ ዘስማ ፡ ደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ ሀደገ ፡ ምድረ ፡ ደጎ–ደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ በምትባለው ፡ ሥፍራ ፡ ሳለ ፡ የአርዌ ፡ በድላይን ፡ መምጣት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የደጎን ፡ ምድር ፡ ትቶ ፡ ሄደ ፡ ማለቱ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ለውጊያ ፡ ሳይፈልጉት ፡ እርሱ ፡ ለውጊያ ፡ መምጣቱን ፡ ያስረዳል። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አሁን ፡ የጦርነቱን ፡ ሁኔታና ፡ ፍጻሜ ፡ ከግዕዙ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ በቀጥታ ፡ የተረጐምሁትን ፡ እንመልከት።

“ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ደብረ ፡ ምጥማቅ (ተጉለት) ሳሉ ፡ አርዌ ፡ በድላይ ፡ መጣ ፡ ማለትን ፡ ቢሰሙ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ የደጎን ፡ አገር ፡ ትተው ፡ በኣር ፡ ገበያ ፡ በምድረ ፡ አፋፍ ፡ ፤ በየለበሸበአጋም ፡ ገበያ ፡ ሐሳብ ፡ በወሰን ፡ ከሚባለው ፡ ከቲንሹ ፡ ሥራዊት ፡ ጋር ፡ ደዋሮ ፡ ደረሱ። በዚያም ፡ ሳሉ ፡ ወደ ፡ ደብረሊባኖስና ፡ ወደ ፡ ሌላም ፡ ቅዱሳን ፡ ወደሆኑ ፡ ሰዎች (ምሕላ ፡ እንዲያዝላቸው) ልከዋቸው ፡ የነበሩት ፡ ተመልሰው ፡ መጥተው ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ጸሎታችንን ፡ ሰምቶናል ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ኃይል ፡ አሸንፈህ ፡ ትጥለዋለህ ፡ የሚል ፡ መልእክት ፡ ይዘውላቸው ፡ ደረሱ። እንደዚሁም ፡ የሐድያው ፡ ገራድ ፡ መጥቼ ፡ እንድረዳህ ፡ ትፈልግ ፡ እንደሆነ ፡ ቃልህን ፡ ላክብኝ ፡ የሚል ፡ መላክተኛ ፡ ላከ። ይኸው ፡ የሐድያ ፡ ገራድ ፡ ለአርዌ ፡ በድላይም ፡ “እኔ ፡ ሕብረቴ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ነውና ፡ መጥቼ ፡ እረዳሃለሁ ፡ የሚል ፡ ልኮ ፡ ነበር። ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እንድመጣ ፡ ቃልህን ፡ ላክብኝ ፡ ብሎ ፡ ለንጉሡ ፡ ልኮ ፡ ለነበረው ፡ ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እስክንጠራህ ፡ ድረስ ፡ በአይፈረስ ፡ አገር ፡ ሠፈርህን ፡ አዘጋጅተህ ፡ ጠብቅ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ጨምረው ፡ አንድ ፡ መልክተኛ (እየሰለለም ፡ እየተቆጣጠረም ፡ የሚጠብቀው ፡ ማለት ፡ ነው) ላኩለት። ይኸም ፡ መሐመድ ፡ የሐድያ ፡ ገራድ ፡ የቀኝዕ ፡ በዓልቲሐት ፡ የንግሥት ፡ ዕሌኒ ፡ አባት ፡ ነው። ነገርግን ፡ ገራድ ፡ መሐመድ (የሐድያው) ና ፡ ኣርዌ ፡ በድላይ (ይፋቱ) ሁለቱም ፡ እስላሞች ፡ ስለሆኑ ፡ የንጉሡ ፡ ሕሊና ፡ አላመነውም ፡ ነበርና ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ቦታ ፡ አትምጣ ፡ ብለው ፡ ያዘዙት ፡ ስለዚህ ፡ ነው።

ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ አርዌ ፡ በድላይን ፡ ከማይቆጠረው ፡ ሠራዊቱ ፡ ጋር ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ተደነቀ ፤ ወደ ፡ **እግዚአብሔር**ም ፡ ተጣርተው (ጸልየው ፡ ማለቱ ፡ ነው) ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ኃይል ፡ ከታጠቁ ፡ በኋላ ፡ ከቲንሸሠራዊታቸውጋርጦርነቱን ፡ ሊዝምሩ ፡ ተዘጋጁ። ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ኣምኃ ፡ ጽዮን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ወታደሮችህን ፡ እንዲያግዙህ ፡ ሳይሰበሰቡ ፡ አንተ ፡ ምነው ፡ ለጦርነቱ ፡ ቸኰልህ ፡ እዚህ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ያሉት ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ፡ አንተም ፡ ራስህ ፡ የጦርነት ፡ ልብስህን ፡ ለብሰህ ፡ ለውጊያ ፡ አልተዘጋጀህም ፡ ምነው ፡ እንደዚህ ፡ ማድረግህ ፡ እያለ ፡ መከራቸው። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ »ንጉሥ ፡ በሠራዊቱ ፡ ብዛት ፡ ኣይድንም ፡ ኣርበኛም ፡ በኃይሉ

፡ ብዛት ፤ ፈረስም ፡ በብርታቱ ፡ ሊያድንም ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጥም ፡ አይችልም ፡ የሚለውን ፡ የዳዊትን ፡ ቃል ፡ ኣልሰማህምን ፡ እኔ ፡ በምሕረቱ ፡ ይረዳኝ ፡ ዘንድ (**እግዚአብሔርን**)ታምኜበታለሁ ፡ ብላው ፡ በቍጣ ፡ ቃል ፡ መለሱለት። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ተነሥተው ፡ ድባብ ፡ እንዲያዝ ፡ ጥሩምባ ፡ እንዲነፋ ፡ ነጋሪት ፡ እንዲጐሸም ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ቀዋመ ፡ ፀርቅ (ሰንደቅ ፡ ዓላማ?) እንዲቆም ፡ ኣዘዙ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከግርማቸው ፡ ታላቅነት ፡ የተነሣ ፡ ሁሉም ፡ ተናወጠ። ኣርዌ ፡ በድላይ ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠ ፡ በልቡም ፡ ሁከት ፡ ገባ ፡ ኣጠገቡም ፡ ያሉትን ፡ «የመጣው ፡ ሀሳብ ፡ ወሰን (ሀሳብ ፡ በወሰን) የሚባለው ፡ ሹሙ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ንጉሡ ፡ አልመጣም ፡ ብላችሁኝ ፡ አልነበረምን ፡ ኣሁን ፡ ግን ፡ እውነት ፡ ኣይደለም ፡ እያለ ፡ ይኸንኑ ፡ ከጭፍሮቹ ፡ ጋር ፡ ሲነጋገር ፡ ንጉሡ ፡ ደረሱበትና ፡ ከወታደሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ገደሉበት ፡ ኣንድ ፡ የንጉሡ ፡ ወታደርም ፡ አንድ ፡ የብረት ፡ ፍላጻ ፡ ሐፅ)ወርውሮ ፡ አርዌ ፡ በድላይን ፡ ግምባሩን ፡ ቢመታው ፡ ኣርዌ ፡ በድላይ ፡ ብረቱን ፡ በእጁ ፡ ሰበረና ፡ ንጉሡን ፡ ለመያዝና ፡ ለመውጋት ፡ ተጠጋ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ግን ፡ ከእግራቸው ፡ በታች ፡ ጣለላቸው። በተጠጋ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ በጦር ፡ አንገቱ ፡ ላይ ፡ ወግተው ፡ ጉረሮውን ፡ ቆረጡት። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ በአጠገባቸው ፡ ካሉት ፡ ጋር ፡ **ለሥላሴ** ፡ ዝማሬ ፡ አቀረቡ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እስላሞች ፡ ሸሽት ፡ ሲዝምሩክርስቲያኖቹ ፡ እየተከተሉ ፡ በሰይፍና ፡ በጦር ፡ እየገደሉ ፡ ፈጁዋቸው ፤ ግማሾቹም ፡ ገደል ፡ እየገቡ ፡ ሞቱ ፤ ከውስጣቸው ፡ ፩ድም ፡ የዳነየለም ፡ **እግዚአብሔር** ፡ እንደትምክህታቸው ፡ ከፈላቸው።

ወንድሙ ፡ ከረዲን ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ ሐዋሽ (አዋሽ) ፡ ሸሽቶ ፡ በዚሁ ፡ ንጉሥ ፡ አዝነው ፡ ሳላ ፡ ዣን ፡ ደገና ፡ የሚባሉት (ወታደሮች) ተከታትለው ፡ ኣረፈበት ፡ ቦታ ፡ አግኝተውት ፡ ራሱን ፡ ቆርጠው ፡ ወደ ፡ ጌታቸው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አመጡላቸውና ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ተደሰቱ። በዚህ ፡ ቀን ፡ ጌታችን ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ የተወለደባት ፡ ቀን ፡ ስለነበረ ፡ በእውነትም ፡ ይህች ፡ ቀን ፡ ተኣምር ፡ የተደረገባት ፡ የደስታ ፡ ቀን ፡ ነች ፡ ሲሉ ፡ ኣሰቡ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሞተው ፡ የተማረከው ፡ ሰውና ፡ ፈረስ ፡ ወደ ፡ ገደል ፡ እየገባ ፡ የሞተው ፡

ጭምር ፡ እንዲቆጠር ፡ ንጉሡ ፡ አዘዙና ፡ ቢቆጠር ፡ ብዙ ሆነ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱ ፡ በማኅሌት ፡ ወንድና ፡ ሴቱ ፡ ከየአገሩ ፡ መጥቶ ፡ በደስታ ፡ እየዘፈኑ ፡ **ለእግዚአብሔር** ፡ ምሥጋና ፡ አቀረቡ። የሐድያውንም ፡ ገራድ ፡ ይኸን ፡ ድንቅ ፡ ሥራ ፡ ይመለከት ፡ ዘንድ ፡ ከአይፈርስ ፡ አስጠርተውት ፡ መጣ፤ ፡ የአሳቡንም ፡ መልካምነት (ሽፍቶ ፡ ወደዚያ ፡ ሳይደረብ ፡ በመቅረቱ) ፡ ከተመለከቱ ፡ በኋላ ፡ ሸልማት ፡ ሸለሙት።

የከሐዲው (የበድላይ ፡ ሺሃብ ፡ አድ ፡ ዲን ፡ አህመድ) ፡ ጭንቅላቱም ፡ እጁም ፡ እግሩም ፡ ሌላውም ፡ አባል ፡ ሁሉ ፡ ተቆረጠና ፡ በያገሩ ፡ ተላከ ፡ ጭንቅላቱ ፡ ወደ ፡ አምባ (ትልቅ ፡ የገበያ ፡ የሚውልበት ፡ ከተማ ፡ ይሆናል) የቀረው ፡ ወደ ፡ አክሱም ፡ ወደ ፡ መንሐድሌ ፡ ወደ ፡ ዋሸል (ወሲል?) ወደ ፡ ጅጅሮ ፤ ወደ ፡ ላዎ ፡ ወደ ፡ ዊዝተላከ። የማዕርግ ፡ ልብሱ ፡ ጦሩና ፡ ሰይፉ ፡ ድባቡ ፡ ሀይከሉ? ከሚስቱ ፡ ልብስ ፡ ጋር ፡ ወደደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ተላከ። ለደብረ ፡ ምጥማቅና ፡ ለጽዮን ፡ ለሌሎችም ፡ ከገንዘቡና ፡ ከልብሱ ፡ እየተደለደለ ፡ ተላከ። በተረፈው ፡ ሰውነቱ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ድንጋይ ፡ እየወረወረ ፡ ወግረው..... ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ከአደረጉ ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ በደስታ ፡ ወደተወለዱበት ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ጥልቅ (ፈጠጋር) ተመለሱ። በዚያም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይተው ፡ የሚካኤልን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ አስዠመሩ። አባታቸው ፡ ዳዊትም ፡ በዚያ ፡ የነበረ ፡ ጊዜ ፡ <u>የለበሻ</u> ፡ የሚባል ፡ ብዙ ፡ አትክልት ፡ ተክሎበት ፡ ነበር ፤ በዚያም ፡ ፩ ፡ ሌላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠርተው፤ ፡ መርጡለ ፡ ሚካኤል ፡ ብለው ፡ ሠየሙት ፡ የታችኛውን (የፊተኛውን ፡ ደግሞ ፡ ዐፀደ ፡ ሚካኤል ፡ ብለው ፡ ሠየሙት። ለሁለቱም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትየካህናት ፡ አላቃ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሾሙ።

እንደዚሁም ፡ ካህናትም ፡ ርስትም ፡ ደልድለው ፡ ሰጡና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሥራ ፡ በቶሎ ፡ እንዲፈጸም ፡ ኣዘዙ። ... ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ኣልፈው ፡ ምድረ ፡ እንክርዳ ፡ ደርሰው ፡ ፩ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ አሠሩና ፡ ደብረ ፡ ስሂን ፡ ብለው ፡ ሠየሙት። በውስጡም ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ካህናትና ፡ መዘመራን ፡ ተከሉ ፤ ለነርሱም ፡ መተዳደሪያ ፡ የሚሆነውን ፡ ሰጡ። በማርያምና ፡ በንጉሡ ፡

መታሰቢያ ፡ ቀንም ፡ በዓሉ ፡ ለሚከበርበት ፡ ብዙ ፡ ርስት ፡ ሰጡ። ከዚያ ፡ የካህናቱንና ፡ የርስቱን ፡ ድልድል ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑንም ፡ ሥርዓት ፡ ፈጽመው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር? ሄዱ ፡ ከዚያም ፡ የወራሪን ፡ ወንዝ ፡ ተሻግረው ፡ ምድረ ፡ ኢባ ፡ ደረሱ ፡ ይህችም ፡ አገር ፡ ስለአማረቻቸው ፡ ተቀመጡባት ፡ » ብሎ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጸሐፊው ፡ በመዠመሪያ ፡ ላይ ፡ የዚህን ፡ ጕዳይ ፡ ይጨርስና ፡ ሌላ ፡ ጕዳይ ፡ ከዠመረ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በመጨረሻው ፡ ግድም ፡ የዚህኑ ፡ ጕዳይ ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ አድርጎ ፡ ሊተርክ ፡ ይዠምራል። ይኸም ፡ እነሆ ፡ ከፊተኛው ፡ ላይ ፡ ያልተገለጸ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ታናንሽ ፡ ዝርዝር ፡ ይገኝበታል። «አርዌ ፡ በድላይን ፡ ድል ፡ ማድረጋቸውን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የደብረሊባኖስ ፡ መነኮሳት ፡ ከመምህራቸው ፡ ከአባ ፡ እንድርያስ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ከየሥፍራው ፡ ከመጡት ፡ ካህናት ፡ ጋር ፡ ኣብረው ፡ መጡ። እነዚህም ፡ የደብረሊባኖስ ፡ ካህናትና ፡ መነኮሳት ፡ መዠመሪያም ፡ ታሸንፈዋለህ ፡ ብለው ፡ የላኩባቸው ፡ ናቸው ፡ በዚህም ፡ ቀን ፡ ንጉሡ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፻፱ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ፱ባለ ፡ ወርቅ ፡ ግምጃ ፡ ፤ ፯ ፡ የሐር ፡ ልብስ ፤ ፯ ፡ የወርቅ ፡ መነሳንስ (ጭራ?) ሰጡ ፡ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ በማኅበር ፡ ተቀምጠው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረጉ። ድል ፡ ያረጉበት ፡ **የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ልደት ፡ በየወሩ ፡ በ፳፱ ቀን ፡ ተዝካር (መታሰቢያ) እንዲደረግበት ፡ ፯ ፡ መስፈሪያ ፡ ምድረ ፡ አላት ፡ ሰጡ። የማኅበሩም (የገዳሙም)ስም ፡ እስካሁን ፡ ደብረ ፡ አስቦ ፡ ይባል ፡ የነበረውን ፡ አስቀርተው ፡ "ደብረ፡ሊባኖስ" ፡ እንዲባል ፡ አዲስ ፡ ሥያሜ ፡ ሠይመው ፡ ይህችን ፡ ደብር (ገዳም)ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥተው ፡ ይበልጥ ፡ ኣከበሯት ፡ ሲል ፡ ይጨርሳል።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጒዳይ ፡ ወደ ፡ አሕመድ ፡ በድላይ ፡ ጦርነት ፡ እንመለስ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በክርስቲያኖቹና ፡ በእስላሞቹ ፡ መካከል ፡ ጥላቻ ፡ ቢበዛ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ሊወጋቸው ፡ የመጣው ፡ ራሱ ፡ ኣሕመድ ፡ በድላይ ፡ ቢሆን ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ ከገደሉት ፡ በኋላ ፡ ከአንገቱ ፡ ዠምሮ ፡ እጁንም ፡ እግሩንም ፡ አካሉን ፡ ሁሉ ፡ ኣስቆርጠው ፡ በየአድባራቱ ፡ በየአገሩ ፡ መላካቸው ፡ የሚገባ ፡ መስሉ ፡ አይታይም። እንደርሳቸው ፡ ያለ ፡ ብዙ ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ያነበበ ፡

**እግዚአብሔርን** ፡ ከልቡ ፡ አምኖ ፡ የሚያመልክ ፡ ንጕሥ ፡ እንደርሳቸው ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ በተፈጠረው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ ጭካኔ ፡ መፈጸም ፡ ማንም ፡ ፍጡር ፡ ኣግባብ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ኣይደፍርም።

ላስተዳደርም ፡ ቢሆን ፡ ምናልባት ፡ ቢቻል ፡ ከጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ማርከው ፡ በቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ኣስቀምጠው ፡ እየጠበቍ ፡ ቢያከባክቡት ፡ ባይቻል ፡ ደግሞ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞተ ፡ በኋላ ፡ ሬሳውን ፡ በክብር ፡ አስነሥተው ፡ እደንበኛ ፡ መስጊድ ፡ አስቀብረውት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ እስላሞች ፡ ዘንድ ፡ እንደዚሁም ፡ የርሳቸው ፡ ወገን ፡ በሆኑት ፡ በሐድያው ፡ ገራድና ፡ በሌሎቹም ፡ እስላሞች ፡ ዘንድ ፡ በቂምና ፡ በበቀል ፡ ፈንታ ፡ ለርሳቸውም ፡ ለልጆቻቸውም ፡ ግንኙነትና ፡ መቀራረብን ፡ ያተርፉ ፡ ነበር። ነገር ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ የተገኘ ፡ ያስተዳደር ፡ ዘዴ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በአውሮፓም ፡ በምስራቅም ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ የመላላትና ፡ የርኅራኄ ፡ መንገድ ፡ ለጠላቱ ፡ የሚያሳይ ፡ ንጕሥ ፡ በጣም ፡ ብርቅ ፡ ነው። ኣሕመድ ፡ በድላይም ፡ ጦርነቱ ፡ ቀንቶት ፡ እርሳቸውን ፡ ከነሕይወታቸው ፡ ወይም ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ አግኝቷቸው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እርሳቸው ፡ በርሱ ፡ የሠሩትን ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ላይ ፡ መፈጸሙ ፡ የማረከውን ፡ ሀብትና ፡ መሣሪያቸውን ፡ በርታ ፡ ታሸንፋለህ ፡ እያሉ ፡ ለአጽናኑት ፡ ቃዲዎችና ፡ ሸህዎች ፡ ማደሉ ፡ የማይቀር ፡ ነበር። በዚያን ፡ ዘመን ፡ የተሸናፊ ፡ ኣንገት ፡ በአሸናፊ ፡ መቆረጡ ፡ እንደልማድም ፡ እንደ ፡ ሕግም ፡ የተቆጠረ ፡ ነገር ፡ ነበር።

ስለዚህ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ለፈጀውና ፡ ላስፈጀው ፡ ሰውዬ ፡ የርኅራኄ ፡ መንገድ ፡ ቢያሳዩ ፡ ከክርስቲያኑ ፡ ሕዝባቸው ፡ ከካህናቱና ፡ ከመነኰሳቱ ፡ ዘንድ ፡ በዚሁ ፡ ሥራ ፡ ተቀይሞ ፡ ርሳቸውን ፡ እንደ ፡ **እግዚአብሔርና** ፡ እንደ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠላት ፡ ቆጥሮ ፡ በርሳቸው ፡ ላይ ፡ የሚነሣ ፡ መነሣት ፡ ባይቻል ፡ የሚያጕረመርመውና ፡ የሚቀየመው ፡ እንደሚበዛ ፡ ሕዝብና ፡ ካህናትም ፡ ሲቀየም ፡ አስተዳደር ፡ እንደሚበላሽ ፡ የታወቀ ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ያን ፡ ጊዜምቢሆን ፡ የሕሊና ፡ ሰው ፡ አይገኝም ፡ ማለት ፡ አይቻልምና ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሐሜትና ፡ ቅያሜ ፡ አልፈው ፡ ለእስላሙ ፡ መሪ ፡ በጎ ፡ ተግባር ፡ ቢያሳዩ ፡ ኖሮ ፡ አበጁ ፡ ደግ ፡ ኣደረጉ ፡ የሚላቸው ፡ ወገን ፡ ይበዛ ፡ ወይም ፡

ያንስ ፡ እንደሆነ ፡ መጠኑንና ፡ ግምቱን ፡ ዛሬ ፡ መለየት ፡ ስለማይቻል ፡ ኣሁን ፡ ወደሌላው ፡ ጕዳይ ፡ እንለፍ።

# ምዕራፍ ፡ ፴፯።

## የደቂቀ ፡ እስጢፋ ፡ ቅጣት—የደብረብርሃንና ፡ የቂርቆስ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ሥራ – ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥርዓትና ፡ ቅዳሜ ፡ እንዲከበር ፡ የወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ "

ባለፈው ፡ ከተተረከው ፡ ሌላ ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የተፈጸመ ፡ ፩ ኣንድ ፡ ነገር ፡ አለ።

ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ከትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ደቂቀ ፡ እስጢፋ (የእስጢፋኖስ ፡ ተከታዮች ፡ ልጆች) ለእመቤታችን ፡ ለማርያምና ፡ ለ**ልጅዋ ፡ ለጌታችን** ፡ መስቀል ፡ ኣይሰገድም ፡ የሚሉ ፡ ተነሡ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ንጉሥ ፡ በፊታቸው ፡ አቆሙና ፡ የሚሉትን ፡ ጠየቍዋቸው (መረመሩዋቸው)። ከሊቃውንትም ፡ ጋር ፡ ኣከራከረው ፡ ኣሸንፈው ፡ ኣሳፈሯቸው። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይኸንኑ ፡ የከፋት ፡ አሳባቸውን ፡ ስለኣልተዉ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያኑንና ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የመጡትን ፡ ሁሉ ፡ እንዲፈርዱባቸው ፡ ሰበሰቡ። የተሰበሰውም ፡ እያንዳንዱ ፡ እንዲሞቱ ፡ ከፈረደባቸው ፡ በኋላ ፡ አፍንጫቸውንና ፡ መላሳቸውን ፡ ተቆርጠው ፡ በየካቲት ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ በደንጊያ ፡ ተወግረው ፡ ተገደሉ። በተወገሩ ፡ በ፴፰ኛው ፡ ቀን ፡ በመጋቢት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ የመስቀል ፡ ለት ፡ ብርሃን ፡ ወርዶ ፡ በብዙ ፡ ሥፍራ ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ታየ። ስለዚህም ፡ ይህችን ፡ ሥፍራ ፡ ስለወደዷት ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ብለው ፡ ሠየሟት ፡ በውስጧም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አሠሩ። እያለ ፡ የደቂቀ ፡ እስጢፋን ፡ የጭካኔ ፡ ቅጣትና ፡ የደብረብርሃንን ፡ የሥያሜ ፡ ምክንያት ፡ ይገልጽልናል።

ደቂቀ ፡ እስጢፋ ፡ የሚባሉት ፡ በጣና ፡ ደሴት ፡ በቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ገዳም ፡ የሚያገለግሉ ፡ በመሆናቸው ፡ ይሆን ፡ ወይም ፡ የዚህን ፡ አዲስ ፡ ኣሳብ

፡ ያመነጩ ፡ እስጢፋኖስ ፡ የሚባል ፡ የርሱ ፡ ተከታዮች ፡ ይሁኑ ፡ ኣላረጋግጥም። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለእመቤታችን ፡ ለማርያም ፡ መስገድ ፡ አይገባም ፡ በማለት ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት (ሺ፬፻፳፮-ሺ፬፻፷) ዓ.ም ፡ ምሕረት ፡ ተነሥተው ፡ የውግረትና ፡ የሞት ፡ ቅጣት ፡ ተፈጽሞባቸው ፡ ነገሩ ፡ ሲደመሰስ ፡ በኣውሮፓ ፡ ሺ፭፻፳ (1520) ዓ.ም ፡ ላይ ፡ ማርቲን ፡ ሉተር ፡ የሚባል ፡ የሮማ ፡ ቄስ ፡ የጀርመን ፡ ተወላጅ ፡ የነበረው ፡ ይኸንንና ፡ ይኸንኑ ፡ የመሰለውን ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይፈጸም ፡ የነበረውን ፡ የቆየ ፡ ሥርዓት ፡ ተቃውሞ ፡ በዚህም ፡ በርሱም ፡ በወገኖቹም ፡ ስደትም ፡ ጦርነትም ፡ ተነሥቶ ፡ ተከታዮቹንም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖትና ፡ ሥርዓት ፡ በሚጠብቀው ፡ በእንግሊዝ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ተሰምቶ ፡ ነገሥታቱ ፡ የጧፍ ፡ ቀሚስ ፡ አልብሰው ፡ አቃጥለዋቸው ፡ ነገሩን ፡ ለመደምሰስ ፡ ተመክሮ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ሌሎች ፡ ተከታዮች ፡ ስላበረከቱ ፡ ነገሩን ፡ ማጥፋት ፡ ሳይቻል ፡ ቀረና ፡ እንዲያውም ፡ አንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ይኸንኑ ፡ ሉተር ፡ ያወጣውን ፡ አዲስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የሃይማኖት ፡ ሥርዓት ፡ መቀበል ፡ ዠመሩ። ከነዚህም ፡ ዋነኛ ፡ አገሮች ፡ የጀርመንና ፡ የእንግሊዝ ፡ አገሮች ፡ ናቸው።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ቀድሞ ፡ ከተሠራው ፡ ጋር ፡ አያይዞ ፡ በፊት ፡ እንደተባለው ፡ ብርሃን ፡ እንደወረደበትም ፡ እየገለጸ ፡ ጸሐፊው ፡ ስለ ፡ ደብረብርሃን ፡ ሥራ ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ብለው ፡ ከሠየሟት ፡ ወዲህ ፡ በጌታችን ፡ በ**ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ስም ፡ የሚያምር ፡ ቤተመቅደስ ፡ ንጉሡ ፡ በፍጥነት ፡ እንዲሠራ ፡ ባዘዙት ፡ መሠረት ፡ የሸዋ ፡ ሹማምንትና ፡ አቄቲዣር (ሥራ ፡ ኣሠሪ ፡ ሹማምንት?) በስምንት ፡ ቀን ፡ አሠርተው ፡ ጨረሱ። ለክዳን ፡ የሚሆነው ፡ የሳር ፡ ሰንበሌጥ ፡ ከግድም ፡ እስከ ፡ ፈጠጋር ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ አገር ፡ በሙሉ ፡ አመጣ። ካህናቱ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ነግሠ ፡ እያሉ ፡ ሲዘምሩ ፡ በቍርባን ፡ ሰዓት ፡ ፫ኛ ፡ ጊዜ ፡ ብርሃን ፡ ወረደ። መዘምራኑም ፡ ብርሃኑን ፡ ተመለከቱ ፤ ንጉሡም ፡ እኔም ፡ በዚች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ሲወርድ ፡ በገሀድ ፡ አየሁ ፡ አሉና ፡ ከግራ ፡ በዓልቲሐት ፡ ወስደው ፡ የኢባን ፡ አገር (ምድር ፡ ለዚች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለካህናቱ ፡ መተዳደሪያ ፡ ለሥርዓቱ

፡ ማስፈጸሚያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብላው ፡ ማሉ። እርሳቸውም ፡ በዚያው ፡ መቀመጥን ፡ ስለወደዱ ፡ ጀጐል (ቤተ ፡ መንግሥት?) እንዲሠራላቸው ፡ ኣጥሩም ፡ እንዲታጠርላቸው ፡ በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ጨዋና ፡ የሸዋን ፡ ሹማምንት ፡ ሁሉ ፡ እርዱኝ ፡ ብለው ፡ አዘዟቸው። ለዚህም ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ እንዲገባላቸው ፡ ያዘዙት ፡ ብዙ ፡ የወይራ ፡ ጨፈ.ቃና ፡ ግንድ ፡ ብቻ ፡ ፡ ነው። የጀጐሉ ፡ ሥራ ፡ እንዲያምር ፡ ልጡንም ፡ በስራት ፡ እየላጡ ፡ ጸዓዳ (ነጭ) እንዲሆን ፡ አደረጉት ፡ .... በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሳሉ ፡ ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ብዙ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥርዓት ፡ አቃኑ። ብዙም ፡ ሰው (ወንጀለኛ) ተገደለ። በ**እግዚአብሔር**ና ፡ በመሢሁ (በመላከተኛው) ዓመፃ ፡ የሠሩትን ፡ ሰዎች ፡ አጋዙዋቸው። የ**እግዚአብሔር**ን ፡ ፈቃድና ፡ የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ የፈጸሙትንም ፡ በዚሁ ፡ ቦታ ፡ አክብረው ፡ ከፍ ፡ አደረጉዋቸው (ሾሟቸው)።

ብዙ ፡ ዘመን ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ትልቅ ፡ በሽታ ፡ ተነሥቶ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አለቀ ፡ የሚቀብረውም ፡ አጣ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ በቀኝ ፡ በኵል ፡ የቂርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲሠራ ፡ መክረው ፡ ኣዘዙ። ይኸንንም ፡ ያደረጉት ፡ "ኢይምጻእ ፡ ብድብድ ፡ ኀበ ፡ ዘሐነፀ ፡ መርጡለከ ፡ ወኢይኵን ፡ ውስቴቱ ፡ ሕፀተ ፡ ማይ ፡ ወኢዐበረ ፡ እክል- ቤተመቅደስህን ፡ በሠራህበት ፡ ቦታ ፡ የወሀ ፡ ድርቀትም ፡ የእህል ፡ ጥፋትም ፡ አይሆንም" ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ቃል ፡ አስበው ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ይኸን ፡ በሽታ ፡ እንዲያስወግድላቸው ፡ ነው። በእውነትም ፡ እንዳሰቡት ፡ ከቤታቸው ፡ በሽታው ፡ ሁሉ ፡ መወገዱን ፡ ሲያዩ ፡ ልጆቻቸውንና ፡ ንግሥቶቻቸውን (ሚስቶቻቸውን) ለቂርቆስ ፡ ከግምጃ ፡ ቤት ፡ ስጦታም ፡ መጻሕፍትም ፡ ስጡ ፡ ብለው ፡ አዘዙ። ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ የሚምልም ፡ የሚያስምልም ፡ በዚሁ ፡ በቂርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይማል ፡ አዘዙ ፡ ከዚያም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሃይማኖት ፡ ሥርዓት ፡ ኣቆሙ። "እኛ ፡ ጴጥሮስና ፡ ጳውሎስ ፡ ባሮች ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ለጌቶቻቸው ፡ ይገዙ ፡ ሁለቱን ፡ ቀን ፡ ለ**እግዚአብሔር** ፡ ያድርጉት ፡ ብለው ፡ ሐዋርያት ፡ በሲኖዶስ (በስብሰባ) እንደጻፉ ፡ ቅዳሜም ፡ እንደ ፡ እሑድ ፡ እኵል ፡ እንዲከበር ፡ አዘዙ። የ**ጌታችንን**

፡ የልደት ፡ ቀንና ፡ እርሳቸውም ፡ አርዌ ፡ በድላይን ፡ ድል ፡ ያደረጉበት ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲሆን ፡ በየወሩ ፡ ፳፱ነኛው ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ እንዲሆን ፡ ጳጳሳትና ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በግዝት ፡ እንዳዘዙት ፡ የእመቤታችን ፡ የእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ፴፪ (፴፫) በዓላት ፡ እንደ ፡ እሑድ ፡ በጥንቃቄ ፡ እንዲከበር ፡ የሚካኤል ፡ በዓልም ፡ በየወሩ ፡ የሊቃነ ፡ ካህናትና ፡ የካህናተ ፡ ሰማይ ፡ የ፬ቱ ፡ እንስሳም ፡ የነቢያትም ፡ የሐዋርያትም ፡ በዓል ፡ እንዲከበር ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲቀርብ ፡ ምጽዋትም ፡ እንዲሰጥ ፡ ለተራቡትም ፡ ሁሉ ፡ ኅብስት ፡ እስኪጠግቡ ፡ ድረስ ፡ እንዲታደል ፡ ኣዘዙ። ይኸን ፡ ሁሉ ፡ በመጻሕፍቶቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ጽፈው ፡ አዘዙ። የጻፏቸው ፡ መጻሕፍትም ፡ ስማቸው ፡ ጦማረ ፡ ትስብእት ፤ መጽሐፈ ፡ ብርሃን ፤ መጽሐፈ ፡ ሚለድ (ምዕላድ?) ክህደተ ፡ ሰይጣን ፤ መጽሐፈ ፡ ባሕርይ ፡ ተአቅቦ ፡ ምሥጢር ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ነግሠ ፡ ይባላሉ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሲሠሩ ፡ ሲያከናውኑ ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡ ኖሩ። በ፲፪ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ፈረን ፡ ሲሄዱ ፡ ሲመለሱ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ ሲሄዱ ፡ ሲመለሱ ፡ ነበር። ይኸውም ፡ ሲሆን ፡ በዚሁ ፡ በ፲፪ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ እዚሁ ፡ እቅርቡ ፡ አገር ፡ ምድረ ፡ ፈረንና ፡ ደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ ደርሰው ፡ ወደዚሁ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን (ተጉለት) ይመለሱ ፡ ስለነበረ ፡ በሙሉ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ የነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ ፲፬ ፡ ዓመት ፡ ነው። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዕረፍታቸው ፡ ሆነ። ምሕረቱ ፡ ብዙ ፡ የሆነው ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ለንጉሣችን ፡ ለዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ የሰማይን ፡ መንግሥት ፡ ያካፍላቸው ፡ ... ፡ ኣሜን ፡ ብሎ ፡ ይጨርሳል።

ከዚያም ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ። አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ባንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፪ ፡ ድርብ ፡ ወይም ፡ የሚበዛ ፡ ታቦት ፡ እንዲ ፡ ቀመጥ ፡ እንጂ ፡ ፩ ፡ ታቦት ፡ ብቻውን ፡ እንዳይቀመጥ። እነዚህም ፡ ታቦታት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከእመቤታችን ፡ ታቦት (ጽላት) አብሮ ፡ እንዲገኝ ፡ ማዛዘቸውን ፡ ከዚያ ፡ በሁለቱ ፡ የሰንበት ፡ ቀኖችና ፡ በሌሎችም ፡ የክብር ፡ በዓል ፡ ቀኖች ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ እየተሰበሰበ ፡ ካህናቱ ፡ ጸሎተ ፡ ሃይማኖትን ፡ ጸሎተ ፡ ወንጌልን ፡ ፲ቱ ፡ ቃላተ ፡ ኦሪትን ፡ ፰ቱ ፡ ቃላት ፡ ወንጌልን ፡ የ**እግዚአብሔርን** ፡ አንድነትና ፡ ሦስትነት ፡ የ**ወልድን** ፡ ያለናት ፡ ከ**አብ** ፡ መወለድ ፤ ፪ኛ ፡ ያለአባት ፡ ከድንግል

፡ መወለዱን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያስተምሩ። ካህናት ፡ በየሥፍራቸው ፡ ይኸን ፡ ሳያስተምሩ ፡ የቀሩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቤታቸው ፡ እየተበረበረ ፡ ገንዘባቸው ፡ ይወረስ ፡ ብለው ፡ ለሹማምንቱ ፡ እንደነገሩ ፡ ይገልጻል።

ስለዚህ ፡ አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ከምሥራቅ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ከቍስጥንጥንያና ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ እየተዘጋጀ ፡ የወጣውን ፡ ሕግ ፡ በሲኖዶስ ፡ ያገኙትን ፡ ሁሉ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓትና ፡ ደንብ ፡ ባገራቸው ፡ በትክክል ፡ ለማስፈጸም ፡ እንደጣሩ ፡ ይታያል። ይኸንንም ፡ ያዘዙትን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ያፈረሰውን ፡ ወገን ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ ቀጥተዋል። አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ ክርክርና ፡ ሐሜታ ፡ የፈጠረው ፡ የቅዳሜ ፡ እንደ ፡ ሰንበት ፡ መቆጠሩ ፡ ነው። ቀድሞ ፡ እስከ ፡ ፱ ፡ ከዓት ፡ ድረስ ፡ እየተሠራ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሰንበት ፡ ገባ ፡ እያለ ፡ ያርፍ ፡ የነበረውን ፡ አሁን ፡ እርሳቸው ፡ ቅዳሜ ፡ እንደ ፡ ሰንበት ፡ ትክክል ፡ ይከበር ፡ ስላሉ ፡ ሥራን ፡ ወዳድ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ በበዓሉ ፡ ብዛት ፡ ቅሬታ ፡ እንደሚሰማው ፡ የታወቀ ፡ ነው። እንደዚሁም ፡ ቅዳሜ ፡ ይከበር ፡ ብለው ፡ ያዘዙትን ፡ ቅዳሜ ፡ የባላ ፡ ኦሪት ፡ የአይሁድ ፡ በዓል ፡ ነውና ፡ አናከብርም ፡ ብለው ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኮሳት ፡ ውስጥ ፡ ብዙዎቹ ፡ ተቀጡ ፡ ይባላል።

# ምዕራፍ ፡ ፴፫።

## አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቀብ ፡ የደረሱዋቸው ፡ መጻሕፍት።

ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ አፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጻፏቸው ፡ ብሎ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጸሐፊው ፡ የዘረዘራቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉንም ፡ ማግኘት ፡ አልቻልኩም። መጻሕፍቶቹ ፡ ጦማረ ፡ ትስብእት ፤ መጽሐፈ ፡ ብርሃን ፤ መጽሐፈ ፡ ሚለድ (ምዕላድ?) ክህደተ ፡ ሰይጣን ፤ መጽሐፈ ፡ ባሕርይ፣ተአቅቦ ፡ ምሥጢር፣ **እግዚአብሔር** ፡ ነግሠ ፡ ከሚባሉት ፡ ውስጥ ፡ ተአቅቦ ፡ ምሥጢር ፡ የሚባላውን ፡ ሙሴ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ ተርጕሞ ፡ ከግዕዙ ፡ ጋር ፡ ያሳተመው ፡ በእጄ ፡ ስለገባ ፡ ልመለከተው ፡ ችያለሁ። እርሱም ፡ ከመዥመሪያው ፡ ላይ ፡ «**ክርስቶስ** ፡ ሕይወትየ ፡ **ክርስቶስ** ፡ መድኃኔ ፡ ገጽየ ፡ አምላኪየ ፡ **ክርስቶስ** ፡

ረዳእየ ፡ ወማርያም ፡ እሙ ፡ እግዝእትየ ፡ ወድንግልና ፡ ሥጋሃ ፡ ጌራ ፡ መንግሥትየ ፡ ወድንግልና ፡ ሕሊናሃ ፡ አስፓዳየ ፡ ጋሻዬ? ».........እያለ ፡ ይሄድና ፡ ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ናሁ ፡ ጸሐፍነ ፡ በእንተ ፡ ተኣቅቦ ፡ ምሥጢር ፡ እምሲኖዶስ ፡ እያለ ፡ ቀጥሎ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ የሚናገረው ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ቍርባን ፡ ነው። በጠቅላላው ፡ ከሲኖዶስ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እየጠቀሰ ፡ የ**ጌታ**ን ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ በቍርባን ፡ ጊዜ ፡ አቀራቢው ፡ ካህን (ቄስ)ቆራቢው ፡ ካህንም ፡ ቢሆን ፡ መሃይምን ፡ በአክብሮት ፡ በፍርሐት ፡ በጥንቃቄ ፡ እንዲፈጽም ፡ ያስገነዝባል። ባለመጠንቀቅ ፡ ቄሱ ፡ ወይም ፡ ተቀባዩ ፡ ቢነጥበው ፡ ቢወድቅበት፻፵፫ ፡ ጊዜ ፡ እንዲገረፉ ፡ ጥብጣቤ ፡ እንዲመቱ ፡ ያዝዛል። እንደዚሁም ፡ ከራሱ ፡ ከንጉሡ ፡ ዠምሮ ፡ በየደረጃው ፡ ለቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥጣኖች ፡ ለተራው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚፈጸመው ፡ ቅጣት ፡ እየተዘረዘረ ፡ ተጽፏል።

መጽሐፉን ፡ ሲመለከቱት ፡ በውስጡ" ፡ ይቤ ፡ ንጉሥነ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘተሰምየ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ዘሠርዓ ፡ ዘንተ ፡ ሥርዓተ ፡ ዓቢየ ፡ ወክቡረ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ስለሚገኝበት ፡ ጸሐፊ ፡ እፊታቸው ፡ ኣስቀምጠው ፡ እየነገሩ ፡ እያዘዙ ፡ ያጻፉት ፡ እንጂ ፡ ራሳቸው ፡ በእጃቸው ፡ የጻፉት ፡ አይመስልም።

የዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ወደፈረንሳዊ ፡ በተረጐሙት ፡ በሙሴ ፡ ዝል ፡ ፔሩሾ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ መጽሐፈ ፡ ብርሃን ፡ የሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ከሁሉ ፡ ትልቅ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው። በ፻፲፯ ፡ ምዕራፍ ፡ ተከፍሏል። እርሱም ፡ በታሪካቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዳነበብነው ፡ የርሳቸው ፡ ዜጋ ፡ የሆነ ፡ ጣዖት ፡ ማምላኩን ፡ ትቶ ፡ ወደፍጹም ፡ ክርስቲያንነት ፡ እንዲመለስ ፡ ቅዳሜ ፡ እንዲከበር ፡ .... ያስጠነቅቃል።

መጽሐፈ ፡ ሚላድ ፡ የሚባለው ፡ የ**ጌታችን** ፡ ልደት ፡ በየወሩ ፡ በ፳፱ ቀን ፡ እንዲከበርና ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ የሚነበበውን ፡ እያስረዳ ፡ ከዚያም ፡ ይኸኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ንጉሡ ፡ በየአብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ መላካቸውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ደስክ ፡ ጕዳሌ ፤ ታፋንት ፤ ዲኖ ፤ ማቅዋዝ ፡ የሚባሉትን ፡ ጣዖታት ፡ ትቶ ፡ በ**ጌታችን** ፡ ልደት ፡ ብቻ ፡ እንዲያምን ፡ ያስገነዝባል።

መጽሐፈ ፡ ባሕርይ ፡ የሚባለው ፡ ስለ ፡ ኑዛዜና ፡ ስለ ፡ ቅብዓት ፡ ይናገራል። ጦማረ ፡ ትስብእት ፡ እዚያው ፡ እመጽሐፈ ፡ ብርሃን ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ከትስብእት ፡ ይልቅ ፡ ስለጠንቋዮች ፡ የሚናገር ፡ ነው።

**እግዚአብሔር** ፡ ነግሥ ፡ ለቅዱሳንና ፡ ለሰማዕታት ፡ የተደረሰ ፡ ሰላምታ ፡ ነው።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ትጋት ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ የውጭና ፡ የውስጥ ፡ ፖለቲካ ፡ በማስኬዳቸው ፡ ላይ ፡ የ**እግዚአብሔር**ና ፡ የልጁ ፡ **የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ የእናቱ ፡ የእመቤታችን ፡ የድንግል ፡ ማርያም ፡ ፍቅር ፡ ስላደረባቸው ፡ የክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲከበር ፡ እንዲዘረጋ ፡ ከደቡቡ ፡ ሕዝብ ፡ ክፍል ፡ በያይነቱ ፡ የገባው ፡ የጣዖት ፡ አምልኮ ፡ እንዲጠፋ ፡ ከልብ ፡ መጣራቸውን ፡ እንመለከታለን።

ከዚያም ፡ ኣልፈው ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ እጨጌዎችና ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓቶች ፡ ሊያስቡበትና ፡ ሊያዘጋጁት ፡ የሚገባውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደንብና ፡ ሥርዓት ፡ የቍርባን ፤ የጾም ፤ የበዓል ፡ ማክበር ፡ ጽሐፍ ፡ እየጻፉም ፡ እያጻፉም ፡ ሕግና ፡ ደንብ ፡ ሲያወጡ ፡ እነሆ ፡ ተመለከትን። ደግሞም ፡ በጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ሁልጊዜ ፡ ሲቃወሙ ፡ የምናው ፡ ጣዖት ፡ አምላኪዎችን ፡ እንጂ ፡ እስላሞችን ፡ አይደለም። በዚህም ፡ እንደዛሬ ፡ ዘመን ፡ ነገሥታት ፡ የእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ ከጣዖት ፡ አምልኮ ፡ ተለይቶ ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ የሚያምን ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ሃይማኖት ፡ መሆኑን ፡ ተረድተው ፡ እንደተዉት ፡ ይታወቃል።

እንደዚሁም ፡ በዘመናቸው ፡ የእመቤታችንን ፡ ተአምረ ፡ ማርያም ፡ ግብዕና ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አስመጥተው ፡ በነገሡ ፡ በ፳ኛው ፡ ዓመት ፡ ከዐረብኛ ፡ ወደግዕዝ ፡ እንዳስተረጐሙት ፡ ኣባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሚባሉት ፡ የአርመን ፡ ተወላጅ ፡ ኣርጋኖነ ፡ ድንግል ፡ የሚባለውን ፡ ስለእመቤታችን ፡ የሚናገረውን ፡ ጽሑፍ ፡ የደረሰው ፡ የጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ኣሚድ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጣርቶ ፡ የተጻፈው ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሕዝበ ፡ ጽዮን ፡ ልጅ (አማራ) ኬልቄዶን ፡ ተሰብስበው ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ ካላልክ ፡ ብለው ፡ ያወገዙበትን ፡ ጉባዔ ፡ ማኅበረ ፡ ካለባት ፡ የውሾች ፡ ጉባዔ'' እያለ ፡ የሚሰድበውን ፡ መጽሐፈ ፡ ምሥጢር ፡ የሚባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ የደረሰው ፡ በርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ መሆኑ ፡

በየመጽሐፉ ፡ ተጠቅሶ ፡ ይገኛል። ስለዚህ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ከውስጥ ፡ የአስተዳደር ፡ ጣጣና ፡ ከአዳሎች ፡ ጦርነት ፡ አልፈው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጽሑፍ ፡ አጥብቀው ፡ የደከሙ ፡ ስለሆኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በተለይ ፡ የቀለም ፡ ሰው ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ ውለታቸውን ፡ እያስታወሰ ፡ ሊያመሰግናቸው ፡ ይገባል።

ራሳቸው ፡ ደረሱዋቸው ፡ የሚባሉትን ፡ መጻሕፍት ፡ እላይ ፡ አሳሰበነው ፡ እንደነበረው ፡ እየነገሩ ፡ ያጻፉት ፡ እንጂ ፡ ራሳቸው ፡ ብርዕ ፡ ጨብጠው ፡ ብራና ፡ ይዘው ፡ የጻፉት ፡ አይመስልም። ይኸም ፡ የጸሐፊነት ፡ ዋጋቸውን ፡ ሊያስቀርባቸው ፡ አይችልም።

በዛሬው ፡ ዘመን ፡ የእንግሊዝ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ምስተር ፡ ዊንስተን ፡ ቸርቸል ፡ ከጀርመን ፡ ጋር ፡ በአውሮፓ ፡ የተደረገውን ፡ ጦርነት ፡ የሚገልጽ ፡ ማስታወሻውን ፡ በመጽሐፍ ፡ ስላወጣ ፡ በስቶኮልም ፡ የሊቃውንት ፡ ጉባዔ ፡ ለታላላቅ ፡ ሊቅና ፡ አዋቂ ፡ በብርቅ ፡ የሚሸልመውን ፡ የኖቤል ፡ ዋጋ ፡ ፕሪ ፡ ኖቤል ፡ የሚባለውን ፡ ሽልማት ፡ በተሸለመ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በሚገባ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በቅናት ፡ እርሱ ፡ እየተንጐራደደ ፡ ጸሐፊ ፡ እየለዋወጠ ፡ በመንገር ፡ ያሠራው ፡ የጦርነት ፡ ማስታወሻ ፡ ሊያሸልመው ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ የተከራከሩ ፡ ነበሩ። ነገር ፡ ግን ፡ ተቀባይ ፡ አላገኙም ፡ የዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ ያራሲነት ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው። ቸርቸል ፡ ቊጭ ፡ ብሎ ፡ ራሱ ፡ እንዳይጽፍ ፡ የመንግሥቱ ፡ መሪነት ፡ ጊዜ ፡ አይሰጠውም። የርሱ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሲሰበሰቡ ፡ የበላዩ ፡ የጉባዔው ፡ አለቃ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ የሕዝብ ፡ ወኪሎች (ሻምብር ፡ ኦፍ ፡ ኮሙን) በሚሰበሰበበት ፡ በታላቊ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አበላሽህ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አበጀህ ፡ ይኸን ፡ እንደምን ፡ ሠራኸው ፡ እያሉ ፡ በጥያቄ ፡ ሲያጣድፉት ፡ መልስ ፡ በዝርዝር ፡ ሰጭው ፡ እርሱ ፡ ነው።

ስለዚህ ፡ የዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ የሥራ ፡ ብዛት ፡ ከዚያ ፡ የባሰ ፡ ነው። የዚያን ፡ ዘመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት (እንደዛሬም) ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ የቤተ ፡ ክህነቱም ፡ መሪ ፡ ሥራውን ፡ በድምርም ፡ በዝርዝርም ፡ የሚያስሄድ ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ የመጨረሻው ፡ ፈራጅ ፡ ዳኛ ፡ የቤተክርስቲያን ፡ የበላይ ፡ መሪ ፡ የሕንጻዎች ፡ አሠሪና ፡ ፕላን ፡ ሰጭ ፡ ርስትና ፡ ጉልት ፡ ደልዳይ ፡ ሿሚና ፡ ሻሪ ፡ እርሱ ፡ ነው።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሲፈጽም ፡ መ፲መት ፡ ማሰብና ፡ ማሰላሰል ፡ ኣለበት። የይፋቱ ፡ ወይም ፡ የአዳሉ ፡ አለዚያም ፡ የስሜንና ፡ የወገራ ፡ ፈላሾች ፡ ሽፈቱ ፡ ሲባል ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ የጦር ፡ መሪው ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሲሠራ ፡ በውስጡ ፡ ቍጥራቸው ፡ የበዛ ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የቤተክህነት ፡ ረዳቶች ፡ አሉት ፡ እነርሱም ፡ ቀጥ ፡ ለጥ ፡ ብለው ፡ ትእዛዙን ፡ በፍርሐት ፡ ይፈጽማሉ። እንዲያውም ፡ ፩ ፡ ኣንድ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ደክመው ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ባደረሱት ፡ ነገር ፡ እርሱ ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ይመሰገንበታል። በዘመኑ ፡ ያለው ፡ የንጉሡ ፡ ጸሐፊም ፡ እርሱን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ማናቸውንም ፡ ደ፲ኛ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ደራርቦ ፡ የሚጽፈው ፡ ለርሱ ፡ ስለሆነ ፡ በሚቀጥለው ፡ ትውልድ ፡ ዘንድ ፡ በማናቸውም ፡ የሥራ ፡ ግንባር ፡ ሲነሣ ፡ የእውነተኛ ፡ ሠሪዎቹ ፡ ስም ፡ እየጠፋ ፡ ይቀራል። ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሳንዘነጋ ፡ መጻፍ ፡ ቢቀር ፡ ማጻፍ ፡ ማሰብ ፡ ጕዳዩን ፡ መደገፍ ፡ ኣይቀርምና ፡ በማናቸውም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በተገኘው ፡ ሌላም ፡ ጻፈው ፡ ራሳቸውም ፡ ጻፉት ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ እርሳቸውን ፡ ሳናመሰግን ፡ ማለፍ ፡ አንችልም።

የእውነት ፡ ጠላቶች ፡ ደግሞ ፡ ሳንሆን ፡ እነዚያንም ፡ ስማቸው ፡ ያልታወቀውን ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ ማመስገን ፡ ኣለብን።

በዛሬው ፡ ዘመን ፡ ስማቸው ፡ ላልታወቀ ፡ ወታደሮች ፡ ሐውልት ፡ እንደሚቆም ፡ የአበባ ፡ አክሊል ፡ በሐውልታቸው ፡ ላይ ፡ እንደሚቀመጥ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ መንግሥታቸውን ፡ በጦርነትም ፡ በጽሑፍም ፡ አገልግለው ፡ ስማቸው ፡ ተደብቆ ፡ ለቀረው ፡ ለጽራግ ፡ ማሰሬዎች ፤ ለጸሐፍት ፡ ትእዛዛት ፤ ለዓቃቤ ፡ ሰዓቶች ፤ ለብሕት ፡ ወደዶች ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ጠቅላላ ፡ መታሰቢያ ፡ ማቆም ፡ ይገባል።

# ምዕራፍ ፡ ፴፫።

## ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ የጻፉት ፡ ደብዳቤ።

ራሳቸው ፡ ስለአምልኮ ፡ ስለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓትና ፡ ደንብ ፡ የጻፉትን ፡ ወይም ፡ የአጻፉትን ፡ እንደዛሬ ፡ ዘመን ፡ ጽሑፍን ፡ የሚያራባ ፡ የማኅተም ፡ ብልሃት ፡ ስለአልነበረ ፡ በጸሐፊ ፡ እጅ ፡ እያስገለበጡ ፡ ለየአድባራቱ ፡ እየላኩ ፡ እየተነበበ ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ እንዲከበር ፡ ከመጣራቸው ፡ በቀር ፡ ጽሑፉ ፡ ራሱ ፡ እንዳይጠፋ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ትልቅ ፡ አገልግሎት ፡ ሠርተዋል። እንደዚሁም ፡ ራሳቸው ፡ ያልደረሱትን ፡ ከቀድሞ ፡ ዝምሮ ፡ የታወቀውን ፡ ታላላቅ ፡ መንፈሳዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ሁሉ ፡ እያጻፉ ፡ መላካቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው።

ሲኖዶስ ፡ የሚባለውን ፡ ከሐዋርያትና ፡ ከቀድሞዎቹ ፡ ሊቃውንት ፡ የተዘጋጀውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግና ፡ ደንብ ፡ በብራና ፡ በጥሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ኣጽፈው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ ለኣሉት ፡ መነኮሳት ፡ የላኩትን ፡ በሮማ ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ተመልክቼዋለሁ። በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ለመገልበጥ ፡ ስለማይቻል ፡ ይኸንኑ ፡ መጽሐፍ ፡ የላኩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ብቻ ፡ በመጽሐፉ ፡ በመዠመሪያዎቹ ፡ ገጾች ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ አግኝቼ ፡ ገለበጥሁ ፤ ቃሉም ፡ እነሆ ፡ በትክክል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ይገኛል።

“በስመ ፡ **አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ** ፡ አሐዱ ፡ አምላክ። በኲሉ ፡ ልብየ ፡ ዘኪያሁ ፡ አመልክ። በኵሉ ፡ ኃይልየ ፡ ወበኵሉ ፡ ነፍስየ ፡ ወበኵሉ ፡ ሕሊናየ ፡ ዘቦቱ ፡ አሰምክ። ዘእኁዝ ፡ በሐብለ ፡ ኣምልኮቱ ፡ ዘኢይት ፡ በተክ። ዘቦቱ ፡ አሐዩ ፡ ለዝሉፉ ፡ ወኢይትዐወክ። ተጽሕፈት ፡ ዛቲ ፡ መልእክት ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ መጽሐፈ ፡ ሲኖዶስ ፡ እምኅቤየ ፡ እምኅበ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወስመ ፡ መንግሥትየ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ እምኅበ ፡ ኣንበረኒ ፡ አምላከ ፡ እስራኤል ፡ በብዝኃ ፡ ምሕረቱ ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ መንግሥተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በ፯ ፡ ዓመት ፡ እንዘ ፡ ሀሎኩ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ሴዋ (ሼዋ)እንተ ፡ ትሰመይ ፡ ተጕለት። ትብጻሕ ፡ ኀበ

፡ ፍቍራንየ ፡ ማኅበረ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሀገር ፡ ቅድስት ፡ በሰላመ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ አሜን። አስተበጽዓክሙ ፡ ፈድፋደ። ቀዳሚኮንክሙ ፡ ፂዉዋነ ፡ ለቃለ ፡ ወንጌል ፡ ዘይቤ ፡ ዘኢኀደገ ፡ ኣባሁ ፡ ወእሞ ፡ ወብእሲቶወውሉዶ ፡ ወገራውሂሁ ፡ ወኵሎሙ ፡ ዘቦ። ወበእንተዝ ፡ ኃደግሙ ፡ ዓለመ ፡ ወቦእክሙ ፡ ውስተ ፡ ኣርዑተ ፡ ምንኵስና። ወዳግመ ፡ ዔወወክሙ ፡ ቃለ ፡ ነቢይ ፡ ዘይቤ ፡ ኢይበውእ ፡ ውስተ ፡ ጽላሎተ ፡ ቤትየ ፡ ወኢየዓርግ ፡ ውስተ ፡ ዓራተምስካብየ ፡ ኢይውሁቦን ፡ ንዋመ ፡ ለአዕይንትየ ፡ ወኢድቃሰ ፡ ለቀራንብትየ ፡ እስከ ፡ እረክብ ፡ መካኖ ፡ ለ**እግዚአብሔር** ፡ ወማኅደሮ ፡ ለአምላከ ፡ ያዕቆብ። ወበእንተ ፡ ዘአጥባዕክሙ ፡ ለነጊደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሀገሩ ፡ ለንጉሥ ፡ ዓቢይ ፡ እንዘ ፡ ኢትፈርሁ ፡ ምንዳቤ ፡ ፍኖት ፡ ሐሩረ ፡ መዓልት ፡ ወቍረ ፡ ሌሊት ፡ ወቀትለ ፡ ፈያት። ወሶበ ፡ በጻሕክሙ ፡ ህየ ፡ ተፈጸመ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ዘተብህለ* ፡ በነቢይንበውእ ፡ እንከሰ ፡ ውስተ ፡ ኣብያቲሁ ፡ ወንሰግድ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ቆመ ፡ እግረ ፡ እግዚእነ። ወከፈለክሙ ፡ ከመ ፡ ተአምኀ ፡ መካናቲሁ ፡ ቅዱሳተ ፡ እመካነ ፡ ቀጽረቱ ፡ እስከ ፡ መካነ ፡ ዕርገቱ። ወበእንተዝ ፡ ኣነሂ ፡ እትአመን ፡ በጸሎትክሙ ፡ ወበኵሉ ፡ ምንዳቤክሙ ፡ በእንተ ፡ ፍቅረ ፡ ኣምላክ ፡ ዘበጽሐክሙ። እምሥርወ ፡ ልብየ ፡ እኤምኅክሙ ፡ እንዘ ፡ እብል ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ፡ ደቂቀ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘዔወወተክሙ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ምድራዊት ፡ ከመ ፡ ታብጽሕክሙ ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰማያዊት። ሰላም ፡ ለሃይማኖትክሙ ፡ እንተ ፡ **በሥላሴ** ፡ ፍጽምት ፡ ወለምንኵስናክሙ ፡ አምሳላ ፡ መላእክት። ሰላም ፡ ለአእጋሪክሙ ፡ እለ ፡ ኬዳ ፡ ወለኣእዳዊክሙ ፡ እላ ፡ ጐድጐዳ ፡ ወለከናፍሪክሙ ፡ እላ ፡ ሰዐማ ፡ በከመ ፡ ፈቀዳ ፡ ወለአዕይንቲክሙ ፡ ነጽሮ ፡ እለ ፡ አግሃዳ። ገሊላሃ ፡ ኀበ ፡ ተሰብአ ፡ ወቤተ ፡ ልሔምሃ ፡ ኀበ ፡ ተወልደ ፡ አምላክ ፡ ነሢአ ፡ ዘዚአነ ፡ ጠባይዐ ፡ ወኀልሃ ፡ ኀበ ፡ ሰከበ ፡ ወተፀንግዓ። ናዝሬትሃ ፡ ኀበ ፡ ተሐፅነ ፡ ወዮርዳኖስሃ ፡ ኀበ ፡ ተጠምቀ ፡ ከመ ፡ ያንጽሐነ። ቆሮንቶስሃ ፡ ኀበ ፡ ጾመ ፡ በእንቲኣነ። ቀራንዮሃ ፡ ኀበ ፡ ተሰቅለ ፡ ከመ ፡ ይቤዝወነ። ወኀልኀታሃ ፡ ኀበ ፡ ተቀብረ ፡ ወተንሥአ ፡ ከመ ፡ ያሕይወነ። ደብረ ፡ ዘይትሃ ፡ ኀበ ፡ ዐርገ ፡ እምህየ ፡ ኀበ ፡ ኣቡሁ ፡ ኣምላክነ ፡ ከመ ፡ ያብአነ ፡ ውስተ ፡ ውሳጤ ፡ መንጦላዕት ፡ አርያማዊ ፡ ኀበ ፡ ቦአ ፡ ለሊሁ ፡ ሐዋርያነ ፡ ዘእምቅድሜነ ፡ ጽርሐ ፡ ጽዮንሃ ፡ ኀበ ፡ ወረደ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ኀበ ፡ ሐዋርያት

፡ ኣበዊነ። ወሰላም ፡ ካዕበ ፡ ለአዕይንቲክሙ ፡ እለ ፡ ነጸራ ፡ ብርሃነ ፡ ዘይወጽእ ፡ እመቃብሪሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ በቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ ዘውእቱ ፡ መሐትወ ፡ ፋሲካነ። ሰላምክሙ ፡ ወፍቅርክሙ ፡ ጸሎትክሙ ፡ ወበረከትከሙ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌየ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን። ናሁ ፡ ፈኖኩ ፡ ለክሙ ፡ ዘንተ ፡ መጽሐፈ ፡ ከመ ፡ ትትናዘዙ ፡ ቦቱ ፡ በቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ ወበእሑድ ፡ ከመ ፡ ይኩነኒ ፡ ተዝካረ ፡ በኀቤክሙ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ይእዜኒ ፡ ሠራዕኩ ፡ ለክሙ ፡ አነ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወስመ ፡ መንግሥትየ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ እምአመ ፡ አንበረኒ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ መንግሥት ፡ እምኣመ ፡ ንግሥየ ፡ በ፳ ፡ ዓመት ፡ ምድረ ፡ ዝበላ ፡ ወእመንፈቀ ፡ ዘይወጽእ ፡ ግብሩ ፡ በ፪ ፡ ዓመት ፡ ፻ ፡ ሕልቀ ፡ ወርቅ ፡ ከመ ፡ ይኩኖሙ ፡ ሲሳዮሙ ፡ ወዓራሙ ፡ ወሀብኩ ፡ ለማኀበረ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ተዝካርየ ፡ ወለተዝካረ ፡ እግዝእትየ ፡ ማርያም ፡ ወግበሩ ፡ በዓላ ፡ ለባሕቲትየ ፡ አመ ፡ ፩ ፡ ለግንቦት ፡ ልደታ። ኣመ ፡ ፳ወ፩ ፡ ለጥር ፡ ዕረፍታ። አመ ፲ወ፮ ፡ ለነሐሴ ፡ ፍልሰታ ፡ ወበዓለ ፡ ወልዳሂ ፡ እግዚእነ ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ አመ ፡ ፳ወ፩ ፡ ለታኅሣሥ ፡ በዘተወልደ ፡ ወግበሩ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ወበዓላ ፡ ፋሲካ ፡ ዝውእቱ ፡ ትንሣኤ ፡ ሞቱ ፡ ማሕየዊት ፡ ወካዕበ ፡ አክብሩ ፡ ኵሎ ፡ በዓላቲሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ተኣምሪሃ ፡ ፴ወ፪። ወዓዲ ፡ ከመ ፡ ታኅትዉ ፡ ሊተ ፡ ቀናዲላ ፡ ውስተ ፡ መቃብረ ፡ እግዚእነ ፡ ፩ ፡ ወበውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ዴዴሁ ፡ ፩ ፡ በየማኑ ፡ ፩ ፡ በፀጋሙ ፡ ፩ ፡ ወበኀበ ፡ ግንዘቱ ፡ ፫ ፡ ወበኀበሂ ፡ ርእየቶ ፡ መግደላዊት ፡ ፩ ፡ ከመ ፡ ሀይከል ፡ ዘዚአነ ፡ ፫ ፡ ወካዕበ ፡ ኀበ ፡ ዝኅራ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ በጌቴሴማን ፡ ፫ ፡ ኀበ ፡ ተወልደሂ ፡ እግዚእነ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ፩ ፡ ወበኀበ ፡ ዐርገ ፡ እግዚእነ ፡ ውስተ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ፩ ፡ ከመዝ ፡ አኅትዉ ፡ በንዋየ ፡ ዚአየ ፡ ወትረ ፡ ወኢታብጥሉ ፡ ወኢትደምሩ ፡ ንዋየ ፡ ካልዕ። እስመ ፡ አነ ፡ እኁዝ ፡ በሐብለ ፡ ፍቅርክሙ ፡ ጸሎትክሙ ፡ ወበረከትክሙ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌየ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

አ ፡ ፍቀኍራንየ ፡ ኢትበሉ ፡ ለባሕቲትነ ፡ ይወርድ ፡ ብርሃን ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ተመክሐ ፡ ላዕሌክሙ። እስመ ፡ አንትሙ ፡ ተአምሩ ፡ ተመክሐ ፡ ዘያመጽእ ፡

እኵያት ፡ ወትሕትና ፡ ዘይመጽእ ፡ ሠናያተ። ሰላም ፡ ላክሙ ፡ ወሰላመ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ የሀሉ ፡ ምስሌክሙ ፡ አሜን። »

ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ የሚያመለክተው ፡ ንጉሡ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ ለሚቀመጡት ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ መነኮሳት ፡ ጌታችን ፡ በተፀነሰበትና ፡ በተወለደበት ፡ በተሰቀለበትና ፡ በተቀበረበት ፡ ሥፍራ ፡ በመኖራቸው፡ከፍ፡ያለ ፡ ዕድል ፡ እንዳላቸው ፡ ንጉሡ ፡ ማመናቸውን ፡ ስለዚህም ፡ ይቺን ፡ አገር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ለረገጠው ፡ እግራቸው ፡ ለዳሰሰው ፡ እጃቸው ፡ ለተመለከተው ፡ ዓይናቸው ፡ ንጉሡ ፡ እንደግጥም ፡ እያደረጉ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርበዋል። ከዚያ ፡ የሲኖዶሱን ፡ መጽሐፍ ፡ መላካቸውን ፡ እያሳሰቡ ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ እየተመሩ ፡ መነኮሳት ፡ የ**ጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን** ፡ የእመቤታችንን ፡ የማርያምን ፡ በዓል ፡ በየወሩ ፡ እንዲያከብሩ ፡ የቀናዲል ፡ ልክና ፡ መጠን ፡ እየወሰኑ ፡ በየቅዱሱ ፡ ሥፍራ ፡ እንዲያስቀምጡ ፡ ያሳስባሉ። ለመነኮሳቱ ፡ መተዳደሪያ ፡ ለምግብና ፡ ለልብስ ፡ እንዲሆናቸው ፡ ምድረ ፡ ዝበላ ፡ ከሚባለው ፡ ኣገር ፡ በ፪ ፡ ዓመት ፡ ለግብር ፡ የሚወጣውን ፡ ፻ (?)ወቄት ፡ ወርቅ ፡ መስጠታቸውን ፡ እየገለጹ ፡ በመጨረሻው ፡ ላይ ፡ እነዚህ ፡ መነኰሳትና ፡ ምዕመናን ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የሚቀመጡ ፡ እነርሱ ፡ ብቻ ፡ በመሆናቸው ፡ ብርሃን ፡ የሚወርድላቸው (የሚጸድቍ)እነርሱ ፡ ብቻ ፡ መስሏቸው ፡ ትምክሕትና ፡ ኵራት ፡ እንዳያድርባቸው ፡ ኣሳስበዋል። ደብዳቤው ፡ የተጻፈውና ፡ ከሲኖዶሱ ፡ ጋር ፡ የተላከው ፡ በነገሡ ፡ በ፳ኛው ፡ ዓመት ፡ በተጉለት ፡ ሳሉ ፡ መሆኑ ፡ ተገልጿል። የነገሡበት ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አቆጣጠር ፡ ሺ፬፻፹፯ ፡ ሲሆን ፡ ደብዳቤውና ፡ ሲኖዶሱ ፡ ባንድ ፡ የብራና ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ በእጅ ፡ ተጽፎ ፡ የተላከው ፡ በሺ፬፻፶፬ ፡ ዓ.ም ፡ ሕረት ፡ መሆኑ ፡ ነው።



ታሪካዊነቱ ፡ እንደ ፡ ብርቅ ፡ ሊታይ ፡ የሚገባው ፡ የዘመኑን ፡ አጻጻፍና ፡ የፊደል ፡ አጣጣል ፡ ከሚያሳየን ፡ ከደንበኛው ፡ ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ደብዳቤ ፡ የመዠመሪያው ፡ ገጽ።

ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ የሚገኝበት ፡ የሲኖዶስ ፡ መጽሐፍ ፡ እላይ ፡ እንዳመለከትሁት ፡ በሮማ ፡ በትልቍ ፡ የሊቀ ፡ ጵጵስናው (ቫቲካን) መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ነው። በምን ፡ አኳኋን ፡ ይህ ፡ የሲኖዶስ ፡ መጽሐፍ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መነኰሳት ፡ እጅ ፡ ተዛውሮ ፡ ወደሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እንደገባ ፡ አይታወቅም። ንጉሡ ፡ ይኸን ፡ መጽሐፍ ፡ እላኵበት ፡ እደብዳቤው ፡ ላይ ፡ "ከመ ፡ ትትናዘዙ ፡ ባቲ ፡ በቀዳሚት ፡ ሰንበት ፡ ወበእሑድ ፡ ከመ ፡ ይኵነኒ ፡ ተዝካረ ፡ በኀቤክሙ ፡ -ቅዳሜና ፡ እሑድ ፡ እንድትጸልዩበትና ፡ በናንተ ፡ ዘንድ ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲሆነኝ" ይላል። ስለዚህ ፡ ከንጉሣቸው ፡ ዘንድ ፡ የተላከላቸውን ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ አንዱ ፡ የገዳም ፡ አለቃ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶት ፡ ይሆን ፡ በትክክል ፡ አይታወቅም።

ነገር ፡ ግን ፡ ከመስቀል ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ የምዕራብ ፡ ኤውሮፓ ፡ የካቶሊክ ፡ ነገሥታት ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከቱርክ ፡ እጅ ፡ ለማስጣል ፡ ተባብረው ፡ በሚዋጉበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ የሮማ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣናቸው ፡ በርክቶ ፡ ነበር። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በፍሎራንስ (ኢጣልያ)ከተማ ፡ ስለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ ወደፊት ፡ እንደምናነበው ፡ በሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በኤውጀኒውስ ፡ ፬ኛ ፡ ሰብሳቢነት ፡ ትልቅ ፡ ጉባዔ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር። በዚህም ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ከዓጼ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ ከኢየሩሳሌሙ ፡ ገዳማችን ፡ መሪ ፡ ከአባ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ተልከው ፡ የስብሰባው ፡ ተካፋይ ፡ መሆናቸው ፡ ሁሉ ፡ የሮማን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የዚህ ፡ ዘመን ፡ ሥልጣናቸውን ፡ ያሳያልና ፡ ምናልባት ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይኸን ፡ ለታሪክ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ደብዳቤ ፡ ከሲኖዶሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ጋር ፡ በስጦታ ፡ ወይም ፡ በግዥ ፡ አግኝተውት ፡ ይሆናል። ወይም ፡ በጦርነቱ ፡ ሰዓት ፡ ገዳሙ ፡ ሲዘረፍ ፡ ይኸም ፡ መጽሐፍ ፡ ተዘርፎ ፡ በቀን ፡ ብዛት ፡ የሮማ ፡ ቀሳውስት ፡ አግኝተው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍቱ ፡ አግብተውት ፡ ይሆናል።

# ምዕራፍ ፡ ፴፱።

## አባ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ብራንካ ፡ ሌዎንየፍሎራንስ ፡ ጉባዔ ፡ የአባ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ደብዳቤና ፡ መልክተኞች።

ከዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ውጭ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በዘመናቸው ፡ ብዙ ፡ የፈጸሙት ፡ በሌላ ፡ ታሪክ ፡ ሲገኝ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ሙሉ ፡ ኣለመሆኑን ፡ እንረዳለን። ለምሳሌ ፡ ባለፈው ፡ ያነበብነውን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ የላኩትን ፡ ደብዳቤና ፡ የሲኖዶስ ፡ መጽሐፍ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ አያነሣውም። እንደዚሁም ፡ በጀምስ ፡ ብሩስ ፤ በረኔ ፡ ባሴት ፤ በዡል ፡ ፔሩሾ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ እነ ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መጽሐፈ ፡ ምስጢር ፡ መጻፋቸውን ፡ ተኣምረ ፡ ማርያም ፡ በዘመናቸው ፡ መተርጐሙንና ፡ ሌላውንም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሁኔታና ፡ ግንኙነት ፡ አይጠቅስም።

ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መኖራቸው ፡ አይታወቅም። በታሪክ ፡ ነገሥት ፡ መጽሐፋችን ፡ ላይ ፡ ባጭሩ ፡ ስለዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሲጽፍ... ፡ "በመዋዕሊሁ ፡ ኮነ ፡ ተቃሕዎ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ወተዋሥአ ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ምስለ ፡ አሐዱ ፡ አፍርንጅ ፡ እስከ ፡ ከሠተ ፡ ወደረሰ ፡ መጽሐፈ ፡ ምስጢር ፡ የሚል ፡ ይገኛል። ትርጓሜው ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን ፡ ኣባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የሚባሉት ፡ ከአንድ ፡ ፈረንጅ ፡ ጋር ፡ ስለሃይማኖት ፡ መከራከራቸውንና ፡ ይኸንኑ ፡ መጽሐፈ ፡ ምስጢር ፡ የሚባል ፡ መጽሐፍ ፡ ደርሰው ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ ከሠተ ፡ ገለጠ ፡ እያለ ፡ መርታታቸውን ፡ ያመለክታል። ነገር ፡ ግን ፡ የክርክሩ ፡ ዓይነት ፡ ተከራካሪው ፡ ፈረንጅ ፡ አገሩና ፡ ስሙ ፡ አልተገለጸም። ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ የሚባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፉ ፡ በ፪ኛው ፡ ቮሊዩም ፡ ገጽ ፡ ፸፬ ፡ ላይ ፡ እንደገለጸው ፡ ይህ ፡ ፈረንጅ ፡ የተባለው ፡ ፍራንቼስኮ ፡ ደ ፡ ብራንካ ፡ ሌዎን ፡ የሚባል ፡ የኢጣልያ (ቬኔሲያ) ተወላጅ ፡ ነው። እርሱም ፡ ሰዓሊ ፡ ስለነበረ ፡ በአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሳለው ፡ ስዕል ፡ የተነሣ ፡ በዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ጊዜ ፡ የሆነውን ፡ ክርክር ፡ ወደ ፡ ፊት ፡

እንመለከታለን። አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የተባሉት ፡ መጽሐፈ ፡ ምስጢር ፡ የሚባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ደረሱ ፡ የሚለው ፡ እውነት ፡ ነው። ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ እንደጠቀስነው ፡ ከአባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከሕዝበ ፡ ጽዮን ፡ ልጅ ፡ መደረሱ ፡ እርግጥ ፡ ነው።

እርሱም ፡ በፓሪስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ በሙሴ ፡ ዞተንበርግ ፡ የካታሎግ ፡ መጽሐፍ ፡ <u>፻፲፫</u> ፡ ቍጥር ፡ ተሰጥቶት ፡ ይገኛል። የሚናገረውም ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ በ**ክርስቶስ** ፡ አምላክነት ፡ በ፩ ፡ ባሕርይና ፡ በ፪ ፡ ባሕርይ ፡ የተነሣ ፡ የእስክድርያና ፡ የሮማ ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ወገን ፡ እየለዩ ፡ በጉባዔ ፡ እየተሰበሰቡ ፡ እየተከራከሩ ፡ ይጣሉ- ፡ ስለነበረ ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እንደመልስ ፡ እያደረጉ ፡ **አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ** ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ያለውን ፡ አባ ፡ ሰባልዮስን (ሳቤልዩስን) **አብ ፡ ከወልድ ፡ ወልድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** የተለየ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ አባ ፡ አቡሪዩስን ፡ **ክርስቶስ** ፡ ከ**አብ** ፡ ያንሳል ፡ ያለውን ፡ <u>አርዮስን</u> ፡ እመቤታችን ፡ **ክርስቶስ**ን ፡ በሥጋው ፡ እንጂ ፡ በመለኮቱ ፡ አልወለደቸውምና ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ መባል ፡ አይገባትም ፡ ያለውን ፡ <u>ንስጥሮስን</u> ፡ ሌሎቹንም ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ ያሉትን ፡ እነልዮንን ፡ ሁሉ ፡ እየወቀሰ ፡ መልስ ፡ የሰጠበት ፡ መጽሐፍ ፡ ነው። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳልነው ፡ <u>ዲዮስቆሮስ</u> ፡ የተወገዘበትን ፡ የኬልቄዶንን ፡ ጉባዔ ፡ "ማኅበረ ፡ ከለባት- የውሾች ፡ ጉባዔ" ፡ ይለዋል።

ስለዚህ ፡ ምናልባት ፡ ይህ ፡ ብራንካ ፡ ሌዎን ፡ የሚባል ፡ የኢጣልያ ፡ ተወላጅ ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ሃይማኖት ፡ **ክርስቶስ** ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ ወይም ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ አጥብቀው ፡ እያራከሱ ፡ በመናቃቸው ፡ ተናዶ ፡ በዚሁ ፡ ከአባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ጋር ፡ ተከራክሮ ፡ ይሆናል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል። በተረፈ ፡ የዚህ ፡ የኢጣልያ ፡ አመጣጥ ፡ እንደምን ፡ እንደሆነ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ የለም። ባሮንዮስ ፡ የሚባል ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰው ፡ የቤተክርስቲያን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በሚባል ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ በሺ<u>፬የሮ፯</u> ፡ እንደ ፡ ኤው ፡ ቀጥር ፡ አሌክሳንድር ፡ ፫ኛ ፡ የሚባሉት ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ለሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ለቄሱ ፡ ዮሐንስ ፡ ደብዳቤ ፡ ልከዋል። የጻፉትም ፡ ፊልጶስ ፡ ለሚባል ፡ ሐኪም ፡ አደራ ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ ይላል።

የሕንድ ፡ ንጉሥ ፡ ቄሱ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚለውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥን ፡ ነው። ምክንያቱም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፓርቱጊዞችና ፡ የአውሮፓ ፡ ሰዎች ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነገሥታት ፡ ቄሱ ፡ ዮሐንስ ፡ እያሉ ፡ ይጠሩዋቸው ፡ ነበር። ኢትዮጵያንም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሕንድ ፡ እያሉ ፡ ይጽፉት ፡ ነበር። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ኣሌክሳንድር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ የጻፉት ፡ አልተገኘም። እንደዚሁም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ለክሌማንስ (ቀሌምንጦስ) ፰ኛ ፡ መላክተኛ ፡ ልኳል ፡ ዓፄ ፡ ይስሐቅም ፡ ደብዳቤ ፡ ልከዋል ፡ የሚባለው ፡ ሁሉ ፡ የዛሬ ፡ ደንበኛ ፡ ታሪክ ፡ መርማሪዎች ፡ ምንም ፡ ምልክት ፡ ኣላገኙም።

ነገር ፡ ግን ፡ በነአብርሃ ፡ በነካሌብ ፡ ጊዜ ፡ ከቍስጥንጥንያና ፡ ከግሪክ ፡ ኣገሮች ፡ ጋር ፡ የተደረገው ፡ ግንኙነት ፡ ሳይቆጠር ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከአውሮፓ ፡ ጋር ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ ግንኙነት ፡ ማድረጓ ፡ የተጻፈው ፡ በፍሎራንስ ፡ ስብሰባ ፡ ነው። የስብሰባው ፡ ምክንያት ፡ የቱርኮችና ፡ የእስላሞች ፡ ኃይል ፡ በታናሽ ፡ እስያ ፡ በአውሮፓ ፡ ምሥራቅ ፡ በአፍሪካ ፡ ሰሜን ፡ እየበረታ ፡ በመሄዱ ፡ እነዚህን ፡ እስላሞች ፡ ለመመለስ ፡ የካቶሊክና ፡ የኮፕት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድ ፡ ሊሆኑ ፡ የሚችሉበትን ፡ መንገድ ፡ ለመነጋገር ፡ ነው። ለዚህም ፡ ስብሰባ ፡ የተመረጠው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የጽሑፍ ፡ የስእልና ፡ የቅርጽ ፡ በጠቅላላው ፡ የጥበብ ፡ መደበኛ ፡ ሥፍራ ፡ በሆነችው ፡ በፍሎራንስ (በኢጣልያንኛ ፡ ፊሬንሴ ፡ በግዕዝ ፡ ፍሎርንጻ) ነበር። ይህቺ ፡ ከተማ ፡ የምትገኘው ፡ በኢጣልያ ፡ አገር ፡ በሰሜን ፡ በኵል ፡ ነው። የጉባዔው ፡ ሰብሳቢ ፡ የሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ኤውዝኒውስ ፡ አራተኛ ፡ ናቸው። ስብሰባ ፡ የተደረገው ፡ እንደ ፡ ፈረንጆች ፡ ቀጥር ፡ ሺ፬፻፴፰-ሺ፬፻፴፱ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ነው። ዣን ፡ ባቲስት ፡ ኵልቦ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መላክተኞች ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በነሐሴ ፡ ወር ፡ ሺ፬፻፴፰ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ (ቆስጠንጢኖስ) ከእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከአባ ፡ ዮሐንስ ፡ እንደተላኩ ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ደግሞ ፡ ከአባ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ መምህር ፡ ተልከው ፡ መምጣታቸውን ፡ የመላክተኞቹ ፡ ስም ፡ ፩ኛው ፡ የቅዱስ ፡ እንጦንዮስ ፡ ገዳም ፡ መነኵሴ ፡ አባ ፡ እንድርያስና ፡ ጴጥሮስ ፡ መሆናቸውን ፡ እነርሱም ፡ እንድርያስ ፡ ከግብፅ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ መምጣታቸውን ፡ ይገልጻሉ። እኚሁ ፡ ዣን ፡ ባቲስት ፡ የሚባሉት ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡

ክርስቲያን ፡ ቄስ ፡ መላክተኞቹ ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ በኤውዢንዩስ ፡ ፊት ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ በሙሉ ፡ የእስክንድርያም ፡ የኢትዮጵያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ ለመሆን ፡ በፍጹም ፡ ልብ ፡ ንኊሡም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱም ፡ የኢየሩሳሌ ፡ መምህርም ፡ መፍቀዳቸውን ፡ ትሕትና ፡ አክብሮ ፡ አድናቆት ፡ በመላበት ፡ አነጋገር ፡ መናገራቸውን ፡ ይገልጻሉ።

የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ለሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የላኰት ፡ ደብዳቤ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያቀረቡትም ፡ እንደዚሁ ፡ አንድ ፡ ቄስ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የሚጽፈው ፡ እንጂ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የሚጽፈው ፡ አይመስልም ፡ ሲሉ ፡ እኚሁ ፡ አባ ፡ ኰልቦ ፡ ይኸንኑ ፡ ጽሑፍ ፡ የገለጹት ፡ በፍሎራንስ ፡ ስብስባ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ጸሐፊ ፡ በመዝገብ ፡ ጽፎት ፡ የነበረውን ፡ በቫቲካን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አግኝተው ፡ መሆኑን ፡ ገልጸዋል ፡

ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ የሚባሉት ፡ የፈረንሳዊ ፡ ሊቅ ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ምርመራ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ በ፲፰፻፹፪ ፡ ገጽ ፡ በ፩ ሺ፬፻፴፱ ፡ ዓ.ም ፡ ፍሎራንስ ፡ ላይ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ ለማድረግ ፡ ንግግር ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከአውሮፓ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ማድረጋቸውን ፡ በዚህ ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ የግሪክና ፡ የላቲን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አንድነት ፡ ይሁኑ ፡ የተባለውን ፡ ኣሳብ ፡ ከምሥራቅ ፡ ኣገር ፡ የመጡት ፡ ቀሳውስትና ፡ ሊቃውንት ፡ ባለመቀበላቸው ፡ ያንድነቱ ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ሳይደርስ ፡ መቅረቱን ፡ ከእምቢ ፡ ባዮቹም ፡ ጋር ፡ የኢትዮጵያ ፡ መላክተኞች ፡ መደረባቸውን ፡ ይገልጻሉ ፡ "

እንደ ፡ እውነቱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ከአባ ፡ ኰልቦ ፡ አጻጻፍ ፡ የሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ነው። አባ ፡ ኰልቦ ፡ በ፪ ፡ ቮሊም ፡ ያዘጋጁት ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ብዙ ፡ ቊም ፡ ነገር ፡ በውስጡ ፡ የተሸከመ ፡ መሆኑ ፡ ሳይካድ ፡ አልፎ ፡ ኣልፎ ፡ በኣጻጻፋቸው ፡ የሮማን ፡ ቤተክርስቲያንና ፡ የርዕሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቱን ፡ ክብር ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ባጻጻፋቸው ፡ ቅስና ፡ ለተቀበሉበትና ፡ ክፍላቸው ፡ ለሆነው ፡ ለካቶሊክ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ የኣድልዎ ፡ መንገድ ፡ ያሳያሉ።

በዚህ ፡ በፍሎራንስ ፡ ስብሰባ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ መላክተኛም ፡ ደብዳቤም ፡ ኣለመላካቸው ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ የተረጋገጠ ፡ ሆኗል። እስካ ፡

ብዙ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በፍሎራንስ ፡ የተገኙትን ፡ መላክተኞች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እንደላኰዋቸው ፡ የሚያምኑ ፡ ብዙ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ነበሩ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ሔንሪኮ ፡ ቼሩሊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሥነጽሑፍ ፡ ታሪክ" ፡በሚል ፡ አርእስት ፡ ባወጡት ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ አባ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ለሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ለኤውጀኒውስ ፡ ፬ኛ ፡ የጻፉትን ፡ ደብዳቤ ፡ ፍሎራንስ ፡ ከሚገኘው ፡ ከላውሪንዚያና ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አግኝተው ፡ ወደ ፡ ኢጣልያ ፡ ተርጕመው ፡ ስላወጡት ፡ በዚሁ ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ መላክተኞቹ ፡ በትክክል ፡ ያባ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ እንጂ ፡ ያፄው ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ አለመሆናቸው ፡ ተገልጿል።

ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወደዚህ ፡ ስብሰባ ፡ መላክተኛና ፡ ደብዳቤ ፡ በገሀድ ፡ ለመላክ ፡ ሁላት ፡ የሚቸገሩባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ እንዳሉ ፡ መገንዘብ ፡ አለብን።

አንደኛው ፡ በመዠመሪያው ፡ ቮሊም ፡ መጽሐፍ ፡ በ፲፻፹ና ፡ ፲፺ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ሱልጣኖች ፡ መናገሻ ፡ ከተማቸውን ፡ በባግዳድ ፡ ኣድርገው ፡ በመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፤ በአፍሪካ ፡ ሰሜን ፡ ተስፋፍተው ፡ በሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ ምድር ፡ ቅድስት ፡ የምትባለዋን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ ከቱርኮቹ ፡ ለማስለቀቅ ፡ ከ፲፩ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ.ም ፡ ዠምሮ ፡ የሚደረገው ፡ ጦርነት ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ አላቋረጠም።

የቱርኮቹ ፡ ሡልጣኖች ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ ኃይል ፡ እያገኙ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ እንኳን ፡ ሊለቁ ፡ እንዲያውም ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ እነሙራድ ፡ ፪ኛ ፡ እነመሐመድ ፡ ፪ኛ ፡ እየተነሡ ፡ ክርስቲያኑን ፡ የቍስጥንጥንያን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ በ፩ሺ፬፻፶፫ ፡ ዓ.ም ፡ ፈጽመው ፡ ጥለው ፡ የራሳቸውን ፡ ግዛት ፡ ካደረጉ ፡ ወዲህ ፡ በየጊዜው ፡ ግዛታቸውን ፡ እያሰፉ ፡ ከአውሮፓ፤ ከሆንግሪያና፤ ከዘርቤያ፤ ዩጎስላቢ፤ ከአልባንያ ፡ ነገሥታት ፡ እየተዋጉ ፡ ግዛት ፡ ይቀሙ ፡ ዠመር።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በቱርኮች ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ በአውሮፓ ፡ ነገሥታት (በእስላሞቹና ፡ በክርስቲያኖቹ) መካከል ፡ ከፍ ፡ ያላ ፡ ጥላቻና ፡ የበረታ ፡

ጦርነት ፡ ስለነበረ ፡ የፍሎራንሱ ፡ ጉባዔ ፡ በኮፕቶቹና ፡ በካቶሊኮቹ ፡ መካከል ፡ ያንድነት ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግና ፡ የእስላሞቹን ፡ ኃይል ፡ ለመቃወም ፡ መሆኑ ፡ ስለተረጋገጠ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በዚህ ፡ ስብሰባ ፡ በቀጥታ ፡ ተካፋይ ፡ ቢሆኑና ፡ ከኣውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ ግንኙነት ፡ ቢያደርጉ ፡ የቱርክ ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ በነርሱ ፡ ሥር ፡ የሚገኙት ፡ የግብፅ ፡ ገዥዎች ፡ የዘቢድ ፡ ፓሻዎች ፡ በቀጥታ ፡ እንደሚነሡባቸው ፡ በውስጣቸው ፡ ያሉትንም ፡ እስላሞች ፡ እንደሚያስነሡባቸው ፡ ያውቃሉ።

ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በበኵላቸው ፡ የእስላሞቹ ፡ መበርታትና ፡ ማየል ፡ የሚያሰጋቸው ፡ ቢሆን ፡ በውስጣቸው ፡ ካሉት ፡ ፩ ፡ ኣንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሚሸፍቱባቸው ፡ የሐድያ ፡ ገራድና ፡ የአዳል ፡ ባላባቶች ፡ ጋር ፡ የነዚያ ፡ ማየል ፡ ግንኙነት ፡ ቢኖረውም ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ የሚያስደስታቸው ፡ ቢሆንም ፡ በቀጥታ ፡ ከአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ተባብረው ፡ ታላቀኑን ፡ የኦቶማንን (ቱርክ) "መንግሥት ፡ የሚያስቆጣ ፡ ሴራ ፡ ከማድረግ ፡ መጠንቀቃቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው።

ሁለተኛው—በመዠመሪያው ፡ ቮሊም ፡ መጽሐፍ ፡ በ፷፪ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ ባንድ ፡ ባሕርይና ፡ በሁለት ፡ ባሕርይ ፡ ክርክር ፡ ያለውን ፡ ጠብና ፡ ጥላቻ ፡ አንብበናል። ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ አካባቢ ፡ ያሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተመንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እስክንድርያ ፡ እናቴ ፡ ማርቆስ ፡ አባቴ ፡ የሚሉ ፡ የሮማን ፡ ርዕሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትንና ፡ የካቶሊክን ፡ ቤተክርስቲያን ፡ የሚጠሉ ፡ ናቸው። የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ እነ ፡ አባ ፡ ብንያሚን ፡ ሁለት ፡ ባሕርዮችን ፡ በመጥላት ፡ ከእስላሞቹ ፡ እንደተደረቡ ፡ እነዚህም ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥር ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ከካቶሊክ ፡ ክርስቲያን ፡ እስላምን ፡ እንመርጣለን ፡ የሚሉ ፡ ይገኙባቸዋል።

ስለዚህ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የእስላሞቹ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ያገራቸው ፡ ቤተክርስቲያን ፡ የማትወደውን ፡ ያንድነት ፡ ስብሰባ ፡ ከማድረግ ፡ ንጉሡ ፡ መወሰናቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው።

በኢየሩሳሌም ፡ ያሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ገዳም ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ኣባ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ግን ፡ ያሉበት ፡ ሁኔታ ፡ በትንሹ ፡ ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ይለያል።

አበ ፡ ምኔቱ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሲኖሩ ፡ በዚያ ፡ ካሉት ፡ ቊጥራቸው ፡ ከበረከተው ፡ ሥልጣንም ፡ ካላቸው ፡ የካቶሊክና ፡ የግሪክ ፡ ገዳማት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ጋር ፡ ይነስ ፡ ይብዛ ፡ በስምምነት ፡ መኖር ፡ ኣለባቸው ፡ እርሳቸውም ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ተከታይነታቸውን ፡ የሁለት ፡ ባሕርይንም ፡ መሠረት ፡ ሳይለቊ ፡ ካፄ ፡ ዘርዓያቆብም ፡ ፈቃድ ፡ ሳይወጡ ፡ በየስብሰባው ፡ መገኘት ፡ አለባቸው። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ፍሎራንስ ፡ ላይ ፡ በምሥራቅና ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ ስብሰባ ፡ ሲደረግ ፡ መላክተኞችና ፡ ደብዳቤ ፡ መላካቸው ፡ ስለዚህ ፡ ነው።

ነገርግን ፡ ራሳቸው ፡ አላመሄዳቸው ፡ ነገሩከፍ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ በእስላሞቹ ፡ ዘንድ ፡ ጠብ ፡ እንዳያጭር ፡ መሆኑን ፡ ራሳቸው ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ በጻፉት ፡ ደብዳቤያቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ ገልጸውታል .... እኔ ፡ እንዳልመጣ ፡ በእስላሞቹ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይታወቅ ፡ ስለፈራሁ ፡ በጥቅምት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ደብዳቤ ፡ አሲዤ ፡ ልጆቼን ፡ ልኬያቸዋለሁና ፡ ለፋሲካ ፡ ተመልሰው ፡ ወደኔ ፡ እንዲመጡልኝ። ከኔም ፡ ዘንድ ፡ ተልከው ፡ ያልካቸውን ፡ ሁሉ ፡ እንዲነግሩ ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ይሄዳሉ። የክርስቶስን ፡ በጎች ፡ ለመጠበቅ ፡ በቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወንበር ፡ ስለተቀመጥህ ፡ የዠመርኸውን ፡ ኣሳብ ፡ ፈጽመው ፡ ••••ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ከሆነ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ እስላሞቹን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከተቀደሰችዋ ፡ ምድር ፡ አውጥቶ.... ይበትናቸዋል ፡ ፈረንጅ ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ ለመሄድና ፡ ለመመለስ ፡ በጣም ፡ አደገኛ ፡ ይሆንበታል ፡ እኛ ፡ ግን ፡ በቲንሽ ፡ ጦር ፡ ብዙውን ፡ በሚያሸንፈው ፡ በንጉሣችን ፡ ብርታት ፡ እኛን ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ኣያስቸግሩንም። ወዳንተ ፡ መላክተኛ ፡ መላኬን ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳችንና ፡ እስላሞቹ ፡ ኣያውቊም...... ይኸንኑ ፡ የቼሩሊን ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፻፹፫ - ፻፹፬ ፡ ተመልከት።

በዚህም ፡ ላይ ፡ ስብሰባው ፡ በፍሎራንስ ፡ ቢደረግም ፡ በዚያው ፡ በታወቀው ፡ የባሕርይና ፡ የእምነት ፡ ልዩነት ፡ ምክንያት ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴት ፡ እንዳመለከቱት ፡ ከምሥራቅ ፡ ኣገር ፡ የተላኩት ፡ ቀሳውስት ፡ የሮማ ፡ ርዕሰ

፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትን ፡ አሳብ ፡ ሳይደግፉ ፡ ቀርተው ፡ መለያየታቸውን ፡ በግልጽ ፡ እንመለከታለን።

የዚህ ፡ የአንድነት ፡ ነገር ፡ እንኳን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጥብቅነትና ፡ እልህ (ፋናቲክነት)በሞላበት ፡ ጊዜ ፡ ዛሬ ፡ እንኳን ፡ በብዙ ፡ አስተያየትና ፡ ትምህርት ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በለዘቡበት ፡ ጊዜ ፡ ሳይቻል ፡ ቀርቶ ፡ እነሆ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተከፋፍለው ፡ ይኖራሉ። ስለዚህ ፡ የቱርክ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የክርስቲያኖቹ ፡ መከፋፈልና ፡ መድከm ፡ አግዟቸው ፡ ግዛታቸውን ፡ እንደልብ ፡ ያሰፉ ፡ ዠመር።

# ምዕራፍ ፡ ፴፯።

## በእቴጌ ፡ ጽዮን ፡ ሞገሳ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ ቅጣት=ስለ ፡ ዐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዕረፍትና ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት— የዘመኑ ፡ ግጥም።

ዐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ፴፫ ፡ ዓመት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲገዙ ፡ ባለፈው ፡ የተመለከትነው ፡ ከሐድያውና ፡ ከይፋቱ ፡ ከአዳሉ ፡ እስላሞች ፡ ጦርነት ፡ በውስጥ ፡ ደግሞ ፡ አምባ ፡ ነሐድ ፡ የስሜንና ፡ የጸለምት ፡ ሹም ፡ ከሸፈተባቸው ፡ በቀር ፡ እንደዚሁም ፡ በጣዖት ፡ አምልኮ ፡ የተነሣ ፡ ከቤተሰቦቻቸውና ፡ ካንዳድ ፡ ባለሥልጣኖቻቸው ፡ ጋር ፡ ከመጋጨታቸው ፡ በቀር ፡ አብዛኛው ፡ የመንግሥታቸው ፡ ዘመን ፡ በሰላም ፡ አልፏል። በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ ግድም ፡ ኣንደኛዪቱ ፡ ባለቤታቸው ፡ እቴ ፡ ጽዮን ፡ ሞገሳ ፡ ልጃቸውን ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ለማንገሥ ፡ በያለበት ፡ ይላላካሉ ፡ ተብለው ፡ መከሠሣቸውንና ፡ በዚሁ ፡ ተገርፈው ፡ መሞታቸውን ፡ ባዔ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ እናገኛለን። ቃሉም ፡ እንደዚህ ፡ ይላል "...ኣንቺ ፡ እኔ ፡ በመንግሥቴ ፡ ሳለሁ ፡ ልጅሽ ፡ እንዲነግሥልሽ ፡ በየአድባራቱ ፡ ከኣሉት ፡ ቅዱሳን ፡ ጋር ፡ ተላልከሻል ፡ ብለው ፡ ንጉሡ ፡ ቢጠይቊዋቸው ፡ እንደምን ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ አደርጋለሁ ፡ በሕሊናዬም ፡ አላሰብሁ፥ ፡

በአፌም ፡ አልተናገርሁ ፡ ስለዚህ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ የከሰሱኝን ፡ ሰዎች ፡ ቃል ፡ አትስማ ፡ ብለው ፡ መለሱ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ተናደው ፡ እንዲገረፉና ፡ እንዲደበደቡ ፡ አዘዙና ፡ ከዚሁ ፡ ከግርፋቱና ፡ ከድብደባው ፡ የተነሣ ፡ ታመው ፡ ሲኖሩ ፡ ከብዙ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሞቱ። በድብቅም ፡ ወስደው ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ኣቅራቢያ ፡ በሚገኘው ፡ መቅደሰ ፡ ማርያም ፡ በሚባለው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀበሩዋቸው። በተዝካራቸውም ፡ ቀን ፡ ልጃቸው ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ለእናቱ ፡ ለጽዮን ፡ ሞገሳ (ማስቀረቢያ)ሲል ፡ ጧፍና ፡ ዕጣን ፡ ወስዶ ፡ ሰጠ። የዚህን ፡ ወሬ ፡ ዐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሰምተው ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ሰጠህ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቊ ፡ ኣወን ፡ የናቴን ፡ ሞት ፡ ብሰማ ፡ የተዝካሯ (የመታሰቢያዋ)ቀን ፡ ጧፍና ፡ ዕጣን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወስጃለሁ ፡ ብሎ ፡ መለሰ። በዚህም ፡ ተቆጥተው ፡ እርሱንና ፡ ጓደኛውን ፡ መሐሪ ፡ ክርስቶስን ፡ እጅና ፡ እግራቸውን ፡ ኣሥረው ፡ ብዙ ፡ አሠቃዩዋቸው። በኋላ ፡ ግን ፡ የበእደ ፡ ማርያምን ፡ ልበ ፡ ንጹሕነት ፡ ተገንዝበው ፡ መልሰው ፡ ፈቱት»።

ይህን ፡ የመሰለው ፡ ያረጀ ፡ ያባትና ፡ የደረሰ ፡ የልጅ ፡ ጠብ ፡ ለልጅዋ ፡ ባደላች ፡ እናትና ፡ አባት ፡ መካከል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠብና ፡ ሁከት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ ነገሥታት ፡ ዘንድ ፡ ደርሷል።

ቢሆንም ፡ የመንፈሳዊ ፡ ዝንባሌ ፡ ያላቸው ፡ የጌታችን ፡ **የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ**ና ፡ የእመቤታችን ፡ ፍቅር ፡ ያደረባቸው ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ነገሩን ፡ ከከሳሽና ፡ ከወቃሽ ፡ አንደበት ፡ ቢረዱትም ፡ ሴቲቱን ፡ እቴ ፡ ጽዮን ፡ ሞገሳን ፡ ወቅሰው ፡ አሥረው ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ማስቀመጥ ፡ ይበቃ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ግርፋትና ፡ ድብደባ ፡ ባልተገባ ፡ ነበር። ነገር ፡ ግን ፡ ይኸኛውም ፡ እላይ ፡ እንዳልነው ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ለዘውዳቸው ፡ ጥብቅ ፡ ቅናት ፡ ያላቸው ፡ ስለሆኑ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠም ፡ የሚያደርጉ ፡ ሞልተዋል። ዙፋኑን ፡ የተቀናቀኑባቸውን ፡ ሚስትና ፡ ልጆቻቸውን ፡ በሰይፍና ፡ በመርዝ ፡ የሚገድሉ ፡ የወንድ ፡ ነገሥታት ፡ ራሳቸው ፡ ለመንገሥ ፡ ወይም ፡ ልጃቸውን ፡ ለማንገሥ ፡ ሲሉ ፡ ባሎቻቸውን ፡ በሰይፍ ፡ በጥይት ፡ መርዝ ፡ የሚገድሉ ፡ የሚያስገድሉ ፡ እቴጌዎች ፡ ሞልተዋል። የኔሮንና ፡ የናቱ ፡ የአግሪጺን ፡ የአግሪጺንና ፡ የባሏ ፡ የቄሣር ፡ ክሎድዩስ ፡ አሟሟት ፡ በመዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ በገጽ ፡ ፪፻፹፮ ፡

ላይ ፡ ያነበብነው ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ነው። ባገራችንም ፡ ያፄ ፡ ኢያሱ ፡ ኣድያም ፡ ሰገድና ፡ የባለቤታቸው ፡ የእቴጌ ፡ መለኮታዊት ፡ የልጃቸው ፡ የተከለ ፡ ሃይማኖት ፡ ታሪክ ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላል።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በትክክል ፡ ፴፬ ፡ ዓመት ፡ ከሁለት ፡ ወር ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ እንደርሳቸው ፡ ያሉትን ፡ ታላላቅ ፡ ነገሥታት ፡ የማይፈራው ፡ ሞት ፡ እርሳቸውንም ፡ ወሰደ። በዕለተ ፡ ሞታቸው ፡ የሆነውን ፡ ለቅሶና ፡ ሐዘን ፡ ፍታትና ፡ ሥርዓተ ፡ ቀብር ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ አያነሣም። በርሳቸውም ፡ ፋንታ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስማቸውን ፡ ያነሣነው ፡ ልጃቸው ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ነገሡ። ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ የተቀበሩበትን ፡ ሥፍራ ፡ ሙሴ ፡ ዢል ፡ ፔሩሾ ፡ ያሳተሙት ፡ ይህ ፡ እኔ ፡ የተመለከትሁት ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ኣይገልጽም። ነገር ፡ ግን ፡ በፓሪስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚገኘው ፡ ሙሴ ፡ ረኔ ፡ ባሴትም ፡ ሌሎቹም ፡ ያሳተሙት ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ዕረፍቱኒ ፡ ለሐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ኮነ ፡ አመ ፡ ፫ ፡ ለጳጒሜን ፡ ወመቃብሪሁ ፡ ደሴተ ፡ ዳጋ ፡ ይላል ፡ ደሴተ ፡ ዳጋ ፡ የሚባለው ፡ የሚገኘው ፡ በጣና ፡ ባሕር ፡ ነው።

ስለ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ኣጭር ፡ ሐተታ ፡ ለማድረግ ፡ የፈለግን ፡ እንደሆነ ፡ ታሪካቸው ፡ የሚያስገነዝበን ፡ ያፄ ፡ ዳዊት ፡ አራተኛ ፡ ልጅ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ መንግሥትን ፡ የተቀበሉት ፡ ከወንድማቸው ፡ ከተክለ ፡ ማርያም (ሕዝበ ፡ ናኝ) ሳይሆን ፡ ከልጁ ፡ ከዓምደ ፡ **ኢየሱስ** ፡ ነው። ምንም ፡ እንኳን ፡ የወንድሞቻቸው ፡ ልጆች ፡ ሥርወ ፡ **ኢየሱስ**ና ፡ ዓምደ ፡ **ኢየሱስ** ፡ የነገሡበት ፡ ጊዜ ፡ ቲንሽ ፡ ቢሆን ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በወንድሞቻቸው ፡ በነዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ በነዓፄ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ እንደዚሁም ፡ በወንድማቸው ፡ ልጆች ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የነገሥታት ፡ ልጆች ፡ በሚቀመጡበት ፡ በአምባ ፡ ግሸን ፡ ሰፊ ፡ ጊዜ ፡ ያገኙ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ትምህርት ፡ የተማሩ ፡ ይመስላል። ከሁሉ ፡ መንፈሳዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ይበልጥ ፡ ሲኖዶስን ፡ ኣጥብቀው ፡ እንደተመለከቱና ፡ እንደአጠኑ ፡ ይታወቃል ፡

ይኸንንም ፡ መጽሐፍ ፡ ባለፉት ፡ ምዕራፎች ፡ እንደተመለከትነው ፡ በነገሡ ፡ በ፫ኛው ፡ ዓመት ፡ በሚያምር ፡ የብራና ፡ ጽፈት ፡ አዘጋጅተው ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ገዳማት ፡ ሲልኩ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ሁሉ ፡

በአገራቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተክርስቲያንና ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ በዚሁ ፡ መጽሓፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የሕግና ፡ የሥርዓት ፡ ደንብ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሲጥሩ ፡ ስለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከፍ ፡ ያላ ፡ ግምት ፡ እንደነበራቸው ፡ ያስረዳል።

ደግሞ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ይልቍንም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ በሚመላለሱ ፡ ሰዎች ፡ አንደበት ፡ በመስማት ፡ ከሲኖዶስና ፡ ከሌላም ፡ መንፈሳዊ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ በማንበብ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባዔ ፡ በፊት ፡ ያለውን ፡ የቍስጥንጥንያን ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ሥርዓቱን ፡ ሕጉን ፡ እንደወደዱና ፡ እንዳከበሩ ፡ ይታያል።

በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸውን ፡ በቍስጥንጥንያው ፡ ንጉሥ ፡ በትልቍ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ስም ፡ መሠየማቸው ፡ የሐድያውን ፡ ገራድ ፡ የማሂኮን ፡ እኅት ፡ የመሐመድን ፡ ልጅ ፡ ክርስትና ፡ ኣስነሥተው ፡ ባገቡ ፡ ጊዜ ፡ በቆስጠንጢኖስ ፡ እናት ፡ ስም ፡ ዕሌኒ ፡ ብለው ፡ ማስጠራታቸው ፡ የነዚያ ፡ ፍቅር ፡ እንዳደረባቸውና ፡ በሥጋዊና ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥራም ፡ እነዚያን ፡ ለመምሰል ፡ እንዳሰቡ ፡ ይታያል።

በተረፈ ፡ ምንም ፡ በትክክል ፡ ባይታወቅ ፡ ከመንገሣቸው ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ስለቆዩ ፡ በዙፋን ፡ ላይም ፡ ፴፫ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ የግዛት ፡ ዕድሜ ፡ ስላገኙ ፡ ዕድሜም ፡ አዱኛም ፡ ጠግበው ፡ እንደሞቱ ፡ ይታወቃል።

ከብዙ ፡ ሚስቶቻቸው ፡ ከዣን ፡ ኃይላ ፡ ፍሬ ፡ ማርያም ፡ ግራ ፡ ባልቲሐት ፡ ከዕሌኒ ፡ ቀኝ፟ዕ ፡ በዓልቲሐት ፡ ከጽዮን ፡ ሞገሳ ፤ ምናልባት ፡ ከሌሎችም ፡ ስማቸው ፡ ካልታወቀ ፡ ቍባቶች ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፤ ዘርዓ ፡ ኣብርሃምን ፤ ቴዎድሮስን ፡ በትረ ፡ ጽዮንን ፤ ገላውዴዎስን ፤ ዓምደ ፡ ጽዮን ፤ ዓምደ ፡ ማርያምን ፤ መድኅን ፡ ዘመዳን ፤ ሮም ፡ ገነየላን፣ እንኮዬ ፡ እስራኤልን ፤ ሶፍያን ፤ ሰብለ ፡ ማርያምን ፤ ዓመተ ፡ መሢሕን ፤ ባሕር ፡ መንግሣን ፤ አዳል ፡ መንግሣን ፤ አጽናፍ ፡ ሰምራን ፤ ዕድል ፡ ሰምራን ፤ ዓባላ ፡ ማርያምን ፤ ዓመተ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ሲወልዱ ፡ በዘር (በልጅ ፡ ብዛት)በኩልም ፡ የታደሉ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው።

በጠባያቸውና ፡ በዝንባሌያቸው ፡ እንደሌሎቹ ፡ ታላላቅ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቶችና ፡ መሪዎች ፡ እንደ ፡ ሞግሻቸው ፡ እንደ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡

መንፈሳዊነትንና ፡ ሥጋዊነትን ፡ ጭካንኔና ፡ ርኅራኄን ፡ ዠግንነትንና ፡ ጥንቃቄን (ፖለቲከን) ኣደባልቀው ፡ ሲሠሩ ፡ የኖሩ ፡ ትልቅ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ናቸው። ዠግንነታቸው ፡ የኣሕመድ ፡ በድላይ ፡ ጦርነት ፡ ፓለቲካቸውን (ጥንቃቄያቸውን)የገራዱን ፡ አሕመድ ፡ ያሕያን ፡ ወደጦርነቱ ፡ ልምጣ ፡ ቢላቸው ፡ አይፈርስ ፡ ሆነህ ፡ ጠብቅ ፡ ብለው ፡ ጦርነቱ ፡ ሲፈጸም ፡ ለርሳቸው ፡ እንደላከው ፡ ዓይነት ፡ ላጠላታቸውም ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ለላከው ፡ ለኣሕመድ ፡ ገራድ (ለሐድያው)ሸልመው ፡ አስደስተው ፡ ወደግዛቱ ፡ መላካቸው ፡ ርኅራኄያቸውን ፡ ያባታቸውን ፡ ዐፅም ፡ ለመውሰድ ፡ የላኰዋቸውን ፡ መልክተኞች ፡ እምቢ ፡ ብለው ፡ የመለሱትን ፡ ባላገሮች ፡ ምሕረት ፡ አድርገው ፡ ወዳገራቸው ፡ በሰላም ፡ መላካቸው ፡ ጭካኔያቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ልጆቻቸውን ፡ እነ ፡ ገላውዴዎስን ፤ እነ ፡ ዓምደ ፡ ማርያምን ፡ በጣዖት ፡ አምልኮ ፡ የተነሣ ፡ ሚስታቸውን ፡ ጽዮን ፡ ሞገሳን ፡ በዙፋን ፡ ምክንያት ፡ አስደብድበው ፡ ማስገደላቸው ፡ ይገለጻል። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዘውድ ፡ ጭኖእንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ ለሚገዛ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ድብልቅ ፡ ጠባይ ፡ ማሳየት ፡ ኣስፈላጊ ፡ ነውና ፡ በተረፈውና ፡ በጠቅላላው ፡ ዐፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እንደነ ፡ አብርሃ ፡ እንደነ ፡ ካሌብ ፡ እንደነ ፡ ላሊበላ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ናቸው።

በዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ ላይ ፡ አብስሎ ፡ ሳይናገር ፡ ጫፍና ፡ ጫፉን ፡ እየነካ ፡ ቢያልፈውም ፡ አንድ ፡ በዘመናቸው ፡ የፈጸሙት ፡ ድርጅት ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው።

**ሀ**–ከርሳቸውም ፡ በፊት ፡ ከርሳቸውም ፡ በኋላ ፡ ያሉት ፡ ችላ ፡ ያሉትን ፡ ለክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ተቃዋሚ ፡ የሆነውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጣዖትና ፡ የመናፍስት ፡ ኣምልኮን ፡ ኣጥፍተው ፡ ክርስትናን ፡ በኣዲስ ፡ ኃይል ፡ ለማስፋት ፡ አዋጅ ፡ እያወጡ ፡ መጽሐፍ ፡ እየደረሱ ፡ የታገሉት።

**ለ**–አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ የየአውራጃው ፡ ባላባትና ፡ ገዥ ፡ ከመሸፈት ፡ የሚደርሰው ፡ ንጉሡ ፡ ሲርቅ ፡ ሥልጣኑ ፡ ሲቀዘቀዝ ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ዞረው ፡ ዞረው ፡ መመለሻቸው ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ቢሆን ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ እስከ ፡ አክሱም ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ አውራጃዎች

፡ እየጐበኙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባነሰበት ፡ ቦታ ፡ እየተከሉ ፡ መተዳደሪያውን ፡ እየሰጡ ፡ ገዥውን ፡ ወይም ፡ ባላባቱን ፡ እንዳቀባበሉ ፡ እየሸለሙ ፡ አክሱም ፡ መድረሳቸው ፡ አክሱም ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ማድረግ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሹም ፡ ሽር ፡ የሕግና ፡ የሥርዓት ፡ ሥራ ፡ ፈጽመው ፡ ሲጨርሱ ፡ በሔዱበት ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ሲመለሱ ፡ ከሔዱበት ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ ንጉሣዊ ፡ ሰውነታቸውን ፡ በየአውራጃው ፡ እያስገኙ ፡ ሥልጣናቸውን ፡ እያሳዩ ፡ መመለሳቸው ፡ ለፖለቲካና ፡ ላስተዳደር ፡ የሚሰጠው ፡ ጥቅም ፡ ብዙ ፡ ነው። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ያገርንና ፡ የወገንን ፡ ኣንድነት ፡ የሚያጠብቀው ፡ ዋናው ፡ ገመድ ፡ ይኸን ፡ የመሰለው ፡ የመታየትና ፡ ሥልጣንን ፡ የማሰማት ፡ ዘዴ ፡ ነው። ንጉሡ ፡ በያውራጃው ፡ ሲዞር ፡ አቤቱታ ፡ ሲሰማ ፡ አጥፊውን ፡ ሲቀጣ ፡ ተበዳዩን ፡ ሲክስ ፡ ኣውራጃ ፡ ገዥ ፡ የሆነው ፡ ባላባት ፡ ከበላዩ ፡ ባለሥልጣን ፡ እንዳለበት ፡ ይሰጋና ፡ ማናለብኝ ፡ በማለት ፡ በባላገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ዕብሪትና ፡ ዓመፅ ፡ ከመሥራት ፡ ይታገዳል። ባላገርና ፡ ሕዝብም ፡ በሚደረገውና ፡ በኑሮው ፡ የበላይ ፡ ንጉሥ ፡ አለ ፡ በማለት ፡ ባለኣለኝታና ፡ ባለተስፋ ፡ እየሆነ ፡ አገሩንና ፡ መንግሥቱን ፡ ይወዳል።

ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ በዘመናቸው ፡ የሠሩትን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ጨርሶ ፡ አልጻፈውም ፡ የደረሱበትንም ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ በትክክል ፡ አላወሳውም ፡ ያለዚያ ፡ እንደተረትና ፡ እንደወሬ ፡ የሚነገረውን ፡ እስከ ፡ ሱማሌ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ እንደግማሾቹም ፡ እስከ ፡ ሕንድ ፡ ውቅያኖስ ፡ ድረስ ፡ መዝለቃውን ፡ ከዚያም ፡ በሲዳሞ ፡ በከፋ ፡ በወለጋ ፡ መመላለሳቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሊገልጽልን ፡ ይችል ፡ ነበር። ደግሞ ፡ በዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ ላይ ፡ ከእገሌ ፡ አገር ፡ ደረሱ ፡ ሲል ፡ ያገሩ ፡ ስም ፡ ለኛ ፡ ሳይገባን ፡ ይለፍ ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ የሚጠራው ፡ ኣገር ፡ ከነዚያ ፡ ውስጥ ፡ እንደሆነ ፡ ኣይታወቅም።

**ሐ–**በተረፈ ፡ ባለፈው ፡ በወግና ፡ በሥርዓት ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመለከተው ፡ ከቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ሲያያዝ ፡ መምጣቱ ፡ ሳይቀር ፡ እስከዚህ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ችላ ፡ የተባለውን ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዓትና ፡ ኣስተዳደር ፡ እርሳቸው ፡ ኣዳዲስ ፡ ሕግ ፡ እየጨመሩ ፡ ባዲስ ፡ ኃይል ፡ ቀሰቀሰውታል ፡ እመዠመሪያ ፡ ላይ ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ የነበሩትን ፡ ሹማምንትና ፡ ያገር ፡ ባላባት

(ባለጕልት) እንዳላ ፡ የተዉት ፡ ይመስላል። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ የርሳቸውን ፡ ሥልጣን ፡ እያቀዘቀዘ ፡ የነዚያን ፡ የሚያሞቅ ፡ መሆኑን ፡ የነዚያ ፡ ሥልጣን ፡ እየሞቀ ፡ ሲሄድ ፡ ለመሸፈትና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ለመነጠል ፡ መንገድ ፡ የሚከፍት ፡ መሆኑን ፡ ሲረዱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴት ፡ ልጆቻቸውን ፡ ወይም ፡ በጣም ፡ የቀረበ ፡ ሹማቻቸውን ፡ እየሾሙ ፡ ደላድለዋል። ይኸንንም ፡ ሲያደርጉ ፡ በያውራጃው ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ ከቤተ ፡ ሰባቸውና ፡ ከቅርብ ፡ ሹማቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፡ የባለጕልትነትና ፡ የባላባትነት ፡ ትምክህትና ፡ ኵራት ፡ ተወግዶ ፡ ሲልኵት ፡ ወዴት ፡ ሲጠሩት ፡ አቤት ፡ የሚል ፡ ባንድ ፡ መንፈስ ፡ ባንድ ፡ አዛዥ ፡ የሚመራ ፡ አገር ፡ ለመፍጠር ፡ ተመኝተዋል ፡ ማለት ፡ ነው። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በነዚህ ፡ አገረ ፡ ገዥዎች ፡ ኣጠገብ ፡ መልከኛ ፡ ቃለ ፡ ሐፄ ፡ የሚባሉ ፡ እንደጠባቂም ፡ እንደተቆጣጣሪም ፡ መላካቸው ፡ ኣልቀረም ፡ ነበር። ዳሩ ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ጠብ ፡ ሆኖ ፡ እነዚሁ ፡ የንጉሡ ፡ ቤተሰቦችና ፡ ሹማምንቶች ፡ አገር ፡ የማጥፋትና ፡ በንጉሡም ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ ማመጥ ፡ ስለ ፡ ዠመሩ ፡ ሁሉንም ፡ አስነሡና ፡ ራቅ ፡ ማዕሬ ፡ ሔገኖ ፡ ተብለው ፡ በዘመኑ ፡ የሚጠሩትን ፡ እንደ ፡ እንደራሴ ፡ የመሰለ ፡ ብቻ ፡ መላካቸው ፡ ሳይቀር ፡ ሁሉንም ፡ ሥልጣን ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ በእጃቸው ፡ ያዙ። ይኸም ፡ ዘዴ ፡ እንደዛሪ ፡ የሕዝብ ፡ ወኪሎች ፡ ያሉበት ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ባልተስፋፋበት ፡ ዘመን ፡ አገርን ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ መሪ ፡ በሚገዛበት ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣኑን ፡ ሁሉ ፡ በእጁ ፡ ሰብስቦ ፡ እንደልቡ ፡ ለመሥራት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደተፈተነ ፡ ተመልክተናል። ይኸውም ፡ ማለት ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ፕሬዚዳን ፡ የመንግሥቱ ፡ ጠቅላይ ፡ አለቃ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ የውጭ ፡ ጕዳዩን ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ሚኒስትርነቱን ፡ ራሱ ፡ እየመራ ፡ ዝርዝር ፡ ሥራውን ፡ በወኪል ፡ እንደሚያስሄደው ፡ ማለት ፡ ነው። ይኸንንም ፡ ዘዴ ፡ የሕዝባዊ ፡ አስተዳደር (ዴሞክራሲ) መሪዎችም ፡ ተጠቅመውበታል።

**መ**–የጨዋ ፡ ድርጅት ፡ ምናልባት ፡ ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ ይኖር ፡ ይሆናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዓፄ ፡ ዘርን ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን ፡ ደንበኛ ፡ ድርጅት ፡ የተደረገለት ፡ ኣይመስልም። ባለፈው ፡ እንዳልነው ፡ ጨዋ ፡ እንደዜና ፡ መዋዕሉ ፡ አነጋገር ፡ ጠቅላላ ፡ የወታደር ፡ የክፍል ፡ ስም ፡ ነው ፡ በጠቅላላው ፡ እንዳማርኛው ፡ ጨዋ ፡ እንደ ፡ ግዕዙ ፡ ፄዋ ፡ ሲባሉ ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ በዝርዝር

፡ ሲከፋፈሉ ፡ ወርዋሪ ፡ ማሕል ፡ ሰፋሪ ፡ ሰይፈ ፡ ዦግሬ ፡ ወሀ ፡ ስንቍ ፡ እንደሚባለው ፡ በርሳቸው ፡ ዘመን ፡ በፀር ፡ ዋጀት ፤ በድል ፡ ደመና ፤ በድል ፡ ሾተል። ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ በፀር ፡ ሾተል ፤ ድብ ፡ ምልዓት ፤ ዣን ፡ ምልዓት ፤ በድል ፡ መብረቅ ፡ በድል ፡ መስቀል ፤ በአዳል ፡ ዣን ፤ አቄት ፡ በኣምባ ፤ በአዳል ፡ ዋዣት ፤ ጸመና ፡ አምባ ፤ በባሕር ፡ ዋገት ፤ በአዳል ፡ መብረቅ ፡ ዣን ፡ ኣሞራ ፤ ዣን ፡ ጸገና ፤ ዣን ፡ ገደብ ፤ ዣን ፡ ቀንጠፋ ፡ ይባላሉ። ከነዚሁ ፡ የፈረሰኛ ፡ የእግረኛ ፡ ባለጦር ፡ ባለ ፡ ቀስት ፡ ባለ ፡ ሰይፍ ፡ ጀሌ ፡ እየተለየ ፡ በሰላም ፡ ዘመን ፡ በየአገሩ ፡ እየተከፋፈሉ ፡ በድልድል (ተሠሪ)? ሆነው ፡ ይቀመጣሉ። ያሉበት ፡ አገር ፡ መሸፈቱን ፡ የንጉሡ ፡ እንደራሴ ፡ ራቅ ፡ ማሰሬ ፡ ወይም ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ ሲያስታውቃቸው ፡ ወይም ፡ ንጉሥ ፡ ሲያዛቸው ፡ መሣሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ በቶሎ ፡ ወግትው ፡ የሸፈተውን ፡ ክፍል ፡ መደምሰስ ፡ ተግባራቸው ፡ ነበር ፡ ባጭሩ ፡ የዛሬን ፡ ወታደርና ፡ የፖሊስን ፡ ሥራ ፡ ደርበው ፡ ጸጥታ ፡ ጠባቂዎች ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው። በጐናቸው ፡ ያለውም ፡ አገር ፡ ሲሸፍት ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጣቸው ፡ ካሉበት ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ ይዋጋሉ። ለምሳሌ ፡ ደዋሮ ፡ ሸፈተ ፡ ሲባል ፡ በአንጐት ፡ በይፋት ፡ የተሠራው ፡ ጨዋ ፡ ይዝመት ፡ ሲባል ፡ ይዘምታሉ።

ስለዚህ ፡ ጦርነት ፡ በተነሣ ፡ ቍጥር ፡ ባላገርን ፡ ወይም ፡ ደንብና ፡ ቍጥር ፡ የሌለውን ፡ ወታደር ፡ ከማዝመት ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ የተለየና ፡ የተደላደለ ፡ ጦር ፡ ማደርጀት ፡ አገርን ፡ መንግሥትን ፡ ያስከብራል።

ስለዚህ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዦምሮ ፡ እስከ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ድረስ ፡ ካሉት ፡ ነገሥታት ፡ ዋነኛ ፡ ሆነው ፡ የሚታዩ ፡ ትልቅ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ናቸው። ታሪኩን ፡ እንደምንመለከተው ፡ ዓፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ከአዳልና ፡ ከይፋት ፡ እስላሞች ፡ እየተዋጋ ፡ ግዛቱን ፡ በማስፈራት ፡ እኵልነት ፡ ወይም ፡ በዦግንነት ፡ ረገድ ፡ ትንሽ ፡ ብልጫ ፡ ይኖረው ፡ ይሆናል። ነገር ፡ ግን ፡ እንደርሳቸው ፡ በብዙ ፡ በቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ያስተዳደርና ፡ የድርጅት ፡ ቅርንጫፍ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ መድከሙን ፡ የሚያሳየን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ አላገኘንምና ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሥራ ፡ ከሁሉም ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንና ፡ ባፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ዘመነመንግሥት ፡ ላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ አሁንም ፡ እኚሁ ፡ ደጃች ፡ ኃይሉ ፡ የደጃች ፡ እሸቱልጅ) ሰበሰቡት ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፍውስጥ ፡ ስለ ፡ ዓዜ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በዘመኑ ፡ የተገጠመ ፡ ኣለ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንዳመለከትነው ፡ የዘመኑ ፡ አማርኛና ፡ ግዕዝ ፡ እየተደባለቀ ፡ ስለሆነ ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ የግጥሙን ፡ ምስጢሩንና ፡ ቃሉን ፡ በግልጽ ፡ መረዳት ፡ ያስቸግራል ፡ በመጨረሻ ፡ ትንሽ ፡ ሐተታ ፡ ጨምረን ፡ እስክናብራራው ፡ ድረስ ፡ በዘመኑ ፡ የተገጠመላቸው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው።

ዣን ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በድል ፡ ፀሐይ ፡
ኣንዢት ፡ የዚከብራይ ፡
ባልዋ ፡ የባርዜላይ ፡
ዣን ፡ በደበና ፡ ቢታይ ፡
በዓልቱት ፡ ያዘለችው ፡ ይመስል ፡ ሥርናይ ፡
ዣን ፡ በደበና ፡ ቢታይ ፡
ኣበባ ፡ ይመስል ፡ ገለገይ ፡
የመስከረም ፡ ይመስል ፡ ጽገይ ፡
ሰይጣን ፡ አርዌ ፡ በድላይ ፡
የለመደው ፡ በሐርጋይ ፡
የለመደው ፡ በግዳይ ፡
ዣን ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በድል ፡ ፀሐይ ፡
ቀለበው ፡ እንደ ፡ እምባይ ፡
አፈረፀው ፡ እንደሎሚ ፡ ኣልዋኆ ፡ ዋጋ ፡ ይታይ ፡
በትግሬ ፡ በነገደ ፡ **ኢየሱስ** ፡ ጋይ ፡
ግብጽ ፡ የወጻ ፡ ፈርዘነይ ፡ የከመሩበት ፡ ደንጌይ ፡
ሰማ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እንዳይቤይ ፡
በቅዳ ፡ ሐሊታይ ፡ በለሽርጌይ ፡ በኣንጎት ፡ አለ ፡ ይታይ ፡
በለዊስይገይ ፡ በአምሐራ ፡ አለ ፡ ይታይ ፡
በሐምበል ፡ ኣቦከር ፡ ጋይ ፡ በኢይፋት ፡ አለ ፡ ይታይ ፡

ምሽቱ ፡ ዜነባ ፡ እንድታይ ፡
ታንጉት ፡ እንደመረወይ ፡
ትደቊስ ፡ እንደበርበረይ ፡
በፈጠጋር ፡ አለ ፡ ይታይ ፡ በቤዘርድ ፡ ገይ ፡
ስሙ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እንደ ፡ ይዕበይ ፡
በደዋሮ ፡ አለ ፡ ይታይ ፡ በለአሊ ፡ ይታይ ፡
በኄድራ ፡ ገይ ፡ በባሊ ፡ ኣለ ፡ ይታይ ፡
በለዓሊ ፡ ገይ ፡ በሐድያ ፡ አላ ፡ ይታይ ፡
በለአመኖ ፡ ገይ ፡ በእንተዝ ፡ አለ ፡ ይታይ ፡
በለጠጣ ፡ ገይ ፡ በወጅ ፡ አለ ፡ ይታይ ፡
በዜብዳ ፡ ገይ ፡ በዳሞት ፡ አለ ፡ ይታይ ፡
በሞተለሚ ፡ ገይ ፡ በጋፋት ፡ አለ ፡ ይታይ ፡
በኣውላሞ ፡ ገይ ፡ በጐጃም ፡ አለ ፡ ይታይ ፡
በዝርን ፡ ክምር ፡ ገይ ፡
ስም ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሐዳይበይ ፡
ይኸመሩ ፡ ቤት ፡ ደገይ ፡
ስም ፡ የኋላ ፡ እንዲቆይ ፡
አንተ ፡ ያዝብ ፡ ሐባይ ፡ ያልገደልህ ፡ ገደልሁ ፡ ባይ ፡
ያላየህ ፡ ኣየሁ ፡ ባይ ፡ ወሬኛ ፡ እንደገብጠን ፡
ግዳይስ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ለዳኛይ ፡
ወይ ፡ ሎሌ ፡ ዳኛይ ፡ በሌሊት ፡ ፃዕር ፡ መቅደሸይ ፡
ይቀንዕ ፡ ብሕትወደደይ ፡ በራ ፡ ፀመዱ ፡ ብዕራይ ፡
ሲቀዳደም ፡ በፊተየ ፡
አርዌ ፡ በድላይ ፡ ግጻይ ፡ በተኣይ ፡ ዳኛይ ፡
ምሽት ፡ ወይዘሮ ፡ ባልሆነም ፡ ለዋይ ፡
ሰፊ ፡ አገር ፡ ባልሆነም ፡ ለዋይ ፡
አካል ፡ ሐመር ፡ ባልሆነም ፡ ለዋይ ፡
ወርቅ ፡ አምባር ፡ አልሆነም ፡ ለዋይ ፡
ኪዳን ፡ ይሁንኽ ፡ በሰማይ

ጕልትህን ፡ አልሰጥ ፡ ለዋይ ፡
ይላል ፡ ዣን ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡

# ምዕራፍ ፡ ፵፩።

## መስቀልና ፡ ክብሩ-ሰንደቅ ፡ ዓለማ-የመገበያያው ፡ ገንዘብ።

## መስቀልና ፡ ክብሩ።

የዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ከመቀጠላችን ፡ በፊት ፡ ስለመስቀልና ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ስለገንዘባችንም ፡ እንመልከት።

በጣዖትና ፡ በአማልክት ፡ ዓለም ፡ በተዋጠበት ፡ ዘመን ፡ **ክርስቶስ** ፡ በቤተልሔም ፡ ተወልዶ ፡ በናዝሬትና ፡ በገሊላ ፡ አድጎ ፡ በቀራንዮ ፡ ተሰቅሎ ፡ ሲሞት ፡ ከሞት ፡ ተነሥቶ ፡ ወደሰማይ ፡ ካረገ ፡ በኋላ ፡ ሐዋርያትና ፡ ሰማዕታት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ መሥዋዕትነትና ፡ ተጋድሎ ፡ አስተምረው ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ ከአራተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ወዲህ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጳጳሳት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ **ክርስቶስ** ፡ ሁለት ፡ እጆቹን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ዘርግቶ ፡ አንገቱ ፡ ቀለስ ፡ ብሎ ፡ ሁለት ፡ እግሮቹ ፡ ተጣምረው ፡ በምስማር ፡ ተቸንክረው ፡ የተሰቀለበት ፡ መስቀል ፡ እንዲከበር ፡ አደረጉ። በጣም ፡ ከመከበሩ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ለዚህ ፡ ክብር ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ።

ትልቁ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ከማክሳንስ ፡ ጋር ፡ ለውጊያ ፡ በተሰለፈበትና ፡ ለድሉ ፡ በሠጋበት ፡ ሌሊት ፡ "በዚህ ፡ ምልክት ፡ ታሸንፋለህ ፡ » ብሎ ፡ መልአክ ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ በእጁ ፡ እያሳየ ፡ ከነገረው ፡ ወዲህ ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ እየበረከተ ፡ ሔደ። በየቤተክርስቲያኑ ፡ በራፍና ፡ አናት ፡ ላይ ፡ በውስጠኛውና ፡ በውጭው ፡ ግድግዳ ፡ በጳጳሳቱና ፡ በቀሳውስቱ ፡ በዲያቆናቱ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ እየተበጀ ፡ ይሠራ ፡ ጀመር።

በሰባተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ኮስሮዬ ፡ የሚባል ፡ ንጉሥ ፡ የ**ክርስቶስን** ፡ መስቀል ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ማርኮ ፡ በወሰደና ፡ የቍስጥንጥንያው ፡ ንጉሥ ፡ ሔራቅልዮስ ፡ ተዋግቶ ፡ ይኸን ፡ መስቀል ፡ ከሌላው ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ጋር ፡ ኣስመልሶ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሲገባ ፡ የተደረገለት ፡ ኣቀባበል ፡ የተዘመረለት ፡ ዝማሬ ፡ ሕዝብና ፡ ካህናት ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ስለመስቀል ፡ የነበራቸውን ፡ የጋለ ፡ ፍቅር ፡ ያመለክታል።

ይህ ፡ የመስቀል ፡ ክብር ፡ ክርስትና ፡ በገባበት ፡ በታናሽ ፡ እስያና ፡ በኣውሮፓ ፡ እየተስፋፋ ፡ ሔደ። የምዕራብ ፡ አውሮፓ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሻርለማኝ ፡ ክርስትናን ፡ በጎርጎርዮስ ፡ እጅ ፡ ከተቀበለ ፡ ወዲህ ፡ የጀርመን ፡ ቈሣሮች ፡ ክርስቲያን ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ የመስቀል ፡ ክብር ፡ መላውን ፡ አውሮፓ ፡ ወረረው። ነገሥታቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቱ ፡ በየዘውዳቸው ፡ ላይ ፡ ማሠራት ፡ ሥራዬ ፡ ብለው ፡ ያዙት ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ለማስለቀቅ ፡ ከቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ የተዋጉት ፡ ነገሥታትና ፡ ወታደሮች ፡ ሁሉ ፡ በመሣሪያቸውም ፡ በልብሳቸውም ፡ በመለዮዋቸውም ፡ ላይ ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ ኣደረጉ።


እንደዚሁም ፡ ባገራችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ በፍሬምናጦስ ፡ አማካይነት ፡ ክርስትና ፡ በኣብርሃ (ዒዛና)ዘመን ፡ ፫፻፴ ፡ ዔ ፡ ም) ከገባ ፡ ወዲህ ፡ ከሌላው ፡ የክርስቲያን ፡ መሣሪያና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ መስቀልም ፡ ኣብሮ ፡ ገባ። ከኣብርሃ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ በገንዘብና ፡ በዘውዳቸው ፡ ላይ ፡ የጨረቃ ፡ ምልክት ፡ ያደርጉ ፡ የነበረውን ፡ እየተዉ ፡ በመስቀል ፡ እንደተኰት ፡ ግማሾቹም ፡ እንደ ፡ አርማህ ፡ ያሉት ፡ በበትረ ፡ መንግሥታቸው ፡ ጫፍ ፡ መስቀል ፡ እየሰኰ ፡ መያዛቸውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፌ ፡ በአንደኛው ፡ ቮሊም ፡ በሰፊ ፡ ተመልክተናል።

ከኣክሱሞች ፡ በኋላ ፡ በዛጕዌዎችም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የመስቀል ፡ ክብር ፡ እንደቀጠለ ፡ ነው። ዓፄ ፡ ላሊበላ ፡ ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ የሚስቱ ፡ ስም ፡ መስቀል ፡ ክብራ ፡ ሲሆን ፡ በመሣሪያና ፡ በንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ በዘውድና ፡ በየገንዘቡ ፡ በየአልባሳቱ ፡ ላይ ፡ ከሚሠራው ፡ በቀር ፡ በሥያሜ ፡ ላይ ፡ መስቀል ፡ ሥልጣኑን ፡ እንደዘረጋ ፡ እንመለከታለን። ላሊበላ ፡

ካሳነፃቸው ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አንደኛው ፡ የተሰጠው ፡ ለመስቀል (ቤተ ፡ መስቀል) መሆኑን ፡ ተመልክተናል።

ከዛጕዬ ፡ መንግሥት ፡ ወደሸዋ ፡ ለይኵኖ ፡ አምላክና ፡ ለተከታዮቹ ፡ ሲተላለፍና ፡ እስከዚህ ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ሲደርስ ፡ የመስቀል ፡ ክብርና ፡ ፍቅር ፡ እንደቀጠለ ፡ ነው። ባፄ ፡ ዳዊት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ዕሌኒ ፡ ንግሥት ፡ ካገኘችው ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ ግማደ ፡ መስቀል ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስላመጣና ፡ የመጣበትም ፡ ቀን ፡ እንደታላቅ ፡ በዓል ፡ ሆኖ ፡ የመስቀል ፡ በዓል ፡ በያመቱ ፡ ሲከበር ፡ ይበልጥ ፡ ክብሩ ፡ በቤተ ፡ ክህነትና ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ በሕዝብና ፡ በምዕመናን ፡ ዘንድ ፡ ሁሉ ፡ እየተወደደ ፡ እየተከበረ ፡ ሔደ። መስቀልን ፡ ማክበርና ፡ መውደድ ፡ የዋና ፡ ክርስቲያንነት ፡ ምልክት ፡ ሆነ። ንጉሡ ፡ በዘውዱና ፡ በገንዘቡ ፡ ላይ ፡ ሲያሠራው ፡ ጳጳሳት ፡ ቀሳውስት ፡ በበዓል ፡ ቀን ፡ በረዥሙ ፡ ከሚይዙት ፡ ከታላላቁ ፡ ጌጠኛ ፡ መስቀል ፡ በቀር ፡ በዘወትሩም ፡ ቀን ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ምዕመናንን ፡ ያሳልሙበት ፡ ዠመር።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ደብዳቤ ፡ ሲጻፍ ፡ ኣንዳንዶቹ ፡ በደብዳቤያቸው ፡ አናት ፡ የ**ክርስቶስ**ን ፡ ሥነ ፡ ስቅለት ፡ መዠመሪያ ፡ ይስሉና ፡ ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ በስመ ፡ **አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ** ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ ብለው ፡ ይዠምራሉ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ደብዳቤ ፡ በጻፉ ፡ ቍጥር ፡ ሥነ ፡ ስቅለት ፡ መሳሉ ፡ ጊዜ ፡ ስለወሰደባቸው ፡ ይመስለኛል ፡ ስዕሉን ፡ ትተው ፡





የሚል ፡ ምልክት ፡ እያበጁ ፡ ከዚያ ፡ ግርጌ ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ይቀጥሉ ፡ ዠመር። በጽሑፍና ፡ በመጽሐፍ ፡ በንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሴት ፡ ወይዛዝር ፡ በመስቀል ፡ ከመነቀሳቸው ፡ በቀር ፡ በቀሚሳቸው ፡ ላይ ፡ ካንገት ፡ ወይም ፡ ከደረት ፡ ዠምሮ ፡ የሚወርደው ፡ ጥልፍ ፡ እታች ፡ መጨረሻው ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ እየተደረገ ፡ ከጊዜያችን ፡ የደረሰው ፡ ከቀድሞና ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ የቀጠለ ፡ ሳይሆን ፡ ኣይቀርም።

ነገሥታት ፡ ለወዳጆቻቸው ፡ ነገሥታት ፡ እንደደረጃው ፡ በብርና ፡ በወርቅ ፡ መስቀል ፡ እያሠሩ ፡ በኣልማዝና ፡ በዕንቍ ፡ እያስጌጡ ፡ ለገጸ ፡ በረከት ፡

ይልኮት ፡ ዠመር። ሕዝቡ ፡ ከነመኳንንቱ ፡ ሴትና ፡ የሴት ፡ ወይዛዝር ፡ እንዳቅማቸው ፡ በአልማዝና ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ በመዳብና ፡ በብረት ፡ እያሠሩ ፡ ባንገታቸው ፡ ያንጠለጥሉ ፡ ዠመር። ደረታቸውን ፡ ግንባርና ፡ ክንዳቸውን ፡ እየተነቀሱ ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ በአካላቸው ፡ ያበጁ ፡ ዠመር።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሲያደርግ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ የማያየውን ፡ **የክርስቶስን** ፡ ፍቅር ፡ በሚያየውና ፡ ሊዳስሰው ፡ በሚችለው ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ለመፈጸም ፡ ነው። ሁሉም ፡ መስቀል ፡ ኃይልየ ፡ መስቀል ፡ መድኃኒትየ ፡ መስቀል ፡ ፀወንየ ፡ እያለ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ እምነቱን ፡ ኣደረገ። ምዕመኑም ፡ ሁሉ ፡ ባንገቱ ፡ ምስቀል ፡ ሲይዝ ፡ በቄስ ፡ እጅ ፡ መስቀል ፡ ሲሳለም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ካጠገቡ ፡ እንደሚርቅ ፡ እየተማመነ ፡ ከዚያን ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እነሆ ፡ እስከ ፡ ጊዜያችን ፡ ድረስ ፡ መዝለቍን ፡ እንመለከታለን። ይኸም ፡ ባገራችን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥልጣን ፡ በተዘረጋባቸው ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ይነስ ፡ ይብዛ ፡ እንዳለ ፡ ነው።

የጻድቃንና ፡ የሰማዕታትን ፡ አማላጅነት ፡ ለስዕልና ፡ ለምስል ፡ ለምልክት ፡ መስገድን ፡ የሚቃወሙት ፡ ፕሮቴስታንቶችና ፡ አድበንቲስቶች ፡ ብቻ ፡



ይህ ፡ መስቀል ፡ በጫፉ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ መልአክ ፡ ከቀኙና ፡ ከግራው ፡ መልኣክና ፡ ሰው ፡ እንደዚሁም ፡ ሁለት ፡ ርግብ ፡ ከሰውት ፡ ከወደላይ ፡ ያለው ፡ ጽሑፍ ፡ አይነበብም። በመካከሉ ፡ የጌታችን ፡ ሥነ ፡ ስቅለት ፡ እመቤታችን ፡ ከቀኝ ፤ ዮሐንስ ፡ ፍቍሩ ፡ ለእግዚእነ ፡ ከግራ ፡ ይታያሉ። ከነርሱ ፡ ቀኝ ፡ እንደተለመደው ፡ ሚካኤል ፡ በግራ ፡ ገብርኤል ፡ መስቀል ፡ ይዘው ፡ ይታያሉ። በላዩ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የሚነበብና ፡ የማይነበብ ፡ ጽሑፍ ፡ አለበት። ዳዊት ፡ ለኣምሐራ ፡ የሰጠው ፡ የሚል ፡ ተነባቢ ፡ ስላለ ፡ ምናልባት ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል (ዘስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ዳዊት) ፡ ቤተ ፡ አምሐራ (መካነ ፡ ሥላሴ?) የሰጡት ፡ ይመስላል። ይህ ፡ መስቀል ፡ በፍሎራንስ ፡ የጥንታዊ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ይገኛል። በምን ፡ ኣኳኋን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደዚያ ፡ እንደሄደ ፡ በትክክል ፡ ኣልታወቀም። በሥራውና ፡ በቅርጹ ፡ ብዙ ፡ ተመልካቾች ፡ ይደነቁበታል። ከነዚሁም ፡ ሙሴ ፡ ላስቲይሪ (Lasteyrie) ባንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ከነሐተታው ፡ አዘጋጅተዋል። የመስቀልን ፡ ክብር ፡ ስለሚቃወሙ ፡ ከእጃቸውም ፡ ከኣንገታቸውም ፡ ኣርቀውት ፡ ይኖራሉ። እነዚህም ፡ የእንግሊዝና ፡ የአሜሪካ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው። እንደነርሱ ፡ ኣስተያየት ፡ መወደድም ፡ መከበርም ፡ የሚገባው ፡ የተሰቀለው ፡ መሢሕ ፡ **ክርስቶስ** ፡ እንጂ ፡ መሢሑ ፡ የተሰቀለበት ፡ እንጨት ፡ ኣይደለም። የኛዎቹ ፡ ደግሞ ፡ መስቀልን ፡ ሲያከብሩ ፡ ለመስቀል ፡ ታቦት ፡ ሲቀርጹ ፡ እርሱንም ፡ ሲሳለሙ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ተጠቃሎ ፡ ክብሩ ፡ የ**ክርስቶስ** ፡ ለ**ክርስቶስ** ፡ ወደ ፡ **ክርስቶስ** ፡ የሚደርስ ፡ መሆኑን ፡ ያምናሉ።

## ሰንደቅ ፡ ዓላማ።

በኣክሱሞችና ፡ በዛጒዌዎች ፡ ዘመን ፡ የነበረውን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ከነቀለሙ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ መሆኑን ፡ መኖርና ፡ አለመኖሩን ፡ በትክክለኛ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ አልችልም።

በዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ከአርዌ ፡ በድላይ ፡ ሊዋጉ ፡ ሲሔዱ ፡ ወኣዘዘ ፡ ያንጦልዑ ፡ ቀዋመ ፡ ጸርቅ ፡ በየማን ፡ ወበጸጋምብሎ ፡ ሲያነሣ ፡ በእርግጥ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ መኖሩን ፡ ያስረዳል። ነገር ፡ ግን ፡ ቀለም ፡ እንዳለውና ፡ ቀለሙ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ መሆኑን

፡ አይናገርም። ወደፊት ፡ በሦስተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ እንደምናገኘው ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ወታደሮቹን ፡ ይዞ ፡ ከዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጋር ፡ ለጦርነት ፡ በተሰላለፈ ፡ ቊጥር ፡ ለራሱ ፡ ብጫ ፡ ቀለም ፡ የሆነውን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አስይዞ ፡ ቀዩን ፡ ወይም ፡ ነጩን ፡ ኣረንጓዴውን ፡ ሰማያዊውን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ለየጦር ፡ አለቆቹ ፡ በየክፍሉ ፡ እየሰጠ ፡ ማዝመቱን ፡ የዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለሚናገር ፡ ኣዲስ ፡ ድርጅት ፡ እማቀም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ግራኝ ፡ ሰንደቅ ፡ አላማ ፡ ሲኖረው ፡ የቆየውና ፡ የደረጀው ፡ መንግሥት ፡ መሪ ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ እንደሚኖራቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው። እርሳቸውም ፡ ሲኖራቸው ፡ የርሳቸው ፡ አባቶች ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንም ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ እንዳላቸው ፡ ኣይጠረጠርም።

የክርስቲያኖቹም ፡ የእስላሞቹም ፡ የቀለም ፡ ዓይነት ፡ ተመሳሳይ ፡ ሲሆን ፡ ምናልባት ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ በሰንደቅ ፡ ዓላማቸው ፡ ላይ ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ ሲያደርጉ ፡ እስላሞቹ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ የእስላም ፡ መንግሥታት ፡ የጨረቃ ፡ ምልክት ፡ ያደርጉ ፡ ይሆናል።

በ፲፰ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ.ም ፡ በዐፄ ፡ ኢያሱ ፡ ብርሃን ፡ ሰገድና ፡ በዓፄ ፡ ኢዮኣስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ተቀምጦ ፡ ወዳገሩ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ባምስት ፡ ቮሊም ፡ የጻፈው ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ በ፫ኛው ፡ ቮሊም (የፈረ ፡ ትርጉም) ፡ ፫፻፶፫-፫፻፶፬ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ስለባንዲራ ፡ ሲናገር ፡ እንደዚህ ፡ ይላል። «የሐበሾች ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ትልልቅ ፡ ነው። በሰንደቊ ፡ ጫፍ ፡ ቀዳዳ ፡ ያለው ፡ ድቡልቡል ፡ ሆኖ ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ጠባብ ፡ የሐር ፡ ጨርቆች ፡ ጫፋቸው ፡ ወደቀኝ ፡ ተጋድሞ ፡ እንደ ፡ መስቀል ፡ ወፍ ፡ ጭራ ፡ የተቀረጸ ፡ ነው። የእግረኛው ፡ ጦር ፡ ብጫና ፡ ነጭ ፡ ከቀይና ፡ ከአረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ጋር ፡ የተመሳቀለ ፡ አለበት ፡ ፈረሰኛው ፡ ደግሞ ፡ አንበሳ ፡ ያለበት ፡ ቀይና ፡ ቅጠልማ (ወይም ፡ ነጭ) ነው። ይኸንንም ፡ በመጀመሪያ ፡ ያመጡ ፡ ፓርቱጊዞች ፡ ናቸው። ጥቊር ፡ ፈረሰኛ ፡ ደግሞ ፡ በቀይ ፡ ቀለም ፡ ይለይና ፡ አንድ ፡ ብጫ ፡ አንበሳ ፡ ይሳልበታል። ከርሱ ፡ በላይ ፡ የነጭ ፡ ኮከብ ፡ ምልክት ፡ ከነዚህ ፡ ቃላት ፡ ጋር ፡ ይሳላል። ይሁዳ ፡ ወጣት ፡ አንበሳ ፡ ነው። ኮከብም ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ ይወጣል (ዕጓለ ፡ ኣንበሳ.... ኮከብ

፡ ይሥርቅ ፡ እምያዕቆብም?) ። » ይልና ፡ የዚህ ፡ የሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ሥራ ፡ ካፄ ፡ ኢዮአስ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ መቅረቱን ፡ ይገልጻል።

## የመገበያያ ፡ ገንዘብ።

የአክሱሞችን ፡ ገንዘብ ፡ በመዠመሪያው ፡ መጽሐፍ ፡ በምዕራፍ ፡ ፴፬ ፡ ተመልክተናል ፡ ራሳቸውን ፡ ገንዘቦቹንም ፡ በፓሪስ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ ከፈይ ፡ በለበሰ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ከሌሎች ፡ አገሮች ፡ ታሪካውያን ፡ ገንዘቦች ፡ ጋር ፡ በጥንቃቄ ፡ ተደርድረው ፡ አይቻቸዋለሁ። እዚህም ፡ እኛ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ በመጠኑ ፡ አሉ።

በዛጕዬና ፡ በሸዋ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ የገንዘብ ፡ ዓይነት ፡ በፍጹም ፡ አላየሁም። መቸም ፡ ከኣክሱም ፡ ውድቀት ፡ ወዲህ ፡ ከግሪክና ፡ ከቍስጥንጥንያ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚፈልቀው ፡ የማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ሥልጣኔ ፡ በእስላሞቹ ፡ መነሣት ፡ ስለተዘጋ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ነፃነቱን ፡ ባያጣ ፡ ሥልጣኔው ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ መሔዱ ፡ እርግጥ ፡ ነው። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ በአክሱም ፡ ብዙ ፡ ሐውልቶች ፡ ጽሑፋቸውንና ፡ ታሪካዊ ፡ ምልክታቸውን ፡ እንደያዙ ፡ የቆሙ ፡ ሲገኙባቸው ፡ በላስታም ፡ በሸዋም ፡ ከአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በቀር ፡ የሐውልትና ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሕንፃ ፡ እምብዛም ፡ የሉም። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ በሸዋ ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ እነ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እነ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በመልካቸው ፡ ገንዘብ ፡ አስቀርፀው ፡ መገበያየትን ፡ አላወቍበትም ፡ ይሆናል። ወይም ፡ የዚህ ፡ ሥራ ፡ አቅላጩና ፡ የመልክና ፡ የጽሑፍ ፡ ቅርጽ ፡ ሰጭው ፡ ጥበበኛ ፡ ጠፍቶ ፡ ይሆናል።

ነገር ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ ደህና ፡ ኣድርገን ፡ ማረጋገጥ ፡ የምንችለው ፡ በሸዋ ፡ የነገሥታት ፡ መቀመጫ ፡ የነበሩት ፡ መርዓዴ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፤ ደብረ ፡ ምጥማቅ ፤ ጥልቅ ፤ ምድረ ፡ ደጎ፣ ደዋሮ፣ ባደቅ ፤ ኣይፈርስ ፡ ኣምባ ፡ .......እያለ ፡ የዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ የልብነ ፡ ድንግል ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ የሚጠራቸው ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ሥፍራዎቹ ፡ ተቆፍረው ፡ ከተመረመሩ ፡ በኋላ ፡ ነው።

ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ ማኅበር ፡ ከጳፉት ፡ ደብዳቤ ፡ ውስጥ ፡ ለማኅበሩ ፡ ገዳም ፡ መተዳደሪያ ፡ ከዝበላ ፡ ምድር ፡ በ፪ ፡ ዓመት ፡ መቶ ፡ ወቄት (፻ ፡ ሕልቅ) የሚወጣውን ፡ እንደሰጡ ፡ ሲናገር ፡ ምናልባት ፡ ግብርም ፡ ካገር ፡ የሚወጣው ፡ ለየሰውም ፡ ደመወዝና ፡ ዳረጎት ፡ የሚሰጠው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ጥራጥሬ ፡ እህልና ፡ ከብት ፡ ማርና ፡ ቅቤ ፡ ብቻ ፡ ይሆናል። በዚህ ፡ ዘመን ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ በማረከው ፡ ቍጥር ፡ ነፃነቱን ፡ አግኝቶ ፡ ለመለቀቂያ (ዋጀ) ራሱ ፡ ወይም ፡ ዘመዶቹ ፡ ለማራኪው ፡ ይከፍሉ ፡ የነበረው ፡ ወርቅ ፡ በወቄት ፡ መሆኑን ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ የሚናገር ፡ ጽሑፍ ፡ ሞልቷል። በተረፈ ፡ ወደመጨረሻው ፡ ዘመን ፡ ጠበንጃና ፡ ጥይት ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ከገባ ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ ቅርቡ ፡ እስከ ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ጥይትና ፡ ቀለህ ፡ እንደ ፡ አሞሌ ፡ ጨው ፡ መገበያያ ፡ እንደነበሩ ፡ ተመልክተናል።

# ምዕራፍ ፡ ፵፪።

## የመካከለኛው ፡ ምሥራቅና ፡ የአውሮፖች ፡ ሁኔታ።

ከ፲፫ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ዠምሮ ፡ እስካሁን ፡ እስከ ፡ ፲፭ኛውመቶ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ድረስ ፡ የነገሥታቱ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ይነስ (ይብዛ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ሁኔታ ፡ አሳይቶናል። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ያለውን ፡ ኣጭር ፡ የዓለም ፡ ሁኔታ ፡ እንመልከት።

በመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ የአባሲድና ፡ የሳሳኒድ ፡ የኡመያን ፡ ሥርወ ፡ መንግሥት ፡ የሚባሉት ፡ በደማስቆና ፡ በባግዳድ ፡ ተቀምጠው ፡ ከገዙ ፡ የአፍሪካን ፡ ሰሜንና ፡ በመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ቀድሞ ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ግዛት ፡ የነበረውን ፡ ሲያስገብሩ ፡ ኖረው ፡ በመካከሉ ፡ የሞንጎል ፡ ዘር ፡ በጀንጂስ ፡ ካን ፡ ቀጥሎ ፡ በታሜርላን ፡ እየተመራ ፡ በምሥራቅና ፡ ሰሜን ፡ በኵል ፡ ወደ ፡ ቱርኪስታን ፡ ወርዶ ፡ ግዛት ፡ ከተፋለመ ፡ በኋላ ፡ መጨረሻውን ፡ በፊተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ቱርኮች ፡

የሞንጎሎችንም ፡ የዐረቦችንም ፡ ግዛት ፡ በኃይል ፡ ደምስሰው ፡ መካከለኛው ፡ ምሥራቅንና ፡ የአውሮፓን ፡ ምሥራቅ ፡ ይዘው ፡ ያስተዳድሩ ፡ ዠመር። ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳልነው ፡ የአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ እየተባበሩ ፡ የቀረው ፡ ቢቀር ፡ የጌታችን ፡ መቃብር ፡ ከሚገኝበት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ እንኳን ፡ ፈጽሞ ፡ ማስወጣት ፡ የማይቻላቸው ፡ ሆኖ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ በኃያላን ፡ ነገሥታት ፡ በነሙራድ ፡ ፪ኛ (ሺ፬፻፳፩ - ሺ፬፻፶፩ ፡ ዓ.ም) በነመሐመድ ፡ ፪ኛ ፡ ጊዜ ፡ እያየለ ፡ ሄዶ ፡ ግዛቱን ፡ ከምዕራብ ፡ በኵል ፡ የአውሮፓን ፡ ክፍለ ፡ አህጉሮች, ፡ ግሪክን ፡ አልባንያን ፡ ዩጎስላቪያን ፡ ቡልጋሪያን ፡ እስከ ፡ ነምሳና ፡ ሆንግሪ ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ፋርስና ፡ እስከ ፡ ቻይና ፡ ግዛት ፡ ድረስ ፡ አደረሰው።

ቈስጠንጢኖስ ፡ የመሠረተው ፡ ታላቍ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ያገነነው ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ መንግሥት ፡ ከዐረቦች ፡ መነሣት ፡ ወዲህ ፡ የአፍሪካ ፡ ሰሜንን ፡ በሙሉ ፡ አጥቶ ፡ በቱርኮችም ፡ ጊዜ ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ ግዛቱን ፡ ከተቀማ ፡ ወዲህ ፡ በመጨረሻ ፡ ኃይለኛው ፡ የቱርክ ፡ ሱልጣን ፡ ዳግማዊ ፡ መሐመድ ፡ እንደ ፡ ኤው ፡ ቍ (ሺ፬፻፶፩-ሺ፬፻፹፩ ፡ ዓ.ም) ሲነሣ ፡ የቍስጥንጥንያን ፡ መንግሥት ፡ ፈጽሞ ፡ ለመደምሰስና ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥት ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ እንዲጠፋ ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ አድርጎ ፡ ከተማይቱን ፡ ከበባት። የመጨረሻው ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ፲፩ኛው ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ እንዲረዱት ፡ ለአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ ጥሪ ፡ አደረገ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ በበኵላቸው ፡ በዙፋንና ፡ በግዛት ፡ በሥልጣን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚከራከሩበት ፡ ጒዳይ ፡ ስላለ ፡ ይኸን ፡ በቱርኮች ፡ ተከቦ ፡ የተጨነቀውን ፡ የመጨረሻ ፡ ቄሣር ፡ ሊረዱት ፡ ኣልቻሉም። ቢሆንም ፡ እንደማያሸንፍ ፡ እያወቀ ፡ ያባቶቹን ፡ ስም ፡ የራሱንም ፡ ክብር ፡ ሳያሳድፍ ፡ ብቻውን ፡ ከተማይቱን ፡ ሲከላከል ፡ ቆይቶ ፡ ከተማይቱ ፡ ተቃጥ ፡ ስትጨስ ፡ በጭሱ ፡ መካከል ፡ ሰይፉን ፡ ይዞ ፡ ውጊያውን ፡ ሲቀጥል ፡ ተመትቶ ፡ የጐበዝ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ አሟሟት ፡ ሞተ። እርሱ ፡ በሺ፬፻፵፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሲሞት ፡ የነቴዎዶስዮስ ፡ የነሔራቅልዮስ ፡ የነፎካስ ፡ የነሞሪስ ፡ አገርና ፡ ከተማ ፡ ፈጽሞ ፡ ወደቀችና ፡ የቱርክ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መቀመጫ ፡ ሆነች ፤ ስሟም ፡ <u>ቍስጥንጥንያ</u> ፡ መባሏ ፡ እያደር ፡ ቀርቶ ፡ በእስላሞቹ ፡ አነጋገር ፡ <u>እስጣምቡል</u> ፡ ትባል ፡ ዠመር።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ግብፆች ፡ የጥንት ፡ ገናንነታቸው ፡ ጠፍቶ ፡ ከፋርስ ፡ ወደ ፡ ግሪክ ፡ ከግሪክ ፡ ወደ ፡ ሮማውያን ፡ ከሮማውያን ፡ ወደ ፡ ዐረቦች ፡ ከገዥ ፡ ወደ ፡ ገዥ ፡ እየተላለፉ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ማመሉክ ፡ የሚባሉት ፡ ሱልጣን ፡ መሊክ ፡ ሳሊህ ፡ የመሠረታቸው ፡ ገዦዎች (ከሊፋዎች)




የዘመኑን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አውራጃዎች ፡ በዘመኑ ፡ ኣጠራር ፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ የሚያሳይ ፡ ደራሲው ፡ ያዘጋጀው ፡ ያገር ፡ ካርታ።

፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በነፃነት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለቱርክ ፡ ሥልጣን ፡ እየገበሩ ፡ የአፍሪካን ፡ ሰሜን ፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅም ፡ ፓለስቲንንና ፡ ሶርያን ፡ ይዘው ፡ ያስተዳድራሉ። የዐረብና ፡ የኑብያ ፡ ክፍልም ፡ ወደ ፡ ነርሱ ፡ ሲሆን ፡ በቱርክ ፡ ሥልጣን ፡ የተደገፉት ፡ የግብፅ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክርስቲያናዊ ፡ መንግሥት ፡ ለመጣል ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልጣሩም። ነገር ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ከአውሮፓ ፡ የክርስቲያን ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ከኢየሩሳሌምና ፡ ከእስክንድርያ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖችም ፡ ጋር ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ግኑኝነት ፡ እንዳያደርጉ ፡

አጥብቀው ፡ እየተቆጣጠሩ ፡ መንግሥቱ ፡ ኃይል ፡ እንዳያገኝ ፡ መጠባበቃቸው ፡ ኣልቀረም። በዚህም ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኣብዛኛ ፡ ሕዝብ ፡ በ፩ ፡ ባሕርይ ፡ የሚያምን ፡ የኮፕት ፡ ክርስቲያን ፡ በመሆኑ ፡ በ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ከሚያምኑት ፡ ከአውሮፓ ፡ ነገሥታትና ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ እምብዛም ፡ ከልብ ፡ መስማማት ፡ ስለማይሆንለት ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እንደ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ያሉ ፡ ብርቱ ፡ ነገሥታት ፡ ስለሚነሡበት ፡ ኢትዮጵያን ፡ የመውረሩን ፡ ነገር ፡ ችላ ፡ ያሉት ፡ ይመስላል።

በመካከለኛው ፡ ምስራቅና ፡ በአፍሪካ ፡ በኵል ፡ ያለውን ፡ በጥቂቱ ፡ ከተመለከትን ፡ በኋላ ፡ ኣሁን ፡ የአውሮፓን ፡ ሁኔታ ፡ እንመልከት። ሁሉ ፡ በአንድነት ፡ በሮማ ፡ የቄሣር ፡ ግዛት ፡ ተጠቅልሎ ፡ የኖረው ፡ አውሮፓ ፡ በኋላ ፡ በ፰ኛውና ፡ በ፱ነኛው ፡ መቶ ፡ ዓ.ም ፡ ላይ ፡ በሻርለማኝ ፡ በፈረንሳዮች ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በኦቶን ፡ በጀርመን ፡ የቄሣር ፡ ነገሥታት ፡ እየተከፋፈለ ፡ ሲዛ ፡ የኖረው ፡ በኣሁን ፡ ጊዜ (ሺ፫፻–ሺ፭፻ ፡ ዓ.ም) ሁሉም ፡ በነገሥታትና ፡ በመሣፍንት ፡ ተከፋፍሎ ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ይተዳደራል።

ከምዕራብ ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገርና ፡ ከሰሜን ፡ ዝምሮ ፡ ኖርቬዥ ፡ ስዊድን ፡ ዳኒማርክ ፡ ከዚያ ፡ ትልቍ ፡ የጀርመን ፡ የቄሣር ፡ ግዛት ፡ የፈረንሳዊ ፡ የፓርቱጋልና ፡ የኤስፓኝ ፡ የናባራ ፡ የአርጎና ፡ ከወዲህ ፡ የፖሎኝ ፡ የሆንግሪ ፡ መንግሥታት ፡ በየክፍላቸው ፡ በነገሥታት ፡ እየተገዙ ፡ መንግሥት ፡ አቆሙ። የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ትልቍ ፡ የመስኮብ ፡ መስፍን ፡ ትልቍ ፡ የሊቷኒ ፡ መስፍን ፡ ግዛት ፡ ይባላሉ። ሌላውን ፡ ሰፊውን ፡ የአውሮፓ ፡ ግዛት ፡ በነዩልዩስ ፡ ቄሣር ፡ በነአውግስጦስ ፡ ጊዜ ፡ መጠቅለል ፡ የቻለው ፡ የኢጣልያ (ሮማ) መንግሥት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከሁሉ ፡ የባሰ ፡ በብዙ ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሥታትና ፡ መሣፍንት ፡ ተከፋፍሎ ፡ ይተዳደራል። እነሱም ፡ የቬኔሲያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ የሚላኖ ፡ መስፍን ፡ የጀኖሳ ፡ ሬፑብሊክ ፡ የፊሬንሴ (ፍሎራንስ)ሬፑብሊክ ፡ የኤሚሊያ ፡ መስፍን ፡ የናፖሊ ፡ መንግሥት ፡ ይባላሉ።

የሮማ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ደግሞ ፡ መቀመጫቸውን ፡ በሮማ ፡ አድርገው ፡ በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ የአውሮፖ ፡ ነገሥታትና ፡ መሣፍንት ፡ ላይ ፡

በመንፈሳዊ ፡ አባትነት ፡ እያመካኙ ፡ በሥጋዊ ፡ አስተዳደር ፡ ጭምር ፡ እየገቡ ፡ የበላይነታቸውን ፡ አጽንተውባቸው ፡ ኖሩ።

በመዠመሪያው ፡ ሾሊም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በምዕራፍ ፡ ፳፱ ፡ ገጽ፻፸፫ ፡ ፻፸፯ ፡ ላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ የአሞን (ጣዖት) ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ የናፓታንና ፡ የመርዌን ፡ ነገሥታት ፡ በመልእክት ፡ ይሾሙ ፡ ይሽሩ ፡ እንደነበረ ፡ እነዚህም ፡ የሮማ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አንተን ፡ ቀብቸሃለሁ ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ዙፋን ፡ አይገባህምና ፡ አልቀባህም ፡ አንተ ፡ መናፍቅ ፡ ነህ ፡ ተቀጣ ፡ አንተ ፡ ፍጹም ፡ ካቶሊካዊ ፡ ክርስቲያን ፡ ነህ ፡ ቄሣር ፡ ሁን ፡ ግዛትህን ፡ አስፋ ፡ እያሉ ፡ የበላይነታቸውን ፡ እያሳዩ ፡ እስከ ፡ ፲፭ኛው ፡ መቶ ፡ ዓ.ም ፡ ከዘለቀ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻው ፡ እነሉዶቪክ ፡ እነፍሬዴሪክ ፡ የጀርመን ፡ ነገሥታት ፡ በጊዜያቸው ፡ የሮማን ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ሥልጣን ፡ እየተቃወሙ ፡ የመንፈሳዊና ፡ የሥጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲለይ ፡ አደረጉ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከተደረገው ፡ ከብዙው ፡ ዓይነተኛ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ክሪስቶፍ ፡ ኮሎምብ ፡ አሜሪካንን ፡ ማግኘቱ ፡ የማተሚያ ፡ የሰዓት (በግድግዳ ፡ የሚንጠለጠል) ጥበብ ፡ መገኘቱ ፡ የፓርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ መዠመሪያ ፡ እነማርኮ ፡ ፓሎ ፡ የመረመሩትን ፡ የምሥራቅ ፡ መንገድ ፡ በመከተል ፡ መርከብ ፡ እያዘጋጀ ፡ የምሥራቅን ፡ አገሮች ፡ እየመረመረ ፡ ሕንድን ፡ መያዙ ፤ በአፍሪካና ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ጠረፍ ፡ ከቱርክ ፡ መንግሥት ፡ እየተፋለመ ፡ አገር ፡ መያዙ ፡ ነው። የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ታሪክ ፡ ብዙገጽ ፡ የሚፈጅ ፡ ሰፊ ፡ ሐተታ ፡ ስላለው ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጕዳይ ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ ታሪክ ፡ ወደ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ እንመለስ።

# ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ ፵፫ ፡

## ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የመንግሥትን ፡ ሥልጣን ፡ መያዝ።

ከዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ቀጥሎ ፡ ልጃቸው ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ነገሡ። በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ አካሔድ ፡ የነገሡበት ፡ ዘመን ፡ ፲ ዓመት ፡ የሞቱት ፡ በ፴ ዓመታቸው ፡ ስለሆነ ፡ ሲነግሡ ፡ የ፳ ፡ ዓመት ፡ ወጣት ፡ ነበሩ ፡ ማለት ፡ ነው።

ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ወደመጨረሻው ፡ ግድም ፡ እናትዮዋ ፡ ጽዮን ፡ ሞገሳ ፡ እኔ ፡ በሕይወቴ ፡ እያለሁ ፡ ልጅሽን ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ለማንገሥ ፡ ከየአድባራቱ ፡ ቀሳውስት ፡ ጋር ፡ ተላልከሻል ፡ ተብለው ፡ በዚሁ ፡ ተገርፈው ፡ መሞታቸውን ፡ የለቱለት ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በ፲፪ ፡ በ፴ ፡ ወይም ፡ በ፵ኛው ፡ ቀን ፡ ለናታቸው ፡ ቍርባን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጧፍ ፡ ዕጣን ፡ ቢወስዱ ፡ ኣሮጌውን ፡ ንጉሥ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ አናደኊቸው ፡ እማሥር ፡ መድረሳቸውን ፡ ባለፈው ፡ ተመልክተናል።

ስለዚህ ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ መጨረሻውላይ ፡ ባባትና ፡ በልጁ ፡ መካከል ፡ ፍቅርና ፡ ስምምነት ፡ እንዳልነበረ ፡ እንረዳለን። ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ ጠቡ ፡ ሳይዘልቅ ፡ በጠብ ፡ ፈንታ ፡ ሰላምና ፡ ይቅርታ ፡ መተካቱን ፡ ለመግለጽ ፡ በዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ተጽፏል።

«......፡በመጨረሻ ፡ ንጽሕናውን ፡ ተመልክተው (ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በእደ ፡ ማርያምን) ፈትተው ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ወደ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ልኳቸው ፡ የነበሩት ፡ መላክተኞችም ፡ ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አይደርስብህም ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ይዘው ፡ ከደብረ ፡ ሊባኖስ ፤ ከደብረ ፡ ከሶ ፤ ከመምህር ፡ አቡቂር (የእንደገብጠኑ)መጡለት። እነዚህ ፡ ቅዱሳን ፡ ወደኛና ፡ ወዳባትህ ፡ ወደተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተማጥኗልና ፡ ልጅህን ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ አትበድለው ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ልከው ፡ ነበር። ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ ከቅዱሳኑ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ መልእክት ፡ በደረሳቸው ፡ ጊዜ ፡ ልጃቸውን ፡ በእደ

፡ ማርያምን ፡ በጣም ፡ ወደዱት ፡ በሁሉም ፡ ላይ ፡ እንዲያዝ ፡ ሹመት ፡ ሰጡት ፡ ንጽራግንም ፡ እንዲያዝ ፡ ከሰውም ፡ ገንዘብ (ጒቦ?) እንዳይፈልግ ፡ ሌሎቹ ፡ ልጆች ፡ በማሉበት ፡ ቀን ፡ አስማሉት። በታመሙ ፡ ጊዜ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ባለበት ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ጠርተው ፡ የምልክህ ፡ ሥፍራ ፡ አለኝና ፡ አረማመድህን ፡ ኣሳምር ፡ ብለው ፡ አስጠነቀቀኍት። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሲሞቱ ፡ የቀሩት ፡ የነጋሢ ፡ ልጆች ፡ ታሥሩና ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ጳጕሜ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ እሑድ ፡ እዙፋን ፡ አውጥተው ፡ አነገሡት። »

ስለዚህ ፡ ባንዳንድ ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ በቆዩ ፡ በአረጁ ፡ ነገሥታትና ፡ ለአልጋ ፡ በደረሱ ፡ ልጆቻቸው ፡ መካከል ፡ በሌላም ፡ አገር ፡ ባንዳንድ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ እንደሚደርሰው ፡ በለቃቂው ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ በተቀባዩ ፡ በበእደ ፡ ማርያም ፡ መካከል ፡ ጠብ ፡ ሆኖ ፡ ልጅየው ፡ በእሥራት ፡ እንዳሉ ፡ የየገዳማቱ ፡ መነኰሳት ፡ አማልደው ፡ ማስፈታታቸውን ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የየገዳማቱ ፡ መምህራንና ፡ ቅዱሳን ፡ ልባቸው ፡ ወደ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ማዘንበሉን ፡ በሌላውም ፡ ወገን ፡ እርሳቸው ፡ በእርጅና ፡ መዳከማቸውን ፡ ተረድተውና ፡ አመዛዝነው ፡ ታመው ፡ ባልጋ ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ ለልጃቸው ፡ ምሕረት ፡ ማድረግ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሥልጣንም ፡ ሰጥተው ፡ ሲሞቱም ፡ እንዲነግሡ ፡ በኑዛዜ ፡ እንዳጸደቀኍላቸው ፡ ይታያል። በዚህም ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ በልጃቸው ፡ አለማምረራቸው ፡ ልጅየውም ፡ ኣባትዮውም ፡ ሳይሞቱ ፡ ልንገሥ ፡ ብለው ፡ ሳይሸፍቱ ፡ በትእግሥት ፡ ዘውድን ፡ በሰላም ፡ መቀበላቸው ፡ ሁለቱንም ፡ ያስመሰግናቸዋል። ይኸን ፡ ምሳሌ ፡ ያፄ ፡ ኢያሱ ፡ ኣድያም ፡ ሰገድ ፡ ልጅ ፡ ዓፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት (አብራክ ፡ ሰገድ ፡ ወይም ፡ ልዑል ፡ ሰገድ) ሊከተሉት ፡ ይገባ ፡ ነበር። የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ምዕራፍ ፡ ፵፮ ፡ ከገጽ ፡ ፻፵፫-፻፵፫ ፡ በዓፄ ፡ ኢያሱ ፡ ኣድያም ፡ ሰገድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ መጨረሻ ፡ ባፄ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ የሆነውን ፡ አንባቢ ፡ ቢያስታውስ ፡ በነዚያና ፡ በነዚህ ፡ መካከል ፡ የሆነውን ፡ ልዩነት ፡ ሊረዳው ፡ ይችላል።

# ምዕራፍ ፡ ፵፬።

## የእሥረኛ ፡ ምሕረትና ፡ ሹም ፡ ሽር-ያስተዳደር ፡ ልዩነት።

ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ መንግሥትን ፡ እንደያዙ ፡ በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የፈጸሙት ፡ ለእስረኛ ፡ ምሕረት ፡ መስጠትና ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ ማድረግ ፡ ነው። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ በቀጥታ ፡ የሚለውን ፡ እንመልከት ፡ «በመሸ ፡ ጊዜ ፡ የደብረዳሞን ፡ ነበርዕድ (ንቡረ ፡ ዕድ) አባ ፡ ማቴዎስን ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ኣልፋንና ፡ አባ ፡ ሙሴን ፡ ጠርተው ፡ ስለርሳቸውም ፡ ስለአባታቸውም ፡ ምሕላ ፡ እንዲይዙ ፡ ኣዘዟቸው። የሚያጥኑበት ፡ ዕጣንም ፡ ሰጧቸው። በማግሥቱ ፡ ሰኞ ፡ ጧት ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ አዋጅ ፡ አስነገሩ። በወህኒ ፡ ቤትም ፡ በግዞትም ፡ ያላችሁ ፡ እስረኞች ፡ ስላእመቤታችን ፡ ስንል ፡ አባቴም ፡ እኔም ፡ ምሕረት ፡ አድርገንላችኋልና ፡ በደስታ ፡ ወደየቤታችሁ ፡ ተመለሱ ፡ ይኸንንም ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ በዣን ፡ በለው ፡ በዣን ፡ አስፈሬ ፡ በሌላም ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ ፈረሶች (ፈረሰኞች?) በዙሪያቸው ፡ ሰብስበው ፡ በትእዛዛቸው ፡ ውስጥ ፡ አደረጓቸው። በዚህም ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸው ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ያመሰግናቸው ፡ ዠመር። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ቀድሞ ፡ ሹመቱ ፡ ሁሉ

በኣባታቸው ፡ እጅ ፡ ተይዞ ፡ የነበረውን ፡ አሁን ፡ በያገሩ ፡ ቀጥሎ ፡ እንዳለው ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ ኣደረጉ።

ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዘየማን ፡
» » ዘፀጋም ፡

ከነዚህ ፡ በታች ፡ ደግሞ ፡ ሌሎቹን ፡ በየማዕርጋቸው ፡

- በሸዋ ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡
- በኣምሐራ ፡ ጻሕፈ ፡ ላም
- በኣንጎት ፡ በቅዳ ፡ በትግሬ ፡ ባሕር ፡ ነጋሢ
- በዳሞት ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡

- ወጅ ፡ ቃጽ (ወጅያዝ?)
- በሐድያ ፡ ገራድ ፡
- በገንዝ ፡ ገራድ ፡
- በደዋሮ ፡ ገራድ ፡
- በፈጠጋር ፡ ራስ ፡
- በይፋት ፡ ወላስማ ፡ ኣስኳ ፡
- በግድም ፡ ኣቃጸን ፡
- በገኝ ፡ ንጉሥ ፡

እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ በራስ ፡ ወርቅ ፡ ና (በሽፍሽፍት?) ሾሟቸው። ሊቃነ ፡ ካህናቱንና ፡ ንቡራነ ፡ እዱንም ፡ በራሳቸው ፡ ኣክሊል ፡ እየደፉ ፡ በየአገራቸው ፡ ሾሟቸው። »

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በመዠመሪያው ፡ የተጻፈው ፡ የሚያመለክተን ፡ ኣባትዮው ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እሑድ ፡ ሲሞቱ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የዚያኑ ፡ ለት ፡ መንግሥቱን ፡ ይዘው ፡ አዲስ ፡ ነጋሢ ፡ በሕዝብና ፡ በደሀ ፡ ዘንድ ፡ ለመወደድ ፡ እንደሚያደርገው ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥፋት ፡ ለታሠረውና ፡ ለተጋዘው ፡ ምሕረት ፡ ማድረጋቸውን ፡ ነው። የምሕረቱን ፡ ቃል ፡ ሲያውጁ ፡ "አቡየሂ ፡ መሐረክሙ ፡ አነሂ ፡ መሐርኰክሙ » ፡ ብለው ፡ በራሳቸው ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ኣባቴም ፡ ማራችሁ ፡ ማሰኘታቸው ፡ ቅቱን ፡ አባታቸውንም ፡ ለማስወደድ ፡ ያደረጉት ፡ ይመስላል። የዚህም ፡ ዓይነት ፡ አያያዝ ፡ በመካሪም ፡ ተደርጎ ፡ እንደሆነ ፡ በራሳቸውም ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ እንደሆነ ፡ በጠቅላላው ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው። አባቴ ፡ አሥሯችሁ ፡ ነበር ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ፈታሁዋችሁ ፡ ብሎ ፡ ራስን ፡ በማስወደድና ፡ ሟች ፡ አባትን ፡ በማስጠላት ፡ ፈንታ ፡ ሁለታችንም ፡ ማርናችሁ ፡ ማለት ፡ የበሰለ ፡ ኣእምሮን ፡ ያሳያል።

ሁለተኛ ፡ ከእሥረኛው ፡ ምሕረት ፡ በኋላ ፡ ከሹም ፡ ሽሩ ፡ በፊት ፡ ፈረሰኛውን ፡ ሁሉ ፡ ከየአገሩ ፡ ሰበሰቡ ፡ የሚለው ፡ ምናልባት ፡ ወደፊት ፡

በሚያደርጉት ፡ ሹም ፡ ሽረት ፡ የተቀየመና ፡ የሚሸፍት ፡ ቢኖር ፡ በፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ለመደምሰስ ፡ አስቀድሞ ፡ ጥንቃቄ ፡ ለማድረግ ፡ የታሰበ ፡ ይመስላል።

ሦስተኛ ፡ ኣባታቸው ፡ የሁሉንም ፡ የሹመት ፡ ሥልጣን ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ በወኪል ፡ ያስሄዱ ፡ የነበረውን ፡ ደንብ ፡ ኣፍርሰው ፡ የመንግሥቱንም ፡ የቤተ ፡ ክህነቱንም ፡ ሹማምንት ፡ አክሊልና ፡ የራስ ፡ ወርቅ ፡ እየሰጡ ፡ በያገሩ ፡ ሹምሽር ፡ ማድረጋቸው ፡ ዓፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ በሹመት ፡ አሿሿም ፡ ከአባታቸው ፡ አሳብ ፡ ጋር ፡ መለያየታቸውን ፡ ያሳያል። ምናልባት ፡ ባባታቸውም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ባላባቶቹና ፡ ታላላቆቹ ፡ ሹማምንት ፡ የሹመታቸው ፡ ማዕርግና ፡ ሥልጣኑ ፡ ሁሉ ፡ ባባታቸው ፡ እጅ ፡ በመሆኑ ፡ ከባለ ፡ ጥቅሞቹ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ እየተወያዩ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ባባታቸው ፡ ዘመን ፡ ሲያዝኑበት ፡ ቆይተው ፡ ይሆናል።

ስለዚህ ፡ ባባታቸው ፡ ጊዜ ፡ ሲያዝኑበት ፡ የቆዩትን ፡ ኣሁን ፡ በርሳቸው ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ራሳቸው ፡ አሳብና ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ልማድ ፡ ሥልጣን ፡ እየሰጡ ፡ ሹምሽር ፡ አደረጉ ፡ ማለት ፡ ነው። ከነዚህ ፡ ከአባትና ፡ ከልጁ ፡ አሳብ ፡ የትኛው ፡ እንደሚሻል ፡ አንባቢ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ካለው ፡ ሁለት ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ ሊያመዛዝነው ፡ ይችላል።

**ሀ-**ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ አሳብ ፡ የየአውራጃ ፡ ባላባቶች ፡ ሲመቻቸው ፡ እየሸፈቱ ፡ መነጠል ፡ ሳይመቻቸው ፡ እየገበሩ ፡ በመገዛት ፡ የሚኖሩት ፡ ትክክለኛና ፡ ባለጉልት ፡ የሆኑት ፡ ባላባቶች ፡ ተነቅለው ፡ የነርሱ ፡ ኃይል ፡ በጭራሽ ፡ እንዲደክም ፡ የዋናው ፡ መሪ ፡ የንጉሡ ፡ ሥልጣን ፡ ከፍ ፡ ሲልና ፡ ሲጠነክር ፡ በየአውራጃውም ፡ በባላባትነትና ፡ በትልቅ ፡ ሰው ፡ ልጅነት ፡ ሹምሽር ፡ በማድረግ ፡ ፈንታ ፡ መንግሥትን ፡ ያገለገለና ፡ ለንጉሡ ፡ የታመነ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ እንዲሾምበት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ መንግሥትን ፡ በማገልገሉ ፡ እንጂ ፡ በራሱ ፡ በአውራጃው ፡ ባላባትነቱ ፡ እንዳይኮራ ፡ መሆኑ ፡ ነው። ምዕራፍ ፡ ፵ን ፡ እንደገና ፡ ተመልከት።

**ለ-**ያፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ አሳብ ፡ ከአባታቸው ፡ ተለይቶ ፡ የንጉሡን ፡ ሥልጣን ፡ አላልቶ ፡ የነዚያን ፡ የባላባቶቹን ፡ የሚያጠነክር ፡ ነው። በርሳቸውም ፡ ኣሳብ ፡ ውስጥ ፡ ሁሉም ፡ የባላባትነት ፡ መብቱንና ፡ ሥልጣኑን ፡ ሊያገኝ ፡

ይገባዋል። አልገዛም ፡ አልገብርም ፡ ብሎ ፡ ቢሸፍት ፡ በፈረሰኛና ፡ በእግረኛ ፡ ጦር ፡ ይመታል።

ከሁለቱ ፡ ኣሳብ ፡ የሕዝብ ፡ ኣማካሪ ፡ ሥልጣን ፡ የዴሞክራሲ ፡ አስተዳደር) ባልተመሠረተበት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ንጉሡ ፡ ሥልጣኑ ፡ እንዲጠነክርና ፡ እንደልቡ ፡ መሥራት ፡ እንዲችል ፡ ለሥልጣኔ ፡ ለሕግ ፡ እንቅፋት ፡ የሚሆኑትን ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነጻነትና ፡ ዙፋን ፡ እየተመኙ ፡ በመሸፈት ፡ ላገር ፡ ሁከት ፡ የሚፈጥሩትን ፡ ወላስማ ፡ ይፋት ፡ ገራድ ፡ ደዋሮ ፡ ገራድ ፡ ሀድያ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽ ፤ ጐዣም ፡ ነጋሽ ፡ የሚባሉትን ፡ ሥልጣናቸውን ፡ ትክለኛነታቸውንና ፡ ባላባትነታቸውን ፡ ነቅሎ ፡ የመንግሥቱን ፡ ባለሥልጣን ፡ ማደርጀት ፡ ላገር ፡ የሚጠቅምበት ፡ መንገድ ፡ ኣለው። ይኸም ፡ የሚሆነው ፡ ዋናው ፡ መሪ ፡ ራሱን ፡ ወዳድ ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ ሰብሳቢ ፡ ሳይሆን ፡ ራሱ ፡ ፍጹም ፡ አዛዥ (ዲክታተር) ቢሆንም ፡ ከልቡ ፡ ለሕዝብና ፡ ለመንግሥቱ ፡ በሙሉና ፡ በቅንነት ፡ አገልግሎቱን ፡ የሠዋ ፡ እንደሆነ ፡ ባላባትነትን ፡ በነቀለበት ፡ ሥፍራ ፡ የርሱን ፡ መንፈስ ፡ የሚከተሉትን ፡ ቅን ፡ አገልጋዮች ፡ ኣግብቶ ፡ በበላይ ፡ እየተቆጣጠረ ፡ ማሠራትም ፡ ራሱም ፡ መሥራትም ፡ የሚችል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው። የዚህም ፡ ዓይነት ፡ ዲክታተር ፡ ኣስተዳዳሪ ፡ ምንም ፡ የግል ፡ አሳብን ፡ ቢጨቍን ፡ መብትንም ፡ ሁሉ ፡ ለራሱ ፡ ቢያደርግ ፡ በጠቅላላው ፡ ላገር ፡ ጠቃሚ ፡ ሥራ ፡ ትቶ ፡ ሰውዬው ፡ በመጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ ያልፋል።

ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ሥራ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ መፈጸማቸውን ፡ በትክክል ፡ ለመመስከር ፡ እዘመናቸው ፡ ላይ ፡ መገኘትና ፡ ዝርዝር ፡ ሥራቸውን ፡ መመልከት ፡ ያስፈልጋል። አዝማሚያውን ፡ ዓይተን ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ የፈለግን ፡ እንደሆነ ፡ ባላባቱን ፡ ስነቅለው ፡ እሱም ፡ ሕዝቡም ፡ ያማኛል ፡ ብለው ፡ እምብዛም ፡ ለጊዜው ፡ ሰው ፡ ይውደደኝ ፡ የማይሉ ፡ ሌላም ፡ ብዙ ፡ አዳዲስ ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ደንብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለማስገባት ፡ የጣሩ ፡ ሕጉን ፡ ጥሰው ፡ ሲገኙ ፡ የገዛ ፡ ልጆቻቸውን ፡ ሳይቀር ፡ በሞት ፡ ለመቅጣት ፡ ያልተመለሱ ፡ ሐቀኛ ፡ ግትር ፡ ጽኑ ፤ ንጉሥ ፡ መስለው ፡ ይታያሉ። እንኳን ፡ የባላባቶቹን ፡ በፍቅራቸው ፡ ለማንሣት ፡ በጠባቸው ፡ ለመጣል ፡ የሚያስፈሩትን ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖችንም ፡ ሳይፈሩ ፡ እነዚያን ፡

ሽረው ፡ የቤተ ፡ ክህነቱን ፡ ሥልጣን ፡ ሳይቀር ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ነበር። ይኸም ፡ በጠቅላላ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ሊራመድ ፡ የሚገባውን ፡ ቤተ ፡ መንግሥትንና ፡ ቤተ ፡ ክህነትን ፡ ባንድ ፡ ዘመን ፡ ለማሻሻል ፡ ከልብ ፡ የተነሡ ፡ ይመስላል። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ የንጉሥነት ፡ ዕድሜ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ሊያስፈጽም ፡ ስለማይችል ፡ እርሳቸው ፡ በእርጅና ፡ ኣልፈው ፡ ወደሞት ፡ ሲሄዱ ፡ ልጃቸው ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የአባቴ ፡ አያያዝ ፡ የማያዛልቅ ፡ ነው ፡ ባላባትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣንም ፡ ያማኝ ፡ የጠላኝ ፡ እንደሆነ ፡ ሊጥለኝ ፡ ይችላል ፡ ብለው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ምሥጋናን ፡ በመውደድ ፡ ሐሜትን ፡ በመፍራት ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም ፡ በሹመትና ፡ በአስተዳደር ፡ ወደቀድሞው ፡ ደንብ ፡ ተመለሱና ፡ ይኸን ፡ እላይ ፡ ያየነውን ፡ ሹም ፡ ሽር ፡ ኣድርገው ፡ ሥልጣንን ፡ አከፋፍለው ፡ ለሹማምንትና ፡ ለባላባት ፡ ሰጥተው ፡ ኣስደስተው ፡ እየሾሙ ፡ በየሥፍራቸው ፡ ደለደሉዋቸው።

# ምዕራፍ ፡ ፵፫።

## ወደ ፡ አማራ ፡ ሳይንትና ፡ ወደ ፡ ወረይሉ (ደብረ ፡ ነጐድጓድና ፡ አትሮንስ ፡ ማርያም) ጉዞ—የአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ሥራና ፡ የበዓሉ ፡ አከባበር።

ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የሚለውን ፡ መደዳውን ፡ ስንመለከት ፡ በመስከረም ፲ ፡ ቀን ፡ ለደስክ (ጣዖት) የሰገዱ ፡ ሰዎች ፡ ተይዘው ፡ ባደባባይ ፡ ተፈርዶባቸው ፡ እንደተገረፉ። የዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ወዳዘዘበት ፡ ቦታ ፡ እንሄዳለንና ፡ ስንቅህንና ፡ በቅሎህን ፡ ኣዘጋጅ ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ እንዳወጡና ፡ ሕዝቡ ፡ ተሰብስቦ ፡ ለሠራዊትህ ፡ ራራለት ፡ አሁን ፡ የክረምቱ ፡ ወራት ፡ ስለአላለቀ ፡ ክረምቱ ፡ ሲያልቅ ፡ ከመስቀል ፡ በኋላ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ወዳዘዘህ ፡ ቦታ ፡ እንሂድ ፡ ብለው ፡ እንደለመኑዋቸውና ፡ ልመናቸውን ፡ እንደተቀበሉ። የመስቀልን ፡ በዓል ፡ በደብረ ፡ ብርሃን (ተጉለት) ኣክብረው ፡ ውለው ፡ ከዚያ ፡ ከኣዳራሻቸው ፡

እየወጡ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ **ኢየሱስ** ፡ ቤተ ፡ መስቀል ፡ ቤተ ፡ ማርያም ፡ ድረስ ፡ እየሄዱ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ እየታዩ ፡ ለካህናቱ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖ ፡ እየሸለሙ ፡ ሁሉንም ፡ ማስደሰታቸው ፡ ኣምሮ ፡ በተዘጋጀው ፡ በደመራ ፡ ቀን ፡ በታላቅ ፡ ግርማ ፡ ሆነው ፡ ደመራውን ፡ ሲዞሩ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እያያቸው ፡ መደሰቱ ፡ ተጽፏል። በቀጥታ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ከዚሁ ፡ አያይዞ ፡ የሚተርከውን ፡ እንመልከት ፡ «ከዚያ ፡ የክረምቱ ፡ ወራት ፡ ስለአለቀ ፡ ገንዘቡ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ዕቃና ፡ መሣሪያ ፡ ሁሉ ፡ ከናዝሬት ፡ ቤት ፡ ከመንግሥት ፡ ቤት ፡ ከበረከት ፡ ቤት ፤ ከገደል ፡ ቤት ፡ ተሰብስቦ ፡ ወደገስምቤ ፡ ሸዋ ፡ ሄዶ ፡ በዘበኛ ፡ እንዲጠበቅ ፡ አደረጉና ፡ በመስከረም ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ ተነሥተው ፡ ደብረምጥማቅ ፡ ደርሰው ፡ የእመቤታችን ፡ በዓል ፡ ኣከበሩ። ከዚያ ፡ መዕከል ፡ ሰፍረ (ሰፈር) ወደሚባለው ፡ ወደምድረ ፡ መንዝህል ፡ ከምድረ ፡ መንዝህል ፡ ምድረ ፡ ስወረ ፡ ገደል ፡ ከዚያ ፡ ምድረ ፡ ግሴ ፡ ደረሱ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የአማራው ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ ብዙ ፡ መታያ ፡ መብልና ፡ መጠጥም ፡ ይዞ ፡ ተቀበላቸው። ንጉሡም ፡ በዚያ ፡ አዳር ፡ ኣድርገው ፡ ትልቅ ፡ ግብር ፡ አደረጉ። ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ምድረየርሕ ፡ ደረሱና ፡ አባታቸው ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ወደሠሩት ፡ ወደደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ኣክሊላቸውን ፡ ደፍተው ፡ የሹመት ፡ ልብሳቸውን (ሽልማታቸውን) ለብሰው ፡ የአርዌ ፡ በድላይን (ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ያሸነፈው ፡ የይፋት ፡ ባላባት) ጋሻና ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ፈረሱን ፡ ተቀምጠው ፡ ይቀበሏቸው ፡ እንደነበረው ፡ እርሳቸውንም ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡ እንዲቀበሉዋቸው ፡ ወደደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ላኩ። ይኸም ፡ ክብረ ፡ በዓል ፡ ማድረግ ፡ የተለመደው ፡ የጌታችን ፡ በዓል ፡ በሚውልበት ፡ በየወሩ ፡ በጽሁ ፡ ቀን ፡ ስለነበረ ፡ በዚሁ ፡ መስከረም ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ በመኳንንቱ ፡ በሠራዊቱ ፡ ታጅበው ፡ ሲሄዱ ፡ እንደዚሁ ፡ እንደተባለው ፡ ተዘጋጅተው ፡ መጥተው ፡ ተቀበሉዋቸው። እርሳቸውም ፡ አቀባበላቸውን ፡ ተመልክተው ፡ አመስገኗቸውና ፡ ወደደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ገቡ። ሲገቡም ፡ ሺ ፡ መብራት ፡ በቀኝ ፡ ሺ ፡ መብራት ፡ በግራ ፡ ይዘው ፡ አስገቡዋቸው። ደብተራው ፡ ሁሉ ፡ ነጫጭ ፡ ጧፍ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ያበራላቸው ፡ ነበር። መጋረጃ (መንጠዋልዓ ፡ ኮከቤ) ይዘውላቸው ፡ ዑደት ፡ ኣደረጉ። ሕገ ፡ ቍርባንም ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ወጥተው ፡ በብዙ ፡ ልብስ ፡ ተጌጦ ፡ ወደተደራጀው ፡ ደብረ ፡ ዘይት

፡ ወደሚባለው ፡ ሠፈር ፡ ሔዱ። በዚህም ፡ ቀን ፡ ለካህናት ፡ ብዙ ፡ ሰንጋ ፡ ታረደ። እነርሱም ፡ ለንጉሡ ፡ ላም ፡ በግ ፡ ዶሮ ፡ ሙብልም ፡ መጠጥም ፡ ቢያመጡላቸው ፡ እናንተ ፡ ግብር ፡ መገበር ፡ የለባችሁም (ከግብር ፡ ነጻ ፡ ናችሁ) ብለው ፡ በጉንና ፡ ላሙን ፡ ዶሮውን ፡ መለሱላቸው። የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ማኅበርም ፡ መጋቢ ፡ እንድርያስና ፡ እመ ፡ ምኔት ፡ ትርንጎ ፡ ሎሚ ፡ ሙዝ ፡ ይዘውላቸው ፡ መጡና ፡ አመሰገኗቸው። በዚሁም ፡ ሳሉ ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ያባታቸውን ፡ ያዬ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ የአርቧኛውን ፡ ቀን ፡ ተዝካር ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ራሳቸው ፡ የደረሱትን (መዝሙርና ፡ አርያም) ማኅሌት ፡ አስቀኍመው ፡ አከበሩ። ስላባታቸው ፡ ምጽዋትም ፡ ለድሆች ፡ መጸወቱ ፡ ......ከዚያ ፡ ከላንቶ ፡ ወደሚባለው ፡ አገር ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡ እንዲቀበሉዋቸው ፡ ቍጥራቸው ፡ ትንሽ ፡ የሆነ ፡ መኳንንት ፡ ላኩ። በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ስትቀበሉኝ ፡ የምትለብሱት ፡ ብለው ፡ ፶ ፡ ግምጃ (ቀሚስ) ሰጧቸው። ይኸንንም ፡ ማድረጋቸው ፡ ይቺ ፡ አገር ፡ ገና ፡ ኣዲስ ፡ ቅኝ ፡ ስለሆነች ፡ ነው። ቀጥሎም ፡ ይቺን ፡ አገር ፡ ከላንቶን ፡ አትሮንሰ ፡ ማርያም ፡ ብላችሁ ፡ ጥሯት ፡ ብላው ፡ አዲስ ፡ ሥያሜ ፡ አወጡላት። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ አትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ሔዱ። በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱም ፡ ሕዝቡም ፡ የበዓል ፡ ልብሳቸውን ፡ ለብሰው ፡ ተቀበሉዋቸው።

በዚያም ፡ በዛፍና ፡ በሳር ፡ ጭፍግ ፡ ያለውን ፡ ትልቅ ፡ ቦታ ፡ አዩና ፡ መጥረቢያና ፡ ማጭድ ፡ ኣምጡ ፡ ብለው ፡ ሠራዊቱን ፡ ኣዘው ፡ ከወይራው ፡ በቀር ፡ የቀረውን ፡ ዛፍና ፡ ሣር ፡ እየቆረጣችሁ ፡ አጥፉ ፡ ድንጋዩንም ፡ እያነሣችሁ ፡ ደልድሉ ፡ ብለው ፡ አዘዙና ፡ ሥራው ፡ ተዠመረ። እርሳቸውም ፡ ባንድ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ መጋረጃ ፡ ተጋርዶላቸው ፡ ከውስጥ ፡ ሁሉንም ፡ ሲመለከቱ ፡ እርሳቸውን ፡ ግን ፡ ከውጭ ፡ ማንም ፡ አያያቸውም ፡ ነበር። ጫካው ፡ ተመንጥሮ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ትልቅ ፡ ሰቀላ (ቤተ ፡ ክርስቲያን) ፡ ተሠራ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ የሐር ፡ ልብስም ፡ ተጌጠ። ከዚያ ፡ በታላቅ ፡ ክብርና ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ የእመቤታችን ፡ የማርያምን ፡ ታቦት ፡ አስገቡ። ይቺም ፡ ሥፍራ ፡ የ**እግዚአብሔር** ፡ ፈቃድ ፡ ሆኖ ፡ ሳይፈጸምላት ፡ ቀርቶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በላይዋ ፡ ላይ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ለማሠራት ፡ ብለው ፡ በራሳቸው ፡ ገንዘብ ፡ የገዟት

፡ ሰይፈ ፡ አርእድ ፡ ንዋየ ፡ ክርስቶስ (፲፫፻፶፪ ፲፫፻፷፫) ነበሩ። አባታቸውም ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በደብረ ፡ ብርሃን (ተጕለት) ሳሉ ፡ ስሟን ፡ ደብረ ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ ብለው ፡ ታቦት ፡ ኣስቀምጠውበት ፡ ነበር። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሥራት ፡ ሳይቻላቸው ፡ ቀርቶ ፡ ታቦቱን ፡ በቲንሽ ፡ ቤት ፡ ኣስቀምጠውት ፡ ሲኖሩ ፡ ሞቱ። ስለዚህ ፡ ልጃቸው ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ እሥፍራዋ ፡ ላይ ፡ መጥተው ፡ በፍጥነት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ሥራ ፡ አሠርተው ፡ ለመጨረስ ፡ ቻሉ። የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሥርዓት ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ዓምዱ ፡ የሚባለው ፡ መከብብነት (ኣለቅነት) በወርቅና ፡ በብር ፡ ያጌጠ ፡ ልብስ ፡ ተሸልሞ ፡ ተሾመ። የጽጌረዳና ፡ የወይን ፡ ዘለላ ፡ ቀለም ፡ ያለውንም ፡ ሁለት ፡ አክፋር (በራስ ፡ የሚደፋ ፡ ጎፈር ፡ ወይም ፡ የሚጠመጠም) ፡ ሰጡት። አክፋሩም ፡ ከፊት ፡ ፲፪ ፡ ከኋላ ፡ ፲፪ ፡ ዘርፍ ፡ ነበረው። ቍልፉም ፡ የወርቅ ፡ እንጂ ፡ የብር ፡ ኣልነበረም። የወርቅ ፡ ኣክሊልም ፡ ከድባብና ፡ ከሥጋጃ ፡ ከሰንና ፡ ከብርት ፡ ጋር ፡ ሰጡት። ፲፪ ፡ መስቀል ፡ ከፊት ፡ እንዲቆምለት። ፲፪ ፡ ሰብአ ፡ ጤጤ (ጢጢ) የሚባሉት ፡ እንዲጋርዱለት ፡ የውሹቴ? ፡ ቀለም ፡ ባለው ፡ ብርሌ ፡ እንዲጠጣ ፡ ሥጋ ፡ እየቆረጠ ፡ የሚባለበት ፡ የብር ፡ ቢላዋ ፡ እንዲሆን ፡ ኣዘዙለት። በዚህም ፡ ቀን ፡ ለራቅ ፡ ማሰሬ ፡ ረባነ ፡ ደብር ፡ ለመራህያኑ (መሪዎች) ረበናተ ፡ ማኅሌት ፡ መዝሙር ፡ ፤ ለተመረጡት ፡ ቀሳውስት ፡ ጤር ፡ ዜቤጤር (ፔርዜፔጤር) የሚባል ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ሰጧቸው።

ካህናቱ ፡ የሚተዳደሩበት ፡ የእመቤታችንና ፡ የቀረው ፡ ሁሉ ፡ በዓል ፡ በሚከበርበት ፡ ቀን ፡ ለበዓሉና ፡ ለግብሩ ፡ የሚሆን ፡ ብዙ ፡ ርስት ፡ ሰጡ። የዚህ ፡ ሁሉ ፡ መታሰቢያ ፡ ሰንጋና ፡ በግ ፡ እየታረደ ፡ ጠላና ፡ እንጀራ ፡ እየተሰናዳ ፡ እንዲከበር ፡ አዘዙ። ከልጅነት ፡ ጀምሮ ፡ እስኪነግሡ ፡ ድረስ ፡ ያጠራቀሙትን ፡ ከነገሡም ፡ በኋላ ፡ ያገኙትን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ለአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ሰጡ። ለዚች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሰጡትን ፡ የገንዘብና ፡ የመጻሕፍት ፡ ብዛት ፡ ከራሳቸው ፡ ከንጉሡ ፡ በቀር ፡ የሚያውቀው ፡ የለም ፡ »

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባጭሩ ፡ ተመልክተን ፡ የምንረዳው ፡ አባታቸው ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴን ፡ መርጡ ፡ ለማርያምን ፡ ወይም ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድን ፡ ይወዱ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለነዚህም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ርስትና ፡ ስጦታ ፡ እየሰጡ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ማድረግ ፡ ይወዱ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ደግሞ ፡ በፋንታቸው ፡ ደኑን ፡ ኣስመንጥረው ፡ የእመቤታችንን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተከለው ፡ ይቺን ፡ ኣትሮንስ ፡ ማርያምን ፡ ማሳደጋቸውን ፡ ነው። ይኸንንም ፡ የመሰለ ፡ ለየግል ፡ ከተማ ፡ የመቆርቆርና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የመትከል ፡ ልማድ ፡ እስከዛሬ ፡ ኣልቀረም። ንጉሡ ፡ ሁሉ ፡ ኣባቱ ፡ የቆረቆረውን ፡ ከተማ ፡ ማድመቅ ፡ ኣባቱ ፡ የተከለውን ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ማሳደግ ፡ ኣይወድም። ሁሉም ፡ ለየራሱ ፡ የራሱን ፡ ታሪክ ፡ የራሱን ፡ ዝና ፡ ስለሚፈልግ ፡ ያባቱን ፡ ከተማ ፡ እየተወ ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ የእገሌ ፡ ትከል ፡ የሚባልበትን ፡ ቢመሠርት ፡ ይወዳል። ፩ዱም ፡ ንጉሥ ፡ የወጠነውን ፡ ሳይጨርስ ፡ ስለሚሞት ፡ ዛሬ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አውራጃ ፡ ይኸን ፡ ሥፍራ ፡ እገሌ ፡ ንጉሥ ፡ ቈርቍሮት ፡ ነበር ፡ የማይባለው ፡ ሥፍራ ፡ በልክ ፡ ነው። የዚህም ፡ ልማድ ፡ የሚጐዳበትና ፡ የሚጠቅምበት ፡ መንገድ ፡ አለው። የሚጐዳበት ፡ በያለበት ፡ ሁሉም ፡ ለየራሱ ፡ ከተማ ፡ ሲቆረቍር ፡ አንድ ፡ የታወቀና ፡ የደመቀ ፡ ትልቅ ፡ ከተማ ፡ ባንድ ፡ ሥፍራ ፡ ባለመገኘቱ ፡ የሚጠቅምበት ፡ ደግሞ ፡ አዲሱ ፡ ንጉሥ ፡ አባቱ ፡ ያቀናውን ፡ ነገር ፡ እያለፈ ፡ አዲስ ፡ ያልቀና ፡ ያረመኔ ፡ አገር ፡ እየፈለገ ፡ ጫካውን ፡ ኣስመንጥሮ ፡ ቤተክርስቲያኑን ፡ ተከትሎ ፡ ሲያቀና ፡ አዲስ ፡ ዝምድና ፡ አዲስ ፡ ኣንድነት ፡ ስለሚገኝ ፡ ነው።

በዚህ ፡ ጥንት ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ እነ ፡ አብርሃ ፡ እነ ፡ አልዓሜዳ ፡ እነ ፡ ካሌብ ፡ በአክሱም ፡ እነ ፡ ላሊበላ ፡ በላስታ ፡ የኋለኞቹ ፡ እነ ፡ ፋሲል ፡ እነ ፡ ኢያሱ ፡ አድያም ፡ ሰገድ ፡ በጐንደር ፡ ሊመሰገኑ ፡ ይገባል። ምንም ፡ እንኳን ፡ ለየራሳቸው ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚያው ፡ ባጠገቡ ፡ በራሳቸው ፡ ስም ፡ መትከላቸው ፡ ባይቀር ፡ ያለውን ፡ ከተማ ፡ ከማድመቅ ፡ በቀር ፡ በያለበት ፡ በሩቅ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ከተማ ፡ እየቆረቆሩ ፡ ከተማውን ፡ አልበታተኑትም። በሸዋ ፡ ግን ፡ ይኵኖ ፡ አምላክ ፡ በመንዝ ፡ ሲዝምር ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ደብረ ፡ ብርሃንን (ተጉለትን)ሲመርጡ ፡

ልብነድንግል ፡ በየረር ፡ በቦካን ፡ በሽምብራ ፡ ኵሬ ፡ ሲመሠርቱ ፡ የመንግሥቱ ፡ መደብ ፡ ሽዋ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የቤት ፡ ሕንፃና ፡ በድንጋይ ፡ የተሠራ ፡ የሐውልት ፡ ቅርጽ ፡ የሞላበት ፡ ታላቅ ፡ የደመቀ ፡ ከተማ ፡ ሳይገኝ ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ እመዛወር ፡ ደረሰ።

ነገሩ ፡ የተነሣው ፡ በአትሮንዕ ፡ ማርያም ፡ ሆኖ ፡ በውስጡ ፡ የተነገረው ፡ ስለከተማ ፡ በመሆኑ ፡ አንባቢን ፡ ግር ፡ ይለው ፡ ይሆናል ፡ ቀድሞ ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ የታወቀ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተተክሎ ፡ ንጉሡ ፡ ስጦታ ፡ ሲያበዛለት ፡ እየሔደ ፡ ሲከርምበት ፡ ለንጉሡ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አጠገብ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የግምብ ፡ አዳራሽ ፡ መሠራቱ ፡ ስለማይቀር ፡ እንደ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ሥላሴ ፡ እንደ ፡ አትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ያሉት ፡ አድባራት ፡ የቤተክርስቲያን ፡ ሥፍራ ፡ መሆናቸውን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ቤተ ፡ መንግሥትም ፡ ባጠገባቸው ፡ የቆመ ፡ እንደ ፡ ከተማ ፡ የሚቆጠሩ ፡ መሆናቸውን ፡ በማወቅ ፡ ነው። ደግሞ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ኣንድ ፡ ልንመለከተው ፡ የሚገባ ፡ ኣለ። በዚያን ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ስሜን ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወደ ፡ ሽዋ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወደ ፡ ጐጃምና ፡ ወደ ፡ ቤገምድር ፡ ነገሥታቱ ፡ ካልተመላለሱ ፡ ግዛት ፡ ኣይጸናላቸውምና ፡ በያለበት ፡ ከተማ ፡ ሲበዛ ፡ ለማረፊያ ፡ ይጠቅማቸዋል። ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድ ፡ ዳዊት ፡ ከነርሱ፣ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ በጒዞ ፡ ላይ ፡ አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ በድንኳን ፡ ብቻ ፡ ሲገለገሉ ፡ እነዚህ ፡ የኋለኞቹ ፡ እነ ፡ በእደ ፡ ማርያምና ፡ ተከታዮቹ ፡ ለጒዞ ፡ ድንኳንን ፡ ሳይተዉ ፡ ወደታወቀው ፡ ኣገር ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ሳይንት ፡ ቢሔዱ ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ወረይሉ ፡ ቢጓዙ ፡ አትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ወደ ፡ ሽዋ ፡ ሲመለሱ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ያለው ፡ ከተማና ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለማረፊያ ፡ ይመቻቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው።

ሁለተኛ ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ የምንመለከተው ፡ በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ላይ ፡ ...፡ወለጎሩያን ፡ ቀሳውስት ፡ ሠመዮሙ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ቤርዜቤጤር(ፔርዜቤጢር)......ያለውን ፡ ነው። ፔርዜቤጢር ፡ የሚባል ፡ የቤተክህነት ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ለቀሳውስት ፡ መኖሩን ፡ ይህ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ይገልጻል። ቋንቋው ፡ ከአማርኛም ፡ ከግዕዝም ፡ የራቀ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡

ቋንቋ ፡ ይመስላል። ምናልባት ፡ ሙሴ ፡ ዝል ፡ ፔሩሾ ፡ በምልክት ፡ ላይ ፡ ፕሬስፒተርያን ፡ ማለት ፡ ይሆናል ፡ ያሉት ፡ አውነት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም። ፕሬስፒተርያን ፡ በእንግሊዝ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ላንድ ፡ ክፍል ፡ ቀሳውስት ፡ የተሰጠ ፡ ሥያሜ ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፵፪።

## ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ -- የሐሜተኞች ፡ ቅጣት ፡ የመሐመድ ፡ ቤን ፡ በድላይ ፡ መገበር ፡ የዚያን ፡ ዘመንና ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ የሕዝብ ፡ መብት ፡ ልዩነት።

ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ በአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ክብረ ፡ በዓሎና ፡ ስጦታው ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ ለማክበር ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ እንደሰበሰቡ ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይገልጽልናል። ደብተራው ፡ ሁሉ ፡ ከየደብሩ ፡ ኣክሱሞችም ፡ ሕጋቸውን ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ ከተሰባሰቡ ፡ በኋላ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ኣትሮንስ ፡ ማርያምን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ጅጅኖ (ደጅኖ?) ሔዱና ፡ በዚያ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ ኣከበሩ።

እንደ ፡ ሕጉ ፡ ለስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ የሚሆነውን ፡ ሥያሜ ፡ በዕጣ ፡ ለመምረጥ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፤ ዳዊት ፤ ቆስጠንጢኖስ ፡ ፫ ፡ ስም ፡ ቀረበ። ዕጣው ፡ ከተጣለ ፡ በኋላ ፡ ዳዊት ፡ ስለወጣ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ዳዊት ፡ ብለው ፡ ሠየሙዋቸው። የልጅነት ፡ ሚስታቸውን ፡ ግራ ፡ በዓልቲሐትን ፡ ዣን ፡ ሰይፋ ፡ ቀኝዕ ፡ በዓልቲሐት ፡ ዕሌኒን ፡ አድማስ ፡ ሞገሳ ፡ ብለው ፡ ሠየሟቸው። በዚህም ፡ ቀን ፡ ሹማምንቱም ፡ ሠራዊቱም ፡ እንደሚገባቸው ፡ ተሸለሙ። ከአዳራሹ (ሰቀላ) በ፫ ፡ ሰዓት ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ኣንበሳና ፡ አንድ ፡ ጐሽ ፡ ከጥንት ፡ እንደተለመደው ፡ ንጉሥ ፡ በእጃቸው ፡ ወግተው ፡ እንዲገድሏቸው ፡ ቢያቀርቡላቸውና ፡ ይኸንንም ፡ ሥርዓት ፡ ቢነግሩዋቸው ፡ እምቢ ፡ አሉና ፡ ጐሹን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እንዲገድለው ፡ አንበሳው ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አባታቸው (ዘርዓ ፡ ያዕቆብ) በአክሱም ፡ በሥርዓተ ፡ ንግሣቸው ፡


ጊዜ ፡ እንዳደረጉት ፡ አንዲለቀኍት ፡ አዘዙ። ሌላ ፡ ሰው ፡ ሳይጨመር ፡ ከሕግ ፡ አዋቂዎቹ (ከባለሕጎቹ) ጋር ፡ ሆነው ፡ የንግሣቸውን ፡ ሥርዓት ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አትሮንሰ ፡ ማርያም ፡ ተመልሰው ፡ የጥምቀትን ፡ በዓል ፡ አከበሩ። በጥር ፡ ወር ፡ የእመቤታችንን ፡ የዕረፍቷን ፡ ቀን ፡ አክብረው ፡ ሲጨርሱ ፡ የኣባታቸውን ፡ የመንፈቅ ፡ ተዝካር ፡ ለመፈጸም ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ሔዱ። ከዚያ ፡ ተመልሰው ፡ አትሮንሰ ፡ ማርያም ፡ መጡ። ከዚያ ፡ ኣልፈወ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ታቦት ፡ የሚተከሉበትን ፡ ቦታ ፡ በምድረ ፡ መንዝሕ ፡ ይመርጡ ፡ ዠመር። ወዲያው ፡ እንዳሰቡት ፡ ደጎና ፡ ቦታ ፡ አገኙና ፡ በጣም ፡ ተደሰቱ። የቤተ ፡ ክርስቲያኑንም (ሰቀላ)ሥራ ፡ ሲጨርሱ ፡ ከመርሐ ፡ ቤቱ (መርሐ ፡ ቤቴ?) ብዙ ፡ ታቦት ፡ ኣስመጡና ፡ የእመቤታችንን ፡ ታቦት ፡ አስገብተው ፡ ስሟንም ፡ ምስሐላ ፡ ማርያም ፡ ብለው ፡ ሠየሙት ፡ ለርሷም ፡ ካህናትንም ፡ መሬትንም ፡ ደልድለው ፡ ሰጡ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዘወትር ፡ ፈረስ ፡ ይጋልባል ፡ እንጂ ፡ ተቀምጦ ፡ የመንግሥትን ፡ ሥርዓት ፡ እየፈጸመ ፡ ፍርድ ፡ አይሰማም ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እየተባሉ ፡ መታማታቸውን ፡ ስለሰሙ ፡ በጣም ፡ ተናደዱ። በቶሎ ፡ ሠራዊቱንም ፡ ሰበሰቡና ፡ ፈረስ ፡ ከመጋለብ ፡ በቀር ፡ የመንግሥትን ፡ ሥርዓት ፡ እየፈጸመ ፡ ተቀምጦ ፡ ፍርድ ፡ ሲሰማ ፡ ኣይውልም ፡ ብላችሁ ፡ አምታችሁኛል ፡ ቀድሞ ፡ በአባቶቼ ፡ በነገሥታቱ ፡ ጊዜ ፡ ፈረስ ፡ መቀመጥ ፡ ቀስት ፡ መወርወር ፡ አልነበረምን ፡ ኣሁንም ፡ እንደዚህ ፡ እያሉ ፡ ያሙኝን ፡ ሰዎች ፡ አውጥታችሁ ፡ ስጡኝ ፡ ያለዚያ ፡ ሁላችሁም ፡ ትሞታላችሁ» አሏቸው። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዣን ፡ ጠባቂ ፡ ጌቶች (የሴት ፡ አዛዥ ፡ የቤት ፡ ከፍል?) ሊቀ ፡ መጣኒ (ዳኛ) ብዙ ፡ መነኮሳት ፡ ተይዘው ፡ ቀረቡ። ተጠይቀው ፡ አላልንም ፡ ብለው ፡ ቢክዱ ፡ ወደ ፡ መድኃኒት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አምጥተው! ፡ የእግራቸውን ፡ ሥር ፡ እየቆረጡ ፡ ወደ ፡ ደቅ ፤ ወደ ፡ ጉንድ ፤ ወደ ፡ ጐሽዓሮ ፤ ወደ ፡ ደራ ፤ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ ፈጠር ፡ ሊቀ ፡ መጣኒን (ብዙ ፡ ይሆናሉ) ወደ ፡ ፍንጌ ፤ ወደ ፡ አምባ ፡ ሳኔት (አምባስኒት) ወደ ፡ ደብረ ፡ ማዕዖ ፡ በግዞት ፡ ላኰዋቸው። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይኸስ ፡ ከአባቱ ፡ ይበልጥ ፡ ጨካኝ ፡ ነው ፡ እየተባባለ ፡ በልቡ ፡ ፍርኃት ፡ አደረበት።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በትዕግሥትና ፡ በሥርዓት ፡ ኑሩ» ፡ የሚል ፡ አዋጅ ፡ አስነግረው ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ የነበረውን ፡ ጨዋና ፡ ደብተራ ፡ በያገሩ ፡ ላኩት። ርሳቸው ፡ ግን ፡ በምስሐለ ፡ ማርያም ፡ የፋሲካን ፡ በዓል ፡ አክብረው ፡ የለበሱትን ፡ የራሳቸውን ፡ ልብስ ፡ አውጥተው (አውልቀው)ምስሐላ ፡ ማርያም ፡ ተብላ ፡ ለተሠየመችው ፡ ለዚች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰጡና ፡ ሸለሟት። ከዚያ ፡ ወደ ፡ አትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ተመልሰው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ሹማምንት ፡ አምጡልኝ ፡ ብለው ፡ አዘዙ። እነሱም ፡ እንደትእዛዙ ፡ ቃል ፡ በሐምሌና፡በነሐሴ፡ወር፡ደረሱ። የደብረ፡ሊባኖስ፡መነኮሳትም ፡ ከመምሕራቸው (ከእጨጌው)ከአቡነ ፡ መርሕነ ፡ ክርስቶስ ፡ ጋር ፡ መጥተው ፡ ስለነበረ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖሱ ፡ መምህር ፡ እንደዚህ ፡ አሏቸው ፡ “ይቺን ፡ መቅደስ ፡ ይባርኳት ፡ እናንተም ፡ መነኮሳቱ ፡ ባርኳት ፡ አባቴ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ለአባታችሁ ፡ ለእንድርያስ ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድን ፡ ርስት ፡ ይሆነው ፡ ዘንድ ፡ እንደሰጠው ፡ እስከዛሬም ፡ እንደቆየለት ፡ እኔም ፡ ዛሬ ፡ ይቺን ፡ መቅደስ (አትሮንሰ ፡ ማርያምን) ርስት ፡ ትሆናችሁ ፡ ዘንድ ፡ ሰጠሁዋችሁ “በዚህ ፡ ንግግር ፡ ከመምህራኑ ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረጉ።

ለቤተ ፡ መቅደሱም ፡ በየለቱ ፡ ስጦታ ፡ እየጨመሩ ፡ ሰጡ። በዚሁ ፡ ቦታ ፡ ሳሉ ፡ የአዳል ፡ ሰዎች ፡ ለንጉሡ ፡ የሚቀርበውን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ብዙ ፡ ግምጃ ፡ ይዘው ፡ መጡ። ከመሐመድ ፡ ከአርዌ ፡ በድላይ ፡ ልጅ ፡ ተልከናል ፡ ብለው ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ፡ ከአቀረቡ ፡ በኋላ ፡ “ጌታችን ፡ ሆይ ፡ እንግዴህ ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፡ እኔም ፡ በያመቱ ፡ ግብርህን ፡ እየያዝሁ ፡ እመጣለሁ ፡ አንተም ፡ ጨዋ ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ እየወረደ ፡ እንዳይዋጋ ፡ እዘዝልኝ ፡ ይልሃል ፡ የአዳሉ ፡ ንጉሥ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ። ንጉሡ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ይኸን ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ለመልክተኞቹ ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ ሸልማትም ፡ መታሰቢያም ፡ ሰጧቸው።

# ያፄ ይኩኖ አምላክ የዘር ሀረግ



ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ምድረ ፡ ጐደሎ ፡ ደረሱና ፡ ኣራዊት ፡ ኣደኑ። ነሥታቱ ፡ ሁሉ ፡ እዚች ፡ አገር ፡ ሲደርሱ ፡ ኣደን ፡ ማደናቸው ፡ ከጥንት ፡ የቆየ ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ ከዚያ ፡ አልፈው ፡ ምድረ ፡ ደጎ (መካነ ፡ መርያም) ደረሱና ፡ በዚያው ፡ አቅራቢያ ፡ አዲስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፡ ስሟንም ፡ ደብተራ ፡ ማርያም ፡ ብለው ፡ ሠይመው ፡ ለደብተሮቹና ፡ ለበዓሉ ፡ መተዳደሪያ ፡ ከምድረ ፡ ጸለም ፡ ሺህ ፡ መስፈሪያ ፡ መሬት ፡ ሰጡ። በዚህ ፡ ሳሉ ፡ ወደ ፡ ዶባ ፡ ሊዘምቱ ፡ የተጠሩት ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ መጡ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሊቀ ፡ መጣኒ ፡ ትዕይንቲ ፡ ከሚባለው ፡ ከቃለ ፡ ሐፄና ፡ ከገደብ ፡ ሐወርድ ፡ ጋር ፡ ከአዳል ፡ ተልከው ፡ ለመጡት ፡ እስላሞች ፡ ለሁሉም ፡ ሽልማት ፡ ሰጥተው ፡ "አንተው ፡ እንዳልከው ፡ ይሁን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ተጠንቀቅ ፡ መሐላህን ፡ እንዳታፈርስ" የሚል ፡ ቃል ፡ ጨምረው ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ ላኳቸው"

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የተጻፈው ፡ የሚገልጽልን ፡ ዋና ፡ ዋናው ፡ ባጭሩ ፡ ከመዝመሪያው ፡ ዝምሮ።

*ሀ*–፩ዱ ፡ ንጉሥ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ተከታዩ ፡ ለጊዜው ፡ መንግሥቱን ፡ ይዞ ፡ የስመ ፡ መንግሥቱን ፡ ሥያሜና ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሡን ፡ በሚቀጥለው ፡ ጊዜ ፡ ሥፍራና ፡ ጊዜ ፡ መርጦ ፡ ሊፈጽም ፡ መቻሉን ፡ ነው። እነሆ ፡ በእደማርያም ፡ አባታቸው ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሺ፬፻፷ ፡ ዓ•ም ፡ ጳጕሜ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ሲሞቱ ፡ መንግሥትን ፡ ያዙ ፡ በ፰ኛው ፡ ወይም ፡ በ፺ኛው ፡ ወር ፡ በ፳፰ኖ (ወረይሉና ፡ አማራ ፡ ሳይንት ፡ መካከል) ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ ኣከበሩ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከአክሱም ፡ ሕግ ፡ አዋቂዎቹተጠርተው ፡ መምጣታቸውን ፡ ይገልጻል። ስለዚህ ፡ አክሱም ፡ መሄድ ፡ ያልቻለው፣ ፡ ከኣክሱም ፡ ባለሕጎቹን ፡ ኣስመጥቶ ፡ ከነገሠ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሡን ፡ ሄዶ ፡ እንዳከበረ ፡ ያህል ፡ ይቆጠር ፡ ይሆናል።

**ለ**–ስመ ፡ መንግሥት ፡ ለንጉሡ ፡ የሚሰጠው ፡ ብዙ ፡ የስም ፡ ዓይነት ፡ እየቀረበ ፡ ከብዙው ፡ ውስጥ ፡ በእጣ ፡ እየተመረጠ ፡ መሰጠቱን ፡ በሥርዓተ ፡ ንግሡ ፡ ላይ ፡ አንበሳና ፡ ጐሽ ፡ ለንጉሡ ፡ እየቀረበ ፡ ንጉሡ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ እንዲገድለው ፡ ልማድ ፡ መኖሩን ፡ ይናገራል።

አንበሳናጐሸንጉሡ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሡን ፡ በሚያከብርበት ፡ ቀን ፡ እፊቱ ፡ ቀርበው ፡ አንበሳው ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ ተገድሎ ፡ የቀሩት ፡ እንስሶች ፡ እንደሚለቀቀኍ ፡ ስለ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ በተመደበው ፡ ምዕራፍ ፡ ተገልጿል" ነገር ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ ሕግ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምም ፡ አልፈጸሙትም። ምናልባት ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ብዙ ፡ የቤት ፡ ክህነት ፡ ሥርዓትና ፡ ደንብ ፡ በለዋወጡ ፡ ጊዜ ፡ የዚህንም ፡ የሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ደንብ ፡ ለውጠው ፡ የተያዘው ፡ ኣንበሳ ፡ እንዳይገደል ፡ ስለወሰኑ ፡ ልጃቸው ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የኣባታቸውን ፡ ምሳሌ ፡ ተከትለው ፡ ይሆናል።

ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ መርያም ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ ባከበሩበት ፡ ቀን ፡ ለስመ ፡ መንግሥት ፡ የሚሆን ፡ ገብረመስቀል ፡ ዳዊት ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ የሚል ፡ ፫ዓይነት ፡ ስም ፡ ቀርቦ ፡ ከነዚሁ ፡ በእጣ ፡ ዳዊት ፡ ስለወጣ ፡ ስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ ሆኖ ፡ በዚሁ ፡ መታወጁን ፡ እየገለጸ ፡ በሌላ ፡ ዘንድ ፡ ያላገኘነውን ፡ የብዙ ፡ ስም ፡ አቀራረብና ፡ በእጣ ፡ የመመረጡን ፡ ደንብ ፡ ይህ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ይገልጽልናል።

ነገር ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ አላፈን ፡ ሌላ ፡ መጻሕፍት ፡ ስንመለከት ፡ ምስተር ፡ ዊሊያም ፡ ራይት ፡ ባሳተሙት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ መጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ከመቅድሙ ፡ ላይ ፡ በገጽ ፡ ፯ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ወይም ፡ ሕርያቆስ (ኪርያቆስ) ብለውት ፡ ይገኛል። ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ሺሃብ ፡ ኤዲን ፡ አህመድ (ዐረብ ፡ ፋቂህ) የሚባለው ፡ የየመን ፡ ተወላጅ ፡ የግራኝንና ፡ ያፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ በጻፈበት ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያፄ ፡ ናዖድ ፡ አባት ፡ ያፄ ፡ ወናግ ፡ ሰገድ ፡ ኣያት ፡ አድማስ ፡ እያለ ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ ሲጽፍ ፡ ይገኛል። ስለዚህ ፡ እኚህ ፡ ንጉሥ ፡ ከመጠሪያ ፡ ስማቸው ፡ ከበእደ ፡ ማርያም ፡ ከስም ፡ መንግሥታቸው ፡ ከዳዊት ፡ በቀር ፡ እንደ ፡ ምስተር ፡ ውሊያም ፡ ኪርያቆስ ፡ እንደ ፡ ዐረብ ፡ ፋቂህ ፡ ኣድማስ ፡ የሚባል ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ ነበራቸው ፡ ማለት ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ እኛ ፡ የምንከተለው ፡ በጣም ፡ የታወቀውን ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የሚባለውን ፡ ስማቸውን ፡ ነው።

**ሐ**–ከዚህ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ የምንመለከተው ፡ አንገዛም ፡ እያሉ ፡ ዘወትር ፡ ይሸፍቱ ፡ የነበሩት ፡ የአዳልና ፡ የይፋት ፡ ባላባቶች ፡ አሁን ፡ ባፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ጊዜ ፡ ባላባታቸው ፡ መሐመድ ፡ ቤን ፡ ቤድ ፡ ላይ ፡ "እንግዲህ ፡ በመካከላችን ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፡ እኔም ፡ በያመቱ ፡ ዓገሬን ፡ ይገኘ ፡ እየመጣሁ ፡ ልገዛልህ ፡ ኣንተም ፡ ጨዋ ፡ የሚባሉትን ፡ ወታደሮችህን ፡ ወዳገሬ ፡ አትላክብኝ ፡ ብሎ ፡ በውለታ ፡ መስማማቱን ፡ ነው።

በዘሩ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ አንባቢ ፡ ሊመለከተው ፡ እንደሚችለው ፡ ይህ ፡ መሐመድ ፡ ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተው ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ አርዌ ፡ በድላይ ፡ የሚለው ፡ የበድላይ ፡ ሺሃብ ፡ ኤዲን ፡ መሐመድ ፡ ልጅ ፡ ነው። ዳሩ ፡ ግን ፡ መሐመድ ፡ በዘመኑ ፡ ከዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ጋር ፡ በስምምነት ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ ኦትማን ፡ ቤይ ፡ ሶለይማን ፡ በመሐመድ ፡ ፋንታ ፡ ተተክቶ ፡ ካፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ ወደፊት ፡ በሚገኘው ፡ ምዕራፍ ፡ እንመለከታለን"

**መ**–ዘወትር ፡ ፈረስ ፡ ይጋልባል ፡ እንጂ ፡ ተቀምጦ ፡ ሥርዓተ ፡ መንግሥትን ፡ እየፈጸመ ፡ ፍርድ ፡ ኣይሰማም ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ያሙዋቸውን ፡ ሹማምንት ፡ የየግራቸውን ፡ ሥር ፡ እያስቆረጡ ፡ በየአውራጃው ፡ መላካቸው ፡ ተጽፏል። ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ሥራቸው ፡ የተቆረጠበትን ፡ ቤት ፡ "ቤተ ፡ መድኃኒት ፡ ብሎታል ፡ ምናልባት ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ የጭካኔ ፡ ቅጣት ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ መጠን ፡ እጅና ፡ እግሩ ፡ የሚቆረጠው ፡ ሥሩ ፡ ተቆርጦ ፡ ወይም ፡ ተገርፎ ፡ የሚጋዘው ፡ ሰው ፡ የሚቀጣበት ፡ ቤት ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ አነጋገር ፡ ቤት ፡ መድኃኒት ፡ ይባል ፡ ይሆናል። ይኸም ፡ ደንበኛውን ፡ አጠራር ፡ « የመቅጫ ፡ ቤት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ በኣካሉ ፡ የተቀጣው ፡ ሰውዬ ፡ ከቅጣት ፡ በኋላ ፡ ደሙን ፡ ለማቆም ፡ ቍስሉን ፡ ለማሻር ፡ የሚደረገውን ፡ መድኃኒት ፡ ብቻ ፡ ተከትሎ ፡ ቤተ ፡ መድኃኒት ፡ ብሎታል ፡ ማለት ፡ ነው። ይኸም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሲያጠፋ ፡ ወደ ፡ እልፍኝ ፡ ተጠርቶ ፡ በእልፍኝ ፡ አሽከር ፡ እጅ ፡ በጥፊ ፡ ወይም ፡ በከርን ፡ ካተመታ ፡ ሲበዛም ፡ በድጅኖ ፡ ከታሸ ፡ በኋላ ፡ እገሌ ፡ ዛሬ ፡ ተመከረ ፡ ይባላል። ይኸም

፡ ቀጥተኛውንና ፡ ክፉውን ፡ ወገን ፡ በስም ፡ እየሸሹ ፡ ክፉውን ፡ ሥራ ፡ በደገኛ ፡ ሥያሜ ፡ ለመሸፈን ፡ ሲሞከር ፡ ነው።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ ነገሥታተ ፡ ሁሉ ፡ በሐሜተኞች ፡ ላይ ፡ የፈቀዳቸውን ፡ ቅጣት ፡ ይፈጽማሉ። በዛሬ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ በሠለጠኑትና ፡ የዴሞክራሲ (ሕዝባዊ ፡ ኣስተዳደር) አገዛዝ ፡ ባለባቸው ፡ አገሮች ፡ ንጉሡ ፡ ወይም ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ተቀምጦ ፡ መፍረድ ፡ አይወድም ፡ የሚወደው ፡ ፈረስ ፡ ግልቢያና ፡ ወሀ ፡ ዋና (ስፖርት) ብቻ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ከማማት ፡ ኣልፈው ፡ በኣደባባይ ፡ ቢናገሩ ፡ በጋዜጣ ፡ ቢጽፉ ፡ እንኳን ፡ የእግራቸው ፡ ሥር ፡ ተቆርጦ ፡ ሊጋዙ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ መልሱን ፡ ከመስጠትና ፡ ነገሩን ፡ ለማስተባበል ፡ ወይም ፡ አስፈላጊነቱን ፡ ከማስረዳት ፡ በቀር ፡ ተግሣጽ ፡ እንኳን ፡ ሊቀርብባቸው ፡ አይችልም።

ነገር ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ መብት ፡ ለሕዝብ ፡ የዕጠ ፡ ከ፲፯ኛውና ፡ ከ፲፯ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ወዲህ ፡ በእንግሊዝና ፡ በፈረንሳዊ ፡ ኣገር ፡ የተደረገው ፡ የሕዝብ ፡ ንቅናቄ ፡ በሽብርና ፡ በደም ፡ የተመሠረተው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ነው። ከዚያ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያም ፡ በሌላውም ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ነገሥታት ፡ ባለጉልት ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ በሕዝብና ፡ በበላገር ፡ በአካሉና ፡ በሐብቱ ፡ እንደልባቸው ፡ ሲያዙበት ፡ ኖረዋል። ከዚህም ፡ አልፈው ፡ ሞራሉንና ፡ መንፈሱን ፡ ለራሳቸው ፡ ጥቅም ፡ ለማዋል ፡ እንደታገሉ ፡ ኣላስገዛም ፡ ያለውን ፡ እንደጨቆኑ ፡ እላይ ፡ እስካመለከትናቸው ፡ ዘመናት ፡ ደረሱ።

ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ ሕዝብ ፡ አማካሪውን ፡ ሲሾም ፡ በአማካሪው ፡ አማካይነት ፡ ልቡ ፡ የፈቀደውን ፡ መሪ ፡ ሲመርጥ ፡ የሕዝብ ፡ ሥልጣን ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ የመሪ ፡ ሥልጣን ፡ እየተቀነሰ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሕዝብን ፡ ሲለማመጥ ፡ የገላቢጦሽ ፡ ሕዝብ ፡ በመሪው ፡ ሲቆነን ፡ እነሆ ፡ እስካሁን ፡ በኣውሮፓ ፤ በአሜሪካ ፤ በአፍሪካ ፤ በእስያ ፡ ባንዳንድ ፡ የዲሞክራሲ ፡ ኣስተዳደር ፡ ባለበት ፡ ክፍል ፡ ይቀጥላል። የዲሞክራሲ ፡ አስተዳደር ፡ የሌለባቸው ፡ አህጉሮችና ፡ እንደዚሁም ፡ የኮሚኒስት ፡ አገሮች ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ መብት ፡ ለሕዝብ ፡ ኣልሰጡም ፡ ወይም ፡ የሰጡት ፡ በመጠኑ ፡ የተወሰነ ፡ ነው።

ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በጊዜያቸው ፡ ወዳደረጉት ፡ ውስጣዊ ፡ ጦርነት ፡ እንመለስ።

# ምዕራፍ ፡ ፵፫።

## የዶብዓ (ዋጅራት - ራያና ፡ አዘቦ) ጦርነት።

በእደ ፡ ማርያም ፡ በዚህ ፡ አሁን ፡ በያዝነው ፡ ምዕራፍ ፡ ሊዋጉ ፡ ሲዘጋጁ ፡ የምንመለከተውን ፡ ነገር ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ አገሩን ፡ ዶብአ ፡ ሰዎቹን ፡ ሰብአ ፡ ዶብኣ ፡ ይላቸዋል። ይህ ፡ አገር ፡ ከዞብልና ፡ ከየጁ ፡ ምሥራቅ ፡ ከአውሳ ፡ ከደንከል ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ያሉት ፡ የራያና ፡ የአዘቦ ፡ ነገዶች ፡ ናቸው። እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያደርጉት ፡ እንደነበረው ፡ ያንጊዜም ፡ የተዋጉበት ፡ ምክንያት ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ እየተቃወሙ ፡ ነጋዴና ፡ አገር ፡ ዘርፈው ፡ ወይም ፡ ግብር ፡ ከልክለው ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም። ስለዚህ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ በደብረ ፡ ነጐድጓድና ፡ በአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ብዙ ፡ የመንፈሳዊና ፡ የሥጋዊ ፡ ጉዳይ ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ በመካነ ፡ ማርያም ፡ ኣጠገብ ፡ ደብተራ ፡ ማርያምን ፡ ተክላው ፡ በሐይቅ ፡ በኵል ፡ አድርገው ፡ ወደዶባ ፡ መዝመታቸውን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ካለው ፡ ከግዕዝኛው ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ የአማርኛውን ፡ ትርጓሜ ፡ እንመልከት።

“…………እነዚህን (እስላሞቹን) ከላኩ ፡ በኋላ ፡ አቡነ ፡ መርሕነ ፡ ክርስቶስንና ፡ መነኮሳቱን ፡ ሰበሰቡና ፡ እንግዴህ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ዶባ (ዶብኣ) መሄዴ ፡ ነው። እናንተም ፡ በየአገራችሁ ፡ ተመለሱ። በጸሎታችሁም ፡ አትርሱኝ ፡ ብላው ፡ ለአቡነ ፡ መርሕነ ፡ ክርስቶስ ፡ ፴ ፡ ግምጃ ፡ ለሌሎቹም ፡ እንደ ፡ ደረጃቸው ፡ ሰጧቸው። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አቡነ ፡ መርሕነ ፡ ክርስቶስ (መርሐ ፡ ክርስቶስ-ይምርሐነ ፡ ክርስቶስ) እሄድክበት ፡ አብሬ ፡ እሄዳለሁ ፡ እንጂ ፡ ካንተ ፡ ኣልለይም ፡ ብለው ፡ እምቢ ፡ አሉ። አባ ፡ ኣቡቂር ፡ የሚባሉት ፡ የእንደገበጥን (እንደገብጠን) መምህር ፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ ታምሜ ፡ ለሞት ፡ ቀርቤያለሁ ፡

**እግዚአብሔር** ፡ ይከተልሃልና ፡ ወደ ፡ አሰብከው ፡ ሂድ። ስለልጅ (ስለዘር) አትዘን ፡ **እግዚአብሔር** ፡ የበቃ ፡ ልጅ ፡ ይሰጥሃል። መንግሥትም ፡ ከዘርህ ፡ አይወጣም። ይኸም ፡ ነገሬ ፡ ሐሰት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ አጥንቴ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠል። ነገር ፡ ግን ፡ ደብሬን ፡ ኣትርሳ ፡ ልጆቼንም ፡ ኣጽናቸው ፡ ብለው ፡ ከላኰ ፡ በኋላ ፡ ሞቱ ፡ ንጉሡም ፡ የኘህን ፡ መነኰሴ ፡ ንግግራቸውንም ፡ ሞታቸውንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በሚገባ ፡ ኣስገንዘው ፡ ባገራቸው ፡ እንዲቀበሩ ፡ ላኰና ፡ እርሳቸው ፡ ከነሠራዊታቸው ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ የጭቃ ፡ ሀገር ፡ ደረሱ። የሐይቅ ፡ ሰዎችም ፡ በሥርዓት ፡ ሆነው ፡ ተቀበሉዋቸው።

እርሳቸውም ፡ ሥርዓታቸውንና ፡ የለበሱትን ፡ የሽልማት ፡ ልብስ ፡ ዓይተው ፡ አመሰገኑና ፡ ወደሥፍራችሁ ፡ ተመለሱ ፡ ብለው ፡ አሰናብተው ፡ በደንካ (ደንኳ)ኣድርገው ፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ይግዛ ፡ ደረሱ። የአንጎት ፡ ሰዎችም ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ በከበሮ ፡ በዘፈን ፡ ካህናቱም ፡ በማኅሌት ፡ ድምጻቸውን ፡ እያሰሙ ፡ ተቀበሉዋቸው። ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ሲሔዱ ፡ ከፍተኛ ፡ ሥፍራ ፡ አግኝተው ፡ መልካም ፡ መሆኑን ፡ ሲረዱ ፡ መቅደስ ፡ አሠሩና ፡ መንበረ ፡ ማርያም ፡ ብለው ፡ ሠየሚት። ከዚያ ፡ በዋንዛጌ ፡ በቋርቋራ ፡ በሜራ ፡ ወንዝ ፡ አልፈው ፡ ዞብል ፡ ደረሱ። የዣን ፡ ቀንጠፋ (ሰብአቀንጠፋ) ሰዎችም (ወታደሮች)መጥተው ፡ ተቀበሉዋቸው። እነርሱንም ፡ ሒዱ ፡ በምታውቊት ፡ አገር ፡ እደሩ (ተሠማሩ)ብለው ፡ ኣዘዝዋቸው ፡ በማግሥቱ ፡ ፈረሰኛውንም ፡ እግረኛውንም ፡ ሌጣውንም ፡ ለጦርነት ፡ አዘጋጅተው ፡ ጥንት ፡ ንጉሥ ፡ ዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ በሱፍ ፡ ድንኳን ፡ ወደነበሩበት ፡ ማንገሮ ፡ ወደሚባለው ፡ ሥፍራ ፡ ደረሱ። በዚያም ፡ ጨዋን (የጦር ፡ ሠራዊቱን) ለያንዳንዳችሁ ፡ ሠፈር ፡ አበጅታችሁ ፡ ተቀመጡ ፡ ብለው ፡ አዘዙ። ስለዚህ ፡ ዣን ፡ ጸገና ፤ ሰብአ ፡ ባሊ (የባሊ ፡ ወታደር) የሚባሉት ፡ ለብቻ ፡ ሲሰፍሩ፣ ፡ የፈጠጋር ፡ የግድም ፡ የገኘ ፡ ጨዋ ፡ በየቦታው ፡ ሠፈረ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ «ሴት ፡ የያዛችሁ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ግራ ፡ በዓልቲሐትና ፡ ቀኝ ፡ በዓልቲሐት ፡ ወደሚገኙበት ፡ ወደ ፡ አይድአ ፡ ምድር ፡ ሴቶቻችሁን ፡ ላኩ ፡ "ሴት ፡ የተገኘበት ፡ ሰው ፡ በሞት ፡ ይቀጣል'' የሚል ፡ አዋጅ ፡ አስነግረው

፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ ወታደር (ጨዋ)ወደ ፡ ምድረ ፡ ሙብራ ፡ አልፎ ፡ ከጠላት ፡ ወገን ፡ ቢያገኝ ፡ እንዲዋጋና ፡ የጦር ፡ መንገድ ፡ እንዲከፍት ፡ አዘዙ ፡ እነርሱም ፡ ወደፊት ፡ ቀድመው ፡ ጠላትን ፡ ቢፈልጉ ፡ ምንም ፡ ሳያገኙ ፡ ስለቀሩ ፡ ወደኋላቸው ፡ ተመልሰው ፡ ለንጉሡና ፡ ለጦሩ ፡ ማለፊያ ፡ የሚሆን ፡ መንገድ ፡ ሲሡሩ ፡ ዋሉ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ የአንበሳ ፡ ለምዳቸውን ፡ ለብሰው ፡ ጋሻና ፡ ጦራቸውን ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ከብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ወጡ። አንዳንድ ፡ ቀን ፡ ቀስት ፡ የሚይዙበት ፡ ቀን ፡ ኣለ። በሩቅ ፡ እርሳቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ስላወቍ ፡ የዶባ ፡ ሰዎች ፡ ንጉሡ ፡ ሳይደርሱባቸው ፡ ላማቸውንም ፡ ግመላቸውንም ፡ ኣሸሽተው ፡ ከሚደበቍበት ፡ ሥፍራ ፡ ምድረ ፡ ተኪኖ ፡ ሔደው ፡ ተቀመጡ።

የንጉሡን ፡ መምጣት ፡ ደንከሌ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፩ ፡ ፈረስ ፤ ፩ ፡ ቴምብር ፡ የተጫነ ፡ በቅሎ ፡ ፪ ፡ ጋሻ ፤ ሁለት ፡ ረዣዥም ፡ ጦር ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ጨምሮ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እኔም ፡ እነዚህ ፡ ጠላቶችህ ፡ ወደኔ ፡ ቢመጡ ፡ ለመያዝ ፡ ከወዲህ ፡ ሠፍሬያለሁ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ወዳንተ ፡ ያልመጣሁት ፡ የሚል ፡ መልክት ፡ ላከ። ንጉሡም "መልካም ፡ አድርገሃል ፡ ወደ ፡ አገርህ ፡ እንዳይወርዱ ፡ ጠብቃቸው" የሚል ፡ መልስ ፡ ላኩበት። በዚሁ ፡ ሳሉ ፡ **የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡** የኤጲፋንያ ፡ በዓል ፡ ስላደረሰው ፡ ጉድጓድ ፡ አስቆፍረው ፡ ከሩቅ ፡ እየተመላለሰ ፡ ወሀ ፡ አስሞሉና ፡ የጥምቀትን ፡ ሕግ ፡ ፈጸሙ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያንድ ፡ ክፍል ፡ የጦር ፡ ወታደሮች ፡ ከነዚህ ፡ ከከሐዲዎቹ (ዓሳውያን)ጋር ፡ እንዲዋጉ ፡ ላኳቸው። ነገር ፡ ግን ፡ ከሐዲዎቹ ፡ አይለው ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ ፈጁዋቸው። ተርፈው ፡ የተመለሱትንም ፡ "ባያችኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ለኔ ፡ ተመልሳችሁ ፡ እንድዋጋ ፡ አልነገራችሁኝም ፡ ብቻችሁን ፡ ለምን ፡ ተዋጋችሁ" ብለው ፡ ንጉሡ ፡ ተቆጡና ፡ እንደ ፡ ጥንት ፡ ልማድ ፡ እራቍታቸውን ፡ አቍመው ፡ የአህያና ፡ የላም ፡ ሳንባ ፡ እመቀመጫና ፡ አፍንጫቸው ፡ ላይ ፡ አስደርገው ፡ ቀጧቸው። እንደዚህ ፡ ሆነው ፡ ምሕረት ፡ ሳያገኙ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ተቀጡ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ በዚች ፡ ኣገር ፡ እርሻ ፡ ኣሳርሼ ፡ እህል ፡ ዘርቼ ፡ ከሚበቅለው ፡ እህል ፡ ፈረሴን ፡ ሳላበላ ፡ ከዚች ፡ አገር ፡ አልሔድም ፡ » ብለው ፡ በጉባዔ ፡ ማሉና ፡ ጸንታችሁ ፡ ተዋጉ

፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ሀገራችሁ ፡ መመለስ ፡ አትመኙ ፡ ብለው ፡ ሠራዊቱን ፡ አስጠነቀቋቸው። ከዚያ ፡ ብዙ ፡ ጨዋ (ወታደር)ጨምረው ፡ የባሊውን ፡ ገራድ ፡ ሔዶ ፡ እንዲዋጋ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ጋሞ ፡ ላኩት። ዳሩ ፡ ግን ፡ እርሱንም ፡ ከነጭፍራው ፡ ጠላቶች ፡ ገደሉት። ንጉሡም ፡ የርሱን ፡ መመለስ ፡ እየጠበቊ ፡ እስኪመሽ ፡ ድረስ ፡ የግብር ፡ ማዕድ (ምሳ)ሳያደርጉ- ፡ ዋሉ። ከዚያም ፡ ሔዳችሁ ፡ ወሬ ፡ ጠይቊ ፡ ያሏቸው ፡ ሰዎች ፡ ሔደው ፡ መርምረው ፡ ተመለሱና ፡ የእንቅልፍ ፡ ጊዜ ፡ ከኣለፈ ፡ በኋላ (ሌሊት)ቀርበው ፡ ግራድ ፡ ሳሊ ፡ ከነጦሩ ፡ መሞቱን ፡ ነገሩዋቸው። ስለዚህ ፡ በማግስቱ ፡ ንጉሡ ፡ "ጦርነት ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ እያሸነፉ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ መሸነፍ ፡ የቆየ ፡ ነውና ፡ አሁን ፡ ፍርሃት ፡ በሕሊናችሁ ፡ ኣይግባ ፡ ልባችሁን ፡ አጽኑ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ በጊዜው ፡ ይረዳናል ፡ » ብለው ፡ ለሠራዊቱ ፡ ተናገሩ ፡ ቢሆንም ፡ በሠራዊቱ ፡ መካከል ፡ የሆድ ፡ በሽታ (ሕማመ ፡ ከርሥ) ስለተነሣ ፡ ዶብዓን ፡ ለቀቊና ፡ የትግሬ ፡ መኰንን ፡ ግዛት ፡ ወደሚሆን ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ሐያ ፡ ሔዱ። በዚያም ፡ የዓቢይ ፡ ጾም ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ቆዩ ፡ ንግሥታቶቹንም ፡ ግራ ፡ በዓልቲሐትንና ፡ ቀኝ ፡ በዓልቲሐትን ፡ ከነበሩበት ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ አይዳ ፡ እንዲመጡና ፡ ከብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ በከተማ ፡ እንዲቀመጡ ፡ አደረጉ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ "ሠራዊቴ ፡ ሁላችሁም ፡ መቀመጫችሁን ፡ በዚች ፡ አገር ፡ ሥሩ። አባቴ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን (ተጉለት)እንደነበረ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ለመኖሪያ ፡ ይቺን ፡ ሥፍራ ፡ መርጫለሁ። ፈረሶቼም ፡ በትግሬ ፡ እስከ ፡ አምባ ፡ ሠናይት ፡ ድረስ ፡ እየበሉ ፡ እንዲቀመጡ ፡ አዝዣለሁ" የሚል ፡ ኣዋጅ ፡ ኣስነገሩ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከጸለምት ፡ ሹም ፡ ከአምባ ፡ ነሐድ ፡ ሊዋጉ ፡ የሔዱትን ፡ ዣን ፡ አሞራ ፡ የሚባሉትን ፡ የጨዋ (የወታደር)ክፍሎች ፡ እንዲጠሩዋቸው ፡ ወደጸለምት ፡ ላኩ። እነርሱም ፡ ኣጠገባቸው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ በጸለምት ፡ የሆነውን ፡ የአምባ ፡ ነሐድን ፡ ነገር ፡ ጠይቀው ፡ በዶብአ ፡ በኩል ፡ የሆነውንም ፡ የጦርነት ፡ ሁኔታ ፡ ገለጹላቸው። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡ መለሱላቸው ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከኣምባ ፡ ነሐድ ፡ ጋር ፡ እንዳዘዝኸን ፡ ስንዋጋ ፡ ነበር። ወደ ፡ ዶብኣ ፡ በዘመትህ ፡ ጊዜ ፡ መጥተን ፡ እንድንዋጋ ፡ ለምን ፡ ሳታስጠራን ፡ ቀረህ ፡ አባትህ ፡ በዚህ ፡ ኣገር ፡ ያሠማራን

(የተከለን)ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ አይደለምን? ፡ ወታደርስ ፡ ሁሉ ፡ መንገዱን ፡ በሚያውቀው ፡ በያገሩ ፡ ቢዋጋ ፡ ይሻል ፡ የለምን። አሁን ፡ ግን ፡ እኛ ፡ ባሮችህ ፡ ፈቃድህን ፡ ፈጽመን ፡ እናስደስትሃለን ፡ ስላንተም ፡ እየሞትን ፡ የዶብዓን ፡ ሰዎች ፡ እናጠፋቸዋለን።

ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ሰምተው ፡ ምሕላቸውን ፡ ሰውነታቸው ፡ እስኪለወጥ ፡ ድረስ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ፈጸሙ። ልብሰ ፡ መንግሥታቸውንም ፡ ሳይለብሱ ፡ በዙፋን ፡ ተቀመጡ። በአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ የነበረውንም ፡ ገንዘባቸውን ፡ አውጥተው ፡ ምንም ፡ ሳይቀር ፡ ለእመቤታችን ፡ ላቅድስት ፡ ማርያም ፡ ሰጡ። ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ **እግዚአብሔር** ፡ እንዲሰማቸው ፡ ለድሆችና ፡ ለችግረኞች ፡ እንዲታደል ፡ ሽህ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ላኩ።

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ የዶብዓ ፡ ሰዎች ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ይኸ ፡ ንጉሥ ፡ አልለቀቀንም ፡ እኛንም ፡ አገራችንንም ፡ ለማጥፋት ፡ ቆርጧል። ስለዚህ ፡ ከብታችንን ፡ ሴቶችና ፡ ልጆቻችንን ፡ ሰብስበን ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ አገር ፡ ብንሰደድ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ፲፪ቱ ፡ የዶብአ ፡ ሹማምንት ፡ ሰዎቻቸውን ፡ ጭነታቸውን ፡ ይዘው ፡ ለሽሽት ፡ ዝግጅታቸውን ፡ ንጉሡ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ትግሬ ፡ መኰንንን ፡ የቅዳን ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ የዳሞትን ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ ሔዳችሁ ፡ ከመንገድ ፡ እየጠበቃችሁ ፡ ተዋጉ ፡ ብለው ፡ ኣዘዟቸው። ፈረሶቹንም ፡ ከመነኣታቸው ፡ በፊት ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ፊንደን (ፊንዶን)እንዲያወርዱዋቸው ፡ አዘዙ። በመንፈቀ ፡ ሌሊትም ፡ ተነሥተውያለጫማ ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይሉ ፡ ነበር። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልብስ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለብሰው ፡ እፈረሳቸው ፡ ላይ ፡ ወጡና ፡ ለጦርነት ፡ ተዘጋጁ። ከዚያ ፡ ልጆቻቸውንና ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ከብቶቻቸውን ፡ ሰብስበው ፡ ሳለ ፡ ደረሱባቸውና ፡ ጦርነት ፡ ገጥመው ፡ ጨረሷቸው። ተርፈው ፡ የሸሹትንም ፡ የዳሞትና ፡ የትግሬን ፡ ጦር ፡ ልከው ፡ አስወጓቸው። እግዚአብሔር ፡ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ ስለተቀበለው ፡ ምሥጋናቸውንም ፡ ስለአልናቀባቸው ፡ ምኞታቸው ፡ ተፈጸመ። እንደዚሁም ፡ የልጃቸውን ፡ የእስክድርን ፡ ምኞት ፡ ይፈጽምለት ፡ የዚህን ፡ ንጉሥ ፡ ሞቱን ፡ የሚመኘውን ፡ ዘሩን ፡ ያጥፋው ፡ አሜን ፡ ወደነገራችን ፡

እንመለስ። ይልና ፡ አሁንም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጸሐፊው ፡ የተረፈውን ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይቀጥላል። «ንጉሡ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ የነዚህን ፡ የከሀዲዎች (የሹሞቹን፡?) ጭንቅላት ፡ አስቆርጠው ፡ አስይዘው ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ ከተማቸው ፡ ተመለሱ (ሌሎቹም) ለየሴቶቻቸው ፡ ሰለባና ፡ ምርኮ ፡ ይዘው ፡ ነበር ፡ እከተማው ፡ ሲገቡ ፡ በሠፈር ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሆነ። የዘፈንና ፡ የማኅሌት ፡ ድምጽም ፡ በየሥፍራው ፡ አብዝቶ ፡ ተደረገ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚያው ፡ አቅራቢያ ፡ ቀድሞ ፡ በነበሩበት ፡ ሥፍራ ፡ እንዲከርሙ ፡ ስለተወሰነ ፡ ከንጉሡ ፡ አልለይም ፡ ብለው ፡ አብረው ፡ ለነበሩት ፡ ለአቡነ ፡ ይምርሐነ ፡ ክርስቶስ ፡ ፪፻፲፫ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ፣ የወርቅ ፡ መስቀል ፡ አክፋርና ፡ መንዲል ፡ ሰጥተው ፡ በሰላም ፡ ወዳገራቸው ፡ አሰናበቷቸው።

ለመነኮሳቱም ፡ ልብስ ፡ ኣደሏቸው። ከዶብዓ ፡ ሰዎች ፡ የተማረካውን ፡ ከብት ፡ ለዣን ፡ አሞራ ፤ ለዣን ፡ ቀንጠፋ ፡ እንዲጠብቍ ፡ ምሪት ፡ ሰጧቸው። ምሕረት ፡ የለመኑትንም ፡ የዶብዓ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ክርስቲያንነት ፡ መልሰው ፡ የተማረከውን ፡ ከብታቸውንም ፡ እንዲያውም ፡ ከወጅና ፡ ከገንገ ፡ የራሳቸውን ፡ ከብት ፡ አስመጥተው ፡ ጨምረው ፡ ሰጧቸው። በመካከላቸውም ፡ ዳዊት ፡ አምባ ፡ በማን ፡ ገደፎ ፡ የሚባሉትን ፡ ጨዋ (ወታደሮች)ተሠሪ ፡ አደረጓቸው። ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሠርተው ፡ በእመቤታችን ፡ ስም ፡ ሠየሟት። ብዙም ፡ አትክልት ፡ ትርንጎ ፤ ሎሚ ፤ ወይን ፡ ኣስተክለው ፡ የዶብዓን ፡ ኣገር ፡ ኣለሙት። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ኣሣርሼ ፡ እህል ፡ ዘርቼ ፡ የበቀለውን ፡ እህል ፡ ለፈረሴ ፡ ሳላበላ ፡ ከዚህ ፡ ኣገር ፡ አልሄድም ፡ ብለው ፡ እንደነበረው ፡ ከዚሁ ፡ አገር ፡ እርሻ ፡ አሣርሠው ፡ ያበቀሉትን ፡ እህል ፡ ለፈረሶቻቸወና ፡ ለበቅሎቻቸው ፡ አብልተው ፡ ኣሳባቸን ፡ ፈጸሙ። በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ባለቤታቸውን ፡ በዓልተ ፡ ሸሕና (ሸኾና) ዳዊት ፡ ኤራ ፡ አሰኝተው ፡ አነገሥዋቸው (ንግሥት ፡ አደረጓቸው)

ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ አክሱም ፡ ሄጄ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሤን ፡ ባከብር ፡ መልካም ፡ አይደለምን ፡ ብለው ፡ ለንስሐ ፡ አባታቸው ፡ ለደብረዳሞው ፡ መምሕር ፡ ለአቡኝ ፡ ማቴዎስ ፡ አማከሯዋቸው። እርሳቸውም ፡ ደህና ፡ አሳብ ፡ ነው። **እግዚአብሔርም** ፡ ፈቃድህን ፡ ይፈጽምልህ ፡ አሉዋቸው። ስለዚህ ፡ ትግሬ ፡ መኰንንና ፡ ሹማምንቱን ፡ መነኮሳቱንም ፡ አክሱም ፡ ሄዳችሁ ፡

ለሥርዓተ ፡ ንግሡ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እያዘጋጃችሁ ፡ ጠብቁኝ ፡ ብለው ፡ ልከዋቸው ፡ ሳለ ፡ ለደስ ፡ እስማን ፡ የሚባለው ፡ የኣዳል ፡ ሹም ፡ መምጣቱን (ለውጊያ) በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኣክሱም ፡ የላኳቸውን ፡ ሹማምንት ፡ ወደኔ ፡ ተመለሱ ፡ ብለው! ፡ ላኵባቸውና ፡ ተመልሰው ፡ መጡ። ከዚያ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ዶብዓ ፡ አገር ፡ ወረዱና ፡ የጥምቀትን ፡ በዓል ፡ አከበሩ። የዶብዓ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ ሁሉ ፡ አዘጋጁ ፡ የሚያስተዳድራቸውንም ፡ ሾሙ። የእመቤታችንም ፡ የዕረፍቷ ፡ ቀን ፡ በጥር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ እንዲከበር ፡ ኣዘዙ። ሹማምንቱ ፡ ሁሉ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ እያመጡ ፡ ትእዛዙን ፡ በደስታ ፡ ፈጸሙ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንግዲህ ፡ ጦር ፡ በያዛችሁበት ፡ እጅ ፡ ማረሻ ፡ እየያዛችሁ ፡ እረሱ (አገሩን ፡ አልሙት) ፡ ብለው ፡ የዶብዓን ፡ ኣገር ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ አንጎት ፡ ጉዞ ፡ ዠመሩ። ብሎ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ይጨርሳል።

ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጎብአ ፡ ዶብዓ ፡ የሚባሉትን ፡ በደንከል ፡ በአንጎት ፡ በኣማራ ፡ ሳይንት ፡ በትግሬና ፡ በላስታ ፡ መካከል ፡ የሚገኙትን ፡ ዛሬ ፡ ዋጅራት ፡ ራያና ፡ ኣዘቦ ፡ የሚባሉትን ፡ በጦርነት ፡ ማስገበር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በጦርነቱ ፡ ተገድደው ፡ የሞቱት ፡ ሞተው ፡ የተረፉትን ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ለመመለስ ፡ መፈተናቸው ፡ ነዋሪ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መትከላቸው ፡ ያስመሰግናቸዋል። ጦርነቱ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ጦር ፡ በጨበጣችሁበት ፡ እጅ ፡ እረሱበት ፡ በሚል ፡ የሊቅ ፡ አነጋገር ፡ አስረድተው ፡ ጠፍና ፡ በረሀ ፡ የሆነውን ፡ አገር ፡ በእርሻ ፡ እንዲለማ ፡ ማድረጋቸው ፡ በምሥጋና ፡ ላይ ፡ ምሥጋና ፡ ይጨምርላቸዋል። በረሀውን ፡ አርሼ ፡ የታረሰውን ፡ አዘርቼ ፡ የሚበቅለውን ፡ እህል ፡ ለፈረሴ ፡ ሳላበላ ፡ ይኸን ፡ አገር ፡ ኣልለቅም ፡ ማለታቸው ፡ ያሰበውን ፡ እፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ እንደሚችል ፡ እንደ ፡ ጽኑ ፡ መሪ ፡ ሁሉ ፡ እርሳቸውም ፡ የመንፈስ ፡ ቆራጥነት ፡ የሕሊና ፡ ጥብቅነት ፡ እንደላቸው ፡ ይታወቃል። ጦርና ፡ በሽታ ፡ በበረታ ፡ ጊዜ ፡ ይኸን ፡ የማሉበትን ፡ ሥፍራ ፡ ለመልቀቅና ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ግዛት ፡ ለመግባት ፡ ቢገደዱም ፡ በኋላ ፡ ተመልሰው ፡ ምኞታቸውን ፡ ፈጽመዋልና ፡ ያላቸውን ፡ የጽኑ ፡ ኣሳብ ፡ ዋጋ ፡ ሊቀንስባቸው ፡ አይችልም።

ነገር ፡ ግን ፡ የጦርነቱን ፡ መላና ፡ ዘዴ ፡ የተመራመርን ፡ እንደሆነ ፡ እንደተሳሳቱ ፡ እንኳ ፡ ባይሆን ፡ በጣም ፡ እንዳላሰቡበት ፡ እንመለከታለን። በመዠመሪያ ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ አድርገው ፡ የላኩዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ ተገናኝተው ፡ ተዋግተው ፡ ቢሸነፉ ፡ የተረፉትን ፡ ለኔ ፡ ለምን ፡ ተመልሳችሁ ፡ ሳትነግሩኝ ፡ ተዋጋችሁ ፡ ብለው ፡ ቀጧቸው። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የባሌን ፡ ጦር ፡ በሹሙ ፡ በገራድ ፡ ባሊ ፡ መሪነት ፡ ብቻ ፡ ልከው ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ሳይጨምሩ ፡ እርሱም ፡ ጦሩም ፡ በጠላቶቹ ፡ እጅ ፡ እንዲወድቅ ፡ ኣደረጉት።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጸለምት ፡ የነበሩትን ፡ የዣናሞራ ፡ ወታደሮች ፡ ጠርተው ፡ ቢነግሩዋቸው ፡ "ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ዶብዓ ፡ በዘመትህ ፡ ጊዜ ፡ መጥተን ፡ እንድንዋጋ ፡ ለምን ፡ ሳታስጠራን ፡ ቀረህ ፡ አባትህ (ዘርዓያዕቆብ)ከዚህ ፡ አገር ፡ ያስቀመጠን ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ አይደለምን ፡ ወታደርስ ፡ ሁሉ ፡ መንገዱን ፡ በሚያውቀው ፡ በያገሩ ፡ ቢዋጋ ፡ ይሻል ፡ የለምን? » የሚል ፡ ውስጠ ፡ ወቀሳ ፡ ያለበት ፡ የአክብሮ ፡ ጥያቄ ፡ ሲያቀርቡ ፡ ገራድ ፡ ባሊ ፡ አስቀድሞ ፡ ብቻውን ፡ በመሔድ ፡ ፈንታ ፡ መውጫና ፡ መግቢያውን ፡ የሚያውቁት ፡ እነዚህ ፡ የዣናሞራ ፡ ወታደሮች ፡ መጥተው ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ባንድነት ፡ ዘምተው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የድል ፡ መንገዱ ፡ በትክክል ፡ ባይታወቅ ፡ ማሸነፋቸው ፡ ኣይቀርም ፡ ነበር ፡ ያሰኛል። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ንጉሡ ፡ ከመዠመሪያው ፡ ጦርነት ፡ የተረፉትን ፡ ለምን ፡ ተመልሳችሁ ፡ ለኔ ፡ ሳትነግሩኝ ፡ ተዋጋችሁ ፡ ብለው ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ በጥንት ፡ ዓይነት ፡ ኣቀጣጥ ፡ እንደቀጡዋቸው ፡ ዣናሞሬዎች ፡ እኛ ፡ አገሩንና ፡ መንገዱን ፡ የምናውቀው ፡ ሳንጠራ ፡ ገራድ ፡ ባሊን ፡ ብቻውን ፡ ልከው ፡ ካስገደሉት ፡ ይቀጡ ፡ ማለት ፡ አይችሉምና ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ አሁንም ፡ ስላንተ ፡ እየሞትን ፡ እነዚህን ፡ የዶብዓ ፡ ሰዎች ፡ እናጠፋቸዋለን" ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ ፎክረው ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ ሔዱ ፡ ለማሸነፍም ፡ ቻሉ።

ይኸን ፡ ፍርድ ፡ የምንፈርደው ፡ በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ላይ ፡ የተጻፈውን ፡ ቃል ፡ ተከትለን ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ታሪክና ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ኣዘጋጅ ፡ ይልቁንም ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ ጸሐፊ ፡ ብዙውን ፡ ጠንቅቆ ፡ መጻፍ ፡ አይሆንለትምና ፡

የእርሳቸውን ፡ የጦር ፡ መላ ፡ የሚደግፍ ፡ ሳይጻፍ ፡ የቀረ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ማረጋገጥ ፡ ስለማንችል ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ እንተወው።

ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ስለተቀጡት ፡ ሰዎች ፡ ሲያመለክት ፡ "ወበእንተዝ ፡ ኰነንዎሙ ፡ እንዘ ፡ ይወድዩ ፡ ሰንቡአ ፡ አድግ ፡ ወላሕም ፡ ውስተ ፡ ኣዕናፊሆሙ ፡ ወውስተ ፡ ምንባሪሆሙ ፡ ከመ ፡ ሥሩዕ ፡ ቀዳሚ ፡ እንዘ ፡ ያቀውምዎሙ ፡ ዕሩቃኒሆሙ" ያለውን ፡ ወደ ፡ ኣማርኛ ፡ የተረጐምነውን ፡ ባለፈው ፡ አንብበናል። የአህያና ፡ የላም ፡ ሳምባ ፡ በአፍንጫና ፡ በመቀመጫ ፡ ላይ ፡ እያስቀመጡ ፡ ራቍትን ፡ የመቅጣት ፡ ልማድ ፡ መኖሩን ፡ በጽሑፍም ፡ በቃልም ፡ ገና ፡ ኣሁን ፡ መረዳቴ ፡ ነው። መቼም ፡ በአክሱምና ፡ በዛጉዬ ፡ ኣሁንም ፡ በሸዋ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ በመሳፍንትና ፡ በመኳንንት ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡ ይደረግ ፡ የነበረውን ፡ ልማድ ፡ በትክክል ፡ ኣጠናቆ ፡ ወደጊዜያችን ፡ እንዲተላለፍ ፡ ያደረገው ፡ ባለመኖሩ ፡ ባንዳንድ ፡ ዜና ፡ መዋዕልና ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ የልማድ ፡ ዓይነት ፡ ብልጭ ፡ ሲል ፡ ያንን ፡ ለመያዝ ፡ ሲቻል ፡ ማብራራቱ ፡ ይቸግራል። ወይም ፡ ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ ሲደረግ ፡ የቆየ ፡ መሆኑን ፡ የሚያውቅ ፡ አረጋዊ ፡ ማግኘቱ ፡ እንደዚህም ፡ ከበረከተው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ነገድ ፡ ውስጥ ፡ አሁንም ፡ የዚህን ፡ ተግባር ፡ የሚፈጽሙ ፡ ነገዶች ፡ መኖር ፡ አለመኖራቸውን ፡ ማረጋገጡ ፡ ችግር ፡ ነው።

በቅጣት ፡ ረገድ ፡ ስቅላት ፤ ግርፋት ፡ እጅና ፡ እግር ፡ መቍረጥ ፤ ዓይን ፡ በፍላት ፡ ማውጣት ፤ በጋለ ፡ ብረት ፡ መተኮስ ፤ በምሥራቅም ፡ በምዕራብም ፡ ሲደረግ ፡ የኖረ ፡ ልማድ ፡ ነው። ከዚህም ፡ የተረፈ ፡ ብዙ ፡ የማሠቃያ ፡ መንገድ ፡ ገዥዎች ፡ ዘመናዮች ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ሢሰሩ ፡ ኖረዋል። ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ የእግርን ፡ ሥር ፡ በጥሶ ፡ ሮጦ ፡ የሚያመልጥበትን ፡ የሚሸፍትበትን ፡ መራመጃውን ፡ አሰናክሎ ፡ ማስቀመጥ ፡ እንዳየን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ የአህያ ፡ ሳምባ ፡ አፍንጫው ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥ ፡ ምናልባት ፡ የሞራል ፡ ውርደት ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ የአካል ፡ ስቃይ ፡ ያለበት ፡ አይመስለኝም። ባገራችን ፡ ባንዳንድ ፡ አውራጃ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ በሐሰት ፡ ከሶ ፡ ሳይረታ ፡ ሲቀር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ አስነዋሪ ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ እንደሆነ ፡ በአህያ ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው ፡ ኣደባባይ ፡ ለአደባባይ ፡ ገበያ ፡ ለገበያ ፡ ያዞሩት ፡ ነበር። ባፄ ፡ በእዩ ፡ ማርያም

፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አጥፊውን ፡ በአህያ ፡ ላይ ፡ በማስቀመጥ ፡ ፈንታ ፡ ያህያውን ፡ ሳምባ ፡ በአጥፊው ፡ አፍንጫ ፡ ላይ ፡ ማስቀመጥ ፡ የበለጠ ፡ አዋራጅ ፡ በመሆኑ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ቅጣት ፡ ሲፈጸም ፡ ኖሮ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ባንዱ ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ ቀርቶ ፡ አህያው ፡ ላይ ፡ በማስቀመጥ ፡ ብቻ ፡ ተለውጦ ፡ ይሆናል።

# ምዕራፍ ፡ ፵፰።

## በአዳል ፡ ሽፍትነት ፡ የተነሣ ፡ ከዶብዓ ፡ እስከ ፡ ይፋት ፡ የተደረገ ፡ ጕዞ።

ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የዶብዓን ፡ ራያ ፡ አዘቦ ፡ ዋጅራት) ፡ ጦርነት ፡ ሹም ፡ ሽሩንና ፡ ድልድሉን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ከዶብዓ ፡ በኣንጎት ፡ በኵል ፡ አድርገው ፡ ወሲል ፡ ገቡ። ከወሲል ፡ ንግሥታቶቹን ፡ ከብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኣማራና ፡ ወደ ፡ መንዝ (መንዝህ) ልከው ፡ እርሳቸው ፡ ወደ ፡ ግድም ፡ ሄዱና ፡ በላዎ ፡ ገበያ ፡ ሄደው ፡ ፈረስና ፡ ኮርቻ ፡ ጥሩር ፡ ያስቆጥሩ ፡ ዠመር። ይኸውም ፡ ማለት ፡ አሁን ፡ በፊታቸው ፡ የተደቀነው ፡ ከኣዳሎቹ ፡ ባላባት ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ገበያ ፡ የፈረሰኛ ፡ ወታደራቸውን ፡ ኣዘጋጁ ፡ ማለት ፡ ነው።

ባለፈው ፡ ሁሉ ፡ ታሪክ ፡ እንደተመለከትነው ፡ አርዌ ፡ በድላይ (በድላይ ፡ ሺሃብ ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ አህመድ) ፡ ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጋር ፡ ሲዋጋ ፡ ከሞተ ፡ ወዲህ ፡ ልጁ ፡ መሐመድ ፡ ቤን ፡ በድላይ (ምሕመድ ፡ ወልደ ፡ ኣርዌ ፡ በድላይ) ላፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ሲገብር ፡ ኖሮ ፡ ለዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምም ፡ መላክተኛና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ልኮ ፡ እሱም ፡ ሊገብር ፡ እርሳቸውም ፡ የጨዋን ፡ ወታደር ፡ ባገሩ ፡ ልከው ፡ ላያስወጉት ፡ ውል ፡ ኣድርገው ፡ የነበረውን ፡ ተመልክተናል። ኣሁን ፡ ደግሞ ፡ የዶብዓን ፡ ጦርነት ፡ ጨርሰው ፡ በጀጅኖ ፡ የፈጸሙትን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ እደንበኛው ፡ ታሪካዊ ፡ ቦታ ፡ ኣክሱም ፡ እንዳባቴ ፡ ሄጀ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሤን ፡ አድሳለሁ ፡ እያሉ ፡ ሲዘጋጁ ፡ በመሐመድ ፡ እግር ፡ የተተካው ፡ ኦትማገ (ኡስማን) ቤይ ፡ ሶለይማን ፡ ለውጊያ ፡ ከኣዳል ፡ መጣ ፡

ማለትን ፡ ሰሙ። ይኸን ፡ ባላባት ፡ የግዕዙ ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ መኰንነ ፡ አዳል ፡ ዘስሙ ፡ ለደስ ፡ እስማን ፡ ይለዋል።

ስለዚህ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ወደ ፡ ኣክሱም ፡ ለንግሥ ፡ በመሄድ ፡ ፈንታ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተመልሰው ፡ በግድም ፡ የፈረሰኛ ፡ ወታደራቸውን ፡ በሰልፍ ፡ አስቆጥረው ፡ ለጦርነት ፡ መዘጋጀታቸውን ፡ እንመለከታለንና ፡ አሁን ፡ ግዕዝኛው ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ የሚለውን ፡ ትርጓሜ ፡ በቀጥታ ፡ እንመልከት።

«በግድም ፡ በላዎ ፡ ገበያ ፡ ፈረሶችን ፡ ጥሩርን ፡ ከኣስቆጠሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ይፋት ፡ ሄደው ፡ ምድረ ፡ ቀጭኖ ፡ ደረሱ። በዚያም ፡ ቆሙና ፡ ያገሮች ፡ ስም ፡ ይጠይቁ ፡ ዠምር። ተጠያቂዎቹም ፡ ይህ ፡ መከሬ (የግዞት ፡ ቦታ) ፡ ይህ ፡ ግንድ ፡ ብሎ ፤ ይቺ ፡ አሁን ፡ ያለንባት ፡ የአጋት ፡ ወንዝ (ፈለገ ፡ አጋት) ትባላለች ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው ፡ የአዳል ፡ ሰዎች ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ይመጣሉን ፡ ብለው ፡ ፪ተኛ ፡ ቢጠይቁ ፡ አወን ፡ እዚህ ፡ ድረስ ፡ እየመጡ ፡ ይውላሉ ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው።

በዚያም ፡ ሳሉ ፡ የሸዋና ፡ የይፋት ፡ ሕዝብ ፡ ተሰብስበው ፡ ተቀበሉዋቸው። ብዙ ፡ ፈረሰኞቹንና ፡ እግረኞቹን ፡ ከሩቁ ፡ በተመለከቱ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ እንዳይሞት ፡ ብለው ፡ በዚያው ፡ በመንገዳቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ እንጂ ፡ እንዳይመጡ ፡ ኣዘዙ። ከዚያ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ጦብያ (ይፋት) ሄደው ፡ የሱፍ ፡ ድንኳናቸውን ፡ አስተከሉ። በዚች ፡ ሥፍራ ፡ ቀድሞ ፡ ንጉሡ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ ይቀመጡባት ፡ ነበር። ብዙም ፡ አትክልት ፡ ካስተከሉ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡም ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ በደጎ ፡ ምችግ ፡ አልፈው ፡ የደብረ ፡ ብርሃን ፡ ምድር ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ጋሳይ ፡ ወንዝ ፡ ሄደው ፡ አደሩ። በዚያም ፡ ሳሉ ፡ «የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኮሳት ፡ ምነው ፡ መጥተው ፡ አልተቀበሉኝም ፡ አንተ ፡ የሸዋ ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ አይደለህምን ፡ የነርሱስ ፡ ምድር (ክፍል) ሸዋ ፡ አይደለምን ፡ ብለው ፡ ጻሕፈ ፡ ላም ፡ ደብረ ፡ ጽዮንን ፡ ጠየቁት። እርሱም ፡ «ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ መነኮሳቱ ፡ ሁሉ ፡ ከአባታችን ፡ ከይምርሐነ ፡ ክርስቶስ ፡ ጋር ፡ መጥተው ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ደርሰዋል ፡ ብሎ ፡ መለሰ።

ስለዚህ ፡ ንጉሡ ፡ በማግስቱ ፡ ካደሩበት ፡ ተነሥተው ፡ ሲጓዙ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኮሳትና ፡ የደብረ ፡ ብርሃን ፡ ደብተሮች ፡ በሥርዓት ፡ ሆነው ፡ ድባብና ፡ ጽናቸውን ፡ ይዘው ፡ መጡ። ንጉሡም ፡ ባዩዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ተደስቱና ፡ እነዚያ ፡ የሚመጡት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኮሳት ፡ አይደሉምን ፡ ብለው ፡ አጠገባቸው ፡ ያሉትን ፡ ጠየቁና ፡ አወን ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አቡነ ፡ ይምርሐነ ፡ ክርስቶስን ፡ በቶሎ ፡ አምጧቸው ፡ ብለው ፡ አዘዙ። በፍጥነትም ፡ አምጥተዋቸው ፡ እፊታቸው ፡ በቆሙ ፡ ጊዜ ፡ እጅ ፡ ሲነሡ ፡ ከደስታ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ወደቁ ፡ ንጉሡም ፡ አንሷቸው ፡ ብለው ፡ አዘዙ። መነኮሳቱንና ፡ ደብተሮቹን ፡ አመሥግነው ፡ ሲጨርሱ ፡ ጉዞው ፡ ቀጠለና ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ደረሱ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ገብተው ፡ ተሳለሙና ፡ ዙሪያውን ፡ ሁሉ ፡ እየዞሩ ፡ ተመልክተው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወደ ፡ መኖሪያቸው ፡ ሥፍራ ፡ ደረሱ። በዚያም ፡ ሲደርሱ ፡ ከአባታቸው ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ ጊዜ ፡ በልጅነታቸው ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ የተከሉትን ፡ የቀጋ ፡ ዛፍ ፡ አገኙና ፡ ግምጃ ፡ ኣለበሱት። ከዚያ ፡ በምድረ ፡ ሰርማት ፡ በኵል ፡ ኣልፈው ፡ የልጅነታቸውን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኣሳለፉበት ፡ ሥፍራ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ዘንጎ ፡ ደርሰው ፡ የሆሣዕናን ፡ የፋሲካን ፡ የዕርገትን ፡ በዓል ፡ አክብረው ፡ ሲጨርሱ ፡ ወደ ፡ የለባሻ (መርጡለ ፡ ሚካኤል) ፡ ገቡ" ፡ በዚያም ፡ ቀድሞ ፡ ዓፄ ፡ ዳዊትና ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በነበሩበት ፡ ሥፍራ ፡ ቤተ ፡ ንጉሥ (እልፍኝ) አሠርተው ፡ የክረምቱ ፡ ጊዜ ፡ እስኪያልፍ ፡ በዚሁ ፡ ከረሙ። በዚህ ፡ እንዳሉና ፡ በሐምሌ ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ ማቴዎስ ፡ የሚባለው ፡ ዣን ፡ ደረባ ፡ መጣና ፡ እመቤታችን ፡ ሮምና ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ተደሰቱና ፡ **እግዚአብሔር**ንም ፡ አመሰገኑ። ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሄዱ። ደብተሮቹ ፡ ተሰብስበው ፡ ማኅሌት ፡ እንዲያደርጉ ፡ ጠሩዋቸው። ቀኑም ፡ የእግዝእትነ ፡ ማርያምና ፡ የቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ መልአክ ፡ የበዓል ፡ ቀን ፡ ነበረ። ከቅዳሴ ፡ ውጭ ፡ ለካህናት ፡ ግብር ፡ ተደረገ ፡ ለደሆችም ፡ ምጽዋት ፡ ታደለ። ይኸን ፡ የደስታ ፡ ወሬ (ብሥራት) የነገረውን ፡ ማቴዎስን ፡ የሚያምር ፡ ልብስ ፡ ሸለሙት። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በጊዜው ፡ ክርስትና ፡ እንዲነሣ ፡ ታዘዘና ፡ ስሙንም ፡ እስክንድር ፡ ብለው ፡ ሠየሙት።

፪ኛ ፡ በዚሁ ፡ ሳሉ ፡ ከእሬሽ ፡ ገዜት (ራስ ፡ ገዚት) ፡ ቴዎድሮስ ፡ የሚባል ፡ ልጅ ፡ ተወለደ። የመስቀልን ፡ በዓል ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ጋርማ ፡ ሄደው ፡ እከ ፡ ፳፪ ፡ ኅዳር ፡ ድረስ ፡ ተቀመጡ። ከዚያ ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡ በደስታ ፡ የሚካኤል ፡ ለት ፡ ወደ ፡ እላማላሊ ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ሰደቀበባ ፡ ደረሱ። በዚህ ፡ ሥፍራ ፡ ሳሉ ፡ ተናጭ ፡ የሚባሉት ፡ በባሊ ፡ ያሉት ፡ የገራድ ፡ ገብረ ፡ **ኢየሱስ** ፡ ሰዎችና ፡ የንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ ኣዳል ፡ ከድተው ፡ ሊገቡ ፡ ኣድመዋል ፡ የሚሉ ፡ ወሬ ፡ ተሰማ። ይኹን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ሁሉንም ፡ ከባሊ ፡ አስጠርተው ፡ ኣስመጡዋቸው ፡ መጥተውም ፡ እፊታቸው ፡ በቆሙ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ ተሸልመው ፡ ወዳገራቸው ፡ የሚመለሱ ፡ መስሏቸው ፡ ነበር።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ የተገኙትን ፡ ፈረሰኞቹንና ፡ የእግረኛ ፡ ወታደሮቹን ፡ ፲ ፡ በሬ ፡ እረዱና ፡ ቆዳውን ፡ ገፋችሁ ፡ ጠፍሩን ፡ በደንብ ፡ አውጡት ፡ ብለው ፡ አዘዙ። በወጣውም ፡ ጠፍር ፡ ቊጥራቸው ፡ ሺ፯፻፰ ፡ የሚሆነው ፡ ተናጭ ፡ የሚባሉትን ፡ እነዚህን ፡ አድመኞች ፡ ኣንገታቸውን ፡ ኣስረው ፡ ወደ ፡ ጐዣም ፡ ላኳቸው። ዓባዊ (ዓባይ) ሲደርሱ ፡ ጐዣም ፡ ነጋሽ ፡ ሠራዊቱንና ፡ ጨዋ ፡ አስከትሎ ፡ ተቀበለና ፡ በገምቦታ ፡ ምድር ፡ አሠማራቸው። ስማቸውንም ፡ ዳዊት ፡ ሐረሳ ፡ ብለው ፡ ሠየሟቸው። ሴቶቻቸውንም ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ከብቶቻቸውንም ፡ ወደዚሁ ፡ አገር ፡ አመጡላቸውና ፡ ተቀመጡ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የደዋሮ ፡ ጨዋ ፡ የባሊንና ፡ የዳሞትን ፡ ሀዳሪ (ተሠሪ ፡ ወታደር?) ወደ ፡ አዳል ፡ አገር ፡ እንዲዋጉ ፡ ላኩና ፡ እርሳቸው ፡ ወደ ፡ ደዋሮ ፡ ሄዱ። እነዚያም ፡ የተላኩት ፡ ወታደሮች ፡ የአዳልን ፡ አገር ፡ አጥፍተው ፡ ተመልሰው ፡ በደስታ ፡ ደዋሮ ፡ ላይ ፡ ከንጉሣቸው ፡ ጋር ፡ ተገናኙ። በደዋሮ ፡ የጥምቀትንና ፡ የእመቤታችንን ፡ የኣስተርእዮን ፡ በዓል ፡ አክብረው ፡ ወደ ፡ እላማሌ (ደጕ ፡ ደጕመኚ) ሄዱና ፡ የሁዳዴን ፡ ጾም ፡ ኣሳለፉ። ይችንም ፡ ሥፍራ ፡ ይወዷት ፡ ስለነበረ ፡ ሸንኮር ፤ ሎሚ ፤ ትርንጎ ፡ አስተከሉባት። በዚያም ፡ ሳሉ ፡ አንበሳ ፡ ዳዊት ፡ የሚባለውን ፡ ጐዣም ፡ ነጋሽ (የጐዣም ፡ ገዥ) ፡ ግብሬን ፡ ይዘህ ፡ ና ፡ ብለው ፡ አዘዙት። ጐዣም ፡ ነጋሽም ፡ የመንግሥቱን ፡ ግብር ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አምጥቶ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ተገናኘ። ንጉሡም ፡ በጣም ፡ አመሰገኑት።

ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ «እርሱም ፡ ልጅ ፡ ይሁንህ ፡ አንተም ፡ አባት ፡ ሁነው" ፡ ብለው ፡ እስክድርን ፡ ለጐዣም ፡ ነጋሽ ፡ ለመስጠት ፡ እዚያው ፡ እንደተቀመጠ ፡ ሕፃኑን ፡ በጐዣም ፡ ነጋን ፡ በጭኑ ፡ ላይ ፡ አስቀመጡለት። እንደዚሁም ፡ ንጉሡ ፡ ለሕፃኑ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ ፈረስና ፡ በቅሎ ፡ ሰጡት። ጐዣም ፡ ነጋሽም ፡ « ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ እኔው ፡ ከራሴ ፡ እሰጠዋለሁ ፡ ይልቅስ ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ የርሱ ፡ ከብቶች ፡ የሚቀመጡበት ፡ ምድር ፡ ይሰጠኝ ፡ ብሎ ፡ አመለከተ። ንጉሡም ፡ እሺ ፡ ብለውት ፡ ሳለ ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የንዳድ ፡ በሽታ ፡ ተነሣና ፡ አንበሳ ፡ ዳዊት ፡ ሞተ። በዚሁ ፡ ሰሞን ፡ ከዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ አሁንም ፡ በዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ የሆነው ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ ታመመ ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሯቸው።

ንጉሡም ፡ በጣም ፡ የሚወዱት ፡ ታማኛቸው ፡ ነበርና ፡ አምጡልኝና ፡ ሕመሙን ፡ ልየው ፡ ብለው ፡ አዘዙ። በመጣም ፡ ጊዜ ፡ ቅብዓ ፡ ቅዱስ ፡ አጠጡት። እርሱ ፡ ግን ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ኣልድንም ፡ ብሎ ፡ ተናገረ? ። በዚህ ፡ ሳሉ ፡ እግዝእት ፡ ሮምና (ባለቤታቸው)ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለዱና ፡ ስሙ ፡ ዕንቍ፭ኤል ፡ ተባለ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የክሌ ፡ የሚባለው ፡ ሊቀ ፡ መፃኒ (ሊቀ ፡ መጣኒ) እንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቆመና ፡ ለብቻ ፡ የምናገረው ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ አመለከተ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ድንኳናቸው ፡ ሄደው ፡ አስጠርተው ፡ የልቡን ፡ ጠየቁትና ፡ ተናገረ። ከዚያ ፡ በማግስቱ ፡ ዣን ፡ ማሰሮችን ፡ ሁሉንም ፡ አምጡልኝ ፡ ብለው ፡ አዘዙና ፡ ሲመጡ ፡ እያንዳንዳቸውን ፡ እያሳነቁ ፡ አስያዙዋቸው። በዚያን ፡ ጊዚ ፡ እነሱም ፡ የሚመለከተውም ፡ ሁሉ ፡ በፍርሐት ፡ ተንቀጠቀጠ። ንጉሡም ፡ የታሠሩትን ፡ መንግሥቴን ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ጠላችሁት ፡ በእኔስ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ አሰባችሁ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቋቸው ፡ እነርሱም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ኣላሰብንም ፡ ብለው ፡ ክደው ፡ እንደታሠሩ ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ፬ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ቆዩ። በኋላም ፡ ሊቀ ፡ መጣኒው ፡ ተጠራና ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ስለተናገርኸው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ መርቻ ፡ አለህ ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ ወደ ፡ መድኃኒት (መሐላ?) ልድረስ ፡ አለ ፡ እነርሱም ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ ተስማሙ። በኋላ ፡ ግን ፡ ንጉሥ ፡ በል ፡ አንተም ፡ እነርሱ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ለማሰባቸው ፡ በእመቤታችን ፡

በጽዮን ፡ ማል ፡ እናንተም ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አለማሰባችሁን ፡ ማሉ ፡ አሉዋቸውና ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ማሉ (ተፈቱ?) ። በዚህም ፡ ሳሉ ፡ አሁንም ፡ መሐሬ ፡ ክርስቶስ ፡ ፃስርጓ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ የሚባለውን ፡ ከዳሞት ፡ አሥሮ ፡ ኣመጣውና ፡ ባገሩ ፡ በግዛቱ ፡ የማይገባውን ፡ ደረጃ ፡ ኣልፎ ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ መሥራቱ.... ስለታወቀ ፡ ተገረፈና ፡ በግራ ፡ በጽርዋጀት ፡ እጅ ፡ ታሠረ። ጕሽአሮ ፡ የሚባለውም ፡ ተገርፎ ፡ ታሠረና ፡ በግዞት ፡ ወደ ፡ ሐይቅ (ወሎ)ተላካ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የአዳሉ ፡ ጦርነት ፡ አንድ ፡ ውሳኔ ፡ ሳያገኝ ፡ በውስጥ ፡ በያውራጃው ፡ ፩ ፡ ኣንድ ፡ ኣድማ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ እየተደረገ ፡ ጥፋተኛም ፡ እየበረከተ ፡ በጠቅላላው ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ መንግሥት ፡ ሁከት ፡ እንዳገኘው ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ያመለክታል። አድመኛውም ፡ በበዛ ፡ መጠን ፡ ለንጉሡ ፡ ነጋሪውም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ስለሆነ ፡ ጥፋተኞቹም ፡ መቀጣታቸው ፡ ኣይቀርም። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ የመሳሰለው ፡ የውስጥ ፡ ልዩነት ፡ ሲኖር ፡ ለጠላቶቻቸው ፡ ለአዳሎች ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው።

በመዠመሪያ ፡ የባሌው ፡ የገራድ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ ከድተው ፡ ሊገቡ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ ወሬ ፡ ቢሰሙ ፡ ለሹመትና ፡ ለሽልማት ፡ አስመስለው ፡ በለዘብታ ፡ ጠርተው ፡ በጠፍር ፡ ኣንገታቸውን ፡ አቆራኝተው ፡ ለጐጃሙ ፡ መስፍን (ለጐጃም ፡ ነጋሽ ፡ አንበሳ ፡ ዳዊት) መላካቸውን ፡ ተመልክተናል።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሊቀ ፡ መጻኒ ፡ የክሌ ፡ በቆይታ ፡ የምናገረው ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ለንጉሡ ፡ ዣን ፡ ማሠሮች ፡ መንግሥትዎን ፡ ጠልተው ፡ በርስዎ ፡ ላይ ፡ ኣድማ ፡ አድርገዋል ፡ ብሎ ፡ ተናግሮኖሮ ፡ ተጠርተው ፡ ታሥረው ፡ ቢጠየቁ ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ማላታቸውን ፡ ንጉሡም ፡ ነጋሪያቸውን (አሳባቂውን)ጠርተው ፡ ማስረጃ ፡ እንዲያቀርብ ፡ መጠየቃቸውን ፡ ያስረዳል። ለተጠየቀው ፡ ማስረጃ ፡ በማቅረብ ፡ ፈንታ ፡ “ወይቤ ፡ እበጽሕ ፡ ኀበ ፡ መድኃኒት ፡ ወውእቶሙኒ ፡ ይቤሉ ፡ ከማሁ” ብለው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ወደ ፡ መድኀኒት ፡ ለመድረስ ፡ መስማማታቸውን ፡ ይገልጻል።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ንጉሡን ፡ አምተዋል ፡ ተብለው ፡ የተከሰሱት ፡ ሰዎች ፡ የእግራቸው ፡ ሥር ፡ የተቆረጠበትን ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መድኀኒት ፡ እንዳለው ፡ ተመልክተናል። በዚህ ፡ በአሁኑ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መድኃኒት ፡ እንሒድ ፡ ብለው ፡ ሲስማሙ ፡ ጥፋተኛውን ፡ ሊለይ ፡ ይችላል ፡ የሚባል ፡ ባሕታዊ ፡ ጠንቋይ ፡ ወይም ፡ እንደሌባ ፡ ሻይ ፡ ዓይነት ፡ ይመስላል። ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሡ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ እፊታቸው ፡ ምለው ፡ በነጻ ፡ እንዲለያዩ ፡ አድርገዋቸዋል።

# ምዕራፍ ፡ ፵፱።

## የመሐሪ ፡ ክርስቶስና ፡ የገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ በአዳሎች ፡ መሸነፍ ፡ - ፡ የአባ ፡ ሚካኤል ፡ ሕልምና ፡ ያመጣባቸው ፡ እሥራት።

በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የደዋሮንና ፡ የባሊን ፡ ጨዋ ፡ የዳሞትን ፡ ሀዳሪ ፡ ወታደሮች ፡ የላኰ ፡ ጊዜ ፡ የተላኰትም ፡ አሸንፈን ፡ ተመለስን ፡ ብለው ፡ እነሱም ፡ ንጉሡም ፡ ደስታ ፡ ኣደረጉ ፡ ብሎ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የሚገልጸው ፡ ከኣዳሎቹ ፡ ከአንድ ፡ ክፍል ፡ ጋር ፡ ተጋጥመው ፡ አሸንፈው ፡ የተመለሱትን ፡ እንጂ ፡ መላውን ፡ አዳልን ፡ አሸንፈው ፡ ኣይደለም። ስለዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ደግሞ ፡ ይኸው ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በዚሁ ፡ ሰሞን ፡ ከኣዳሎቹ ፡ ጋር ፡ ጦር ፡ ልከው ፡ ማዋጋታቸውን ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይተርካል። « በዚች ፡ ምድረ ፡ ኣበሲ (አበሊ?) ንጉሡ ፡ የነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ብሕት ፡ ወደድና ፡ ባሊ ፡ ገራድ'' የሆነውን ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስን ፡ ከባሊና ፡ ከደዋሮ ፡ ጨዋ ፡ ጋር ፡ ሌላም ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ ላኰት። እርሱም ፡ ወደሀገራቸው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የአዳሉቹ ፡ ሹማምንት ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አገር ፡ ወረራ ፡ ሊያደርጉ ፡ ባንድ ፡ ተሰብስበው ፡ አገኛቸው። ጦርነቱንም ፡ ዠምሮ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ በእጁ ፡ ጣላቸው (አሸነፋቸው)የሚበዙትንም ፡ ገደለና ፡ የቀሩትን ፡ ማረከ። ከተማረኰት ፡ ውስጥ ፡ ጸሐፊው ፡ የሚያውቃቸው ፡ ጐሳች ፡ ጌታሲድ ፡ አህመድ፣ እሮር ፡ ገራድ ፤

ግዳይ ፡ ገራድ፣ ኰሽም ፡ ግራድ ፤ ሐርጋይ ፡ ገራድ ፤ ግዳያ ፡ ገራድ ፤ ፈራሽ ፡ ሹም ፡ ይባላሉ። ሌሎችም ፡ ስማቸው ፡ ያልታወቀ ፡ ብዙ ፡ አሉ።

ንጉሡም ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ድል ፡ አልሰሙም ፡ ነበርና ፡ ስለወታደሮቻቸው ፡ ሁኔታ ፡ እየተከዙ ፡ በእሑድ ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡ ድረስ ፡ ሥርዓተ ፡ አማን (ግብር ፡ ሳያደርጉ ፡ ዋሉ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሕልፍ (በይለፍ) የተላከ ፡ ፩ ፡ ደብዳቤ ፡ መጣላቸው። ንጉሡም ፡ በደብዳቤው ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈውን ፡ በተመለከቱ ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮቻቸው ፡ አይለው ፡ ማሸነፋቸውን ፡ ስለተረዱት ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ አደረጉ። ወዲያው ፡ ሥርዓተ ፡ አማኑ (ግብሩ)በደስታ ፡ እንዲደረግ ፡ ኣዘዙ። ፪ኛ ፡ ደግሞ ፡ በ፱ ፡ ሰዓት ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ሌላ ፡ ደብዳቤ ፡ መጣ ፡ በጸሎትህ ፡ ድልን ፡ አግኝተናልና ፡ ንጉሣችን ፡ ሆይ ፡ ደስ ፡ ይበልህ። እኛም ፡ ገንዘባችንም ፡ ፈረሶቻችንም ፡ ደህና ፡ ሁነን ፡ ባሊ ፡ ገብተናል።

ስለዚህ ፡ ንጉሥ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ለ**እግዚአብሔር** ፡ ምሥጋና ፡ አቀረቡ። ወዲያውም ፡ ይኸንኑ ፡ የምሥራች ፡ ለዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ኣምኃ ፡ ጽዮን (እንደሌላው ፡ ጽሑፍ ፡ ምኣኃ ፡ **ኢየሱስ**) ቢነግሩት ፡ እርሱም ፡ ደስ ፡ አለውና ፡ ምሥጋና ፡ ለ**እግዚአብሔር** ፡ አቀረበ ፡ "ይኸውም ፡ የደስታ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ኣዋጅ ፡ ሆኖ ፡ በማግስቱ ፡ ለሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ከተነገረ ፡ በኋላ ፡ ታላቅ ፡ ዘፈንና ፡ ማኅሌት ፡ ተደረገ። »

ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ በዘመናቸው ፡ ከአዳል ፡ ጋር ፡ ያደረጉት ፡ የጦርነት ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ይፈጸማል። በዚህ ፡ የጦርነት ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ የቢቶደድነት (ብሕት ፡ ወደድነት) ና ፡ የገራድነት ፡ ማዕርግ ፡ ደርቦ ፡ ሊይዝ ፡ መቻሉን። የጦር ፡ አለቆቹ ፡ የድል ፡ አድራጊነትም ፡ ሌላም ፡ አስቸኳይ ፡ ጉዳይ ፡ ሲኖራቸው ፡ በደብዳቤ ፡ በይለፍ ፡ ማስታወቃቸውን ፡ እንረዳለን። በይለፍ ፡ ስለሚባለው ፡ አነጋገር ፡ የማያውቅ ፡ ወጣት ፡ አንባቢ ፡ ምናልባት ፡ ቢኖር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንዳለው ፡ እናስረዳለን።

እንደዛሬ ፡ የስልክና ፡ የመኪና ፡ መገናኛ ፡ ባልነበረበት ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ አስቸኳይ ፡ ጉዳይ ፡ ሲገጥም ፡ ከንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሹሙ ፡ ወይም ፡ ከሹሙ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ በቃል ፡ ወይም ፡ በጽሑፍ ፡ መልእክት ፡ ሲላክ ፡ ካገሩ ፡ ርቀት ፡ የተነሣ ፡ ፭ዱ ፡ ፈጣን ፡ ፈረሰኛ ፡ ተመርጦ ፡ በግልቢያ ፡ ላንዱ ፡ አገር ፡ ሹም ፡ ያቀበላል ፡ የዚያ ፡ አገር ፡ ሹም ፡ በቶሎ ፡ ተቀብሎ ፡ ባዲስ ፡ ጉልበት ፡ ለሌላወ ፡ ፈረሰኛ ፡ ይሰጠውና ፡ ያ ፡ ደግሞ ፡ በግልቢያ ፡ እተላከበት ፡ ሥፍራ ፡ ያደርሳል። ገና ፡ ሩቅም ፡ እንደሆነ ፡ ለሌላው ፡ አገር ፡ አቀብሎ ፡ ያኛው ፡ እንዲያደርስ ፡ ያደርጋል ፡ ይኸን ፡ የመሰለው ፡ የመቀባበል ፡ አላላክ ፡ የፈረስም ፡ ሲሆን ፡ የእግረኛ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ «የይለፍ ፡ መልእክት ፡ ይባላል ፡ እላይ ፡ እንዳልነው ፡ እንደዛሬ ፡ ባቡር ፡ መኪና ፡ አውሮፕላን ፡ ስልክ ፡ ከመገኘቱ ፡ በፊት ፡ በሌላውም ፡ በአውሮፓም ፡ በምሥራቅም ፡ ያሉ ፡ ኣገሮች ፡ መልእክታቸውን ፡ የሚያከናውኑት ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ነበር።

፪ኛ ፡ ደግሞ ፡ የድሉን ፡ የምሥራች ፡ ቃል ፡ ንጉሡ ፡ ከመላከተኛው ፡ እንደሰሙ ፡ ለዐቃቤ ፡ ሰዓት ፡ አምኃ ፡ ጽዮን ፡ ነገሩት ፡ ሲል ፡ የዐቃቤ ፡ ሰዓትነት ፡ ደረጃ ፡ የያዘው ፡ ከይኩኖ ፡ አምላክና ፡ ከአባ ፡ ኢየሱስ ፡ ሞዐ ፡ ዠምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሁሉ ፡ ክብር ፡ የነበረው ፡ የቅርብ ፡ የሥራ ፡ ረዳትና ፡ ባለሟል ፡ ስው ፡ መሆኑን ፡ እንረዳለን። ስለሹማምንት ፡ በሰጠነው ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ በማዕርግ ፡ ከብሕት ፡ ወደዶቹ ፡ እንደሚበልጥ ፡ ተገንዝበናል። ስለዚህ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ደስታንም ፡ ክብርንም ፡ ጨዋታንም ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ የሚካፈል ፡ ታላቅ ፡ ባለሟል ፡ መሆኑን ፡ ያለፈውም ፡ ወደፊትም ፡ የምናገኘው ፡ ጽሑፍ ፡ ሁሉ ፡ ባጭሩ ፡ ያስረዳል።

በተረፈ ፡ ስለአዳሉ ፡ ጦርነት ፡ ሁኔታና ፡ ፍጻሜ ፡ የተመለከትን ፡ እንደሆነ ፡ አሁንም ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ምንም ፡ ድልና ፡ ደስታ ፡ ተደረገ ፡ ቢል ፡ አዳሎቹ ፡ ጨርሰው ፡ አልተሸነፉም ፡ መሪያቸው ፡ ኡትማን ፡ ቤይ ፡ ሶለይማንም ፡ ኣልሞተም ፡ ወይም ፡ አልተማረከም። እንዲያውም ፡ ይኸው ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ የዚህኑ ፡ የኣዳል ፡ ጦርነት ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ዓይነት ፡ መፈጸሙን ፡ ከአሳየ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ግድም ፡ ጉዳዩን ፡ ኣንሥቶ

፡ ሲተርክ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ወጅ ፡ የነበሩ ፡ ጊዜ ፡ በመዠመሪያ ፡ መሐሪ ፡ ክርስቶስን ፡ ቀጥሎ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስን ፡ እንዲዋጉ ፡ ወደ ፡ ኣዳል ፡ ቢልኳ ፡ በውስጣቸው ፡ ስምምነትና ፡ ፍቅር ፡ ስለአልነበረ ፡ ሁለቱም ፡ ተሸነፉና ፡ ተመለሱ። የቀረውም ፡ የክርስቲያን ፡ ጦር ፡ አለቀ ፡ ሲል ፡ ሹማምንቱንም ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ አድርጎ ፡ ንጉሡም ፡ ይኸን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ መሐሪ ፡ ክርስቶስና ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስን ፡ ይወዷቸው ፡ ነበርና ፡ ስለሞታቸው ፡ ኣዝነው ፡ ይልቁንም ፡ ከሁለቱ ፡ ይበልጥ ፡ መሐሪ ፡ ክርስቶስ ፡ ታማኛቸውና ፡ ኣገልጋያቸው ፡ ስለነበረ ፡ በጣም ፡ መጸጸታቸውን ፡ ይገልጻል። ስለዚህም ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ልከው ፡ ለአቡነ ፡ መርሐ (ይምርሐነ) ክርስቶስ ፡ ፳፻ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ለምጽዋት ፡ ላኩ» ፡ ሲል ፡ ከአለፈው ፡ አተራረኳ ፡ ለይቶ ፡ ይገልጻል። ይኸንንም ፡ ከተረከ ፡ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ከዚህ ፡ ከወጅ ፡ ወደ ፡ አራሪ ፡ ከኣራሪ ፡ ወደ ፡ አባሲ ፤ ከኣባሲ ፡ ወደ ፡ ዌራ ፡ ገበያ ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሳይሄዱ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ በተወለዱ ፡ በ፴ ፡ ዓመታቸው ፡ መሞታቸውን ፡ ይገልጽልናል።

ከዓፄ ፡ እስክንድርና ፡ ካፄ ፡ ናዖድ ፡ አጫጭር ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጋር ፡ ተደባልቆ ፡ የተጻፈ ፡ ሌላ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ደግሞ ፡ ባፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዘመን ፡ የሆነውን ፡ የዚህን ፡ የአዳልን ፡ ጦርነት ፡ ሲተርክ ፡ አሳቡ ፡ ከዚሁ ፡ ከአላፈው ፡ ያልተለየ ፡ ቢሆንም ፡ በመጠኑ ፡ ቲንሽ ፡ ዝርዝር ፡ ስለሚሰጥ ፡ ጠቃሚነት ፡ አለው። ቃሉም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው።

“በኅዳር ፡ ወር ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሰበሰብ ፡ ኣዘዙ። እነሱም ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ መጡ። ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ አስሯቸው ፡ የነበሩት ፡ ገራዶችም (የእስላም ፡ ሹማምንት፡) ለኣዳሉ ፡ ጦርነት ፡ እኛ ፡ በምናውቀው ፡ መንገድ ፡ እንመራችኋለን ፡ ስላሉ ፡ ተፈትተው ፡ መጡ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ከሰቀላቸው (ከእልፍኛቸው) ወጡና ፡ ከከተማው ፡ ርቆ ፡ ወደሚገኘው ፡ ትልቅ ፡ ኣኅበር ፡ ገቡ። የዚህም ፡ ያኅበር ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ ያስደንቃል ፡ ዓምዶቹም (ምሰሶዎቹም) ወፍራሞች ፡ ርዝመታቸውም ፡ እስከ ፡ ፳ ፡ አንድ ፡ ይሆናል። በላዩ ፡ ላይ ፡ ኮከቢ (ኮከብማ ፡ ልብስ?) ኣልብሰውት ፡ ነበር። በውስጡ ፡ ከፍ

፡ ያለ ፡ ዙፋን ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በነበረው ፡ ላይ ፡ ንጉሡ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የግራውን ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ መሐሪ ፡ ክርስቶስንና ፡ የቀኙን ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስን ፡ ገራዶቹንና ፡ ሠራዊቱን ፡ ሁሉ ፡ ንጉሡ ፡ አስጠርተው ፡ ግማሹ ፡ ሠራዊት ፡ ለመሐሪ ፡ ክርስቶስ ፡ ግማሹ ፡ ለገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ተከፍሎ ፡ ተሰጣቸው። እስላሞቹም ፡ እንደዚሁ ፡ እሁለት ፡ ተከፍለው ፡ በሚያውቁት ፡ እንዲመሩ ፡ ተደረጉ። ሁሉንም ፡ በየበኩላቸው ፡ ወደ ፡ ኣዳል ፡ ሄደው ፡ እንዲዋጉ ፡ ኣዘዟቸውና ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ መኖሪያቸው ፡ ተመለሱ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የደቅ ፡ ኢታ ፡ የደብረ ፡ መለኅ ፡ መምሕር ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ “በሕልሜ ፡ መሐሪ ፡ ክርስቶስንና ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስን ፡ ጥቍር ፡ ደመና ፡ ሲውጣቸው ፡ አይቻለሁና ፡ ወደ ፡ ጦርነቱ ፡ እንዳይሄዱ ፡ እዘዝ ፡ ጌታዬ ፡ ብለው ፡ አመለከቱ። መነኵሴው ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ በመናገራቸው ፡ ተግዘው ፡ ወደ ፡ ዟይ ፡ ተላኩ። ወደ ፡ አዳል ፡ የተላኩትንም ፡ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ እስላሞቹ ፡ አሸንፈው ፡ ጨረሷቸው። የዚህን ፡ ወሬ ፡ የመሐሪ ፡ ክርስቶስንና ፡ የገብረ ፡ ኢየሱስን ፡ መሞት ፡ ለንጉሡ ፡ በነገሩዋቸው ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ አዘኑ። በዚያው ፡ ሳሉ ፡ የጥምቀትንና ፡ የፋሲካን ፡ በዓል ፡ አከበሩ። ሕልሙም ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ ስለተረዱት ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ የተባሉትን ፡ መነኵሴ ፡ ከተጋዙበት ፡ ቦታ ፡ መለሱዋቸው። ንጉሡም ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ገበርጌ ፡ ሄዱ። በዚያም ፡ ሳሉ ፡ ናዖድ ፡ ተብሎ ፡ የተሠየመው ፡ ቀለዮጳ ፡ ተወለደ ፡ ከዚያ ፡ አልፈው ፡ ምድረ ፡ ጠንጣር ፡ ሄደው ፡ ከረሙ። በዚህ ፡ ሳሉ ፡ ባሕር ፡ ነጋሽን ፡ የገደለውን ፡ የገራድ ፡ ኣሊቆታን ፡ ጭንቅላት ፡ ዣን ፡ ጸገና (ወታደሮቹ) አመጡላቸው። ክረምቱ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ልጆቹ ፡ ወደ ፡ ገንዝ ፡ ሄደው ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፡ ሕግና ፡ ልማድ ፡ እንዲያድጉ ፡ ስደዳቸው ፡ ብለው ፡ ገንዝ ፡ ገራድ ፡ ማቴዎስን ፡ ኣዘዙና ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ኣራራ ፡ ሄደው ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ቆዩ። በዚህም ፡ ሳሉ ፡ ከነገሡ ፡ ፺ ፡ ዓመት ፡ ሆነ ፡ የጥምቀትንም ፡ በዓል ፡ በዚሁ ፡ አከበሩ። ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ እንድኖር ፡ ዝገር ፡ ስለሄድሁ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቀጥሎ ፡ የሆነውን ፡ አላውቅም (የጸሐፊው ፡ ቃል ፡ ነው) ። »

በዚህ ፡ ውስጥ ፡ የምንመለከተው ፡ አዳሎች ፡ አይለው ፡ የዓፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያምን ፡ ጦር ፡ ማሸነፋቸውን ፡ እንደዚሁም ፡ ዜና ፡ መዋዕሉን ፡ ያዘጋጀው ፡ ጸሐፊ ፡ ልጆቹን ፡ ጠብቅ ፡ ወይም ፡ አስተምር ፡ ተብሎ ፡ ወደ ፡ ገንዝ ፡ እስኪሄድ ፡ ድረስ ፡ ለዚህ ፡ ለሚጽፈው ፡ ታሪክ ፡ የዓይን ፡ ምስክር ፡ መሆኑን ፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዓፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ ከነገሡ ፡ ፯ ፡ ዓመታቸው ፡ ነበር ፡ ሲል ፡ የነገሡት ፡ በሺ፬፻፷ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ያዳል ፡ ጦርነት ፡ የተደረገው ፡ በሺ፬፻፷፯ ፡ ዓ.ም ፡ መሆኑ ፡ ነው። በተረፈ ፡ እዚህ ፡ ቦታ ፡ ኣረፉ ፡ ከዚያ ፡ ኣልፈው ፡ እዚህ ፡ ደረሱ ፡ እያለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስም ፡ የሚሰጣቸውን ፡ አገሮች ፡ ዛሬ ፡ በትክክል ፡ ለመለየት ፡ ችግር ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ በይፋትና ፡ በሸዋ ፡ አካባቢ ፡ መሆናቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው። ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደግሞ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ የተወለዱበትን ፡ ጊዜ ፡ ለማወቅና ፡ እድሜያቸውንም ፡ ለመወሰን ፡ ይጠቅማል። እንደዚሁም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ እንኳን ፡ የማይታወቀውን ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ በልጅነታቸው ፡ ቀለዮጳ ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ እንደነበራቸው ፡ ይገልጻል።

፩ ፡ ክረምት ፡ በምድረ ፡ ጣንጣር ፡ አሳልፈው ፡ በምድረ ፡ አራሪ ፡ ጥምቀትን ፡ ሲኣከብሩ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ከነገሡ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ነበር ፡ ካለ ፡ ናዖድ ፡ የተወለዱት ፡ በሺ፬፻፷፯ ፡ ዓ.ም ፡ መሆኑ ፡ ነው። በዚህ ፡ ላይ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ፬ ፡ ዓመት ፡ እስክንድር ፡ የነገሡበት ፡ ፲፯ ፡ ዓመት ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ የነገሡበት ፡ ፯ ፡ ወር ፡ ሲደመር ፡ ናዖድ ፡ የነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜኣቸው ፡ ፳፪ ፡ ዓመት ፡ ግድም ፡ እንደነበረ ፡ ያስረዳል። ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ገዝተው ፡ ሲሞቱ ፡ ደግሞ ፡ ጠቅላላ ፡ ዕድሜአቸው ፡ ፴፫ ፡ ዓመት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው።

እንደዚህም ፡ የሚሆነው ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ በጽሐ ፡ ገበርጌ። ወበህየ ፡ ተወልደ ፡ ቀለዮጳ ፡ ወበህየ ፡ ተሰምየ ፡ ናዖድ ፡ የሚለው ፡ የግዕዝኛ ፡ አነጋገር ፡ በተወለደበት ፡ አገር ፡ ለማለት ፡ ሳይሆን ፡ በዚያ ፡ ተወለደ ፡ ማለቱ ፡ እንደሆነ ፡ ነው። ይህ ፡ ትርጉም ፡ በእደማርያም ፡ ናዖድ ፡ ወደተወለደበት ፡ አገር ፡ ደረሰ ፡ የሚያሰኝ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ዕድሜ ፡ ለማወቅ ፡ ይቸግራል። ነገር ፡ ግን ፡ ባለፈው ፡ የእስክንድርን ፡ የዕንቈ ፡ ፳ኤልን

፡ ሲናገር ፡ የናዖድን ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መናገሩ ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ተወለደ ፡ ማለቱ ፡ አዲስ ፡ መወለዳቸውን ፡ ማሳየቱ ፡ ነውና ፡ ሲነግሡ ፡ ፳፪ ፡ ዓመት ፡ ሲሞቱ ፡ ፴፫ ፡ ዓመታቸው ፡ ነው ፡ የተባለውን ፡ ኣሳብ ፡ መልሰን ፡ እናጸድቃለን።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ባዔ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ባዔ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ የተዳከሙት ፡ አባሎች ፡ አሁን ፡ በዓፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ ጊዜ ፡ መልሰው ፡ ማየላቸውን ፡ የቀኙንና ፡ የግራውን ፡ ብሕት ፡ ወደዶች ፡ ከነጦራቸው ፡ ማሸነፋቸውን ፡ እንረዳለን። በሁለቱ ፡ ከፍተኞች ፡ የጦር ፡ አላቆች ፡ መካከል ፡ በግዛት ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በሹመት ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጠብ ፡ በመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ በኣዳሎቹ ፡ መሸነፋቸውን ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ገልጿል። ምናልባት ፡ ሁለቱ ፡ የሚናናቁ ፡ ደረጃቸው ፡ የተመዛዘነ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ በጦርነቱ ፡ ሰዓት ፡ ምናልባት ፡ ኣንዱ ፡ ሌላውን ፡ እያዘዘ ፡ እንዲያዘምት ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶት ፡ በዚሁ ፡ ፩ኛው ፡ ተቀይሞ ፡ ይሆናል ፡ ወይም ፡ ሁለቱም ፡ በየግንባራቸው ፡ እንዲያዘምቱ ፡ ታዘው ፡ አንደኛው ፡ ሌላውን ፡ ካጋለጠ ፡ በኋላ ፡ ብቻውን ፡ ሲዋጋ ፡ ሞቶ ፡ ይሆናል። ቢሆንም ፡ የሁለቱን ፡ አለመስማማት ፡ ምናልባት ፡ ንጉሡ ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በወሬ ፡ ነጋሪ ፡ ሳይረዱት ፡ አይቀሩምና ፡ የማይስማሙትን ፡ ባንድነት ፡ መላካቸው ፡ የማይገባ ፡ ነው።

በዚህ ፡ መካከል ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ የሚባሉ ፡ የደብረ ፡ መላኅ ፡ መነኩሴ ፡ በሕልሜ ፡ መሐሪ ፡ ክርስቶስንና ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስን ፡ ጥቍር ፡ ደመና ፡ ሲውጣቸው ፡ ዓይቻለሁና ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ አይሂዱ ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ በማመልከታቸው ፡ መታሠራቸውን ፡ ስናነብ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የበዕደ ፡ ማርያምን ፡ የሕልም ፡ ንቀት ፡ ብንረዳ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ዕውቀት ፡ መነኮሳትና ፡ ባሕታውያን ፡ የነበራቸውን ፡ ሥልጣን ፡ እንመለከታለን።

የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ዕውቀት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የቆየ ፡ ነው። ከክርስትና ፡ በፊት ፡ በግብፅ ፡ የአሞን ፡ የፐታህ ፡ በአሶርና ፡ በባቢሎን ፡ የነብዔል ፡ በግሪክ ፡ በሮማ ፡ የነዡፒተር ፡ የነኣጵሎን ፡ ካህናት ፡ ተጠይቀው ፡ ይበጃል ፡ አይበጅም

፡ ሳይሉ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ አይኬድም ፡ ነበር። በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ በ፳ኤል ፡ ዘንድ ፡ ነቢያትንና ፡ ካህናትን ፡ ሳይጠይቍ ፡ መሳፍንቱና ፡ ነገሥታቱ ፡ ከፍልስጥኤማውያንና ፡ ከሞዓባውያን ፡ ጋር ፡ አይዋጉም ፡ ነበር። እንደዚሁም ፡ የኛ ፡ ነገሥታት ፡ ከክርስትና ፡ ወዲህ ፡ አንድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጕዳይ ፡ ወይም ፡ ጦርነት ፡ ሲመጣባቸው ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ምሕላ ፡ ያዙልን ፡ ከማለት ፡ ጋር ፡ ጦርነቱ ፡ የሚቀናቸው ፡ መሆኑንም ፡ አስቀድመው ፡ ከሚያምኑት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ የደብረ ፡ ዳሞ ፡ ወይም ፡ ካንዱ ፡ ገዳም ፡ መነኵሴና ፡ የበቃ ፡ ባሕታዊ ፡ መጠየቅ ፡ ልማዳቸው ፡ ነበር።

ነገር ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ላይ ፡ የምንመለከተው ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ የአባሉን ፡ ጦርነት ፡ ለማድረግ ፡ ከልብ ፡ በችኮላ ፡ ፈልገውት ፡ ኖሮ ፡ መነኩሴው ፡ ሳይጠየቍ ፡ ሕላማቸውን ፡ በመተማመን ፡ ሁለቱ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ እንዳይላኵ ፡ ስለተቃወሙ ፡ ጦርነቱን ፡ ከልብ ፡ የፈለጉት ፡ ንጉሥ ፡ አሥረዋቸው ፡ ከድሉ ፡ በኋላ ፡ የመነኵሴው ፡ አሳብ ፡ ሲፈጸም ፡ ከእሥር ፡ ወጡ ፡ ማለት ፡ ነው። ስለዚህ ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ የመንግሥት ፡ መሪዎች ፡ ጦርነት ፡ ለማወጅ ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ባለበት ፡ አገር ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አስቀድሞ ፡ እንደሚጠየቅ፥ ፡ የምክር ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ በደከመበትና ፡ መሪው ፡ እንደልቡ ፡ የፈቀደውን ፡ በሚሠራበት ፡ አገር ፡ የምክርን ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ መጠየቅ ፡ እንደማያስፈልገው ፡ የተቃወመ ፡ አማካሪ ፡ ሲኖርም ፡ የአማካሪው ፡ አሳብ ፡ በአግባቡ ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ አሥሮ ፡ መሪው ፡ የልቡን ፡ እንደሚሠራ ፡ እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ሲያሰኛቸው ፡ መነኵሴና ፡ ባሕታዊ ፡ ወይም ፡ አማካሪ ፡ ይጠይቃሉ ፡ ሳያሰኛቸው ፡ የተቃወመውን ፡ አሥረው ፡ አሳባቸውን ፡ ወደፊት ፡ ይገፋሉ። የገፉበት ፡ አሳብ ፡ ሕዝብንና ፡ ወታደርን ፡ ወደሞት ፡ ገደል ፡ የሚጨምርም ፡ ቢሆን ፡ ጠያቂ ፡ የለባቸውም። ጠያቂም ፡ ቢኖር ፡ ተጠያቂው ፡ በጠያቂው ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ እሥራት ፡ ለማምጣት ፡ የዘመኑ ፡ ሥልጣን ፡ ይፈቅድለታል።

ነገር ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ የመሰለው ፡ አመራርና ፡ አስተዳደር ፡ አገርን ፡ ሕዝብን ፡ ጐጅነቱ ፡ ስለታወቀ ፡ ከዚያን ፡ ዘመን ፡ ወዲህ ፡ በአውሮፓና ፡ በሠለጠኑት ፡ አገሮች ፡ እያደር ፡ የመሪዎች ፡ ሥልጣን ፡ እየተወሰነ ፡ አብዛኛው ፡ ያገር ፡ የጦርነትና ፡ የሰላም ፡ ጕዳይ ፡ ማናቸውም ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ በመማክርት ፡

አሳብና ፡ በክርክር ፡ እየተጣራ ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ እየተወሰነ ፡ ይሠራበት ፡ ዝመር።

# ምዕራፍ ፡ ፶።

## በ፪ኛ ፡ ክፍል ፡ ተደግሞ ፡ የተጻፈው ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የዜና ፡ መዋዕል ፡ ጭማሪ

ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ እንደ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ከመዠመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ባለፈው ፡ ያነበበውን ፡ ጨርሶ ፡ ከጻፈ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ አድርጎ ፡ ከዚያው ፡ ከጨረሰበት ፡ ቀጥሎ ፡ ያንኑ ፡ በድጋሚ ፡ ይጽፈዋል። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በጨረሰውና ፡ እንደገና ፡ ዝምሮ ፡ በሚጽፈው ፡ መካከል ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ልዩነት ፡ አለ። እመዠመሪያው ፡ ላይ ፡ የጻፈውን ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ እዚህ ፡ እሁለተኛው ፡ ላይ ፡ ትቶታል ፡ እመዠመሪያው ፡ ላይ ፡ የተወውን ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ እዚህ ፡ እሁለተኛው ፡ ላይ ፡ ጽፎታል። ስለዚህ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ከተጻፈው ፡ ከመዠመሪያው ፡ ላይ ፡ የቀረውንና ፡ በዚህ ፡ በ፪ተኛው ፡ ላይ ፡ የጻፈው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ይገኛል።

### ሀ ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ።

"በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ኣምኃ ፡ ጽዮን ፡ በትልቁ ፡ መንበር ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ ቃል ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፡ ንጉሥ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ በኔ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይሆን ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ፈቃድ ፡ አነግሥላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ጌታዬ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ነገረኝ። ይኸንንም ፡ ምስክርነት ፡ በመላእክትና ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ እሰጣለሁ። እኔም ፡ ሐሰት ፡ ብናገር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምስክሬ ፡ ነው። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ዝምሮ ፡ ቀይም ፡ ነጭም ፡ የፈለጋችሁትን ፡ ልበሱ ፡ እሥረኛም ፡ በየቤትህ ፡ ግባ ፡ የሚል ፡ አዋጅ ፡ ተነገረ። ይህ ፡ ቃል ፡

ከመዠመሪያው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ያልነበረ ፡ አዲስ ፡ ያነጋገሥ ፡ ሥርዓት ፡ እንደዚሁም ፡ የፈቀዳችሁትን ፡ ልበሱ ፡ ሲል ፡ ቀድሞ ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ ይኸ ፡ የንጉሥ ፡ የጳጳስ ፡ ይኸ ፡ የመሳፍንት ፡ ወይም ፡ የመኳንንት ፡ ልብስ ፡ ተብሎ ፡ ለሌላው ፡ ሕዝብ ፡ የተከለከለና ፡ ኣሁን ፡ ግን ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የፈቀደውን ፡ ቀይም ፡ ነጭም ፡ እንዲለብስ ፡ የተፈቀደ ፡ ይመስላል።

## ለ -- ፡ ስለአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ሥራና ፡ ስለ ፡ ነገሥታት ፡ ዐፅም።

አማራ ፡ ሳይንት ፡ ሔደው ፡ አትሮንሰ ፡ ማርያምን ፡ ኣሠርተው ፡ በዓሏን ፡ ኣከብረው ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ ለካህናቱ ፡ መተዳደሪያ ፡ ከዓባይ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዣማ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ምድር ፡ ሰጡ። ....ከዚያ ፡ የንጉሥ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ዐፅም ፡ ከመርሐ ፡ ቤቴ (መራቤቴ) ፤ የግርማ ፡ አስፈሬን (ንዋየ ፡ ማርያምን) ዐፅም ፡ ከአሥሮ ፡ የይኵኖ ፡ አምላክን ፡ ዐፅም ፡ ከይኵኖ ፡ የሌሎችንም ፡ ነገሥታትና ፡ ፲፰ ፡ የሚሆኑ ፡ ጳጳሳት ፡ ዐፅም ፡ እያስመጡ ፡ በክብር ፡ እዚሁ ፡ አትሮንሰ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስቀመጧቸው። በልጅነታቸው ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ያስተማራቸውን ፡ የመምህራቸውንና ፡ የወዳጃቸውን ፡ የተክለ ፡ ኢየሱስንም ፡ ዐፅም ፡ ከደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ አስመጥተው ፡ ከፍቅሩ ፡ የተነሣ ፡ በድኑን ፡ የሚያምር ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ አልብሰው ፡ ወደዚያው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲቀበር ፡ ኣደረጉ። ለናቱም ፡ ፴ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ሰጧት። ለዘመዶቹም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሽልማት ፡ ሰጧቸው። በዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ጊዜ ፡ ያመፁትን ፡ አምባ ፡ ነሐድን ፤ ፀጋይን ፤ ከንቲባን ፡ ከጸለምት ፡ ተልኮ ፡ ሔዶ ፡ ያመጣቸውን ፡ ማርቆስንም ፡ በጣም ፡ አከበሩት። እነዚህም ፡ ሹማምንት ፡ ቀድሞ ፡ እያቃጠሉ ፡ ያፈረሱትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልሰው ፡ እንዲያሠሩ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርገው ፡ ወዳገራቸው ፡ ተመለሱ። ንጉሡም ፡ ባገራቸው ፡ የክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ እንዲገባ ፡ ጨዋም (ወታደርም)እንዲተከል ፡ ኣደረጉ።

## ሐ -- ፡ ስለሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ስለግራና ፡ ስለቀኝ ፡ በኣልቲሐት።

የራሳቸውን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ በጅግኖ (ጅጅኖ)ከአከበሩ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ሣሉ ፡ ግራ ፡ በአልቲሐትን ፡ ሰይፋንም ፡ እንደልማዱና ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ አነገሥዋት። ሥርዓተ ፡ ንግሡን ፡ ለማየት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቆሜ ፡ ሳለ ፡ ምስጢራዊ ፡ የሆነውን ፡ የንግሥ ፡ ሥርዓት ፡ እንዳላይ ፡ በፊቴ ፡ የሐር ፡ መጋረጃ ፡ ጋረዱብኝ። ለልብሷ ፡ የሚሆነው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሽልማት ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ በዡሮዋ ፡ ባንገቷ ፡ በእጅዋና ፡ በእግሯ ፡ ላይ ፡ የምታደርገውን ፡ የወርቅ ፡ ጌጣጌጥ ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ አመጡላት። ይኸን ፡ የመሰለውም ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ (ሕገ ፡ ቊርሐት) ለግራ ፡ በአልቲሐት ፡ እንጂ ፡ ለሌሎቹ ፡ ንግሥታት ፡ ኣይደረግም።

ሥርዓተ ፡ ንግሡ ፡ ከአለቀ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ በብዙ ፡ ጨዋ ፡ ታጅበው ፡ በታላቅ ፡ ግርማና ፡ ግርግር (ድልቅልቅ) ወደ ፡ መኖሪያቸው ፡ ሲገቡ ፡ ግራ ፡ በአልቲሐትም ፡ በኋላዋ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ አብራ ፡ የነገሡችውን ፡ እሌኒ ፡ ንግሥትን ፡ አስከትላ ፡ ንጉሡን ፡ ትከተላቸው ፡ ነበር። ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ማደሪያቸው ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ግራ ፡ በአልቴሐትም ፡ የግራውና ፡ የቀኙ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ሠራዊቱም ፡ ሁሉ ፡ እንደተከተላት ፡ ወደ ፡ መኖሪያዋ ፡ ሥፍራ ፡ ገባች። አንበሳ ፡ ጠባቂዎችም ፡ ለንጉሡ ፡ እንደሚደረገው ፡ አንበሶቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ብዙ ፡ መብራት ፡ አብርተው ፡ በእጃቸው ፡ እንደጨበጡ ፡ ይከተሏት ፡ ነበር ፡ ለአሒ ፡ ገብሩ (የርሷ ፡ አዛዥ ፡ ይሆናል) ትልቅ ፡ ዙፋን ፡ መነሣንስ ፡ ነጭ ፡ ጨርቅ ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ሕግ ፡ ተቀበለ።

ብዙ ፡ በሬዎች (ሠንጎች)ለአንበሶቹ ፡ ተሰጡ ፡ አንበሶቹም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ሠንጎቹን ፡ ገደሏቸው ፡ ለኣንበሳ ፡ ጠባቂው ፡ ለሌሎቹም ፡ ሹማምንት ፡ የሽልማት ፡ ልብስ ፡ ተሰጣቸው።

ቀኝዕ ፡ ባልቴሐት ፡ ንግሥት ፡ እሌኒን ፡ በበኵሏ ፡ ንጉሡ ፡ በጣም ፡ ወደዳት። ምክንያቱም ፡ በ**እግዚአብሔር** ፡ ዘንድ ፡ ምጽዋትና ፡ ቊርባንን ፡ የምትፈጽም ፡ ሃይማኖትና ፡ ምግባር ፡ የተመላች ፡ ፍጽምት ፡ ስለሆነች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ መጻሕፍትንና ፡ ንግግርን ፡ ሕግንና ፡ የማዕድን ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ የምታውቅ ፡ ስለሆነች ፡ ነው። በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ ንጉሡ ፡ ንግሥት ፡ ዕሌኒን ፡ እንደ ፡ እናታቸው ፡ አደረጓት። ከዚያ ፡ እንደ ፡ ሀገሩ ፡ ልማድ ፡

ጠይቀው ፡ እንደነገሩዋቸው ፡ ሥርዓተ ፡ ቡራኬ ፡ ለመፈጸም ፡ ባለሕጎቹን ፡ ከአምሐራ ፡ ውስጥ ፡ ከአሉበት ፡ አስጠሩና ፡ በጐናቸው ፡ አስቀመጧቸው። ባለሕጎቹም ፡ የለበሱት ፡ እንደ ፡ ደምቡ ፡ መሐቅ (ማቅ-በርኖስ?) ነበር። በነርሱ ፡ መካከል ፡ ከገብረ ፡ ዋሕድና ፡ ከማርቆስ (ዘእግር ፡ ዘቀኖች?) ከግራና ፡ ከቀኝ ፡ ጌቶች ፡ ከአዛዥ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ኣልነበረም። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እነዚህ ፡ የአምሐራ ፡ በዓለ ፡ ሕጎች ፡ እንደደንባቸውና ፡ እንደ ፡ ሕጋቸው ፡ ከባረኩዋቸው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ተመለሱ »

በዚህ ፡ ላይ ፡ የምንረዳው ፡ ዓፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ የአትሮንስ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዘመናቸው ፡ ካሠሩ ፡ በኋላ ፡ ይህቺ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ግላቸው ፡ ተቆጥራ ፡ በሐብት ፡ በልብስ ፡ በጕልት ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠች ፡ እንድትሆን ፡ መፈለጋቸውን ፡ የበለጠ ፡ እንድትከብር ፡ ያባቶቻቸውን ፡ የነገሥታቱን ፡ ያፄ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ያፄ ፡ ንዋየ ፡ ማርያምን ፡ ያፄ ፡ ይኵኖ ፡ አምላክን ፡ የሌሎችንም ፡ ነገሥታትና ፡ ጳጳሳት ፡ ዐፅም ፡ እያሰበሰቡ ፡ በዚች ፡ ደብር ፡ እንዲቀመጥ ፡ ማድረጋቸው ፡ ነው። ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ ነገሥታትና ፡ ጳጳሳት ፡ የተቀበሩበት ፡ ወይም ፡ ዐፅማቸው ፡ ያረፈበት ፡ ደብር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሐብት ፡ በስለት ፡ ስለሚከብር ፡ ዓፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ የነገሥታቱን ፡ ዐፅም ፡ ኣሰብስበው ፡ በዚች ፡ ደብር ፡ ማስቀመጣቸው ፡ አትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ የከበረች ፡ ሆና ፡ እንድትዘልቅ ፡ በመመኘት ፡ ነው።

፪ኛ ፡ የዚህ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ ላንድ ፡ ወንድ ፡ የሚለውን ፡ የወንጌል ፡ ቃል ፡ ችላ ፡ በማለት ፡ በዙሪያቸው ፡ እንዳሉት ፡ የአረማውያንና ፡ የእስላም ፡ ነገሥታትና ፡ ባላባት ፡ ካንዲት ፡ በላይ ፡ በገሀድ ፡ ብዙሚስት ፡ ማግባታቸውን ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንም ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ተመልክተነዋል። አሁንም ፡ በዚያው ፡ መሠረት ፡ ዓፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ ግራ ፡ በኣልቲሐት ፡ ዣን ፡ ሰይፋንና ፡ ቀኝ ፡ በኣልቲሐት ፡ ዕሌኒን ፡ ደንበኛ ፡ ሚስት ፡ ማድረጋቸውን ፡ ከቀኙዋም ፡ የግራዋ ፡ ብልጫ ፡ እንዳላት ፡ ለቀኝዋ ፡ የማይፈጸም ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ለግራዋ ፡ መፈጸሙን ፡ የቀኙዋ ፡ የማትደፋውን ፡ አክሊል ፡ የግራዋ ፡ ለመድፋት ፡

መቻሏን ፡ እንገነዘባለን። ነገር ፡ ግን ፡ ይኸን ፡ ሕግና ፡ የደረጃ ፡ ማበላለጥ ፡ ጉዳይ ፡ ባፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያምና ፡ በጥቂት ፡ ነገሥታት ፡ ወይም ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ መፈጸሙን ፡ አናረጋግጥም። ምክንያቱም ፡ አንዱ ፡ ንጉሥ ፡ ከዘመኑ ፡ ጳጳስና ፡ ከዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ ጋር ፡ ተማክሮ ፡ የገነባውን ፡ ተከታዩ ፡ ንጉሥ ፡ በቀላሉ ፡ መልሶ ፡ ያፈርሰዋል።

እንደዚሁም ፡ የንጉሡ ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ቀድሞ ፡ መራቂዎቹ ፡ በአክሱም ፡ ባለሕጎች ፡ ጳጳሳት ፡ ይመርቁታል ፡ ብሎ ፡ ያለፈውን ፡ ኣሁን ፡ ግን ፡ የምረቃውን ፡ ደንብ (ሥርዓተ ፡ ቡራኬ) ፡ የሚፈጽሙት ፡ በተለይ ፡ የኣማራ ፡ ባለሕጎች ፡ መሆናቸውን ፡ ያስረዳል። አማራም ፡ ሲል ፡ አማራ ፡ ሳይንትን ፡ ማለቱ ፡ ነው። ይህ ፡ ኣገር ፡ የአማራዎች ፡ ምንጭና ፡ መደበኛ ፡ ሥፍራ ፡ የነበረ ፡ ይመስላል። እነበዕደ ፡ ማርያምም ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ከሰሎሞን ፡ የወረዱ ፡ እስራኤላውያን ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ከነድል ፡ ነዓድ ፡ ዘር ፡ የመጡ ፡ አክሱማውያን ፡ ቢያደርጋቸውም ፡ እነርሱ ፡ አማራነት ፡ ስለሚሰማቸው ፡ ይሁን ፡ በትክክል ፡ አይታወቅም ፡ ከአምደ ፡ ጽዮን ፡ ወዲህ ፡ የተነሡት ፡ ነገሥታት ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድም ፡ ዳዊትም ፡ ይስሐቅም ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ ያሁኑ ፡ በዕደ ፡ ማርያምም ፡ ከአሉበት ፡ ከሸዋ ፡ ከመንዝና ፡ ከተጉለት ፡ ከመራቤቴ ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ሳይንትና ፡ ወደ ፡ አካባቢው ፡ እየሄዱ ፡ ከተማ ፡ መከተም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መትከልን ፡ ሥራችን ፡ ብለው ፡ ይዘውት ፡ ነበር። ወደፊት ፡ በ፫ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ እንደምንረዳው ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልም ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ከመቅደላ ፡ ወዲያ ፡ ባለው ፡ ቤተ ፡ አምሐራ ፡ በሚባለው ፡ ኣገር ፡ መካነ ፡ ሥላሴን ፡ ተክለው ፡ የነበረውን ፡ የግራኝ ፡ ጦር ፡ ኣፍርሶታል። የሥራውን ፡ ኣስደናቂነት ፡ በሥፍራው ፡ ስንደርስ ፡ እንመለከታለን።

# ምዕራፍ ፡ ፶፩።

## ስለ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕልስለሌዎን ፡ ብራንካ ፡ ስእል።

ይህ ፡ እስካሁን ፡ የምንመለከተው ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ እንደዚያው ፡ እንዳባታቸው ፡ እንደ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ምዕራፍ ፡ ሳይመደብለት ፡ በአርእስት ፡ ሳይከፈል ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ መደዳውን ፡ የተጻፈውን።

**ሀ-**ወደ ፡ አማርኛ ፡ እየተረጐምሁ፡

**ለ-**ለማንበብ ፡ እንዳይሰለች ፡ በየጕዳዩ ፡ መካከል ፡ አርእስትና ፡ ምዕራፍ ፡ እያበጀሁ፡

**ሐ-**በቅንፍ ፡ ከታጠረው ፡ ከዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ንግግር ፡ ቀጥሎ ፡ የራሴን ፡ ሐተታ ፡ እየጨመርሁ ፡

የሠራሁት ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ደርሷል። ያፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንና ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ያህል ፡ ከነርሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቢኖራቸው ፡ ኖሮ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ በጠቀመ ፡ ነበር። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዘመኑ ፡ ሳይጻፍ ፡ በመቅረት ፡ ወይም ፡ የተጻፈው ፡ ከዮዲት ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ ድረስ ፡ በተደረገው ፡ የጦርነት ፡ ሁከትና ፡ ወረራ ፡ ጽሑፉ ፡ በመጥፋቱ ፡ የአክሱሞችና ፡ የዛጕዬዎች ፡ እንደነ ፡ አብርሃ ፡ እንደነ ፡ ካሌብ ፡ እንደነ ፡ ላሊበላ ፡ ያሉት ፡ የጥቂቶች ፡ ሞላ ፡ ከጐደል ፡ ሲገኝ ፡ የቀሩት ፡ ሳይገኝ ፡ በመቅረቱ ፡ ረዥሙ ፡ የታሪክና ፡ የሥራ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ጨለማና ፡ ባዶ ፡ ስለሆነ ፡ በዝምታ ፡ ውስጥ ፡ ለማለፍ ፡ ግዴታ ፡ ሆነ።

ስለ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ጽፈናል። ስለ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ግን ፡ በዓሥር ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ያለፈውን ፡ አጭሩን ፡ የንጉሡን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በሚበቃ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ በዘመኑ ፡ አጻጻፍ ፡ ተርኮት ፡ መገኘቱ ፡ ለዛሬ ፡ ታሪክ ፡ ጠቃሚነቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ

፡ ስለሆነ ፡ ጸሐፊው ፡ ምሥጋና ፡ ይገባዋል። መጽሐፉም ፡ የተጻፈው ፡ በራሳቸው ፡ ዘመን ፡ ወይም ፡ በልጃቸው ፡ በእስክንድር ፡ ጊዜ ፡ ለመሆኑ ፡ ጥርጥር ፡ የለበትም። ጸሐፊው ፡ በግዕዝኛ ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ተናግሮ ፡ ሲጨርስ ፡ የግራ ፡ በአልቲሐትን ፡ የዣን ፡ ሰይፉን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ ለመጻፍ ፡ ሲዠምር ፡ «ወአንገሥዋ ፡ በህየ ፡ ለንግሥት ፡ ግራ ፡ ባልቲሐት (በኣልቴሐት) ዣን ፡ ሰይፉ ፡ በከመ ፡ ሕግ ፡ ዘልማድ ፡ ወሊተሰ ፡ ኢያርአዩኒ ፡ ወአንጦልዑ ፡ በቅድሜየ ፡ መንጦላዕተ ፡ ሐሪር ፡ እንዘ ፡ ሀሎኩ ፡ ህየ ፡ ቀዊምየ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ ሕጎሙ ፡ ኀቡኡ ፡ **ትርጓሜ ፡ -** በዚያም ፡ ንግሥት ፡ ግራ ፡ ባልቲሐት ፡ ዣን ፡ ሰይፉን ፡ እንደ ፡ ሕጋቸው ፡ ልማድ ፡ አነገሥዋት ፡ ለማየትም ፡ እዚያው ፡ ቆሜ ፡ ሳዕ ፡ የተሠወረ ፡ ሕጋቸውን ፡ እንዳልመለከት ፡ የሐር ፡ መጋረጃ ፡ በፊቴ ፡ ጋረዱብኝ ፡ ስላለ ፡ ጸሐፊው ፡ ታሪኩን ፡ ሁሉ ፡ የጻፈው ፡ ባይኑ ፡ የተመለከተውን ፡ በዡሮው ፡ የሰማውን ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል። የበእደ ፡ ማርያምን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በጻፈበት ፡ ውስጥ ፡ ስለንጕሡ ፡ መልካም ፡ ምኞቱን ፡ ከገለጸ ፡ በኋላ ፡ "ከማሁ ፡ ለወልዱ ፡ እስክንድር ፡ ይፈጽም ፡ ኵሎ ፡ ተምኔቶ ፡ እንደዚሁም ፡ ለልጁ ፡ ለእስክድር ፡ ምኞቱን ፡ ሁሉ ፡ ይፈጽምለት ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ጨምሮ ፡ ስለተገኘ ፡ ምናልባት ፡ ባፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ጊዜ ፡ ሰብስቦና ፡ ኣጠራቅሞ ፡ ወይም ፡ ግማሹን ፡ ጽፎ ፡ በልጃቸው ፡ በእስክንድር ፡ ጊዜ ፡ የእስክንድርን ፡ እየጨመረ ፡ ሁሉንም ፡ አጠናቆ ፡ ይሆናል።

ከዚህ ፡ ከዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ውጭ ፡ ስለ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ታሪካቸውን ፡ የፈለግን ፡ እንደሆነ ፡ በሌላው ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ እናገኛለን። በእደ ፡ ማርያም ፡ ነግሠ ፡ ፲ተ ፡ ዓመተ ፡ ውእቱኒ ፡ አሥዐለ ፡ ሥዕለ ፡ ማርያም ፡ ወሥዕለ ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡** በእደ ፡ ኣፍርንጅ ፡ ወበእንተዝ ፡ አንጐርጐሩ ፡ ሕዝበ ፡ ኢትዮጵያ። ወሥዕሉኒ ፡ ነበረ ፡ በአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ሠሉሱ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለሐፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ወአሜሃ ፡ ቦኣ ፡ ጋላ ፡ ሰቢሮ ፡ አናቅጼሃ ፡ ለአትሮንሰ ፡ ማርያም ፡ ወቀተለ ፡ ካህናቲሃ ፡ ወማህረከ ፡ ኵሎ ፡ እደ ፡ ወኣንስተ ፡ ለውእቱ ፡ ሥዕል ፡ ወለአስከሬነ ፡ ዐፅሙ ፡ ለሐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዘረዎሙ ፡ ውስተ ፡

ጸድፍ ፡ ውእቱ ፡ ጋላ ፡ ኣመ ፡ ፲ወ፱ ፡ ለነሐሴ ፡ ወዕለቱ ፡ እሑድ ፡ ዕረፍቱኒ ፡ ለሐፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ኮነ ፡ አመ ፡ ፲ወ፪ ፡ ለዓዳር።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈው ፡ የሚያስረዳን ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ በዘመናቸው ፡ በአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ የእመቤታችንንና ፡ የጌታችንን ፡ ሥዕል ፡ ባንድ ፡ ፈረንጅ ፡ እጅ ፡ አሥለው ፡ ሳለ ፡ በስዕሉ ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ማንገራገራቸው ፡ ይኸው ፡ ሥዕል ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት (፲፻፯፻፪ ፲፻፯፻፱ ፡ ዓ.ም ) ድረስ ፡ ሲኖር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ጋሎች ፡ በነሐሴ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ በር ፡ ሰብረው ፡ ገብተው ፡ ካህናቱን ፡ ገድለው ፡ ሥዕሉንም ፡ ሰውንም ፡ ማርከው ፡ መውሰዳቸውን ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምንም ፡ ዐፅም ፡ ወስደው ፡ ወደገደል ፡ መበተናቸውን ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የሞቱበትም ፡ ቀን ፡ ኅዳር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ መሆኑን ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ፈረንጁ ፡ ማን ፡ መሆኑን ፡ የጠቡን ፡ ምክንያት ፡ ጭምር ፡ ሳይገልጽ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደዚሁ ፡ አልፎታል።

ዣምስ ፡ ብሩስ ፡ የሚባለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ በጻፈው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፉ ፡ በ፪ኛው ፡ ቮሊም ፡ ከገጽ ፡ ፺፪ -፺፫ ድረስ ፡ ባለው ፡ ውስጥ ፡ እንደተረከው ፡ ባፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዘመን ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ በአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ የእመቤታችንንና ፡ የጌታችንን ፡ ስዕል ፡ የሳለው ፡ ፍራንቼስኮ ፡ ደ ፡ ብራንካ ፡ ሌዎን ፡ የሚባለው ፡ የኢጣልያ (ቪኒስያ) ተወላጅ ፡ ነው። ካህናቱ ፡ በዚህ ፡ ስዕል ፡ የተነሣ ፡ ከፈረንጁ ፡ ጋር ፡ ጠብና ፡ ክርክር ፡ ያበቀሉት ፡ በፈረንጅነቱ ፡ ወይም ፡ ካቶሊክ ፡ በመሆኑ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ ካቶሊኮች ፡ ደንብ ፡ እመቤታችን ፡ ጌታችንን ፡ አቅፋ ፡ የያዘችው ፡ በግራ ፡ እጅዋ ፡ ስለሆነ ፡ እንደ ፡ ምሥራቅና ፡ እንደ ፡ እስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደንብ ፡ በቀኝ ፡ እጅዋ ፡ እንዳቀፈችው ፡ አድርጎ ፡ ለምን ፡ አልሳለም ፡ በማለት ፡ ነው።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዋናው ፡ አሳባቸው ፡ አትሮንስ ፡ ማርያም ፡ በሐብት ፡ በክብር ፡ ከፍ ፡ እንድትል ፡ በጣሩበት ፡ መንገድ ፡ በስዕል ፡ ረገድ ፡ ውስጧ ፡ እንዲያምር ፡ ና ፡ ኣሳባቸው ፡ ስለነበረ ፡ በስዕሉ ፡ ማማር ፡

የተነሣ ፡ በፈረንጁ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ጉዳት ፡ አላደረጉበትም። በምዕራፍ ፡ ፴፱ ላይ ፡ ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ እንደተጻፈው ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ከአንድ ፡ ፈረንጅ ፡ ጋር ፡ በሃይማኖት ፡ ተከራከረ ፡ የሚለው ፡ ይኸንኑ ፡ ፍራንቼስኮ ፡ ብራንካ ፡ ሌዎን ፡ ( Francesco ፡ de ፡ Branca ፡ Leone) የሚባለውን ፡ ነው። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ስዕሉ ፡ ሳይነሣ ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ኖሮ ፡ በኋላ ፡ ጋሎች ፡ አፈረሱት ፡ ሲል ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ የጻፈው ፡ የሚያጠራጥር ፡ አሣብ ፡ አለበት።

፩ኛ–ራሱ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ወደፊት ፡ በ፫ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ እንደምናገኘው ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የሆነውን ፡ የግራኝን ፡ ወረራና ፡ ቃጠሎ ፡ በሚተርክበት ፡ ላይ ፡ ወአመ ፡ ፺ ፡ ለኀዳር ፡ አውዓዮሙ ፡ ግራኝ ፡ በእሳት ፡ ለመካነ ፡ ሥላሴ ፡ ወለደብረ ፡ ነጐድጓድ ፡ ወለአትሮንሰ ፡ ማርያም....” ብሎ ፡ ግራኝ ፡ በኅዳር፺ ፡ ቀን (ሺ፭፻፳፩ ፡ ዓ.ም) አትሮንሰ ፡ ማርያምን ፡ ከሌሎቹ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጋር ፡ ማቃጠሉን ፡ ይገልጻል።

፪ኛ ፡ የግራኝንና ፡ የዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ የጦርነት ፡ ታሪክ ፡ በሥፍራው ፡ እየተገኘ ፡ በየጊዜው ፡ የጻፈው ፡ ኣራብ ፡ ፋቂህ ፡ ሺዚር ፡ ኑር ፡ የሚባለው ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ይዞ ፡ ሄዶ ፡ አትሮንሰ ፡ ማርያምንና ፡ ዕቃውን ፡ ብሩንና ፡ ወርቁን ፡ ልብሱን ፡ ሁሉ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ቦታ ፡ አግኝቶ ፡ ዘርፎ ፡ ከብዛቱም ፡ የተነሣ ፡ ዕቃውና ፡ በውስጡ ፡ ያለው ፡ ሐብት ፡ ወጥቶ ፡ የማያልቅ ፡ መሆኑን ፡ ተመልክቶ ፡ ከነዕቃው ፡ አቃጥሉት ፡ ብሉ ፡ ወታደሮቹ ፡ እፊቱ ፡ አትሮንሰ ፡ ማርያምንና ፡ ዕቃ ፡ ቤቱን ፡ አቃጥለው ፡ አመድ ፡ አደረጉት ፡ ብሎ ፡ በዝርዝር ፡ ጽፏል።

ስለዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የአትሮንዕ ፡ ማርያም ፡ የማርያምንና ፡ የ**ክርስቶስን** ፡ ስዕል ፡ ኣሳለ ፡ ስዕሉም ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ኖሮ ፡ ሳለ ፡ ጋሎች ፡ በሩን ፡ ሰብረው ፡ ገብተው ፡ ኣቃጠሉት» ሲል ፡ ነገሩ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ የማይገናዘብና ፡ ስሕተት ፡ ያለበት ፡ መሆኑ ፡ በግልጽ ፡ ይታያል። ምናልባት ፡ የግራኝ ፡ ጦር ፡ ለማቃጠል ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ቀሳውስቱ ፡ ስዕሉን ፡ አንስተው ፡ እሌላ ፡ ዘንድ ፡ ደብቀውት ፡ ሲኖር

፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ቤተክርስቲያኑ ፡ እንደገና ፡ ከተሠራ ፡ በኋላ ፡ ለጥፈውት ፡ ይሆን ፡ እንዳይባል ፡ የአትሮንስ ፡ ማርያም ፡ ዕቃው ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖው ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ ምስሉና ፡ ወርቁ ፡ ታቦቱም ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ተደብቆ ፡ ሳለ ፡ መነኰሳቱም ፡ የተደበቀበትን ፡ አሳዩን ፡ ቢባሉ ፡ አናሳይም ፡ ግደሉን ፡ ብለው ፡ በዚሁ ፡ ከተገደሉ ፡ በኋላ ፡ የተቀመጠበትን ፡ ቤት ፡ ዕቃው ፡ ከመሬት ፡ እስከ ፡ ጣራው ፡ እንደሞላ ፡ ፈራቃሃም ፡ ኣሊ ፡ አግኝቶ ፡ የቻሉትን ፡ ያህል ፡ ዘርፈው ፡ የቀረውን ፡ ከነቤቱ ፡ የማቃጠላቸው ፡ በዚሁ ፡ በኣራብ ፡ ፋቂህ ፡ መጽሐፍ ፡ በትክክል ፡ ተጽፏልና ፡ ይህ ፡ በብራንካ ፡ ሌዎን ፡ እጅ ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ያሳሉት ፡ ስዕል ፡ ከቃጠሎ ፡ ተርፎ ፡ እስከ ፡ ኣፄ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የደረሰ ፡ አይመስልም።

# ያፄ ፡ እስክንድር ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ ፵፪።

## በእስክንድር ፡ ሕፃንነት ፡ የተነሣ ፡ የንግሥት ፡ ሮምና ፡ የዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ተስፋ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ የጋራ ፡ ግዛት።

ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ከሺ፰፻፳ ፡ እስካ ፡ ሺ፰፻፵ ፡ ዓ.ም ፡ ድረስ ፡ ዓሥር ፡ ዓመት ፡ ገዝተው ፡ በተወለዱ ፡ በ፴ ፡ ዓመታቸው ፡ ሲሞቱ ፡ ሕፃኑ ፡ ልጃቸው ፡ እስክንድር ፡ ነገሡ። የ፴ ፡ ዓመት ፡ ጐልማሳ ፡ ሆነው ፡ በወጣትነታቸው ፡ ጊዜ ፡ እሞት ፡ ያደረሳቸው ፡ ትክክለኛው ፡ ምክንያት ፡ ኣይታወቅም። ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ በ፪ኛው ፡ ቮሊም ፡ መጽሐፉ ፡ ገጽ ፡ ፹፮–፺፫ ፡ ላይ ፡ በመርዝ ፡ ሞተው ፡ ይሆናል ፡ ሲል ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ኣልቻለም።

ነገር ፡ ግን ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ ግድም ፡ ጽራግ (ራቅ)ማሰሮችና ፡ ዣን ፡ ማሰሮች ፡ የሚባሉት ፡ ብዙዎች ፡ ሹማምንት ፡ ሌሎችም ፡ በተለይ ፡ መሐሪ ፡ ክርስቶስ ፡ ጐስአሮ ፡ ተብለው ፡ የተጠቀሱት ፡ ሁሉ ፡ ግማሾቹ ፡ ሲያሙ ፡ ግማሾቹ ፡ ሲያድሙ ፡ በዚሁ ፡ መታሠር ፡ መፈታት ፡ መገረፍ ፡ መጋዝ ፡ በርክቶ ፡ ስለነበረ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ማረጋገጥ ፡ ባይቻል ፡ ፊትለፊት ፡ ተዋግተው ፡ ለማስወገድ ፡ ያልቻሉዋቸውን ፡ ንጉሥ ፡ በመርዝ ፡ ገድለዋቸው ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ለመጠራጠር ፡ ይቻላል።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በሺ፰፻፵ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ሲሞቱ ፡ ከእመቤት ፡ ሮማነ ፡ ወርቅ ፡ የተወለዱት ፡ ልጃቸው ፡ እስክንድር ፡ በሕፃንነታቸው ፡ ሰዓት ፡ ነገሡ። እስክንድር ፡ የተወለዱት ፡ አባታቸው ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ አማራ ፡ ሳይንትና ፡ ወሎ ፡ ከርመው ፡ የዶብዓ (ዋጅራትና ፡ ራያ) ጦርነትን ፡ ጨርሰው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ስለሆነ ፡ ቢበዛ ፡ በነገሡ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ፮ ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ፯ ፡ ቢሆን ፡ ነው። ዕድሜያቸውን ፡ አይለይም ፡ እንጂ ፡ ሕፃን ፡ መሆናቸውን ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸውም ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ይገልጻል።

«ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ሊሞቱ ፡ አቅራቢያ ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ ልጄን ፡ እስክንድርን ፡ ኣንግሡት ፡ ብለው ፡ ስለነበረ ፡ ይኸው ፡ ቃል ፡ ለሕዝብ ፡ ተነግሮ ፡ ነገሡ። እስክንድር ፡ ቸር ፡ ቅን ፡ ንጹሕ ፡ ትንሽ ፡ ሕፃን ፡ ነበሩ። ስለዚህ ፡ እስክንድር ፡ እናታቸውን ፡ ባፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ጊዜ ፡ ከተጋዙበት ፡ ከኣማራ ፡ አገር ፡ እንዲመጡ ፡ ሰለኣዘዙ ፡ እናትዮዋ ፡ በቶሎ ፡ መጡ። ወዲያው ፡ ለዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እናት ፡ ለእግዚእ ፡ ክብራ ፡ እንደተደረገው ፡ ሊቃውንቱ ፡ ጽራግ ፡ ማሰሬ ፡ ሊቀ ፡ ደብተራ ፡ ቀሲስ (ቄስ ፡ ቀይስ) ሐፄ ፡ ሕጉን ፡ ፈጽመው ፡ አነገሡዋቸውና ፡ እዙፋን (መንበር)አስቀመጧቸው። በዚህም ፡ ዘመን ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ተስፋ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ግራ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምደ ፡ ሚካኤል ፡ ቀኝ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ በድላርዕድ (በድል ፡ ራዕድ– በድል ፡ ረዓድ) ነበሩ ፡ በማለት ፡ ዓፄ ፡ እስክንድር ፡ ሕፃን ፡ ስለነበሩ ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ በሥራም ፡ በኣሳብም ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት ፡ ለማውጣት ፡ በመምከርም ፡ መተባበራቸውን ፡ እየገለጸ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ በግዕዝ ፡ ይቀጥላል።

“.....ወኮነ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለንጉሥነ ፡ እስክንድር ፡ ዛኅን ፡ በፍሥሐ ፡ ወበሐሤት ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ምድር ፡ ወኮኑ ፡ ስንዕዋነ ፡ እመ ፡ ንጉሥ ፡ ሮምና ፡ ወዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ተስፋ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ እሉ ፡ ፫ቱ ፡ ኣይትፈለጡ ፡ በገቢረ ፡ ምክር ፡ ወሥርዓተ ፡ ትእዛዝ ፡ ወንጉሥሰ ፡ ኢየአምር ፡ ሥርዓተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወነገራቲሆሙ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብኣ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እስመ ፡ ሕፃን ፡ ውእቱ ፡ ጥቀ ፡ በውእቱ ፡ ዘመን ፡ ........”

ከዚሁ ፡ ኣያይዞ ፡ ከትንሽ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ከነዚህ ፡ ከሦስቱ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ ብቻውን ፡ መግዛቱን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ሐስቦ ፡ አባ ፡ ዓምዱ ፡ ምዕመን ፡ በጽድቊ ፡ የሚባሉ ፡ ጠብ ፡ አንሥተው ፡ ስለነበረ ፡ ከአባሪዎቻቸው ፡ ጋር ፡ ተይዘው ፡ እንደተገረፉና ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ቦታ ፡ እንደተላኩ ፡ ግማሾቹም ፡ በመንገድ ፡ እንደሞቱ ፡ ያስረዳናል።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ቀድሞ ፡ የሮማን ፡ መንግሥት ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ በስድሳ ፡ ዓመት ፡ ላይ ፡ ፖምፔ ፡ ዩልዩስ ፡ ቄሣር ፤ ክራሱስ ፡ ሦስቱ ፡ የሥልጣን ፡

ጓደኞች (ትሪውምቪራቱስ)ሆነው ፡ ያስተዳድሩ ፡ እንደነበረ ፡ በዚህም ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሡ ፡ እስክንድር ፡ ሕፃን ፡ ከመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ እናታቸውና ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ ከግራው ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ በስምምነት ፡ አገሪቱን ፡ ያስተዳድሩ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው።

ዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ ኣብዛኛ ፡ የሥልጣኑ ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ወደ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡ ስለሚያደላ ፡ እናትዮዋ ፡ ንግሥት ፡ ሮምና (ሮማነ ፡ ወርቅ) ሴት ፡ ስለሆኑ ፡ ከሦስቱ ፡ ይበልጥ ፡ ወታደሩንም ፡ አገዛዙንም ፡ እየመራ ፡ መንግሥቱን ፡ በሙሉ ፡ እንደ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ የሚመራው ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ (ዓምደ ፡ ሚካኤል) ሆኖ ፡ ባጭሩ ፡ ፫ቱ ፡ መክረው ፡ የወሰኑትን ፡ በሥራ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ የሚያደርሰው ፡ ብሕት ፡ ወደዱ ፡ መስሎ ፡ ይታያል። በዚሁ ፡ ከሌሎቹ ፡ ሥልጣኑ ፡ ስለ ፡ ገነነ ፡ ጠብና ፡ ምቀኝነት ፡ ባንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ አብቅሉበት ፡ በዚሁ ፡ ጠበኞቹ ፡ እየተያዙ ፡ የተገረፉትንና ፡ የተጋዙትን ፡ ተመልክተናል።

ባዔ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ላይ ፡ ንግሥት ፡ ዣን ፡ ሰይፋ ፡ ግራ ፡ በአልቲሐት ፡ ሆና ፡ ሳለ ፡ አክሊል ፡ ደፍቶ ፡ በመንገሥና ፡ በሌላም ፡ ደረጃ ፡ ከቀኝ ፡ በኣልቲሐት ፡ በልጣ ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ አሁንም ፡ ባዔ ፡ እስክንድር ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከቀኙ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ከበድላ ፡ ርዕድ ፡ ይልቅ ፡ የግራው ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምደ ፡ ሚካኤል ፡ በሥልጣንና ፡ በኣስተዳደሪነት ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ እናያለን።

ሁላችን ፡ እንደምናውቀው ፡ እስከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሲደረግ ፡ እንዳየነው ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ከግራ ፡ ጌታ ፡ ቀኝ ፡ ጌታ ፡ በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ ከግራ ፡ ወምበር ፡ ቀኝ ፡ ወምበር ፡ ሲበልጥ ፡ ሳለ ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ከቀኟ ፡ የግራዋ ፡ ባለቤት ፡ ከቀኙም ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ የግራው ፡ እንዲበልጥ ፡ የተደረገበት ፡ ምክንያት ፡ አይገባንም።

# ምዕራፍ ፡ ፶፫።

## ያፄ ፡ እስክንድር ፡ አገር ፡ መጐበኘትና ፡ የአዳል ፡ ኣገር ፡ ዘመቻ-ያፄ ፡ እስክንድር ፡ አማሟት።

ያገራችን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጸሐፊ ፡ ቢበዛ ፡ ወርና ፡ ቀን ፡ መጻፍ ፡ እንጂ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ እየለየ ፡ መጻፍ ፡ አይሆንለትም። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ያፄ ፡ እስክንድርን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥና ፡ አገር ፡ መጐብኘት ፡ ሲነግረን ፡ በምን ፡ ዘመን ፡ እንደሆነ ፡ አይገልጽልንም። ንጉሡ ፡ በዚህ ፡ አሁን ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ በፈጸሙበት ፡ እየዞሩ ፡ አገር ፡ ጎብኝተው ፡ በመጨረሻም ፡ ከኣዳሎች ፡ በተዋጉበት ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜያቸው ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ እንደደረሰ ፡ መለየት ፡ ችግር ፡ ነው። ምናልባት ፡ ቢበዛ ፡ ፲፫ ዓመት ፡ ቢሆናቸው ፡ ነው። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የሚለውን ፡ እንመልከት።

"ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስክንድር ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ የለባሳ (ሸዋ) ሄደው ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ሕግ ፡ እንዳባቶቻቸው ፡ ፈጸሙ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከቅድስት ፡ ኣገር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ጳጳሳት ፡ መጡ። ከህናት ፡ በረከቱ። አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ታደሱ ፡ በየሀገሩም ፡ ደስታ ፡ ሆነ። ከዚያም ፡ ከሸዋ ፡ ኣገር ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ አምሐራ ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ ገነተ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድን ፡ አትሮንስ ፡ ማርያምን ፡ እየዞሩ ፡ ጐበኙ። በኅዳር ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ የቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ለት ፡ ያባታቸውን ፡ ተዝካር ፡ አወጡ። አባታቸው ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዠምረው ፡ የተውትን ፡ የአትሮንስ ፡ ማርያምንም ፡ ሥራ ፡ አሠርተው ፡ አስጨረሱ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተመለሱ። ከርሳቸውም ፡ ጋር ፡ በሸዋ ፡ ዘሥሉስ ፡ ነበረ..." በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ደግሞ ፡ ስለእስክንድር ፡ የተጻፈው ፡ እንደዚህ ፡ ይላል።

«ንጉሡ ፡ እስክንድር ፡ ውጊያ ፡ የሚያውቊ ፡ ኃይል ፡ የተመሉ ፡ ነበሩ። ፈረስ ፡ መጋለብ ፡ በጋሻና ፡ በጦር ፡ በቀስት ፡ የመዋጋትን ፡ ደንብ ፡ ያውቊ ፡ ነበር። ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ መሐሪና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ልባቸው ፡ ርኅሩኅ ፡ በቀልን ፡ የሚጠሉ ፡ መልካምን ፡ የሚወዱ ፡ ናቸው ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ወታደሮቹ ፡

አገር ፡ እያጠፉ ፡ ደህን ፡ ሲያስለቅሱ ፡ ኣልተቆጧቸውም ፡ ነበርና ፡ ስለዚህ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ተቆጣ። በ፪ተኛው ፡ ዓመት (ከነገሡ ፡ በኋላ፡?) ፡ ሠራዊታቸውን ፡ ሰብስበው ፡ ቅዱሳኑ ፡ ወደ ፡ ኣዳል ፡ አገር ፡ አትሂድ ፡ አትጠቀምም ፡ እያሉ ፡ ሲመክሩዋቸው ፡ እምቢ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ አገር ፡ ለውጊያ ፡ ሄዱ ፡ ዳካር ፡ ደርሰው ፡ ቤቱንም ፡ ሁሉንም ፡ አፈራርሰው ፡ ሲመለሱ ፡ እስላሞቹ ፡ ቲንሽ ፡ ሆነው ፡ ተከትለው ፡ ጦርነት ፡ ገጠሟቸው። አፄ ፡ እስክንድርም ፡ ጦርንቱን ፡ ገጥመው ፡ ሲዋጉ ፡ ሠራዊታቸው ፡ ግማሹ ፡ መሸሸ ፡ የቀረው ፡ ሞተ ፡ ግማሹ ፡ ተማረከ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ **እግዚአብሔር** ፡ በመላእክቱ ፡ ክንፍ ፡ ከልሏቸው ፡ በደህና ፡ ወደ ፡ ከተማቸው ፡ ገቡ። ከዚያ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ የሚበቀሉበትን ፡ ጊዜ ፡ በሐዘን ፡ በትካዜ ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጠብቊ ፡ ነበር። ዳሩ ፡ ግን ፡ አልሆነላቸውም።

በዘመናቸው ፡ ቤተ ፡ መቅደስ (በእዴሁ ፡ በእጁ) አሠርተው ፡ ሲጨርሱ ፡ ደብረ ፡ ምሥዋዕ ፡ ብለው ፡ ሠይመው ፡ ኣከበሩት ፡ ካህናቱንና ፡ አለቃቸውን (መክብበሙ)በጣም ፡ አከበሯቸው።

ከዕለታት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ በእልፍኛቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ የአርኖ ፡ ሰዎች ፡ የምትወደውን ፡ አገልጋይህን ፡ ተክላይን ፡ ገደሉት ፡ ብለው ፡ ነገሩዋቸው። ስለዚህ ፡ ከመሽ ፡ በኋላ ፡ ተነሥተው ፡ ወደነዚያ ፡ ሄደው ፡ ደረሱ። እነዚያም ፡ ባለፈው ፡ ተክላይን ፡ በገደሉበት ፡ ምክንያት ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ሊወጉዋቸው ፡ የመጡ ፡ መስሏቸው ፡ ንጉሥ ፡ መሆናቸውን ፡ ሳያውቊ ፡ እነዚህ ፡ ማያ ፡ የሚባሉት ፡ የአርኖ ፡ ሰዎች ፡ በጨለማ ፡ ወግተው ፡ ገደሏቸውና ፡ በነገሡ ፡ በ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ከ፺ ፡ ወር ፡ በግንቦት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ አረፉ። ስለዚህ ፡ ሴቶቻቸውንም ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ሳይተዉ ፡ እነዚህ ፡ የአርኖ ፡ ሰዎች ፡ ገደሏቸው። (በሌላ ፡ ቀን ፡ ማለቱ ፡ ነው።) የንጉሡ ፡ የእስክንድርም ፡ ሬሳ ፡ እደንበኛው ፡ ሥፍራ ፡ ሄዶ ፡ ከመቀበሩ ፡ በፊት ፡ ዘሥሉስ ፡ ወገኖቹን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ አገር ፡ ሄደና ፡ ልቡ ፡ የፈቀደውን ፡ አነገሠ። የምችግንም ፡ ሰዎች ፡ የእስክንድርን ፡ ሬሳ ፡ እንዳያሳልፉ ፡ ኣዘዛቸው። ቢሆንም ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የእስክንድር ፡ ልጅ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ነገሠ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ ያነገሡት ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ አምሐራ ፡ አገር ፡ ሄደው ፡ ከዘሥሉስና ፡ ከአነገሠው ፡ ጋር ፡ ተገናኙ። በዚያም ፡

ያሉት ፡ የእስክንድር ፡ ወታደሮች ፡ ባንድነት ፡ ሆነው ፡ ዘሥሉስንና ፡ ተከታዮቹን ፡ ገደሏቸው። »

ባሁኑ ፡ ምዕራፍ ፡ ዓፄ ፡ እስክንድር ፡ እሙሉ ፡ ሰውነት ፡ እንኳን ፡ ባይሆን ፡ እወጣት ፡ ዕድሜ ፡ ላይ ፡ ደርሰው ፡ ከእንደራሴዎቻቸውና ፡ ከሞግዚቶቻቸው ፡ ሥልጣን ፡ ወስደው ፡ እንዳባቶቻቸው ፡ ለማስተዳደር ፡ እንደዠመሩ ፡ እንመለከታለን። ያባቶቻቸውን ፡ የበእደ ፡ ማርያምን ፡ የዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ የይስሐቅን ፡ ኣርኣያ ፡ በመከተል ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሣቸውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ኣገር ፡ ሔደው ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ትከል ፡ ደብረ ፡ ነጐድጓድን ፡ አትሮንሰ ፡ ማርያምን ፡ እየዞሩ ፡ ጐበኙ። ከዚያ ፡ ዘወትር ፡ ቢሸነፉም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አንገዛም ፡ እያሉ ፡ የሚያስቸግሩትን ፡ እንዲያውም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በሊን ፡ ደዋሮን ፡ ይፋትን ፡ ሲመቻቸው ፡ እየወረሩ ፡ ክርስቲያኖቹን ፡ የሚዘርፉትን ፡ የሚገደሉትን ፡ የአዳል ፡ ባላባቶችን ፡ እንደዚያው ፡ አባቶቻቸው ፡ ሲዋጉ ፡ ሲያስገብሩ ፡ እንደኖሩት ፡ እርሳቸውም ፡ ተዋግተው ፡ ለማስገበር ፡ ኣሰቡ።

እነዚህም ፡ የአዳል ፡ ባላባቶች ፡ እነዚያው ፡ የወላስማ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ፡ ለዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ልኮ ፡ የገበረው ፡ መሐመድ ፡ ቤን ፡ በድላ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ታላላቅ ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ ግራ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ መሐሪ ፡ ክርስቶስንና ፡ ቀኝ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስን ፡ ድል ፡ ኣድርጎ ፡ የፈጀ ፡ ኦትማን ፡ ቤይ ፡ ሶለይማን ፡ የሚባለው ፡ ነው። ከርሱም ፡ ጋር ፡ የዙሪያው ፡ የእስላም ፡ ባላባቶች ፡ ከደዋሮና ፡ ከይፋት ፡ ከባሊም ፡ ተከታይና ፡ ወደርሱ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ አይጠፋም። ባሁኑ ፡ በእስክንድር ፡ ጊዜ ፡ የእስላሞቹ ፡ መሪ ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ዝል ፡ ፔሩሶ ፡ ሻምስ ፡ ኣድ ፡ ዲን ፡ መሐመድ ፡ ይባላል ፡ እርሱም ፡ በዚያው ፡ በዘሩ ፡ ሐረግ ፡ ላይ ፡ እንደሚታየው ፡ የበድላይ ፡ ሺሃብ ፡ ኤድ ፡ ዲን ፡ አህመድ (አርዌ ፡ በድላይ) የልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው። እንደ ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ከቀድሞ ፡ ከበእደ ፡ ማርያም ፡ ዠምሮ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የታወቀውን ፡ ግዛት ፡ እየወረረ ፡ አሁንም ፡ ባፄ ፡ እስክንድር ፡ ጊዜ ፡ የተዋጋው ፡ ኤሚር ፡ ማሕፉዝ (ማፉዲ)የሚባለው ፡ ነው። እንደ ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ አጻጻፍ ፡ ምንም ፡ ዋናው ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ዘስሉሥ ፡ ሲከዳቸው ፡ ዓፄ ፡ እስክንድር ፡

እስላሞቹን ፡ ፪ ፡ ጊዜ ፡ አሸንፈው ፡ የአባሉን ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ገድለዋል። የብሩስን ፡ መጽሐፍ ፡ ከ፪ኛው ፡ ቮሊም ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳ ፩፻፯ ፡ ተመልከት።

ሙሴ ፡ ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ይኸን ፡ የ፪ት ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ ሲጽፍ ፡ የማስረጃ ፡ ምንጭ ፡ ስለኣልጠቀሰ ፡ ከዚህ ፡ ተሸንፈው ፡ ሠራዊታቸው ፡ አልቆ ፡ በመላእክት ፡ ክንፍ ፡ ተከልለው ፡ ወደ ፡ ከተማቸው ፡ በደኅና ፡ ገቡ ፡ ከሚለው ፡ ከግዕዝኛው ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጋር ፡ ለማመዛዘንና ፡ የትኛው ፡ እውነት ፡ እንደሆነ ፡ ለመለየት ፡ አልተቻለም። ምናልባት ፡ ዓፄ ፡ እስክንድር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተዋግተው ፡ ሳላ ፡ የመዠመሪያውን ፡ ድል ፡ ማድረግ ፡ ዠምስ ፡ ብሩስ ፡ የመጨረሻውን ፡ ድል ፡ መሆን ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ጽፎት ፡ እንደሆነ ፡ ኣይታወቅም።

የተገኘው ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ በያላበት ፡ የተቆራረጠና ፡ ሙሉ ፡ ኣለመሆኑ ፡ በጽሑፉ ፡ ላይ ፡ ያስታውቃል። በዓፄ ፡ እስክንድር ፡ የሕፃንነት ፡ ዘመን ፡ የብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱን ፡ እንደራሴነት ፡ ከንግሥቲቱና ፡ ከዓቃቤ ፡ ሰዓቱ ፡ ጋር ፡ ሲያነሣ ፡ በዚህ ፡ በኣዳል ፡ ጦርነት ፡ ይልቁንም ፡ ንጉሡ ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ልግዛ ፡ ባሉበት ፡ ጊዜ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ አሜን ፡ ብሎ ፡ ታዛዥና ፡ ተከታይ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ በሥልጣኑ ፡ መቀነስ ፡ መቀየሙን ፡ ሳይገልጽ ፡ በፊት ፡ ስሙ ፡ ያልተነሣውን ፡ ዘሥሉስን ፡ "የንጉሡ ፡ ሬሳ ፡ ሳይቀበር ፡ የፈቀደውን ፡ ለማንገሥ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ አማራ ፡ ሔዶ ፡ ተዋግቶ ፡ መሞቱን ፡ ይጠቅሳል። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በጠቀስነው ፡ በጀምስ ፡ ብሩስ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ዘሥሉስ ፡ ዋና ፡ የጦር ፡ አለቃና ፡ እንደራሴ ፡ የነበረ ፡ ከኣዳሉ ፡ ጦርነት ፡ ንጉሡን ፡ እስክንድርን ፡ አጋልጦ ፡ የተመለሰ ፡ በኋላም ፡ የማያን (የአርኖንን) ሰዎች ፡ ቀስቅሶ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ዶልቶ ፡ እስክንድርን ፡ ያስገደለ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል። እነዚህም ፡ ዓፄ ፡ እስክንድርን ፡ የገደሉ ፡ የማያ (አርኖ)ሰዎች ፡ በአፋርና ፡ በትግሬ ፡ መካከል ፡ የሚገኙ ፡ ከአሰብ ፡ ከኣንጎት ፡ ጨው ፡ እያመላለሱ ፡ የሚነግዱ ፡ ናቸው። ዘሥሉስም ፡ ዓፄ ፡ እስክንድርን ፡ ኣስገድሎ ፡ ወደ ፡ ኣማራ ፡ አገር ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ የንጉሡ ፡ ወታደሮች ፡ ተዋግተው ፡ ማርከውት ፡ ዓይኑን ፡ አውጥተው ፡ ገደሉት። ብሩስ ፪ኛ ፡ ቮሊም ፡ ገጽ ፡ ፩፻፳፫ ፡ ተመልከት።

ምንም ፡ እንኳን ፡ የብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱን ፡ ሁኔታ ፡ ባይጠቅስ ፡ የስሉሥን ፡ ማመጥ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉም ፡ ስለጠቀሰው ፡ ከዠምስ ፡ ብሩስ ፡

ጽሑፍም ፡ በትክክል ፡ ይገናኛል። ስለዚህ ፡ ዓፄ ፡ እስክንድር ፡ ሥልጣን ፡ በያዙበት ፡ ዘመን ፡ እንደራሴዎቻቸው ፡ በሥልጣናቸው ፡ እየቀኑ ፡ ወይም ፡ ገና ፡ ወጣት ፡ በመሆናቸው ፡ ሥልጣናቸው ፡ ስለላላ ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ የአድማ ፡ ነገር ፡ እየሠሩ ፡ በጦርነትም ፡ በሥራም ፡ ከልብ ፡ አልተከተሏቸውም ፡ ማለት ፡ ነው። የዚህም ፡ ሁኔታ ፡ ለእስላሞቹ ፡ የበቀል ፡ ጊዜ ፡ ሰጥቷቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፶፬።

## የኢትዮጵያና ፡ የፖርቱጋል ፡ የመዠመሪያው ፡ ግንኙነት— ስለፔድሮ ፡ ኮቪልሐኦ ፡ መምጣት።

በምዕራፍ ፡ ፴፱ ፡ ስለ ፡ ፍሉራንስ ፡ ጉባዔ ፡ በምዕራፍ ፡ ፵፪ ፡ ስለ ፡ ኤውሮፓና ፡ ስለ ፡ መካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ሁኔታ ፡ የጻፍነውን ፡ መልሰን ፡ በማስታወስ ፡ ከሌሎቹ ፡ ዝርዝር ፡ መንግሥታት ፡ በቀር ፡ ቱርክና ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ገናኖች ፡ ሆነው ፡ በአፍሪካ ፡ ዙሪያ ፡ ግዛት ፡ ሲሻሙ ፡ በየወደቡ ፡ ሲዋጉ ፡ እንመለከታለን።

ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ የሕዝብን ፡ አነሣስና ፡ አወዳደቅ ፡ ስንመለከት ፡ ኣስደናቂ ፡ ሆኖ ፡ እናገኛቸዋለን። ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ከ፫ሺ ፡ እስከ ፡ ፯፻ ፡ ዓመት ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ግብፅን ፡ በሥልጣኔ ፡ በገናንነት ፡ የሚያህላት ፡ ኣልነበረም። በርሷ ፡ ደረጃም ፡ ባይሆን ፡ የሥልጣኔ ፡ ተከታታይ ፡ የኃይል ፡ ተፎካካሪ ፡ ለመሆን ፡ የቻሉ ፡ አሶርና ፡ ባቢሎን ፡ ከዚያም ፡ ፋርሶች ፡ ነበሩ።

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በግዛት ፡ በሥልጣኔ ፡ በተቋቋሙበት ፡ ዘመን ፡ ነገሥታቶቻቸው ፡ ቱትሞሲስ ፤ ራምሴስ ፤ አሱርባኒፓል ፤ አሳርሐዶን ፤ ሰናክሬም ፤ ናቡከደነፆር ፤ ቂሮስ ፤ ካምቤዝና ፡ ኮስሮዌ ፡ በዙሪያቸው ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ለማስገበር ፡ ሕዝብን ፡ በሚያምሱበት ፡ ሰዓት ፡ ግሪኮች ፡ በየደሴቶቻቸው ፡ ገና ፡ ሞኞች ፡ ነበሩ። ሮማውያን ፡ ገበሬዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ዐረቦች ፡ ደግሞ ፡ በበረሃ ፡

ግመል ፡ እየነዱ ፡ የሚዞሩ ፡ ዘላኖች ፡ ነበሩ ፡ የቱርክ ፡ የፖርቱጋል ፡ የፈረንሳዊና ፡ የእንግሊዝም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያውም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ድምፃቸው ፡ ገና ፡ አልተሰማም።

ነገር ፡ ግን ፡ ሥልጣኔና ፡ ገናንነት ፡ ከዛፍ ፡ ወደዛፍ ፡ እየበረረ ፡ እንደሚያርፍ ፡ ወፍ ፡ ከግብፅ ፤ ከኣሶርና ፡ ከባቢሎን ፡ ወደፋርስ ፤ ወደ ፡ ግሪክ ፡ ከግሪክ ፤ ወደ ፡ ሮማውያን ፡ ከሮማውያን ፤ ወደ ፡ ዐረቦች ፡ ሲተላለፍ ፡ ቆይቶ ፡ አሁን ፡ የዐረብን ፡ ሥልጣኔና ፡ ሃይማኖት ፡ ያቀፉት ፡ ቱርኮች ፡ የሮማውያንን ፡ ሥልጣኔና ፡ የሮማን ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተቀበሉት ፡ የፓርቱጋል ፡ ተወላጆች ፡ በዚህ ፡ በመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ በእግር ፡ ጦር ፡ በባሕር ፡ ኃይል ፡ እየበረቱ ፡ ሄዱ። ስለ ፡ ዐረቦችና ፡ ስለ ፡ ቱርኮች ፡ አነሣሥ ፡ በመዠመሪያው ፡ መጽሐፍ ፡ በምዕራፍ ፡ ፳፮ ፡ ና ፡ ፸፫ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በምዕራፍ ፡ ፵፪ ፡ ጽፈናል።

የፖርቱጋል ፡ ሕዝብና ፡ አገር ፡ በምዕራብና ፡ በደቡብ ፡ ከአትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ በምሥራቅ ፡ ከኤስፓኝ ፡ የሚዋሰን ፡ አገር ፡ ነው። በመዠመሪያ ፡ ባገሪቱ ፡ ሰልቶ ፡ ሂቤሪክ ፡ የሚባሉ ፡ የሕንድ ፡ ኤውሮፒዎ ፡ ዘር ፡ ሆነው ፡ በኋላ ፡ በየጊዜው ፡ በደረሰባቸው ፡ ወረራ ፡ በጀርመንና ፡ በኖርማንዲ ፡ በሮማውያንና ፡ በዐረቦች (ሞሪ_ማውሪታኒ) ፡ በሚባሉ ፡ የአፍሪካ ፡ ሕዝቦች ፡ ተቀያይጧል። ነገር ፡ ግን ፡ ሮማውያን ፡ ሰፊ ፡ ዘመናት ፡ ስለገዟቸው ፡ በዘርም ፡ በልምድም ፡ በሃይማኖትም ፡ ኣብዛኛው ፡ የፖርቱጋል ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ሮማውያንነት (ወደ ፡ ላቲንነት) ፡ ተለውጧል። የሮማን ፤ የጀርመንን ፤ የቪዚጎትን ፤ የዐረብን ፡ ወረራ ፡ ካሳለፉ ፡ በኋላ ፡ ከ፲ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ዠምረው ፡ የራሳቸውን ፡ መንግሥት ፡ ኣቋቍመው ፡ በዚህ ፡ በ፲፬ ኛውና ፡ በ፲፫ ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ ላይ ፡ እላይ ፡ እንደተመለከትነው ፡ ገናንነት ፡ ተሰምቷቸዋል።

የኤውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ እንግሊዝ ፤ ፈረንሣዊ ፤ ጀርመን ፤ ኤስፓኝ ፤ ኢጣሊያ ፡ በየወሰናቸው ፡ በየዙፋናቸው ፡ በሃይማኖትና ፡ በዘውድ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲጣሉና ፡ ሲዋጉ ፡ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ መርከብ ፡ እያዘጋጀ ፡ የአሜሪካንን ፡ የእስያን ፡ የአፍሪካን ፡ አገር ፡ እያስመረመረ ፡ ግዛቱን ፡ ያስፋፋ ፡ ዠመር። የዚህንም ፡ ታሪክ ፡ ወደፊት ፡ በምናሳትመው ፡ በሦስተኛ ፡

መጽሐፍ ፡ እስክናነብ ፡ ድረስ ፡ አሁን ፡ ስለ ፡ ኢትዮያና ፡ ስለ ፡ ፖርቱጋል ፡ ግንኙነት ፡ እንመልከት።

የዓለም ፡ ገዥዎችና ፡ ገናኖች ፡ እንደተለዋወጡ ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሁኔታ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በመጠኑ ፡ የተለዋወጠ ፡ ነው። ቀድሞ ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ ዝምሮ ፡ ከክርስትና ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ዘጠነኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ድረስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መናገሻ ፡ ከተማዋን ፡ በኣክሱም ፡ ኣድርጋ ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነቷን ፡ ከቍስጥንጥንያ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ እየቀጠለች ፡ የግዛቷን ፡ ወሰን ፡ እስከ ፡ ዐረብ ፡ አገር ፡ ኣድርሳ ፡ ኖረች። በዐረቦች ፡ መነሣት ፡ የኣክሱም ፡ መንግሥት ፡ ሲደክም ፡ የሰሜን ፡ ፈላሾች ፡ የአገው ፡ የበጂያ ፡ ነገዶች ፡ በአክሱም ፡ ነጋሢዎች ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ መንግሥት ፡ ከኣክሱም ፡ ወደ ፡ ዛጕዬ ፡ ተዛውሮ ፡ የነበረው ፡ ኣሁን ፡ ደግሞ ፡ ከዛጕዬ ፡ ወደ ፡ ጥንቶች ፡ የገዥዎች ፡ ዘሮች ፡ ተዛውሮ ፡ የመንግሥቱ ፡ መደብ ፡ በሸዋ ፡ የተመሠረተበት ፡ ጊዜ ፡ ነው። ይኸም ፡ ዘመን ፡ ከይኵኖ ፡ ኣምክ ፡ ዝምሮ (ሺ፪፻፸) ዓ.ም ፡ እስከ ፡ እዚህ ፡ እስከ ፡ ሺ፫፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ድረስ ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ታላላቅ ፡ ነገሥታት ፡ እነ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ እነ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ኣልፈውበታል።

ከአክሱም ፡ ዛጕዬ ፡ ከዛጕዩ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ የነገስታቱ ፡ መቀመውጫ ፡ እየራቀ ፡ በሄደበት ፡ መጠን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሃይማኖት ፡ የሥልጣኔ ፡ ምንጭ ፡ ከሆኑት ፡ ከእስክንድርያ ፡ ከሶርያ ፡ ከአንጾኪያ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከተሞች ፡ ስትለይ ፡ ከወደቦቿ ፡ ከምጥዋ ፡ ስትርቅ ፡ የቀድሞ ፡ ገናንነትዋ ፡ ሥልጣኔዋ ፡ እየጐደለ ፡ መሄዱ ፡ በግልጽ ፡ ይታወቃል። ከሌሎች ፡ መንግሥታት ፡ ዘመናዊውን ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዳትካፈል ፡ ጳጳሶቿን ፡ እንደልብ ፡ ከእስክንድርያ ፡ እንዳታገኝ ፡ በቱርኮቹና ፡ በግብፆቹ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሲዘጋበት ፡ የውስጥ ፡ ጦርነት ፡ ከሰሜን ፡ ፈላሾች ፡ ከአዳል ፡ ባላባቶች ፡ ሲቀሰቀስባት ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ተባብሮ ፡ በሥልጣኔ ፡ በኃይል ፡ ወደኋላ ፡ እየጐተተ ፡ አደከማት። ሆኖም ፡ ትድከም ፡ እንጂ ፡ እንደሌሎቹ ፡ በቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ አልተንበረከከችም። ክርስቲያናዊ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዳይጠፋ ፡ ግዛቷ ፡ እንዳይከፈል ፡ ነገሥታቶቿ ፡ ከሊቃውንቱና ፡ ከመኳንንቱ ፡ ጋር ፡ እንደታገሉ ፡

ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ያለ ፡ እረፍት ፡ እየተዘዋወሩ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ግዛት ፡ እንደጠበቊ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደተከሉ ፡ ናቸው።

እንደዚህ ፡ ጸንታ ፡ ከስላሞች ፡ ወረራ ፡ እየመከተች ፡ ነፃነቷን ፡ ሃይማኖቷን ፡ ይዛ ፡ የመቀመቀጧ ፡ ወሬ ፡ በአውሮፓ ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ በሩቊ ፡ የፍቅርን ፡ ስሜትና ፡ ስመ ፡ ጥርነትን ፡ አስገኝቶለታል። ከኢትዮጵያ ፡ ለመሣለም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሚመላለሱት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መነኰሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ምዕመናን ፡ ምክንያት ፡ በግብፅ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በዐረቦች ፡ አገር ፡ በግልጽ ፡ የታወቀች ፡ ሆና ፡ ሳለ ፡ በኤውሮፖች ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ የታወቀችው ፡ በወሬና ፡ በዝና ፡ ነው። በትክክል ፡ ካለመታወቋ ፡ የተነሣ ፡ የአውሮፓ ፡ ነገሥታትና ፡ ጳጳሳት ፡ ቀሳውስትና ፡ አገር ፡ መርማሪዎች ፡ ሁሉ ፡ ግማሹ ፡ በኑብያ ፡ ግማሹ ፡ በምሥራቅ ፡ በሕንድ ፡ የቀረው ፡ በዐረብ ፡ ኣገር ፡ ወይም ፡ በኣፍሪካ ፡ ዮሐንስ ፡ በሚባል ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ካህን ፡ የምትገዛ ፡ የክርስቲያን ፡ ኣገር ፡ ኣለች ፡ እያሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በጽሑፍም ፡ በቃልም ፡ ይነጋገሩባት ፡ ነበር። ብዙዎቹም ፡ የአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ በመልእክት ፡ ከዚች ፡ የክርስቲያን ፡ አገር ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ ፈትነዋል። ባዔ ፡ ይስሐቅ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት (ሺ፬፻፲ ሺ፱፻፳፪ ፡ ዓ.ም ፡ እንደ ፡ ኢትዮ ፡ ቊ ፡ ከኣራጎን) ኤስፓኝ ፡ ሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ ከኣልፎንሱ ፡ ፭ኛ ፡ እንደዚሁም ፡ ከባሪ (ፈረንሣይ) መስፍን ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ መደረጉ፤ ፡ በየመጽሐፉ ፡ ይገኛል። የዣን ፡ ዶሬዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፹፫–፪፻፹፭ ፡ ተመልከት።

በዚሁ ፡ መጽሐፍ ፡ የቤሪ ፡ መሥፍን ፡ መልከተኛ ፡ የእስላም ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ሸዋ ፡ መድረሱና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ማድረጉ ፡ ቀጥለው ፡ ባሉት ፡ ጊዜዎች ፡ በሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትና ፡ በአራጎን ፡ ነገሥታት ፡ ባዔ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ ባዔ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ መካከል ፡ የመልእክት ፡ ግንኙነት ፡ መደረጉ ፡ በየመጽሐፉ ፡ ይጠቀሳል። ነገሩንም ፡ ከፍሎራንስ ፡ ጉባዔ ፡ ጋር ፡ የሚያያዙት ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው።

ነገር ፡ ግን ፡ ደንበኛው ፡ ማስረጃ ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዚህ ፡ ዘመን ፡ ግንኙነት ፡ ከፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ነው። ፩ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ብራንካ ፡ ሌዎን ፡ ያሉትም ፡ የኢጣሊያ ፡ ተወላጆች ፡ እየተነጠሉ ፡ መምጣታቸው ፡

እርግጥ ፡ ነው። የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከሌሎች ፡ የበለጠ ፡ በምሥራቅና ፡ በአፍሪካ ፡ ተጠቃሚነት ፡ ስለአለው ፡ በዚህም ፡ ከቱርክ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ጠብ ፡ ስለአበቀለ ፡ እርሱን ፡ ለማጥቃት ፡ እንዲመቸው ፡ ከክርስቲያኑ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ መገናኘትና ፡ መወዳጀት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ታይቶት ፡ ነበር።

ስለዚህ ፡ ዮሐንስ (ዣን)የሚባለው ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ አልፎንሱ ፡ ደ ፡ ፓይቫ (Alofnso ፡ de ፡ Paiva) ፤ ፔድሮ ፡ ደ ፡ ኮቪልሐኦ (pedro ፡ de ፡ Covilhao) ፡ የሚባሉትን ፡ ሁለት ፡ የፓርቱጋል ፡ ተወላጆቹን ፡ መርጦ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ፈልገው ፡ እንዲያገኙና ፡ ከንጉሥዋ ፡ ተገናኝተው ፡ የወዳጅነት ፡ ግንኙነት ፡ እንዲወጥኑ ፡ ላካቸው።

እነርሱም ፡ እንደ ፡ ኤው ፡ ቍጥር ፡ በ፩ሺ፬፻፹፯ ፡ ዓ.ም ፡ ከፖርቱጋል ፡ ተነሥተው ፡ የቱርኮች ፡ በረኞች ፡ አግኝተው ፡ እንዳይዟቸው ፡ የነጋዴ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ በሮድ ፡ ደሴትና ፡ በግብጽ ፡ በሱአኪም ፡ በኵል ፡ አድርገው ፡ አደን ፡ ደረሱ። ኣደን ፡ ላይ ፡ ሁለቱ ፡ ተለያይተው ፡ ኣልፎንሶ ፡ ደፓይቫ ፡ ከአደን ፡ ወደ ፡ በርበራ ፡ ሲደርስ ፡ ሞተ ፡ ፔድር ፡ ኮቪል ፡ ሐኦ ፡ ግን ፡ ወደሕንድ ፡ ሄዶ ፡ በካልኵታና ፡ በጐአ ፡ ቆይቶ ፡ ከዚያ ፡ በሶፋላ ፡ በኣደን ፡ በኵል ፡ አድርጎ ፡ ካይሮ ፡ ሄዶ ፡ የጓደኛውን ፡ ወሬ ፡ ሲያጠያይቅ ፡ መሞቱን ፡ የሚያስረዳና ፡ እርሱ ፡ መልእክቱን ፡ እንዲፈጽም ፡ በዦስ ፡ ላሜጎና ፡ በራባ ፡ ኣብርሃም ፡ አማካይነት ፡ ከፓርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ደብዳቤ ፡ ተቀበለ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኮቪልሐኦ ፡ የቀይ ፡ ባሕርን ፡ ተሻግሮ ፡ በዘይላ ፡ በኵል ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጣ። ዓፄ ፡ እስክንድርም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከአዳሎች ፡ ጋር ፡ የሚዋጉበት ፡ ሰዓት ፡ ነበርና ፡ በብዙ ፡ ችግር ፡ ከዓፄ ፡ እስክንድር ፡ ተገናኝቶ ፡ ከፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ የተላከለትን ፡ ደብዳቤ ፡ አቀረበ። ንጉሡም ፡ ለዚህ ፡ ለፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ መላክተኛ ፡ መልካም ፡ ኣቀባበል ፡ አደረጉለት። ከዚያም ፡ አብረው ፡ ወደ ፡ ተጉለት ፡ መጥተው ፡ እንደተቀመጡ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳይቆዩ ፡ ዓፄ ፡ እስክንድር ፡ ሞቱ። እርሱም ፡ ከዓፄ ፡ እስክንድር ፡ ወዲህ ፡ ከነገሡት ፡ ነገሥታት ፡ ከዓፄ ፡ ናዖድም ፡ ከዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልም ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ልሂድም ፡ ልቅርም ፡ እያለ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተቀመጠ። እንዲያውም ፡ ቀኝ ፡ በአልቲሐት ፡

የሚባሉት ፡ ንግሥት ፡ እሌኒ ፡ የዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ባለቤት ፡ በኋላ ፡ ለልብነ ፡ ድንግል ፡ እንደሞግዚት ፡ ሆነው ፡ ያስተዳድሩ ፡ የነበሩት ፡ ካንዲት ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ጋር ፡ አጋብተውት ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ ይወጣ ፡ ይገባ ፡ ነበር ፡ ወደ ፡ አገሬም ፡ ልሂድ ፡ ቢል ፡ እዚሁ ፡ ከኛው ፡ ጋር ፡ ተቀመጥ ፡ ብለው ፡ በውዴታም ፡ በግዴታም ፡ በእዚሁ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስቀመጡት። በርሱ ፡ ምክር ፡ ወደፊት ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንደሚገኘው ፡ ማቴዎስ ፡ የሚባለው ፡ ከንግሥት ፡ እሌኒ ፡ የወዳጅነት ፡ ደብዳቤ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ፓርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ተልኮ ፡ ሄደ። ጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ፪ኛ ፡ ቮሊም ፡ ገጽ ፡ ፩፻፲፫-፩፻፲፰. ዣን ፡ ባቲስት ፡ ኰልቦ ፡ ፪ኛ ፡ ቮሊም ፡ ገጽ ፡ ፵፩–፵፬ ፡ ፶፱–፷ ፡ ባሴት ፡ ረኔ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፵ ፡ ተመልከት።

ንግሥት ፡ እሌኒ ፡ ይኸንን ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ መላክተኛ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዲቀመጥ ፡ የፈለጉበት ፡ ምክንያት ፡ በክርስቲያኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እስላሞቹ ፡ የወረራ ፡ ስሜት ፡ እንዳላቸው ፡ ስለሚያውቁና ፡ እነዚህን ፡ ባላጋራዎች ፡ ለመመለስ ፡ ከክርስቲያኑ ፡ የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ዕርዳታ ፡ ለማግኘት ፡ መሆኑን ፡ ወደፊት ፡ በሰፊው ፡ እንመለከታለን ፡ " ፡ ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ ትተን ፡ ካፄ ፡ እስክንድር ፡ ቀጥለው ፡ ወደ ፡ ነገሡት ፡ ወዳሜ ፡ ናዖድ ፡ እንመለስ።

# ያፄ ፡ ናዖድ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ምዕራፍ ፡ ፶፫።

## የዓፄ ፡ ናዖድ ፡ አነጋገሥ -የብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ ፍጻሜ

ዓፄ ፡ እስክንድር ፡ በሺ፬፻፹፯ ፡ ዓ.ም ፡ በግንቦት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ያገሊጋያቸውን ፡ የተክላይን-ደም ፡ እበቀላለሁ ፡ ብለው ፡ ሌሊት ፡ ሔደው ፡ ባንድ ፡ ባልታወቀ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ በቀስት ፡ ፍላጻ ፡ ተመትተው ፡ ስለሞቱ ፡ በደብረወርቅ (ጐጃም)ተቀበሩ። በመንግሥታቸው ፡ በሕይወታቸው ፡ ጊዜ ፡ የከዳቸው ፡ ዘሥሉስ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ በኣማራ ፡ አገር ፡ የወደደውን ፡ ለማንገሥ ፡ ሲል ፡ የእስክንድር ፡ ወገኖች ፡ ተቃውመው ፡ እርሱንም ፡ ያልታወቀውንም ፡ ነጋሚ ፡ ማጥፋታቸውን ፡ ያለፈው ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ገልጿል።

ጀምስ ፡ ብሩስ ፤ ባሴት ፡ ረኔ ፤ ዣን ፡ ባቲስት ፤ ኰልቦ ፡ ሌሎቹም ፡ የቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ቀድሞ ፡ ፖርቱጊዞች ፡ እነ ፡ ዳልማይዳ ፡ እነ ፡ ፔር ፡ ቲላዝ ፡ ካጻፉት ፡ ላይ ፡ እየጠቀሱ ፡ ከዜና ፡ መዋዕሉና ፡ ከታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ የሚመስልና ፡ የሚጠቅም ፡ ታሪክ ፡ ያቀርቡልናል።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ እንዳይሸፍት ፡ እየተባለ ፡ የነጋሚው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ እየተያዘ ፡ በአምባ ፡ ግሼን ፡ በዘበኛ ፡ ይጠበቅ ፡ ነበር። ከዚያ ፡ ፩ ፡ ንጉሥ ፡ ሲሞት ፡ አባቱ ፡ የተናዘዘለት ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ክህነቱና ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አለዚያም ፡ ከ፪ ፡ አንዳቸው ፡ የመረጡት ፡ እየወጣ ፡ በኣዋጅ ፡ ይነግሣል።

ስለዚህ ፡ እስክንድር ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ ግማሾቹ ፡ ናዖድን ፡ ከአምባ ፡ ግሼን ፡ አውጥተው ፡ አነገሡ። ንግሥት ፡ ዕሌኒ ፡ ቀኝ ፡ በአልቲሐት ፡ ደግሞ ፡ የዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያምን ፡ ልጅ ፡ የእስክንድርን ፡ ወንድም ፡ ዕንቆ ፡ ፳ኤልን ፡ ለማንገሥ ፡ ኣስበው ፡ ነበር። ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ካዔ ፡ እስክንድር ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ በእንደራሴነት ፡ አገሩን ፡ ሲያስተዳድር ፡ የነበረው ፡ ብሕት ፡ ወደድ (እንደሌሎቹ ፡ ራስ) ዓምዱ ፡ የናዖድን ፡ ንግሥ ፡ ተቃውሞ ፡ ያፄ ፡ እስክንድርን ፡ የ፯ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ እንድርያስ ፡ ይባል ፡ የነበረውን ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ፪ኛ ፡ አሰኝቶ ፡ አነገሠው። ናዖድም ፡ በወገኖቻቸው ፡ ደጋፊነት ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ በብሕት ፡

ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ ተቃዋሚነት ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ኣምባ ፡ ግሼን ፡ ሔደው ፡ ተቀመጡ። የብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ ምኞትም ፡ በእስክንድር ፡ ጊዜ ፡ እንደተደረገው ፡ ለስሙ ፡ የ፯ቱን ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ አንግሦ ፡ እርሱ ፡ በእንደራሴነት ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደቀድሞው ፡ ለማስተዳደር ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ፯ ፡ ወር ፡ እንደገዛ ፡ በድንገት ፡ ስለሞተ ፡ አሳቡ ፡ ሳይሳካለት ፡ ቀረ። ሕዝቡም ፡ ዓምደጽዮንን ፡ በልጅነቱ ፡ ወራት ፡ የቀጨው ፡ የናዖድ ፡ አምላክ ፡ ተቆጥቶ ፡ ነው ፡ ይል ፡ ዝመር። ስለዚህ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ሞቶ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሁከት ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ በ፫ኛው ፡ ቀን ፡ ናዖድን ፡ እንደገና ፡ አምጥተው ፡ አነገሥዋቸው። ስመ ፡ መንግሥታቸውም ፡ አንበሳ ፡ በፀር ፡ ተባለ።

ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ የዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ልጅ ፡ የዓፄ ፡ እስክንድር ፡ ወንድም ፡ መሆናቸውን ፡ የመዝመሪያ ፡ ስማቸው ፡ ቀለዮጳ ፡ እንደነበረ ፡ ሲነግሡም ፡ ዕድሜያቸው ፡ ወደ ፡ ፳፪ ፡ ሊደርስ ፡ እንደሚችል ፡ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ ገልጸናል። ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የእስክንድርንና ፡ የዕንቈ ፡ ፳ኤልን ፡ እናት ፡ ንግሥት ፡ ሮምና (ሮማነ ፡ ወርቅ) መሆናቸውን ፡ ሲገልጽልን ፡ የናዖድን ፡ እናት ፡ አይገልጽም። ምናልባት ፡ ከደንበኛ ፡ ሚስቶቻቸው ፡ ከግራዋ ፡ ወይም ፡ ከቀኟ ፡ በኣልቲሐት ፡ ሳይሆን ፡ ካንዷት ፡ ከተራ ፡ ዕቍባት ፡ ተወልደው ፡ ይሆናል።

የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ በመንግሥታቸው ፡ ከተደላደሉ ፡ በኋላ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱን ፡ አሲዘው ፡ ከአንገቱ ፡ በታች ፡ አስቀብረው ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ኣስነድተው ፡ ገደሉት ፡ ይባላል። ይኸንን ፡ የጭካኔ ፡ ቅጣት ፡ ያደረጉት ፡ መዝመሪያ ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ ተቃውሞ ፡ ስለመለሳቸው ፡ በዚያ ፡ ቂም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ አሁንም ፡ አላሥነግሥ ፡ ብሎ ፡ ሲዋጋ ፡ ተማርኮ ፡ ይሁን ፡ አይታወቅም። ቢሆንም ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ የክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡ ከዚያም ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ መንፈሳዊነት ፡ ያዘነበሉ ፡ መልክአ ፡ ማርያም ፡ የደረሱ ፡ ሆነው ፡ ሳለ ፡ ይኸን ፡ በመሰለ ፡ በኣረመኔ ፡ ቅጣት ፡ ቍጭታቸውን ፡ በመወጣት ፡ ፈንታ ፡ ኣስረው ፡ ወይም ፡ በጦርና ፡ በቀስት ፡ በትር ፡ ቢያስገድሉት ፡ ይበቃ ፡ ነበር። የዚህም ፡ ሁኔታ ፡ በዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ ውስጥ ፡ ቸር ፡ ታጋሽ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ብሎ ፡ የተጻፈላቸውን ፡ ቃል ፡ ያተባብላል።

ምናልባት ፡ ደግሞ ፡ የርሳቸው ፡ ወገኖች ፡ በዓምዱ ፡ ላይ ፡ የተናደዱና ፡ ከቀድሞ ፡ ዝምሮ ፡ የበሰለ ፡ ቂም ፡ ያላቸው ፡ እስከ ፡ ኣንገቱ ፡ ተቀብሮ ፡ በደንጊያ ፡ ተወግሮ ፡ ይሙት ፡ እያሉ ፡ሲያውኩ ፡ አዲሱ ፡ ንጉሥ ፡ ናዖድ ፡ ይኸን ፡ ኣሳብ ፡ መቃወም ፡ ሳይችሉ ፡ እነዚህን ፡ ለማስደሰት ፡ ውግረቱን ፡ ሲሉ ፡ ፈቅደው ፡ ይሆናል።

# ምዕራፍ ፶፮።

## የተካ ፡ ክርስቶስ ፡ ሽፍትነትና ፡ ፍጻሜው--ባለፈ ፡ ኃጢኣት ፡ ሰው ፡ እንዳይወቀስ ፡ የተደረገ ፡ አዋጅ።

ያፄ ፡ ናዖድ ፡ የግዕዝ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ዓፄ ፡ ናዖድን ፡ ቸርታጋሽ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ አድርጎ ፡ ያሳየናል። ባለፈ ፡ ኃጢአትም ፡ ሰው ፡ እንዳይከሰስ ፡ እንዳይወቀስ ፡ መከልከላቸውን ፡ ያስረዳናል። በዚያውስጥ ፡ የተካ ፡ ክርስቶስ ፡ መቃወም ፡ ሲጻፍ ፡ የብሕት ፡ ወደድ ፡ ዓምዱ ፡ አገዳደል ፡ በፍጹም ፡ የለም። ምናልባት ፡ እንደሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ያፄ ፡ ናዖድም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ሙሉ ፡ ሳይሆን ፡ በከፊል ፡ የተጻፈ ፡ በመሆኑ ፡ ይሆናል። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ ይኸንኑ ፡ ያለውን ፡ ግዕዝኛ ፡ ቃል ፡ ትርጕሙን ፡ በአማርኛ ፡ እንመልከት።

«ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የበእደ ፡ ማርያም ፡ ልጅ ፡ የእስክንድር ፡ ወንድም ፡ ጌታችን ፡ ናዖድ ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ነገሡ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አገር ፡ ጸጥ ፡ አለ። ከመንገሣቸው ፡ በፊት ፡ ፩ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚባል ፡ መነኵሴ ፡ ናዖድ ( ፡ ንዑድ ፡ ብዑድ) ይነግሣል ፡ የሚል ፡ ድምጽ ፡ ከሰማይ ፡ ሰማሁ ፡ እያለ ፡ ሲያወራ ፡ ሰምቼው (የጸሐፊው ፡ ቃል ፡ ነው) ሳደንቅ ፡ ነበርሁ። በኋላ ፡ በጊዜው ፡ የዚህ ፡ የመነኵሴ ፡ ቃል ፡ ዕውነት ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘብሁ። ንጉሣችን ፡ ድንቅና ፡ መልካም ፡ መሆናቸውን ፡ ቸርነታቸውንና ፡ ትእግሥታቸውን ፡ ተመለከትሁ። በሃይማኖታቸውና ፡ በግርማ ፡ መንግሥታቸው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በሥርዓት ፡ አደሩ። ኵራተኞች (ዕቡያን) ራሳቸውን ፡ አዋረዱ። ክፋዎች ፡ ተወገዱ። ምርጥ ፡ ሰዎች ፡ ተመኵበት።

አትሮንስ ፡ ማርያም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ወደሸዋ ፡ ለመሄድ ፡ ጉዞ ፡ ዠመሩ። በመንገድ ፡ ተካ ፡ ክርስቶስ ፡ የትዕቢት ፡ ሥራ ፡ ሊሠራባቸው ፡ ዠመረ። ንጉሡ ፡ ናዖድ ፡ ይኸንኑ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በትእግሥት ፡ ዝም ፡ አሉ። ወታደሩንም ፡ ሁሉ ፡ በያገሩ ፡ በፈቃዳቸው ፡ አሰናበቱ። ሸዋ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ይኸው ፡ ተካ ፡ ክርስቶስ ፡ የትዕቢትና ፡ የኃጢአት ፡ ሥራውን ፡ ለመፈጸም ፡ ፈረሱን ፡ እያዘጋጀ? ከወዳጆቹ ፡ ጋር ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ለማመጽ ፡ ምክር ፡ ያዘ። ይኸንንም ፡ ናዖድ ፡ ሰምተው ፡ «ምኞቱን ፡ ይፈጽም ፡ እኛ ፡ እንከተለዋለን ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ስለሆነ ፡ ይረዳናል። በርሱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ መሥራት ፡ እንዳንዠምር ፡ በመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እሱው ፡ ራሱ (**እግዚአብሔር** ፡ ወይስ ፡ ተካ?) ኣስምሎናል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተናግረው ፡ ታግሠው ፡ ዝም ፡ አሉ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ እንዳሉት ፡ ምኞቱን ፡ ለመፈጸም ፡ ተካ ፡ ክርስቶስ ፡ ፈረሰኞቹን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ከወገኖቹ ፡ ጋር ፡ በዚያ ፡ ያሉትን ፡ ጨዋ (ወታደሮች) በዚህ ፡ የክፋት ፡ ሥራው ፡ እንዲተባበሩ ፡ ለማድረግ ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ ይፋት ፡ ሄደ። ወታደሮቹ ፡ ግን ፡ የልቡን-ክፋትናኣመፃ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ይዘው ፡ አሠሩና ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አመጡት። ስለዚህ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ታምነውበት ፡ እንደነበረ ፡ ጠላታቸውን ፡ በተአምራት ፡ እንደጣለላቸው ፡ መመልከት ፡ ነው። ስለዚህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ **እግዚአብሔርን** ፡ አመሰገኑ ፡ ንጉሡ ፡ ግን ፡ ጨርሰው ፡ ሊያጠፉት ፡ ስለኣልፈለጉ ፡ በግዞት ፡ እንዲቀመጥ ፡ አድርገው ፡ ነበር ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ዓይኑን ፡ ኣጠፉት።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ ባፄ ፡ እስክንድር ፡ ዘመን ፡ ይኸን ፡ ሠርቷል ፡ ይኸን ፡ በድሏል ፡ እያለ ፡ ሰው ፡ ርስበርሱ ፡ በመካሰስ ፡ ሁከት ፡ መብዛቱን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ በንጉሣችን ፡ ባፄ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ጊዜ ፡ እገሌ ፡ ይኸን ፡ ኃጢኣት ፡ ሠርቷል ፡ እያላችሁ ፡ አትካሰሱ ፡ ኣንዱ ፡ ጓደኛውን (ሌላውን) እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው (የከሰሰው) ቢኖር ፡ በሞት ፡ ይቀጣ ፡ የሚል ፡ አዋጅ ፡ አወጡ። ሕዝቡ ፡ የዚህን ፡ የኣዋጅ ፡ ትእዛዝ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በውነት ፡ ጥፋት ፡ የሌለበትና ፡ ያልበደለው ፡ ሁሉ ፡ በመካሰሱ ፡ ሁከት ፡ ሆኖ ፡ ነበርና ፡ እንኳን ፡ ይኸንን ፡ አዋጅ ፡ ኣወጡ ፡ እየተባባለ ፡ የንጉሡን ፡

ብልሕነትና ፡ ዕውቀት ፡ አደነቀ። በርስት ፡ ነገር ፡ የተጐዳው ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ እንዲታይለት ፡ አልተከላከለም። »

የፊተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ በጭካኔ ፡ ካፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ዝምሮ ፡ የከበረውን ፡ ታላቀኑን ፡ የመንግሥት ፡ መኰንን ፡ ራስ ፡ ዓምዱን ፡ ሲገድሉ ፡ የመንግሥታቸውን ፡ አዠማመር ፡ በኃይልና ፡ በማስፈራት ፡ የመሠረቱት ፡ ይመስላል። ያሁኑ ፡ ምዕራፍ ፡ ደግሞ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ጸሐፊው ፡ የሚለውን ፡ ሁሉ ፡ ያመንን ፡ እንደሆነ ፡ በተካ ፡ ክርስቶስ ፡ ላይ ፡ ያደረጉት ፡ ትእግሥት ፡ ከዚያ ፡ የተለየ ፡ በልስላሴና ፡ በይቅር ፡ ባይነት ፡ የአስተዳዳሪነት ፡ ሥራቸውን ፡ እንደዠመሩ ፡ ያሳያል። ቢሆንም ፡ ጸሐፊው ፡ ለተካ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደጥፋቱ ፡ ሳይቀጡ ፡ "በግዞት ፡ ኣሠሩት ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ "ጠባቂዎቹ ፡ ዓይኖቹን ፡ ኣጠፉት ፡ ስላለ ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ለተካ ፡ ክርስቶስ ፡ የተደረገለት ፡ ምሕረት ፡ ጐደሎ ፡ ነበር። መሉ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ያለንጉሡ ፡ ቀጥተኛ ፡ ወይም ፡ የጐን ፡ ፈቃድ ፡ የግዞተኛውን ፡ ዓይን ፡ ለለማጥፋት ፡ አይደፍሩም ፡ ነበር። ያለዚያ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ የመኰንኑን ፡ ዓይን ፡ አጥፍተው ፡ ቢገኙ ፡ በዚሁ ፡ ተይዘው ፡ መቀጣት ፡ ነበረባቸው ፡ "ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ መቀጣታቸውን ፡ ስላልገለጸ ፡ እንዲያውም ፡ በንጉሣችን ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ አመጽህ ፡ ብለው ፡ የእስረኛውን ፡ ዓይን ፡ አጥፍተው ፡ እብሪት ፡ የሠሩትን ፡ ጠባቂዎች ፡ ንጉሡ ፡ በመልካም ፡ ዓይን ፡ ተመልክተው ፡ ሳይሸልሟቸው ፡ ኣይቀርም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል።

ምናልባት ፡ ተካ ፡ ክርስቶስ ፡ ብዙ ፡ ወገንና ፡ ተከታይ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ ንጉሡ ፡ ምሕረት ፡ አድርገውለት ፡ ነበር ፡ አላገባብ ፡ ያሣወሩና ፡ የገደሉት ፡ ዘበኞቹ ፡ ናቸው ፡ ሲባል ፡ የንጉሡን ፡ ያስተዳዳሪነት ፡ ፖለቲካ ፡ ሊያበላሽ ፡ አይቻልም ፡ ያመጸኛው ፡ መታወር ፡ ደግሞ ፡ ተከራካሪያቸውን ፡ በማስወገድ ፡ መንግሥታቸው ፡ የጸና ፡ ሲሆን ፡ ዞሮ ፡ ድርብ ፡ ጥቅሙ ፡ የንጉሡ ፡ ከመሆን ፡ አይዘል።

# ምዕራፍ ፡ ፺፯።

## የፈላሾች ፡ ሸፍትነትና ፡ ቅጣት—ስለሃይማኖት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያና ፡ በአውሮፓ ፡ የነበረው ፡ ግፈኛ ፡ ቅጣት።

በታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ በተለይ ፡ ባዔ ፡ ናዖድ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ከሞቱ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ የሞላቸው ፡ ያዔ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዐፅም ፡ ከነበረበት ፡ ቦታ ፡ ወጥቶ ፡ እዳጋ ፡ ደሴት ፡ ሔዶ ፡ መቀመጡን ፡ ዐፅሙ ፡ እተቀበረበት ፡ ምዕራፈ ፡ ጻድቃን (የጻድቃን ፡ ማረፊያ)እሚባለው ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ ከዐፅሙ ፡ ወስጥ ፡ "ይህቺ ፡ ለዘለዓለም ፡ ማረፊያዬ ፡ ነች (ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ምዕራፍየ ፡ ለዓለም)" የሚል ፡ ድምፅ ፡ ስለተሰማ ፡ የጽድቃቸው ፡ ታላቅነትና ፡ ከፍታቸው ፡ መታወቁን ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስም ፡ በዐፅማቸው ፡ ላይ ፡ ለጸለየና ፡ ለተማጠነ ፡ ሰው ፡ ተኣምራት ፡ መደረጉን ፡ ይገልጻል።

ከዚህ ፡ ጋር ፡ ኣያይዞ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ በዘመናቸው ፡ ክርስቲያን ፡ ነን ፡ እያሉ ፡ በሕሊናቸው ፡ **ክርስቶስ** ፡ ከማርያም ፡ መወለዱን ፡ የሚክዱትን ፡ በዓቢይ ፡ ጾም (ሁዳዴ)ዓርብና ፡ ሮብ ፡ በሥውር ፡ እየበሉ ፡ ቍርባን ፡ ከቆረቡ ፡ በኋላ ፡ ለሥጋውና ፡ ለደሙ ፡ ስግደት ፡ የሚገባውን ፡ መልሰው ፡ የሚተፉትን ፡ ርኵሳን ፡ እንደገለጡባቸው ፡ እነዚህን ፡ እንደውሻና ፡ እንደ ፡ ጅብ ፡ የሚቆጠሩትን ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ እንደጣለቻቸው ፡ ካህናቱም ፡ ወንዱም ፡ ሴቱም ፡ ደማቸውን ፡ አፍስሶ ፡ ኣጥንታቸውን ፡ እንደ ፡ ቀጠቀጣቸው ፡ ሥጋቸውንም ፡ የዱር ፡ አውሬ ፡ እንደበላው ፡ በነርሱ ፡ ሞትም ፡ ቀድሞ ፡ የሐኬት ፡ ሥራቸውን ፡ እየሰሙ ፡ ያዝኑ ፡ የነበሩት ፡ ምርጥ ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ እንደ ፡ ዘለሉ ፡ ስለዚህ (ናዖድ) የነርሱንና ፡ የእመቤታችንን ፡ የቅድስት ፡ ንጽሕት ፡ ማርያምን ፡ ሕሊና ፡ እንደ ፡ አሳረፉ ፡ ይገልጽልናል።

ነገር ፡ ግን ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ አዘጋጂው ፡ እነዚህ ፡ የስም ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑት ፡ አይሁዶች ፡ እነማን ፡ መሆናቸውን ፡ ስማቸውን ፡ እንኳን ፡ ባይችል ፡

ነገዳቸውንና ፡ ክፍላቸውን ፡ ሊገልጽ ፡ ይችል ፡ የነበረውን ፡ በፍጹም ፡ አልገለጸውም። ሌላ ፡ እኔ ፡ ያላየሁት ፡ ጽሑፍ ፡ እንዳለ ፡ አላውቅም። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ባፄ ፡ ናዖድና ፡ በልጃቸው ፡ በልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ የነበሩት ፡ እነ ፡ አልቫሬዝ ፡ በፖርቱጋል ፡ ቋንቋ ፡ የጻፉትን ፡ ወደየ ፡ ቋንቋቸው ፡ ተርጕመው ፡ በቅርቡ ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ የጻፉት ፡ እነ ፡ ኸምስ ፡ ብሩስ; እነ ፡ ዣን ፡ ባቲስት ፡ ኰልቦ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ዓይነት ፡ ጽፈውታል።

ባፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዘመን ፡ ማርቆስ ፡ የሚባለው ፡ መኰንን ፡ የጸለምት ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ፈላሾች ፡ ሸፍተው ፡ ስለነበረ ፡ ሊዋጋ ፡ ሔዶ ፡ ዓመት ፡ ከተዋጉት ፡ በኋላ ፡ አሸንፎ ፡ አስገበራቸው። እራሳቸው ፡ ያቃጠሉትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልሶ ፡ ራሳቸውን ፡ አሠርቶ ፡ ከዚያ ፡ አባ ፡ ተከለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚባሉ ፡ መነኵሴ ፡ ሔደው ፡ በግድም ፡ በውድም ፡ እያደረጉ ፡ እዚያ ፡ በተቀመጠው ፡ የንጉሥ ፡ ሹምና ፡ ወታደር (ጨዋ)እየተረዱ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያንነት ፡ ግማሾቹን ፡ መልሰዋቸው ፡ ነበር። እንደዚሁም ፡ የቀሩትን (ምናልባት ፡ እምቢ ፡ ያሉትን) ማርቆስ ፡ በአዋጅ ፡ ለሌላ ፡ ነገር ፡ አስመስሎ ፡ ሰብስቦ ፡ ፈጃቸው። የቀሩትንም ፡ እንደዚሁ ፡ በግዴታም ፡ በውዴታም ፡ እያቈረቡ ፡ ክርስቲያን ፡ አድርገዋቸው ፡ ሳለ ፡ በመካከል ፡ ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ካለፉ ፡ ወዲህ ፡ እነዚሁ ፡ ፈላሾች ፡ የደፈሩት ፡ ወደ ፡ ቀድሞው ፡ ወደ ፡ ይሁዲ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ስለ ፡ ተመለሱ ፡ የፈሩት ፡ ለሰው ፡ ወይም ፡ ለሹም ፡ ይመስል ፡ እየቈረቡ ፡ ከቈረቡ ፡ በኋላ ፡ እየተፉ ፡ ስለቆዩ ፡ ባፄ ፡ ናዖድ ፡ ጊዜ ፡ ተሰብስበው ፡ እንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቀረቡ። ንጉሡም ፡ ጉባዔ ፡ ኣድርገው ፡ ተቀበሏቸውና ፡ **ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር** ፡ ልጅ ፡ ከማርያም ፡ መወለዱንና ፡ አለመወለዱን ፡ ጠየቍዋቸው። እነርሱም ፡ የ**እግዚአብሔር** ፡ ልጅ ፡ ከማርያም ፡ አልተወለደም ፡ ብለው ፡ በገሀድ ፡ መለሱ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ለእመቤታችን ፡ ክብር ፡ ሲሉ ፡ ግማሾቹን ፡ በጦር ፡ ግማሾቹን ፡ በሰይፍ ፡ እያስመቱ ፡ አስፈጅዋቸው።

ስለዚህ ፡ እነዚያ ፡ እመዠመሪያው ፡ ላይ ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የአይሁዶቹን ፡ ዓመፃ ፡ ናዖድ ፡ ገለጡባቸው ፡ እያለ ፡ በደፈና ፡ ያመለከተው ፡ እነዚህ ፡ በወገራና ፡ በሰሜን ፡ በጸለምት ፡ የሚኖሩትን ፡ ፈላሾች ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ይህም ፡ ሁለተኛው ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ በጉባኤ ፡ ማስፈጀታቸውን ፡ የሚገልጸው ፡ ጽሑፍ ፡

ዣን ፡ ባቲስት ፡ ኵልቦ ፡ በ፶፩ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ መጽሐፈ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ የሚባለው ፡ መሆኑን ፡ ገልጸዋል ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አላገኘሁትም።

ቢሆንም ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ምንም ፡ በሃይማኖት ፡ ቢለዩ ፡ እነዚህ ፡ ወገኖቻችን ፡ የሆኑት ፡ የፈላሻ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሕግ ፡ ሳይጥሱ ፡ ግብር ፡ ሳይከለክሉ ፡ ሳይሸፍቱ ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ እምነት ፡ በግልጽ ፡ ባስታወቁበት ፡ ምክንያት ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ የድብደባና ፡ የሞት ፡ ግፍ ፡ ሲሠራባቸው ፡ በጣም ፡ ያሳዝናል። እንደዚሁም ፡ ይበልጥ ፡ የሚያሳዝነው ፡ በዚህ ፡ ባፄ ፡ ናዖድ ፡ ዘመን ፡ በተደረገው ፡ ግፍ ፡ ብቻ ፡ ሳይቆም ፡ በጐንደር ፡ መንግሥትም ፡ በነዓፄ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዘመን (ሺ፭፻፶፬-ሺ፭፻፹፩) ፡ በተከታዮቻቸው ፡ ጊዜም ፡ መሠቃየታቸው ፡ ነው።

ነገር ፡ ግን ፡ ያለፈውን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ዛሬ ፡ የዛሬን ፡ ጊዜ ፡ ወዳለፈ ፡ ዘመን ፡ መውሰድ ፡ አይቻልምና ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ "የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ዛሬ ፡ ተገኝተው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ግፍ ፡ ከመሥራት ፡ በታገዱ ፡ የዛሬም ፡ ነገሥታት ፡ እዚያ ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይኸን ፡ ከመሥራት ፡ ባልተመለሱም ፡ ነበር። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሃይማኖትን ፡ እልህና ፡ ድርቅና ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ የሥልጣኔና ፡ የፍልስፍና ፡ መንፈስ ፡ የእውቀት ፡ መብሰል ፡ በጠቅላላው ፡ የዘመን ፡ መለዋወጥና ፡ የነፃነት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ አለሰለሰው ፡ ፈላሻና ፡ ክርስቲያን ፡ እስላምና ፡ አረማዊ ፡ ባንዲት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤታቸው ፡ ኣብረው ፡ በሰላም ፡ ይኖራሉ። ያለፈው ፡ ሳይጸጽተው ፡ ዛሬ ፡ ሃይማኖትን ፡ አማካኝቶ ፡ ልዩነት ፡ የሚያደርግ ፡ እውነተኛ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሕሊና ፡ ያለው ፡ እውነተኛ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊባል ፡ አይገባውም። በወንጌልም ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያትም ፡ በመልእክትም ፡ **ጌታችንም** ፡ ሐዋርያትም ፡ ስለጠላታቸው ፡ ከመጸለይ ፡ በቀር ፡ ከጠላታቸው ፡ ጋር ፡ መዋጋት ፡ ቀርቶ ፡ መሳደባቸው ፡ ተጽፎ ፡ ኣይገኝም። ይኸም ፡ የሆነው ፡ የዛሬ ፡ ሺ፱፻፵ ፡ ዓመት ፡ ነው። ነገሥታቶቻችን ፡ በሊቃውንትና ፡ በመነኮሳት ፡ እየተደገፉ ፡ ይኸን ፡ የመሰለ ፡ በሃይማኖት ፡ የተነሣ ፡ ግፍ ፡ የሠሩት ፡ ከክርስትና ፡ ወዲህ ፡ ባለው ፡ በሺ፬፻-ሺ፱፻ ፡ ዓ.ም ፡ መካከል ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉም ፡ የሃይማኖቱን ፡ መሥራች ፡ የጌታችንንና ፡ የሐዋርያቱን ፡ ምሳሌ ፡ አልተከተሉም። ጥንት ፡ ኣይሁድ ፡ የ**እግዚአብሔር** ፡

ምርጥ ፡ የአብርሃም ፡ የሙሴ ፡ የዳዊት ፡ ዘሮች ፡ የእመቤታችንና ፡ የሐዋርያት ፡ ወገኖች ፡ ጌታችንን ፡ ገርፈው ፡ አሰቃይተው ፡ ሲገድሉት ፡ **እግዚአብሔርን** ፡ ያገለገሉ ፡ ይመስላቻው ፡ እንደነበረ ፡ እነዚህም ፡ ኢትየጵያውያን ፡ ክርስቲያኖች ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ግፍ ፡ ሲሠሩ ፡ **ክርስቶስ**ንና ፡ እመቤታችንን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ነው። እነዚህም ፡ እነዚያም ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ **ክርስቶስ** ፡ እዳለው ፡ የሚያደርጉትን ፡ አያውቀኍምና ፡ ይቅርታ ፡ ይገባቸዋል። ይኸን ፡ የመሰለው ፡ ሥራ ፡ በዛሬ ፡ አእምሮና ፡ ሕሊናችን ፡ ስሕተት ፡ መሆኑ ፡ የሚታየን ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ በመላው ፡ የክርስቲያን ፡ አገር ፡ ይነስ ፡ ይብዛ ፡ ያለቅርታ ፡ ይሠራ ፡ ነበር።

ግዛቷ ፡ ስፋቷ ፡ ከተዋህዶ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚበልጠው ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍጥር ፡ በሺ፩፻፹፫ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፡ «INQISITION—ምርመራ” ፡ የሚባል ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጕባዔ ፡ ኣቍማ ፡ እንኳን ፡ ጨርሶ ፡ የካደ ፡ በዚያው ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖቱ ፡ ትንሽ ፡ ኑፋቄ (ጥርጣሬ)የተገኘበት ፡ ሁሉ ፡ ወደዚህ ፡ ጉባዔ ፡ እየተያዘ ፡ እየቀረበ ፡ በልዩልዩ ፡ ሥቃይ ፡ ይገደል ፡ ነበር። በኑፋቄው ፡ የጸናውንም ፡ አብዛኛው ፡ ጊዜ ፡ የሚቀጡት ፡ እሚንቀለቀል ፡ እሳት ፡ ላይ ፡ እየጣሉ ፡ በማቃጠል ፡ ነበር። በዚህም ፡ ሥራ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ከኤስፓኝ ፡ ከሌሎቹም ፡ የካቶሊክ ፡ ነገሥታት ፡ ጋር ፡ ኅብረት ፡ ስም ፡ ነበራቸው ፡ የእገሌ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ያጠራጥራል ፡ የተባለውን ፡ ወይም ፡ ተጠርጣሪው ፡ የኔ ፡ እምነት ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የገለጸውን ፡ ሰው ፡ ቀሳውስቱም ፡ ወታደሩም ፡ እየያዙ ፡ ለዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ተወስነው ፡ ለተቀመጡት ፡ ለዶሚኒካን ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ዳኞች ፡ ያቀርቡታል። ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ እየተደበደበ ፡ እየተቃጠለ ፡ በሥቃይ ፡ የሚሞተው ፡ ብዙ ፡ ነበር። በዚህ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ስሙ ፡ የተጠራው ፡ የኤስፓኝ ፡ ኣገርና ፡ በዚያ ፡ ያሉ ፡ ቀሳውስት ፡ ናቸው። ይህ ፡ «INQISTION ፡ ምርመራ” የሚባለው ፡ የቀሳውስት ፡ ጉባዔ (ችሎት) እስከ ፡ ናፖሌዎን ፡ ዘመነ ፡ መንግምት ፡ ድረስ ፡ እየተሠራበት ፡ ዘልቆ ፡ እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ቍ ፡ ሺ፰፻፰ ፡ በሕግ ፡ ከሻረው ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ እስከ ፡ ሺ፰፻፴፬ ፡ ዓ.ም ፡ ቀጥሎ ፡ ሳለ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የአሳብና ፡ የሃይማኖት ፡

ነፃነት ፡ ሕዝቡ ፡ እየጠየቀ ፡ በአዋጅ ፡ ሲሰጠው ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ የዚህ ፡ ምርመራና ፡ ግፍ ፡ በፍጹም ፡ በሕግ ፡ ተከልክሎ ፡ ቀረና ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይሻለኛል ፡ ብሎ ፡ ላሕሊናው ፡ መርጦ ፡ የያዘውን ፡ ሃይማኖት ፡ እንደልቡ ፡ በሰላም ፡ ያመልክ ፡ ዠመር። በኛም ፡ ዘንድ ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ ከሺ፰፻፹፪ ፡ ዓ.ም ፡ ወዲህ ፡ እየቀዘቀዘ ፡ ሄዶ ፡ ዛሬ ፡ ጨርሶ ፡ መጥፋቱ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል።

# ምዕራፍ ፡ ፵፰።

## ባፄ ፡ ናዖድና ፡ በማሕፉድ ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ጦርነት።

ስለ ፡ ኣዳሎች ፡ ጦርነት ፡ እስካሁን ፡ ያገኘሁት ፡ ያፄ ፡ ናዖድ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ አይናገርም። ነገር ፡ ግን ፡ መዋጋታቸው ፡ በሌሎች ፡ ጸሐፊዎች ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ሆኗል። በዚህም ፡ ዘመን ፡ የይፋት ፡ ወላስማ ፡ ባላባቶች ፡ መቀመጫቸውን ፡ በይፋት ፡ ድንበር ፡ በዳካር ፡ ሳይመቻቸው ፡ ወደ ፡ አዳል ፡ ኣገርና ፡ ወደ ፡ ዘይላ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩት ፡ በኣሁኑ ፡ ሰዓት ፡ መቀመውጫቸውን ፡ ወደ ፡ ሐረርጌ ፡ አዙረዋል። ግማሾቹ ፡ ግን ፡ በዚያው ፡ በወላስማ ፡ ባንደኛው ፡ ቅርንጫፍ ፡ ዘር (መሐመድ?) እየተመሩ ፡ በኣዳል ፡ አገር ፡ ቀርተዋል። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ግዛት ፡ ወደ ፡ ባሊ ፡ ወደዋሮ ፡ እየመጡ ፡ አገር ፡ በመውረር ፡ በመዝረፍ ፡ ስማቸው ፡ የሚጠራው ፡ አቡበክርና ፡ ማሕፉዝ (ማሕፉድ)ናቸው። አቡበከር ፡ በዘሩ ፡ ሐረግ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ነው። ግዛቱንም ፡ ከኣዳል (ዳካር)ወደ ፡ ሐረርጌ ፡ ያዞረ ፡ እርሱ ነው። ማሕፉዝ ፡ የአቡበከርን ፡ ወንድም ፡ የባረካትን ፡ ልጅ ፡ ያገባል ፡ ከነዚህ ፡ ከሁለቱም ፡ ጋብቻ ፡ ባቲ ፡ ድል ፡ ወምባራ (ባቲያ ፡ ዴል ፡ ዋኣምባራ) የምትባለው ፡ ስመ ፡ ጥሩይቱ ፡ የግራኝ ፡ አህመድ ፡ ሚስት ፡ ተወለደች። የርሷንም ፡ ሥራ ፡ ወደፊት ፡ በሚታተመው ፡ በ፫ኛው ፡ መጽሐፍ ፡ በግራኝና ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ እናነባለን።

ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ በዘመናቸው ፡ እንደ ፡ አባቶቻቸው ፡ ከእስላሞቹ ፡ ጋር ፡ እየተዋጉ ፡ የበላይነት ፡ ማሳየታቸውን ፡ ሳይለቀሉ ፡ ደግሞ ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ነገሩ ፡ የሚቃናበትን ፡ የጋብቻ ፡ መንገድ ፡ ፈለጉ። የዚህንም ፡ ምሳሌ ፡ የወሰዱት ፡ ካያታቸው ፡ ካፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ካባታቸው ፡ ከዓፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ ነው። ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ በእስላሞቹና ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ መካከል ፡ ሰላም ፡ እንዲመሠረት ፡ የዘመኑን ፡ የጋብቻ ፡ ዘዴ ፡ በመከተል ፡ የሐድያውን ፡ ባላባት ፡ የገራድ ፡ መሐመድን ፡ እኅት ፡ እስላሚቱን ፡ ክርስትና ፡ አስነሥተው ፡ ኣግብተው ፡ እንደአባታቸው ፡ "ንግሥት ፡ ዕሌኒ ፡ ቀኝ ዕ ፡ በዓልቲሐት ፡ አሰኝተው ፡ ኣብረው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር። ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ሚስቱን ፡ ንግሥት ፡ ዕሌኒን ፡ እንደናቱ ፡ ይወዳት ፡ ነበር ፡ ሲል ፡ ዜና ፡ መዋዕሉ ፡ የገለጸልን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከወላስማ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ መሆኑ ፡ ባይገለጽ ፡ የእስላም ፡ ተወላጅ ፡ ነበሩ። እኝህም ፡ ንግሥት ፡ ዕሌኒ ፡ ወደፊት ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ እንደምናገኘው ፡ ለመንግሥቱ ፡ ሞግዚትም ፡ መሪም ፡ መካርም ፡ ሆነው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ያገለገሉ ፡ ታላቅ ፡ ሴት ፡ መሆናቸውን ፡ ወደፊት ፡ በሚታተመው ፡ ባፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንመለከታለን።

ስለዚህ ፡ ኣሁንም ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ የደዋሮውን ፡ ገራድ ፡ የእስላሙን ፡ ልጅ ፡ ክርስትና ፡ በተነሡበት ፡ ቀን ፡ ስማቸውን ፡ እንዳባቶቻቸው ፡ ዕሌኒ ፡ ኣሰኝተው ፡ በሕግ ፡ አገቡ። እኚሁም ፡ ሴት ፡ ሥርዓተ ፡ ንግሥ ፡ በተደረገላቸው ፡ ቀን ፡ ናዖድ ፡ ሞገሳ ፡ የሚባል ፡ ስመ ፡ መንግሥት ፡ ተሰጣቸው።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ በክርስቲያኖቹና ፡ በእስላሞቹ ፡ መካከል ፡ ነዋሪ ፡ ሰላም ፡ ሊመሠርት ፡ አልቻለም። የደዋሮው ፡ የሐድያው ፡ ባላባትና ፡ እስላሞች ፡ በሰላም ፡ ሲገዙ ፡ ሌላው ፡ በአዳልና ፡ በሐረርጌ ፡ ያለው ፡ የወላስማ ፡ ዘር ፡ ያንኑ ፡ ያባቶቹን ፡ ቂም ፡ ለመወጣት ፡ ወይም ፡ ከክርስቲያኖቹ ፡ የግዛት ፡ ቀንበር ፡ ነጻ ፡ ለመውጣት ፡ የእስላም ፡ ነክነት ፡ ያላቸውንም ፡ አገሮች ፡ ይፋትን ፡ ደዋሮን ፡ ሐድያን ፡ ባሊን ፡ ነፃ ፡ አውጥቶ ፡ በነዚህ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ሥልጣኑን ፡ ለመዘርጋት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደደከመ ፡ ነው። አሁንም ፡ ከነ ፡ አልባሬዝ ፡ ጥንታዊ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እያገኙ ፡ በጻፉት ፡ በጀምስ ፡ ብሩስ ፡ ፪ኛ

፡ ሾሊም ፡ ገጽ ፡ ፻፳፰-፻፴፪ ፡ በዣን ፡ ባቲስት ፡ ኰልቦ ፡ ፩ኛ ፡ ሾሊም ፡ ገጽ ፡ ፵፰-፶ ፡ እንደሚገኘው ፡ ማሕፉዝ ፡ የኣጻሉ ፡ ንጉሥ ፡ በያለበት ፡ አገር ፡ እየዘረፈ ፡ ባስቸገረ ፡ ጊዜ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ የነበሩትን ፡ እስላሞች ፡ እየሰለሉ ፡ ወሬ ፡ ከማቀበልና ፡ ከመጕዳት ፡ በቀር ፡ ሊጠቅሙኝ ፡ አይችሉም ፡ ብለው ፡ በያገራቸው ፡ አሰናብተው ፡ ምርጥ ፡ የሆነውን ፡ የክርስቲያን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ማሕፉዝን ፡ ለመውጋት ፡ ሔዱ። ማሕፉዝም ፡ ጦሩን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለመግጠም ፡ ወደፊት ፡ ኣመራ። ይህ ፡ ጥር ፡ ዓቢይ ፡ ጾም (ሁዳዴ)የነበረበት ፡ ወር ፡ ስለነበረ ፡ የክርስቲያኑ ፡ ወታደር ፡ በሁዳዴ ፡ ጾም ፡ ይልቁንም ፡ ሰዓት ፡ ሳይደርስ ፡ እህል ፡ እንደማይቀምስ ፡ ስለሚያውቅ ፡ ማሕፉዝ ፡ ገሥግሶ ፡ በጾም ፡ የደከመውን ፡ ወታደር ፡ ሊወጋ ፡ መጣ። የዚህንም ፡ ወሬ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በጦርነት ፡ ሰዓት ፡ ወታደር ፡ ኣይጾምምና ፡ ብሉ ፡ ብለው ፡ ፈቀዱ። ኣባ ፡ እንድርያስ (ገብረ ፡ ታድርያስ-ገብረ ፡ እንድርያስ?) የሚባሉት ፡ መነኰሴም ፡ በመንፈሳዊ ፡ አባትነት ፡ ወታደሩ ፡ በዚህ ፡ በጦርነት ፡ ሰዓት ፡ በልቶ ፡ በሰላሙ ፡ ቀን ፡ ንስሐ ፡ ገብቶ ፡ ለመጾም ፡ እንደሚችል ፡ ኣስገነዘቡና ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ለጦርነት ፡ ተሳለፉ።

ጦርነቱ ፡ ከመዠመሩ ፡ በፊት ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ የጦርነት ፡ ዘዴ (መላ) ያውቁ ፡ ስለነበረ ፡ ብዙውን ፡ ጦር ፡ ወደኋላ ፡ ሸሽገው ፡ ኣስቀርተው ፡ ቲንሽ ፡ ጦር ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ ወደፊት ፡ እንዲቀድም ፡ አደረጉ። የማሕፉዝ ፡ ወታደሮችም ፡ እኋላ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ ሳይጠረጥሩ ፡ ወደፊት ፡ የቀደመውን ፡ ጦር ፡ በቀላሉ ፡ ለማሸነፍ ፡ ከማሕፉዝም ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይጠብቁ ፡ ውጊያ ፡ ዠመሩ። ውጊያው ፡ መዠመሩን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እኋላ ፡ የነበረው ፡ ያፄ ፡ ናዖድ ፡ ጦር ፡ ደረሰና ፡ የእስላሞቹን ፡ ጦር ፡ ፈጀው።

ስለዚህ ፡ ማሕፉዝ ፡ የጦሩን ፡ መመታት ፡ መማረክና ፡ መሞት ፡ ሸሽተው ፡ ከተረፉት ፡ ከጥቂቶቹ ፡ ወገኖቹ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አዝኖ ፡ ተመለሰ። እርሱም ፡ እስከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የማይበገር ፡ ዠግና ፡ እየተባለ ፡ በእስላሞቹ ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ነበረውና ፡ ተሸንፎ ፡ መመለሱ ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ መገረምንም ፡ ፍርኀትንም ፡ አሳደረበት። ስለዚህ ፡ መሐመድ? የሚባለው ፡ የአዳሉ ፡ ሱልጣን ፡ ናዖድ ፡ ማሕፉዝን ፡ ኣሸንፎ ፡ ወደኔ ፡ መምጣቱ ፡ ኣይቀርም

፡ ብሎ ፡ በመላክተኛ ፡ በኵል ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለዎት ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ላከ። ቀጥሎም ፡ ባፄ ፡ ናዖድና ፡ በርሱ ፡ በኵል ፡ የተደረገውን ፡ የሰላም ፡ ቃል ፡ አስታውሶ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ እንዳይመጡበት ፡ አሳሰበ። ዓፄ ፡ ናዖድም ፡ ባንተ ፡ ውስጥ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ያሉትን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ስጠኝና ፡ ኣልመጣብህም ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ጨምረው ፡ መላክተኞቹን ፡ መለሱዋቸው። ክርስቲያኖቹን ፡ የሚያስረክብበትንም ፡ ጊዜ ፡ ወስነው ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ሰጡት።

ስለዚህ ፡ ያዳሉ ፡ ሱልጣን ፡ ይኸን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከወገኖቹ ፡ ተማክሮ ፡ ከ፴ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከየጦርነቱ ፡ እየተማረኵ ፡ በዘረፋም ፡ በመሸጥም ፡ በመሸፈትም ፡ እየሔዱ ፡ በግዛቱ ፡ የነበሩትን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ላካቸው። ንጉሡም ፡ እነርሱን ፡ ይዘው ፡ በድል ፡ ኣድራጊው ፡ ወታደራቸው ፡ ታጅበው ፡ በታላቅ ፡ ክብርና ፡ ደስታ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ተመለሱ።

ይኸን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ የአዳል ፡ የጦርነት ፡ ምንጭ ፡ የሰጡ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ስማቸውን ፡ ያነሣናቸው ፡ የፖርቱጋል ፡ ጸሐፊዎች ፡ ናቸው። ለዓፄ ፡ ናዖድም ፡ ይኸ ፡ ድል ፡ አድራጊነት ፡ የመጨረሻ ፡ ድል ፡ ነው። ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ለክርስቲያኑ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥትና ፡ ለሕዝቡ ፡ የጨለማ ፡ ጊዜ ፡ ነው። ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ኣልፈው ፡ ልጃቸው ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ በነገሡበት ፡ ዘመን ፡ ሲዋጉ ፡ ሲሸነፉ ፡ ሲሸሹ ፡ ሲማረኵ ፡ አምነው ፡ ሲገዙ ፡ ሸፍተው ፡ ትግላቸውን ፡ ሲቀጥሉ ፡ የኖሩት ፡ እስላሞች ፡ በግራኝ ፡ መሪነት ፡ ሕብረት ፡ አድርገው ፡ ከዐረብና ፡ ከዘቢድ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ የወታደር ፡ እርዳታ ፡ ይዘው ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግልን ፡ ከነጦራቸው ፡ አሸንፈው ፡ አገሪቱን ፡ ወርረው ፡ ኣብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ኣቃጥለው ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ የኖረ ፡ ጥቃታቸውንና ፡ ቍጭታቸውን ፡ ሲወጡ ፡ ወደፊት ፡ እንመለከታለን።

# ምዕራፍ ፡ ፶፱።

## ኣምባ ፡ ግሼንና ፡ የነጋሢ ፡ ልጆች ፡ የቤተ ፡ ማርያምና ፡ የመርጡ ፡ ለማርያም ፡ ሥራ-ዓፄ ፡ ናዖድ፡ለቤተ ፡ ማርያም ፡ የሰጡዋቸው ፡ መጻሕፍት።

ባለፈው ፡ እንደተገነዘብነው ፡ ሁሉ ፡ የነገሥታቱ ፡ ልጆች ፡ እንዳይሸፍቱ ፡ እየተባለ ፡ በአምባ ፡ ግሼን ፡ በጠባቂ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አምባ ፡ ግሼን ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አምባ ፡ ነገሥት ፡ ይባላል። በዚያም ፡ ሲኖሩ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከተራራው ፡ ወርደው ፡ እንደልባቸው ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ የማለት ፡ ነጻነት ፡ ባያገኙ ፡ በዚያው ፡ ባሉበት ፡ ለነጋሢ ፡ ልጆች ፡ የሚገባው ፡ አክብሮትና ፡ ኣስተያየት ፡ አይጐድልባቸውም። ከእነዚህም ፡ የነገሥታት ፡ ልጆች ፡ ውስጥ ፡ ለቀለም ፡ ዝንባሌው ፡ ያላቸው ፡ ዜማ ፡ ቅኔ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ ሁሉ ፡ እየተማሩ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሊቅ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ነገሥታት ፡ ይወጡበታል።

ስለዚህ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድም ፡ በወንድማቸው ፡ ባፄ ፡ እስክንድር ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በአምባ ፡ ግሼን ፡ ሲማሩ ፡ የኖሩ ፡ ሊቅ ፡ መሆናቸውን ፡ ወደፊት ፡ የምንመለከታቸው ፡ ቅኔዎቻቸው ፡ ያስረዱናል።

እነ ፡ ፓኤዝ ፤ እነ ፡ ዳልማይዳ ፡ የጻፉት ፡ በካሪ ፡ ባንድነት ፡ ሰብስቦ ፡ ያሳተመው ፡ ዣን ፡ ባቲስት ፡ ኵልቦ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ተርጒመው ፡ የጠቀሱት ፡ እንደሚያስረዳው ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ከዚህ ፡ ከአምባ ፡ ግሼን ፡ ወጥተው ፡ በዙፋን ፡ ተቀምጠው ፡ በሚያስተዳድሩበት ፡ ጊዜ ፡ ከዕለታት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ንጉሡና ፡ ሹሞቻቸው ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ በሚነጋገሩበት ፡ ጊዜ ፡ ከናዖድ ፡ ልጆች ፡ አንዱ ፡ ገባና ፡ ያልሆነ ፡ ንግግር ፡ ተናገረ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከሹሞቹ ፡ አንዱ ፡ "ይህ ፡ ልጅ ፡ ኣደገ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ አሰፈው ፡ እኮ" ቢል ፡ ልጁ ፡ ደነገጠና ፡ አወን ፡ ለአምባ ፡ ግሼን ፡ ደርሻለሁ› ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ልባቸው ፡ በኀዘን ፡ ተነከቶ ፡ ከልጆቼ ፡ ማንንም ፡ ወደ ፡ አምባ ፡ ግሼን ፡ አልሰድም ፡ ብለው ፡ በሹሞቻቸው ፡ ፊት ፡ ማሉ ፡ እርሳቸውም ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ይኸን ፡ ቃላቸውን ፡ ጥሰው ፡ ልጆቻቸውን ፡ ወደ ፡ አምባ ፡ ግሼን ፡

እንዳይልኵባቸው ፡ መኳንንቱን ፡ አስምለው ፡ ቃል ፡ አስገቡዋቸው ፡ ይባላል። ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ከልብነ ፡ ድንግልና ፡ ከሶስቱ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ከወለተ ፡ ቀለምሲስ ፤ ከራስ ፡ ደጋልሃን ፡ ሚስት ፡ ከዓመት ፡ ድንግል ፤ ቅጥ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ እንዳላቸው ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ የለምና ፡ ሹሙ ፡ "ይኸ ፡ ልጅ ፡ ኣደገ" ያላቸውም ፡ አወን ፡ አድጌ ፡ በኣምባ ፡ ግሼን ፡ ለመታሠር ፡ ደርሻለሁ ፡ ብላው ፡ ያለቀሱትም ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል (ዳዊት)መሆናቸው ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ በደኅና ፡ አያያዝ ፡ ቢቀመጡ ፡ ለኑሮው ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሁሉ ፡ ባይጐልባቸውም ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ እንደልብ ፡ ነጻነት ፡ ከሌላቸው ፡ ሁሉም ፡ ከንቱ ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡ አተራረክ ፡ የአምባ ፡ ግሼን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ኑሮ ፡ የነጋሢዎቹን ፡ ልጆች ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንዳስመረረው ፡ ያስረዳል። ከሁሉ ፡ የበለጠ ፡ የዚያን ፡ ኑሮ ፡ የሚያውቍት ፡ ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ግን ፡ በንጉሥ ፡ ነገሥትነት ፡ ዙፋን ፡ የተቀመጡት ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ይኸን ፡ ሕግ ፡ ለመሻር ፡ ሞክረዋል። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ሳያከበር ፡ ከግራኝ ፡ ወዲህ ፡ በጐንደር ፡ መንግሥት ፡ የነገሥታት ፡ ልጆች ፡ በተወሰነ ፡ ሥፍራ ፡ ተገድደው ፡ መቀመጣቸው ፡ አልቀረም።

ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ በዘመናቸው ፡ በዚህ ፡ በኣምባ ፡ ግሼን ፡ ለኖሩበት ፡ መታሰቢያ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ እነ ፡ እራስ ፡ ዓምዱ ፡ ያወኳቸው ፡ ጊዜ ፡ ላባቴ ፡ ዙፋን ፡ ያበቃሽኝ ፡ እንደሆነ ፡ መቅደስ ፡ እሠራልሻለሁ ፡ ብለው ፡ ተስለው ፡ እንደሆነ ፡ አይታወቅም። በዘመናቸው ፡ በዚሁ ፡ በኣምባ ፡ ግሼን ፡ ተራራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእመቤታችን ፡ ስም ፡ ለማሠራት ፡ መሣሪያውና ፡ እንጨቱ ፡ በስንት ፡ ችግር ፡ ተራራውን ፡ እየወጣ ፡ እንዲሠራ ፡ ኣዘዙ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ከማለቁ ፡ በፊት ፡ እርሳቸው ፡ ስለሞቱ ፡ ልጃቸው ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ አስጨርሰው ፡ የእመቤታችንን ፡ ታቦት ፡ አስገቡላቸው። የቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ሥራውና ፡ ዓይነቱ ፡ ክብነቱ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንደሚገኘው ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጎልጎታ ፡ ይመስላል። ሠራተኞቹንም ፡ ከግብፅ ፡ ድረስ ፡ አስመጥተው ፡ አሠሩት ፡ ሲሉ ፡ እነ ፡ ዳልሜይዳ ፡ በሰፊው ፡ መጻፋቸውን ፡ ከኰልቦ ፡ መጽሐፍ ፡ ፶፫ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ መመልከት ፡ ነው።

# ምዕራፍ ፡ ፳፩።

## አፄ ፡ ናዖድ ፡ በዘመናቸው ፡ የተቀኙዋቸው ፡ ቅኔዎች።

ከይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ዠምሮ ፡ ከነገሡት ፡ ነገሥታት ፡ ውስጥ ፡ አፄ ፡ ኣምደ ፡ ጽዮን ፡ ፩ኛ ፡ አፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ፩ኛ ፡ ወደ ፡ ወታደርነት ፡ ወደ ፡ ኣርበኝነት ፡ ዓፄ ፡ ዳዊት ፡ ዓፄ ፡ ይሥሐቅ ፡ ዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ከአርበኝነት ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ መንፈሳዊነት ፡ ያዘነበሉ ፡ ይመስላል። ይህንንም ፡ የምንልበት ፡ ምክንያት ፡ እነዚያን ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱና ፡ ዜና ፡ መዋዕላቸው ፡ ጥብቅ ፡ ተዋጊነታቸውን ፡ ሲተርክልን ፡ የነዚህን ፡ ከተዋጊነት ፡ ጋር ፡ ስለመጽሓፍ ፡ ስለመንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ ያላቸውን ፡ ዝንባሌና ፡ ዕውቀት ፡ እየጨመረ ፡ ይገልጽልናል።

አብዛኛ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ተምረው ፡ ቅኔ ፡ ተቀኝተው ፡ ድርሰት ፡ ደርሰው ፡ የምንመለከታቸው ፡ ነገሥታት ፡ ባባቶቻቸው ፡ ወይም ፡ በወንድሞቻቸው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ኣገር ፡ እንዳያውኩ ፡ እየተባለ ፡ በአምባ ፡ ግሼን ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ እንደ ፡ ግዞት ፡ ሲቀመጡ ፡ ረዥም ፡ የመማሪያ ፡ ጊዜ ፡ እያገኙ ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ ቀድሞ ፡ የተማሩትን ፡ ሲሠሩበት ፡ እየተገኙ ፡ ነው። መጻሕፍት ፡ እመማር ፡ ድርሰት ፡ እመድረስ ፡ የማይደርሱት ፡ ደግሞ ፡ አባታቸው ፡ ወንድማቸው ፡ በልጅነታቸው ፡ ዘመን ፡ ይሞትና ፡ እነሱን ፡ በቶሎ ፡ ስለሚያነግሡዋቸው ፡ ከነገሡም ፡ በኋላ ፡ የመንግሥቱ ፡ የመሪነት ፡ ሐተታና ፡ ጣጣ ፡ የመማሪያ ፡ ጊዜ ፡ ስለማይሰጣቸው ፡ ነው። ነገር ፡ ግን ፡ ደግሞ ፡ በነዚህ ፡ መካከል ፡ በጠባዩ ፡ የቀለም ፡ መንፈስ ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ በልጅነቱም ፡ ሳላ ፡ ከነገሠም ፡ በኋላ ፡ ሊማር ፡ ይችላል። የቀለም ፡ መንፈስ ፡ የሌለው ፡ እንደሆነ ፡ ረዥም ፡ የመማሪያ ፡ ጊዜ ፡ ቢያጋጥመውም ፡ በጊዜው ፡ የማይጠቀም ፡ መኖሩን ፡ አንዘነጋምና ፡ አሁን ፡ የዚህን ፡ ጉዳይ ፡ እንተወው።

ዓጼ ፡ ናዖድ ፡ ግን ፡ በአምባ ፡ ግሼን ፡ ባሉበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ያገራችንን ፡ ትምህርት ፡ በየደረጃው ፡ ተምረው ፡ ኖሮ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥቱ ፡ መልክኣ ፡ ማርያም ፡ መድረሳቸውን ፡ ይገልጻል። ይህ ፡ መልክአ ፡ ማርያም ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትና ፡ ገዳማት ፡ በየበዓሉ ፡ ቀን ፡ እየታደለ ፡ የሚደገመው ፡ ምዕመናን ፡ ሁሉ ፡ የሚጸልዩበት ፡ እንደሆነ ፡ ለእመቤታችን ፡ ከራሷ ፡ ዠምሮ ፡

ለየአንዳንዱ ፡ አባሏ ፡ ሙገሳና ፡ ምስጋና ፡ እያቀረቡ ፡ ያሳኮት ፡ ግዕዝኛ ፡ ግጥም ፡ በውነት ፡ ሊቅነታቸውን ፡ ያስረዳል።

ከዚሁ ፡ ድርሰት ፡ ጋር ፡ የተመሳሰሉ ፡ በዘመናቸው ፡ የተቀኙዋቸው ፡ ቅኔዎች ፡ ደግሞ ፡ በመጽሐፍ ፡ ረገድ ፡ ዕውቀታቸው ፡ የዘለቀ ፡ እንደነበረ ፡ ይታወቃል። በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ባለፈው ፡ እንደጻፍነው ፡ በአምባ ፡ ግሼን ፡ የእመቤታችንን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማሠራት ፡ ዠምረው ፡ እንደነበረ ፡ ስናውቅ ፡ ለእመቤታችን ፡ መልክ ፡ መድረሳቸውን ፡ ስንመለከት ፡ በተለይ ፡ እመቤታችንን ፡ ከልብ ፡ ይወዱና ፡ ያምኑ ፡ እንደነበረ ፡ ያስረዳል። አሁንም ፡ ከቅኔዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ ለእመቤታችን ፡ የተቀኙዋቸው ፡ ናቸው።

ምናልባት ፡ የቅኔው ፡ ምሥጢርና ፡ ኣካሄድ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ በጐንደርና ፡ በጐጃም ፡ በሸዋ ፡ ከሚደረሰው ፡ ቅኔ ፡ ደረጃው ፡ ያነሠ ፡ ይሆናል" ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንደዘመኑ ፡ ርቀት ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ በብዙ ፡ ሥራና ፡ ኣስተዳደር ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ የተደረሰ ፡ የንጉሥ ፡ ቅኔ ፡ በመሆኑ ፡ ንጉሡን ፡ " ፡ በጣም ፡ ያስመሰግናቸዋል ፡ እንጂ ፡ የቀለም ፡ ሰውነታቸውን ፡ ኣይቀንስባቸውም። ከርሳቸውም ፡ በፊት ፡ በድርሰት ፡ በኵል ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብን ፡ ከመመልከት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ የተቀኘው ፡ ቅኔ ፡ ባለመገኘቱ ፡ በታሪክና ፡ በጽሑፍ ፡ ረገድ ፡ በዚያው ፡ እንደ ፡ ዘመኑና ፡ እንደመጠኑ ፡ ለዚህ ፡ ላፄ ፡ ናዖድ ፡ ቅኔዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ልንሰጣቸው ፡ ይገባል።

እነዚህ ፡ ቅኔዎች ፡ የሚገኙበት ፡ መጽሐፍ ፡ ገድለ ፡ ፋሲለደስ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፍ ፡ በተለይ ፡ ስለ ፡ ኣባ ፡ ኖብ ፡ ገድል ፡ እሚናገረው ፡ ውስጥ ፡ ነው። ይኸም ፡ መጽሐፍ ፡ ሎንዶን ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ስለሚገኝ ፡ ምስተር ፡ ራይት (M. RIGHT) ፡ ቊጥር ፡ <u>፪፻፹፪</u> ፡ ሰጥተው ፡ ካታሎጉን (ዝርዝሩን) ኣውጥተውታል።

ከወደ ፡ መዠመሪያው ፡ ላይ ፡ ሥላሴ ፡ ዘንጉሥነ ፡ ናዖድ ፡ ወበጺጋ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ዘተሰምየ ፡ አንበሳ ፡ በፀር ፡ ዘተቀንየ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ አመ ፡ ፩ ፡ ለመጋቢት ፡ በበዓለ ፡ ልደታ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም» ፡ ይላል። ስለዚህ ፡ ቅኔውን ፡ የተቀኙት ፡ በተጉለት ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ ቤተ ፡

ክርስቲያን ፡ የእመቤታችን ፡ በዓል ፡ በዋለበት ፡ ቀን ፡ መሆኑ ፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ ግማሾቹ ፡ "ምድረ ፡ ዘብር (መንዝ) ምድረ ፡ ወይ? ፡ በሚባሉ ፡ ኣገሮች ፡ የተቀኙዋቸው ፡ አሉ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ቅኔዎቹን ፡ እንመልከት

## ፩ኛ

## ሥላሴ ፡ ዕዝል።

መሶበ ፡ ወርቅ ፡ ንጽሕት ፡ መሥዋዕተ ፡ ኣዕርጎ
እሳተ ፡ አርያም ፡ ሠምረ ፡ በማኅፀንኪ ፡ ይሠጎ
ለኣእምሮ ፡ ጥበብ ፡ ተረወይኒ ፡ ሕጎ፡
በዓለ ፡ ልደትኪ ፡ ዮም ፡ ማርያም ፡ ለሕሊናየ ፡ መዘጎ
በቅድመ ፡ ሕዝብ ፡ በአንገልጎ፡
ስብሐተኪ ፡ እሕሊ ፡ በኢያንትጎ፡
ኣእትቲ ፡ እምዐውድየ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ፁጎ።

## ፪ኛ

## ዘበዓለ ፡ መስቀል

## ክ ፡ ዕ።

ነጸርኰ ፡ ብእሴ ፡ ከመ ፡ ርእየተ ፡ ብርት ፡ ርሱን፡
ኀላት ፡ ዘዐቅም ፡ ጸዊሮ ፡ በእዴሁ ፡ ዘይምን፡
በትንቢት ፡ ዘይቤ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ምዕመን፡
ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ እደ ፡ መስቀሉ ፡ ለመድኅን፡
ዘተረከበ ፡ በጎልጎታ ፡ በፍጻሜ ፡ ሰንበት ፡ ሳምን፡
ኮኖሙ ፡ ለክርስቲያን ፡ ቀጸላ ፡ ስብሐት ፡ ዘሥን።

## ፫ኛ

## ክ ፡ ዕ።

ቀስተ ፡ መከርካዕ ፡ ጽኑዓ ፡ ወበትረ ፡ ለውዝ ፡ ኅሩያ፡
በእንተ ፡ መስቀሉ ፡ ለወልድ ፡ ነጸረ ፡ ወርእየ፡
ኤርምያስ ፡ ካህን ፡ በዘመነ ፡ አሪት ፡ ተነበየ፡
ዝኬ ፡ አስተርአየ ፡ እለ ፡ አመ ፡ ነ ፡ ቦቱ ፡ አድማዕነ ፡ ናህየ
ወእለ ፡ ጸልእዎ ፡ ረከቡ ፡ ሥቃየ፡
ለአእርፎ ፡ ሕዝቡ ፡ አቀመ ፡ ሰንበታተ ፡ ተስፋ ፡ ዕሩየ
ፍሬሁ ፡ ጥዑም ፡ ወምሉእ ፡ ኮነኒ ፡ ሲሳየ፡
ነቅዐ ፡ ቅድሳት ፡ ረዊውየ ፡ ኪያሁ ፡ ተመርጕዝየ፡

ስብሐቶ ፡ ይነብብ ፡ ወትረ ፡ ኣደየ፡

**፬ኛ**
**አመ ፡ ፳ ፡ ወ፩ ፡ ለመጋቢት፡**
**ሥ ፡ ዕ።**

ኣመ ፡ አበሰ ፡ ወጌገየ ፡ ቀዳሜ ፡ ልሕኵት ፡ አዳም ፡ ወሬዛ፡
ለሔዋ (ን) ብእሲቱ ፡ እንዘ ፡ ይተልው ፡ ግዕዛ፡
ዘእንበሌኪ ፡ ማርያም ፡ ኢረከበ ፡ ቤዛ።
ሰዋስወ ፡ ትንቢት ፡ አንቲ ፡ ዘምድረ ፡ ሎዛ፡
መሥዋዕተ ፡ ኣምልኮ ፡ ንጹሕ ፡ ዘጠረጼዛ፡
እምከርሥኪ ፡ ተቀስመ ፡ መዓዛ።

**፭ኛ**
**አመ ፡ ፳ ፡ ወ፱ ፡ ለመጋቢት ፡ በበዓለ ፡ ትስብእት**
**ሥ ፡ ዕ።**

ማርያም ፡ እግዝእትየ ፡ እንዘ ፡ ትፈትል ፡ ወርቅ ፡ ወሜላተ፡
ከመ ፡ ይዜንዋ ፡ ብሥራተ ፡ ፍሥሐ ፡ ገሐደ፡
ሊቀ ፡ አእላፍ ፡ ገብርኤል ፡ ወረደ፡
**እግዚአብሔር** ፡ ኮነ ፡ ምስለ ፡ ሥጋሃ ፡ ኣሐደ፡
ኀደረ ፡ ቃል ፡ ኀበ ፡ ፈቀደ ፡ እምሕላዌሁ ፡ ኢተበዐደ፡
ዮም ፡ በትስብእቱ ፡ ኪዳኖ ፡ ሐለደ።

**፮ኛ**
**ሥ ፡ ዕ።**

ራእየ ፡ ነቢያት ፡ ተዐትበ ፡ ቅዱሰ ፡ ቅዱሳን ፡ ተቀብአ፡
ዐመፃ ፡ ተሐትመ ፡ ወጌጋይ ፡ ጠፍአ፡
በከመ ፡ ቀዳሚ ፡ ገብርኤል ፡ ኣይድኣ፡
**እግዚአብሔር** ፡ ዮም ፡ በከርሠ ፡ ማርያም ፡ ተሰብኣ፡
ኢይኀኑ ፡ አይኀኣ ፡ እምሕፅነ ፡ አቡሁ ፡ መለኮት ፡ ኣይምኣ፡
ዝተገድፈ ፡ ይኀሥሥ ፡ በግዐ።

**፶፯ኛ**

**አመ ፡ ፩ ፡ ለሚያዝያ፡**

**ሥ ፡ ዕ።**

ደቂቀ ፡ ፳ኤል ፡ በገዳመ ፡ ሲና፡
ዘገለውዋ ፡ በወርቅ ፡ ኀዋረ ፡ መና፡
ከመ ፡ ኀሐ ፡ ጽባሕ ፡ ዘድልው ፡ ሥና፡
ተወልደት ፡ ዮም ፡ ማርያም ፡ እምሐቌ ፡ ኢያቄም ፡ ወሐና
ሆሣዕና ፡ ሆሣዕና ፡ ሆሣዕና፡
ተብህለ ፡ ለፍሬ ፡ ማኅፀና፡
እም ፡ አእሩግ ፡ ወደቂቅ ፡ በፍና።

**፶፰ኛ**

**ሥ ፡ ዕ።**

ነቢያተ ፡ ፳ኤል ፡ በመጽሔተ ፡ መንፈስ ፡ ርእይዋ
በሥርጐ ፡ ክህነቱ ፡ ለአሮን ፡ ኣስተማሰልዋ፡
በኣእጹቀ ፡ በቀልት ፡ በስብሐት ፡ ፆድዋ፡
ተወልደት ፡ ዮም ፡ ማርያም ፡ መድኃኒተ ፡ አዳም ፡ ወሔዋ፡
በልዋ ፡ በልዋ ፡ በልዋ ፡ እንዘ ፡ ትዌድስዋ፡
በሐኪ ፡ ሐዳስዩ ፡ ጣዕዋ።

**፶፱ነኛ**

**ክ ፡ ዕ፡**

ወርኀ ፡ አሣእና ፡ ወፀሐይ ፡ ሙጣሔሃ፡
ለማርያም ፡ ብፅዕት ፡ ከርሥ ፡ ዘፆረት ፡ ኪያሃ፡
ለክብረ ፡ ልደታ ፡ ኣቄርብ ፡ ኣምኃ፡
አመ ፡ ዐርገ ፡ ወልዳ ፡ ለገቢረ ፡ በዓል (በ)ፍሥሐ፡
ዲበ ፡ ዕፀ ፡ ሰግላ ፡ ቀዊሞ ፡ ዘከዮስ ፡ ከልሐ፡
ሕይወት ፡ ወመድኃኒት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ በጽሐ።

## ፲ኛ

### በ፪ ፡ ዕ፡

እምነ ፡ ቢሲስ ፡ ፍቱል ፡ ወእምኀብረ ፡ ያላባት ፡ ክዑብ፡
ዘኣነምዋ ፡ በጥበብ፡
ባስልኤል ፡ ወኤልያብ፡
ልብሰ ፡ ቅድሳቱ ፡ ለአሮን ፡ ካህነ ፡ ኦሪት ፡ ዕቱብ፡
አምሳላ ፡ ማርያም ፡ እግዝእትየ ፡ ዘተወልደት ፡ ዮም ፡ እም
ሐቌ ፡ ኢያቄም ፡ ሠያብ፡
እምከርሠ ፡ ሐና ፡ በንጹሕ ፡ ሰብሳብ፡
እንዘ ፡ ደመናሃ ፡ ግልቡብ፡
እሳተ ፡ መለኮት ፡ ልሁብ፡
ዲበ ፡ ዕዋለ ፡ አድግ ፡ ተጽዕነ ፡ ዘይፀውርዎ ፡ ኪሩብ፡
ስንዳኖ ፡ ወልብስ ፡ ዘየኀዕብ፡
በደመ ፡ አስካል ፡ ወወይን ፡ ዘውስተ ፡ ማኅብብ።
ሆሣዕና ፡ ለወልደ ፡ ኣብ፡
እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ወደስዋ ፡ ሕዝብ።

## ፲፩ኛ

### ዘፋሲካ ፡ ሥ ፡ ዕ፡

መስተጽዕነ ፡ ፈረስ ፡ ጸዐዳ ፡ ዘቀስታም ፡ ያጸንዕ፡
ወሀብዎ ፡ መጥባሕተ ፡ ከመ ፡ ይማእ፡
በትንቢት ፡ ዘይቤ ፡ ቴዎኀሎስ ፡ ረድእ፡
ዝኬ ፡ ውእቱ ፡ ፋሲካዊ ፡ በግዕ፡
እምገቦሁ ፡ ዘይነቅዕ፡
ፈልፈለ ፡ ሕይወት ፡ ስቴ ፡ ጽሙዕ፡
ዘያረዊ ፡ ለተድላ ፡ ወፍግዕ።

## ፲፪ኛ፡

### ሥ ፡ ዕ፡

ዘኣማሰነ ፡ ወአመዝበረ፡

በቃለ ፡ ተግሣጽ ፡ ከመ ፡ ይዝልፍ ፡ ንስረ፡
ኣንበሳ ፡ ገዳም ፡ ተንሥአ ፡ ወጥሕረ፡
ትንሣኤ ፡ ሞቱ ፡ ለወልድ ፡ ሱቱኤል ፡ አመረ፡
ኢወሀበ ፡ ወርቀ ፡ ወብሩረ፡
ለቤዝዎ ፡ አዳም ፡ መጠወ ፡ ደሞ ፡ ክቡረ፡
ፋሲካሁ ፡ ሚካኤል ፡ ነገረ።

## ፲፫ኛ

### አመ ፡ ፳ወ፩ ፡ ለሚያዝያ ፡ ሥ ፡ ዕ፡

አብርሃም ፡ በከመ ፡ ተስኣ ፡ በግዐ ፡ ወላሕመ፡
ምስለ ፡ ዕጕለ ፡ ርግብ ፡ መንጢጠ፡
ኣመ ፡ ዕለተ ፡ ርእየ ፡ ራእየ ፡ ሥሉጠ፡
ከማሁ ፡ አቁርብ ፡ ኣስተዓ ፡ ጋዳኪ ፡ በመቅደሰ ፡ ቤትኪ፡ውስጠ
በትንሣኤ ፡ ወልድኪ ፡ ተቀጥቀጠ፡
በበሊዓ ፡ ዕፅ ፡ እንተ ፡ ዘአስፈጠ፡
ረስዩኒ ፡ ማርያም ፡ ብፁዓዊ ፡ ዘንጽሕኪ ፡ ሤጠ።

## ፲፬ኛ

### አመ ፡ ፩ ፡ ለግንቦት ፡ ሥ ፡ ዕ፡

ትወጽእ ፡ በትር ፡ እምሥርወ ፡ እሴይ ፡ ፍሬ ፡ ሐዋዝ ፡
ዘዐርገ ፡ እምጕንዱ
ኢሳይያስ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ዘአሞፅ ፡ ወልዱ፡
ተወልደት ፡ ዮም ፡ ማርያም ፡ ለበኵረ ፡ ትንሣኤ ፡ ማኅፈዱ፡
ቅድሜሃ ፡ እንዘ ፡ ይሰግዱ፡
ማሕሌት ፡ ዚአሃ ፡ ያንጐደጕዱ፡
ፍጥረታት ፡ በልሳን ፡ ፆዱ።

፲፫ኝ

ሥ ፡ ዕ፡

ሚ ፡ አዳም ፡ ዘአዕይንትኪ ፡ ርኅራኄ፡
እምስርቀት ፡ ፀሐይ ፡ ይበርሕ ፡ ዘሥነ ፡ ገጽኪ ፡ ሠራኄ፡
ወመላትሕኪ ፡ ይጼኑ ፡ እምርሔ፡
ለክብረ ፡ ልደትኪ ፡ ዮም ፡ ኣቄርብ ፡ ስባሔ፡
በሰጊድ ፡ ወበእማኄ፡
ምስላ ፡ እሊኣየ ፡ በውህዋሄ፡
ውዳሴኪ ፡ እሰብክ ፡ ኵለሄ።

፲፬ኛ፡

ሥ ፡ ዕ።

ኀፍረተ ፡ ትክት ፡ ሶበ ፡ ሰአመ፡
ብሂለ ፡ ኣፈ ፡ ወርቅ ፡ ዮሓንስ ፡ ተደግመ ፡ ስመ፡
በአፈ ፡ ድንግል ፡ እንተባ ፡ ማኅተመ፡
ከማሁ ፡ ትሰምዮ ፡ እስክንድር ፡ ስመ፡
ሂሩና ፡ ጥዑመ።
ዳግመ ፡ ዳግመ ፡ ከመ ፡ ዘበምድር
ይንግሥ ፡ በሰማይ ፡ ዳግመ፡
ወሚካኤል ፡ ይኵኖ ፡ ቃውመ።

፲፯ኛ፡

ሥ ፡ ዕ።

እምአፈ ፡ ልዑል ፡ ያዕቆብ ፡ ተሰምየ ፡ ፳ኤል፡
ወላዮሐንስ ፡ ጳሊስ ፡ ዘቁስጥንጥንያ ፡ ደወል፡
ኣፈ ፡ ወርቅ ፡ ትቤሎ ፡ ማርያም ፡ ድንግል፡
ሞገሰ ፡ ይርከብ ፡ ቅድሜሃ ፡ እስክንድር ፡ ኣዛል፡
ውስተ ፡ ብሔር ፡ ሥዑር ፡ ወጥሉል፡
ይሰዶ ፡ ሚካኤል ፡ ኣዕዲዎ ፡ እምሲኦል ፡ ቀልቀል።
እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ በምድረ ፡ ዘብር፡

## ፲፰ኛ

**ሥ ፡ ዕ ፡ ዘዕርገት፡**

ውስተ ፡ ኣርያም ፡ ዐረገ ፡ ዔዊወከ ፡ ዔዋ፡
ወወሀብከ ፡ ጸጋከ ፡ ለደቂቀ ፡ አዳም ፡ ወሔዋ።
ዳዊት ፡ ዘይቤ ፡ ተፈጸመ ፡ ነዋ፡
የማነ ፡ አቡሁ ፡ ነበረ ፡ ዐሪጎ ፡ ለጥበብ ፡ ሥርዋ
ቃለ ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘይዜንዋ፡
ለጽዮን ፡ ደምጸ ፡ በውስተ ፡ በድዋ፡
ኣድባር ፡ አንፈርዓፁ ፡ ከመ ፡ ጣዕዋ፡

## ፲፱ነኛ፡

**ሥ ፡ ዕ።**

እማየ ፡ አይኅ ፡ አትረፈ ፡ እምነ ፡ ርኵሳን ፡ በበክልኤ፡
ወእምንጹሓን ፡ ዓዲ ፡ በበ ፡ ሱባዔ፡
በከርሠ ፡ ታቦት ፡ ከዊኖ ፡ ኃባዬ፡
በሥጋ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ አርኣየ ፡ ትንሣኤ፡
እንዘ ፡ የዐርግ ፡ ይቤ ፡ በውዋዔ፡
እምድኅሬየ ፡ እፈኑ ፡ መንፈሰ ፡ በቋዔ፡
ኅበ ፡ ሀለዉ ፡ አርዳእየ ፡ በጽዮን ፡ ጉባዔ።

## ፳ኛ፡

**ሥ ፡ ዕ።**

ለሙሴ ፡ ነቢይ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ኃረዮ፡
እምነ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ፈድፋደ ፡ አዕበዮ፡
ኣብአ ፡ ማእከለ ፡ ቆባሩ ፡ ወገጹ ፡ ኣርአዮ፡
በትንሣኤሁ ፡ ለሞት ፡ ዘለፎ ፡ ወለጽልመት ፡ ሣቀዮ፡
ቅድሜሁ ፡ እንግድ ፡ በተጋንዮ፡
ወእትነሐይ ፡ አንተ ፡ እርኣይ ፡ ላሕዮ፡
ለዘዐርገ ፡ በስብሐት ፡ ሰማዮ።

**፳፩ኛ፡**

**ሥ ፡ ዕ።**

እምነ ፡ ምውታን ፡ እምድኅረ ፡ ተንሥአ፡
ለአርዳኢሁ ፡ ሄራን ፡ ውስተ ፡ ጉባዔሆሙ ፡ ቦአ፡
ዓሣተ ፡ ወጸቃውዐ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በልዐ፡
ወአለበዎሙ ፡ ምሥጢረ ፡ መዋዕል ፡ ኀቡአ፡
በቃለ ፡ ቀርን ፡ ወበውውዓ፡
በሥጋ ፡ ማርያም ፡ እንተ ፡ ዘነሥአ፡
ዐርገ ፡ ሰማያት ፡ በዕለት ፡ ዐርባዓ

**፳፪ኛ፡**

**ዘደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ ሥ ፡ ዕ።**

በደብረ ፡ ምጥማቅ ፡ በከመ ፡ ኣስተርአይኪ ፡ በገሀድ
አስተርኢ ፡ ዮም ፡ ማርያም ፡ በሕገ ፡ ፈቂድ፡
እብለኪ ፡ ዘበአእኵቶ ፡ ገብርኪ ፡ ናዖድ፡
ለኪ ፡ ይደሉ ፡ እግዝእትየ ፡ ዘበሥነ ፡ አምልኮ ፡ ሰጊድ
ሣህልኪ ፡ ላዕሌየ ፡ ይፈድፍድ፡
አስተብቍዒ ፡ ዮም ፡ እመ ፡ ዋሕድ፡
መርዔትየ ፡ ኢይልክፍ ፡ ብድብድ፡

**፳፫ኛ፡**

**አመ ፡ ፩ ፡ ለሰኔ ፡ ሥ ፡ ዕ።**

ኃይመተ ፡ አብርሃም ፡ ወልደ ፡ ታራ፡
ደብረ ፡ መድኃኒት ፡ ለይስሐቅ ፡ ዘሣራ፡
ሰዋስወ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘንካር ፡ ሕብራ፡
እስብክ ፡ ዮም ፡ ክብረ ፡ ልደትኪ ፡ በውስተ ፡ ዛቲ ፡ ደብራ፡
ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወለተ ፡ ቅስራ፡
ለሰርጎ ፡ ርእስየ ፡ ረሰይኵኪ ፡ ጌራ፡
አስትይኒ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ በገዳም ፡ እንተ ፡ ሰትየ ፡ ዕዝራ፡

እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ በምድረ ፡ ወይ።

**፳፬ኛ፡**

**ሥ ፡ ዕ**

ሚካኤል ፡ ክቡር ፡ ሊቀ ፡ ኣእላፍ፡
ነፋኄ ፡ ቀርን ፡ ውእቱ ፡ እንዘ ፡ ይሰርር ፡ በክነፍ፡
መልኣከ ፡ ገጽ ፡ ዘአርያም ፡ ፆፍ፡
ዓለመ ፡ ዓለም ፡ ይትዓየን ፡ ጕባዔ ፡ እንበለ ፡ ጐንድዮ ፡ ለዘልፍ፡
ጠለ ፡ በረከቱ ፡ ዲቤየ ፡ ይነፍንፍ፡
ኣጽራሐ ፡ ቤትየ ፡ ኢታትርፍ፡
እምእዴሁ ፡ ዘመልኀት ፡ ሰይፍ።

**፳፫ኛ፡**

**ዘፍልሰታ ፡ ሥ ፡ ዕ።**

ወለተ ፡ ዳዊት ፡ ወሰሎሞን ፡ እንተ ፡ ትጸውር ፡ ትእዛዘ ፡ ሕግ ፡ ዘጽሌ፡
ታቦተ ፡ ሕርመት ፡ ዘኣልባ ፡ ምሳሌ፡
በዓርያመ ፡ ስብሐት ፡ ዮም ፡ ፈለሰት ፡ ሉዓሌ
ማርያም ፡ ድንግል ፡ ዕንቈ ፡ ቢረሌ፡
ለይኵኖ ፡ አምላክ ፡ ታዕድዎ ፡ እምብካይ ፡ ወወይሌ፡
ትንባሌሃ ፡ ይኵኖ ፡ ከላሌ።

ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ እነዚህን ፡ ቅኔዎች ፡ ሲቀኙ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ከሐዲስ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ከብሉይ ፡ ስለሚጠቅሱ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ ነጠላውን ፡ ወይም ፡ ከነትርጕሙ ፡ ማወቃቸውን ፡ ያስረዳል። ቅኔው ፡ በዘመን ፡ ብዛት ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ሲገለበጥ ፡ ፩ ፡ አንድ ፡ የፊደል ፡ ስሕተት ፡ ያለበት ፡ ይመስላል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የዛሬ፬፻፶ ፡ ዓመት ፡ የነበረው ፡ የሰዋስውና ፡ የግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ ኣሰካኰ ፡ የቅኔው ፡ አደራደር ፡ የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ እንጂ ፡ ስሕተት ፡ አይደለም።

ቢሆንም ፡ ያለው ፡ እንዳለው ፡ ታትሞ ፡ ቢገኝ ፡ በነዚህ ፡ በብዙ ፡ ቅኔዎች ፡ የቀረውን ፡ ኣንባቢ ፡ ቢያስለችና ፡ ባይጠቅምም ፡ እንኳን ፡ የግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡

የቅኔ ፡ ጣዕም ፡ ያላቸውን ፡ የዛሬ ፡ ሊቃውንት ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ የቅኔ ፡ የምስጢርና ፡ የሰዋስዉን ፡ መንገድ ፡ ከአሉበት ፡ ጊዜ ፡ ቅኔ ፡ ጋር ፡ አመዛዝነው ፡ ሊጠቀሙበት ፡ ይችላሉ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ገዝተው ፡ በሺ፭፻ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በነሐሴ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ባረፉ ፡ ጊዜ ፡ በዙፋን ፡ ልጃቸው ፡ ዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ተከተሏቸው። ስለ ፡ ናዖድ ፡ አሟሟት ፡ እንደተለመደው ፡ በዝርዝር ፡ የሚናገር ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ የለም። ታሪክ ፡ ነገሥቱ ፡ ባጭሩ ፡ « ዕረፍቱኒ ፡ ኮነ ፡ ኣመ ፡ ፯ ፡ ለነሐሴ ፡ አሜሃ ፡ ተፈጸመ ፡ ፸፻ ፡ ዓመት ፡ ወመቃብሪሁ ፡ ግሼ ፡ አምባ ፡ ይላል። « አሜሃ ፡ ተፈጸመ ፡ ፸፻ ፡ ዓመት “ ፡ የሚለው ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ ርሳቸው ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ ፯ሺ ፡ ዓመት ፡ መሙላቱን ፡ ለማስረዳት ፡ ነው። እንዳገራችን ፡ ሊቃውንት ፡ ኣሳብ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ **ክርስቶስ** ፡ ልደት ፡ ድረስ ፡ የነበረው ፡ ጊዜ ፡ ፭ሺ፭፻ ፡ ስለሆነ ፡ ናዖድ ፡ የሞቱበት ፡ ጊዜ ፡ **ከክርስቶስ** ፡ ልደት ፡ ወዲህ ፡ በሺ፭፻ ፡ ዓ.ም ፡ ስለሆነ ፡ ሁለቱ ፡ ሲደመር ፡ ፯ሺ (፸፻) ዓመትን ፡ ይሰጣልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ናዖድ ፡ ሲሞቱ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ፯ሺ ፡ ዓመት ፡ ሞላ ፡ የሚለው።

ነገር ፡ ግን ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሊቃውንት ፡ ብዙ ፡ ሐውልትና ፡ ጽሑፍ ፡ እየመረመሩ ፡ የዓለምን ፡ አዠማመር ፡ ከዚህ ፡ ይበልጥ ፡ በጣም ፡ ማራቃቸውን ፡ አንባቢ ፡ ስለማይስተው ፡ ኣሁን ፡ የዚህን ፡ ጕዳይ ፡ እንለፈው።

ለአምባግሸን ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ላለችው ፡ ለማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሁን ፡ መጻሕፍት ፡ የሰጡበት ፡ በምስተር ፡ ራይት ፡ ዝርዝር ፡ ገጽ ፡ ፻፹፯ ፡ ይገኛል። እንደጽሑፉ ፡ አነጋገር ፡ ለደብረ ፡ ብርሃን ፡ ማርያም ፡ የሰጡት ፡ ይመስላል። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እንግሊዛዊው ፡ ምስተር ፡ ውሊያም ፡ ራይት ፡ በሎንዶን ፡ ባሳተሙት ፡ የመጻሕፍቶቻችን ፡ ዝርዝር ፡ በገድለ ፡ ፋሲለደስ ፡ ውስጥ ፡ ከነቅኔያቸው ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ለቤት ፡ ማርያም ፡ የሰጡት ፡ የመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ቀጥሎ ፡ እንደተመለከተው ፡ ነው። በ፫፻ወ፱፻፹፯ ፡ ዓ.ም (፩)ኣመ ፡ ፳ወ፬ ፡ ለሚያዝያ ፡ በቀዳሚ ፡ አመተ ፡ መንግሥቱ ፡ እንዘ ፡ ሀለወ ፡ በምድረ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ንጉሥነ ፡ ናዖድ ፡

ወበጺጋ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ዘተሰምየ ፡ አንበሳ ፡ በፀር ፡ መጻሕፍት ፡ ዘወሀበ ፡ ለቤተ ፡ ማርያም።

፩ ፡ ኦሪት ፡
፩ ፡ ነገሥት ፡
፩ ፡ መቃብያን ፡
፩ ፡ ወንጌል ፡
፩ ፡ ገድላ ፡ ሐዋርያት ፡
፩ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡
፩ ፡ ሓሳብ ፡
፩ ፡ ተአምረ ፡ ማርያም ፡
፩ ፡ ክብረ ፡ ነገሥት ፡
፩ ፡ መጽሐፈ ፡ ዕንቍ ፡
፩ ፡ ሲኖዶስ ፡
፩ ፡ መጽሐፈ ፡ ምስጢር ፡
፩ ፡ መጽሐፈ ፡ ዘላፌ ፡ እስጢፋ ፡ ለእመቤታችን ፡ ስግደት ፡
አይገባም ፡ ያሉትን ፡ የሚወቅስ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም።

፩ ፡ ዐዳለ ፡ ፀሐይ ፡
፩ ፡ ገድለ ፡ ሐዋርያት (፪ኛ) ፡
፩ ፡ ስንከሣር ፡
፩ ፡ መጽሐፈ ፡ ብርሃን ፡
፩ ፡ ድርሳነ ፡ ጾም ፡
፩ ፡ ገድለ ፡ ፋሲለደስ ፡
፩ ፡ ወኣባ ፡ ኖብ ፡ ወለ**እግዚአብሔር** ፡ ኣብ ፡ ጦማረ…ኃብእት ፡
፩ ፡ ገድለ ፡ ሐዋርያት (፫ኛ?)
፩ ፡ ወንጌል (፪ኛ፡)
፩ ፡ ሲኖዶስ (፪ኛ)
፩ ፡ ወቀዳሚኒ ፡ ዘፈነውኮ ፡ ለ**እግዚአብሔር** ፡ አብ ፡ ዘወርቅ ፡ ወንጌል
፩ ፡ ተአምረ ፡ ሚካኤል ፡ በወርቅ ፡ ልቡጥ ፡
፩ ፡ ዳዊት ፡
፩ ፡ ዳዊት ፡

በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ያፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ ባለቤት (ቀኝ ፡ በዓልቲሐት) የነበሩ ፡ ንግሥት ፡ ዕሌኒ ፡ በጐጃም ፡ ውስጥ ፡ እነብእሴ ፡ ላይ ፡ የመርጡለ ፡ ማርያምን ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ኣሠሩ። እርሳቸውም ፡ ይህቺን ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ለራሳቸው ፡ መታሰቢያ ፡ እንድትሆን ፡ ስለመረጧት ፡ ለሥራውም ፡ ለንዋየ ፡ ቅድሳቱና ፡ ለአልባሳቱ ፡ መግዣ ፡ ያለ ፡ ሀብታቸውን ፡ ሰጡ ፡ ይባላል።

(፩) ፲፱፻፹፯፡ የሚለው፡ ፭ሺ፭፻፡ ዓመተ፡ ዓለምን፡ ንጉሡ፡ ከነበሩበት፡ ከሺ፬፻፹፯፡ ዓ፡ ም፡ -ጋር፡ ባንድነት፡ እጋጥሞ፡ ፯ ሺ፱፻፹፯፡ (፲፱፻፹፯) ፡ ዓ፡ ም፡ አድርጎታል።

# ምዕራፍ ፡ ፳፩።

## ከዓፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ እስከ ፡ ዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ድረስ ፡ ያሉ ፡ የነገሥታትና ፡ የንግሥታት ፡ የመሳፍንትና ፡ የመኳንንት ፡ ዝርዝር።

በእነዚህ ፡ በኣርእስቱ ፡ በተጠቀሱት ፡ ነገሥታት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የቤተ ፡ መንግሥትና ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሞልተዋል። ነገር ፡ ግን ፡ በሙሉ ፡ ዝርዝራቸውን ፡ ማግኘት ፡ አይሆንልንም። ምክንያቱም ፡ የዘመኑ ፡ ጸሐፊ ፡ ስማቸውንና ፡ የማዕርግ ፡ ስማቸውን ፡ ከነሥራቸው ፡ በዝርዝር ፡ አላቆየልንም።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የአንዳንዶቹን ፡ ሥራና ፡ ስማቸውን ፡ በዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ውስጥ ፡ የንጉሡን ፡ ሥራ ፡ በሚገልጥበት ፡ ጊዜ ፡ እንደአጋጣሚ ፡ በሥራ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸውን ፡ ስለጠቀሰ ፡ ለአንባቢ ፡ እንዲመች ፡ ከንጉሡና ፡ ከንግሥታቱ ፡ ዝምረን ፡ የመሳፍንቱንና ፡ የመኳንንቱን ፡ ስምና ፡ ሥራ ፡ ከዜና ፡ መዋዕሉ ፡ ውስጥ ፡ ለቅመን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ባሉት ፡ ገጾች ፡ ጽፈናቸዋል። የእነሱንም ፡ የማዕርጋቸውንና ፡ የስማቸውን ፡ ዓይነት ፡ ከዛሬው ፡ ጋር ፡ ለማስተያየትና ፡ ልዩነቱን ፡ ለመረዳት ፡ ይጠቅማል። ከነዚሁ ፡ ነገሥታት ፡ ውስጥ ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብና ፡ የልጃቸው ፡ ያፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ከሌሎቹ ፡ ከዓፄ ፡ እስክንድርና ፡ ከዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ረዘም ፡ ስለሚል ፡ የመኳንንቱም ፡ ዝርዝር ፡ በነዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ በርከት ፡ ይላሉ። ይኸውም ፡ ከነዓፄ ፡ ናዖድ ፡ ጊዜ ፡ የነዓፄ ፡ በዕደ ፡ ማርያም ፡ ሹማምንት ፡ በርክተው ፡ አይደለም። ነገር ፡ ግን ፡ የነዚህ ፡ ተጽፎ ፡ የነዚያ ፡ ሳይጻፍ ፡ በመቅረቱ ፡ መሆኑን ፡ ለአንባቢ ፡ እያመለከትን ፡ ኣሁን ፡ ዝርዝራቸውን ፡ እንመልከት።

## ባፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን።

| ተራ ፡ | ስም ፡ | የማዕርግ ፡ ስም | ፩ ፡ ፩ ፡ ማስረጃ ፡ |
|---|---|---|---|
| ፴፮ | ጸጋይ ፡ ከንቲባ ፡ ....? | የስሜን ፡ ሹም | |
| ፴፯ | ምጡስ ፡ | ጻሰርጓ | |
| ፴፰ | ገብረ ፡ አልፋ | | ያቃቤ ፡ ሰዓት ፡ አምኃየስ ፡ ልጆች |
| ፴፱ | ተክለ ፡ ማርያም | | |
| ፵ | ተዐውቀ ፡ ብርሃን | | |
| ፵፩ | ዘራዐ ፡ ጽዮን | | |
| ፵፪ | ይስሐቅ ፡ ነዳይ | | |
| ፵፫ | ገብረ ፡ ክርስቶስ(ገብሩ) | | |

# ባፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ዘመን።

| ተራ፡ | ስም፡ | የማዕርግ ፡ ስም፡ | ፩ ፡ ፩ ፡ ማስረጃ፡ |
|---|---|---|---|
| ፩ | ዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም፡ | ዳዊት፡አድማስ ሕርያቆስ (ስመ ፡ መንግሥት) | ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ያፄ ፡ ዘርዓ ፡ ያቆብ ፡ ልጅ። |
| ፪ | . . . . . . .? | ዣን ፡ ሰይፉ ፡ | ግራ ፡ በአልቲሐት ፡ የዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የልጅነት ፡ ሚስት። |
| ፫ | ዕሌኒ | አድማስ ፡ ሞገሳ ፡ | ቀኝ ፡ በአልቲሐት ፡ የዓፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ የቀኝ ፡ ባለቤት። |
| ፬ | ንግሥት፡ሮማነ፡ወርቅ ፡ | ሮምና ፡ (ዣን፡ሰይፉ ፡ ትሆን?) | የእስክንድርና ፡ የዕንቆ ፡ ፳ኤል ፡ እናት። |
| ፭ | | ዳዊት ፡ ኤራ ፡ | በአልተ ፡ ሽሕና (ሾኾና)ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ፫ኛ ፡ ባለቤት ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ገዚት (ራስን ፡ የምትገዛ፡?) የምትባል። |
| ፮ | ኣምኃ ፡ ጽዮን ፡ | ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ | |
| | ኣባ ፡ መርሀ (ይምርሐነ ፡ መርሐ ፡ ክርስቶስ) | መምህር፡ዘደብረ ፡ ሊባኖስ (እጨጌ) | |
| ፯ | መሐሪክርስቶስ ፡ | የግራ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ | ከአዳሎች ፡ ጋራ ፡ ሲዋጋ ፡ የሞተ |
| ፰ | ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ | የቀኝ ፡ ብሕት ፡ ወደድ ፡ | |
| ፱ | አንበሳ ፡ ዳዊት ፡ | ጐጃም ፡ ነጋሽ ፡ | |
| ፲ | ማርቆስ ፡ | ዋና ፡ የጦር ፡ ኣለቃና ፡ የተከበረ ፡ ሰው። | |
| ፲፩ | ዓምዱ ፡ | መከብበ ፡ አትሮንስ ፡ ማርያም ፡ | ብዙ፡ማዕርግና፡ልብስተሰጥቶት ፡ የከበረሰው። |
| ፲፪ | ተክለ ፡ ኢየሱስ ፡ ዓፄ ፡ | የጸስርጓ ፡ አብሳዲ ፡ ተወላጅ ፡ | በእደ ፡ ማርያምን ፡ ዳዊት ፡ ያስደገመ ፡ መምህርና ፡ ጓደኛ። |
| ፲፫ | አባ ፡ አቡቂር ፡ | መምህር ፡ ዘእንደገብጠን ፡ | (እንደገብጣን ፡ በሸዋ ፡ የነበረ ፡ ገዳም) |
| ፲፬ | አባ ፡ ማቴዎስ ፡ | ንቡረ ፡ ዕድ ፡ ዘደብረ ፡ ዳሞ ፡ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፲፭ | ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ | የባሌ ፡ ሹምገ (ራድ ፡ ዘባሊ) ፡ | በኣድማ ፡ ተገኝቶ ፡ የታሠረ። |
| ፲፮ | የክላ ፡ | ሊቀ ፡ መፃኒ (መጽአኒ–መጣኒ–መጫኒ) | |
| ፲፯ | ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ | ጻሰርጓ ፡ | |
| ፲፰ | መሐፊ ፡ ክርስቶስ ፡ | የዳሞት ፡ ገዥ ፡ | በፈረስና ፡ በዕቃ ፡ በልብስ ፡ የማይገባውን ፡ ኣደረገ ፡ ተብሎ ፡ ገብረ ፡ ዋሕድ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ያመጣው (በ፮ኛ ፡ ቊጥር ፡ የተጻፈው ፡ ይሆን፡?) |
| ፲፱ | ትዕይንተ ፡ | ሊቀ ፡ መጣኒ (ቃለ ፡ ሕዴ) | |
| ፳ | ገደብ ፡ ሐሚድ ፡ | | የደዋሮ ፡ እስላምና ፡ የንጉሡ ፡ መላክተኛ ፡ |
| ፳፩ | ማቴዎስ ፡ | ዣን ፡ ደረባ ፡ | |

# ባፄ ፡ እስክንድር ፡ ዘመን ፡

| ተራ፡ | ስም፡ | የማዕርግ ፡ ስም | ፩ ፡ ፩ ፡ ማስረጃ፡ |
|---|---|---|---|
| ፩ | ዓፄ ፡ እስክንድር ፡ | ቆስጠንጢኖስ (ስመ ፡ መንግሥት) | ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ |
| ፪ | ሮምና (ሮማነ ፡ ወርቅ) | ንግሥት። | እናታቸው (ድጋሜ) |
| ፫ | ዕሌኒ ፡ | | እንጀራ ፡ እናት (ድጋሜ) |
| | ይምርሐነ (መርሐ) ክርስቶስ። | እጨጌ። | |
| ፬ | ተስፋ ፡ ጊዮርጊስ ፡ | ዓቃቤ ፡ ሰዓት። | |
| ፭ | ዓምደ ፡ ሚካኤል ፡ | ግራ ፡ ብሕት ፡ ወደድ (ራስ) | |
| | በድላ ፡ ርዕድ (በድል ፡ ራዕድ-ራዓድ) | ቀኝዕ ፡ ብሕት ፡ ወደድ። | |
| | ዘሥሉስ ፡ | | ንጉሡን ፡ በአድማ ፡ ያስገደሰ፡ |
| | አባ ፡ ሐስቦ ፡ | | |
| | ኣባ ፡ ዓምዱ። | | |
| | ምእመን ፡ በጽድቀ | | |
| | ተክላይ። | | የንጉሥ ፡ አገልጋይ። |

# ባዼ ፡ ናዖድ ፡ ዘመን።

| ተራ፡ | ስም፡ | የማዕርግ ፡ ስም | ፩ ፡ ፩ ፡ ማስረጃ፡ |
|---|---|---|---|
| ፩ | ዓፄ ፡ ናዖድ (ቀለዮጳ) | ስመ ፡ መንግሥት (አንበሳ ፡ በፀር) | የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት። |
| ፪ | ዕሌኒ ፡ ንግሥት ፡ | ያፄ ፡ በእደ ፡ ማርያም ፡ ባለቤት ፡ | ፫ኛ ፡ በድጋሜ ፡ የተጻፉ ፡ |
| ፫ | ዕሌኒ ፡ | ናዖድ ፡ ሞገሳ ፡ | ያፄ ፡ ናዖድ ፡ ባለቤት (የደዋሮ ፡ ባላባት ፡ የመሐመድ ፡ ልጅ) ። |
| ፬ | ዳዊት (ልብነ ፡ ድንግል) ፡ | ያፄ ፡ ናዖድ ፡ ልጅ | |
| ፭ | ዓምደ ፡ ሚካኤል ፡ | ብሕት ፡ ወደድ ፡ | በዓፄ ፡ እስክንድር ፡ ጊዜ ፡ እንደራሴ ፡ የነበረው ፡ ካፄ ፡ ናዖድ ፡ ተጣልቶ ፡ የተገደለው። |
| ፮ | ኣባ ፡ ገብረ ፡ ታድያስ (ገብረ ፡ እንድርያስ) | | |
| ፯ | ተካ ፡ ክርስቶስ ፡ | | ካፄ ፡ ናዖድ ፡ ጋር ፡ ተጣልቶ ፡ የታሠረ። |
| ፰ | ወለተ ፡ ቀለምሲስ ፡ | | ያፄ ፡ ናዖድ ፡ ልጅ ፡ የራስ ፡ ደገልሃን ፡ ሚስት። |
| ፱ | ዓመተ ፡ ድንግል | | |
| ፲ | ዓመተ ፡ ውጥን። | | ያፄ ፡ ናዖድ ፡ ልጅ። |



## Carlo Conti Rossini

- **Born ፡** April 25, 1872, Salerno, Italy
- **Died ፡** August 21, 1949, Rome, Italy
- **Books ፡** The History of Ethiopia ፡ From Ancient Times to the Medieval Ages,

He was director of the State Treasury from 1917 to 1925, a partner of the Lincei from 1921 and academic of Italy from 1939. In 1937 he received the Mussolini Prize of the Academy, for moral and historical sciences. He is owed various works on the historical geography of Ethiopia, of which the most famous is undoubtedly Italy and Ethiopia from the Treaty of Uccialli to the Battle of Adua (1935), and works of Ethiopian phonetics (Tigrinya language,1940)

He was one of the founders of the magazine Rassegna di studi Etiopici, still published by the Institute for the East Carlo AlfonsoNallino (in whose Board of Directors and scientific for a long time he ensured his commitment), together with Vinigi Lorenzo Grottanelli.

Click here for more info Carlo Conti Rossini - Wikipedia



# James Bruce

- **Born** 14 December 1730 Kinnaird, Stirlingshire, Scotland
- **Died** 27 April 1794 (aged 63)
- **Nationality** Scottish
- **Occupation** traveller, travel writer
- **Known for** Traced the origins of the Blue Nile.

James Bruce of Kinnaird (14 December 1730 – 27 April 1794) was a Scottish traveller and travel writer who spent more than a dozen years in North Africa and Ethiopia,

James Bruce was born at the family seat of Kinnaird, Stirlingshire, and educated at Harrow School and Edinburgh University, and began to study for the bar, but his marriage to the daughter of a wine importer and merchant resulted in him entering that business instead. His wife died in October 1754, within nine months of marriage, and Bruce thereafter travelled in Portugal and Spain as part of the wine trade. The examination of oriental manuscripts at the Escorial in Spain led him to the study of Arabic and Ge'ez and determined his future career. In 1758 his father's death placed him in possession of the estate of Kinnaird.

Click here for more info ፡ James Bruce - Wikipedia



# René Basset

- **Born ፡** July 24, 1855, Lunéville, France
- **Died ፡** January 4, 1924, Algiers, Algeria
- **Books ፡** Moorish Literature, New BerberTales, More
- **Children ፡** André Basset, Henri Basset
- **Education ፡** School of Higher Education, Collège de France, Inalco

René Basset was the first director of the "School of Letters of Algiers"[1] created in 1879[1] during the French colonization of Algeria.

- A member of the Asian society of Paris as well as those of Leipzig and Florence, he collaborated with the Journal Asian and studied Chinese Islam.

- 427 works in 1,523 publications in 5 languages and 4,992 library holdings Linguist, specialist in Berber and Arabic languages.
- A member of Asian societies in Paris, Leipzig and Florence, he contributed to the Asian Journal and studied Islam in China.



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ተክለጻድቅ ፡ መኩሪያ ፡ ባ፲፱፻፯ ፡ ዓ.ም ፡ በተጉለትና ፡ ቡልጋ ፡ አውራጃ ፡ አሳግርት ፡ ልዩ ፡ ስሙ ፡ ሣር ፡ አምባ ፡ በተባለ ፡ ሥፍራ ፡ ተወለዱ። ዕድሜያቸው ፡ ለትምህርት ፡ ሲደርስ ፡ መዠመሪያ ፡ ካባታቸውና ፡ ቀጥሎም ፡ ባጥቢያቸው ፡ ባህላዊውን ፡ ትምህርት ፡ እስከ ፡ ቅኔ ፡ ያለውን ፡ ቀስመዋል።

ከዚያም ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ አሊያንስ ፡ ፍራንሴዝና ፡ ከተፈሪ ፡ መኮንን ፡ ት/ቤት ፡ ገብተው ፡ የጊዜውን ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ አጠናቀቅዋል።

ኢጣሊያ ፡ አገራችንን ፡ የወረረች ፡ ጊዜም ፡ በየካቲት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ.ም. ፡ ፍጅት ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ ሶማሊያ ፡ ደናኔ ፡ ተግዘው ፡ ለሦስት ፡ ዓመታት ፡ ታሥረዋል።

ከነጻነትም ፡ መልስ ፡ አገራቸውን ፡ በተለያዩ ፡ የኃላፊነት ፡ ደረጃዎች ፡ አገልግለዋል። መዠመሪያ ፡ ተቀጥረው ፡ ያገለገሉት ፡ በትምህርትና ፡ ሥነጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነበር። እዚያም ፡ እያሉ ፡ ባነራችን ፡ ሰው ፡ የተጻፈ ፡ የአገራችን ፡ ታሪክ ፡ አንድም ፡ ባለመኖሩ ፡ በቁጭትና ፡ በመቆርቆር ፡ ነበር ፡ 'መጻፍ ፡ አለብኝ' ፡ ብለው ፡ በደንብ ፡ ከሚታወቀው ፡ ከቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ በቅጡ ፡ ወደማይታወቀው ፡ የሩቁ ፡ ዘመን ፡ መጣፍ ፡ የዠመሩት። ፡ የመዠመሪያውን ፡ መጽሐፍ ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ከዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እስከ ፡ ቀ.ኃ.ሥ." ፡ ባ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ.ም. ፡ አሳተሙ። ከጫፍ ፡ እስከጫፍ ፡ ጽፈው ፡ የመጨረሻውን ፡ መጣፍ ፡ የታሪካችን ፡ መዠመሪያ ፡ የሚኾነውን ፡ የኢትዮጵየ ፡ ታሪክ ፡ ኑብያ – አክሱም – ዛጉዌ ፡ እስከ ፡ ዐፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ – መንግሥት ፡ የሚለውን ፡ ባ፱፻፷፩ ፡ ዓ.ም. ፡ አቅርበዋል። እንህኑ ፡ መጻሕፍት ፡ ትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ታሪክ ፡ ለማስተማሪያ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ተጠቅሞባቸዋል።

ተክለጻድቅ ፡ ከታሪክ ፡ ውጭ ፡ የጻፉዋቸው ፡ "የሰው ፡ ጠባይና ፡ ዐብሮ ፡ የመኖር ፡ ዘዴና ፡ በሚዮቶሎዠያ ፡ ላይ ፡ ያተኮረ ፡ ከጣዖት ፡ አምልኮ ፡ እስከ ፡ ክርስትና" ፡ የሚሉም ፡ መጣፎች ፡ አሏቸው።

ተክለተድቅ ፡ በምድር ፡ ባቡር ፡ በዋና ፡ ጸሐፊነት ፡ በቤተመጽሐፍት ፡ ወመዘክር ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅነት፤ እንዲሁም ፡ በፈረንሣይ፣ በእስራኤል፣ በዩጎዝላቪያ ፡ በዲፕሎማሲ ፡ ሥራ ፡ በመጨረሻም ፡ የትምህርትና ፡ የባህል ፡ ሚኒስትር ፡ ኾነው ፡ አግልግለዋል። በፈቃዳቸው ፡ ጡረታ ፡ ከወጡም ፡ በኋላ ፡ በምርምር ፡ የታገኑ ፡ ሦስት ፡ ታላላቅ ፡ የታሪክ ፡ ሥራዎችን ፡ አቅርበዋል።

ተክለጻድቅ ፡ ከረዥም ፡ ያገልግሎት ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በተወለዱ ፡ በ፹፮ ፡ ዓመታቸው ፡ ሐምሌ ፡ ፲፮ቀን ፡ ባ፲፱፻፺፪ ፡ ዓ.ም. ፡ ዐርፈዋል።

## የደራሲው ሥራዎች

1. የግራኝ አሕመድ ወረራ (**ታሪክ**)
2. ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት (**ታሪክ**)
3. ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት (**ታሪክ**)
4. ዐፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት (**ታሪክ**)
5. የኢትዮጵያ ታሪክ - ኑቢያ [ሜርዌ - ናፓታ] (**ታሪክ**)
6. የኢትዮጵያ ታሪክ - ኑብያ-አክሱም ዛጉዬ እስከ ዐፄ ይኩኖ አምላክ (፩ኛ መጽሐፍ) (**ታሪክ**)
7. የኢትዮጵያ ታሪክ - ከዐፄ ይኵኖ አምላክ እስከ ልብነ ድንግል (፪ተኛ መጽሐፍ) (**ታሪክ**)
8. የኢትዮጵያ ታሪክ - ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ (፫ተኛ መጽሐፍ) (**ታሪክ**)
9. የኢትዮጵያ ታሪክ - ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (፬ተኛ መጽሐፍ) (**ታሪክ**)
10. ጥንታዊት ኢትዮጵያና ግብፅ (**ታሪክ**)
11. ከጣኦት አምልኮ እስከ ክርስትና (**ታሪክ**)
12. የሕይወቴ ታሪክ (**ታሪክ**)